አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ የጋዜጠኝነት እና

ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የአልከሶ መውሊድ የአከባበር ስርዓት እና ፎክሎራዊ ገጽታ በስልጤ ብሔረሰብ



አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የካቲት 2010 ዓ.ም

# የአልከሶ መውሊድ የአከባበር ስርዓት እና ፎክሎራዊ ገጽታ በስልጤ ብሔረሰብ


አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ

የማህበራዊ ሳይንስና ሂዩማኒቲስ የጋዜጠኝነት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


በፎክሎር ለዶክተሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


በ

አብዲ ተማም ዓሊ

አማካሪ፡- ዘሪሁን አስፋው (ተባባሪ ፕሮፌሰር)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# ምስጋና

ይህን ጥናት አንቀጽ በአንቀጽ እያረሙ በርካታ ገንቢ የሆኑ አስተያየቶችን እየሰጡ ጥናቱ እዚህ ደረጃ እንዲደርስ ያላሰለሰ ጥረት ላደረጉት መምህሬ እና አማካሪዬ ዘሪሁን አስፋው ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

መስክ ላይ መረጃ በመስጠት ያተባበራችሁኝን መረጃ አቀባዮች በሙሉ ከልብ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ደጋግሜ ወደ አልከሶ ስሄድ ቤታቸው እንዳርፍ በማድረግ እና ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች ጋር እንድንገናኝ በማድረግ ለዋልክልኝ ውለታ እኔ ውለታህን መመለስ ስለማልችል አመሰግናለሁ እይልኩ ፈጣሪ ምንዳህን ይክፈልህ፤ ልጅ ስለሆንክ እደገ ተመንደግ ብቻ ነው የምልህ - ፈተረሁፍ ሰኢድ፡፡ እንዲሁም እሜት(የፈተረሁፍ እናት) እንደ እናቴ ሆነው ስለተንከባከቡኝ ከልብ ከልብ አመሰግነዎታለሁ፡፡

ጥናቴን ደጋግሜ ስልክላችሁ ሰለቸኝ ደከመኝ ሳትሉ ከማበረታታ ጋር ለተመለከታችሁልኝ፣ ላረማችሁልኝ እና የተለያዩ ጽሁፎችን በመስጠት ለተባበራችሁኝ መሰረት ብርሃኔ(ባህር ዳር ዩኒቨርስቲ)፣ መሀመድ ጀማል(ጂማ ዩኒቨርስቲ)፣ ዶ/ር መሀመድ ጀማል(መዳወላቡ ዩኒቨርስቲ)፣ ዶ/ር ሰዋገኝ አስራት(መዳወላቡ ዩኒቨርስቲ)፣ ዶ/ር እንድሪስ ሙሀመድ(አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ)፣ ጋሽ አህመድ ዘካሪያ(አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ)፣ ዶ/ር አህመድ ሀሰን(አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ)፣ ዶ/ር ጄይላን ወሊዩ (ሀሮማያ ዩኒቨርስቲ)፣ ሰሚራ መሀመድ(አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ)፣ ኑረዲን አማን(አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ)፣ የኔሀሳብ(ድሬደዋ ዩኒቨርስቲ)፣ አራጋው ግዛው(አየርጤና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት)፣ ይበልጣል(መረዋ ኢንተርናሽናል አካዳሚ)፣ ሼኽ አደም ከማል፣ ሼኽ መሀመድ አሚን(አረብኛ ቃላትን ወደ አማርኛ በመተርጎም የተባበሩኝ) እና ቤቴሌሔም መብራቴ(ተማሪዬ) ከልብ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እና መዳወላቡ ዩኒቨርስቲ ይህን ትምህርት እንድማር ሁኔታዎችን ስላመቻቹልኝ እና የገንዘብ ድጋፍ ስላደረጉልኝ ሳላመሰግን አላልፍም፡፡በአዲስ አበባ ዩኒቨርስት ቤተመጻህፍት ውስጥ የሚገኙ ሰራተኞች የተለያዩ መጻህፍትን በምፈለግበት ወቅት ሳይሰለቹ በማቅረብ ላደረጉልኝ ትብብር አመሰግናለሁ፡፡ እንዲሁም ወደ ስልጢ ወረዳ እና ስልጤ ዞን በሄድኩበት ወቅት በየቢሮው የሚገኙ ሰራተኞች አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ትብብር ያደረጉልኝ (በተለይ አቶ ሁሴይኒ ሰኢድ) ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡ በመጨረሻም መላው ቤተሰቦቼ ይህን ጥናት ሳጠና በሀሳብ እና በቁሳቁስ ላደረጋችሁልኝ ትብብር ሁሉ ልባዊ ምስጋናዬን የላቀ ነው፡፡

# ማውጫ

ርዕስ ገጽ


ማውጫ III

የፎቶ ግራፍ ማውጫ VIII

ሙዳየ ቃላት IX

አጠቃሎ XII

ምዕራፍ አንድ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች 5

1.3 የጥናቱ ዓላማዎች 7

1.3.1.የጥናቱ ዋና ዓላማ 7

1.3.2.የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች 7

1.4 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች 8

1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች 9

1.6 የጥናቱ ወሰን 10

1.7 የጥናቱ አደረጃጀት 11

1.8 የጥናቱ ስነ ምግባር 11

1.9 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች 12

2. የስልጤ ብሔረሰብ አጭር ማስተዋወቂያ 17

2.1. የስልጤ ዞን አመሰራረት እና መገኛ ቦታ 17

2.2. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ጸባይ 20

2.3. የስልጤ ብሔረሰብ ታሪክ እና አመጣጥ 21

2.4. ቋንቋ ______ 23
2.5. ኃይማኖት ______ 24
2.6. ባህላዊ አስተዳደር ______ 25
2.7. የጋብቻ ስርዓት ______ 26
2.8. የለቅሶ ስርዓት ______ 28
2.9. የስልጤ ብሔረሰብ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለው ዝምድናና ግንኙነት ______ 29
ምዕራፍ ሶስት ______ 32
3. የአጠናን ዘዴ ______ 32
3.1 የጥናቱ ስልት ______ 32
3.2 የመረጃ ምንጮች ______ 35
3.2.1. የሁለተኛ ደረጃ (ካልዓይ) የመረጃ ምንጮች ______ 35
3.2.2. የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳማይ) የመረጃ ምንጮች ______ 36
3.2.2.1 ምልከታ ______ 36
3.2.2.2 ቃለ መጠይቅ ______ 38
3.2.2.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት ______ 40
3.3 የመረጃ አቀባዮች ምርጫ እና የከበራ አመራረጥ ______ 44
3.3.1 የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ ______ 44
3.3.2 የከበራ አመራረጥ ______ 46
3.4 መረጃ መሰብሰቢያ የመስክ መቼቶች ______ 46
3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻር ______ 48
3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ______ 49
3.7 የመስክ ቆይታ ጊዜዎች ______ 50
3.8 የማጥሪያ ዘዴ (Triangulation) ______ 52
3.9 የጥናቱ የትንተና ስልት ______ 53

ምዕራፍ አራት _______________ 57

4 የጽንሰ ሀሳብ፣ የቀደምት ጥናቶች እና የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፎች ቅኝት _______________ 57

4.1 የጽንሰ ሀሳብ ማዕቀፍ _______________ 57
4.1.1 የፎክሎር ምንነት _______________ 57
4.1.2 የክብረ በአል ጽንሳባዊ ሀሳብ ምንነት _______________ 62
4.1.3 ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ለማክበር የሚደረግ ጉዞ _______________ 65
4.1.4 የአውድ ጽንሰ ሀሳባዊ ምንነት _______________ 68
4.1.5 የመውሊድ በዓል ምንነት እና አጀማመር በዓለም _______________ 70
4.1.6 የመውሊድ አጀማመር እና አከባበር በአፍሪካ _______________ 75
4.1.7 የመውሊድ አጀማመር እና አከባበር በኢትዮጵያ _______________ 77
4.1.7.1 መውሊድ በሀገራችን እንዴት ሃይማኖታዊ ህዝባዊ በዓል ሆነ? _______________ 81
4.1.7.2 በሀገራችን የመውሊድ አከባበር ምን ይመስላል? _______________ 86
4.1.8 የመውሊድ አጀማመር እና አከባበር በስልጤ _______________ 87

4.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት _______________ 91

4.3 የጥናቱ የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ _______________ 98
4.3.1 የክዋኔ ንድፈ ሀሳባዊ ምንነት እና አተገባበር _______________ 98
4.3.2 ሥነ ፋይዳ (ተግባራዊ) ንድፈ ሀሳብ _______________ 106
4.3.4 ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳብ _______________ 108

5. የአልከስዬ አጭር የህይወት ታሪክ፣ ከራማ እና የመስጂዳቸው አመሰራረት _______________ 111

5.1. የአልከስዬ አጭር የህይወት ታሪክ _______________ 111

5.2 የአልከስዬ አልከሶ አሰፋፈር _______________ 116

5.3 የአልከስዬ ከራማ ተረኮች _______________ 121

5.4. የአልከስዬ ትንቢቶች _______________ 132

5.5 የአለከሶ መስጂድ አመሰራረት _______________ 137

5.6 ኸለዋዎች በአልከሶ መስጂድ ዙሪያ _______________ 145

6. የአልከሶ መውሊድ ከበራዎች እና ፎክሎራዊ ገጽታ 150

6.1 ቅድመ መውሊድ 150

6.2 ዕለተ መውሊድ እና ዋና ዋና ፎክሎራዊ ክንውኖች 155

6.2.1 የሶላት የመስገድ ስነ ስርዓት 155

6.2.2. ሀዲስ መናገር 159

6.2.3 መንዙማ ማለት እና ማዳመጥ 163

6.2.4 ዱኣ (ምርቃት) እና ፎክሎራዊ ክንውኖች 186

6.2.5 ዚያራ 194

6.2.5.1 የዶሪህ/የመቃብር ቦታ ዚያራ 195

6.2.5.2 የመስጂዱን መሪ (ቃዲ)መዘየር 199

6.2.6 ጫት የመቃም ስነ ስርዓት እና ፎክሎራዊ ክንውኖች 203

6.3. የወጣቶች የመውሊድ አከባበር እና ፎክሎራዊ ክንውን 206

6.4 የድሬ ሼኽና ሁሴን ወዳጆች በአልከሶ መውሊድ 214

6.5. ድህረ መውሊድ 220

ምዕራፍ ሰባት 223

7. ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በአልከሶ መውሊድ 223

7.1 የንግድ እንቅስቃሴ በአልከሶ መውሊድ 223

7.2 በአልከሶ መውሊድ ለሽያጭ እና ለስጦታ የሚቀርቡ ምግቦችና መጠጦች 229

7.3 ማህበራዊ ክንውኖች በአልከሶ መውሊድ 232

ምዕራፍ ስምንት 235

8. የሃይማኖት መስተጋብር በአልከሶ መውሊድ 235

8.1 የክርስትያን ምዕመናን የምግብ አዘገጃጀት እና አመጋገብ 240

8.2 የክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች መውሊድ የሚያከብሩበት ምክንያት 242

8.3. በመውሊድ የሙስሊሞች እና የክርስትያኖች ተመሳስሎ 248

ምዕራፍ ዘጠኝ 255

9. ለውጥ፣ ቀጣይነት እና የከበራው ፋይዳዎች 255

9.1 የአልከሶ መውሊድ ለውጥ፣ ቀጣይነት እና የለውጡ ዋና ዋና ምክንያቶች 255

9.2 የአልከሶ መውሊድ ከበራ ተግዳሮቶች 262

9.3 በአልከሶ መውሊድ የተንጸባረቁ ስልጤ ብሔረሰብ ባህሎች 274

9.4 የመውሊዱ መከበር ፋይዳ/ተግባር 276

10. የጥናቱ ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳቦች 280

10.1 የጥናቱ ማጠቃለያ 280

10.2 የጥናቱ ግኝቶች 282

10.3 የይሁንታ ሀሳቦች 283

የተጣቀሱ ምንጮች 286

አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች መግለጫ በፊደል ቅደም ተከተል መሰረት 300

አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ አቀባዮች የተዘጋጁ ጥያቄዎች 303

**የካርታ ማውጫ**

ካርታ 1፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ካርታ 17
ካርታ 2፡- የስልጤ ዞን ካርታ 19

## የፎቶ ግራፍ ማውጫ

ፎቶ 1፡- የሀገር ሽማግሌዎች በዋርካ ስር የዳኝነት ስርዓት ሲያካሄዱ 26
ፎቶ 2፡- ዋና ዋና መረጃ አቀባዮች በከፊል 40
ፎቶ 3፡-ወጣቶች እና ሴቶች የቡድን ቡድን ውይይት ሲያካሄዱ 42
ፎቶ 4፡- “ታምረኛው ምሶሶ” የሚባለው ምሶሶ እንዴት እንደመጣ አቶ ሲራጂ ሲያስረዱ 131
ፎቶ 5፡- አሮጌው የአልከሶ መስጂድ 141
ፎቶ 6፡- የታደሰው የአልከሶ መስጂድ 143
ፎቶ 7፡- ምዕመናኑ የዙህር ሷላት ሲሰግዱ 158
ፎቶ 8፡- ምዕመናን በሽምሰል ጀማል ውስጥ ቁመው መንዙማ ሲሉ 185
ፎቶ 9፡- አጥኚው ለሼኽ አብዱልረዛቅ ከዚያራ መልስ ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ 198
ፎቶ 10፡- ስጦታ ለመስጠት ቃል የገቡ ሰዎች ስጦታቸውን ለመስጠት ሲሄዱ 202
ፎቶ 11፡- መውሊድ አክባሪዎች ሜዳ ላይ ጫት ስቅሙ 206
ፎቶ 12፡- ወጣቶች ሜዳ ላይ መውሊዱን ሲያከብሩ 209
ፎቶ 13፡- የወጣቶች እና የልጆች አለባበስ በከፊል 213
ፎቶ 14፡- ገሪቦች የአልከሶን መውሊድ የሚያከብሩበት ዋርካ 216
ፎቶ 15፡- አጥኚው ከገሪቦች ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ 219
ፎቶ 17፡- ለንግድ ስራ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች በከፊል 224
ፎቶ 18፡- በንግድ ስራ የተሰማሩ ልጆች እና ወጣቶች 226
ፎቶ 19፡-የሥጋ ጥብስ በቅርጫት ተደርጎ ሲከፋፈል 230
ፎቶ 20፡- እናቶች በአልከሶ ሀረም ጣቢታ እና አተካኖ ሲያዘጋጁ 231
ፎቶ 21፡- በአልከሶ ሀረም የክርስትያኖች ማረፊያ ኸለዋ 239
ፎቶ 22፡- ክርስትያን ምዕመናን ጫት እየቃሙ መውሊድ ሲያከብሩ 242
ፎቶ 23፡- አቶ ታደሰ ታዬ የሙስሊም ኮፊያ ለብሰው መውሊድ ሲያከብሩ 249

# ሙዳየ ቃላት

ሀረም(አረብኛ)---------- ሙስሊሞች ተሰባስበው መንፈሳዊ ስርዓት የሚካሄድበት ስፍራ

ሀፊዝ(አረብኛ)----------- [ሀፊዝ አል-ቁርዓን] 114 ምዕራፎች (ሱራዎች)፣ 6,236 አንቀፆች (አያት) ያሉትና በ30 ክፍሎች (ጅዝእ) የተከፈለውን ቁርዓን በቃሉ መያዝ የቻለ ሰው። ቁርዓን የአላህ ቀጥተኛ ቃልና ዋንኛው የእስልምና ምንጭ ሲሆን ይህም ጅብሪል (ገብርኤል) አማካኝነት ለነብዩ ሙሐመድ የወረደ/የተላከ ነው።

መስጂደል ሀረም(አረብኛ)------------በመካ የሚገኘው ቅዱስ መስጂድ ነው። ይህም ሁሉም ሙስሊሞች ከያሉበት ሆነው ወደሱ አቅጣጫ ዞረው የሚሰግዱበት ካዕባ የሚገኝበትና ለሐጅ ጉዞም የሚደረግበቱ የተቀደሰ ኃይማኖታዊ ስፍራ ሲሆን

መድረሳ(አረብኛ)------------በዋንኛነት የቁርዓን ትምህርት እንዲሁም አጠቃላይ የእስልምና ኃይማኖትና አስተምህሮትን የተመለከተ ትምህርት የሚሰጥበት እስላማዊ ትምህርት ቤት ነው። ትምህርት ቤቱ መድረሳ፤ ተማሪዎቹ ደግሞ ደረሳ ይባላሉ።

ሙአዚን(አረብኛ)------------አዛን የሚያደርግ/የሚያወጣ ወይም በቀን አምስት ጊዜ ሰዎችን ለሷላት ወደ መስጂድ የሚጠራ ግለሰብ።

መግሪብ(አረብኛ)------------ፀሐይ እንደጠለቀች የሚሰገድ ባለሦስት ረከዓ እስላማዊ ፀሎት ወይም ስግደት።

መቅቡል(አረብኛ)-----------ዱዓ ሲደረግ (ሲፀለይ) ተቀባይነት እንዲኖረው ሙሉ ተስፋ ፈጣሪ ላይ መጣል።

ሚዕራጅ(አረብኛ)------------[አል-ሚዕራጅ] ነብዩ ሙሐመድ በጅብሪል እየተመሩ ከመካ ወደ እየሩሳሌም (ቤይተልመቅደስ) ከዚያም ወደ ሰማየ ሰማያት ያደረጉት የምሽት ጉዞና እርገት።

ሰሂህ(አረብኛ)---------------የተረጋገጠ ታማኝነት ያለው።

ሰሀባ/ዎች/(አረብኛ)------------የነብዩ ሙሐመድ ባለሟሎች ወይም ደቀመዝሙሮች ሲሆኑ እነሱም ነብዩን በሕይወት እያሉ በአካል ያገኙዋቸውና በግንባር የሚያውቋቸው።

ሱቢሂ(አረብኛ)-----------------ከፀሐይ መውጣት በፊት በማለዳ የሚሰገድ ባለሁለት ረከዓ እስላማዊ ፀሎት ወይም ስግደት።

ረቢኡል አወል(አረብኛ)---------- የአረብኛው የወር አቆጣጠር መሰረት ሶስተኛው ወር።

ሸልላት(አረብኛ)----------------ድርቅ ሲከሰት ወይም ችግር ሲፈጠር የሚደረግ ወቅታዊ ፀሎት ወይም ዱዓ::

ሸሪአ(አረብኛ)-------------------የእስልምና መተዳደሪያ ደንብ ወይም መመሪያ::

ቂብላ(አረብኛ)------------------ለስግደት ፊት ማዞሪያ አቅጣጫ(መካ፣ካባ)::

ቃዲ(አረብኛ)--------------------ዳኛ

ቢስሚላሂ አራህማን አረሂም(አረብኛ)----------------በአላህ ስም፣ እጅግ በጣም ርኅሩኅ፣ በጣም አዛኝ በሆነው::

ተይሙም(አረብኛ)----------------ውሃ በማይገኝበት ወቅት ለስግደት በአፈር መፀዳዳት (ጧሀራ) ማድረግ::

አኺራ(አረብኛ)-------------------ከሞት በኋላ ያለው ሁለተኛው ዓለም::

አሱር(አረብኛ)--------------------ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት የሚሰገድ ባለአራት ረከዓ እስላማዊ ፀሎት ወይም ስግደት::

ኡለማ(አረብኛ)------------------የሸሪዓ አዋቂዎች ወይም ሊቃውንት::

ኡማ ወይም ኡመት(አረብኛ)-----------------ማህበረሰብ(ህዝብ)::

ዉዱእ(አረብኛ)------------------ለስግደት የሚደረግ ፅዳት (መተጣጠብ)::

ኢሻ(አረብኛ)--------------------ምሽት በአራት ሰዓት አካባቢ የሚሰገድ ባለአራት ረከዓ እስላማዊ ፀሎት ወይም ስግደት::

ኢማም(አረብኛ)---------------መሪ ወይም አዛዥ::

ኢቃም(አረብኛ)----------------ለመስገድ ወይም ለፀሎት ዝግጅት እንዲያደርጉ ትዕዛዝ ማስተላለፍ::

ኢጅማዕ(አረብኛ)--------------ታላላቅ የሃይማኖት ሊቃውንት የተስማሙበት ሀሳብ::

ኪታብ-----------------ፀሎትና መተዳደሪያ ደንቦችን አካቶ የያዘ ሰማያዊ ወይም መንፈሳዊ መፅሐፍ::

ኻዳሚ(አረብኛ)-----------------የኃይማኖት አገልጋይና ሌሎችንም አገልግሎቶች የሚሰጥ ሰው::

ኸለዋ(አረብኛ)------------------ሃይማኖታዊ ስርዓት ወይም ጸሎት የሚካሄድበት ቦታ::

ወልይ(አረብኛ)------------------ፍፁም ለፈጣሪ ተገዥ የሆነ ሰው::

ወህይ(አረብኛ)-------------------ከፈጣሪ ወደ ነብይ የሚመጣ ሰማያዊ ወይም መንፈሳዊ አስተምህሮ/ትምህርት::

ዙህር(አረብኛ)-------------------እኩለ ቀን ላይ የሚሰገድ ባለ አራት ረከዓ እስላማዊ ፀሎት ወይም ስግደት::

ዚያራ(አረብኛ)-------------------መጎብኘት ወይም ሰላምታ ማቅረብ፡፡

ዠር(ስልጥኛ)--------------------“ወለባ” “ፉጋ”÷”ፋቂ”÷”ቀጥቃጭ” ወዘተ ያልሆነ ሰው

ደረሳ(አረብኛ)--------------------የእስልምና ሃይማኖት ትምህርት ተማሪ ወይም የሸሪዓ ተማሪ፡፡

ደንቄ ወይም አላማ(ኦሮምኛ)--------- ገሪቦች የሚይዙት ባለ ቀንድ ዱላ፡፡

ድቤ(አረብኛ)--------------------ከበሮ -በሠርግና በደስታ ጊዜ የሚመታ ነገር፡፡

ዶሪህ(አረብኛ)----------------- አስክሬን ያረፈበት ቦታ ወይም የመቃብር ቦታ

ገን(ስልጥኛ)--------------------- ዳግማዊ፡፡

ጡሀራ(አረብኛ)-----------------ለፀሎት ወይም ለስግደት መፀዳዳት፡፡

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአልከሶ መውሊድ የአከባበር ስርዓት እና ፎክሎራዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል ማሳየት እና መሰነድ ነው። ይህ ጥናት መጠናቱ ወደ ፊት መውሊድን እና እስላማዊ ከበራዎችን ከፎክሎር አንጻር ለማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች መነሻ በመሆን ያገለግላል። የጥናቱን አላማ ከግብ ለማድረስ መረጃዎች በዋናነት በመጀመሪያ(Primary) እና በተጓዳኝነት በሁለተኛ(secondary) የመረጃ ምንጮች ተሰብስቧል። መረጃው በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት ተሰብስቧል። መረጃ አቀባዮች በዋናነት በታላሚ የናሙና ዘዴ ተመርጠዋል። የተሰበሰበው መረጃ አይነታዊ የጥናት አይነትን በመከተል በዋናነት በክዋኔያዊ ኢትኖግራፊ ንድፈ ሀሳብ ተተንትኗል።

ከላይ የተጠቀሱትን ንድፈ ሀሳቦች በመጠቀም መውሊዱ ሶስት ወር ሲቀረው ጀምሮ እስከ ድህረ መውሊድ ድረስ ያለውን የአከባበር ሁኔታ ተቃኝቷል። የመውሊዱ አከባበር በየጊዜው ያሳየውን ለውጥ፣ በመውሊዱ እነ ማን እንደሚሳተፉበት እና የሃይማኖት መስተጋብር ምን እንደሚመስል በእነዚህ ንድፈ ሀሳቦች ተተንትኖ ቀርቧል።

በዚህ መውሊድ ከከተማ እስከ ገጠር፣ ከልጅ እስከ አዋቂ፣ ከሙስሊም እስከ ክርስትያን እና ሁለቱም ጾታዎች ይሳተፋሉ። በመውሊዱ በርካታ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ፎክሎራዊ ክንውኖች ይከናወኑበታል። ለአብነት ሶላት በጀማ መስገድ፣ መንዙማ ማለት፣ ዚያራ ማካሄድ፣ ንግድ ማከናወን፣ የተለያዩ የስልጤ ብሔረሰብን ፎክሎር መከወን ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። የአልከሶ መውሊድ በዚህ ሁኔታ መከበሩ ለአካባቢው ማህበረሰቡ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ እንደምያስገኝ ጥናቱ አረጋጧል። ከዚህ አንጻር ይህ ጥናት የተከተለው ክዋኔያዊ ኢትኖግራፊክ ምርምር አይነትን ነው።

የበዓሉ መከበር ለአካባቢው ማህበረሰብ ከላይ የተጠቀሱትን ጠቀሜታዎች የሚያስገኝ በመሆኑ በዓሉ በተጠናከረ ሁኔታ እንዲቀጥል የመስጂዱ አስተዳደር እና የዞኑ መንግስት ጠንክሮ መስራት ይጠበቅበታል። ምሁራንም ስፍራውን እና የመውሊዱን አከባበር ከየራሳቸው የጥናት መስክ አንጻር ሊያጠኑት ይገባል።

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

“ፎክሎር” “ፎክ” እና “ሎር” ከሚሉ ሁለት ቃላት የተዋቀረ ፅንሰ ሃሳብ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ “ፎክ” የሰዎች ስብስብ ማለት ነው፡፡ “ሎር” ማለት ደግሞ ዕውቀት ወይም ሰዎችን ያሰባሰበ ርዕሰ ጉዳይ ማለት ነው፡፡ እንደ Dundes (1980፣1)[1] አገላለጽ የሁለቱ ቃላት ጥምረት “የቡድን ዕውቀት” የሚል ነው፡፡ Dundes (1980፣6) “ፎክ” የሚለውን ቃል “የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ፎክ ይባላል” ይላሉ፡፡ ፎክሎር የአንድን ማህበረሰብ አጠቃላይ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ስርዓት፣ እሴት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ አኗኗር ወዘተ የሚያጠና ሰፊና ጥልቅ የሆነ የማህበረሰብ ሳይንስ ዘርፍ ነው፡፡ ለፎክሎር ብያኔ ከመስጠት ይልቅ በስሩ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች መዘርዘር ተመራጭ መሆኑን Alan Dundes (1965) እና Michael Owen Jones (1994) ያስረዳሉ፡፡

Dorson (1972:3-4) ፎክሎርን በአራት ምድብ የመደቡት ሲሆን እነሱም ቁሳዊ ባህል፣ ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድ ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር የሚመደበው ክብረ በዓል ነው፡፡ ክብረ በዓል በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ከሚጠኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ የሀገረሰባዊ ልምድ ዘውግ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ሀይማኖታዊም ሆነ ባህላዊው ክብረ በዓል አንድ ማህበረሰብ ከባህሉ፣ ከሀይማኖቱ እና እምነቱ ጋር በማይጋጭበት ሁኔታ በተወሰነ ጊዜ ተሰብስቦ የሚያከብረው ነው፡፡ ክብረ በዓሉ ስር ከሚጠኑ ጉዳዮች መካከል ደግሞ መውሊድ ይገኝበታል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት ደግሞ የአልከሶ መውሊድ ላይ ነው፡፡

### 1.1 የጥናቱ ዳራ

መውሊድ የአረብኛ ቃል ሲሆን ልደት ወይም መወለድ ከሚሉ የአማርኛ ቃላት ጋር አቻ ትርጉም ቢኖረውም በተለያየ አውድ (Context) የተለያየ ፍቺ አለው፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች

[1] በዚህ ጥናት ውስጥ የሚገኘው የዘመን አቆጣጠር የተገለጸው በአማርኛ የተጻፉ መጻሕፍት በኢትዮጵያ የዘመን አቆጣጠር ሲሆን በእንግሊዝኛ የተፃፉት ግን በአውሮፓ አቆጣጠር ነው፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ዓ.ሂ ሲባል ዓመተል ሂጅራ ወይም በእስላማዊ አቆጣጠር ለማለት ነው፡፡ እንዲሁም የጸሀፊዎችን ስም ስጽፍ በእንግሊዘኛ የጻፉትን በእንግሊዘኛ፣ በአማርኛ የጻፉትን በአማርኛ ጽፌያቸዋለሁ፡፡ እንዲሁም ዓ.ም፡- ዓመተ ምህረት ወይም በኢትዮጵያ አቆጣጠር ማለት ነው፡፡ ዓ.ሂ፡- ዓመተል ሂጅራ ወይም በአረብኛው አቆጣጠር ማለት ነው፡፡ እ.አ.አ፡- እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ማለት ነው፡፡

ጥናት ማዕከል የአማርኛ መዝገበ ቃላት (2001፣36) ልደት የሚለውን ቃል ማንኛውም ሰው የተወለደበት ቀን የሚል ፍቺ ሲሰጠው ብርሃን ተሰማ የአማርኛ መዝገበ ቃላት (1951፡ 52) ደግሞ ልደትን "ሰው ሁሉ በእናቱ ማህጸን ውስጥ ዘጠኝ ወር ተረግዞ መወለድ በስጋ በአካል መለየት ከጠባብ ቦታ ወደ ሰፊ ቦታ የሚወጣበት ቀን" በማለት በይነውታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Encyclopedia of Islam (1987 ቅጽ 4 ገጽ 419) "Mawlid:- time, place, celebraton of the birth of any one. Particularly prophet Muhammad" በማለት ዘግቦት ይገኛል፡፡ Bronislav (2008፣133) "The Arabic word *mawlid* (plural *mawālid*) means simply birthday, birthplace or anniversary, or—in the strict sense of the word—the anniversary of a Muslim "saint"." በማለት ይገልጹታል፡፡

ሀሰን (2008፣11) "መውሊድ ስርወ ቃሉ ወለደ የሚለው የዐረብኛ ግስ ሲሆን ቋንቋዊ ትርጉሙ የመወለጃ ቦታ ወይም ዕለት ማለት ነው" ይላሉ፡፡ ሼኽ ሲራጅ ማህሙድን እና ሼኽ ዐብደላ ኢድሪስን ዋቢ በማድረግ "በሀገራችን አጠቃቀም ደግሞ በየትኛውም ጊዜ ወይም ቦታ በዱዐ አላህን ለመለመን የሚደረግን መሰብሰብ ወይም ድሆችን ሶደቃ ማብላትን የሚያካትት ሰፋ ያለ ትርጉም ይይዛል" በማለት ሀሰን (2008፣12) ያስረዳሉ፡፡ Erman (2016፣) ደግሞ "In the Islamic literature, being derived from the root w-l-d (و□د), the word 'mawlid' (in Turkish, mevlid), which have lexical meanings of birth/giving birth, birth time and birth place, has almost always been used on the purpose of indicating Prophet Muhammad's birthday" በማለት መውሊድ መወለድ፣ የመወለጃ ጊዜ እና ቦታን የሚያመላክት ጽንሰ ሀሳብ እንደሆነ እና በዋናነትም ነብዩ ሙሀመድን እንደሚመለከት ያስረዳል፡፡

መውሊድ የነብዩ ሙሀመድን የልደት ቀን ምክንያት በማድረግ በየአመቱ ረቢኡል አወል ወር የሚከበር ክብረ በዓል ነው፡፡ መውሊድን Encyclopedia Aethiopica (ቅጽ 3 ገጽ 2007፡ 878-880) መውሊድ በሙስሊሞች ዘንድ የነብዩ ሙሀመድ መወለድን ምክንያት በማድረግ ለመታሰቢያነት የሚከበር በዓል እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ቢላል መጽሔት (1967፣23) እና Hisham (1998፣125) እና ሌሎቹም ጸሀፍት መውሊድ መከበር የጀመረው ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው ቢሉም መውሊድ ነብዩ በህይወት በነበሩበት ወቅት ይከበር እንደነበር የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ቡኻሪ እና ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ ነብዩ ሰኞ ቀንን ለምን እንደሚጾሙ ሲጠየቁ "ሰኞ ቀን የተወለድኩባት እና መልዕክተኛ የሆንኩባት ቀን ስለሆነች ነው" እንዳሉ ሀሰን

(2004፣185) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ሀዲስ መረዳት የሚቻለው ነብዩ ለተወለዱባት ቀን ልዩ ትኩረት እንደሰጡ እና ቀኑን በጾሎት (በኢባዳ) ማሳለፋቸውን ነው፡፡ ነገር ግን የነብዩ ሙሀመድ የልደት ቀን ህዝባዊ ወይም ኦፊሴላዊ ሆኖ መከበር የጀመረው በ13ኛው ክፍለ ዘመን ግብጽ ውስጥ እንደሆነ Saleh (2010፣89) ጽፈዋል፡፡ መውሊድ መሰረቱን የጣለው ግብጽ ውስጥ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ተለያዩ የሙስሊም ሀገራት መሰራጨት መቻሉን Gori (2010: 51) እና Schussman (1998:216) ያስረዳሉ፡፡

የመውሊድ አከባበርን ከአፍሪካ አንጻር ስንመለከተው በ4ኛው ክፍለ ዘመን በግብጽ እንደተጀመረ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ መውሊድ የተጀመረው ግብጽ ውስጥ የጀመሩትም "ፋጢሚያህ" ሺዐዎች እንደሆኑ እና "ፋጢሚያህ" ግብጽ ላይ የነገሱት 357 ዓ.ሂ እንደሆነ HILLENBRAND(1994፣59) ያስረዳሉ፡፡ Damas (2011፣10) ደግሞ ነብዩ ሙሀመድ የተወለዱበትን ቀን በተለያየ ሁኔታ ካከበሩ በኋላ የእሳቸውን አርአያ በመከለተል ግብጽ ውስጥ ይኖሩ የነበሩ ሺዐዎች ማክበር እንደጀመሩት እና ከእነሱ በመከተል ሙዛፋር የተባለ የአርቢል ንጉስ ህዝባዊ በዓል አድርጎ ማክበር እንደጀመረ ያስረዳሉ፡፡ ከግብጽ በመቀጠል የሰሜን አፍሪካ ሀገራት መውለድን ማክበር መጀመራቸውን Seid (2011፣8) ያስረዳሉ፡፡

ከኢትዮጵያ አንጻር ስንመለከተው ደግሞ በሀገራችን በተለይም በሰሜኑ ክልል በተናጠል ይከበር የነበረውን የመውሊድ መታሰቢያ ወደ ተደራጀ ስርዓት የለወጡት እስከ 1798 ዓ.ህ የቆዩትና ጀማንጉስ ወይም ሙጃሂዱ በመባል የሚታወቁት ታላቁ ዐሊም ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ መሆናቸው ይነገራል በማለት ሀሰን (2008፣39-41) ያስረዳሉ፡፡ መውሊድ ይፋ ባልሆነ ወይም ህዝባዊ በዓል ሳይሆን ሲከበር ለረጅም አመታት ከቆየ በኋላ በይፋ እና መንግስት በሚያውቀው ሁኔታ መስጂድ ውስጥ በመሰባሰብ መከበር የተጀመረው ግን በ1953 ዓ.ም በአዲስ አበባ ከተማ በአንዋር መስጂድ ነው፡፡ የደርግ መንግስት ለህዝቡ ጥያቄ መልስ እየሰጠሁ ነው ለማለት ከተጠቀመባቸው ጉዳዮች መካከል የረቢኡል መውሊድ አንዱ ነው፡፡ እንደ Encyclopedia Aethiopica (ቅጽ 3 ገጽ 2007፡ 878-880) አገላለጽ የደርግ መንግስት መውሊድ ሶስተኛ እስላማዊ በዓል ሆኖ እንዲከበር ፈቃድ ሰጠ፡፡ በመሆኑም በዓሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ በዓል(Public holiday) በመሆን ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ በይፋ መከከበር ጀመረ፡፡

በሀገራችን የረቢኡል አወል ሆነ ዓሊሞችን መሰረት በማድረግ የሚከበሩ መውሊዶች በአከባበር ይዘታቸው በብዛት ተመሳሳይነት እንዳላቸው ከተመለከትኳቸው ጥናቶች መረዳት ችያለሁ፡፡ በረቢኡል አውል መውሊድ በብዛት የሚወሱት ነብዩ ሙሀመድ ሲሆን ዓሊሞችን መሰረት

አድርገው በሚከበሩ መውሊዶች ላይ ግን በብዛት የሚወሱት መውሊዱ የሚከበርላቸው ዓሊም ገድል ነው፡፡

በሀገራችን መውሊድ ህዝባዊ በዓል ሆኑ እንዲከበር ጥረት የተጀመረው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ምክንያቱም ከ18ኛው በፊት መውሊድ በሀገራችን በተበታተነ ሁኔታ ይከበር ነበር፡፡ ነገር ግን ከዚህ ዘመን ጀምሮ ታላቁ ዐሊም ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ እና ዳኒዮ አወል አማካኝነት መውሊድ በተደረጃ ሁኔታ እንዲከበር ጥረት እንዳደረጉ ሙፍቲህ ዑመር እድሪስ፣ ሀሰን(2008፣40) እና አህመዲን(2008፣247) ያስረዳሉ፡፡

ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ዓሊሞች መውሊድን በተጠናከረ ሁኔታ እንዲከበር ማድረጋቸው መውሊድን ማጠናከር ብቻ ሳይሆን ከሃይማኖታዊነት በስተጀርባ በርካታ ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ስነልቦናዊ ዓላማ ያነገበ እንደነበር አህመዲን(2007፣129) ያስረዳሉ፡፡ አህመዲን እና ሀሰን ለዚህ ሀሳባቸው ማጠናከሪያ ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ የቁሳቁስ እርዳት ለመጠየቅ ወደ ሳውዳረቢያ(መካ) ያደረጉትን ጉዞ በምሳሌነት ይጠቅሳሉ፡፡ በመሆኑም መውሊድ መከበሩ ከሃይማታዊነቱ በሻገር ሌላም አንድምታ እንዳለው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ Saeid (2011፣10) የተባለ አጥኚ ሊቢያ ውስጥ ስለሚገኙ መስጂዶች እና ስለሚከናወንባቸው ክንውን ባጠናበት ጥናት በመስጂዶች ውስጥ ከሃይማታዊ ክንውን በተጨማሪ በርካታ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሌሎችም ክንውኖች እንደሚከናወኑ ያስረዳል፡፡ የሀገራችንንም የመውሊድ አጀማመር ታሪክ ስናጤን አጥኚው ከገለጸው ሁኔታ ጋር መሳለመሳ የሚሄድ መሆኑን እንረዳለን፡፡

ባህሩ (2007፣240)፣ ቢላል መጽሔት(1967፣45)፣ እና Hussein (2006:10) በ1966 ዓ.ም የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ ሙስሊሙ ማህበረሰብ መውሊድ አንዱ ህዝባዊ የሙስሊም በዓል እንዲሆን ከመጠየቅ የዘለለ በወቅቱ በአጼው ስርዓት በሙስሊም ህዝብ ላይ ይደርስ የነበረውን ጭቆና እንዲቆም የጠየቀበት እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ ማሳያ በሰላማዊ ሰልፉ ከተስተዋሉ መፈክሮች መካከል “እኚ ሙስሊሞች መብታችን ይከበር”፣ “በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች መባላችን ቀርቶ ኢትዮጵያዊያን እስላሞች እንባል”፣ “መውሊድን ተሰብስበን በጋር እንድናከብር ይፈቀድል”፣ “የመስጂድ ማሰሪያ ገንዘብ መንግስት ይስጠን”፣ የሙስሊም ትምህርት ቤቶች ይከፈቱልን ወዘተ ይዘት የነበራቸው እንደነበሩ Østebø (2008፣417) እና Hussein (2006:12) ያስዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በህንድ ሀገር የሚገኙ ሙስሊሞች መውሊድን ከሃይማኖታዊ በዓልነት ባሻገር ለፖለቲካዊ ፍጆታ እንደሚውል FAREEN(2017፣218)

ያስረዳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በተመሳሳይ ሁኔታ ግብጽ ውስጥ እንዳለም Bronislav(2008፣135) ያስረዳ፡፡

ስለዚህ ከእነዚህ እና መሰል መረጃዎች መረዳት የምንችለው በሀገራችን መውሊድ ህዝባዊ ሆኖ እንዲከበር ጥረት የተደረገበት ምክንያት ለሃይማኖታዊ አላማ ብቻ ሳይሆን የሙስሊሞችንም መብት ለማስከበር የተለመ እንደነበር መረዳት ይቻላል፡፡ ይህ እውነታ ሀገራችዊ ብቻ ሳይሆን አለማቀፋዊ ጉዳይ እንደሆነ በመውሊድ ላይ ከተካሄዱ ጥናቶች መረዳት ይቻላል፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለማካሄድ ያነሳሱኝ ምክንያች በርካታ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

➢ ከዚህ ጥናት በፊት በእስላማዊ ክብረ በዓላት ላይ የተካሄዱ ጥናቶች ክፍተት እንዳለባቸው መረዳቴ ይህን ጥናት ለማጥናት አነሳስቶኛል፡፡ በዚህ የትምህርት መርሐ ግብር ውስጥ ለተለያዩ ኮርሶች ማሟያ የተለያዩ ጥናታዊ ጽሁፎችን በምሰራበት ጊዜ እስላማዊ ክብረ በአላት ላይ የተጠኑ ጥናቶች ክፍተት እንዳለባቸው ተመለከትኩ፡፡ የተመለከትኳቸው ጥናቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ Amira Kedir “The Qatbare Sheikh Mawlid Celebration and intera faith debate on the mawlid celebration”፣ Gemechu Jemal “The Faraqasa indigenous pilgrimage center: History and ritual practices and “Pilgrimages and Syncretism: Religious Transformation among the Arsi Oromo of Ethiopia”፣ Mamarama Seck “The Structure of Wolof Sufi: Oral Narratives: Expanding the Labovian and Longacrean Model to Accommodate Wolof Oral Tradition”፣ Erman “The Royal Mawild Ceremonies in the Ottoman Empire (1789-1908)”፣ እና ሌሎችም በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተሰሩ ናቸው፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ደግሞ ሰሚራ መሀመድ “ጡሩሲና የሙስሊም ገዳም እና በገዳሙ ውስጥ የሚከበሩ በአላት ስርአተ ክዋኔ” እና አብዱልረህማን ፋንታሁን፤ “የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼኽ ዳንግላ) የመውሊድ በአል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት” የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ በእነዚህ ጥናቶች ላይ የተመለከትኳቸውን ክፍተቶቹን ከሶስት አቅጣጫ የሚታዩ ናቸው፡፡ አንደኛ ከስነ ዘዴና ንደፈ ሀሳብ አንጻር፣ ሁለተኛ አልመውት የተነሱት ዓላማ

ከግብ ካለማድረስ አንጻር እና ሶስተኛ መረጃ ከማጥራት፣ በትክክለኛው አውድ ከመሰብሰብና ከመተንተን አንጻር ነው፡፡ ስለዚህ ከዚህ በላይ የጠቀስኳቸው ጥናቶች የየራሳቸው የሆነ ክፍተት አለባቸው፡፡ በመሆኑም እኔ በክብረ በአላት ውስጥ የሚመደበው መውሊድ ላይ ጥናት በማካሔድ ክፍተቱን በተወሰነ ደረጃ እሞላለሁ ብዬ ስላሰብኩ በመውሊድ ላይ ጥናት ለማካሔድ ወሰንኩ፡፡

ከዚህ በላይ ክፍተት አለባቸው ያልኳቸው ጥናቶች ክፍተታቸው እና ጥንካሬያቸው ምን እንደሆነ በምዕራፍ ሶስት የቀደምት ጥናቶች ቅኝት በሚለው ንኡስ ስር አሳይቻለሁ፡፡ በ2009 ዓ.ም መሀመድ ዓሊ በቦረና ወሎ በሶስት የሱፊ ማዕከሎች የሚካሄዱ ከበራዎችን የዳሰሰበት ጥናት ካሄዷል፡፡ ይህ ጥናት የራሱ የሆነ ክፍተት አለው፡፡ በዚህ ጥናት የእሱን ክፍተት እንደመነሻ ያላነሳሁበት ምክንያት የመሀመድ ጥናት የቀረበው የእኔ ጥናት ሊጠናቀቅ ወራት ሲቀሩት ስለሆነ ነው፡፡ ነገር ግን የመሀመድን ጥናት በምዕራፍ ሶስት የቀደምት ጥናቶች ቅኝት በሚለው ርዕስ ስር ዳስሼዋለሁ፡፡

- ሌላው የአነሳሳኝ ምክንያት የስልጤ ብሔረሰብ ባህል በወጉ በስፋ እና በጥልቀት አልመጠናቱ ነው፡፡ ፎክሎር አካባቢውን፣ ቋንቋውን እና ባህሉን የሚያውቀው ሰው ቢያጠናው በአንጻራዊነት የተሻለ መረጃ ሊገኝ እንደሚችል ፈቃደ (1991፣85) እና Ben-Amos (1993፣127) ይስማማሉ፡፡ በ1999 የመጀመሪያ ዲግሪዬን የስልጤ ብሔረሰብ ተረት ላይ የሰራሁ ሲሆን የሁለተኛ ዲግሪዬን የስልጤ ብሔረሰብ የባህል ምግብ ላይ በመስራት ባህሉን ማሳየት ችያለሁ፡፡ ከእኔ በተጨማሪ ስሩር በድሩ በ1995 የስልጤ ብሔረሰብ ተረት ላይ፣ አሊማ ጀማል በ1989 የስልጤ ብሔረሰብ የሰርግ ዘፈኖች ላይ፣ ደረጀ ተፈራ በ2003 የስልጤ ብሔረሰብ የግጭት አፈታት፣ ከይረዲን 2016 የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ ግጭት አፈታት ከሃይማኖት አንጻር፣ ዘሪሁን ወልደስላሴ በ2013 በብሔረሰቡ ወልይ ስለሚባሉ ሰዎች ወዘተ ጥናቶችን አካሂደዋል፡፡ እነዚህ ጥናቶች የተጠኑት በመጀመሪያ እና ለሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያነት የተጠኑ በመሆናቸው የብሔረሰቡ ባህል በሰፊው እና ሳይንሳዊ በሆነ ሁኔታ አጥንተውታል ለማለት ያዳግታል፡፡ ስለዚህ ብሔረሰቡ ባህል በሰፊው፣ በጥልቀት እና ሳይንሳዊ በሆነ ሁኔታ መጠናት አለበት፡፡ የብሔረሰቡ ባህል በሰፊው የሚጸባረቅበት እና የባህሉ አንድ አካል የሆነውን እና በደመቀ ሁኔታ የሚያከብረው የአልከሶ መውሊድም በሚገባ አልተመረመረም አልተጠናም፡፡ ስለዚህ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ጥናት በማካሔድ ብሔረሰቡን እና ባህሉን የበለጠ ማስተዋወቅ እችላለሁ ብዬ ስላሰብኩኝ የሦስተኛ ዲግሪዬንም በዚሁ በሰፊው ባልተጠናው ብሔረሰብ ባህል ለማካሄድ ተነሳሳሁ፡፡

➢ በ2006 ዓ.ም “Seminar on Oral History” ለሚለው ኮርስ(ትምህርት) ማሟያ አንድ አጠር ያለ ጥናታዊ ጽሁፍ እንድናዘጋጅ መምህሩ አድርገው ነበር፡፡ በዚህ ወቅት እኔ “የመውሊድ አከባበር በአዲስ አበባ በሶስቱ የመንግስት የአስተዳደር ዘመናት” በሚል ርእስ ጥናት አካሂጃለሁ፡፡ ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ በአንዋር መስጂድ የ2006 ዓ.ም መውሊድ ሲከበር እና “ነሲሃ ኢስላዊ የዳዕዋ ቡድን” በአዲስ አበባ የስብሰባ አዳራሽ መውሊድን ሲያከብሩ ተመልክቻለሁ፡፡ ከእነዚህ ቦታዎች በተጨማሪ የተለያዩ መውሊድ የሚከበርባቸው መኖሪያ ቤቶች ተዘዋውሬ ተመልክቻለሁ፡፡ በተዘዋወርኩበት ወቅት መውሊድ በሀገራችን ሲከበር በርካታ ባህላዊ እና ማህበራዊ ክንውን እንደሚከናወንበት ተረዳሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ሁኔታ መውሊድ በሰፊው ከፎክሎር አንጻር መጠናት እንዳለበት አሳይቶኛል፡፡ ይህን ሁኔታ በመገንዘብ መውሊድ ከፎክሎር አንጻር ቢጠና ጥሩ ምርምር ይሆናል ብዬ ማመኔ ይህን ጥናት እንዳጠና አነሳስቶኛል፡፡

## 1.3 የጥናቱ ዓላማዎች

ይህ ጥናት ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች አሉት፡፡ እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 1.3.1. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የአልከሶ መውሊድ አጠቃላይ የአከባበር ስርዓት፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል ከፎክሎር አንጻር መመርመር፣ መተንተን እና መሰነድ ነው፡፡

### 1.3.2. የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- ➢ የመውሊድ በዓል አጀማር እና አከባበር በስልጤ ብሔረሰብ ምን እንደሚመስል ማሳየት፣
- ➢ በመውሊድ ከበራ ወቅት ምን ምን ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክንውኖች እንደሚከናወኑ ማብራራት፣
- ➢ በመውሊድ ከበራ ወቅት ምን አይነት ማህበራዊ መዋቅር እንዳለ እና የመውሊዱን የአከባበር ስርዓት የሚመራው ሃይማኖታዊ የአመራር ስርዓት ምን እንደሚመስል ማሳየት፣
- ➢ ይህ መውሊድ ለበርካታ ዓመታት የተከበረ በመሆኑ በዘመን እና በሁኔታዎች መለወጥ የተነሳ የተስተዋሉ ጉልህ ጉልህ ለመውጦችን ማመላከት ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ፎክሎር በባህርይው ተለዋዋጭ እንደሆነ እሙን ነው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረትም የአልከሶ መውሊድን ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት በመሆኑ የበዓሉ አከበባር ሁኔታ የድሮው እና የአሁኑ መጠነኛ

ልዩነት እንዳለው መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት መረጃ አቀባዮቹ ልዩነት አላቸው ያሏቸውን ጉዳዮች ላይ ለረጅም ጊዜ በዓሉን የአከበሩ የእድሜ ባለጸጋዎችን በማነጋገር ማሳየት አንዱ ንዑስ ዓላማው ነው፡፡

- መንዙማዎች ከነክዋኔያቸው ምን እንደሚመስሉ እና በመውሊድ ጊዜ የሚነገሩ ስነቃሎችን እና ስለአልከስዬ የሚተረኩ ተረኮችን መተንተን ፣
- በመውሊድ የሃይማኖት መስተጋብር ምን እንደሚመስል እና መስተጋብሩ በአካባቢው ማህበራዊ ህይወት ላይ ምን አይነት ተጽዕኖ እንዳለው ማሳየት[2]፣
- የአልከሶ መውሊድ አከባበር እንዳይቀጥል የሚያደርጉ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ እና ምን ምን ምቹ ሁኔታዎች እንዳሉ ማስረዳት ናቸው፡፡

## 1.4 ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች

- መውሊድ በዓለም፣ በአፍሪካ፣ በኢትዮጵያ እና በስልጤ ብሔረሰብ ዘንድ መቼ እና እንዴት መከበር ተጀመረ?
- የአልከስዬ የህይወት ታሪክ ምን ይመስላል? ስለ አልከስዬ ከራማ ምን ምን ትርክቶች ይተረካሉ?
- በመውሊዱ ምን ምን የስልጤ ብሔረሰብ ፎክሎር/ባህል ይንጸባረቃል? እንዴትስ ይንጸባረቃል?
- በመውሊድ ሰሞን ምን ምን ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ክንውን ይከናወናሉ?
- በበዓሉ የሃይማኖት መስተጋብር እንዴት ይንጸባረቃል?
- የበዓሉ መከበር ለአካባቢው ማህበረሰብ ምን ምን ጠቃሜታ አለው?
- በበዓሉ ምን ምን ባህላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ክዋኔዎች ይከወናሉ?

---

[2] ፎክሎር እና ልማት የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ ፎክሎር እና ልማት እንዴት እንደሚቆራኙ ፈቃደ አዘዘ በ2004፣110-111 ቁዘማ- ፎክሎር(ባህል) እና ልማት በኢትዮጵያ በሚል ርዕስ በጻፉት መጣጥፍ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ "ቁሳዊና መንፈሳዊ ባህልን መሰብሰብ፣ ማጥናት፣ እና መተንተን ለልማት አስተዋጽኦ አለው? የእኔ አጭር መልስ አዎ ነው፡፡ ስለ ልማት ሲወሳ ስለሳይንስና ቴክኖሎጂ እና ስለልማት እና እድገት ብቻ ማውራት በጣም ተለምዷል፡፡ ምክንያቱም ልማት ሲባል ቁሳዊ ለውጥ ብቻ ተደርጎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ አንድ የልማት ስራ ሲታሰብ ስራው ይስራል ተብሎ የሚታሰበው የሰው ፍላጎት፣ እምነት፣ የህይወት ፍልስፍና የመኖሪያ አበይት እሴቶች፣ ክሂሎቶች ወዘተ መታወቅ አለባቸው፡፡ እነዚህንም ለማወቅ ደግሞ የተለያዩ ባህሎችን ወይም ፎክሎሮችን (ማለትም ተረቶችን፣ አሂዶዎችን፣ገድሎችን፣ ታምራቶችን፣ እቆቅሎሾችን፣ የህይወት ፍልስፍናዎችን፣የሽክላና የአንጥረኛ ስራዎች፣ ልዩ ልዩ እምነቶችን እሴቶችን እና የአምልኮዎችን ወዘተ) ማጥናት ይገባል፡፡ በዚህ መልክ ባህሉን አውቆ ሊሰራ የታቀደውን ስራ በዚህ ባህል ውስጥ አቀላጥፎ እንዴት ማከናወን እንደሚቻል አስቦ፣ ዋና ተዋናይ እና ጥንካሬ ሀይል አድረጎ መራመድ ካልተቻለ የልማቱ ስራ ችግር ይገጥመዋል፡፡ በጥቅሉ ሲነገር፣ ባህል ለልማት አስተዋጽኦ ያደርጋል ማለት ይህ ይመስለኛል፡፡"

- በበዓሉ ከበራ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ምን ምን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ጥናቱ ለመመለስ ሞክሯል፡፡

## 1.5 የጥናቱ ጠቀሜታዎች

ይህ ጥናት የሚከተሉት ዋና ዋና ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ብዬ አስባለሁ፡፡

- እስልምናን መስረት ያደረጉ እንደ መውሊድ ያሉ ክብረ በዓላት ከፎክሎር አንጻር በሰፊው እንዳልተጠኑ በተለያዩ ቤተመጻህፍት እና ድረ ገጾች ባደረኩት ቅኝት መረዳት ችያለሁ- በተለይ የኢትዮጵያ፡፡ መውሊድ ብቻ ሳይሆን የሙስሊሞች አጠቃላይ ባህል ወይም ፎክሎር በሚገባ ትኩረት ተሰጥቶት ሲጠና አይስተዋልም፡፡ ጥቂት ብልጭታዎች የሚስተዋሉ በመሆኑ ግን ይበል የሚያስብል ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ጥናት በእስላማዊ የፎክሎር ጥናት ላይ ያለውን ክፍተት በመሙላት የራሱን አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡
- ይህ ጥናት የበዓሉን አከባበር በፎቶግራፍ፣ በድምጽ እና በቪድዮ ይሰንዳል፡፡ ምክንያቱም ፎክሎር በባህርይው ተለዋዋጭ በመሆኑ አሁን ያለው ሁኔታ ተሰንዶ መቀመጥ አለበት፡፡ መሰነዱ ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ አንዱ ለመጪው ትውልድ አሁን ያለውን ሁኔታ ሰንዶ ማስቀመጥ ሲሆን ሌላው የድሮውን ካሁኑ ጋር ወይም ያሁኑን ወደፊት በዚያን ዘመን ከሚኖረው ጋር በንጽጽር ለማጥናት ይረዳል፡፡ የአልከሶ መውሊድ መጠናት ከዚህ በላይ የተገለጹትን ሁለቱንም ሚና የሚጫወት መሆኑ የዚህ ጥናት መጠናት ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡
- ጥናቱ የሚካሔደው በስልጤ ህዝብ ዘንድ በሚከበረው በዓል ላይ ስለሆነ የስልጤ ዞን እና የአካባቢውን ማህበረሰብ (ባህል፣ዕምነት፣አኗኗር፣ ፍልስፍና፣ እሴት፣ ወዘተ) በተወሰነ ደረጃ ለማያውቁት ያስተዋውቃል፡፡
- ይህ ጥናት የበዓሉን ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ስለሚያሳይ የመውሊድ በዓል የሚከበርበትን ባህላዊና ማህበራዊ አውድ ማወቅ ለሚፈልጉ ሰዎች ያገለግላል፡፡
- በዓሉን በሚያከብሩት እና በማያከብሩት መካከል ያለው ማህበራዊ ግንኙነት ምን ይመስላል በመካከላቸው ያለው ግንኙነት በአካባቢው ማህበራዊ እና ልማታዊ ጉዳይ ላይ ምን አይነት አዎንታዊ እና አሉታዊ ተጽዕኖ እንዳለው ለማወቅ ይረዳል፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በጊዜ፣ በቦታ እና በርዕሰ ጉዳይ የተገደበ ነው፡፡ ከርዕሰ ጉዳይ እና ከቦታ አንጻር ጥናቱ የሚያተኩረው በስልጤ ዞን፣ በስልጢ ወረዳ ውስጥ በሚገኘው አልከሶ መውሊድ ላይ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የሚዳሰሰው ርዕሰ ጉዳይ የተገደበ ነው፡፡ በአልከሶ መውሊድ አከባበር ጊዜ ይህ ጥናት የሚመለከተው የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ፣ የምርቃት (የዱኣ) አደራረግ ሁኔታ፣ የጫት አቃቃም ሁኔታ፣የአዘያየር(የጉብኝት) ስርዓት፣ የወጣቶች፣ የገሪቦች እና የክርስትያኖች የመውሊድ አከባበር ሁኔታ፣ የአመጋገብ ሁኔታ እና በመውሊድ ሰሞን የሚከናወኑ አጠቃላይ ማህበራዊ እና ባህላዊ ክንውኖች የዚህ ጥናት ዋና ዋና ትኩረቶች ናቸው፡፡ ስለዚህ በቅድመ መውሊድ፣ በመውሊድ ቀን እና በድህረ መውሊድ የሚከናወኑ ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ክንውኖች የሚዳሰሱ ይሆናል፡፡ ስለዚህ የመውሊዱ ዝግጅት ሶስት ወራትን የሚፈጅ ቢሆንም የዚህ ጥናት በዋናነት የሚያተኮረው ግን ዋና በዓሉ ሊከበር አስራ አምስት ቀን ሲቀረው ጀምሮ እስከ በዓሉ ከወጣ አስራ አምስት ቀን ድረስ ያለው ላይ ነው፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት የበዓሉ ዝግጅት በዋናነት የሚጀምረው ለዋናው በዓል አስራ አምስት ቀን ሲቀረው በመሆኑ ቅድመ ዝግጅቱ ምን እንደሚመስል ለመከታተል ነው፡፡ በዓሉ ከተከበረ በኋላ እስከ አስራ አምስት ቀን የሆነበት ምክንያት ዋናው በዓል ከወጣ በሶስተኛው ቀን የመሰነባበቻ “ስልስላ” የሚባለውን ዝግጅት ለመከታተል (ለመመልከት) ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዓሉ ከወጣ እስከ አስራ አምስት ቀን ድረስ በቦታው የሚቆዩ ምዕመናን ስላሉ ለጥናቱ የሚሆን ተጨማሪ መረጃዎች ከእነዚህ ምዕመናን ስለሚገኝ እቦታው ላይ በመቆየት መረጃ ለማሰባሰብ ነው፡፡

በሌላ መልኩ ከመረጃዎች መሰባሰቢያ ዘዴዎች ፣ ከመተንተኛ ቲዮሪዎች፣ የመረጃ አቀባዮች ብዛት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መቼት ብዛት ውስን እንዲሆን ተደርጓል:: የመቼት፣ የመረጃ አቀባዮች እና የትዮሪዎች ብዛት የተገደበው ከተሰበሰበው ጥሬ መረጃ አንጻር ነው፡፡ ዝርዝር ሁኔታው በምዕራፍ ሶስት ውስጥ ቀርበው ከምዕራፍ አምስት ጀምሮ ተግባራዊ ሆነዋል:: ከትንታኔ አኳያ በርካታ ቲዮሪዎች የተዳሰሱ ሲሆን ከእነዚህም ውስጥ አብዛኞቹ በደጋፊ መተንተኛነት ሲያገለግሉ በዋና መተንተኛነት ክዋኔያዊ እና ተግባራዊ ቲዮሪዎች ላይ እንዲወሰን አድርጌያለሁ:: ዝርዝር ሁኔታው በምዕራፍ ሶስት ውስጥ ቀርቦ ከምዕራፍ አምስት እስከ ዘጠኝ በሥራ ላይ ውለዋል::

ምንም እንኳን ከዚህ በታች እንደምንመለከተው መረጃው ተሰብስቦ ቢተነተንም የራሱ የሆነ ውስንነት እንደሚኖረው አያጠያይቅም፡፡ ጥናቱን ምልዑ ለማድረግ ጥረት ቢደረግም የሚጎሉት ጉዳዮች የሉትም ለማለት አይቻልም፡፡ ይህም የሆነው የጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ በጣም ሰፊ በመሆኑ ሁሉንም የአከባበር ስርዓት ለመውሊዱ ሶስት ወር ሲቀረው ጀምሮ መዳሰስ ባለመቻሉ ውሱንነቶች አሉት፡፡ ይህ የሆነው ለጥናቱ የተበጀተው ጊዜና ገንዘብ ማነስ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ እንዲሁም ጥናቱ የሚሰራው በአማርኛ ቋንቋ በመሆኑ እና ለመረጃነት የሚያገለግሉት ጥናታዊ ጽሑፎችም ሆኑ አጋዥ መጻሕፍት በእንግሊዝኛ እና አረብኛ ቋንቋዎች የተሰሩ በመሆናቸው ወደ አማርኛ ቋንቋ በመመለሱ ሂደት ላይ ውሱንነቶች አጋጥመውኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አብላጫ መረጃ አቀባዮች መረጃ የሰጡት በስልጥኛ በመሆኑ ወደ አማርኛ ሲተረጎም ክፍተቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡

## 1.7 የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት በአጠቃላይ አስር ምዕራፎችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ አንድ አጠቃላይ ጥናቱን ያስተዋውቃል፡፡ ምዕራፍ ሁለት የስልጤ ብሔረሰብን በአጭሩ ያስተዋውቃል፡፡ ምዕራፍ ሶስት የጽንሰ ሀሳብ እና የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፎችን ይዟል፡፡ ምዕራፍ አራት የጥናቱን የአጠናን ስልት ሲያሳይ ምዕራፍ አምስት የአልከስዬ ህይወት ታሪክ፣ ከራማ እና የመስጂዳቸው አመሰራረት የቀረበበት ነው፡፡ ከምዕራፍ ስድስት እስከ ዘጠኝ ከመስክ በተለያዩ ዘዴዎች የተሰበሰቡ ጥሬ መረጃዎች በፈርጅ ፈርጅ ተደራጅተው ከቀድምት ጥናቶች እና ከተለያዩ ትወራዎች አንጻር ተተንትነዋል፡፡ በመጨረሻም በምዕራፍ አስር የጥናቱ ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳቦች ቀርበውበታል፡፡

## 1.8 የጥናቱ ስነ ምግባር

አንድ አጥኝ ጥሩና ትክክለኛ የሆነ ጥናትና ለማካሄድ ተጠኚውን ማህበረሰብ እና የማህበረሰቡን ባህል እና ወግ በሚገባ ማወቅ እና ማክበር፣ የጥናቱን ዓላማ በግልፅ ማሳወቅ የጥናት ስነ ምግባሮች ሊጠብቅና ሊተገበር እንደሚገባው Dawson (2007፣28) ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥናት የዋለው መረጃ የተሰበሰበው የሙያው ስነ ምግባር በሚያዘው መሰረት እና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ነው፡፡ በመጀመሪያ ለስልጢ ወረዳ ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ቀጥሎም ለስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች መምሪያ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ያጻፍኩትን ደብዳቤ በማቅረብ ጥናቴን

በመረጥኩት ቦታ እንዳካሄድ እንዲፈቀድልኝ አድርጌያለሁ፡፡ በመቀጠልም መስጂዱን እና ሀረሙን ለሚጠብቁ እና ለሚያስተዳድሩ ሰዎች ማንነቴን እና ለምን አላማ እንደሄድኩ በማሳወቅ በቦታው ጥናቴን እንዳካሄድ እንዲፈቅዱልኝ አድረጌያለሁ፡፡

መስክ ላይ ደግሞ ለእያንዳንዱ መረጃ አቀባዮች ስለ ማንነቴ እና መረጃ ለምን አላማ እንደምሰበስብ አስረድቻለሁ፡፡ አንድንም መረጃ አቀባይ በተለየዩ ጥቅማ ጥቅም በመደለል ወይም በሌላ መንገድ መረጃ እንዲሰጠኝ አላደረኩም፡፡ ነገር ግን መረጃ አቀባዮች መረጃ በሚሰጡኝ ቦታ ጫት እና ምግብ ገዝቻለሁ፡፡ ለምሳሌ አልከሶ ከተማ ላይ ለወጣት አብዱልባቅ ጀማል ቃለ መጠይቅ ሳደርግለት መጀመሪያ ምሳ ገዝቼለት ነው፡፡ ይህን ያደረኩት ለመደለል ሳይሆን ሰአቱ የምሳ ሰዐት ስለነበረ እና "ለምሳ ወደ ቤት ልሄድ ነው" ሲለኝ ጊዜ ለመቆጠብ ነው፡፡ እንዲሁም በ2007 እና 2008 ዓ.ም የተተኳሪ የቡድን ውይይት ሳደርግ ጫት ገዝቻለሁ፡፡ ጫት የገዛሁበት ምክንያት አንደኛ በአካባቢው ጫት በስፋት ስለሚቃም ሲሆን ሁለተኛ የአካባቢው ነዋሪዎች ለረጅም ሰአት ቁጭ ብለው መወያየት የሚችሉት አጠገባቸው ጫት ሲኖር እንደሆነ ስለተረዳሁ ነው፡፡ ለምሳሌ በ2007 ዓ.ም የቡድን ውይይት በማደርግበት ቀን ሀረሙ አካባቢ ጫት ስላልነበረ ለወጣት ፈተረሁፍ ብር ሰጥቼ አልከሶ ከተማ ሄዶ ጫት እንዲያመጣ አድርጌያለሁ፡፡ በዚህ ቀን ተወያዮቹ ጫት ሳይመጣላቸው ውይይታቸው ቀዝቀዝ ያለ ነበር፡፡ ነገር ግን ጫት ከመጣላቸው እና ከቃሙ በኋላ ሁሉም በንቃት ተሳትፈዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መረጃ አቀባዮቹ ስማቸው እና ፎቶ ግራፋቸው በዚህ ጥናት እንዲወጣ አስፈቅጃለሁ፡፡ የአንድም መረጃ አቀባይ ስምም ሆነ ፎቶ ያለመረጃ አቀባዩ ፈቃድ በዚህ ጥናት አላካተትኩም፡፡ ከመረጃ አቀባዮች መካከል ድምጻቸው እንዲቀረጽ እና ፎቶ ለመነሳት ፈቃደኛ ያልሆኑ መረጃ አቀባዮች ሲያጋጥሙኝ መረጃቸውን በማስታወሻ ደብተር ይዣለሁ፡፡

## 1.9 ያጋጠሙ ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሔዎች

አንድ አጥኚ ጥናቱን በሚያካሄድበት ወቅት ያላንዳች ተግዳሮት ጥናቱን ያከናውናል ማለት አይቻልም፡፡ እኔም እንደማንኛውም አጥኚ ጥቂት የማይባሉ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ ዋና ዋና የምላቸው ችግሮች እና ችግሮቹን ለመፍታት የወሰድኳቸው መፍትሔዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

በ2007 ዓ.ም ከአካባቢው ከራቅሁኝ ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ የአልከሶ መውሊድ ሲከበር ለማየት ወደ አልከሶ በሄድኩበት ቀን የትራንስፖርት ችግር አጋጥሞኛል፡፡ ወደ ስፋራው

ለመሄድ አዲስ አበባ አውቶብስ ተራ መናኸሪያ ሲሄድ ወደ ወራቤም ሆነ አልከሶ የሚሄድ መኪና አጣሁኝ፡፡ ጠዋት አራት ሰአት መናኸሪያ የገባሁት እዝያው እያለሁ ከቀኑ ሰባት ሰአት ሆነ፡፡ ዕለቱ የረቢየል አወል መውሊድ የሚከበርበት ቀን ስለነበረ መቅረት እንደሌለብኝ በመወሰን ጉዞ ወደ ቡታጀራ አደረኩኝ፡፡ ቡታጅራ ደግሞ የሳምንቱ የገበያ ቀን ነበር፡፡ ወደ አልከሶ መሄዱን ተውኩትና የወረዳው መቀመጫ ወደ ሆነችው ቅበት ከተማ ሄድኩ፡፡ በዚህ ወቅት የወረዳ ባህል፣ቱሪዝም እና  የመንግስት ኮሚኒኬሽን ቢሮ በመሄድ ምልከታ እንዳደርግ እና ሰዎችን እንዳናግር ፈቃድ እንዲሰጠኝ ጠየኩኝ፡፡ በወቅቱ የቢሮው ሀላፊ የነበሩት ወ/ሮ ሽምሲያ ያለ ምን ቅድመ ሁኔታ ፈቃድ ሰጥተውኝ ከቢሯቸው ወጣሁኝ፡፡

በመቀጠልም ወደ አልከሶ ሀረም  በመሄድ የማታውን ድባብ መመልከት ስለነበረብኝ ምናልባት መኪና ካገኘሁ ልሞክር ብዬ መኪና መንገድ ዳር ከአንድ ሰአት በላይ ብቆምም መኪና ላገኝ አልቻልኩም፡፡ በመጨረሻም ማደሪያ ቦታ ለማፈላለግ በመንቀሳቀስ ላይ እያለሁ ከአዲስ አበባ ወደ ወራቤ የሚሄድ በተለምዶ ፒካፕ የሚባለው ኋላው ክፍት የሆነ የቢሮ መኪና አግኝቼ እስከ አልከሶ ከተማ እንዲወስደኝ ጠየኩት፡፡ የመኪናው አሽከርካሪም "እንደምታየው ጋቢና ቦታ የለኝም፡፡ ከኋላ እንዳትሆን ብርዱን አትችለውም" አለኝ፡፡ እኔም እዚህ ከማደር ብርድም ቢሆን ከኋላ ተጭኜ ብሄድ ይሻለኛል በማለት አሽከርካሪውን እንዲያሳፍረኝ ጠየኩት፡፡ እሱም ፈቃደኛ ሆኖ ጫነኝ፡፡ ከቅበት እስከ አልከሶ ድረስ ያለው መንገድ ለእኔ በጣም አስቸጋሪ ነበር ምክንያቱም አዋራውና ንፋሱ በጣም ከባድ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ማታ አንድ ሰአት ተኩል አካባቢ አልከሶ ከተማ ስደርስ በከተማው መብራት የለም፡፡ ወደ የት መሄድ እንዳለብኝ ግራ ሲገባኝ ከእኔ እኩል በክፍቷ መኪና ተጭኖ አልከሶ ከተማ የገባውና የከተማው ተወላጅ የሆነውን ሱልጣንን ሁኔታውን ሳስረዳው "አረ ምንም ችግር የለም ማደሪያ ቦታ ሞልቷል፡፡ እዚህ ማደር ከልፈለክ ባጃጅ ኮንትራት ይዘን ወደ ሀረም  እንሂድና እዛው እናድራለን" አለኝ፡፡ እኔም በሀሳቡ ተስማምቼ ባጃጅ ኮንትራት ይዘን ወደ አልከሶ ሀረም  ሄድን፡፡ ከቡታጀራ እስከ አልከሶ ከተማ አስራ አምስት ኪሎ ሜትር ሲሆን ከአልከሶ ከተማ እስከ አልከሶ ሀረም  ሶስት ኪሎ ሜትር ይርቃል፡፡ አልከሶ ሀረም  እንደደረስንም በሀረሙ ያለውን ድባብ ዞር ዞር ብለን ከተመለከትን በኋላ እሜቱ የሚባሉ ዘመዱ ቤት ሄደን ማታውን ሙሉ ዱኣ ተቀምጠን ስለ አልከስዬ እና ስለመውሊዱ አከባበር የተለያዩ ሰዎች የተለያየ መረጃ ሰጡኝ፡፡ እንዲሁም በበለጠ ሁኔታ ጥሩ መረጃ ሊሰጡኝ የሚችሉ ሰዎችንም ጠቆሙኝ፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ በተለያየ ጊዜ ወደ አልከሶ ሀረም  ሲሄድ ሳርፍ የነበረው እሜቱ ቤት ነበር፡፡

በ2007 ዓ.ም ከአጋዥ መረጃ ሰብሳቢዬ ሰሚራ መሀመድ ጋር አልከሶ መስጂድ ሀረም ውስጥ ተዛዙረን ፎቶ እያነሳን እያለን አንድ ግለሰብ ወደኛ በመምጣት በስልጥኛ "ቢቢታይ ሀረም ውስጥ ፎቶ ሊትነቅሉ ማ ፈቀደኩማን (እዚህ ሀረም ውስጥ በመግባት ፎቶ ለማንሳት ማን ፈቀደላችሁ)" በማለት ክፉኛ ተቆጡን፡፡ በዚህ ጊዜ እኔ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለጥናት ወደእዛ መምጣቴን ከወረዳውና ከዞኑ ፈቃደ እንዳገኘሁ እና በሀረሙም ውስጥ ማስፈቃዴንና የአካባቢው ተወላጅም መሆኔን ነገርኳቸው፡፡ እኚህ ሰው ወደ ሰሚራ በመዞር "አሽው (አንቺስ)" ሲሏት ስልጥኛ ስለማትችል ግራ ተጋባች፡፡ በዚህ ጊዜ እኔ ጣልቃ በመግባት የአካባበቢ ተወላጅ እንዳልሆነች እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር እንደሆነች እና ከእኔ ጋር መረጃ ለመሰብሰብ መሄዷን ነግሪያቸው መረጃውን እንድንሰበስብ ፈቅደውልናል፡፡

ሌላው መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ በሄድኩበት ወቅት ያጋጠመኝ ችግር አንዳንድ ጥሩ መረጃ አቀባይ ይሆናሉ ተብለው የተመረጡ መረጃ አቀባዮች "የዘመኑ ወጣቶች መውሊድን ተቃውማችሁ እንጅ ደግፋችሁ አትጽፉም" በሚል ምክንያት መረጃ ሊሰጡኝ ፈቃደኞች አልነበሩም፡፡ እዚህን መረጃ አቀባዮች ጥናቱን ለምን አላማ እና እንዴት እንደምጽፍ ባስረዳቸውም ሊይምኑኝ ስላቻሉ እነርሱ ዘንድ እማገኝ የነበረውን መረጃ ሳላገኝ ቀርቻለሁ፡፡ በመሆኑም እንደ እነሱ ጥሩ መረጃ አላቸው የሚባሉ ሰዎችን ከቀድኩት ጊዜ እና በጀት ውጭተጨማሪ ጊዜ እና በጀት በመመደብ የተለያዩ ቦታዎችን ተዘዋውሪ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡

ይህን ጥናት ሳጠና ያጋጠመኝ ተግዳሮት ስለዞኑ እና አልከሶ ሀረም የተጻፈ መረጃ ፍለጋ ወደ ቢሮዎች በሄድኩበት ወቅት ነው፡፡ በ2007 በመጀመሪያ ወደ ስልጢ ወረዳ (አልከሶ መስጂድ የሚገኝበት ወረዳ ነው) ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ሳመራ ስለ አልከሶ መስጂድም ሆነ ስለ መውሊዱ አከባበር የሚያወሳ ምንም ጽሁፍ እንደሌላቸው ገለጹልኝ፡፡ ነገር ግን አስፈላጊ ከሆነ በቪድዮ የተቀረጸ ምስል መኖሩን ቢነግሩኝም መረጃውን የያዘው የቢሮው ሰራተኛ ሊገኝ ባለመቻሉ መረጃውን ሳላገኝ ቀርቻለሁ፡፡ ከወረዳው ቀጥዬ የስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች መምሪያ ነበር ያቀናሁት፡፡ ዞኑም ልክ እንደ ስልጢ ወረዳ ሁሉ ስለ ዞኑም ሆነ ስለ አልከሶ እና አልከስዬ የሚያወሳ በቂ መረጃ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ በተወሰነ ደረጃ ግን ስለዞኑ መረጃ የሚሰጡ ጽሁፎችን ባገኝም በቂ አልነበሩም፡፡ ከመመሪያ ኃላፊዋ ጀምሮ አብላጫው ሰራተኞች "እኔ ለቦታው አዲስ ስለሆንኩኝ መረጃ የት እንዳለ አላውቅም እና ለመደቡ አዲስ ነኝ" ወዘተ የሚሉ ምክንያቶችን የሚደረድሩ ሰራተኞችም ነበሩ፡፡ በ2002 ዓ.ም የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ

ለመጻፍ መረጃ ለማሰባሰብ ወደ ዞኑ በሄድኩበት ጊዜ ተመሳሳይ ሁኔታ አጋጥሞኝ ነበር፡፡ ይህንን ችግር ለመፍታት ከዞኑ ውጭ በተለይ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ቤተመጻህፍቶችን ስለ ስልጤ የተጻፉ ጽሁፎችን ተጠቅሜያለሁ፡፡ እንዲሁም በተለያዩ ግለሰቦች እጅ ያሉ ስለ ስልጤ እና አልከስዬ የሚዳስሱ ጽሁፎችን በማፈላለግ ችግሩን ለማቃለል ሞክሬያለሁ፡፡

የበጀት እጥረት ይህን ጥናት ሳካሄድ አጋጥሞኛል፡፡ ለጥናቱ አዲስ አበባ እና መዳወላቡ ዩኒቨርስቲ ምንም አንኳን ድጋፍ ቢያደርጉልኝም ድጋፉ በቂ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ከተመደበው በጀት የበለጠ ገንዘብ ያስፈልገዋል፡፡ ለምሳሌ የመውሊድ ቅድመ ዝግጅት ሶስት ወር ያህል ይፈጃል፡፡ ይህን ቅድመ ዝግጅት ሶስት ወራት ያህል በቦታው ተገኝቶ ለመመልከት የተመደበው ገንዘብ በቂ አይደለም፡፡ በአካባቢው ባህል መሰረት ሰዎች ተሰባስበው ሲጨዋወቱ አጠገባቸው ጫት መኖር አለበት፡፡ በመሆኑም ለመረጃ አቀባዮች ቃለ መጠይቅ ሳደርግ እና የቡድንን ውይይት ሳካሄድ ጫት የመግዣ እና ሌሎችንም ወጪዎች አውጥቻለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱን ለማስተየብ እና ቁሳቁስ ለመግዣነት ብዙ ብር ወጪ አድርጌለሁ፡፡ ይህ ሁሉ ወጪ ዩኒቨርስቲዎች ባደረጉልኝ ድጋፍ ሊሸፈን ባለማቻሉ በደመወዜ እና በቤተሰብ ድጋፍ ልሸፍነው ችያለሁ፡፡

ከመስክ ተሞክሮዬም እንደተረዳሁት መረጃ አቀባዮች እንደልባቸው የሚናገሩት እነርሱ የሚፈጽሙትን ድርጊት አብሮ ከሚፈጽም ሰው ጋር ነው፡፡ ለምሳሌ እኔ አንድ ገሪብ ቁጭ ብሎ ጫት እየቃመ እያለ አጠገቡ ቁጭ ብዬ ሰላምታ እንደሰጠሁት ጫት ከኪሱ አውጥቶ በመስጠት “ቃም” አለኝ፡፡ እኔም አይ ትንሽ እቆያለሁ ስለው በተቀመጥኩበት ቦታ ትቶኝ ሄደ፡፡ ከዚህ በኋላ ገሪቦች ጋር ስሆን እነሱ የሚያደርጉትን ማድረግ እንዳለብኝ ወሰንኩ፡፡ ይህን ሁኔታ እንደ ተሞክሮ በመወሰድ ገሪብ መሀመድ እና ቶፊቅ አብረው ጫት ወደ ሚቅሙበት ቦታ ሄጄ ሰላምታ እንደሰጠኋቸው ቡና በቆሪዬ(የገሪቦች ቡና መጠጫ ነው) ሲሰጡኝ ተቀብዬ በመጠጣት ስለ ገሪብ የሚያውቁትን በሙሉ እንዲነግሩኝ ማድረግ ችያለሁ፡፡

አንድን ጥናት ስናጠና ተግዳሮቶች እንደሚያጋጥሙን ሁሉ ጥናቱ ስኬታማ እንዲሆን ምቹ ሁኔታዎችም ይኖራሉ፡፡ እኔ ይህን ጥናት ጥቂት የማይባሉ ምቹ ሁኔታዎች ነበሩኝ፡፡ ከእነዚህ መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

1. **የብሔረሰቡ ተወላጅ መሆኔ፡-** የብሔረሰቡ ተወላጅ በመሆኔ በቀላሉ ከመረጃ አቀባዮች ጋር መግባባት ችያለሁ፡፡ ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች ጋር ስገናኝ የቋንቋ ሆነ የባህል ችግር አላጋጠመኝም፡፡

2. **ቀድሞ አብረውኝ የተማሩ ሰዎች በወራቤ እና በአልከሶ አካባቢ መኖራቸው፡-** የእነዚህ ሰዎች እዝያ አካባቢ መኖራቸው በተለያየ ጊዜ ወደ መስክ ስሄድ እነሱ ቤት በማረፍ በተረጋጋ ሁኔታ መረጅ እንድሰበስብ እድል ፈጥሮልኛል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች ጋር እንድገናኝ እና መረጃ አቀባዮቹ እንዲተባበሩኝ አድርገዋል፡፡

3. **በዞኑ ለአጭር ጊዜም ቢሆን የባህል እና ቱሪዝም ቢሮ መስራቴ፡-** በ2000 ዓ.ም በአሊቾ ዊሪሮ ወረዳ የባህል እና ቱሪዝም ጽ/ቤት ሰርቻለሁ፡፡ በዚህ አመት አብረውኝ የሰሩ ሰዎች በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ቢሮዎች በኃላፊነትና በባለሙያነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ስለ ብሔረሰቡ መረጃ ሳሰባስብ ከፍተኛ እገዛ አድርገውልኛል፡፡


# ምዕራፍ ሁለት

## 2. የስልጤ ብሔረሰብ አጭር ማስተዋወቂያ

ይህ ጥናት የሚካሄደው በስልጤ ብሔረሰብ ዘንድ ነው፡፡ በመሆኑም ይህ ምዕራፍ ስለ ስልጤ ብሔረሰብ መገኛ ቦታ፣ መልክዓምድራዊ አቀማመጥ፣ ታሪክና አመጣጥ፣ ባህላዊ አስተዳደር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ሰርግ፣ ለቅሶ ፣ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለው ዝምድና እና ግንኙነት ወዘተ የሚዳስስበት ነው፡፡

### 2.1. የስልጤ ዞን አመሰራረት እና መገኛ ቦታ

የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ከሚገኙ አስራ አራት ዞኖች መካከል የስልጤ ዞን አንዱ ነው፡፡ እንደ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ምክር ቤት ፕሮፋይል (2001፡310) አገላለጽ የስልጤ ዞንን በሰሜን ምዕራብ የሰሜን ጉራጌ ዞን፣ ደቡብ ምዕራብ የሀላባ ልዩ ወረዳ እና የሀዲያ ዞን እና በምስራቅ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ያዋስኑታል፡፡




**ካርታ 1፡- የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ክልል ካርታ**[3]

የስልጤ ዞን እስከ 1993 ዓ.ም ድረስ በጉራጌ ዞን ውስጥ እንደ አንድ ቤተ ጉራጌ ተቆጥሮ በጉራጌ ዞን ስር ይተዳደር ነበር፡፡ ነገር ግን መጋቢት 1993 ዓ.ም በህዝበ ውሳኔ ራሱን ችሎ ዞን


[3] ምንጭ የክልሉ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ

ሆኖ ሊመሰረት መቻሉን ከይረዲን (2004፡87) ገልጸዋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Sarah Vaughan (2013፡265) “Ethnicity and power in Ethipia” በሚል ርእስ ለዶክተሬት ዲግሪ ባጠኑት ጥናት የስልጤ ብሔረሰብ ከ2004 እ.ኤ.አ በፊት እንደ አንድ ቤተ ጉራጌ ይቆጠር እንደነበር እና ከላይ ከተጠቀሰው ዘመን ጀምሮ በህዝበ ውሳኔ የራሱን ዞን እንደመሰረተ ያስዳሉ፡፡

ይህ ብሔረሰብ ከጉራጌ ተይቶ የራሱን ዞን ለመመስረት ባደረገው ጥረት በርካታ መሰናክሎች እንዳጋጠሙት ይነገራል፡፡ ብሔረሰቡ የመገጠል ጥያቄ ለክልል ሲያቀርብ ክልሉ በ1997 እ.ኤ.አ ቡታጀራ ከተማ ላይ 927 የስልጥኛ ቋንቋ ተናጋሪዎችን በመሰብሰብ የእንገልጠል እንገልጠን በሚለው ዙሪያ ውሳኔ እንዲወስኑ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል 781 ያህሉ ከጉራጌ ጋር አብረን ብንቆይ ይሻላል ሲሉ 146 ያህሉ ደግሞ ድምጸ ታቅቦን መርጠዋል፡፡ በዚህ ሰብሰባ አንድም ተሰብሳቢ የስልጤን ከጉራጌ ተገንጥሎ መውጣትን ደግፎ ድምጽ የሰጠ አልነበረም፡፡ ከዚህ ውጤት በመነሳት የክልሉ መንግስት የስልጤን መገንጠል የሚሹት ጥቂት ሰዎች እንጂ የአብላጫው ህዝብ ፍላጎት አይደለም የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሶ ነበር፡፡ ነገር ግን Silt’e People Democratic and Unity Party (SPDUP) በሚባል መጠሪያ ይታወቅ የነበረው ፓርቲ ውሳኔውን ሳይቀበለው ቀርቷል፡፡ በመሆኑም በወቅቱ በሀገር ውስጥ እና ከሀገር ውጭ በሚኖሩ የብሔረሰቡ ተወላጆች ዘንድ የስልጤነትን ጉዳይ በከፍተኛ ሁኔታ ትኩረት ሰጥተው አቀንቅነውታል፡፡ በመሆኑም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕዝበ ውሳኔ በ1993 ዓ.ም እንዲካሄድ አድርጓል፡፡ እንደ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አገላለጽ በዚህ ህዝበ ውሳኔ በጠቅላላው 421188 ሰዎች የተሳተፉ ሲሆን ከነዚህ መካከል 416,481 ያህሉ የስልጤ ብሔረሰብ ከጉራጌ ዞን ተገንጥሎ የራሱን ዞን ይመስርት የሚል ውሳኔ አሳልፈዋል፡፡

ከዚህ ውሳኔ በኋላ የስልጤ ብሔረሰብ ከጉራጌ ተለይቶ የራሱን ዞን መስርቷል፡፡ እንደ መረጃ አቀባዩ አበጋዝ አህመድ አገላለጽ የስልጤ ህዝብ የራሱን ዞን መመስረቱ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮችን እንዲያሳድግ ምቹ ሁኔታ ፈጥሮለታል፡፡ እንደ አበጋዝ አህመድ ሌሎቹም መረጃ አቀባዮች አገላለጽ የስልጤ ብሔረሰብ ከጉራጌ ዞን ተለይቶ የራሱን ዞን በመሰርትም ሁለቱ ህዝቦች በባህል፣ በቋንቋ፣ በማህበራዊ ህይወት የተቆራኙ ናቸው ካሉ በኋላ ከጥንትም ጀምሮ አሁንም ቢሆን ሁለቱ ብሔረሰቦች በጋብቻ እና በሌሎችም ጉዳዮች ማህበራዊ ግንኙነታቸውን በማጠናከር ላይ ይገኛሉ፡፡ ዞኑ ለመጀመሪያ ጊዜ ሲመሰረት ስድስት ወረዳዎች የነበሩት ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ስምንት ወረዳዎች አሉት፡፡ እነሱም አሊቾ ውሪሮ፣ ዳሎቻ፣

ሁልባራግ፣ ላንፎሮ፣ ምስራቅ አዘርነት በርበሬ፣ ምዕራብ አዘርነት በርበሬ፣ ስልጢ፣ እና ሳንኩራ ናቸው፡፡




ካርታ 2፡- የስልጤ ዞን ካርታ[4]

Dirk Bustorf የተሰኙ ጸሀፊ "Imam Sugato Zäyni. A war-lord of the Selt'é Gogot." በሚለው አጭር መጣጥፍ ስለ ስልጤ ብሔረሰብ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> The ethnonym Selt'é was officially recognized as the common name for the speakers of the East Guragé" language of Selt'innya only in 2002. In a referendum the Selt'innya-speakers (excluding the Wällane whose language is very similar) claimed their own ethnic identity separate from that of the Guragé and voted for the establishment of an independent administrative zone within the "Southern Nations, Nationalities and Peoples Region". Before, the Selt'é were identified as "[East] Guragé", "Islam", "Adäré" or "Adéa" or by the names of their sub-groups such as the Azärnät-Bärbäré, Alichcho-Wuriro, Selt'i, Mälga

[4] ምንጭ፡- የስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች መምሪያ

(or Welbaräg). Selt'é, the name of the entire ethnic group is not to be confused with Selt'i, the name of the sub-group (Dirk, 2009፥151).

ሲተረጎም

ስልጤ የሚለው የማህበረሰብ ስያሜ በ1994 ዓ.ም በመንግስት በይፋ እውቅና ከማግኘቱ በፊት ስልጤ የሚለውን ስያሜ ተሰጥቶት የነበረው ለምስራቅ ጉራጌ ስልጥኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ነው፡፡ ነገር ግን በ1994 ዓ.ም በተካሄደው የሕዝብ ውሳኔ መሰረት የስልጥኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች(ከእነርሱ ቋንቋ ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው ወለኔዎች ሳያካትቱ) ከጉራጌ ማህበረሰብ የተለየ የራሳቸው ማንነት እንዳላቸው አሳይተዋል፡፡ በዚህም የተነሳ የራሳቸውን ነጻ ዞን በደቡብ ክልል ውስጥ እንዲመሰረትላቸው ድምጽ ሰጥተዋል፡፡ ስልጤዎች ከጉራጌ ተለይተው የራሳቸውን ዞን ከመመስረታቸው በፊት በተለያየ ስም ይጠሩ ነበር፡፡ ከነዚህም መካከል ጉራጌ(ምስራቅ)፣ ኢስላም፣ አደሬ(አዲይ)፣ አዘርነት በርበሬ፣ አሊቾ ዊሪሮ፣ስልጢ፣ መልጋ(ውልባራግ) በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ ስልጤ የሚለው አጠቃላይ የማህበረሰብ መጠሪያ ስልጢ ከሚለው ንዑስ ቡድን ስም መጠሪያ ጋር አንድ አድርጎ ሊወሰድ ይገባል፡፡

ይህ ጥቅስ የስልጤ ብሔረሰብ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የምስራቅ ጉራጌ ቋንቋ ቤተሰብ ተናጋሪ እና እንደ አንድ ቤተ ጉራጌ ይቆጠር እንደነበር እና በጊዜው እስላም፣ አደሬ፣ አዲያ፣ ወዘተ ተብሎ ይጠራ እንደነበር ያትታል፡፡

የስልጤ ዞን ዋና ከተማ ወራቤ ስትሆን ከአዲስ አበባ በ172 ኪ.ሜ ርቀት በሆሳዕና ጂንካ በሚወስደው መንገድ ላይ ትገኛለች በማለት ከይረዲን (2004፥87) እና ፈረጃት (2002:3) ገልጸዋል፡፡ ወራቤ ከተቀረቀረች ረጅም ዓመታትን በታስቆጥርም የዞኑ ዋና ከተማ ሆና በአዲስ መልኩ የተደራጀችው ግን በ1995 ዓ.ም ነው፡፡

## 2.2. መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ እና የአየር ጸባይ

እንደ ፈረጃት (2006፥10) አገላለጽ የዞኑ አጠቃላይ ቆዳ ስፋት 2537.50 ካሬ ሜትር ነው፡፡ የደ/ብ/ብ/ህ/ም/ቤት ፕሮፋይል (2001:310) የመሬቱ አቀማመጥ ሜዳማ የበዛበት ለእርሻና ለከብት እርባታ ምቹ የሆነ የአየር ጠባይ ያለው እንደሆነ እና የዞኑ የአየር ጸባይ ደጋ 20.6%፣ ወይና ደጋ 74.4% እና ቆላ 5% እንደሚሸፍን ይገልጻል፡፡ ፕሮፋይሉ አያይዞም የወይናደጋው

አካባቢ ከፍተኛውን የአየር ንብረት የሚሸፍን ሲሆን አብዛኛው የዞኑ ህዝብም በዚሁ አካባቢ ይኖራል፡፡ የዞኑ የመሬት ከፍታ ከ1500 እስከ 3700 ከባህር ጠለል በላይ ነው፡፡ የሙቀት መጠኑ ከ10.1 እስከ 22.5 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ሲደርስ ዓመታዊ የዝናብ መጠኑ ከ801 ሜ.ሌ እስከ 1200 ሜ.ሌ ይደርሳል ይላል፡፡ በ2007 እ.ኤ.አ በተደረገው የህዝብና የቤት ቆጠራ ውጤት መሰረት የዞኑ ህዝብ ብዛት 750398 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ወንድ 364108 ሲሆን ሴት 386290 ነው፡፡ ከዞኑ ህዝብ ውስጥ 47097 ከተማ ነዋሪ ሲኖር 703301 ገጠር እንደሚኖር የህዝብና የቤት ቆጠራ ውጤቱ ያሳያል፡፡[5]

የዞኑ ዌብሳይት በቅርብ ይፋ ባደረገው መረጃ መሰረት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ የብሔረሰቡ ህዝብ ብዛት 1,288,000 እንደሆነ ያሳያል[6]፡፡ በዞኑ ከሚኖረው ህዝብ ውስጥ 95.5% የገጠር ነዋሪ ሲሆን የተቀረው 4.5% ከተማ ነዋሪ ነው፡፡ የዞኑ ህዝብ አብላጫው ገጠር ነዋሪ በመሆኑ ኑሮው በዋናነት የተመሰረተው በእርሻ ነው፡፡ ከእርሻ በተጨማሪ ከብት ማርባት፣ መነገድ እና የእደጥበብ ውጤቶች በማምረት የተለመደ መሆኑን እና በዞኑ በርበሬ፣ እንሰት፣ ጤፍ፣ ስንዴ፣ በቆሎ፣ ገብስ፣ አተር፣ ባቄላ፣ ቦለቄ፣ አደንጓሬ፣ ቡና፣ ጫት፣ ወዘተ በብዛት ይበቅላሉ፡፡ የብሔረሰቡ ዋና ባህላዊ ምግብ የበቆሎና የቆጮ ቂጣ “ፍናንቾ” ነው፡፡ “አተካኖ”፣ የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የቆጮና የቡላ ገንፎ “ሞቃ” ተጨማሪ ምግቦች ናቸው (አብዱ 2003፡12)፡፡

## 2.3. የስልጤ ብሔረሰብ ታሪክ እና አመጣጥ

ስልጤ የሚለው ስያሜ የብሔረሰቡ እና የዞኑ መጠሪያ ሲሆን ስለ ቃሉ  እና ስለ ብሔረሰቡ አመጣጥ የተለያዩ ጸሀፊዎች ጽፈዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ከይረዲን፣ አባስ፣ አብዱልፈታ፣ ድንበሩ፣ ላጺሶ፣ ሀብታሙ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የስልጤ ብሔረሰብ የዛሬውን መጠሪያ ከማግኘቱ በፊት ዠራ፣ ሀዲያ፣ ኢስላም እና ጉራጌ ተብሎ ይጠራ እንደነበር አባስ (2004፡30) ሲገልጽ ከይረዲን (2004፡21) ደግሞ ሀርላ፣ ሀዲያ፣ የሀዲያ ሀደሬ ይባል እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል ድንበሩና ሌሎቹም “ጎጎት” በሚለው መጽሀፍ (1988፡48) “የስልጤ ህዝቦች ስልጤ የሚለውን መጠሪያ ስም ያገኙት የብሔረሰቡ ግንድ መሰረት እና የመጀመሪያ ሱልጣን በሆነው “ገን” ሲልጢ ነው፡፡ ሱልጣን የሐጂ አልዩ ልጅ እንደሆነ በሰፊው ይነገራል” ይላሉ፡፡

[5] THE 2007 POPULATION AND HOUSING CENSUS OF ETHIOPIA. Results for SOUTHERN NATIONS, NATIONALITIES AND PEOPLES' REGION.Augest 2010 p 9.

[6] www.Islamic Centre Leicester 12/1/2015 at 5:25 PM እና et.geoview.info/siltie_zone, ስለ ስለጤ ዞን የሚያትተው ድረ ገጽ ያስረዳሉ፡፡

በሌላ በኩል የስልጤ ህዝቦች ስልጤ የሚለውን መጠሪያ ያገኙት በ16ኛው ክፍለ ዘመን የአህመድ ግራኝን ጦር ለማገዝ ከአጎራባች የአረብ ሀገራት ከመጡት ሀጅ አልዬ እንደሆነ የሚያሳዩ መረጃዎች መኖራቸውን ድንበሩና ሌሎቹም (1988፡48) ይገልጻሉ፡፡ እነ ድንበሩ አያይዘውም የሀጅ አልዬ ልጆቻቸው ዛሬ ላይ ለሚገኙ በርካታ የስልጤ ጎሳዎች መመስረት ምክንያት የሆኑ ናቸው፡፡ ከልጆቻቸው መካከልም የቀዳማዊ ሱልጣን ተከታይ እንደሆነ የሚነገርለት "ገን" ሲልጢ የተባለው ልጃቸው የአካባቢው አስተዳዳሪ በመሆኑ ምክንያት ስልጤ ለሚለው መጠሪያ ሰበብ እንደሆነ ይነገራል በማለት አብራርተዋል፡፡ ሐጂ አልዬ የሚባሉ ታላቅ የሀይማኖት መሪ ከበርበራ ተነስተው ከሐረር ወደ መሀል ሀገር ከዚያም ወደ ደቡብ ኢትዮጵያ በርካታ የሃይማኖት ሰዎችን አስከትለው ከመጡ በኋላ ቀደም ብሎ በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩት የ"ዠር" ጎሳዎች መካከል አንዷን በማግባት አንድ ሴትና አምስት ወንድ ልጆችን እንደወለዱ እና እነሱም በአሁኑ ወቅት አዘርነት በርበሬ፣ ስልጢ፣ ሁልባራግ፣ ዳሎቻ፣ ሳንኩራ፣ አልቾውሪሮ፣ ወለኔ፣ ገደባኖ እና ሌሎችም የስልጢኛ ቋንቋ ተናጋሪ አካባቢ እንደተሰራጩ አብርሃም እና ሀብታሙ (1984፣30-31) ያስረዳሉ፡፡

አብደላህ (1989፡180) የስልጤዎች አባት ሀጅ አልዬ ከሀረሪው ሼኽ አባድር ጋር በ1216 እ.ኤ.አ ከምድረ አረቢያ መምጣታቸውን እና የስልጤ ህዝብ ከሀረር ህዝብ ጋር ዝምድና እንዳላቸው የሚያሳዩ መረጃዎች መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡[7] ላጺሶ (1990፡58) ደግሞ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ተከትሎ በደቡብ ምስራቅ ጥንታዊ **የአዘርነት በርበሬ፣ ኡልባራግ፣ ስልጢ**[8] የቡሼና የማረቆ፣ ሀዲያ፣ ሲዳሞ የተለያዩ ጎሳዎች … በግምት ከ1530-1660 ድረስ በብዛት አገሮቻቸውን በመተው ዛሬ በሚኖሩበት አካባቢ መኖር መጀመራቸውን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው የስልጤ ብሔረሰብ ታሪክ የሚጀምረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን መሆኑን ነው፡፡

ድንበሩ፣ ላጺሶ ወዘተ የስልጤ ብሔረሰብ ታሪክ የሚጀምረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን ነው ቢሉም ከይረዲን፣ አባስ፣ አብደልፈታህ እና ሌሎችም በሀሳቡ አይስማሙበትም፡፡ ከይረዲን (2004:21) ስለ ስልጤ ብሔረሰብ ታሪክና አመጣጥ በርካታ የተሳሳቱ መረጃዎች ተጽፈው ይገኛሉ፤ የስልጤ ህዝብ የ500 አመት ታሪክ ብቻ ያለው ህዝብ ነው ይላሉ፡፡ ነገር ግን ብሔረሰቡ ዛሬ በሚጠራበት ስም ባይጠራም ታሪኩ የሚጀምረው ከ9ኛ ክፍለ ዘመን ጀምሮ መሆኑን እና የ500 አመት ታሪክ ብቻ ያለው ብሔረሰብ እንዳልሆነ ያስረዳሉ፡፡ ከይረዲን አያይዘውም የስልጤ

[7] Kedir Adem (2008፡13) ስልጤ የሚለው ቃል የመጣው ከገን ስልጤ ሳይሆን የሀረር መሪ ከነበረው አሚር ሱልጣን እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ ይላል፡፡

[8] እነዚህ ቦታዎች በአሁኑ ጊዜ በስልጤ ዞን ስር የሚገኙ ወረዳዎች ናቸው፡፡

ብሔረሰብ ስልጤ የሚለው መጠሪያ በታሪክ ሰነድ ውስጥ ተሰንዶ የተገኘው በ14ኛው ክፍለ ዘመን ንጉስ አምደ ጽዮን (1314-1344) ነው፡፡ ንጉሱ በቁጥጥር ስር ካዋሏቸው ህዝቦች እና መንግስታት አንዱ የስልጤ ብሔረሰብ ነበር ይላሉ፡፡ Braukämper (2002:65) በተመሳሳይ ሁኔታ ስለ ስልጤ በንጉስ አምደ ጽዮን ዘመነ መንግስት በሰነድ ሰፍሮ እንደሚገኝ ያስረዳሉ፡፡

ከከይረዲን በተጨማሪ የስልጤ ህዝብ ታሪክ ከ500 ዓመት አይዘልም የሚለውን የአንዳንድ ጸሃፊዎችን ሀሳብ በመቃወም አብዱልፈታህ (1989፡189) "የወለኔ ህዝብ አባት የሆኑት ሰይድ ከቢር ሀሚድ ወደ አካባቢው የመጡት በአጼ ዘርያዓቆብ ዘመን (ከ1434-1468) ነው፡፡ አያሌ የታሪክ ምሁራን የስልጤ እና የወለኔ ህዝቦች ወደ አካባቢው የመጡት በኢማም አህመድ ዘመቻ ጊዜ እንደመጡ እንደጻፉ እና በዘርያዓቆብ ዘመን ስልጤዎች እና ወለኔዎች አሁን የሚኖሩበት ቦታ ሰፍረው እያለ የታሪክ ጸሀፊዎች ግን ጉዳዮን ከኢማም አህመድ ዘመቻ ጋር ማያያዛቸው አጠያያቂ ነው" በማለት የከይረዲንን ሀሳብ ይጋሩታል፡፡

በስልጤ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች ተመሳሳይ ባህል፣ አንድ አይነት ቋንቋ (ስልጢኛ) እንዲሁም በአስተዳደር ስርዓት ብቻ ሳይሆን በአኗኗር ሁኔታ፣ በጋብቻና በብዙ ማህበራዊ ሁኔታዎች አጎራባች ከሆኑት ከጉራጌ፣ ከሀዲያና ከቀቤና ህዝቦች ጋር እንደሚመሳሰሉ እና በሐረር ክፍለ ሀገር ከሚገኘው ከሀደሬ ህዝብም ጋር በቋንቋ፣ በኃይማኖት እና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተቀራራቢነት እንዳላቸው አብርሀምና ሀብታሙ (1984፡ 64 እና 78) እና ከይረዲን (2004፡135-151) ያስረዳሉ፡፡

## 2.4. ቋንቋ

የስልጤ ብሔረሰቡ መግባቢያ ቋንቋ ስልጥኛ ነው፡፡ እንደ አባስ (2004፣46) አገላለጽ አጼ ሚኒሊክ አካባቢውን ወረው እስከያዙበት 1881 ዓ.ም ድረስ ስልጤ የራሱ የሆነ አካባቢያዊ መንግስት ነበረው፤ በጊዜው የነበረው መንግስትም የስራ ቋንቋ ስልጥኛ ነበረ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የስልጥኛ ቋንቋ በ8ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ ቋንቋ እንደሆነ የሚያሳዩ መረጃዎች መኖራቸውን ከይረዲን (2004፡535) በመግለጽ የቋንቋውን ጥንታዊነት ያጸናሉ፡፡ እነ Bender (1976)፣ Hetzro(1969) እና Leslau(1992) የስልጥኛ ቋንቋ ደቡብ ምስራቅ ጉራጌ ከሚባሉት የኢትዮጵያ ሴማዊ ቤተሰብ ከሆነው የምስራቅ ጉራጌ የቋንቋ ቅርጫፍ ውስጥ መድበውት ይገኛል፡፡ Tiglu(2015፣33) የስልጥኛ ቋንቋ ከሴማዊ የቋንቋ ቤተሰብ እንደሚመደብ ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ አጥኚዎችና ሌሎችም በጉራጊኛ በቋንቋ ላይ ጥናት ሲያደርጉ ስልጥኛን እንደ አንድ ቤተ

ጉራጌ ቋንቋ አድርገው አጥንተውታል። ነገር ግን ረውዳ (2002፣16) የስልጥኛ ቋንቋ ጉራጌ በሚል ስም ከሚጠሩት ቋንቋዎች ይልቅ ከሌሎች የሴም ቋንቋዎች የበለጠ ይቀራረባል በማለት አመዳደቡ ችግር እንዳለበት ያስረዳሉ።

ስልጥኛ ከአደርኛ፣ ከትግርኛ፣ ከአማርኛ፣ ከአርጎብኛ፣ ከጉራጊኛ እና ከሌሎች ሴማዊ ቋንቋዎች ጋር ተቀራራቢነትና ዝምድና እንዳለው እና ቋንቋው የተወሰነ ቀበልኛ ቢኖረውም የብሔረሰቡ ተወላጆች በቀላሉ መግባባት እንደሚችሉ Hetzro (1973፡11) ያስረዳሉ። ስልጢኛ በመሰረተ ትምህርት ዘመቻ ወቅት በተለይም በ1970ዎቹ ለማስተማር በመማሪያ ቋንቋነት በስራ ውሎ የነበረ ቋንቋ መሆኑን የደ/ብ/ብ/ህ/ም/ቤት ፕሮፋይል (2001፡310)፣ አብርሀምና ሀብታሙ (1984፡85) እና ከይረዲን (2004፡533-540) ያስረዳሉ። ከዚህ በተጨማሪ የደ/ብ/ብ/ህ/መ ም/ቤት ፕሮፋይል (2001፡310) ስልጢኛ ቋንቋ ከ60 ዓመት በፊት የአረብኛ ፊደልን በመጠቀም ለጽሑፍ የዋለ ቋንቋ በመሆኑ ከ1967 ዓ.ም ጀምሮ ልዩ ልዩ አዋጆች እና የመሰረት ትምህርት ማስተማሪያ መጻሕፍት የሳባ ፊደልን በመጠቀም በቋንቋው መተርጓሙንና ከ1987 ዓ.ም ጀምሮ 1ኛ ደረጃ ሳይክል የመማሪያ መጻሕፍት በቋንቋው እንደተዘጋጀ ያስረዳል።

## 2.5. ኃይማኖት

የስልጤ ብሔረስብ በ8ኛው ክፍለ ዘመን እስልምናን በመቀበል እና በሀገሪቱ እስልምና እንዲስፋፋ ትልቅ አስተዋጽኦ ማበርከቱን ከይረዲን (2004፡490) እና አባስ (2004፡14) ያስረዳሉ። በስልጤ ብሔረሰብ ውስጥ የተለያዩ ሀይማኖቶች ቢኖሩ የአንበሳውን ድርሻ የሚወስደው የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ቁጥር ነው። በአሁኑ ወቅት ከህብረተሰቡ ውስጥ 99% የእስልምና ኃይማኖት ተከታይ ሲሆን 1% ያህሉ የሌላ ኃይማኖትና የተለያዩ እምነት ተከታዮች እንደሆኑ ፈረጃት (2001፡16) ያሳያል። የስልጤ ብሔረሰብ አጠቃላይ ቁጥር 1,288,000 ሲሆን ከዚህ ውስጥ ሙስሊም 96.0%፣ ኦርቶዶክስ 2.0% እና ፕሮቴስታንት 0.50% ነው።[9]

የስልጤ ብሔረሰብ እስልምናን ከተቀበለበት ጊዜ ጀምሮ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ በአላትን ሲያከብር ኖሯል፤ አሁንም በማክበር ላይ ይገኛል። ከባህላዊ ክብረ በአላት መካከል "ዱመፈቾ"፣ "የዳዶቃዋ"፣ "ኢዶት"፣ "ኖቆ" ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። ኢድአልሃዳ፣ ኢድ አልፈጥር እና መውሊድ ደግሞ ሃይማኖታዊ ክብረ በአላት ናቸው። መውሊድን ከሚያከብሩ ብሔረሰቦች

[9] www. Islamic Centre Leicester.com . asecced 12/5/2015.

መካከል አንዱ የስልጤ ብሔረሰብ መሆኑን zelalem (2013፣146) እ.ኤ.አ ያስረዳሉ፡፡ ብሔረሰቡ ዓሊም መሰረት አድርጎ የሚያከብራቸው "የአበከሳዮ ዋጆ"፣ "የሀጅ አሊዬ" "የኢማም ሱጋቶ"፣ "የአልከሶ" ፣"የሼኽ ነስራላ"፣ "የዳንጌ ሼኽ" ወዘተ መውሊዶች የነበሩት ሲሆን ከእነዚህ መካከል በአሁኑ ጊዜ በዋናነት በደመቀ ሁኔታ የሚከበረው የአልከሶ መውሊድ ነው፡፡ ሌሎቹ አንዳንዶቹ ሙሉ በሙሉ ሲጠፉ የተቀሩት ደግሞ እንደ አልከሶ ባይሆንም በተወሰነ ደረጃ ይከበራሉ፡፡ ይህ የሆነበት ምክንያት መውሊዶቹ መጀመሪያም ቢሆን እንደ አልከሶ በተጠናከረ ሁኔታ እየተከበሩ ስላልነበሩ ነው፡፡

ብሔረሰቡ በብዛት የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ እንደመሆኑ በሃይማኖቱ በቂ እውቀት ላላቸው እና አንቱ ለተባሉ ሰዎች የተለያየ የማዕረግ ስም ይሰጣል፡፡ ከሚሰጡ ስሞች መካከል ሙፍቲ፣ ኡለመ፣ ሼኽ፣ ሀጃጅ/ቲ፣ ኢማም እና ቃዲ ዋና ዋናዎቹ እንደሆኑ የስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች መምሪያ በየአመቱ የሚያሳትመው መጽሔት የ2006 እትም ያሳያል፡፡

## 2.6. ባህላዊ አስተዳደር

የስልጤ ብሔረሰብ በቀደሙት የአስተዳደር ዘመናት የራሱ የሆነ መተዳደሪያ ደንብ ነበረው፡፡ ይህ ብሔረሰብ ከትውልድ ትውልድ እያስተላለፈ የመጣው ያጠፋውን በመቅጣት ትምህርት እንዲያገኝና ከህብረተሰቡ ጋር እንዲቀላቀል የሚያደርግበት ስርዓት አለው፡፡ ይህ የባህላዊ ስርዓት "ጉማ"[10] ይባላል፡፡ "ጉማ" በዋናነት ሶስት ደረጃዎች ያሉት ሲሆን እነሱም "ማጋ"÷ "ራጋ" እና "ፈረስአገኝ" የሚባሉት ናቸው፡፡ አልፎ አልፎ "ወጋገኘ" የተሰኘ አራተኛ የዳኝነት ደረጃ አለ፡፡ እንደ አብርሃም እና ሀብታሙ (1984:40-43) አገላለጽ ብሔረሰቡ ሶስት ፖለቲካዊና ማህበራዊ አስተዳደራዊ ስርአቶች የነበሩት ሲሆን የመጀመሪያው የማእከላዊ ስልጣን አስተዳደር ሲሆን በሐጂ አልዬ ዑመር ይመራ የነበረው ማእከላዊ አስተዳደር ነው፡፡ ህዝቡን በማስተባበርና በማደራጀት ኃይማኖትና ፖለቲካ አቀናጅቶ የሚመራ ከፍተኛ ስልጣን እንደነበረው ይነገራል፡፡ ሁለተኛው "ዳምቡስ" አስተዳደር በመባል ይታወቃል፡፡ "ዳምቡስ" በአካባቢው ሽማግሌዎች የተመረጡ ሀያ ወይም ሰላሳ በተለይም በጦር መሪነታቸው የታወቁ ግለሰቦችን ያቀፈ አስተዳደር ወይም ጉባኤ ነው፡፡ ሶስተኛው የግለሰብ መሪዎች አስተዳደር ነው፡፡ ይህ የአስተዳደር ሁኔታ የተከሰተው በየአካባቢው አንዳንድ ጀግናዎች በመፈጠራቸው እና "ዳምቡስ" ስርዓት ተቀባይነት

[10] ጉማ የኦሮምኛ ቃል ውስጥ የሚገኝ ሲሆን ካሳ የሚል ትርጉም አለው፡፡ ቃሉ በስልጥኛውም የተበደለን ሰው መካስ የሚል ትርጉም ስላለው በስልጥኛ እና በኦረምኛ ተመሳሳይ ትርጉም አለው፡፡

እየቀነሰ በመምጣቱ የተነሳ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ እነዚህ የአስተዳደር እና የዳኝነት ስርአቶች በብዛት በመተው ለዘመናዊ አስተዳደር እና ዳኝነት ቅድሚያ እየሰጠ መምጣቱን የአካባቢው የእድሜ ባለጸጋዎች ይናገራሉ፡፡

እንደ ፈረጃት መፅሔት ቅጽ 1 ቁጥር 17 (2007፣38) አገላለጽ ብሔረሰቡ አንድ ሰው በአካባቢው በአስተዳደር ስርአቱ በአሳየው ብቃት እንደ ፈጸመው ድርጊት በማየት የማዕረግ ስም ይሰጠዋል፡፡ እነዚህ የማዕረግ ስሞች ገራድ፣ ኡንገራድ፣ አዲገራድ፣ ወለብገራድ፣ የሳርገራድ፣ በሀር፣ ባህረቶሎ፣ ሙረ፣ ገንዝ፣ ኮንተብ፣ በርከፊት፣ አበጋዝ፣ አጃሞ፣ ኢቲ/ኢቲኮ፣ ጊስት/ጊስቲት ናቸው፡፡




ፎቶ 1፡- የሀገር ሽማግሌዎች በዋርካ ስር የዳኝነት ስርዓት ሲያካሄዱ[11]

## 2.7. የጋብቻ ስርዓት

በስልጤ ብሔረስብ ዘንድ የማህበረሰቡ አባላት ተሰብስበው በደመቀ ሁኔታ ከሚያከናውኑት ክንውን ውስጥ የጋብቻ ስርዓት አንዱ ነው፡፡ የስልጤ ብሔረሰብ 99 ከመቶ የእስልምና ሀይማኖት ተከታይ እንደ መሆኑ መጠን የጋብቻ ስነ ስርዓት የሚፈጸመው በሸሪአው መሰረት ነው፡፡ ይህ ሲባል ግን በብሔረሰቡ ዘንድ ከእስላማዊ መንገድ ውጭ የሚደረግ የጋብቻ ስርዓት የለም ማለት አይደለም፡፡ በብሔረሰቡ በትጭጭት ከሚፈጸመው የጋብቻ ሥርአት በተጨማሪ

[11] ምንጭ፡- የስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒካሽን እና ጉዳዮች መምሪያ

ማስኮብለል፣ ወዶገብነት፣ ጠለፋ፣ ባል ፊት የሆነችን ማግባት፣ እና ሌሎች የትዳር መመስረቻ ዘዴዎች ናቸው (አብርሀም እና ሀብታሙ 1984፡80)፡፡ የደቡብ ክልል ፕሮፋይል (2001፡33-34) ደግሞ "ኩል"፣ "ጠለፍ"፣ "አጋ"፣ "ውርስ" እና መተጫጨት የሚባሉ የጋብቻ ስርአቶች እንደሚገኙ ያስረዳል፡፡ አባስ (2004፡39-40) ብሔረሰቡ በረጅም ጊዜ ታሪኩ ወዶገብ(አጋ)፣ ጠለፋ(ዝመዶት)፣ ድንገተኛ(ተኳሎ ግቦት)፣ ድህረ ጋብቻ(ወጌት)፣ በመተጫጨት(ጡቀሾ) እና የውርስ ጋብቻ(ውርሽት) የሚባሉ የጋብቻ አይነቶችን ሲተገብሩ መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡ ከይረዲን (2004፡328) ከላይ ከተገለጹት የጋብቻ አይነቶች በተጨማሪ "ሄሬ" የሚባል በሁለቱ ተጋቢዎች ስምምነት ብቻ ለቤተሰብ ሳይናገሩ የሚመሰረት የጋብቻ አይነት መኖሩን ገልጸዋል፡፡ ከነዚህ መካከል በህብረተሰቡ ዘንድ በሰፊው የሚተገበረውና ተቀባይነት ያለው በመተጫጨት(ጡቀሾ) እንደሆነ እና በብሔረሰቡ የጋብቻ ስርዓት የራሱ የሆነ ቅደም ተከተል እንዳለው አብዲ (2003፡19)፣ አባስ (2004፡40-41) እና ስልጢና አልከሶ የተሰኘው መጽሄት በሚከተለው መልክ አስፍረውት ይገኛል፡፡

**"ችግ"፡-** ይህ ስርዓት የሚፈጸመው የልጅቷ ቤተሰቦች ልጃችንን ለልጃችሁ ወደንና ፈቅደን ሰጥተናል የሚሉበትና የልጁም ወገን የልጅቷን፣ የአባትና የእናት ልብስ የሚሰጡበት ነው፡፡

**"ገንዬ"፡-** ለሁለቱ ተጋቢዎች በየዘመዶቻቸው ቤት ሴቷን ከሴት ሚዜዎቿ ፣ወንዱን ከወንድ ሚዜዎቹ ጋር በመጥራት የሚደረግላቸው የምግብ የግብዣ ስርዓት ነው፡፡

**"ማንደሮ"** በሰርጉ ዋዜማ ምሽት ላይ በሁለቱም ተጋቢዎች በኩል የሚደረግ የጭፈራ ስርዓት ነው፡፡ "ረጃቶ"፣ "ላሎ"፣ "ሱክሲኬ"፣ "ቦልቦሌ"፣ እና "መስቀና" በዚህ እለት የሚጨፈሩ የብሔረሰቡ ባህላዊ ጭፈራ አይነቶች ናቸው፡፡

**"ቦለቾ"፡-** ቦለቾ ማለት ሰርግ ማለት ነው፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ በብዛት ሰርግ የሚፈጸመው ሰኞ ወይም ሐሙስ ነው፡፡ የብሔረሰቡ የሀገር ሽማግሌ የሆኑት አቶ አህመድ አሊ ይህ ቀን መርጦ መጋባት በዘልማድ እንጂ የተለየ እምነት የለውም ይላሉ፡፡ የብሔረሰቡ ወጣቶች ለጋብቻ የመተጫጫ በርካታ አጋጣሚዎች አሏቸው፡፡ ከነዚህም መካከል በዋናነት የተለያዩ ህዝባዊ ክብረበአላት፣ የሰርግ ቦታ እና ገበያ እንደሆነ አቶ አብድልረዛቅ[12] ይናገራሉ፡፡ ከነዚህ በተጨማሪ ሃይማኖታዊ እና ባህላዊ ክብረ በአላትም ሌላው የመተዋወቂያ እና የመተጫጫ አጋጣሚዎች ናቸው፡፡ ከክብረ በአላት መካከል በዞኑ በሚከበሩ መውሊዶች ላይ መተዋወቅ እና ለወግ ማዕረግ መብቃት የተለመደ ነው፡፡ በአልከሶ መውሊድም የዚህ አይነት ሁኔታ ከድሮ ጀምሮ እንደነበረ

[12] ቃለመጠይቅ 02/01/09 ዜባድ

እና አሁንም እንዳለ በመስክ ቆይታዬ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ይህ ነጥብ በአልከሶ መውሊድ እንዴት እንደሚፈጠር በምዕራፍ ሰባት ስር ተብራርቶ ቀርቧል፡፡

## 2.8. የለቅሶ ስርዓት

አንድ ሰው ንብረት ካለውና በጠና ከታመመ በባህሉ መሰረት ኑዛዜ የመናዘዝ ግዴታ አለበት፡፡ ይህን ደግሞ እስልምና ግድ አድርጎታል፡፡ ምክንያቱም ሟች በሚቀበርበት እለትም ሆነ ከዚያ በኂላ ለለቅሶው የሚወጣው ወጪ በሟች ኑዛዜ መሰረት በመሆኑ ነው፡፡ ሟች ሀብት ንብረት ከሌለው ግን የአካባቢው ማህበረሰብ እና ዘመድ አዝማድ አቅሙ የፈቀደውን በማዋጣት የቀብር ስርዓቱ እንዲከናወን ያደርጋሉ፡፡ የለቅሶ ስርዓቱ የሚፈጀው ጊዜ እንደሟች ማንነት እና ማህበራዊ ደረጃ የተለያየ ቢሆንም በዋናነት የመቆያ ጊዜው አስራ ሁለት ቀን ድረስ ነው፡፡ ሟች ከሞተበት እለት ጀምሮ ለአስራ ሁለት ቀናት ያህል "ደረሳዎች" እና የሃይማኖት አባቶች ተጋብዘው ለሟች አላህ ምህረት እንዲለግሰው የነብዩ መሀመድ የውዳሴ ንባብ (ሰለዋት) እያነበቡ ይጸልያሉ፡፡ የለቅሶ ስርአቱን ሁኔታ አባስ (2004፡40-41) እንደሚከተለው ጠቅለል አድርገው አስፍረውታል፡፡

> አንድ ሰው ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ለዘመድ አዝማድ ጥሪ ይተላለፋል፡፡ አስክሬኑ ታጥቦ ወደ መስጂድ እስኪገባ ይለቀሳል፡፡ አስክሬኑ መስጂድ ከገባ በኂላ እንዲሰገድበት ከማድረግ በስተቀር የማይለቀስ ሲሆን ዘመድ አዝማድ እስኪሰበሰብ ተጠብቆ በጠዋቱ ክፍለ ጊዜ ተቆፍሮ በተዘጋጀው የቀብር ጉድጓድ ላይ ከሰዓት በኂላ የቀብር ስነ ስርዓት ይፈጸማል፡፡ አስክሬኑ መቃብር ስፍራ ሲወሰድ በወንዶች ታጅቦ ሲሆን ሴቶች ወደ ቀብር ቦታ አይሄዱም፡፡

የለቅሶ ስርአቱ በተለያየ ስርዓት ለአስራ ሁለት ቀናት ከተካሄደ በኂላ በአስራ ሶስተኛው ቀን ሁሉም ወደ መጣበት ይሄዳል፡፡ ለቀስተኛ ለቅሶውን ጨርሶ ከተበታተነ በኂላ የቤተሰቡ የቅርብ ጓደኛ ወይም ዘመድ (በብዛት የተለመደው በዘመድ ነው) የተለያዩ የብሔረሰቡን የባህል ምግቦችና መጠጦችን አዘጋጅተው ወደ ሟች ቤት ይሄዳሉ፡፡ ይህ የሚደረገው የሟችን ቤተሰብ ለማጽናናት ሲሆን ይህ ባህል በብሔረሰቡ "መያስኮ" በመባል ይታወቃል፡፡ "መያስኮ" የመጣለት ሰው ባመጣው ሰው ቤት ሰው ከሞተ ተራውን የመውሰድ ግዴታ እንዳለበት አብዲ (2003፤18) ያስረዳል፡፡

እንደ ዞኑ ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን እና ጉዳዮች መምሪያ መጽሄት (2006፤25) አገላለጽ ይህ ብሔረሰብ የራሱ የሆነ የዘመን አቆጣጠር አለው፡፡ የአመቱ መጀመሪያ

ሰኔ 19 ቀን የሚውል ሲሆን በወረዳ እና በዞን ደረጃ "አሹራ" ተብሎ ይከበራል፡፡ ወራቶቹም አስራ ሶስት ሲሆኑ እነሱም መሰሮ፣ ጥቅምት፣ ኢዳር፣ መሼ፣ ኢንቶጎት፣ መንገስ፣ ወቶ፣ ማዜ፣ አስሬ፣ ሰኜ፣ ሀምሌ፣ ናሴ፣ እና ቃቅሜ ናቸው፡፡

## 2.9. የስልጤ ብሔረሰብ ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለው ዝምድናና ግንኙነት

የስልጤ ዞንን በሰሜን ምዕራብ የሰሜን ጉራጌ ዞን፣ ደቡብ ምዕራብ የሀላባ ልዩ ወረዳ እና የሀዲያ ዞን እና በምስራቅ የኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት እንደሚያዋስኑት ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ የስልጤ ዞን ከእነዚህ ዞኖቹ ጋር በዚህ መልክ መዋሰኑ የስልጤ ብሔረሰቦች ጋር በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚዊ፣ በፖለቲካዊ እና በሌሎችም ጉዳዮች የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖረው ምክንያት ሆኗል፡፡
የታሪክ ምሁሩ ላጺሶ(1990፣50) "በኢትዮጵያ መስተጋብር ያልፈጠረ ህዝብና ብሔረሰብ የለም፡፡" ይላሉ፡፡ የስልጤ ብሔረሰብም እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች ሁሉ ከሌሎች አጎራባች እና ሌሎችም ብሔረሰቦች ጋር የጠነከረ ግኑነት አለው፡፡ ይህ ግንኙነቱ የጀመረው በሔረሰቡ አሁን በሚገኝበት አካባቢ ለመጀመሪያ ጊዜ ሰፍሯል ከሚባለው 1530ዎቹ አካባቢ ጀምሮ ነው፡፡ ይህ ዘመን ሀጂ አሊዬ ከአጎራባች የአረብ ሀገራት ተነስተው ከሀረር ከዛም በጨርጨር አድርገው ኡምናን (በአሁኑ ጊዜ በስልጤ ዞን በምዕራብ አዘርነት በርበሬ የሚገኝ ቦታ ነው) በሚባል ቦታ እንደሰፈሩ እና በአከባቢው ከነበሩ ሰዎች ወይም ዝረዋች መካከል አንድ ሚስት አግብተው አምስት ወንድ ልጆችን እንዳፈሩ የአከባቢው ታሪክ አዋቂ ሽማግሌዎች ይናገራሉ፡፡ እነዚህ የሀገር ሽማግሌዎች አንዳንዶቹ በወቅቱ ዝራ የሚባሉ ሰዎች ጉራጌዎች ነበሩ ሲሉ ሌሎቹ ደግሞ ሀዲያዎች ነበሩ ይላሉ፡፡ ይህን ሀሳብ የትኛውም የታሪክ ምሁር መርምሮ ትክክለኛውን መረጃ እስካሁን አላቀረበም፡፡ ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ሀጂ አሊዬ በአካባቢው ከሰፈሩበት ጊዜ ጀምሮ ከሀዲያ እና ከጉራጌ ጋር መልካም ግንኙነት እንደነበራቸው ነው፡፡

ላጺሶ (1990፡58) ደግሞ የኢማም አህመድ ግራኝ አመጽ ተከትሎ ወደ ደቡብ ምስራቅ ያቀናው የስልጤ ህዝብ ከቡሼና ማረቆ፣ ከሀዲያ፣ ከሲዳሞ ህዝበ ጋር መልካም ግንኙነት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ አብርሃም እና ሀብታሙ (1984፣30-31) የስልጤ ብሔረሰብ ከወለኔ፣ ከገደባኖ እና ሌሎችም ብሔረሰቦች ጋር የጋራ ታሪክ እና የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ አብዱልፈታህ (1989፡189) የወለኔ ህዝብ አባት የሆኑት ሰይድ ከቢር ሀሚድ ከስልጤው አባት ሀጂ አሊዬ ጋር በአንድ ዘመን አሁን ወደ ሚኖሩበት አካባቢ እንደሄዱ እና ዝምድና እንደቀጠሉ ያስረዳል፡፡ Sarah (2003፣23) የስልጤ ህዝብ በአሁኑ ጊዜ ከጎራጌ ብሔረሰብ ጋር

ተመሳሳይነት ያለው ባህል እና ቋንቋ እንዳለው ታስረዳለች፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Dirk Bustor የተባለ ጸሀፊ ስለ ኢማም ሱጋቶ በሚያትትበት መጣጥፍ ኢማም ሱጋቶ ሀዲያዎች ጠላት ሲመጣባቸው ሀዲያዎችን አግዘው ይዋጉ እንደነበር ያትታል፡፡ የአካባቢው ሽማግሌዎች ኢማም ሱጋቶ የሀዲያ ብሔረሰብ ደም ወይም ዝምድና እንዳላቸው ይገልጻሉ፡፡

የስልጤ ብሔረሰብ በአሁኑ ጊዜ የጠበቀ ቁርኝት ካለው ህዝብ መካከል የሀረሪ ህዝብ አንደኛው እና ዋነኛው ነው፡፡ አብድልፈታህ (1999፣176-177) ስለ እነዚህ ሁለት ብሔረሰቦች ግንኙነት የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ሰኔ 4/1998 በአዲስ አበባ በኦሮሚያ የስብሰባ አዳራሽ የሀረሪ እና የስልጤ ሕዝቦችና መሪዎች ተገናኝተው "የሀረሪ እና የስልጤ የህዝብ ለህዝብ ግንኙነት መድረክ" በይፋ መስርተዋል፡፡ መተዳደሪያ ደንብ ቀርጸው በጋራ ለጋራ ዕድገት የሚጓዙበትን መንገድ ነድፈዋል፡፡ የተለያዩ ኮሚቴዎች አቋቁመው በትምህርት፣ በባህል፣ በኢኮኖሚ፣ በፖለቲካ የሚሰሯቸውን ተግባራት ጀምረዋል፡፡ ይህ ለኢትዮጵያ መልካም ዜና ነው፡፡ ተምሳሌታዊ ተግባር ጭምር ነው፡፡ በህገ መንግስታችን መግቢያ ላይ ለተጠቀሰው "ጥቅማችንን፣ መብታችንና ነጻነታችንን በጋራና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ የመገንባቱ አስፈላጊነት ..." ለሚለው ብሩህ ራዕይ ፋና ወጊ ነው፡፡

WEHIB በ2015 "HISTORY OF HARAR AND THE HARARIS" በሚል ርዕስ ባሳተመው ጥናታዊ ጽሁፍ የሀረሪ ህዝብ የጠነከረ እና የጠበቀ ግንኙነት ከላቸው ብሔረሰቦች መካከል የስልጤ ብሔረሰብ ግንባር ቀደሙ እንደሆነ ያትታል፡፡ Kedir (2008፡13) ስለ ሀሪሪ እና ብሔረሰብ ቋንቋ ተመሳስሎ ባጠናበት ጥናት የስልጤ ብሔረሰብ ከሀረሪ ህዝብ ጋር በቋንቋ ብቻ ሳይሆን በባህልም ጭምር ተመሳሳይነት እንዳለው ያስረዳል፡፡ ከእነዚህ ጸሀፊዎች በተጨማሪ Braukämper (1980:428) ስልጤዎች እና ሀረሪዎች በቋንቋ የሚመሳሰሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ፡፡ በአሁኑ ጊዜ የስልጤ ብሔረሰብ በየአመቱ የባህል ቋንቋ እና የታሪክ ሲፖዚየም ሲዘጋጅ የሀረሪ ብሔረሰብ ተወካዮች ተጋብዘው በሲምፖዚየሙ ይታደማሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የሀረሪ ህዝብም በተለያየ ጊዜ በሚያከብራቸው ክብረ በዓላት ላይ የስልጤ ብሔረሰብ ተወካዮች እንዲገኙ ያደርጋሉ፡፡ የስልጤ ብሔረሰብ ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው ብሔረሰቦች በተጨማሪ ከኦሮሞ ብሔረሰብ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አላቸው፡፡ ለዚህ አባባል ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ በባሌ ዞን በየአመቱ በሚከበረው የድሬ ሼኽና ሁሴን መውሊድ ላይ መውሊዱ መከበር ከጀመረበት ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ስልጤዎች እንደሚሳተፉ እና

በአሁኑ ዘመን ስልጤዎች መውሊድ የሚያከብሩበት የራሳቸው የተወሰነ ቦታ እንዳላቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡[13] ሌላው በርካታ የብሔረሰቡ ባለሀብቶች በተለያዩ የኦሮሚያ ክልል ቦታዎች እና በተለያዩ  ላይ መዋለነዋያቸውን በማፍሰስ እና ክልሉን በማልማት ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የስልጤ ብሔረሰብ ተወላጆች በሀገራችን ከሚገኙ ሌሎች ብሔረሰቦች ጋር አብሮ እንዲኖር አልፎም ተጋብቶና ተዋልዶ እንዲኖር አድርጎታል፡፡

የስልጤ ብሔረሰብ ከ99 ከመቶ በላይ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ቢሆንም ከሃይማኖቱ ውጭ ካሉ ማህበረሰቦችም በጋብቻም ሆነ በሌላ መንገድ ዝምድና ፈጥሮ ይኖራል፡፡ ለምሳሌ ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ በሄድኩት ወቅት በአንድ ቤት ውስጥ ባል የክርስትና ምስት ደግሞ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ሆነው አግቼያቸዋለሁ፡፡ በመሆኑም በመውሊድ ሰሞን ባል መውሊድን ክርስትያን ኸለዋ ሲያከብር ምስት ደግሞ ከሙስሊም ከዘመዷቿ እና ከጎደኛቿ ጋር በመሆን ሙስሊሞች በሚገኙበት ኸለዋ ውስጥ ታከብራለች፡፡ ይህ የሚያሳየው የስልጤ ብሔረሰብ መልካም ግንኙነት ያለው ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ብቻ ሳይሆን አብላጫው የብሔረሰቡ አባል ከሚከተለው ሀይማኖት ውጭከሚከተሉ ማህበረሰቦችም ጭምር መልካም ግንኙነት አለው፡፡

በስልጤ አካባቢዎች የሚኖሩ ህዝቦች ተመሳሳይ ባህል፣ አንድ አይነት ቋንቋ (ስልጢኛ) እንዲሁም በአስተዳደር ስርዓት ብቻ ሳይሆን በአኗኗር ሁኔታ፣ በጋብቻና በብዙ ማህበራዊ ሁኔታዎች አጎራባች ከሆኑት ከጉራጌ፣ ከሀዲያና ከቀቤና ህዝቦች ጋር እንደሚመሳሰሉ እና በሐረር ክፍለ ሀገር ከሚገኘው ከሀደሬ ህዝብም ጋር በቋንቋ፣ በኃይማኖት እና በሌሎችም ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ተቀራራቢነት እንዳላቸው አብርሀምና ሀብታሙ (1984፡ 64 እና 78) እና ከይረዲን (2004፡135-151) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው ታሪኮች እና ሌሎችም የምንረዳው የስልጤ ብሔረሰብ ከአጎራባች ብሔረሰቦች ከጥንት ጀምሮ የጠነከረ ግንኙነት እንዳለው ያሳያል፡፡ ይህ ግንኙነት ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋራ በጋብቻ ጭምር ተሳስሮ እና ተዋልዶ የኖረ እንደሆነ ያሳያሉ፡፡ ባጠቃላይ የስልጤ ብሔረሰብ ከጥንት ጀምሮ በሀገሪቱ ከሚገኙ የተለያዩ ብሔረሰቦች እና አብላጫ የብሔረሰቡ አባላት ከሚከተሉት ሃይማኖት ውጭ ከሆኑ ማህበረሰቦች ጋር መልካም ግንኙነት ያለው  ብሔረሰብ ነው፡፡

[13] ሰለሞን ተሾመ ከ2006 ዓ.ም ጀምሮ የዶክተሬት ዲግሪውን በድሬ ሼኸና ሁሴን የሙዳ ስርዓት ላይ ሲሰራ የቆየ ሲሆን በዚህ ቦታ ላይ ስልጤዎች የራሳቸው የሆነ የመውሊድ ማክበሪያ ቦታ እንዳላቸውና በቦታው ስልጤ ከሚለው መጠሪያ ይልቅ "ሜጢ" በሚል መጠሪያ እንደሚታወቁ መስከረም 2010 ዓ.ም ስለ መውሊድ በምንወያይበት ወቅት አጫውቶኛል፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የአጠናን ዘዴ

የዚህ ምዕራፍ አላማ ይህ ጥናት ምን አይነት የምርምር ዘዴ እንደሚከተል እና መረጃ እንዴት ተሰብስቦ እንዴት እንደሚተነተን ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም ምዕራፉ ጥናቱ ምን አይነት የምርምር ዘዴ እንደሚከተል እና ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ከምን ከምን ምንጮች እንደተሰበሰበ እና እንደተተነተነ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መረጃ አቀባዮች እና የመስክ መቼቶች በምን ዘዴ እንደተመረጡ እና መረጃ ለመሰብሰብ ምን ምን የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች እና መሳሪያዎች አገልግሎት እንዳገለገሉ ያሳያል፡፡

### 3.1 የጥናቱ ስልት

አብዛኛው አይነት የትምህርት ዘርፍ የየራሱ የሆነ የማጥኛ ዘዴ አለው፡፡ አንዳንዶቹ ግን የራሳቸው የሆነ የማጥኛ ዘዴ ስለሌላቸው ከእነሱ የትምህርት ዘርፍ ጋር ተቀራራቢነት ካለው ዘርፍ የማጥኛ ዘዴ በመውሰድ ተግባራዊ ያደርጋሉ፡፡ ለዚህ ገለጻ ፎክሎር ጥሩ ማሳያ መሆን ይችላል፡፡ ይህን በማስመልከት Goldstein (1964:2) "ለፎክሎር አንድ ወጥ ብያኔ እንደሌለው ሁሉ አንድ ወጥ የሆነ የፎክሎር የማጥኛ ዘዴም የለውም…" በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ የምንረዳው ፎክሎርን ለማጥናት አንድ ወጥ የሆነ የምርምር ዘዴ አለመኖሩን እና የተለያዩ ዘዴዎች መጠቀም እንደሚቻል ነው፡፡

ይህን ጥናት ለማጥናት የተሻለ መንገድ ይሆናል ተብሎ የተመረጠው አይነታዊ የምርምር ዘዴ "Qualitative Method" ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዘዴ ቃለ መጠይቅን፣ ምልከታን እና ተተኳሪ የቡድን ውይይትን እና የተለያዩ የጽሁፍ መዛግብትን ለመጠቀም ከማስቻሉ በተጨማሪ ቀመራዊ ወይም ቁጥራዊ አሀዝ የሌላቸውን ምርምሮችን ለማካሔድ የሚያስችል መሆኑን Best (1981:28) ያስረዳሉ፡፡ አንድ ማህበረሰብ የሚያከናውነውን ማህበራዊ ልማድ የሚያጠና አጥኚ የማህበረሰቡን ልማድ፣ ወግ፣ ባህል፣ታሪክ በአጠቃላይ ማንነቱን በአይነታዊ የምርምር ዘዴ ሊቃኝ ይችላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት ደግሞ በሀገረሰባዊ ልማድ ስር በሚመደበው ክብረ በዓል ላይ በመሆኑ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡በማህበረሰብ ጥናት ውስጥ በርካታ አይነት የአይነታዊ የምርምር ስልት እንዳለ ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ይህን በማስመልከት Johnson & Christensen (2012፣2) የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> Quantitative methods, there are actually many varieties of qualitative methods. Similar to the way you can group usability testing methods, there are also a number of ways to segment Qualitative methods. A popular and helpful categorization separate qualitative methods into five groups: ethnography, narrative, phenomenological, grounded theory, and case study. While the five methods generally use similar data collection techniques (observation, interviews, and reviewing text), the purpose of the study differentiates them–something similar with different types of usability tests. And like classifying different usability studies, the differences between the methods can be a bit blurry.

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በርካታ አይነት የአይነታዊ የምርምር ስልት እንዳለ እና በዋናነት ግን አምስት አይነት እንደሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አምስቱም የምርምር ስልቶች መረጃ የሚሰበስቡት በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ እና በሰነድ ፍተሻ መረጃ የሚሰበስቡ በመሆናቸው ተመሳሳይነት እንዳላቸው እና የሰበሰቡትን መረጃ በመከልሰፍ እና ከመተንተን አንጻር ግን ልዩነት እንዳለ ጥቅሱ ያሳያል፡፡ ከዚህ ገለጻ አንጻር ይህ ጥናት የተከተለው ኢትኖግራፊ የሚባለውን የአይነታዊ የምርምር ስልትን ነው፡፡

እንደ Oreilly (2005:118) አገላለጽ የአንድ ብሔረሰብ ባህል ሲጠና የብሔረሰቡ አስተሳሰብ አብሮ ይጠናል፡፡ በዚህ ጥናትም የአልከሶ መውሊድ ሲጠና በዓሉ የሚከበርበትን አካባቢ ማህበረሰብ አስተሳሰብ፣ አኗኗርና የእርስ በእርስ ግንኙነት የሚጠና በመሆኑ ጥናቱ ከአይነታዊ የምርምር አይነት በተጨማሪ ኢትኖግራፊክ (Ethnographic) የጥናት አይነትንም ይከተላል፡፡ ስለ ኢትኖግራፊክ የጥናት አይነት Fetterman የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> Ethnography gives voice to people in their own local context, typically relying on verbatim quotations and a “thick” description of events. The story is told through the eyes of local people as they pursue their daily lives in their own communities. The ethnographer adopts a cultural lens to interpret observed behavior, ensuring that

the behaviors are placed in a culturally relevant and meaningful context (Fetterman 2010:1).

ሲቶረጎም

ኢትኖግራፊ ድምጽ ሌላቸው ሰዎች ድምጽ (ይሰጣል) ይሆናል፡፡ ይህ ማለት ድምጽ የሚሰጣቸውም በአካባቢያቸው አውድ ውስጥ በመሆን ነው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው በዋናነት የራሳቸውን ቀጥተኛ ንግግር(ቃላት) በመጥቀስ እና ስለ ክስተቶች ሰፊ የሆነ ማብራሪያ በመስጠት ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ የማህበረሰቡ ታሪክ የሚነገረው በማህበረሰቡ እይታ ነው፡፡ የማህበረሰቡን የእለት ተእለት ይሕወት በመመልከት ሂደት ውስጥ ነው፡፡ የስነ ማህበረሰብ ባህል አጥኚዎች የአንድን ማህበረሰብ ባህል ሲያጠኑ የሚያጠኑትን ማህበረሰብ መላበስ አለባቸው፡፡ ምክንያቱም የማህበረሰቡን አኗኗር ትክክለኛውን ባህላዊ ፋይዳውን እና ትርጉም ሰጪ አውድ ውስጥ መቀመጡን ለማረጋገጥ ይረዳል፡፡

እንደ O'Reilly (2005:8) አገላለጽ የኢትኖግራፊክ ጥናት ዋና የመረጃ ምንጩ እና ትኩረቱ መስክ ነው፡፡ የኢትኖግራፊክ የመስክ ሥራ በሦስት ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ ያተኩራል፡፡ እነሱም የሚጠናውን ማህበረሰብ ወግና ልማድ፣ ተቋማት፣ የተቋማቱ መዋቅር ምን እንደሚመስል፣ ወግና ልማዱ እንዴት እንደሚዋቀርና እንደሚከውኑ እና ከማህበረሰቡ ተቋማትና ባህል ጋር የተያያዙ አመለካከቶች እና ስሜቶች ምን እንደሆኑ ማሳየት ነው፡፡ Loshini, (2011፣1) ደግሞ "Ethnography, emerging from anthropology, and adopted by sociologists, is a qualitative methodology that lends itself to the study of the beliefs, social interactions, and behaviours of small societies, involving participation and observation over a period of time, and the interpretation of the data collected." ስለዚህ የአልከሶ መውሊድ ሲጠና የመውሊዱ አክባሪዎች ወግ እና ልማድ ወግና ልማዱ እንዴት እንደሚዋቀርና እንደሚከውኑ እና ከማህበረሰቡ ተቋማትና ባህል ጋር የተያያዙ አመለካከቶች፣ እምነቶች እና ስሜቶች ምን መመልከት አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም ከበርካታ የኢትኖግራፊክ ምርምር አይነቶች ቢኖሩም ይህ ጥናት የተከተለው ክዋኔያዊ ኢትኖግራፊክን(Prefomance Ethnography) ተከትሏል፡፡ ምክንያቱም ጥናቱ ለአይነታዊ የምርምር ስልት ትኩረት በመስጠት የመውሊድ አክባሪዎችን የመውሊድ አከባበር ሁኔታ እና የእርስ በእርስ ግንኙነት ምን እንደሚመስል በክዋኔያዊ ኢትኖግራፊ ቀርቧል፡፡

## 3.2 የመረጃ ምንጮች

የዚህ ጥናት መረጃ በዋናነት የሚሰበሰበው ከመስክ ቢሆንም ከጥናቱ ርዕስ እና ጥናቱ ከሚካሄድበት ማህበረሰብ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጽሁፍ መረጃዎች ዳስሻለሁ፡፡ በመሆኑም መረጃውን ከሁለተኛ ደረጃ (ካልዓይ) እና ከሁለተኛ ደረጃ (ካልዓይ) የመረጃ ምንጮች ተሰብስቦዋል፡፡

### 3.2.1. የሁለተኛ ደረጃ (ካልዓይ) የመረጃ ምንጮች

የቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ትኩረቱ መስክ ላይ ሲሆን የካልዓይ የመረጃ ምንጭ ደግሞ አርካይቭ፣ ሙዚየም፣ ቤተመጻህፍት፣ ወዘተ ናቸው፡፡ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ መረጃ ለመሰብሰብ የአጥኚው የመስክ ክሂል ወሳኝነት እንዳለው ሁሉ በአርካይቭ፣ በሙዚየም፣ በቤተመጻህፍት፣ ወዘተ የመጠቀም ክሂል ሊኖረው እንደሚገባ Dorson (1986:58) እና Jonson (1994:75) ያስረዳሉ፡፡ እንደ Hammensley and Atkinson (1991:146) አገላለጽ እነዚህ መረጃዎች ደግሞ ሊገኙ የሚችሉት ከበራሪ ወረቀቶች እስከ ትላልቅ ጥናቶች እና ምርምሮች ውጤት ድረስ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲሁም ከተቀረጹ ድምጾች እስከ ፊልምና ቪድዮ መረጃዎች ይደርሳል፡፡ ከቦታ አንጻር ደግሞ የሚገኙበት አካባቢ እና ቦታም ከግለሰብ መኖሪያ ቤት እስከ ቤተ-መዘክር፣ ቤተ መጻሕፍት፣ እስከ ቤተ-እምነት ያሉትን ያጠቃልላል፡፡

አንድ መስከኛ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ከመሔዱ በፊት ሊያስብባቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ ፈቃደ (1991፡124-125) “እኔ እስከማውቀው ድረስ ማንኛውም መስከኛ (field worker) በተለይ ለስራ ወደ ገጠር የሚሰማራ… በባዶ ሆዱ መስክ አይወጣም፡፡ የስነቃል ተመራማሪውም… ለመስክ ስራ በባዶ ሆዱ ለመስክ ስራ መውጣትን አያስብም፡፡ የሚሆን ነገር አይደለም፡፡ በዚህ ዓይነት በባዶ ራሱ መስክ መሰማራት የለበትም፡፡ እዝያ ሔጄ ምን እንደምጠይቅና ምን እንደምሰራ አስባለሁ ማለት አይፈቀድለትም” ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Goldstein (1964፡38) የታሪክ እና የቋንቋ፣ የስነ ልሳን እና የማህበረሰብ ተመራማሪዎች ወደ መስክ ከመሰማራታቸው በፊት ለመስክ የሚሆን ስንቅ የተለያዩ መዛግብቶችን በመቃኘት መቋጠር እንዳለባቸው ያስረዳሉ፡፡ Goldstein (1964:40) አክለውም አንድ መስከኛ ጥናት በሚያካሔድበት ወቅት ስለ ጥናቱ ቦታና ማህበረሰቡ ጥልቀት ያለው እውቀት ሊኖረው ይገባል ይላሉ፡፡ MacDonald (1972፡408) አንድ ተመራማሪ ሰው በባህል ወደ በለጸገው አካባቢ በመሔድ የተወሰኑ

ጠቃሚ ነገሮችን ለማግኘት ይችላል፤ ነገር ግን በስርዓት የተነደፈ የመስክ ምርምር ንድፍ የሚነድፈው በቤተመጻህፍት እና በቤተመዛግብት ውስጥ መሆኑን ተገንዝበን ለጉዳዩ ትኩረት ልንሰጠው እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተው ይመክራሉ፡፡

ስለዚህ እኔም ወደ መስክ ከመሰማራቴ በፊት ስለ ፎክሎር ምንነት፣ ስለ መረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ፣ በብሔረሰቡ ላይ የተደረጉ ጥናቶችን፣ ስለ መውሊድ የሚያወሱ ጽሁፎችን እና የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦችን እና ንድፈ ሀሳቦችን ቃኝቻለሁ፡፡ ለዚህም ይረዳኝ ዘንድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ቤተመጻህፍት ከመቃኘቴ በተጨማሪ ስለ ስልጤ ብሔረሰብ የሚያወሱ የተለያዩ ጽሁፎችን በስልጤ ዞን ከሚታተሙ ጽሁፎች፣ ከስልጤ ልማት ማህበር ጽህፈት ቤት እና ከተለያዩ ጽሁፎችና መጻህፍት ሰብስቤያለሁ፡፡ ስለመውሊድ የሚያውሱ ጽሁፎች ከታላቁ አንዋር መስጂድ ቤተመጻህፍት፣ ከእስልምና ጉዳዮች ጽህፈት ቤት እና ከተለያዩ ድረ ገጾች ለማሰባሰብ ችያለሁ፡፡

## 3.2.2. የመጀመሪያ ደረጃ (ቀዳማይ) የመረጃ ምንጮች

በቀዳማይ የመረጃ ምንጭ መረጃ የሚሰበሰበው በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ነው፡፡ ይህ ማለት የቀዳማይ የመረጃ ምንጭ ትኩረቱ መስክ ላይ ነው፡፡

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ምንጭ የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን፣ ቴክኒኮችን እና መቼቶችን በመጠቀም መረጃ ከአውዱ ወይም ከትክክለኛ ቦታው የሚሰበሰብበት ነው፡፡ Goldstien (1964፡77)፣ Robert and Junes (1995፡15)፣ ፈቃደ (2001፡90) እና ሌሎችም ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ አውዳዊ ጥናት ለሚያካሔድ ተመራማሪ የሚያገለግል መሆኑን እና በዋናነት መረጃው የሚሰበሰበው በሶስት ዘዴዎች እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ዘዴዎቹም ምልከታ፣ ቃለ መጠይቅ፣ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ናቸው፡፡ እነዚህ ሶስት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ለዚህ ጥናት አገልግሎት የሰጡ በመሆናቸው ስለምንነታቸው ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

### 3.2.2.1 ምልከታ

አውዳዊ የማጥኛ ስልትን ተከትሎ ለማጥናት ያቀደ ተመራማሪ በዋናነት መረጃ ከአውድ ከሚሰበስብበት ዘዴ ውስጥ አንዱና ዋነኛው ምልከታ ነው፡፡ ይህ ዘዴ በአይነ ስጋ ብቻ

የሚካሔድ ሳይሆን ሌሎችም የስሜት ህዋሳት የሚሳተፉበት ጭምር ነው፡፡ ምክንያቱም ልቦና ካላየ አይን ቢያይም አይን ብቻውን ትርጉም የለውምና ነው፡፡ Golidstien (1964፡77) ምልከታ የምንለው በቀጥታ በአይነ ስጋችን ብቻ የምናየው ሳይሆን የተለያዩ የስሜት ህዋሳቶችን የምናሳትፍበት ተግባር ነው ይላሉ፡፡ O'Reill (2005፡104) ደግሞ ምልከታ አጥኝው ለተወሰነ ጊዜ ከሚያጠናው ማህበረሰብ ጋር አብሮ በመኖር አጠቃላይ የማህበረሰቡን እሴትን፣ ባህሉን፣ ወጉን፣ ልምዱን፣ ስርአቱን፣ ቋንቋውን፣ አኗኗሩን፣ ወዘተ በተመለከተ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Hammers and Atkinson (2007፡1) ለምናጠናው ጥናት አስፈላጊውን እና ትክክለኛውን መረጃ ለማግኘት የምናጠናውን ማህበረሰብ አጠቃላይ አኗኗር፣ እምነት እና እሴት ጠንቅቀን በማወቅ እና የሚበሉትን በመብላት የሚጠጡትን በመጠጣት የሚተገብሩትን በመተግበር በአጠቃላይ እነሱን መስሎ በመኖር ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ዘዴ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Kothari (2004፡96) ምልከታ ለማድረግ ወደ መስክ ከመሔዳችን በፊት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አስቀድመን ማሰብ አለብን ይላሉ፡፡ እነሱም እንዴት መመልከት አለብን፣ ምልከታውን በምን ሁኔታ መቅረጽ አለብን፣ ማስታወሻ አያያዛችን ምን መምሰል አለበት፣ እና ምልከታችን በትክክለኛ መንገድ ማካሔዳችንን በምን አይነት ዘዴ ማረጋገጥ አለብን የሚሉትን በጥልቀት ማጤን የሚሉት ናቸው፡፡

ምልከታ በሚካሔድበት ወቅት ሶስት አይነት ምልከታዎች እንዳሉ Goldstein (1964:76) ይገልጻሉ፡፡ እነሱም አንደኛው በአውዱ በመገኘት እንደ ማንኛውም ተመልካች ወይም ታዛቢ ሆኖ መረጃ የሚሰበስብበት፣ ሁለተኛው በንቃት መሳተፍና መመልከት ናቸው፡፡
በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ የተገለጹት ሁለቱም የምልከታ አይነቶች ተካሔደዋል፡፡ በመጀመሪያው የምልከታ አይነት እንደ ታዛቢ ወይም ጎብኚ በመሆን ሀረሙ ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ድባብ እና እንቅስቃሴ ተመልክቻለሁ፡፡ በተሳትፏዊ ምልከታ ደግሞ በዓሉን ከሚያከብሩ ሰዎች ጋር አብሮ በመሳተፍ ስራ በማገዝ፣ እንግዳ በመቀበል፣ ፣መንዙማ በሚሉበት ጊዜ አብሮ በማለት እና ሌሎችንም ስራዎች በማገዝና በመሳተፍ መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ በዚህ ጊዜ ዳር ላይ ቆሞ ከማየት በተሻለ ሁኔታ መረጃ ማግኘት ችያለሁ፤ እንዲሁም ከተሳታፊዎችም በጥሩ ሁኔታ የመቀራረብ ዕድል እንዲፈጠርልኝ ረድቶኛል፡፡ በከፊል ተሳትፏዊ ምልከታ በተወሰነ ደረጃ ስራ እያገዝኩ አብላጫ ትኩረቴን ምልከታ ላይ በማድረግ ጥሩ መረጃ ማግኘት ችያለሁ፡፡ እንዲሁም አጠቃላይ በበዓሉ ያለውን ድባብ ምን

እንደሚመስል ተመልክቻለሁ። መረጃ ስሰበስብ አራት ጊዜ ምልከታ አካሄጃለሁ። የመጀመሪያው በ2007 ዓ.ም ታህሳስ ወር የነብዩ መሀመድ መውሊድ ሲከበር አልከሶ ሀረም በመገኘት ምልከት አካሄጃለሁ። ሁለተኛው ሚያዝያ 2007 ዓ.ም ዋናው የአልከሶ መውሊድ ሲከበር አጠቃላይ የአከባበር ሁኔታ ምን እንደሚመስል ተመልክቻለሁ። ሶስተኛውን ምልከታ መጋቢት 2008 ዓ.ም አልከሶ ሀረም  በመገኘት ሀሙስ ቀን የሚከበረው ወርዊ መውሊድ ሲከበር ምልከት አካሄጃለሁ። አራተኛውን ምልከታ ሚያዝያ 2008 ዓ.ም ዋናው የአልከሶ መውሊድ ሲከበር ምልከታ አካሄጃለሁ። በምልከታ ማካለል ወይም መመልከት ያልቻልኩትን መረጃ ለማግኘት በበዓሉ ከሚታደሙ ሰዎችን አድራሻ በመቀበል በዓሉ ከአለፈ በኂላ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት አካሂጃለሁ።

መውሊዱ በሚከበርበት ወቅት አጠቃላይ ድባቡን አንድ ሰው ብቻውን መመልከት አዳጋች ስለሆነ ለአካባቢው እና ለባህሉ አዲስ (የፎክሎር እውቀት ያለው) የሆነ ሰው አግዞ ምልከታ ማድረጉ አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የስነጽሑፍ እና ፎክሎር መምህርት የነበረችዋን ሰሚራ መሀመድ በምልከታ መረጃ በመሰብሰብ ረድታኛለች። በመሆኑም በሴቶች ክፍል ያለውን የአከባበር ስርአት ተመልክታ መረጃ እንድትሰበስብልኝ ማድረግ ችያለሁ። ይህን ማድረግ የፈለኩበት ምክንያት እኔ በከበራው ደጋግሜ ስለተሳተፍኩ ቀላልና አያስፈልጉም ብዬ ያለፍኳቸውን መረጃዎች አዲሱ ተመልካች በእንግዳ አይን ስለሚመለከታቸው ለጥናቱ ጥሩ ግብአት ይሆናል ብዬ ስላሰብኩ ነው። አጋዥ መረጃ ሰብሳቢዋ የሰበሰበችውን መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥ መረጃውን ከተመለከትኩ በኂላ በተተኳሪ የቡድን ውይይት እና ለሴቶች ቃለ መጠይቅ በማደረግ ለማረጋገጥ ሞክሬያለሁ።

### 3.2.2.2 ቃለ መጠይቅ

በዚህ ጥናት መረጃ ከተሰበሰበበት ዘዴ መካከል ቃለመጠይቅ አንዱ ነው። አንድ ተመራማሪ ከሚያጠናው ማህበረሰብ አካል ጋር ፊት ለፊት በመገናኘት መረጃ ከሚሰበሰብበት ዘዴ መካከል አንዱ ቃለ መጠይቅ እንደሆነ Julia (2008፡68) ያስረዳሉ። ቃለመጠይቅ ለፎክሎር ጥናት ሁነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው።

> Interviewing is the most common field method employed by folklore collectors. Interviewing data may include information on what the informant knows, belives, expacts, feels, wants, does, or has done,

> or which explains or gives reasons for any of the preceding. It supplies the collector with an insaider's view to the individual, his cultural and his folklore. And it is also the chief means of supplying the collector with the folklore materials(Goldestein 1964,104).

ከጥቅሱ የምንረዳው በቃለመጠይቅ የመረጃውን ውጫዊ ገጽታ ብቻ ሳይሆን የመረጃውን ውስጣዊ ባህሪ ለማወቅ የሚያስችል ጭምር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መረጃ አቀባዮች ስለሚሰጡት መረጃ ያላቸውንም ስሜት፣ አስተሳሰብ ወዘተ ለማወቅ ጭምር የሚያገለግል ነው፡፡

ይህ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ከመረጃ አቀባዮች በአካል በማግኘት ስለሚፈልገው ጉዳይ የሚወያይበት ዘዴ ነው፡፡ ቃለ መጠይቅ የሚጠየቀውን ማህበረሰብ (ሰው) እምነት፣ ስሜት፣ ከዚህ በፊት ስለተደረጉ ጉዳዮች የሚያውቀውን እና የሚያስታውሰውን ለማወቅ የሚያስችል ነው (Goldstein 1964፡140)፡፡ ይህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ የሚፈለገውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል፣ ለመረጃ አቀባዩም ነጻነት የሚሰጥ እና በመረጃ አቀባዩ እና በመረጃ ሰብሳቢው መካከል መልካም የሚባል ግንኙነት ለመፍጠር የሚያስችል እንደሆነ Goldstein (1964፡108) ያስረዳሉ፡፡ ዘዴው በምልከታ ወቅት መመልከት ያልተቻለን መረጃ ለማግኘት በዋናነት ያገለግላል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ ጊዜ በግልጽ የማይከወኑ እና የማይታዩ እንደ አይነኬ የሆኑ ጉዳዮችን ስለምንነታቸው ሰዎችን በመጠየቅ ማወቅ ይቻላል፡፡ Ferraro (1998፡91) ይህን ዘዴ አስመልክቶ "The technique is used for obtaining information on what people think or feel (attitudinal data) as well as on what they do (behavioral data)"ይላሉ፡፡

እንደነ O'Reilly (2005፡116) እና ፊቃደ (1991፣95) አገላለጽ ሁለት አይነት የቃለ መጠይቅ አይነቶች አሉ፡፡ እነሱም የተዋቀረ እና ያልተዋቀረ ቃለ መጠይቅ ናቸው፡፡ የተዋቀረ ሲባል አጥኚው ወደ መስክ ከመሔዱ በፊት አልሞ የተነሳውን ዓላማ ግብ በሚመታበት ሁኔታ የሚያዘጋጀው ጥያቄ ነው፡፡ ያልተዋቀረ አጥኚው ቃለ መጠይቅ በሚያደርግበት ወቅት ካለው ሁኔታ ወይም ግልጽ ካልሆነለት ጉዳይ በመነሳት ቀድሞ ያላዘጋጀውን ተጨማሪ ሀሳብ መሰንዘር ወይም ጥያቄ የሚቀርብበት ሁኔታ ነው፡፡ ያለው (1998፣ 183) ደግሞ ውስን ቃለ መጠይቅ (structured interview)፣ ከፊል ነፃ ቃለ መጠይቅ (Semistructured interview)

እና ነፃ ቃለ መጠይቅ (Unstructured interview) በማለት የቃለ መጠይቅ አይነቶችን በሶስት ይከፋፍሉታል፡፡ በዚህ ጥናት ለዋና መረጃ አቀባዮች የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ወደ መስክ ከመሄዴ በፊት አዘጋጅቻለሁ፡፡ መስክ ላይ ሆኜ መረጃ ስሰበስብ ከተመለከትኳቸው ሁኔታዎች በመነሳት እዚያው አዳዲስ ጥያቄዎችን በመፍጠር ለመረጃ አቀባዮቼ አቅርቤያለሁ፡፡ ስለዚህ በዚህ መልክ እነዚህ የቃለ መጠይቅ አይነቶች ተግባራዊ ሆነዋል፡፡ በቃለ መጠይቅ ወቅት አንድ መረጃ አቀባይ የነገረኝ መረጃ ሌላ መረጃ አቀባይ በማነጋገር ለማመሳከር እና ለማረጋገጥ ሞክሬያለሁ፡፡ ቃለ መጠይቅ የተደረገላቸው ሰዎች እንዴት ተመረጡ የሚለውን በ2.3 ስር መመልከት ይቻላል፡፡



ፎቶ 2፡- ዋና ዋና መረጃ አቀባዮች በከፊል [14]

## 3.2.2.3 ተተኳሪ የቡድን ውይይት

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ካገለገሉ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል ተተኳሪ የቡድን ውይይት አንዱ ነው፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ምክንያት መረጃ በምልከታ እና በቃለ መጠይቅ በተለያዩ ምክንያቶች ማግኘት የማይቻልበት ሁኔታ ሲፈጠር እና ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት ሲፈለግ የሚዘጋጅ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው፡፡ ይህ ዘዴ መረጃ ለመሰብሰብ ከማገዙ በተጨማሪ የተሰበሰበው መረጃ ትክክለኛነት ለማረጋገጥም እና

[14] ፎቶ ባጥኚው 14/05/2008 አልከሶ

መረጃውን ሚዛናዊ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ምክንያቱም በውይይቱ ወቅት አንዱ ተሳታፊ ያነሳውን ሀሳብ ሌላኛው እየደገፈ፣ እየተቃወመ እና እያዳበረ ስለሚሔድ መረጃው ሚዛናዊነት እና ትክክለኛነት እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

“ተተኳሪ የቡድን ውይይት ጥልቅና ዝርዝር መረጃን ለማግኘት የሚረዳ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሲሆን ለምርምሩ የሚረዳ ሀሳብ ለማፍለቅም ይረዳል” በማለት ያለው (2004፣192) ያብራራሉ፡፡ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በአጭር ጊዜ ውስጥ ከብዙ ሰዎች አስፈላጊውን መረጃ ማግኘት የሚያስችል የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (Bloor and Wood 2006: 88)፡፡ በቡድን ውይይት ወቅት በአንድ ቡድን ውስጥ መሳተፍ ያለበት የሰው ብዛት ከአምስት ያላነሰ ከአስራ ሁለት ያልበለጠ መሆን እንዳለበት Tester (1997፡6) እና Robson (2002፡2) ይገልጻሉ፡፡ እነዚህ ምሁራን የተሳታፊዎች ቁጥር ከአምስት ማነስ የለበትም ያሉበት ምክንያት መረጃው ተአማኒነት ላይኖረው ይችላል በማለት ሲሆን ከአስራ ሁለት ማለፍ የለበትም ያሉበት ምክንያት ደግሞ ውይይቱን በሚገባ መቆጣጠር አዳጋች ይሆናል ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡

ተተኳሪ የቡድን ውይይት ለዚህ ጥናት ጥሩ የመረጃ ምንጭ በመሆን አገልግሏል፡፡ በመሆኑም ሁለት ጊዜ የቡድን ውይይት በማዘጋጀት ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ የመጀመሪያው የቡድን ውይይቱ የተካሄደው ግንቦት 24/2007 ዓ.ም አልከሶ ሀረም ውስጥ ነው፡፡ በዚህ የቡድን ውይይት ወቅት እያንዳንዱ ቡድን ሰባት ሰባት አባላት ያሉት ሦስት ቡድን ተዋቅሯል፡፡ በጠቅላላ በወይይቱ የተለያየ እድሜ፣ ጾታ፣ የትምህርት ደረጃ እና ማህበራዊ ስልጣን ያላቸው ሃያ አንድ ሰዎች ተሳትፈውበታል፡፡ ከነዚህ መካከል አስራ ሁለቱ ወንዶች ሲሆኑ ዘጠኙ ሴቶች ናቸው፡፡ በዚህ የቡድን ውይይቱ የተሳተፉ ተወያዮች የተመረጡት አንዳንዶች በታላሚ ዘዴ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ብድግ ብድግ (Random Sampling) ዘዴ የተገኙ ናቸው፡፡ በዚህ ሁኔታ ተወያዮቹ ከተሰበሰቡ በኋላ በመጀመሪያ ሶስቱም ቡድኖች በተናጠል እንዲወያዩ ካደረኩ በኋላ እንደገና በጋራ እንዲወያዩ አድርጌያለሁ፡፡ በጋራ እንዲወያዩ ያደረኩበት ምክንያት ሶስቱም ቡድኖች አንድ ላይ ሲወያዩ ከቀድሞው የተሻለ መረጃ እንደሚገኝ ስላመንኩ ነው፡፡ በውይይቱ ከሚሳተፉ መረጃ አቀባዮች መካከል በቃለ መጠይቅ የተሳተፉም ይገኙበታል፡፡

በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እያንዳንዱ ተካፋይ አባል ሀሳቡን በነጻነት ስለሚያቀርብ ውስጣዊ ስሜቱን የመግለጽ እድል ፈጥሯል:: በዚህ ጊዜ የተለያዩ ሀሳቦች በቀልድ፣ በምሳሌያዊ አነጋገር፣ በተረትና ምሳሌ በመሳሰሉት እየተዋዙ ተንሸራሽረዋል:: በዚህ ሂደት ተመራማሪውም ቢሆን ከጥያቄ አቅራቢነት ጥንቃቄ በተሞላው ሁኔታ /የሚያውቅ እንኳን ቢሆን ራሱን እንደአላዋቂ ቆጥሮ/ ወደ ሀሳብ አጠናካሪነት የሚሸጋገርበት እድል ፈጥሯል። በዚህ ውይይት መውሊድ መከበር አለበት እና መከበር የለበትም የሚሉ ወገኖች ተሳትፈውበት ለሀሳባቸው ማጠናከሪያ ሀሳብ ከቁርአን እና ከሀዲስ መረጃ በማቅረብ ተወያይተዋል።



ፎቶ 3፡-ወጣቶች እና ሴቶች የቡድን ቡድን ውይይት ሲያካሄዱ[15]

ሁለተኛው የቡድን ውይይት ጥር 25/2008 ዓ.ም ተካሂዷል። በዚህ የቡድን ውይይት አስር ሰዎች የተሳተፈዋል። በዚህ ውይይት ስምንት ወንዶች እና ሁለት ሴቶች ተሳተፈዋል። በዚህ ቀን በተካሄደው ውይይት በአሁኑ ጊዜ ሀረሙን በዋናነት የሚመሩት አቶ ነስሮ ሰኢድ እና የመስጂዱ ምክትል ኢማም የሆኑት ሼኽ ከድር መሳተፋቸው ስለ መውሊዱ እና ሀረሙ በርካታ ጠቃሚ መረጃዎችን ማግኘነት ችያለሁ። ይህ ውይይት የተካሄደው ከዋና

[15] ፎቶ በአጥኚው 24/09/07 አልከሶ

ዋና መረጃ አቀባዮች መረጃ ከሰበሰብኩ በኋላ ነው። በመሆኑም በቡድን ወይይቱ ወቅት ያነሳኋቸው ሀሳቦች አንዳንዶቹ በዋና መረጃ አቀባዮች የተዳሰሱ ሲሆኑ አብላጫዎቹ ግን ያልተዳሰሱ ናቸው። በዚህ ውይይት በአጠቃላይ የአልከሶ መውሊድ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለው የአከባበር ሁኔታ ተዳሷል። ከዚህ በተጨማሪ ስለ አልከስዬ ማንነት፣ ስለሳቸው የሚወሩ ተረኮች፣ አፈ ታሪኮች እና ፈጸሟቸው የሚባሉ ተአምራቶች ተነስተው ውይይት ተደርጎባቸዋል።

በዚህ የቡድን ውይይት የሚቀርቡበት በመሆኑ ብዥታዎች እና ድንግርግሮች ጠርተውበታል፣ ስህተቶች ታርመውበታል፣ ያልተሟሉ መረጃዎች ተሟልተውበታል። በተለይ በውይይቱ ጊዜ ሰዎች እርስ በእርስ ስህተትን የሚተራረሙ በመሆኑ የመረጃዎች እውነትነት አስተማማኝ እንዲሆን አድርጓል። እንዲሁም መውሊድ መከበር አለበት የለበትም የሚሉ ወገኖች በጉዳዩ ላይ የመወያያ አጋጣሚ ፈጥሯል። በሁለቱም የቡድን ውይይት ጊዜ ቡድኑ ሲዋቀር የዕድሜ ባለጸጋዎች ለብቻቸው፣ ወጣቶች ለብቻቸው እና ሴቶች ለብቻቸው በማድረግ እንዲወያዩ አድርጌያለሁ። ይህን ያደረኩበት ምክንያት በተቀራረበ የዕድሜ ደረጃ ያሉ ሰዎች እርስ በእርስ ሲወያዩ እና ተመሳሳይ ጾታ ያላቸው ሰዎች እርስ በእርስ ሲወያዩ የበለጠ ነጻነት እንደሚሰጣቸው በአካባቢው በቆየሁበት ጊዜ ስለተረዳሁ ነው።

ባጠቃላይ በውይይቱ በዓሉን የሚያከብሩ እና የማያከብሩ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ የተሻለ እውቀት አላቸው ተብለው የተጠቆሙ የተለያየ ዕድሜና ጾታ ያላቸው ሰዎች እንዲሳተፉ ተደርጓል። ይህ የተፈለገበት ምክንያት በዓሉን የሚያከብሩ እና የማያከብሩ ሰዎች አንድ ላይ በመሆን ለምን እንደሚያከብሩ እና ለምን እንደማያከብሩ ሲወያዩ አስፈላጊውን መረጃ ለማሰባሰብ ታስቦ ነው። የተለያየ ዕድሜ እና ጾታ ያላቸው ሰዎች እንዲሳተፉ የተፈለገው ሁሉንም የህብረተሰብ አካል በጥናቱ ለማሳተፍ በማሰብ ነው። የጾታ እና የዕድሜ ስብጥር ቢኖርም በውይይቱ የሴቶች ቁጥር አንሷል። ይህ የሆነበት በሁለት ምክንያት ነው። አንደኛው በአካባቢው ሴቶች ከወንዶች እኩል ቁጭ ብለው በአንድ ርእሰ ጉዳይ መወያየት የተለመደ አይደለም። በመሆኑም በተፈለገው ቦታ፣ ሁኔታ እና ወቅት ሴቶች ሊገኙ አልቻሉም። ሁለተኛው ከወንዶች ይልቅ ሴቶች ስራ ስለሚበዛባቸው በተፈለጉበት ወቅት በቀላሉ ስለማይገኙ ነው።

### 3.3 የመረጃ አቀባዮች ምርጫ እና የከበራ አመራረጥ

በዚህ ንኡስ ስር በዋናነት መረጃ አቀባዮች እንዴት እንደተመረጡ፣ ባጠቃላይ መውሊድ ከበራዎች መካከል በየትኞቹ ላይ ትኩረት እንደተደረገ እና በየትኛው ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ፎክሎራዊ ክንውኖች ላይ ትኩረት እንደተደረገ የምንመለከትበት ነው፡፡

## 3.3.1 የመረጃ አቀባዮች አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ የተከናወነው የመረጃ አቀባዮቹ ሚናቸው ተለይቶ ታውቆ ሲሆን ሲመረጡም የተለያዩ መስፈርቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ እንደ Goldstien (1964፣126)፣ Jackson (1987፣186)፣ እና Hammersly and Atkinson (1991:186) አገላለጽ በፎክሎር ጥናት የመረጃ አቀባዮች ምርጫ የናሙና ጉዳይ አይደለም፡፡ የፎክሎር ጥናት መረጃ አቀባዮች የምርጫ ጉዳይ መሆን ያለበት ዓላማ ተኮር ነው፡፡ ምርጫውም የሚከናወነው የተለያዩ መሰረታዊ ወይም ሳይንሳዊ የሆኑ ጉዳዮችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡ ለምሳሌ ለፎክሎር ጥናት መረጃ አቀባዮችን ስንመርጥ ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች መኖራቸውን ከዚህ በላይ የተገለጹት ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ ጉዳዮቹም መረጃ አቀባዮቹ ለባህሉ ያላቸው ቀረቤታ፣ ልምድ፣ እውቀት፣ ክህሎት፣ ፈቃደኛነት፣ ተነሳሽነት ወይም ፍላጎት እና ባስፈላጊው ቦታ እና ጊዜ የመገኘት ጉዳይ ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ምሁራን አያይዘውም የሚሰበሰበው መረጃ የተወሰኑትን የህብረተሰብ ክፍሎችን አስተያየት ወይም ስሜት ብቻ እንዳይሆን የሚመረጡት መረጃ አቀባዮች የአብላጫውን (የሁሉንም ስለማይቻል) ማህበረሰብ ሀሳብ የሚያንጸባርቁ መሆናቸውን ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን ያስገነዝባሉ፡፡

በመሆኑም በዚህ ጥናት ታላሚ የናሙና አመራረጥ ዘዴን (purposive sampling) በመጠቀም የተለያየ ዕድሜ፣ ጾታ፣ ስልጣን፣ ማህበራዊ ማዕረግ ወዘተ. ካላቸው ሰዎች መረጃ ተሰብስቧል፡፡ ከታላሚ የናሙና አመራረጥ በተጨማሪ ጠቋሚ ናሙና አመራረጥንም ተጠቅሜያለሁ፡፡ ምክንያቱም በታላሚ ናሙና የተመረጡ ሰዎችን ቃለ መጠይቅ በማደርግበት ወቅት በማጠናው ርእስ ጉዳይ ላይ "ከእኔ የተሻለ መረጃ እከሌ ሊሰጥህ ስለሚችል እሱን ብታናግረው የተሻለ ነገር ይነግርሀል" የሚሉ መረጃ አቀባዮች ስላጋጠሙኝ ነው፡፡ ይህን ካሉኝ መረጃ አቀባዮች መካከል ሀጂ ከይረዲን እና አቶ ነስረዲን ይገኙበታል፡፡ ከነዚህ ሁለት ዘዴዎች በተጨማሪ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የብድግ ብድግ (Random Sampling) ዘዴን

በአይነታዊ የምርምር ዘዴ የመረጃ አቀባዮች ቁጥር የሚወሰነው እንደሚገኘው መረጃ ብዛት እና ጥራት ነው:: በዚህ መረጃው የተሰበሰበው በጠቅላላው ከሃምሳ ስድስት መረጃ አቀባዮች ነው። እንደ Mullen (1992፡93) አገላለጽ የባህል መረጃ ከየትኛውም ዕድሜ ደረጃ መሰብሰብ ቢቻልም ዕድሜያቸውን የገፉ ሰዎችን መጠቀም የተሻለ መረጃ ለማግኘት ያስችላል። በዚህ ጥናት በዋናነት ስለ አልከሶ መውሊድ የተሻለ እውቀት ያላቸው፣ እድሜያቸው የገፉ እና በዓሉን ለረጅም ጊዜ በማክበር ለተሳተፉ ወንድ እና ሴት አዛውንቶች እንዲሁም ለሃይማኖት አባቶች ቅድሚያ ተሰቷል። ይህ የሚሆንበት ምክንያት በዓሉ ከብዙ ዓመታት በፊት ጀምሮ የአከባበሩ ሁኔታ ምን እንደሚመስል እና ያሳየውን ለውጥ በተሻለ ሁኔታ ማስረዳት ስለሚችሉ ነው። ወጣቶች እና ልጆች መረጃ አቀባይ ሆነዋል፤ ምክንያቱም የተመለከቱትን ነገር በጥሩ ሁኔታ በአእምሯቸው ቀርጸው የማስቀረት አቅም አላቸው። እነዚህ ወጣቶች እና ልጆች የተፈለጉበት ምክንያት ከአዛውንቶች በተጨማሪ በአሁኑ ወቅት ያለውን የአከባበር ስርዓት ምን እንደሚመስል መናገር ስለሚችሉ ነው።

ከላይ እንደተገለጸው በዚህ ጥናት ሃምሳ ስድስት መረጃ አቀባዮች ተሳትፈዋል። ከነዚህ መካከል ሃያ ሁለቱ ቁልፍ መረጃ አቀባይ ናቸው። የተቀሩት አጠቃላይ መረጃ አቀባዮች ናቸው። ዋና ዋና የሚባለው መረጃ የተሰበሰበው ከእነዚህ ዋና መረጃ አቀባዮች ነው። ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች መረጃ የተሰበሰበው በተለያየ ሁኔታ እና አጋጣሚ በመጠየቅ እና አስተያየት እንዲሰጡ በማድረግ ነው። ይህ አጋጣሚ ደግሞ መረጃ አቀባዮችን ደጋግሞ ለማግኘት በር ከፍቶልኛል። በአጠቃላይ በቃለመጠይቁ ከተሳተፉት መካከል ዋና ዋና መረጃ አቀባዮች በታላሚ የናሙና አመራረጥ (purposive sampling) የተመረጡ ናቸው። የተቀሩት መውሊዱን ሲያከብሩ በአጋጣሚ ቀርቦ በማነጋገር እና በዋና መረጃ አቀባዮች ጥቆማ መሰረት የተገኙ ናቸው። ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል ከጾታ አንጻር ሰላሳ ስምንቱ ወንዶች ሲሆኑ አስራ ስምንቱ ሴቶች ናቸው። የሴቶች ቁጥር ያነሰው ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ሴቶች በብዛት ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ ስላልሆኑ እና ስራ ስለሚበዛባቸው ነው። ፈቃደኛ ያልሆኑበት ምክንያት ደግሞ ከዚህ በፊት ከከተማ ከመጣ ሰው ጋር ቁጭ ብለው መነጋገር አለመልመዳቸው እና ማፈራቸው ነው። ከዚህ በተጨማሪ "እኔ ስለዚህ ጉዳይ የማውቀው ነገር የለም ሌላ ሰው ጠይቅ" በማለታቸው ነው። ከዕድሜ አኳያ ከአስራ አራት እስከ ሰላሳ አስራአንድ፣ ከሰላሳ እስከ አርባ አምስት ሃያ አንድ፣ ከአርባ አምስት እስከ ስልሳ አስራአራት፣ እና ከስልሳ አመት በላይ አስር መረጃ አቀባዮች በቃለ መጠይቁ

ተሳትፈዋል፡፡ ከሃይማኖት አንጻር አርባ ስድስቱ  ሙስሊም ሲሆኑ አስሩ የክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው፡፡

### 3.3.2 የከበራ አመራረጥ

በዚህ ጥናት መረጣ የተካሄደው በመረጃ አቀባዮች ላይ ብቻ ሳይሆን መውሊድ ሲከበር በሚከናወኑ የተለያዩ ሃይማኖታዊ፣ ባህላዊ እና ፎክሎራዊ ከበራዎች ላይ ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም በመውሊድ ሰሞን ከሚካሄዱ በርካታ ሃይማኖታዊ ክንውኖች መካከል ይህ ጥናት ሶላት መስገድ፣ ሀዲስ መናገርና ማዳመጥ፣ ዚያራ ማድረግ ተመርጠዋል፡፡ ከማህበራዊ ክንውን መካከል እርስ በእርስ ግንኙነት ማጠናከር፣ መማማር፣ የንግድ ስራ መስራት፣ እና የተቸገረ ሰው መርዳት የመሳሰሉት ክንውኖች ሲከናወኑ ተመርጠዋል፡፡ ከፎክሎር አንጻር ደግሞ አጠቃላይ በመውሊድ ሰሞን የሚካሄዱ መንፈሳዊ እና ቁሳዊ ፎክሎሮች ላይ ተተኩሯል፡፡ ስለዚህ ናሙና የተወሰደው የመረጃ አቀባዮችን ብቻ ሳይሆን በመውሊድ ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል በተወሰኑት ከበራዎች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ክንውኖች የተመረጡት አጠቃላይ በሆነ ሁኔታ የመውሊድ አክባሪዎች አመለካከታቸውን ሃይማኖታዊ እና አለማዊ አስተሳሰባቸውን እና ፎክሎራቸውን ያሳያሉ ተብለው የታመነባቸውን ነው፡፡

## 3.4 መረጃ መሰብሰቢያ የመስክ መቼቶች

አንድ መስከኛ ወደ መስክ ከመሰማራቱ በፊት መስክ ላይ መረጃ እንዴት መሰብሰብ እንዳለበት አስቦ እቅድ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡ አጥኚው እቅድ ሲያዘጋጅ ከሚያስብበት ጉዳይ መካከል በመስክ ላይ በምን ሁኔታ መረጃ መሰብሰብ አለብኝ የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ሲያስብ ደግሞ ስለመቼት ማሰቡ አይቀርም፡፡ አንድ የፎክሎር ተመራማሪ አውድ ላይ መረጃ ሲሰበስብ ሶስት አይነት የምልከታ መቼቶችን ሊጠቀም ይችላል፡፡ እነሱም ተፈጥሯዊ መቼት፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት እና አርቲፊሻል መቼት ናቸው (ፈቃደ 1991፡11-13)፡፡ ከእነዚህ መካከል በዚህ ጥናት በዋናነት መረጃ ለመሰብሰብ ያገለገለው ተፈጥሯዊ መቼት ነው፡፡ ተፈጥሯዊ መቼት አንድን የፎክሎር ዘውግ ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ ወይም በትክክለኛው ቦታ፣ወቅት እና ሁኔታ በመገኘት መረጃን መሰብሰብ የሚያስችል መቼት ነው፡፡

Goldstein (1964:76) “በፎክሎር ጥናት በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን አገልግሎት በትክክል ለመረዳት ተመራጩ መቼት ተፈጥሯዊ አውድ ነው” ይላሉ፡፡ ይህ ማለት አንድን የፎክሎር ዘውግ ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ መመልከት ማለት ነው፡፡ እንደ Goldstein (1964:38)

አገላለጽ ተፈጥሯዊ መቼት አንድ ማህበረሰብ የሚተገብረውን ልማድ ሌላ በአንድ አካል እንዳለ ሳያውቅ ወይም እንደሌለ በማሰብ የሚተገብረውን ጉዳይ ሲተገብር (ሲከውን) በአካል በመገኘት መረጃ መሰብሰብ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ሀሳብ ፈቃደ (1991፡17) ተፈጥሯዊ መቼት ከመስክ ከዋናነው የመረጃ ምንጭ መረጃ የሚሰበሰብበት መቼት ነው በማለት ያጠናክሩታል፡፡ በመሆኑም ለዋናው መውሊድ አስራ አምስት ቀን ሲቀረው ጀምሬ በቦታው በመገኘት በመውሊድ ቅድመ ዝግጅት ምን ምን እንደሚከናወን፣ በዋናው የመውሊድ ቀን ምን ክንውን እንደሚከናወን እና በድህረ መውሊድ የአልከሶ አካባቢ ምን እንደሚመስል የተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን በመጠቀም መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ባጠቃላይ ይህን መቼት በመጠቀም የአልከሶ መውሊድ የሚከበርበት ቦታ በመገኘት አጠቃላይ ሃይማታዊ፣ ማህበራዊ እና ፎክሎራዊ ክንውን ሲከናወን መመልከት ችያለሁ፡፡

መስክ ላይ ሁል ጊዜ መረጃ መሰብሰብ በተፈጥሯዊ መቼት ብቻ መሰብሰብ አዳጋች ነው፡፡ ምክንያቱም በአንድ ጊዜ ሁሉም የፎክሎር ዘውጎች ሊከወኑ ይችላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አንዱን ክዋኔ ስንመለከት ሌላኛው ሊያመልጠን ይችላል፡፡ ለምሳሌ የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ የሰርግ ስነ ስርዓት ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ መሰብሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም ወንዶች በፈረስ ሆነው አይሎጋሆ እያሉ ሲሔዱ ሴቶች ከበሮ እየመቱ ከኋላ ሲከተሉ ያለውን ሁኔታ በሙሉ ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ ተከታትሎ መረጃ መሰብሰብ ይከብዳል፡፡ በወንዶቹ በኩል ያለውን ሁኔታ ስንመለከት በሴቶቹ በኩል ያለው ክዋኔ ስለሚያመልጠን መረጃችን ምሉዕ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡ ሌሎቹንም የፎክሎር ዘውጎቹን በተፈጥሯዊ መቼት ለመሰብሰብ ብንሞክር ተመሳሳይ ሁኔታ ሊገጥመን ይችላል፡፡ ስለዚህ በተፈጥሯዊ መቼት መረጃ መሰብሰብ ለማይችል ተመራማሪ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት አንዱ እና ተመራጭ መንገድ ነው፡፡

ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት አንድ መስከኛ መስክ ላይ ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ መረጃ መሰብሰብ በማይችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ተፈጥሯዊ የሚመስል መቼት በማዘጋጀት መረጃ የሚሰበሰብበት መቼት ነው፡፡ ልዩ ልዩ የፎክሎር ዘውጎችን መረጃ ለመሰብሰብ ሲታቀድ ከተፈጥሯዊ መቼት በተጨማሪ ቅንብር ተፈጥሮአዊ መቼትን ማደራጀት አስፈላጊ እንደሆነ ፈቃደ (1999፡18) ይገልጻሉ:: ይህን የመቼት አይነት ለማዘጋጀት ጥንቃቄ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ በተቻለ መጠን የሚጠናውን ማህበረሰብ ጠንቅቆ ማወቅ ተገቢ ነው፡፡ እንደ Goldstein (1964፡58) አገላለጽ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት ድንገት ደርሶ የሚዘጋጅ ባለመሆኑ ከማህበረሰቡ ጋር ለተወሰነ ጊዜ አብሮ መቆየት አስፈላጊ ነው፡፡

በቅንብር ተፍጥሯዊ የመቼት አይነት የአልከሶ መውሊድን ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ መመልከት ያልተቻሉ ጉዳዮችን ለመመልከት አስችሏል፡፡ ለምሳሌ ይህን መቼት በማዘጋጀት አንዳንድ ባህላዊ ምግቦች እንዴት እንደሚዘጋጁ፣ በየኸለዋዎቹ መንዙማ ሲባል ያለው ድባብ ምን እንደሚመስል፣ ወዘተ ተመልክቻለሁ፡፡ እንዲሁም በኸለዋዎች ስዞር እና በሸምሰል ጀማል(ትልቁ መስጂድ ነው) እና ከሀረሙ ውጭ በሚገኙ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ ያለው ድባብ በቃለ መጠይቅ ማወቅ ቢቻልም መረጃው የበለጠ ለማጠናከር እና ተአማኒነት እንዲኖረው በአሉ ካለፈ በኋላ ሁለት ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በማዘጋጀት መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ ነገር ግን በዚህ መቼት የተሰበሰበው መረጃ በተፈጥሯዊ መቼት ከሚሰበሰበው አንጻር ስንመለከተው ተፈጥሯዊነቱ ያነሰ ነው እንዲሁም ከዋኞቹም ሲከውኑ እንደ መጀመሪያው የማይከውኑ በመሆኑ መረጃው ክፍተት ስለሚኖርበት በዚህ ጥናት የተካተቱት አብላጫ መረጃዎች የተሰበሰቡት ወደ አልከሶ ሀረም ደጋግሞ በመሄድ በተፈጥሯዊ መቼት ነው፡፡

ባጠቃላይ ለዚህ ጥናት ከዚህ በላይ ከተገለጹት የመቼት አይነቶች መካከል ተፈጥሯዊ እና ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በተፈጥሯዊ መቼት በዓሉ ሲከበር አጠቃላይ ድባቡ ምን እንደሚመስል መመልከት ችያለሁ፡፡ በበዓሉ ከሚከወኑ ጉዳዮች መካከል ጫት መቃም፣ ድቤ መምታት፣ መንዙማ ማለት፣ ዚያራና ሌሎችም ጉዳዮች በተፈጥሯዊ መቼት ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡ ነገር ግን ሁሉንም ድባብ በተፈጥሯዊ መቼት መሰብሰብ ያልቻልኩኝ በመሆኑ በዓሉ ካለፈ በኋላ የመውሊዱን አከባበር ከሚመሩ ኮሚቴዎች ጋር በመነጋገር ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት በማዘጋጀት የጎደለ መረጃ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በመሆኑም በእነዚህ መቼቶች አማካኝነት የመውሊድ አክባሪዎች አጠቃላይ አኗኗር፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት፣ ሃይማኖታዊ እና ፎክሎራዊ ተግባራቸው ምን እንደሚመስል መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡

## 3.5. የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻር

የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻር ማለት በተጠኚው ማህበረሰብ እና በአጥኚው አካል ወይም ሰው አንጻር የሚታይ ርዕስ ጉዳይ ነው፡፡ እንደ Jackson (1987:86) አገላለጽ የአንድ ማህበረሰብ ባህል ሲጠና የሚያጠናው አጥኚ የማህበረሰቡ አባል ከሆነ ውስጣዊ (emic/insider) አንጻር

ተብሎ ይጠራል፡፡ ከዚህ ተቃራኒ ደግሞ የሚጠናው ማህበረሰብ የሚጠናው ከማህበረሰቡ ውጭ በሆነ አጥኚ ከሆነ (etic/ out-sider) አንጻር ይባላል፡፡ በፎክሎር ጥናት ውስጣዊ አንጻር የተሻለ እንደሆነ ወይም በርካታ ጠንካራ ጎኖች እንዳሉት ፈቃደ (1991፡58) እና Dundes (1975፡124) ያስረዳሉ፡፡ ለዚህ የአንጻር አይነት ጠንካራ ጎኖች መካከል አጥኚው የማህበረሰቡ አባል ስለሆነ ትክክለኛ መረጃ አቀባዮችን በቀላሉ ማግኘት ይችላል፣ ለአካባቢው፣ ለማህበረሰቡ ባህርይ፣ የአየር ጸባይ፣ አለባበስ፣ ምግብ ወዘተ አዲስ አይሆንም፡፡ እንደ Dundes (1975፡132) አገላለጽ አንድ አጥኚ አንጻሩ ውስጣዊ ከሆነ በፎክሎር ጥናት ቁልፍ የሆነው የቋንቋ ችግር አያጋጥመውም፡፡ እንዲሁም በማህበረሰቡ የሚፈቀዱ እና የማይፈቀዱ ህግጋቶችን ስለሚያውቃቸው በጥናቱ ወቅት የሚያጋጥመው ችግር መጠኑ ይቀንሳል፡፡ ይህ ሲባል ግን ይህ የአንጻር አይነት የራሱ የሆነ ክፍተት የለውም ማለት አይደለም፡፡ በዚህ ማብራሪያ መሰረት የዚህ ጥናት አጥኚ ውስጣዊ (emic/insider) ነው፡፡ በመሆኑም ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ጥናቱን ሳካሄድ የቋንቋ፣ የባህል እና የተግባቦት ችግር አላጋጠመኝም፡፡

## 3.6 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለአንድ ጥናት መረጃ ለመሰብሰብ በሚደረገው ጥረት ውስጥ የተለያዩ መረጃ መያዣ (መሰነጃ) ዘመናዊ መሳሪያዎች ያገለግላሉ፡፡ ከነዚህ መካከል መቅረጸ-ድምጽ፣ ቪድዮ ካሜራ እና ፎቶ ካሜራ ናቸው፡፡ ከመስክ መረጃ ሲሰበሰብ የምስል እና የድምጽ መቅረጫ ዘመናዊ መሳሪያዎችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን Mattews and Ross (2010:197) ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም Toelken (1996:359) መስክ ላይ የፎክሎር የመረጃ አሰባሰብ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን መጠቀም አስተማማኝ የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንደሚያግዝ ያብራራሉ፡፡ ስለዚህ በዚህም ጥናት እነዚህ መሳሪያዎች ለመረጃ መሰብሰቢያነት አገልግለዋል፡፡ በቪዲዮ ካሜራ መውሊዱ በሚከበርበት ወቅት የአከባበር ስርአቱን ምን እንደሚመስል የተለያዩ በዓሉ የሚከበርባቸው ቦታዎች በመዘዋወር ቀረጻ አካሂጃለሁ፡፡ ቀረጻ የተካሄደባቸው ቦታዎች ኸለዋዎች፣ የምግብ ማዘጋጃ ስፍራዎች፣ ዱኣ የሚደረግባቸው ቦታዎች፣ የክርስትያኖች ማረፊያ፣ የንግድ እንቅስቃሴ የሚካሄድባቸው ስፋራዎች፣ ከከተማ የሚመጡ ሰዎች ማረፊያዎች፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ክዋኔዎች እና መረጃ አቀባዮች በፎቶ ካሜራ ተቀርጸዋል፡፡ መቅረጸ ድምጽ ደግሞ ከመረጃ አቀባዮች ጋር ቃለ መጠይቅ ሲደረግ አገልግሏል፡፡ አልፎ አልፎ ምስልና ድምጽ በመቅረጸ ድምጽ ለመቅረጽ

የማያመች ሁኔታ ሲያጋጥም መረጃው በማስታወሻ ደብተር የተያዘ በመሆኑ የተለያዩ ማስታወሻ መያዣ ደብተሮች ተጠቅሜያለሁ፡፡

## 3.7 የመስክ ቆይታ ጊዜዎች

ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ለመሰብሰብ በአጠቃላይ በአምስት ዙር ለስልሳ አምስት ቀናት ያህል መስክ ላይ ቆይቻለሁ፡፡ እነዚህ ቀናት እና ዙሮች የተመረጡበት የየራሳቸው የሆነ ምክንያቶች አሏቸው፡፡ በመጀመሪያው ጉዞ ከ23/04/07 እስከ 28/04/07 ድረስ ቆይቻለሁ፡፡ ይህን ጉዞ ያደረኩት ራሴን የበለጠ ከአካባቢው ማህበረሰብ ለማስተዋወቅ እና ወደ ፊት መረጃ ለማሰባሰብ ሁኔታዎች ለማመቻቸት ነው፡፡ በዚህ የመስክ ቆይታዬ ከመስጂዱ አስተዳዳሪዎች እና ከአካባቢው ሰዎች ጋር በሚገባ ተዋውቂያለሁ፡፡ እንዲሁም ሀረሙን እና በሀረሙ ዙሪያ ያሉ ኸለዋዎችን ተመልክቻለሁ፤ ፎቶዎችን አንስቻለሁ፡፡ በተጨማሪም የተወሰኑ ሰዎችንም ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ በመጨረሻም ወደ ፊት ጥሩ መረጃ አቀባይ ሊሆኑኝ የሚችሉ ሰዎችን በማፈላለግ እና ለዋናው መውሊድ እንደምመለስ በመንገር አድራሻቸውን ተቀብዬ ተመልሻለሁ፡፡

በሁለተኛው ዙር ከ15/09/07 እስከ 05/10/2007 ድረስ ቆይቻለሁ፡፡ ይህን ጊዜ የመረጥኩበት ምክንያት የ2007ቱ የአልከሶ ዋናው መውሊድ የሚከበርበት ሰሞን በመሆኑ ነው፡፡ በቆይታዬም ከተለያዩ መረጃ አቀባዮች ጋር ቃለ መጠይቅ ከማድረጌ በተጨማሪ የተተኳሪ ቡድን ወይይትም አድርጌያለሁ፡፡ ቃለመጠይቁን እና ውይይቱን በመቅረጸ ድምጽ፣ በፎቶ እና ቪዲዮ ካሜራ ቀርጫለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሊቾ ዊሪሮ እና ዳሎቻ ወረዳዎች በመሄድ መረጃ አሰባስቤያለሁ፡፡ ዞኑ ውስጥ ካሉ ወረዳዎች ውስጥ ሁለቱ የመረጥኩት ስለ ብሔረሰቡ እና ስለ አልከስዬ ጥሩ መረጃ አቀባዮች መኖራቸው ስለተነገረኝ ነው፡፡

በሁለተኛው ዙር የሰበሰብኩትን መረጃ ወደ ወረቀት ከገለበጥኩ (ትራንስክራይብ) በኋላ ይጎላል ያልኩትን መረጃ ለማሰባሰብ ሶስተኛ ዙር መረጃ ለመሰብሰብ ወደ መስክ ሄጃለሁ፡፡ በሶስተኛው ዙር በአልከሶ መስጂድ የወሩ መውሊድ ሲከበር ከ20/06/08 እስከ 10/07/08 ድረስ መስክ ላይ በመቆየት በቦታው መውሊድን ሲያከብሩ ላገኘኋቸው ምዕመናን ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ከመውሊድ አክባሪዎች በተጨማሪ በወራቤ እና በአልከሶ ከተማ የሚገኙ መውሊድ የሚያከብሩ እና የማያከብሩ ሰዎችንም አነጋግሪያለሁ፡፡ በዚህ ቆይታዬ

ከመረጃ አቀባዮቼ በድምጽ የሰበሰብኩትን መረጃ ወደ ወረቀት ቀይሬያለሁ። በእነዚህ ዙሮች የሰበሰብኳቸውን መረጃ በመተንተን ለአማካሪዬ እና ለተለያዩ ሰዎች ካሳየሁ በኋላ መጨመር አለባቸው የተባልኳቸውን መረጃ ለማሰባሰብ ለአራተኛ ጊዜ ወደ መስክ ሄጃለሁ። በአራተኛው ዙር የ2008ቱ ዋናው መውሊድ ሲከበር ከ10/09/08 እስከ 25/09/08 ድረስ ቆይቻለሁ። በዚህ ዙር ልክ እንደ ቀድሞው የመስክ ቆይታዬ ለተለያዩ ሰዎች ቃለ መጠይቅ አድርጌያለሁ። በተጨማሪም ምልከታ አካሂጃለሁ። ምልከታዬ ተሳትፏዊ እና ኢ-ተሳትፏዊ ነበር። በመሆኑም በሁለቱም የምልከታ ወቅት ለጥናቱ የሚሆን መረጃ ማግኘት ችያለሁ።

ህዳር 2009 ዓ.ም በ11ኛው የስልጤ ብሔረሰብ ባህል፣ቋንቋ እና ታሪክ ሲፖዝየም ላይ ጥናታዊ ጽሁፍ ለማቅረብ ወደ ወራቤ ሄጄ ነበር። በዚህ ሲፖዝየም ከተሳተፍኩ በኋላ ከ16/03/09 እስከ 20/03/09 ድረስ በመቆየት በአማካሪዬ እና በደረጃ ማበልጸጊያ ፈታኞቼ መጨመር አለባቸው የተባልኳቸውን መረጃዎች ወራቤ ከተማ እና አልከሶ ሀረም ላገኘኋቸው ሰዎች ቃለ መጠይቅ ለማድረግ ለአምስተኛው ጊዜ የመስክ ጉዞ በማድረግ የተጓደሉ መረጃዎችን ማሟላት ችያለሁ። ስለዚህ እነዚህ አምስት የመስክ ጉዞ በአጋጣሚዎች የተፈጠሩ ሳይሆኑ ምክንያታዊ በሆነ ሁኔታ የተያያዙ ናቸው።

መውሊድን የሚያከብሩ ሰዎች ከተለያዩ ቦታዎች የሚሰባሰቡ በመሆኑ ከአልከሶ እና አከባቢው በተጨማሪ በስልጤ ዞን ወረዳ ከሆኑት ከቶላ ዳሎቻ ወረዳ እና ከደጋ አሊቾ ዊሪሮ ወረዳ እና ወራቤ ከተማ በመሄድ መረጃ ሰብስቤያለሁ። ከነዚህ ወረዳ ነዋሪዎች በተጨማሪ ከቡታጅራ፣ ከአዲስ አበባ፣ ከጅማ፣ከወላይታ፣ ከሻሸማኔ፣ ከጉራጌ ዞን እና ከአርሲ ከተሰባሰቡ ምዕመናን መረጃ ለመሰብሰብ ሞክሪያለሁ። እንዲሁም ለጉብኝት ወደ ስፍራው የሄዱ ሁለት የውጭ ሀገር ዜጎችን(የመናዊያን) አነጋግሪያለሁ። ስለዚህ መረጃው የተሰበሰበው በአልከሶ አካባቢ ከሚኖሩ ነዋሪዎች በተጨማሪ ከተለያዩ ወረዳዎች እና ከተለያዩ ከተማዎች ከተሰባሰቡ የበዓሉ ተሳታፊዎች ነው። በመሆኑም ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች በቃለመጠይቅ የተሰበሰበው መረጃ የትሪያንጉሌሽን መርህን በመከተል በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት አመሳክሬያለሁ።

## 3.8 የማጥሪያ ዘዴ (Triangulation)

አንድ ጥናት ውስጥ ተመራማሪው ለሚሰራው ስራ መረጃ የሚሰበስብበትም ሆነ የሚተነትንበት ስልት ከመረጃው ትክክለኛነት ወይም ተአማኒነት ሊኖረው ይገባል፡፡ ይህም ጉዳይ በተለያየ ዘዴ ማጣራት ወይም ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ዘዴዎች መካከል የሶስትዮሽ ማጣሪያ ስልት በእንግሊዘኛው "Triangulation" አንዱ ነው፡፡ እንደ Hammersley & Atkinson (1991፤198) እና Creswell (2014፤211) አገላለጽ በዚህ ስልት የአንድን ርእሰ ጉዳይ ምንነት እና ትክክለኛነት ከተለያዩ አካላት በተሰበሰበ መረጃ አማካይነት ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ይህ ማለት በቃለ መጠይቅ የተሰበሰበን መረጃ በምልከታ ይረጋገጣል፤ይፈተሻል እንዲሁም በምልከታ የተሰበሰበ መረጃ በቃለ መጠይቅ ይረጋገጣል፡፡ በቃለ መጠይቅም ሆነ በምልከታ የተሰበሰበው መረጃ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ይመረመራል፡፡ በሌላ መንገድ ደግሞ በምልከታ የተሰበሰበን መረጃ በቃለ መጠይቅ ይረጋገጣል፤ይፈተሻል፡፡ እንዲሁም በሁለቱ ስልቶች የተሰበሰበው መረጃ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ይረጋገጣል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ይህ መርህ አንድን መረጃ በምልከታ ወይም በቃለ መጠይቅ ብቻ ከመሰብሰብ ይልቅ የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባል፡፡ ከመረጃ አቀባዮች አንጻር ደግሞ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ አንድ መረጃ አቀባይ የነገረንን መረጃ ብቻ አምኖ ከመቀበል በተጨማሪ መረጃውን የተለያዩ ሰዎችን በማነጋገር ማረጋገጥ አስፈላጊ እንደሆነ ያስረዳል፡፡

Patton (2001፤2) የ"ትሪያንጉላሽን" መርህን ምንነት በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል፡፡ ይህ ስልት የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም እና በአንዱ ስልት የተሰበሰበ መረጃ በሌላኛው ስልት መደገፍ አስፈላጊ እንደሆነ ያስገነዝባሉ፡፡ እንዲሁም በአንዱ ስልት የሚስተዋለው ክፍተት በሌላኛው ስልት ይሞላል ካሉ በኋላ "Rather than seeing triangulation as a method for validation or verification, qualitative researchers generally use this technique to ensure that an account is rich, robust, comprehensive and well-developed." በማለት ይህ ስልት ለአይነታዊ የጥናት አይነት ምን ያክል ጠቃሚ እንደሆነ ያብራራሉ፡፡ Creswell (2014: 212) ደግሞ ይህን ስልት ከተከተልን ጥሬ መረጃችንን ስንተነትን ከቀደምት ጥናቶች ጋር ማስተያየት ወይም ማረጋገጥ እንዳለብን ይመክራሉ፡፡

Denzin (1978) and Patton (2001) አራት አይነት የ"ትሪያንጉሌሽን" አይነቶች እንዳሉ ይገልጻሉ፡፡ እነሱም አንደኛ "Methods triangulation" መረጃ የምንሰበስብበት ዘዴ ትክክል መሆኑን እና አንዱ ከአንዱ ጋር ተጣምሮ የሚሰራበት መሆኑን ማረጋገጥ፡፡ ሁለተኛ "Triangulation of sources" የሰበሰብነው መረጃ ትክክል መሆኑን የተለያዩ ጊዜያትን፣ መረጃ አቀባዮችን በግል እና በቡድን በማግኘት እና ለመረጃ አቀበዮች የምናቀርበው ጥያቄ በተለያየ እይታ(view points) እንዲያዩት በማድረግ ማረጋገጥ፡፡ ሶስተኛ "Analyst Triangulation" መረጃ ሲሰበሰብ የተለያየ ሰው ምልከታ እንዲያካሄድ እና የተሰበሰበው መረጃ በተለየዩ ሰዎች ትንታኔ እንዲሰጥበት ማድረግ፡፡ አራተኛ "Theory/perspective triangulation" የተሰበሰበው መረጃ የተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችን በመከተል መመርመር እና መተንተን የሚሉት ናቸው፡፡

በዚህ ጥናት የ"ትሪያንጉሌሽን" መርህ ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ በመሆኑም መጀመሪያ የአልከሶ ሀረምን እና የመስጂዱን አሰራር ጨምሮ አጠቃለይ ምልከታ አደረኩኝ፡፡ በመቀጠልም ስለተመለከትኩት ነገር ሰዎችን ጠየኩ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት በቃለ መጠይቅ ያገኛሁትን መረጃ በምልከታ እንዲሁም በምልከታ ያገኛሁትን በቃለ መጠይቅ በማጠናከር ለማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በእነዚህ ዘዴዎች ያገኘሁትን መረጃ ተተኳሪ የቡድን ውይይት በማዘጋጀት መረጃውን ለማጠናከር እና ተአማኒነት እንዲኖረው ለማድረግ ጥሬያለሁ፡፡ ከትዮሪ አንጻር ደግሞ አንድን መረጃ ከተለያዩ ትዮሪዎች አንጻር በመመልከት ለመተንተን ሞክሪያለሁ፡፡ እንዲሁም የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች እርስ በእርስ የማመሳከር ስራ ሰርቻለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለዚህ ጥናት የሰበሰብኩትን መረጃ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ካለቸው ጥናቶች ጋር በማገናዘብ የሚያመሳስላቸው እና የሚያለያየቸው ጉዳይ አሳይቻለሁ፡፡

## 3.9 የጥናቱ የትንተና ስልት

መረጃን መተንተን ከመስክ የተገኘን ጥሬ መረጃ ከተለያዩ ትወራዎች እና ቀድሞ ከተገኙ ውጤቶች ጋር በማዋሀድ ጥሬ መረጃው ትርጉም እንዲኖረው ማድረግ ነው (Maykut and Morehouse 1994፡110):: እንደ ፈቃደ (1991፡138) እና Schoemaker (1990፡8) አገላለጽ ከመስክ የተገኘን ጥሬ መረጃ ለመተንተን ወይም ትርጓሜ ለመስጠት ከማሰባችን በፊት

ትኩረት ልንሰጣቸው የሚገቡ በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ ከነዚህም መካከል አውዳዊ እና ክዋኔያዊ የትንታኔ ዘዴዎች ተመራጭ ናቸው፡፡

በፎክሎር የመስክ ጥናት የተሰበሰቡ መረጃዎች በሁለት ደረጃዎች ይገለጻሉ:: እነሱም መረጃዎችን መለየት (መመደብ) እና መተርጎም ናቸው (Dundes፣1980፣ 211):: ይህም ትርጓሜ (ትንታኔ) ከዘዴዎቹ ጋር ተስማሚ ከሆኑ ንድፈ ሀሳብ አንጻር መሆን አለበት:: በተለያዩ መንገዶች የተሰበሰቡት መረጃዎች በየፈርጁ ተደራጅተው ተስማሚ ከሆኑ ንድፈ ሀሳቦች አኳያ መተንተን እንዳለባቸው Marshal & Rossman (2006:156) እና Creswell (2007:161) ይገልጻሉ:: በአንድ ጥናት ውስጥ ከመስክ የሚሰበሰቡ መረጃዎች በአግባቡ ተለይተው ለአንባቢ ግልጽ የሆነ ትርጉም እንዲሰጡ በልዩ ልዩ ንድፈ ሀሳቦች መተንተን እንደለባቸው Dundes (1980፣120)፣ Marshae and Rossman (2006፣20) እና Creswell (2007፣85) ይገልጻሉ::

እንደ Goldstein (1964፣125) አገላለጽ በአንድ የጥናት እና የምርምር የስራ ሂደት የተዛማጅ ጥናቶች ተከልሰው የጥናቱ ክፍተት የሚለየው፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎቹ ተመርጠው መረጃ የሚሰበሰበው እና የመተንተኛ ዘዴዎቹ ተቀይሰው መረጃዎች የሚተነተኑት አንድ ዓላማ ለማሳካት ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ ሊመልሰው የሚፈልገውን ጥያቄ ወይም ሊፈታው ያቀደውን ችግር ወይም የጥናቱ የርዕሰ ጉዳይ በተግባር ፈትሾ አንድ ድምዳሜ ላይ መድረስ ነው፡፡ በዚህ መሰረት በፎክሎር ጥናት መረጃ መሰብሰብ አንድ የጥናት አካል ሆኖ መሰረታዊው ጉዳይ ግን ከመስክ የተሰበሰበን መልሶ ከመናገር ባሻገር በተግባር ማከናወን ማስቻል ነው፡፡ ይህ ተግባር ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ በማደራጀት ከሌሎች ተዛማጅ ጉዳዮች ጋር አያይዞ እና አዛምዶ የመተንተን እና የመተርጎም ጉዳይ እንደሆነ Bauman (1986፣22) እና Hammersley and Atkinson(1991፣203) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ እንደ Dundes (1980፣22) አገላለጽ የመረጃ ትንተና ሶስት ዋና ዋና ጉዳዮችን መሰረት አድርጎ ሊከናወን ይችላል፡፡ እነሱም (Texure) ፎክሎሩ የተገለጸበት ስልት(መንገድ)፣ (Text) የፎክሎሩ አይነት እና (Context) ፎክሎሩ የተከናወነበት አውድ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መረጃ መተንተን ማለት ምን ማለት እንደሆነ ፈቃደ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

መተንተን ማለት… የየዘውጉን የተለያዩ መረጃዎች አጥንቶ፣ በመሀከላቸው ያሉትን ገናን አስተሳሳሪ ወይም ከተለያዩ ነጥቦች እያነሱ በመወያየት ወደ አንድ በመረጃው የሚደገፍ ማጠቃለያ ማምራት ማለት ነው። ይህ ሲፍታታ (1ኛ) የየዘውጉን ቅንጣቶች ዓበይት የይዘትና የቅርጽ ባህሪያት አጥንቶ መለየት እና በባህሪያቱ ላይ ተመስርቶ ማጠቃለል ማለት ነው። (2ኛ) በዘውጎቹ ውስጥ ሙሉ የተከሰቱ የጋራ ቅርጽ እና ይዘት- ነክ ገናን ባህሪያት (ጭብጦች) ሊኖሩ እነሱን ለይቶ ለማጠቃለል የሚቻለውን ሁሉ ማድረግ ነው (ፈቃደ 2004፣3)።

እንደ Ben- Amos (1993፣82) አገላለጽ ደግሞ የአንድ ጥናት መረጃ መደራጀት እና መተንተን ያለበት የባህል ባለቤቶች በሚሰጡት ፍች እና መረጃዎቹ ከተሰበሰቡበት ማህበራዊ እና ባህላዊ አውድ ውስጥ በመነጨ አኳኋን ነው። በሌላ አገላለጽ የአደረጃት እና የአገላለጽ ስልቱ በባለቤቶች ድምጽ ወይም አገላለጽ ላይ መመስረት እንዳለበት ከ Ben- Amos ሀሳብ መገንዘብ ይቻላል። በአጠቃላይ ከእነዚህ በላይ ከተጠቀሱት ሶስት ምሁራን ገለጻ በዋናነት የምንገነዘበው የፎክሎሩን ዘውግ ለይቶ መረዳትና የት እና መቼ ወይም በምን ሁኔታ ውስጥ እንደተከናወነ ለይቶ ማወቅ ለትንተናው ሂደት የሚጠቅም ቅድመ ሁኔታ ነው። የፎክሎሩን ፍች በመለየት እና የተገለጸበትን መንገድ በመመርመር ትንተና ሊካሄድ ይችላል። እንዲሁም ተመራማሪው መረጃውን ማደራጀትም ሆነ መተንተን ያለበት የባህሉ ባለቤቶችን ድምጸት ወይም ሀሳብ መሰረት ባደረገ አኳኋን ነው። ባጠቃላይ የትኛውም ከመስክ የተሰበሰበ መረጃ በዘርፉ፣ በቅርጹ፣ በይዘቱ፣ በጭብጡ፣ በሥነ ፋይዳው፣ እንዲሁም በጊዜ ቅደም ተከተል ተለይቶ እና ተደራጅቶ ሊተነተን ይችላል። ከዚሁ አንጻር ለዚህ ጥናት ጠቃሚ የሆኑ ልዩ ልዩ የመተንተኛ ትወራዎች ተዳሰዋል።

አይነታዊ የአጠናን ዘዴን ተከትለን ጥናት ስናካሔድ መተንተኛ ዘዴያችን የሚወሰነው በሚሰበሰበው መረጃ ነው። በመሆኑም ከተሰበሰበው መረጃ አንጻር ጥናቱ በዋናነት ለአይነታዊ የምርምር ዘዴ ትኩረት በመስጠት በክወኔያዊ፣ በስነ ፋይዳ እና ለውጥ እና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት ተተንትኗል። በዚህ መሰረት ለዚህ ጥናት በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች መጀመሪያ እንደወረዱ ወደ ወረቀት ተገልብጠዋል። በመቀጠልም በይዘታቸው ወይም በርዕስ ጉዳያቸው ከተደራጁ በኋላ እንደ አስፈላጊነቱ ከሌሎች መሰል እና ቀደምት ጥናቶች እና ጉዳዮች ጋር እየተሰናኙ ተብራርተው እና ተተንትው ቀርበዋል። ከዚህ በላይ የተገለጹትን የምርምር እና የመተንተኛ ዘዴዎች በመከተል ጥናቱ በገላጭ ስልት (Descriptive Method) ቀርቧል።

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የጥናቱ የአጠናን ዘዴ፣ የጥናቱ ስልት፣ የጥናቱ መረጃ ምንጮች ምን ምን እንደሆኑ ተዳሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመረጃ አቀባዮች ምርጫ (የናሙና አመራረጥ) ምን እንደሚመስል፣ የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻር ምን እንደሆነ፣ መረጃ መሰብሰቢያ የመስክ መቼቶች ምን ምን እንደሆነ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ምን ምን እንደሆኑ እና እንዴት ተግባራዊ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡ በመጨረሻም የመስክ ቆይታ ጊዜዎች መቼ መቼ እንደሆኑ እና በእነዚህ የመስክ ቆይታ ወቅቶች ምን ክንውኖች እንዳከናወንኩ ተመልክተናል፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4 የጽንሰ ሀሳብ፣ የቀደምት ጥናቶች እና የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፎች ቅኝት

የዚህ ምዕራፍ ዓላማ ከዚህ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦችን፣ ንድፈ ሀሳቦችን እና ተዛማጅ ጽሁፎችን መዳሰስ ነው። በመጀመሪያው ክፍል ስለ ፎክሎር፣ ስለ ክብረ በአል፣ ስለ ፎክሎር ስለሚከወንበት አውድ፣ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ለማክበር ስለሚደረግ ጉዞ ቀኝቻለሁ። ከዚህ በተጨማሪ የመውሊድ ምንነት እና አጀማመር በዓለም፣ በአፍሪካ፣ በኢትዮጵያ እና በስልጤ ብሔረሰብ ምን እንደሚመስል ተብራርቶ ቀርቧል። በሁለተኛው ክፍል ይህን ጥናት ለማጥናት የሚረዱ ንድፈ ሀሳቦች ተቃኝተዋል። በመጨረሻው ክፍል ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያላቸው የተለያዩ ቀደምት ጥናቶች ቃኝቻለሁ።

### 4.1 የጽንሰ ሀሳብ ማዕቀፍ

በዚህ ንኡስ ርዕስ ስር ስለ ፎክሎር፣ ስለ ክብረ በአል፣ ስለ አውድ፣ ስለ ሃይማኖታዊ ጉዞ እና ስለ መውሊድ ምንነት እና አጀማመር በዓለም፣ በአፍሪካ፣ በኢትዮጵያ የወጣቶች ግንኙነት፣ በስልጤ ብሔረሰብ ምን እንደሚመስል ተብራርተው ቀርበዋል።

#### 4.1.1 የፎክሎር ምንነት

“ፎክሎር” “ፎክ” እና “ሎር” ከሚሉ ሁለት ቃላት የተዋቀረ ፅንሰ ሃሳብ ነው። “ፎክ” የሰዎች ስብስብ ማለት ነው። “ሎር” ማለት ደግሞ ዕውቀት ወይም ሰዎችን ያሰባሰበ ርዕሰ ጉዳይ ማለት ነው። እንደ Dundes (1980፣1) አገላለጽ የሁለቱ ቃላት ጥምረት “የቡድን ዕውቀት” የሚል ነው። Dundes (1980፣6) “የጋራ ጉዳይ ያሰባሰባቸው ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች ስብስብ ፎክ ይባላል” ይላሉ። ብያኔው ውስጥ የቡድኑ አባላት ለመሰባሰብ ምክንያት የሆናቸው የጋራ ባህርይ እንዳለ ያስገነዝባል። Toelken (1996፣56) ቡድን፣ መገለጫቸው ባህልን መሰረት ያደረገ ተግባቦት ያላቸው ሰዎች ስብስብ ነው ብለዋል። በጥቅሉ የፎክሎር ባለሙያዎች ስለፎክ ቡድን ምንነት ሲያስረዱ ዘር፣ ጎሳ፣ ፆታ፣ ስራ፣ መደብ፣ ዕድሜ፣

የጋራ ፍላጎት ለመሰባሰባቸው ምክንያት የሆኗቸው ከመደበኛ ህጎች ይልቅ ልማዳዊ በሆነ መንገድ የተመሰረቱና የሚኖሩ ሰዎች ስብስብ መሆኑን መረዳት ይቻላል፡፡

ባጠቃላይ ስለ “ፎክ” እና “ሎር” ምንነት Dundes በሚከተለው አስፍረውታል፡፡

> The term “folk” can refer to any group of people what so ever who share at least one common factor. It does not matter what the linking factor is- it could be a common occupation, language or religion-but what is important is that a group formed for what ever reason will have some traditions which it calls its own. In theory a group must consist of at least two persons, but generally most groups consist of many individuals. A member of the group may not know all other members, but he will probably know. The common core of traditions belonging to the group, tradition which help the group have a sense of group identity (Dundes 1965፣2)፡፡
>
> ሲተረጎም
>
> ፎክ የሚለው ስያሜ ማንኛውም የሰዎች ስብስብ የሚገልጽ ሲሆን እነዚህም ሰዎች በጋራ ያገናኛቸው ማንኛውም አይነት ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ማለት የራሳቸው የተለየ ጸባይ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሃይማኖት ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ለዚህ ቡድን መፈጠር ምክንያት ምንም ይሁን ምን አንድ የኔ ነው የሚሉት የጋራ ልማድ(እሴት) ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በጽንሰ ሀሳብ ደረጃ አንድ ቡድን ቡድን ነው እንዲባል ቢያንስ ሁለት ሰዎችን መያዝ ይገባዋል፡፡ ነገር ግን በተለምዶ ቡድኖቹ በርከት ያሉ ግለሰቦችን ያቅፋሉ፡፡ የአንድ ቡድን አባል የሆነ ግለሰብ ሁሉንም የቡድኑን አባላት ላያውቃቸው ይችላል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ግለሰቦች ድርጊቱን ሲፈጽሙ ሲመለከት የእርሱ ቡድን አባላት መሆናቸውን ለይቶ ሊያውቅ ይችላል፡፡ በመሆኑም በጋራ የሚፈጽሙት ድርጊት የማንነታቸው መገለጫ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው ምሁራን ሀሳብ የምንረዳው ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የፎክ እና ሎር ውህድ ውጤት ነው፡፡ ፎክሎር በጠቅላላ እይታ ሲታይ አንዳች ጉዳይ

ያስተሳሰራቸው ወይም ያገናኛቸው ሁለት እና ከዚያ በላይ ሰዎች ስብስብ ማለት ነው፡፡ በመሆኑም ፎክሎር የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ሲነሳ ሁሌም የሰው ልጅ እና ህይወቱ ይቃኛል፡፡

ዛሬ ፎክሎር ብለን የምንጠራው ቃል በቀደሙት ዘመናት oral literature, oral folklore, verbal lore, verbal folkart, verbal form, mentifacts እና በሌሎችም የእንግሊዘኛ ቃላት (ሀረጋት) ይጠራ ነበር፡፡ በሀገራችንም ጽንሰ ሀሳብ ትውፊት፣ ስነቃል፣ ወዘተ የሚሉ ስያሜዎች ነበሩት፡፡ በፈረንሳይ “Traditional Population”፣ በጀርመን “volkskunde”፣ በስዊዲን “folklife” ወዘተ የሚል ስያሜ እንደነበረው ምንጮች እንደሚያስረዱ Dorson (1975፡56) እና ፈቃደ (2001፣12) ያስረዳሉ፡፡

ፎክሎርን (willam tomms) ዊሊያም ቶማስ 1846 “popular antiquities” ከሚለው ወደ “folklore” ከቀየረበት ጊዜ ጀምሮ ስለምንነቱ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ብያኔ ሰጥተዋል፡፡ ከእነዚህም መካከል Maria Leach፣ Bayard፣ Alan Dundes፣ Jones እና ሌሎችንም መጥቀስ ይቻላል፡፡ ለፎክሎር የተለያዩ ምሁራን ብያኔ ለመስጠት ከመሞከራቸው በተጨማሪ በተለያዩ ዘርፎችም ከፋፍለውታል፡፡ ከነዚህም መካከል Dorsonን፣ Maria Leachን፣ Bayardን፣ Magoulickን ወዘተ መጥቀስ እንደሚቻል ፈቃደ (2001፣35) ያስረዳሉ፡፡

ፎክሎር የአንድን ማህበረሰብ አጠቃላይ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ስርዓት፣ እሴት፣ አስተሳሰብ፣ ፍልስፍና፣ አኗኗር ወዘተ የሚያጠና ሰፊና ጥልቅ የሆነ የማህበረሰብ ሳይንስ ዘርፍ ነው፡፡ ለፎክሎር ብያኔ ከመስጠት ይልቅ በስሩ የሚያካትታቸውን ጉዳዮች መዘርዘር ተመራጭ መሆኑን Alan Dundes (1965) እና Michael Owen Jones (1994) ያስረዳሉ፡፡ ይህም ሆኖ ምሁራኑ ፎክሎርን በአራት፣ በአምስት፣ እና በሰባት መድበውታል፡፡ Brunvand (1972፣8) ፎክሎርን “ቃላዊ ፎክሎር፣ ልማዳዊ ፎክሎር እና ቁሳዊ ፎክሎር” በሚል በሶስት ሲመድቡት Toelken (1996፣9) “ቃላዊ ፎክሎር፣ ቁሳዊ ፎክሎር እና ልማዳዊ ፎክሎር” በሚል በሶስት ምድብ መድበውታል፡፡ እንዲሁም Magoulick (2008፣23) “ቃላዊ፣ ልማዳዊ፣ ምልክታዊ እና ቁሳዊ” በሚል በአራት ሲከፍሉት Indiana University Library(2005) “ልማድ፣ የፎክሎር ጥናት፣ ባህላዊ ስነጽሁፍ፣ የባህላዊ ሙዚቃዎች ጥናት፣ ሃገረሰባዊ

እምነቶች፣ ወግ ማዕረግ እና ቁሳዊ ባህል" በሚል በሰባት ከፋፍለውታል።[16] ከነዚህ በተጨማሪ Dorson (1972:3-4) ፎክሎርን በአራት ምድብ የመደቡት ሲሆን እነሱም ቁሳዊ ባህል፣ ስነቃል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ሀገረሰባዊ ልማድ ናቸው።[17] ስለምንነታቸው ቀጥለን በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን።

ሀ. **ቁሳዊ ባህል፡-** ቁሳዊ ባህል አንድ ማህበረሰብ አጠቃላይ ባህሉን፣ ወጉን፣ልማዱን፣ እሴቱን፣ እምነቱን፣ አስተሳሰቡን፣ ፍልስፍናውን ወዘተ በሚገልጽ መንገድ የሚያዘጋጀውን ቁስ የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ ነው። ቁሳዊ ባህል ከጥንት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሰው ልጅ ለልዩ ልዩ ግልጋሎት የሰራቸውን በአይን የሚታዩና በእጅ የሚዳሰሱ ቁሳቁሶችን የሚያጠቃልል እሳቤ ነው። እንደGlassie (1991:1) አገላለጽ የቁሳዊ ባህል ጥናት በተፈጥሮ እና በባህል መካከል ያለውን ልዩነት በአዕምሯችን የምናመላልስበት፣ ወዲያውኑ ከዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያችን ውስጥ ፍላጎታችንን መሪ አድርገን ተፈጥሮን መልሰን መላልሰን የምንመለከትበትና አዲስ ቅርጽ የምናስይዝበትን መንገድ እና የምናጠናበት ዘዴ ነው። ቁሳዊ ባህል ቁሱን በመመልከት በአንድ ጊዜ የነበረን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ እሴት፣ ሀሳብ፣ አስተሳሰብ፣ አመለካከት ወዘተ ለማወቅ ያስችላል (Prown 1982:1)። በመሆኑም በአልከሶ መውሊድ ምዕመናኑ የሚጠቀሙበት ቁሳቁስ ምን ምን እንደ ሆነ ለመዳሰስ ሞክሬያለሁ።

ለ. **ስነቃል፡-** ስነቃል የአንድ ማህበረሰብ ባህል፣ ታሪክ፣ ወግ፣ ልማድ፣ ወዘተ በቃል አማካኝነት ከትውልድ ወደ ትውልድ ማሸጋገሪያ መንገድ ነው። ይህ የፎክሎር ዘርፍ አንድ ማህበረሰብ ያሳለፈውን ህይወት ዛሬ ላይ ሆኖ ለማስታወስ ከመርዳቱ ባሻገር አሁን ያለበትን ሁኔታ ለመጪው ትውልድ ቀርሶ የሚያቆይበት ስልት ነው። ስነቃል በመነገር፣ በመተረት፣ በመዜም፣ በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግ እና ልማድ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያ መንገድ እንደሆነ ፈቃደ (1991:11) እና ዘሪሁን (1992፣235) ያስገነዝባሉ። Finnegan (1972:25) ስነቃል

---

[16] http//www.faculty de gesu edu/mmagouli/folkloresyllabus.htm. 20/05/2014::

[17] የDorson አመዳደብ ከሌሎች ምሁራን አመዳደብ አንጻር የተሻለ ተቀባይነት ያገኘ ይመስላል። ምክንያቱም በርካታ መጻህፍት ፎክሎርን ሲከፋፍሉ መሰረት የሚያደርጉት የዶርሰንን የአመዳደብ ዘዴን ነው። ነገር ግን ሁሉንም የፎክሎር ዘርፎችን በእነዚህ አራት ምድቦች ማካተት አይቻልምና ምደበው ከአራት ይበልጣል ብለው የሚሞግቱ ምሁራን አሉ።

የስነጽሁፍ ዘርፍ ሆኖ ክዋኔ፣ተስላልፎ፣ እና ማህበራዊ አውድ የሚይዝ መለያ ባህርይ አለው ይላሉ፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ ስለ አልከሶ መስጂድ እና አልከስዬ ለተነገሩ አፈ ታሪኮች ወይም ሚቶች ትኩረት በመስጠት ተተንትኗል፡፡ አፈ ታሪክን ወይም ሚትን የተለያዩ ጸሀፊዎች አንድ እንደሆነ አድርገው ይጽፋሉ፡፡ በርግጥ ሁለቱን የሚያመሳስላቸው ነገር ቢኖርም ፍጹም አንድ ናቸው ማለት ግን አይቻልም፡፡

**ሐ. ሀገረሰባዊ ትጥበባት፡-** ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት አንድ ማህበረሰብ ለተለያየ ዓላማ በተለያየ ጊዜ የሚከውናቸውን እንደ ሀገረሰባዊ ሙዚቃ፣ ሀገረሰባዊ ድራማ፣ ሀገረሰባዊ ዳንስ ወዘተ የሚያጠቃልል ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ እነዚህ ትውን ጥበባት ማህበረሰቡ ማህበራዊ እና ሃይማኖታዊ ፋይዳ አላቸው ብሎ ስለሚከውናቸው ደስታን የመፍጠር አቅም እንዳላቸው ሁሉ በሀዘን ወቅትም ሀዘንን ለማጉላት ትልቅ ሚና ይጫወታሉ፡፡ ትውን ጥበባት አከዋወናቸው በጭፈራ፣ በሙዚቃ፣ በእንጉርጉሮ፣ ወዘተ መልክ ሊሆን ይችላል፡፡ እነዚህ ክዋኔዎች የሚከወኑት ማህበረሰብ ማንነት በሚያንጸበርቅ መልክ ነው፡፡ Bruno (2008፡254) ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት በስሩ ሀገረሰባዊ ዳንስን፣ ሀገረሰባዊ ዝማሬን(ሙዚቃን)፣ የማስመሰል ክዋኔን፣ የድራማዊ እንቅስቃሴዎችን እና የተለያዩ መሳሪያዎችን በመጠቀም የሚጫወቷቸውን ጨዋታዎች አካቶ የያዘ ጽንሰ ሀሳብ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Dorson (1972፡2-4) እና ፈቃደ (1991፡12) ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት የፎክሎር ዘርፍ ሆኖ ማህበረሰቡ የሚከውናቸው ሙዚቃን፣ ዳንስንና ድራማን ይመለከታል ይላሉ፡፡

**መ. ሀገረሰባዊ ልማድ፡-** ይህ የፎክሎር ዘርፍ በስሩ መዝናኛዎችን፣ ጨዋታዎችን፣ ክብረ በአላትን፣ ሀገረሰባዊ ሀይማኖቶችንና ሀገረሰባዊ መድሃኒቶችን አካቶ ይገኛል (Dorson 1972፡2-4):: ሀገረሰባዊ ልማድ በሰለጠነው ዓለም ግልጽ የሆነ መለኪያ ያልተቀመጠለት እና በሙከራ ያልተረጋገጠ በማህበረሰቡ አካባቢያዊ ዕውቀት፣ ክህሎትና ልምድ ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ ሀገረሰባዊ ልማዱ በሚተገበርበት አካባቢ ማህበረሰብ የእውነት መሰረት ሆነው የሚቆጠሩ እምነታዊ አባባሎችን እና ድርጊቶችን ያካተተ እንደሆነ Mullen (1969፡215) እና Motz (1998፡340-9) ያስረዳሉ፡፡ ስለ ክብረ በአላት የተለያዩ ምሁራን ከተለያየ እይታ አንጻር በመመልከት ተቀራራቢነት ያለው ትርጓሜ አቅርበዋል፡፡ ከነዚህም መካከል Sims and

Stephens (2005)፣ Finnegan (1992)፣ Bell (1997)፣ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ የሀገረሰባዊ ልምድ ዋነኛ ማጠንጠኛ ደግሞ ልማድ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡

ልማድ በፎክሎር ጥናት ውስጥ መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ይህንን መሰረታዊ ፅንሰ ሃሳብ በመተርጎም ሂደት Hield (2007)፣ እነ Sims (2005) እና ሌሎችም የፎክሎር ባለሙያዎች የተለያዩ ብያኔዎችን ሰጥተዋል፡፡ ለምሳሌ Hield (2007፣59) “Tradition has widely been associated with stability through processes of unchanging transmission and the preservation of authentic practices” ይላሉ፡፡ ይህ ማለት የአንድ ቡድን መለያ ሆነ ተጠብቆ በኖረ ተግባራዊ ልማድ ውስጥ በሚካሄድ የተስተላልፎ ሂደት ካለ ዘላቂነት ጋር የሚያያዝ ፅንሰ ሃሳብ ነው የሚል ትርጉም አለው፡፡ Sims and Stephens (2005፣254) ልማድ፣ አንድ ቡድን ያለውን ሀገር በቀል ዕውቀትና ዕውቀቱን ያገኘበት ኢመደበኛ መንገድ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ልምድ፣ ቡድኑ ባለው ዕውቀት ማንነቱን ለመገንባትና ለማጠናከር የሚያገለግለው ጉዳይ እንደሆነ ቡድኖች ልምድን የሚተገብሩት መርጠው በመውሰድ ነው ካሉ በኋላ ይህ በመሆኑ ልምዱ የማንነታቸው መለያ ይሆናል ይላሉ፡፡ እነSims አያይዘውም በአንድ በተወሰነ ቡድን ውስጥ አባላቱ መሳተፋቸው የልምዱ አካል የመሆን ስሜት ይፈጥርባቸዋል፡፡ በልምዱ አማካይነትም ማንነታቸው የሚፈጠር ብሎም የሚረጋገጥ ይሆናል፡፡ በዚህ የተነሳ ይህ ቡድን ከሌሎች ቡድኖች ተለይቶ ይታያል፡፡

የዚህ ጥናት ትኩረት በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ከሚጠናው ክብረ በዓል መካከል አንዱ በሆነው መውሊድ ላይ በመሆኑ በከበራው ሂደት ውስጥ የሚተገበሩ ልማዶችን ተንተኜያለሁ፡፡

## 4.1.2 የክብረ በአል ጽንሳባዊ ሀሳብ ምንነት

ክብረ በዓል በሀገረሰባዊ ልማድ ውስጥ ከሚጠኑ የፎክሎር ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ይህ የሀገረሰባዊ ልማድ ዘውግ ሃይማኖታዊ ወይም ባህላዊ ሊሆን ይችላል፡፡ ሀይማኖታዊም ሆነ ባህላዊው ክብረ በዓል አንድ ማህበረሰብ ከባህሉ፣ ከሀይማኖቱ እና ከእምነቱ ጋር በማይጋጭበት ሁኔታ በተወሰነ ጊዜ ተሰብስቦ የሚያከብረው ነው፡፡ Sims and Stephens (2005፡95) ክብረ በዓል አንድ ማህበረሰብ ደጋግሞ የሚያከብረው፣ የተለመደ እና ተደጋጋሚ ክዋኔ የሚስተዋልበት ዘወትር ከምናውቃቸው ድርጊቶች የተለየ እና በተለየ አጋጣሚ ብቅ የሚል እና የተለየ ዓላማ ያለው ክዋኔ ነው ይላሉ፡፡ እንደ Sims and Stephens

(2005፡110-115) አገላለጽ አንድ ማህበረሰብ ክብረ በአላትን የሚያከብረው ከወቅታዊ፣ ከማህበራዊ እና ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች ጋር በማያያዝ ነው፡፡ Rappaport (1999:22) ደግሞ ክብረ በአላት ከአለማዊ ይልቅ ሃይማኖታዊ ገጽታ እንዳላቸው በመግለጽ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ በተለያየ ጊዜ የሚከበር ክብረ በዓል የራሱ የሆነ የአከባበር ቅርጽ እና ይዘት እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እኚህ ምሁር አያይዘውም በከበራው ወቅት የሚከወኑ ጉዳዮች እርስ በእርስ ግንኙነት እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡

> Festival is an event, a social phenomenon, encountered in virtually all human cultures. The colorful variety and dramatic intensity of its dynamic choreographic and aesthetic aspects, the signs of deep meaning underlying them, its historical roots and the involvement of the o'natives" have always attracted the attention of casual visitors, have consumed travelers and men of letters alike. Since the last century, scholars from disciplines such as comparative religion, anthropology, sociology, and folklore have concerned themselves with the description, the analysis, and, more recently, the interpretation of festivities. (Falassi፣1987፣1).

ሲተረጎም

> ክብረ በዓል ክስተት ነው፡፡ እንዲሁም ማህበራዊ ሁነት ነው፡፡ ክብረ በዓል በማንኛውም የሰው ልጅ ባህል ውስጥ ከሞላጎደል ሊያጋጥም የሚችል ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ክብረ በዓል በህብረ ቀለማት የሚያንጸባርቅ እና ድራማዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ ክብረ በዓል የተለየ የአጨፋፋር ስልትና ስነ ውበታዊ ገጽታ እንዲሁም የጠበቀ ትርጉም እና ምልክት አለው፡፡ የእነዚህ ክንውኖች ታሪካዊ ዳራ እና የነባር ማህበረሰቦች የነቃ ተሳትፎ ሁሌም የጎብኚዎችን፣ የተጓዦችን እና የጸሀፊዎችን ቀልብ የሚስብ ነው፡፡ ካለፈው ክፍለ ዘመን ወዲህ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሚገኙ ምሁራን እንደ ንጽጽራዊ ሃይማኖት፣ ስነሰብ፣ ስነ ማህበረሰብ፣ እና ፎክሎር የክብረ በዓልን የተለያዩ ገጽታዎች በማብራራት፣ በመተንተን፣ እና በመተርጎመም እየተሳተፉ ይገኛሉ፡፡

ክብረ በዓል የማህበራዊ ግንኙነት የመፍጠር እና ሞራል የማጠናከር ተግባር እንዳለው Rappaport (1999:27) “አንድ ማህበረሰብ የሚያከብረው ክብረ በዓል በርካታ ጠቀሜታዎችን ሊያስገኝለት ይችላል፡፡ ለምሳሌ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ወዘተ ጠቀሜታዎችን በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ የማስገኘት እድል አለው፡፡”[18] ይላሉ፡፡

አንድ ክብረ በዓል ሲከበር በከበራው ወቅት በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በጥምረት ይስተናገዳሉ፡፡ ለምሳሌ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን መውሊድን ብንመለከት በዓሉ ሲከበር ከበራውን ለማድመቅ የተለያዩ መንዙማዎች ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ መንዙማዎች ደግሞ በተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና በተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎች ይታገዛሉ፡፡ መንዙማ አቅራቢዎች ደግሞ ለክወናቸው ድምቀት እንዲሰጥ ወይም ለአከዋወን በሚመቻቸው ሁኔታ በተለያዩ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ይዋባሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ በርካታ የፎክሎር ዘርፎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ክብረ በዓል የሁሉም የፎክሎር አይነቶች ውህድ ውጤት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Sims እና Stephens (2005፣95) ክብረ በዓል የራሱ የሆነ የአተገባበር ውቅር አለው ይላሉ፡፡ አወቃቀሩም በብዛት ቡድናዊ ነው፡፡ አብላጫ ክብረ በዓላት የበርካታ ፎክሎር አይነቶች እንደ ቃላዊ (አባባሎች፣ ግጥም ወይም ሙዚቃ)፣ የአካል እንቅስቃሴ፣ ዳንስ፣ ቁሳቁስ፣ ምግብ፣ አለባበስ፣ አጋጌጥ ወዘተ ውጤት እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡

ፎክሎርን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ምድብ እንደመደቡት ሁሉ ክበረ በዓልንም በተለያየ ምድብ መድበውት ይገኛል፡፡ ከነዚህ መካከል Bell (1997:90-95) እና የተለያዩ ምሁራን ክብረ በዓልን በሶስት፣ በአምስት፣ በስድስት እና በስምንት ጎራ መድበው እንደሚያጠኑት ይገልጻሉ፡፡ Bell (1997:239-240) አያይዘውም ዓመታዊ ክብረ በዓላት ማህበራዊ ትርጉም ከመስጠታቸው ባሻገር የጊዜ ሽግግርን (የዘመን መለወጥን)፣ ሌላ ቀን፣ ወር፣ ዘመን መምጣቱን ጭምር የሚያበስሩ ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡ ምሁራኑ ክብረ በዓልን በተለያየ ምድብ ሲመድቡ ከመደቡት መካከል የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነው አመታዊ እና

[18] ክብረ በአል ምን ምን ጠቀሜታ እንደሚያስገኝ ፈለቀ ታደለ ባህልና ልማት በኢትዮጵያ በሚል ርእስ በ2004 በፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ መድረክ ላይ ያቀረበቡትን ጥናታዊ ጽሁፍ ከገጽ 139-158 መመልከት ይቻላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የፈቃደ አዘዘ የስነቃል መምሪያ በሚለው መጽሀፍ ውስጥ የስነቃል ተግባራት የሚለውን መመልከት ይቻላል፡፡

የመታሰቢያ ክብረ በዓል የሚለው አንዱ ነው፡፡ አመታዊ እና የመታሰቢያ ክብረ በዓል በዋናነት የሚከበሩት በዓመት ውስጥ የተወሰነ ጊዜን መሰረት በማድረግ ነው፡፡

## 4.1.3 ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ለማክበር የሚደረግ ጉዞ

ሃይማታዊ ክብረ በዓል ለማበር የሚደረግ ጉዞ ማለት ምዕመናን ወይም ሃይማታዊ ክብረ በዓል አክባሪዎች ከአንድ ቦታ ተነስተው ክብረ በዓሉ ወደ ሚከበርበት ቦታ የሚያደርጉትን ጉዞ የሚመለከት ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ ክበረ በዓሉ ማህበራዊ ወይም በብዛት ሃይማኖታዊ ሊሆን ይችላል፡፡ “Pilgrimages have been defined as journeys undertaken to aspecific destination on a particular occasion for a spiritual purpose by groups of people who tend to bring offerings in exchange for receiving blessings. (Pankhurst 1994፣950) ይህ ማለት ለሃይማኖታዊ ክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ ሰዎች በቡድን በመሆን አንድን ሃይማኖታዊ የሆነን ክብረ በዓል ለማክበር ተጉዘው ከከበራው በረከትን ወይም ጸጋን ለማግኘት የሚያደርጉትን ሂደት ነው፡፡ ለአንድ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ በብዛት በዓላማችን በአሉ ሁሉም ሃይማኖቶች ውስጥ እንዳለ በመግለጽ የጉዞውም ዓላማ በብዛት ለሃይማኖታዊ ጉዳይ እንደሆነ Eckelman (1990፣89)፣ Kaplan (2010፣151)፣ York (2002፣137) እና Stoddard (1997፣56) ያስረዳሉ፡፡ Sims እና Stephens (2005፣95) ደግሞ የጉዞው አላማ ምንም ሆነ ምን ቡድናዊ ክዋኔ አለው ይላሉ፡፡

Pankhurst (1994፣934-935) ለሃይማኖታዊ ክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ አምስት አይነት መሰረታዊ ገጽታ እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ አንደኛ ለክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ አለ ማለት አንድ የሚከበር ክብረ በዓል አለ ማለት ነው፡፡ ሁለተኛ ከተለያዩ ቦታዎች የሚነሱ ተጓዦች የሚደርሱበት አንድ የጋራ የሆነ ቦታ አላቸው፡፡ የሚደርሱበት ቦታ የሃይማኖት መሪ የሚኖሩበት ስፍራ፣ የተቀደሰ ቦታ፣ተፍጥሯዊ የሆነ ቦታ፣ ተራራ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ሶስተኛ ተጓዦቹ የሚጓዙበት የተወሰነ ጊዜ እና ቀን አላቸው፡፡ አራተኛ ሁሉም ባይባልም አብላጫ ተጓዦች ወደ ስፍራው የሚሄዱት ምድራዊ ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ሳይሆን መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት ነው፡፡ አምስተኛ ተጓዦቹ በብዛት የሚጓዙት በተናጠል ሳይሆን በቡድን ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Stoddard (1997: 43) እና Gesler (1998: 536) ስለ አምስቱ የክብረ በዓል ጉዞ ገጽታ ከPankhurst ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሀሳብ አላቸው፡፡

ለሃይማታዊ ክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ (Pilgrimage) በኢትዮጵያ የተለመደ መሆኑን Pankhurst (1994፣933-34) ያስረዳሉ፡፡ Pankhurst አያይዘውም ይህ ርዕሰ ጉዳይ በኢትዮጵያ ብቻ የሚከናወን ሳይሆን አለማቀፋዊ ጉዳይ ነው ይላሉ፡፡ Lavine (1974፣185) እና Trimingham (1980፣87) የዚህ አይነት ጉዞ በኢትዮጵያ የቆየ ባህል መሆኑን በመግለጽ ተጓዦቹ የሀገር ውስጥ ዜጎች ከመሆናቸው በተጨማሪ ከሱዳን፣ ከኬንያ፣ ከሶማሌ እንዲሁም አልፎ አልፎ ከአውሮጳ እና ከኢሲያ የሚመጡ አሉ ይላሉ፡፡ ለምሳሌ Shimelis(1989፣25) ስለ ፈረቀሳ ክብረ በዓል ባተተበት ጥናታዊ ጽሁፍ በክብረ በዓሉ ቀን ስፍራውን ለመጎብኘት ምዕመናን ከሱዳን፣ ከጁቡቲ፣ ከኬኒያ ወዘተ እንደሚሄዱ ያስረዳል፡፡ Pankhurst (1994፣933) ደግሞ የሌላ ሀገር ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ እንደሚመጡ ሁሉ ኢትዮጵያዊያም ለዚህ ጉዳይ ወደ ሌላ ሀገር ይሄዳሉ ካሉ በኋላ ለምሳሌነት ሙስሊሞች ወደ መካ[19] ክርስትያኖች ወደ እየሩሳሌም የሚያደረጉትን ጉዞ ጠቅሰዋል፡፡

Pankhurst (1994፣944) እነዚህ ምዕመናን ክብረ በዓላቸውን ለማክበር የሚጓዙበት ስፍራ በአካባቢው አስተዳደር እውቅና የተሰጣቸው ወይም ሰዎች እንዲሰባበቡ ፈቃድ ይሰጣሉ ይላሉ፡፡ አያይዘውም  በአክሱም የሚከበር ክብረ በዓልን፣ በኦሮሚያ ክልል የሚከበረውን የአባ ሙዳ ስርዓትን፣ በቢሾፍቱ የሚከበረውን የኢሬቻ ስርዓትን እና የድሬ ሼኽና ሁሴንን መውሊድ በምሳሌነት በመጥቀስ ክብረ በዓልን ለማክበር የሚደረግ ጉዞ እና መንግስት የጠበቀ ቁርኝት አላቸው ይላሉ፡፡ Pankhurst (1994፣936-942) በኢትያጵያ ስላለው ለክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞን ሲያስረዱ የተለያየ ባህል፣ ቋንቋ፣ ጎሳ፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ሃይማኖት፣ ወዘተ ያላቸው ሰዎች በጋራ እንዲጓዙ ያደርጋል፡፡ እንዲሁም ከተጓዙም በኋላ የሄዱበትን ጉዳይ በጋራ እንደሚፈጽሙ ያስረዳሉ፡፡

[19] Pilgrimage to Mecca (Hajj):- The embarkation and return of pilgrims is a joyous annual celebration. Yoruba women used to welcome returning Muslims with waka songs (from Hausa wak'a, "song"), evincing Arab influence (melismatic, nasal, embellished), accompanied by metallic idiophones (seli) (Euba 1971, 177-78; Waterman 1990, 31); this form derived from Hausa women singers (Mack 2004, 133). Sakara praise-singers, accompanied by the molo or goje lutes, sakara clay drum, and other percussion, and ynthesizing Arab and localmusical styles, have performed at hajj celebrations in Yorubaland (Waterman 1990, 39). Returning pilgrims from the Khatmiyya tariqa in Sudan are expected to sponsor a special collective ritual (karama) in their honour (Sudan 1980). Nubian women sing call /response songs for pilgrims, accompanied by handclaps (Nubier 1980, 54). Among illiterate Hausa women pilgrims, composition and performance of personal hajj songs re-enacting their journey confers cultural capital (Cooper 1999).

ይህን ርዕሰ ጉዳይ በማስመልከት በኢትዮጵያ ያለውን ገጽታ Minako Ishihara የተባሉ ጸሀፊ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> The custom of visiting religious leaders considered as 'saints', whether dead or alive, is a common phenomenon found universally in the Muslim world. Although nowadays, criticized as heretical (*bid'a)*, by Islam reformists (locally called *Wahabiyas*) in Ethiopia, the pilgrimage custom remains central to the religious lives of Muslims (Ishihara 2009፣8).
>
> ሲተረጎም
>
> ጉብኝት(ዚያራ) በህይወት ያሉ ወይም የሌሉ ቅዱሳን የሚባሉ የሃይማኖት መሪዎችን የመጎብኘት (የመዘየር) ባህል በአጠቃላይ በመስሊሙ ዓለም የተለመደ ክንውን ነው፡፡ ምንም እንኳን ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ በሃይማኖት ላይ የተፈጠረ አዲስ ክስተት(ቢድዐ) ተደርጎ ቢተችም፡፡ ይህን ትችት የሚያቀርቡት በተለይም የኢስላማዊ ለውጥ አራማጆች በተለምዶ ወሀቢይ በመባል በሚታወቁት ዘንድ ነው፡፡ ይህ ጉዳይ በእነዚህ ሰዎች ቢተችም የሙስሊሞች የሃይማኖት ህይወት(አካል) ነው፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረበው ጥቅስ የምንረዳው አንድን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ለማክበር የሚደረግ ጉዞ በአለማችን ባሉ ሙስሊሞች ዘንድ እንደሚተገበር እና በአሁኑ ዘመን ይህን ጉዞ ከሃይማኖት አንጻር ክልክል ነው በማለት የሚቃወሙ ሰዎች ኢትዮጵያ ውስጥ መኖራቸውን ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Pankhurst (1994፣947) አንድን ክብረ በአል ለማክበር ከአንድ ቦታ ተንስቶ ሌላ ቦታ በመሄድ የሚደረግን ጉዞ ከሃይማኖት አንጻር አይፈቀድም የሚሉ ሰዎች እንዳሉ እና ቦታ ከሄዱ ምዕመናን መካከልም በአከባበር ሁኔታ ልዩነት ያላቸው ሰዎች መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡

እነዚህ ተጓዦች የሚጓዙት የተለያየ ዓላማ አንግበው ዓላማቸውን ከግብ ለማደረስ በማሰብ ነው፡፡ Pankhurst (1994፣947-950) ምዕመናን አንድ ክብረ በዓል የሚከበርበት ቦታ የሚጓዙበት ዓላማ "ሃይማኖታዊ ጉዳይ፣ ቡድናዊነት ወይም አንድነትን ለመግለጽ፣ ከተለያዩ በሽታዎች ለመፈወስ፣ ስለት ለማስገባት፣ ለንግድ ጉዳይ እና ለመዝናናት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

በፈረቀሳ ክብረ በዓል ጥናት ያካሄደው ገመቹ (2012፣140) እና Østebø (2009: 464). የPankhurst ሀሳብ ይጋራሉ። የተለያዩ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ወደ ሚከበርበት ቦታ የሚጓዙ ሰዎች ወደ ስፍራው የሚሄዱት ለጉብኝት፣ ለመዝናናት፣ ለንግድ፣ ለከበራ ወዘተ ነው።

### 4.1.4 የአውድ ጽንሰ ሀሳባዊ ምንነት

የዚህ ጽንሰ ሀሳብ አቀንቃኞች በዋናነት (Bascom 1954) እና (Ben Amos 1993) ሲሆኑ አውዳዊ ጽንሰ ሀሳብ ዋነኛ ትኩረት አንድ የፎክሎር ዘውግ የተከናወነበትን አውድ ማጉላት እንደሆነ ያስረዳሉ። ማንኛውም ክዋኔ ሲተነተን የክዋኔው ዓውድ መገለጽ እንዳለበት Okpewho (1992:10)፣ Ben Amos (1993:1) እና ፈቃደ (1991:37) ያስገነዝባሉ። እንደ Jackson (1986፡4) አገላለጽ ደግሞ አውድ በስነሰብ (Anthropology) ጥናት ውስጥ ላሉ ሁሉም ተመራማሪዎች ወሳኝ ጉዳይ ነው ካሉ በኋላ ለሁሉም ግን አውድ ወሳኝ ቢሆንም ለሁሉም ተመራማሪዎች በተመሳሳይ መንገድ ያገለግላል ማለት አይደለም ይላሉ። እንዲሁም Sims and Stephens (2005፡137) አውድ የፎክሎር አንድ ቅንጣት የሚከወንበት ውስን ማህበራዊ ሁነት በመሆኑ ለፎክሎር ጥናት ሁነኛ መንገድ መሆኑን ይገልጻሉ። በፎክሎር ጥናት ፎክሎራዊ አሀድን ብቻ መመልከት ትርጉም የለውም። ምክንያቱም ከአውድ ውጭየሆነ ክዋኔ የለምና። በመሆኑም ትክክለኛው አካሄድ ፎክሎርን በማህበረሰቡ ውስጥ በመመልከት መመርመር የተፈለገውን ጉዳይ ከባህሉ አውድ፣ ከማህበረሰቡ አውድ እና ከሁኔታ አውድ አንፃር መመልከት ወይም እነዚህን ጉዳዮች ከግምት ውስጥ በማስገባት ማጥናት እንዳለብን Ben Amos (1993፡210) ይመክራሉ። ይህ ማለት የፎክሎር ጥናት ሊከተል ከሚገባቸው መንገዶች መካከል አወዳዊ ጽንሰ ሀሳብ አንዱ ነው።

እንደ Dorson (1972፣215) አገላለጽ የአውዳዊ ጽንሰ ሀሳብ ዋና ትኩረት ክዋኔን ማዕከል ያደረጉ ሁሉን አቀፍ መረጃዎች ከባህላዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች አኳያ የከዋኙን አከዋወን ሁኔታ ከጊዜና ቦታ አንጻር የሚገለጽበት መንገድ ነው። በዘመናዊ አጠቃቀም አውድ ማለት በስፋት ሲታይ ስለ አንድ ድርጊት ክንውን የሚገልጽ ሲሆን በፎክሎር ጥናት ውስጥ ደግሞ ፎክሎር የሚከወንበትን ሁኔታ የሚመለከት መሆኑን Ben-Amos (2006፣236) እና Goldstein (2004፣125) በመግለጽ የአውድን ብያኔ ሰፊ አድርገውታል።

ለፎክሎር ጥናት ክዋኔ ብቻ ሳይሆን የክዋኔው አውድ፣ (*context)* ከዋኙና (performer) ተሳታፊዎቹ (audiences) ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው Green (1997፣254) እና Sims & Stephens (2005፣58) ያስረዳሉ:: Green አያይዘው ክዋኔው ብቻም ሳይሆን ማህበረሰቡ ስለ ክዋኔው ምንነትና ፋይዳ የሚሰጠውን ፍቺ ምን እንደሆነ መገንዘብም አስፈላጊ እንደሆነ አጠንክረው ያስረዳሉ:: Sims & Stephens (2005፣138) አንድን የፎክሎር ነገረ ይዘት (text) ስናጠና ከአውዱ ነጥለን ለቡድኑ የሚሠጠውን ጥቅም በቀላሉ ማስረዳት አዳጋች ነው:: ነገረ ይዘት ከሰፊ የክዋኔ አውድ ላይ ሲከወን መመልከትና መገንዘብን አስፈላጊ ነው:: አንድ የፎክሎር ነገረ ይዘት ከሰፊው የፎክሎር ባህር ውስጥ አንድ ቅንጣት እንደመሆኑ ያ ቅንጣት በፎክሎሩ ቁሶች ውስጥ ምን ማለት እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም የሚያውቁትና መግለፅ የሚችሉት የፎክሎር ቡድኑ አባላት ናቸው:: በመሆኑም ፎክሎረኛው ነገረ ይዘቱን ብቻውን ይዞ ለትንታኔ ከመነሳቱ በፊት በክዋኔ አውዳቸው ላይ በጥንቃቄ መመልከትና የቡድን አባላቱን ስሜት መገንዘብ እና መረዳት ወሰኝ እንደሆነ ያስረዳሉ::

አውድ ሲባል አንድ ጉዳይ ሲከወን በቦታው የነበሩ እና በዙሪያው ያለውን በሙሉ ያካትታል:: ለምሳሌ አንድ የቅኔ ዘረፋን ብንመልከት አውዱን፣ ከዋኙን፣ ታዳሚውን፣ ከዋኙ የሚገለገልባቸው ቁሶችን፣ በከዋኝ እና በታዳሚያን መካከል ያለው መስተጋብር፣ ቅኔው የሚዘረፍበት ቦታና ጊዜ፣ በአካባቢው ያሉ ጉዳዮችን ወዘተ በሙሉ የሚያጠቃልል ሀሳብ እንደሆነ ፈቃደ (1991፡25) ያስረዳሉ:: Ben-Amos (1993፡210-211) አንድ አውዳዊ አጥኚ የሰበሰበውን መረጃ ከአውድ ውጭ ለመተንተን ቢሞክር ችግር ሊገጥመው እንደሚችል አጽንኦት ሰጥተው ይመክራሉ:: እኚህ ምሁር (1993፡210-212) አያይዘውም ከመስክ የተሰበሰበውን መረጃ በጥሬው ከመተንተን ባሻገር አውዳዊ ትንታኔ ወይም ትርጓሜ ቢሰጥ የተሻለ መሆኑን ያስገነዝባሉ:: Alan-McKee (2003፡65) በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ሀሳብ ይጋሩታል::

በዚህ ጥናት ለአውድ ትኩረት የተሰጠ ሲሆን በአልከሶ መውሊድ ከበራ ወቅት ያለው አጠቃላይ ድባብ አውዱን ባለቀቀ ሁኔታ መረጃ ተሰብስቦ ተተንትኗል:: ለምሳሌ በበዓሉ ቀን የመቃብር ቦታ ሲዘየር በመመልከት የአዘያየር ሁኔታውን አውዱን በጠበቀ ሁኔታ ቀርቧል:: በየኸለዋዎቹ ምዕመናን ለቆይታ ጊዜያቸው የሚሆን አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ገንዘብ በፈቃደኛነት ያዋጣሉ:: በዚህ ጊዜ በቦታው የሚገኙ ሽማግሌዎች ዱኣ ስያደርጉ የዱኣ አደራረግ ስርዓት አውዱን በጠበቀ ሁኔታ ቀርቧል:: እንዲሁም የበዓሉ ታዳሚዎች በየዳሳቸው

ተሰብስበው ጫት ሲቅሙ፣ ድቤ ሲመቱ፣ ጡሩንባ ሲነፉ፣ መንዙማ ሲሉ ወዘተ በአጠቃላይ አውዱን በጠበቀ ሁኔታ በምልከታ ተሰብስቦ ተተንትኗል፡፡

### 4.1.5 የመውሊድ በዓል ምንነት እና አጀማመር በዓለም

በክብረ በዓላት ስር ከሚጠኑ ጉዳዮች መካከል የዚህ ጥናት ዋና ትኩረት የሆነው መውሊድ አንዱ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል መውሊድ ማለት ምን ማለት ነው፣ የመውሊድ መከበር ዓላማው ምንድነው፣ የአከባበር ይዘቱ ምን ይመስላል፣ መውሊድ በዓላማችን እንዴት መከበር ጀመረ፣ እነ ማን ጀመሩት፣ በኢትዮጵያስ እንዴት ተጀመረ፣ በመውሊድ ከበራ ላይ አስተዋጽኦ ያበረከቱት እነ ማን ናቸው፣ እንዲሁም በመውሊድ ከበራ ዙርያ ያለው ውዝግብ ምንድን ነው፣ የውዝግቡ ምክንያትስ የሚሉትን ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

መውሊድ የነብዩ ሙሀመድን የልደት ቀን ምክንያት በማድረግ በየአመቱ ረቢኡል አወል በተባለው ወር የሚከበር ክብረ በዓል ነው፡፡ መውሊድን Encyclopedia Aethiopica (ቅጽ 3 ገጽ 2007፡ 878-880) መውሊድ በሙስሊሞች ዘንድ የነብዩ ሙሀመድ[20] መወለድን ምክንያት በማድረግ ለመታሰቢያነት የሚከበር በዓል ነው ይላል፡፡ Encyclopedia Britannica (ቅጽ 4 ገጽ 2008፡ 878) ደግሞ “Mawlid, also spelled Mawlūd, or Mīlād, in Islām, the birthday of a holy figure, especially the birthday of the Prophet Muḥammad (Mawlid an-Nabī)” የሚል ትርጓሜ ሰጥቶታል፡፡ ይህ ማለት መውሊድ ማለት የመወለጃ ቀን ማለት ሲሆን በዋናነት የእስልምና ተምሳሌት የሆኑትን ነብዩ ሙሀመድን ይመለከታል፡፡ Bronislav(2008፣135) J. W. McPherson(1998፣65.)ን በመጥቀስ “It is religious and local festival commemorated in honour of a saint of certain eminence.” ይላሉ፡፡ ይህ ማለት መውሊድ ሃይማኖታዊ እና አንድ ታዋቂ ወልይን መሰረት በማድረግ አካባቢያዊ በሆነ ሁኔታ የሚከበር ክብረ በዓል ነው ማለት ይቻላል፡፡

---

[20] ከስም አገላለጽ አንጻር ሙሀመድ እና መሀመድ ብለው የሚጽፉ እና የሚጠሩ ሰዎች አሉ፡፡ እንዲሁም በእንግሊዘኛ Muhammed እና Mohammad ብለው የምጽፉም አሉ፡፡ በዚህ ጽሁፍ እነዚህን ስሞች የምጽፈው ጸሀፊው በሚጠቀምበት የስም አጠራ ሁኔታ ነው፡፡ በሌላ አገላለጽ መሀመድ ያለውን መሀመድ እንዲሁም ሙሀመድ የሚለውን ሙሀመድ እያልኩ ጽፌያለሁ፡፡ የመረጃ አቀባዮችንም ስም ከዚህ በላይ በገለጽኩት ሁኔታ ተጠቅሜያለሁ፡፡

Encyclopedia Aethiopica (ቅጽ 4፡2007፣420) "--- the origin of the mawilid, the mawild which find first celebrated in Arbela 604 by al-malik Muzaffar." በማለት መውሊድ በአለማችን በ604 ዓ.ሂ Muzaffar በተባለ ግለሰብ አማካይነት መከበር እንደተጀመረ ያስረዳል። በሌላ በኩል ደግሞ በዓሉ መከበር የጀመረው ነብዩ ከሞቱ ከሶስት ትውልድ በኋላ እንደሆነ የሚያሳዩ መረጃዎች አሉ። ለምሳሌ Abu al-'Abbas Ahmad al-Azafi (1162-1236) እ.ኤ.አ በሰሜናዊ የመካ ክፍል መውሊድ እንዲከበር አድርጓል። እኚህ ግለሰብ በህይወት እያሉ **"Kitab ad-Durar al-Munazzam fi 'l-Mawlid al Mu'azzam"** የሚል በመውሊድ ዙሪያ የሚያወራ ኪታብ መጻፍ ቢጀምሩም ሳይጨርሱት በመሞታቸው ወንድ ልጃቸው Abu'l-Qasim ሊጨርሰው ችሏል።[21] Encyclopedia Aethiopica (ቅጽ 3፡ 2007፣ 878) ደግሞ መውሊድ ለመጀመሪያ ጊዜ መከበር የጀመረው al-malik Muzaffar[22] በተባለ ግለሰብ እንደሆነ እና በዋናነት የሚከበረው ነብዩ ሙሀመድ ወደ እዚች አለም የመጡበትን ዕለት ምክንያት በማድረግ ነው ይላል። Mustafa and Haggai (2005፡3) ደግሞ መውሊድ ይፋ በሆነ ሁኔታ (formal manner) መከበር የጀመረው በ13ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ያስረዳሉ።

መውሊድ መከበር የጀመረው ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነው ቢሉም መውሊድ ነብዩ በህይወት በነበሩበት ወቅት ይከበር እንደነበር የሚያሳዩ መረጃዎች መኖራቸውን ሀሰን (2008፣37) ያስረዳሉ። ለምሳሌ ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ ነብዩ ሰኞ ቀንን ለምን እንደሚጾሙ ሲጠየቁ "ሰኞ ቀን የተወለድኩባት እና መልዕክተኛ የሆንኩባት ቀን ስለሆነች ነው" ብለዋል። ከዚህ ሀዲስ መረዳት የሚቻለው ነብዩ ለተወለዱባት ቀን ልዩ ትኩረት እንደሰጡ እና ቀኑን በኢባዳ ማሳለፋቸውን ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ ቡኻሪ እና ሙስሊም በታሪክ በአንድ ጊዜ አላህ ችሮታውን ለማሳየት የፈጠረውን ጉዳይ (ታሪክ) በየጊዜው ማስታወስ እና ማወደስ ተገቢ እንደሆነ ነብዩ መናገራቸውን እና የአፈጻጸም ሁኔታውም በጾም እና በሌሎችም ኢባዳዎች ሊሆን እንደሚችል ዘግበዋል።

---

[21] http://daralhadith.wordpress.com/2009/03/08/the-mawlid-is-an-eid-and-the-malikis-zarruq-ibn-abbadand-ibn-ashir/and WWW.qsep.com>: accessed on November 2015.

[22] Dr. Hafiz(2011፣3) ስለ ሙዘፈር "Sultan Muzaffar of Irbil (d. 630/1232) lived in the time of Salah al-Din Ayyubi. He was a pure-hearted, brave and wise ruler. He was one of the first to turn the Mawlid into a formal event." ይላል።

ከዚህ በተጨማሪ ኢብን ጀቢር በ540 ሂጅሪ በጻፉት ጽሁፍ በረቢዐል አወል ወር ዘውትር ሰኞ የነብዩ ቤት ይከፈትና ታላላቅ ሰዎች ውስጡ በመግባት ከበረካው ይቋደሱ እንደነበር ሀሰን ያስረዳሉ፡፡ እንደ Imam Ibn Kasir አገላለጽ መውሊድ በየአመቱ ኦፊሴላዊ ሆኖ እንዲከበር ያደረገው የኤርቢሉ አስተዳደር የነበረው እና የታላቁ ሙጃሂድ የሶለሀዲን የእህት ባል የነበረው Muzaffar ነው፡፡ Muzaffar ብዙ መልካም ስራዎችን የሰራ እና ለመውሊድ ከፍተኛ ገንዘብ በመመደብ የሚያከብር ታላቅ ዓሊም እና ንጉስ ነበር፡፡ ስለዚህ ከዚህና መሰል መረጃዎች መረዳት የሚቻለው መውሊድ መከበር የጀመረው በነብዩ በራሳቸው እንደሆነ እና ህዝባዊ ወይም ኦፊሴላዊ በዓል ሆኖ በየአመቱ እንዲከበር በማድረጉ ዘንድ Muzaffar ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ነው፡፡

ይህ የሚያሳየው መውሊድ በትክክል መቼ ተጀመረ በሚለው ዙርያ ውዝግብ መኖሩን ነው፡፡ ነብዩ በህይወት እያሉ መውሊድን ያከብሩ ነበር ከሚለው ውጭመውሊድ በሶስት ዋና ዋና አካላት እና በሶስት የተለያዩ ዘመናት መከበር እንደተጀመረ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እነዚህ ሶስት አካላትን Muhammad(2012፣2) እና መሀመድ(2008፣61) በሚከተለው ሁኔታ ዘርዝረዋቸዋል፡፡

1. መውሊድ የተጀመረው ግብጽ ውስጥ የጀመሩትም "ፋጢሚያህ" ሺዐዎች ናቸው፡፡ "ፋጢሚያህ" ግብጽ ላይ የነገሱት 357 ዓ.ሂ ነው፡፡
2. መውሊድ በሼኽ ዑመር ኢብኑ ሙሀመድ አልመላ(571ዓ.ሂ) መውሱል ኢራቅ እንደተጀመረ እና ሙዛፈር ከእሱ እንደወሰደው ይነገራል፡፡
3. በንጉስ አልሙዛፈር አቡ ሰዒድ ኩኩቡሪ(630ዓ.ሂ) አርቢል ላይ ነው የተጀመረው የሚሉ አሉ፡፡

ከዚህ መረጃ የምንረዳው መውሊድ በትክክል በዚህ ጊዜ እና ቦታ ተጀመረ የሚለው ጉዳይ ሁሉንም ሰዎች እማያስማማ መሆኑን ነው፡፡ መሀመድ(2008፣61) ስለ መውሊድ አጀማመር የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ----በአጀማመሩ ጊዜ ቀደም ተከተል ስንመለከት ፋጢሚዮች ግብጽ ላይ እንደጀመሩት ግልጽ መረጃ አለ፡፡ ቀጥሎ ደግሞ ሸይኽ ዑመር አልመላ መውሱል ላይ እንደጀመረው እና ድግሱም ላይ ንጉሳን ይካፈሉ እንደነበር አቡ ሻማል ገልጸዋል፡፡ ቀጥሎ ከሳቸው በመኮረጅ በንጉስ ሙዛፈር ኢርቢል

ላይ ጀምሮታል። ስለዚህ በመረጃ ለሚያምን ሰው የመውሊድ ጠንሳሾች ሺዐዎች ናቸው።

ነገር ግን ሊዚህ ጥናት የሚሆኑ የተለያዩ መጻህፍትን ሳነብ ግን መውሊድ ለመጀመሪያ ጊዜ ህዝባዊ በሆነ ሁኔታ ማክበር የጀመረው ሙዛፈር እንደሆነ ያሳያሉ። ስለዚህ መውሊድ በትክክል መቼ መከበር እንደጀመረ የሚያሳዩ የተለያዩ መረጃዎች አሉ። ምክንያቱም ስለ መውሊድ የተለያዩ ጽሁፎችን የጻፉ ምሁራን የተለያየ ዘመን ይጠቅሳሉ። በመውሊድ ላይ ጥናት ያካሄዱ አጥኚዎች በዓሉ ነብዩ በነበሩበት ዘመን ይከበር ነበር ሲሉ ሌሎች ደግሞ እሳቸው ከሞቱ በኋላ ነው የተጀመረው ይላሉ። እንደ ያህያ (1413፣10 ዓ.ሂ) አገላለጽ ይህ የዘመን ውዝግብ የሚስተዋለው በመውሊድ መጀመሪያ ጊዜ ብቻ ሳይሆን በነብዩ የተወለዱበት ቀንም ጭምር ነው። ነብዩ ሙሀመድ የተወለዱት በ"ረቢኡል አወል" ወር በገባ በ2ኛው፣ በ8ኛው፣ በ9ኛው፣ በ12ኛው እና በ17ኛው ቀን እንደተወለዱ መረጃዎች ያሳያሉ። የተወሰኑ መረጃዎች ደግሞ ነብዩ የተወለዱትም የሞቱትም በተመሳሳይ ሰኞ ቀን እንደሆነ ያሳያሉ (ያህያ 1413 ዓ.ሂ፣15)።

የነብዩ ሙሀመድ የልደት ቀን ህዝባዊ ወይም ኦፊሴላዊ ሆኖ መከበር የጀመረው በ13ኛው ክፍለ ዘመን ግብጽ ውስጥ እንደሆነ መረጃዎች እንደሚያሳዩ ቀደም ብለን ተመልክተናል። መሰረቱን የጣለው ግብጽ ውስጥ ቢሆንም በአጭር ጊዜ ውስጥ በመላው የሙስሊም ሀገራት መሰራጨት ችሏል (Gori 2010: 51) እና (Schussman 1998:216)። መውሊድ በነብዩ ዘመን ይከበር የነበረው በጾም ሲሆን እሳቸው ከሞቱ ከሶስት ትውልድ በኋላ በተለያየ ክብረ በዓላዊ ቅርጽ ባለው ሁኔታ መከበር ጀምሯል (Kabha and Erlich 2005፡4)። እነ Kabha አያይዘውም በዓሉ በሚከበርበት ውቅት የእለት ጉሮሯቸውን መሸፈን የማይችሉ ሰዎችን ሰብስቦ ከማብላትና ከማጠጣት በተጨማሪ ቁርአን መቅራት እና ነብዮ ሙሀመድን በተለያየ መንገድ ማወደስ የተለመደ እንደነበር ያብራራሉ። የመውሊድ በዓል በይፋ እንዲከበር ያደረገው Muzaffar በዓሉ በሚከበርበት ወቅት 5000 በጎችን፣ 10000 ዶሮዎችን፣ እና 1000 ጣፋጭ ኬኮችን ለታዳሚዎች እንዲቀርብ ያደርግ እንደነበር የአይን እማኞች መናገራቸውን Shawana A. Aziz (1982፡25) ጽፈዋል። እንደ Gori (2010፡ 51-52) አገላለጽ በዓሉ በዋናነት ይከበር የነበረው ግጥሞችን በማንበብ እና መንዙማዎችን በማቅረብ ነበር።

መውሊድ የሚከበረው በአመት አንድ ጊዜ በረበኡል አወል በ12ኛው ቀን ብቻ ሳይሆን በየቀኑ፣ በየወሩ እንዲሁም በየመስጂዱ ነው ካለ በኂላ መውሊድን ማክበር ሙስሊሙ ማህበረሰብ ስለ እስልምና እንዲያውቅ ከማስቻሉ ባለፈ የሸሪኣ ህግጋትን በልቡ እንዲጽፍ እድል ይፈጥርለታል ይላል፡፡ ይህ ድረ ገጽ መውሊድ መከበሩ ምን ፋይዳ እንዳለው እና የአከባበር ስርአቱ ምን እንደሚመስል የሚከተለውን ይላል፡፡[23]

> Mawlid gatherings are an effective and efficient means of for the purpose of calling people to Islam and educate children, that these meetings give a golden opportunity that must not be lost, for every scholar and daia to teach and reind the Nation of the Prophet of his good character, his way of worshipping, and his way of treating people, This is a way to make children love and remember their Prophet, by giving them food and juice and gifts to make them happy.

ሲተረጎም

> ለመውሊድ ክብረ በዓል የሚደረግ መሰባሰብ(ስብስብ) ሰዎችን ወደ እስልምና ለመጥራት እና ልጆችን እስልምናን እንደማሩ ለማድረግ ሁነኛ መንገድ(ዘዴ) ነው፡፡ ይህ መሰባሰብ(አጋጣሚ) ለማንኛውም የሃይማኖት ምሁር እና ሰባኪ ሊታለፍ የማይገባው ወርቃማ አጋጣሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ዓላማው የነብዩን መልካም ባህሪያት፣ የአምልኮ መንገዶች፣ እና ሰዎችን የሚያስተናግዱበትን መንገድ በማስተማር በማህበረሰቡ ዘንድ እንዲሰርጽ ማድረግ ነው፡፡ በዚህም መንገድ ልጆች ነብዩን እንዲወዱ እና እንዲያስታውሱ ያስችላቸዋል፡፡ ይህም የሚደረገው ለልጆች ምግቦችን እና የተለያዩ ጣፋጭ መጠጦችን እና ስጦታዎችን በመስጠት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ልጆችን ደስተኛ ያደርጋቸዋል፡፡

ይህ ጥቅስ መውሊድ አክባሪ ምዕመናን መውሊድ ለማክበር በመሰባሰብ ሰዎችን ወደ እስልምና ይጠራሉ፤ ልጆችን እስላማዊ ትምህርት ያስተምራሉ፤ እንዲሁም የነብዩ

[23] http//sunnah.org./ibadaat/mawlid.ttm Acceded 10/05/2015

ሙሀመድን መልካም ስራ ወይም ባህርይ ለልጆች በመንገር ለእሳቸው ፍቅር እንዲኖራቸው እና እንዲያስታውሷቸው ያደርጋሉ የሚል መልዕክት ያዘለ ነው።

Muhammed Ibnl Alewi (2010፣39) መውሊድ በሚከበርበት ወቅት የታላቁ ነብይ ገድል (ሲራ) በሰፊው ይብራራል፣ የነብዩን ትልቅነት፣ ጅብድ እና ዲንን የሚያወሱ የተለያዩ ምክሮች በታላላቅ ዐሊሞች ይሰጣል፤ እንዲሁም ከእለቱ ጋር የሚሄዱ የቁርኣን መልዕክቶች ይተላለፋሉ ይላሉ። Muhammed (2010፣13) አያይዘውም በማንኛውም ወቅት እና ቦታ የነብዩን መውሊድ እንደሚያስቡና በእሳቸው መወለድ እንደሚደሰቱ ገልጸው ደስታቸው ነብዩ በተወለዱበት ሰኞ ቀን እና በረቢዐል አወል ወር እንደሚጨምር ያስረዳሉ።

በShaikh Saleh ibn Fawzan al-Fawzan “The ruling concerning Mawlid an-nabawi” በሚል ርእስ ተጽፎ በ Shawana Abdul Aziz በ1982 የተተረጎመው ኪታብ (መጽሀፍ) የሚከተለውን ይላል። መውሊድ በአሁኑ ጊዜ አለማቀፋዊ በዓል በመሆኑ ከ47 ሀገራት በላይ ህዝባዊ በዓል ሆኖ ይከበራል። በመካከለኛው ምስራቅ ውስጥ ከሚገኙ አስራ አራት ሀገራት መካከል አስራ አንዱ በዓሉን ሲያከብሩ ሳውዲአረቢያ፣ ኳታር እና የመን በዓሉን አያከብሩም። ባህሬን፣ ኢራን፣ ጆርዳን፣ ኩዌት፣ ሊባኖን፣ ኦማን፣ ፊሊስጤም፣ ሶሪያ፣ ዩናይትድ አረብ ኢምሬት፣ በዓሉን የሚያከብሩ ናቸው። ከኢሺያ አፍጋኒስታን፣ ባንጊላዲሽ፣ ብሩኒያ፣ ህንድ፣ ኢንዶኒዥያ፣ ፓኪስታን፣ ማሌዥያ፣ ሲሪላንካ፣ ኡዝቤክስታን፣ ፊጂ፣ እና ጉያና፣ በዓሉን በዋናት የሚያከብሩ ሀገራት ናቸው። ጸሀፊው(1982:30-31) አያይዘውም አብላጫ ህዝባቸው ሙስሊም ያልሆኑ እንደ ህንድ፣ ሲሪላንካ፣ ፊጂ፣ ጉያና፣ ታንዛኒያ፣ ማሊ፣ ወዘተ ሀገሮች የመውሊድ በዓልን ህዝባዊ በዓል በማድረግ ከሚያከብሩት መካከል ይገኙበታል በማለት አብራርተዋል።

### 4.1.6 የመውሊድ አጀማመር እና አከባበር በአፍሪካ

መውሊድ በአፍሪካ መቼ ተጀመረ ብለን ድርሳናትን ስንዳስስ ግንባር ቀደሟ ሀገር ግብጽ ሆና እናገኛታለን። መውሊድ የተጀመረው ግብጽ ውስጥ የጀመሩትም “ፋጢሚያህ” ሺዐዎች እንደሆኑ እና “ፋጢሚያህ” ግብጽ ላይ የነገሱት 357 ዓ.ሂ እንደሆነ ጥናቶች ያስረዳሉ። ከሚለው መረጃ አንጻር በአፍሪካ ታሪክ መውሊድ ለመጀመሪያ ጊዜ መከበር የጀመረው ግብጽ ውስጥ ነው ማለት ይቻላል።

> In Islamic history, the earliest celebrations conducted on the occasion of the Prophet's birthday are encountered in the era of Fatimid Empire (910-1171), mostly in Egypt. Associated with the rise of wealth under their dominance over both Egypt and North Africa Shi'ite Fatimid Caliphate began to place a great emphasis on religious festivals. (Erman, 2016፣12).

ከዚህ ጥቅስ መውሊድ መከበር የጀመረው በፋጢማዊያን አመራር ዘመን ግብጽ ውስጥ እንደሆነ ነው፡፡ በተለይም መውሊዱ እንዲከበር ያደረጉት ሺዐ ሙስሊሞች እንደሆኑ ያስረዳል፡፡ የሺዐ ሙስሊሞች በወቅቱ የነብዩ መሀመድን ብቻ ሳይሆን የቤተሰቦቻቸውንም በተለይም የአሊን፣ የፋጡማን፣ የሁሴን እና የሀሰንን መውሊድ ያከብሩ ነበር፡፡ በወቅቱ እነዚህ የሺዐ ሙስሊሞች መውሊድን በአላዘር መስጂድ ውስጥ ከፍተኛ የሃይማኖት እና የመንግስት አመራሮች በተገኙበት በተለያየ ሁኔታ ያከብሩ እንደነበረ እና የዘር ግንዳቸውን ከነብዩ መሀመድ እንደሚገናኝ የሚያሳይ የዘር ቆጠራ ያካሄዱ እንደነብ Kaptein(1998,23-34) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Bronislav(2008፣133) የተሰኙ አጥኚ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እስካሁን ድረስ የሱፊ ሙስሊሞች ከሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች በመሰባሰብ መውሊድን እንደሚያከብሩ ያስረዳሉ፡፡

ግብጽ ውስጥ መውሊድ መከበር እንዲጀምር ካደረጉ ጉዳዮች መካከል ፖለቲካዊ ጉዳይ እንደሆነ "Thus it can be claimed that despite of their religious content, from the beginning of eleventh century, mawlid ceremonies are instrumentalized with the aim of providing political legitimacy" በማለት ያስረዳሉ፡፡ Damas and Fuad ደግሞ "The Legal framework of Mosque building and Muslim religious affairs in Egypt: towards a strengthening of State control." በማለት ግብጽ ውስጥ መስጂዶች ይቋቋሙ የነበረው ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች በተጨማሪ ለአለማዊ ጉዳይም ጭምር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

ከግብጽ በመቀጠል በአፍሪካ ታሪክ መውሊድን ማክበር የጀመሩት የሰሜን አፍሪካ ሀገራት እንደሆኑ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከነዚህ የሰሜን አፍሪካ ሀገራት መካከል ሊቢያ ግንባር ቀደም ሀገር እንደሆነች "According to an official document, Ottoman government request

reports from the governor of Tripoli province about whether or not the city is safe, certain sufi groups run wild and disturb the other people." በማለት የሊቢያ ሱፊ ሙስሊሞች እንደጀመሩት Süleyman(2005፣13-15) ያስረዳሉ፡፡ ከምዕራብ አፍሪካዊያን በመቀጠል የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት የሆኑት የመን እና ታጋንይካ የአሁኗ ታዘኒያ ከምስራቅ አፍሪካ ሀገራት ቀድመው እንደጀመሩት Philo (2011፣12)ያስረዳሉ፡፡

Shawana(1998፣150) በአፍሪቃ ከሚገኙ ሀገራት መካከል ሀያ አራቱ በዓሉን ህዝባዊ በዓል አድርገው እንደሚያከብሩት ያስረዳሉ፡፡ እነሱም አልጄሪያ፣ ቢኒን፣ ቡርኪናፋሶ፣ ካሜሮን፣ ኮሞሮስ፣ አይቬሪኮስት፣ ጅቡቲ፣ ግብጽ፣ ኤርትራ፣ ኢትዮጵያ፣ ጋምቢያ፣ ጊኒ፣ ሊቢያ፣ ማሊ፣ ሞሪታኒያ፣ ሞሮኮ፣ ኒጀር፣ ናጄሪያ፣ ሴነጋል፣ ሴራሊዮን፣ ሱዳን፣ ታንዛኒያ፣ ቱኒዚያ እና ቶጎ ናቸው፡፡

## 4.1.7 የመውሊድ አጀማመር እና አከባበር በኢትዮጵያ

መውሊድ በኢትዮጵያ መቼ እና እንዴት መከበር ጀመረ በሚለው ጉዳይ ላይ በቂ የሆነ የጽሁፍ ማስረጃ መግኘት አልተቻለም፡፡ በጽሁፍ ከተገኙ መረጃዎች በተጨማሪ ስለ መውሊድ ጥሩ መረጃ አላቸው የሚባሉ ዓሊሞችን እና የኢትዮጵያ ሙስሊሞችን መብት ለማስከበር ከተንቀሳቀሱ የኢትዮጵያ ሙስሊም ተማሪዎች መካከል ከነበሩ ሰዎች መረጃ ሰብስቤያለሁ፡፡ እንዲሁም መውሊድ ለመጀመሪያ ጊዜ በይፋ መከበር ሲጀመር የነበሩ ሰዎችን በመጠየቅ መረጃዬን ለማጠናከር ሞክሬያለሁ፡፡ ከነዚህም መካከል አቶ ሙሀመድ እድሪስ፣ ሼኽ ከድር ሼኽ  አህመድ፣ ተቀዳሚ ሙፍቲህ ሀጂ ኡመር እንድሪስ፣ ሼኽ ሙሀመድ አረፋው እና ሼኽ ሙሀመድ ሼኽ ሽሪፍ ይገኙበታል፡፡

እስልምና ኢትዮጵያ ውስጥ የገባው በ7ኛው ክፍለ ዘመን በቀይ ባህር በኩል እንደሆነ Trimingham (1952፡42) እና Hussien (2006፣6) ገልጸዋል፡፡ እስልምና በነቢዩ ሙሀመድ መልዕክተኞች አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ ከገባ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ብዙ ዓመታት ተቆጥረዋል (Hussein 2006፣4) እና (Trimingham 1952፣42)፡፡ ኢትዮጵያ ከሳአውዲ አረቢያ(መካ) በመቀጠል እስልምናን የተቀበለች ሀገር ናት፡፡ ነብዩ እስልምናን ለማስፋፋት በሚሞክሩበት ወቅት ከገጠማቸው ትልቅ ጠላት ቁረይሽ ልጃቸውን ሩቂያን እና ቤተሰቦቿን ለማዳን ሰላም ወደ ሆነው ሀበሻ ሀገር ልከዋቸው ንጉስ ነጃሽ በአግባቡ ተቀብለው

አስተናግደውላቸዋል Martin (2004: 231) እና Hussein (2006:4)። Martin (2004: 226) አያይዘውም “In Islamic history and tradition, Ethiopia is known as the "Haven of the First Migration or Hijra." For Muslims, Ethiopia is synonymous with freedom from persecution and emancipation from fear.” በማለት ኢትዮጵያ በእስልምና ትልቅ ስፍራ ያላት ሀገር መሆኗን ያብራራሉ።

ከእስልምና አንጻር የሀበሻን ምድር ከሌላው ሀገር ለየት የሚያደርጓት (የሚያቀራኟት) ነገሮች አሉ። ኢትዮጵያን ከእስልምና ጋር የተቀራኘች መሆኗን ከገለጹ ጸሀፍት መካከል አንዱ AR-RAHEEQ (1996)፣ Trimingham (1952)፣ ላጲሶ (1990)፣ Hussein (2006)፣ ባህሩ (2007)፣ አብዱልፈታህ (1998)፣ አደም (2008) እና ሀሰን (2006) ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው። አብዱልፈታህ (1998፣60) ኢትዮጵያን ከእስልምና ጋር ከሚያቀራኟት በርካታ ጉዳዮች እንዳሉ ገልጸዋል። ከነዚህ መካከል ነብዩ ሙሀመድ እናታቸው በህጻንነታቸው በሞቱባቸው ጊዜ ጡት አጥብተው ያሳደጓቸው ኡሙ አይመን የተባሉ ኢትዮጵያዊት ናቸው።[24] ነብዩ ሙሀመድ የሀበሻ ምድር ከአረቦች ጥቃት ነጻ እንዲሆን አዘዋል፤ በሀበሻ ምድር ፍትህ መኖሩን ገልጸዋል። የሀበሻ ሰዎች ጥሩነት በቁርአን ውስጥ ይገኛል። የመካ መስጂድ ሙአዚን ቢላል በትውልድ ኢትዮጵያዊ ነበሩ የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በሀገራችን እስልምና ከገባበት ጊዜ ጀምሮ የሀገሪቱን ባህልና ደንብ ባልጣሰ አኳኋን በርካታ እስላማዊ ክብረ በአላት ሲከበሩ ኖረዋል፤ አሁንም በመከበር ላይ ይገኛሉ። ከነዚህም መካካል በዋናነት፣ ኢድ አልአድሃ፣ ኢድ አልፈጥር እና የነቢዩ ሙሀመድ መውሊድ ተጠቃሾች ናቸው። ኢድ አልአድሃ እና ኢድ አልፈጥር ለረጅም ዘመናት ህዝባዊ በዓል ሆነው ሲከበሩ የኖሩ ሲሆን መውሊድ ግን በይፋ ህዝባዊ ወይም ኦፊሴላዊ ክብረ በዓል ሆኖ መከበር ከጀመረ ከአራት አስርት አመታት የዘለለ እድሜ የለውም። ከዚህ በመቀጠል መውሊድ በኢትዮጵያ እንዴት እና መቼ መከበር ጀመረ የሚለውን እንመለከታለን። ቀደም ተብሎ እንደተጠቀሰው በዚህ ዙሪያ በቂ የጽሁፍ ማስረጃ ባይኖርም የተገኙትንም ያህል መረጃዎች ከመረጃ አቀባዮች ሀሳብ ጋር እያገናዘብኩ አቀርባለሁ።

---

[24] አንድ ሴት አንድን ልጅ በትወልደውም ጡት አጥብታ ካሳደገችው እንደ እናት ትቆጠራለች። እንዲሁም ከተለያየ እናት ተወልደው የአንድ ሴት (እናት) ጡት ጠብተው ያደጉ ልጆች እንደ ወንድማሞች፣ እህትማሞች ወይም እህትና ወንድሞሞች ስለሚታዩ እርስ በእርስ መጋባት አይችሉም። ይህ ሁኔታ ሸሪዐዊ መሰረት እንዳለው ኡስታዝ መሀመድ አሚን ነግረውኛል።

በሀገራችን ከጥንት ጀምሮ የነበሩ የሱፊ መሻኢኾች መውሊድ እንዲከበር ትልቁን ሚና መጫወታቸውን አቶ መሀመድ እንድሪስ[25] ያስረዳሉ፡፡ በሀገራችን መውሊድ መቼና እንዴት መከበር ጀመረ የሚለውን ሀሰን (2008፣39-41) ታላቁን የዲን አባት ሀጂ ሙሀመድ ወሌን ዋቢ በማድረግ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> በሀገራችን በተለይም በሰሜኑ ክልል በተናጠል ይከበር የነበረውን የመውሊድ መታሰቢያ ወደ ተደራጀ ስርዓት የለወጡት እስከ 1798 ዓ.ሀ የቆዩትና ጀማንጉስ ወይም ሙጃሂዱ በመባል የሚታወቁት ታላቁ ዐሊም ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ መሆናቸው ይነገራል፡፡ እኚህ ዐሊም ወደ መካ ተጉዘው የዚያን ጊዜውን የሀረም ሙፍቲ ለጅሀድ ፈቃድና የሎጅስቲክ እርዳታ ይጠይቃሉ፡፡ መፍቲውም እንደ ኢትዮጵያ ያለች ሀገር ከጅሀድ ይልቅ ህዝቡን ሰብስቦ ማስተማሩ የተሻለ መሆኑን መንገድ ይመሯቸዋል፡፡ ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ እዛው ሀረም ውስጥ ለሶስት አመታት ያክል ዒልም ተምረው ወደ ሀገራቸው ከተመለሱ በኋላ ህዝቡን አሰባስበው የሚያስተምሩበትን መንገድ ማፈላለግ ጀመሩ፡፡ ይህን ለማድረግ የተሻለው መንገድ የነብዩን የልደት ቀን መጠቀሙ ተመራጭ መሆኑን አመኑ፡፡ በመሆኑም መውሊድን እንደ ድልድይ በመጠቀም ዐሊሞች ከህዝቡ ጋር እንዲገናኙ በማድረግ ህብረተሰቡ የዲን ፍቅር እንዲኖረው ለማድረግ መውሊድን እንደ ዋነኛ ግብአት ተጠቀሙበት፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መውሊድ በሀገሪቱ ትልቅ የዲን ማስተማሪያ መድረክ በመሆን ማገልገል ጀመረ፡፡

በአሁኑ ጊዜ በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ ዓሊሞች መካከል ሼኽ ሙሀመድ ሼኽ ሸሪፍ አንዱ ናቸው፡፡ እኚህ ዓሊም[26] መውሊድ በሀገራችን በተደራጀ ሁኔታ እንዴት መከበር እንደጀመረ ከሀሰን ታጁ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ እንደ እሳቸው አገላለጽ በሀገራችን ደረጃ በተደራጀ ሁኔታ መውሊድ እንዲከበር ያደረጉት ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ ናቸው፡፡ ሼኽ ሙሀመድ ለእስልምና ልዩ ፍቅር የነበራቸው ታላቅ አሊም በመሆናቸው እስልምናን ለማጠናከር እና ሃይማኖቱን ከጠላት ለመጠበቅ የቁሳቁስ እርዳታ ለመጠየቅ ወደ መካ አቅንተው ሁለት አመት ያህል ቢቆዩም እርዳታው ስላልተሳካለቸው ሀገር ውስጥ

[25] ቃለ መጠይቅ 18/06/06

[26] ቃለ መጠይቅ 13/03/08

መጥተው እስልምና እና ሙስሊሙን ማህበረሰብ እንዴት ማጠናከር እንዳለባቸው ሲያውጠነጥኑ የተሻለ መንገድ መውሊድ መሆኑን እንዳመኑበት ሼኽ ሙሀመድ ሼኽ ሼሪፍ ያስረዳሉ፡፡ እንደ ሼኹ አገላለጽ በሀገራችን መውሊድ በተጠናከረ ሁኔታ መከበር ከጀመረባቸው ቦታዎች መካከል ዋናው ዳኒዬ[27] ነው፡፡

ዳኒዬ የተቆረቆረው ከዛሬ 137 አመት በፊት ማለትም 1870ዎቹ አካባቢ ነው፡፡ ዳኒዬ አወል ሙስሊሙን አንድ በማድረግ እና በማዋደድ ትልቅ ስራ የሰሩ ሰው ናቸው፡፡ ዳኒዬ በወቅቱ እስልምናን ጠንቅቀው አውቀው ካሳወቁ ዓሊሞች አንዱ በመሆናቸው ዲንን ለማስፋፋት በዋናነት የተጠቀሙት መውሊድን እንደሆነ ሼኽ ሙሀመድ ያስረዳሉ፡፡ ሙፍቲህ ሀጂ ዑመር እንድሪስ[28] ስለ መውሊድ አጀማመር ከሼኽ ሙሀመድ ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ ካቀረቡ በኋላ በሀገራችን ዲንን ለማስፋፋት መውሊድ ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ መካ የቆዩበትን ወቅት ሀሰን ሶስት አመት ነው ሲሉ ሼኽ ሙሀመድ ሼኽ ሸሪፍ ግን ሁለት አመት ነው ይላሉ፡፡ አብላጫ መረጃ አቀባዮች ግን የሚስማሙት ሶስት አመት በሚለው ነው፡፡

እንደ ሼኽ ሙሀመድ አገላለጽ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ መውሊድ በተለያዩ ክፍለ ሀገራት የሚኖሩ ዓሊሞች በተደራጀ እና ሰፊውን ህዝብ ባሳተፈ ሁኔታ ማክበር ጀምረዋል፡፡ እንዲሁም የተለያዩ ስልቶችን በመጠቀም ብሔራዊ በዓልም ለማስደረግ በርካታ ጥረቶችን አድርገዋል፡፡ መውሊድን ብሔራዊ በዓል ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ ካበረከቱ ሰዎች መካከል እስከ 1981 ዓ.ም ድረስ የኖሩት ሀጂ ሙሀመድ ሳኒ ሀቢብ ተጠቃሽ ናቸው፡፡

በወለኔ ሼኽ ተጽፎ አብዱልፈታህ "ጥሩነ" በሚል ርእስ የተተረጎመው መጽሀፍ (1998፣60 እና 120) በ19ኛው ክፍለ ዘመን አንዳንድ ዓሊሞች የአካበቢውን ሰው እና የእነርሱን ደረሳዎችን በመሰብሰብ መውሊድ ያወጡ እንደነበር ያስረዳል፡፡ ከነዚህም መካከል የታላቁ የወለኔ ሼኽ አባት የነበሩት ሼኽ በሽር ትክለት[29] ለመውሊድ ብዙ ገንዘብ በመመደብ ትልቅ መውሊድ በማውጣት ስመጥር የነበሩ የወለኔ አካባቢ ዓሊም ነበሩ፡፡ ከእሳቸው በተጨማሪ የአብሬት ሼኽ በመባል የሚታወቁት ሼኽ አቡ አብደላ በተመሳሳይ ሁኔታ መውሊድ ያወጡ

[27] የዳኒዬ መውሊድ ማለት ወሎ ውስጥ በየአመቱ በደመቀ ሁኔታ የሚከበር መውሊድ ነው፡፡
[28] ቃለ መጠይቅ 15/03/08
[29] እኚህ ዓሊም በህይወት የነበሩት 1260ዎቹ እስከ 1340ዎቹ ዓ.ሂ አከባቢ ነው፡፡

ነበር፡፡ ከነዚህ ዓሊሞች በተጨማሪ በወሎ፣ በጎጃም፣ በጅማ፣ በባሌ፣ በስልጤ፣ በሀላባ፣ በወለኔ፣ በጉራጌ፣ በሀረር ወዘተ መውሊድ የሚያወጡ በርካታ ዓሊሞች ነበሩ (አብዱልፈታህ፣1998፣60-61):: ከነዚህ መካከል የተወሰኑት መውሊዶች ዛሬም ድረስ መከበራቸውን ቀጥለዋል፡፡ የተወሰኑት ግን በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ተቋርጧል፡፡

ከዚህ በላይ ከተመለከትነው መረጃ አንጻር መውሊድ በጋራ ተሰባስቦ መክበር ከሃይማኖታዊ ተግባር በዘለለ በርካታ ፋይዳ እንደነበረው እንረዳለን፡፡ ለምሳሌ ሼኽ ሙሀመድ አልሻፊ ወደ መካ የሄዱት የሃይማኖት ትምህርት ለመማር ሳይሆን የኢትዮጵያን ሙስሊሙን ማህበረሰብ በመውሊድ አማካኝነት አሰባስበው በማህበራዊ እና በፖለቲካዊ ጉዳይ ለማጠናከር የወቅቱ የመካ ሙፍቲ የቁሳቁስ ድጋፍ እንዲያደርግላቸው ነበር-ምንም እንኳን ጥረታቸው ባይሳካም፡፡ እኚ ሼኽ ወደ ሀገራቸው ከተመለሱም በኋላ በመውሊድ አማካኝነት ህዝበ ሙስሊሙን ለማጠናከር ሞክረዋል፡፡ ከሼኽ ሙሀመድ በተጨማሪ ዳኒዬ አውል የወሎ ሙስሊሞችን ሃይማኖታቸውን እንዲቀይሩ በመሪዎች በሚገደዱበት ወቅት ይህን ፈተና እንዴት ተቋቁመው ማለፍ እንዳለባቸው ህዝቡን ከሚመክሩባቸው መድረኮች መካከል መውሊድ ዋነኛው ነበር፡፡ ከእነዚህ አሊሞች በተጨማሪ  የአብሬት ሼኽ እና የወለኔ ሼኽ በጉራጌ እና አካባቢው የነበሩ ሙስሊሞችን በመውሊድ በማሰባሰብ በወቅቱ አካባቢው በሚመሩ ሹማምንቶች እና ክርስትያኖች ይደርሱባቸው የነበረውን ጭቆና እንግልት እንዴት መቋቋም እና መመከት እንዳለባቸው ይመክሯቸው እንደነበር ይነገራል፡፡ ስለዚህ መውሊድ በሀገራች መከበር መጀመሩ ከሃይማኖታዊ ፋይዳ ባሻገር በርካታ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ዓላማ እንደነበረው መረዳት ይቻላል፡፡

## 4.1.7.1 መውሊድ በሀገራችን እንዴት ሃይማኖታዊ ህዝባዊ በዓል ሆነ?

መውሊድ በተበታተነ ሁኔታ ሲከበር ለረጅም አመታት ከቆየ በኋላ በይፋ እና መንግስት በሚያውቀው ሁኔታ መስጂድ ውስጥ በመሰባሰብ መከበር የተጀመረው ግን በ1953 ዓ.ም[30] በአዲስ አበባ ከተማ በአንዋር መስጂድ ነው፡፡ እንደ አቶ ሙሀመድ አገላለጽ በዚህ ዘመን የነብዩ መውሊድ በአንዋር መስጂድ ለመጀመሪያ ጊዜ የአዲስ አበባ ሙስሊሞች ተሰብስበው

[30] ይህን መረጃ ያገኘሁት በተጠቀሰው ዘመን በዓሉ ሲከበር የአከባበር ስርአቱን ለመምራት ከተቋቋመው ኮሚቴ አባል እና የበዓሉ ተሳታፊ አቶ መሀመድ እንድሪስ ነው፡፡

ማክበራቸው በሌሎች ክፍለ ሀገራት በዓሉን በተመሳሳይ ሁኔታ ለማክበር በር ከፋች ሆኗል ይላሉ፡፡

መውሊድ በሀገራችን በግልጽ እንዲከበር ያደረጉት የተማሩ ወጣት ሙስሊሞች ናቸው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በመውሊድ ብቻ ሳይሆን በበርካታ እስላማዊ ጉዳዮች ላይ ጥያቄ በማንሳት በሙስሊሞች ዙሪያ ከፍተኛ የሚባል እንቅስቃሴ እንዲፈጠር ማድረግ መቻላቸውን Hussein (1998፡98) እና አህመዲን (2008፣33) ያስረዳሉ፡፡ እንደ መረጃ አቀባዬ አቶ መሀመድ እንድሪስ አገላለጽ የኃይለስላሴ መንግስት ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉም ብሔረሰብ እና ሀይማኖት እኩል መሆን አለባቸው የሚል አስተሳሰብ ነበረው፡፡ Braukämper (2002፣160) ደግሞ 1944/45 እ.ኤ.አ አጼ ኃይለስላሴ የሃይማኖት፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊ፣ እና የባህላዊ እኩልነት ይፈጠር እንዲሁም የሙስሊሞች ጭቆና ይቁም የሚል አዋጅ እንዳወጁ ያስረዳሉ፡፡

ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ወጣት የተማሩ ሙስሊሞች የሙስሊሞችን ጉዳይ የሚከታተል መስሪያ ቤት ሊኖረን ይገባል የሚል ጥያቄ አነሱ፡፡ መንግስት "የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ጽህፈት ቤት" የሚል ጽህፈት ቤት አቋቋመ፡፡ ይህ ጽህፈት ቤት የተቋቋመው ለይስሙላ ያህል ስለነበር ይህ ነው የሚባል ሙስሊሞችን የሚጠቅም ስራ አልሰራምና ተቀባይነቱን አጣ፡፡ ወጣት ሙስሊሞችም በአቶ ሙሀመድ ሳቢር ፕሬዝዳንትነት የሚመራ "የኢትዮጵያ ኢስላማዊ ማህበር" በሚል ርዕስ የሚጠራ ማህበር እንዳቋቋሙ አቶ ሙሀመድ ያስረዳሉ፡፡ እንደ አህመዲን (2008፣33) አገላለጽ ደግሞ ይህ ማህበር በ1955 ስሙ "የሰላም ማህበር" በሚል እንደተለወጠ እና ፕሬዝዳንቱ ሐጅ ከማል ሐጂ የሚባል ሰው እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ይህ ግለሰብ የሙስሊሙ ማህበረሰብ መብት የሚያስከብር ስላልነበረ በፊት አውራሪ አመዴ ለማ ተቀይሯል፡፡ ማህበሩ በእሳቸው በሚመራበት ጊዜ መውሊድ ለመጀመሪያ ጊዜ ሚኒስትሮች በተገኙበት በአንዋር መስጂድ እንደተከበረ አህመዲን (2008፣33-34) ይገልጻሉ፡፡

አቶ መሀመድ የእነዚህ ማህበራት መቋቋም እና የሙስሊሙ ህብረተሰብ ባገኘው አጋጣሚ መብቱን መጠየቅ ስለጀመረ ንጉሱ የመውሊድ በዓል የአዲስ አበባ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ተሰብስቦ በጋራ እንዲያከብር ፈቅደዋል ይላሉ፡፡ አቶ መሀመድ አያይዘውም ሙስሊሙ ማህበረሰብ የዝያን ቀን በዓሉን ከአከበረ በኋላ ሁለት ሰዎችን ወደ ንጉሱ ቤተመንግስት በመላክ "መውሊድን በዚህ ሁኔታ በማክበራችን ደስ ብሎናል፤ እርሶንም እንኳን አደረሶት"

በማለት ለንጉሱ ምስጋና እንዳቀረቡ ይናገራሉ፡፡ አቶ መሀመድ አያይዘውም ምስጋና ለማቅረብ ወደ ንጉሱ ከሄዱ ሰዎች መካከል አንዱ ፊታውራሪ አመዴ ለማ ይገኙበታል በማለት ገልጸዋል፡፡ አህመዲን (2008፣232) ሦስቱ አጼዎች እና ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች በሚል ርእስ ባሳተሙት መጽሐፍ ላይ በ1950ዎቹ ሙስሊሞች በራሳቸው በዓል ቀን ንጉሱን "እንኳን አደረሳችሁ" ማለት የተለመደ እንደነበር ታህሳስ 15 ቀን 1958 ዓ.ም ለንጉሱ የቀረበውን ምስጋና በምሳሌነት በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ የረቢኡል አወል መውሊድ በዝያን ዘመን እንደ ህዝባዊ በዓል (Public holiday) ባይሆንም የአዲስ አበባ ከተማ እና በሌሎችም ቦታዎች ሙስሊሞች በአንድ ቦታ ተሰብሰበው እንዲያከብሩ መፈቀዱ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሌሎቹም መብቶቹን እንዲጠይቅ በር እንደከፈተ ሼኽ ሙሀመድ ያስረዳሉ፡፡

ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ በኢትዮጵያ ታሪክ የሚነሳው በሚያዚያ 1966 በአዲስ አበባ ከተማ የተካሔደው በዋናነት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ያዘጋጀው እና ክርስትያኖችም የተሳተፉበት ሰላማዊ ሰልፍ ነው፡፡ ይህን በማስመልከት ባህሩ (2007፣240) "ለአያሌ ሳምንታት በቆየው ህዝባዊ አመጽ ውስጥ ሌላው ጉልህ ስፍራ የያዘው ሚያዚያ 10 የተካሄደው ከመቶ ሺ በላይ የሚገመት ህዝብ የተካፈለበት ግዙፉ ሰላማዊ ሰልፍ ነው፡፡ ሙስሊሞች እና ክርስትያን ድጋፋቸውን የሰጡበት ይህ ሰልፍ የሃይማኖት እኩልነት እንዲሰፍን፣ የመንግስትና ቤተ ክህነት ቁርኝት እንዲቀር እና **የሙስሊም በዓላት ብሔራዊ በዓላት ሆኖ እንዲከበሩ** አበክሮ ጠየቀ" ይላሉ፡፡

Hussein በሀገራችን በሙስሊሞች እና በክርስትያኖች መካከል ስለነበረው ግንኙነት በሚያወሱበት መጣጥፉ የሰልፉን ሁኔታ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል፡፡

> The mammoth Muslim demonstration of 20 April 1974, inspired by a series of protest movements against the imperial order in February, was a manifestation of a long-simmering discontent and grievances over the discriminatory policy towards Muslims pursued by the preceding Ethiopian regimes. Contrary to the assertions of some foreign observers, the demonstration was an act of Muslim solidarity with the struggle of other sections of the Ethiopian population against the old order (Hussein, 2006:10).

ሲተረጎም

ሚያዝያ 12/1966 ዓ.ም የተካሄደው ታላቁ ሰላማዊ ሰልፍ ለማካሄድ ያነሳሳው በየካቲት ወር ውስጥ በንጉሰ ነገስቱ መንግስት ላይ በተከታታይ ሲካሄድ የነበረው የአመጽ እንቅስቃሴዎች ነው፡፡ ይህ እንዲሆን ያደረገው ባለፉት ዘመናት የኢትዮጵያ የአገዛዝ ስርዐቶች ውስጥ በሙስሊሞች ላይ ሲካሄድ የነበረው የማግለል ፖሊሲ ያስከተለው ቁጭት እና በደል ነው፡፡ አንዳንድ የውጭ ተመልካቾች ከሚሰጡት አስተያየት በተቃራኒ የተካሄደው ሰላማዊ ሰልፍ የሚያሳየው ሙስሊሞች ከሌላው ከኢትዮጵያ ሰፊው ህዝብ ጋር በመሆን የቆየውን የአጼውን ስርዐት ለመገርሰስ  ያላቸውን ወንድማማችነት እና የፖለቲካ ድጋፍ እና አጋርነት ያሳዩበት ነው፡፡

በዚህ ሰልፍ ከተነሱ ጥያቄዎች መካከል "እኛ ሙስሊሞች መብታችን ይከበር"፣ የተለያዩ በዓላቶቻችንን ህዝባዊ በዓል ሆነው በአደባባይ እንድናከብር ይፈቀድልን፣ በኢትዮጵያ የሚኖሩ እስላሞች መባላችን ቀርቶ ኢትዮጵያዊያን እስላሞች እንባል"፣ በአስተዳደር ፍትሕ ይስመር፣ እስላማዊ ምክር ቤት እንድናቋቁም ይፈቀድልን፣ መሰጂድ መስሪያ የገንዘብ ድጋፍ ይደረግልን ወዘተ የሚሉ ጥያቄዎችን እንደተነሱ ቢላል (1967፣18)፣ Hussein (2006:10) እና አህመዲን (2008፣49 እና 225) ያስረዳሉ፡፡

ከ1966ቱ ሰላማዊ ሰልፍ በኋላ ከሙስሊሞች ጋር ተያያዘ በሀገሪቱ የመጣውን ለውጥ አህመዲን (2008፣302) በሚከተለው መልክ አስፍረውታል፡፡

> ታህሳስ 14 ቀን 1967 በብሔራዊ ደረጃ ስለሚከበሩ በአላት ዝርዝር መግለጫ ወጣ፡፡ የሙስሊ ሽቾአሙ ትግል በከፊልም ቢሆን ፍሬ ማፍራት ጀመረ፡፡ እስላማዊ በዓላትም ብሔራዊ በዓላት ሆነው ተቆጠሩ፡፡ "የህዝብ በዓላት አዋጅ" የተሰኘ አዋጅ ወጣ፡፡ ቀደም ብሎ በ1948 የወጣው አዋጅ በቁጠር "151/19481/አ151" ተሻረ፡፡ በአዋጁ እውቅና ከተሰጣቸው አስራ ሁለት በዓላት መካከል ሦስቱ የሙስሊም በዓላት ነበሩ፡፡ እነሱም ዒድ አል ፊጢር፣ ዒድ አል አድሃና **መውሊድ** ነበሩ፡፡

ይህ አዋጅ ከታወጀ በኋላ "ወጣት እስላሞች መንፈሳዊ ክበብ" በተሰኘው ክበብ አማካኝነት ለመጀመሪያ ጊዜ መውሊድ ህዝባዊ ሆኖ መከበሩን ቢላል መጽሔት (1967፣32) ካስረዳ በኋላ "የሰላማዊ ማህበሩ[31] ከፈረሰ በኋላ የታላቁ ነቢይ የልደት በአል ለመጀመሪያ ጊዜ በዚህ ሁኔታ ለማክበር ክበቡ የመጀመሪያ ነው፡፡" በማለት በፎቶ ግራፍ አስደግፎ አቅርቧል፡፡ እንዲሁም ይህ መጽሔት (1967፣7) መውሊድ በ1967 ዓ.ም የነብዩ ሙሀመድ መውሊድ በአዲስ አበባ በይፋ መከበሩን ያስረዳል፡፡ መጽሔቱ(1968፣13) በ1967 የመውሊድ በዓል ከአዲስ አበባ በተጨማሪ በጅግጅጋ እና በጎንደር ከተማዎች ህዝቡ አደባባይ ወጥቶ እንዳከበረ ያስረዳል፡፡ ከዚህና መሰል መረጃዎች መረዳት የሚቻለው በሀገራችን መውሊድ በይፋ መከበር የጀመረው ከ1966ቱ ሰላማዊ ሰልፍ በኋላ መሆኑን ነው፡፡

ከዚህ ሰላማዊ ሰልፍ በኋላ እስላማዊ በዓላት ብሔራዊ በዓላት ከመሆናቸው በተጨማሪ በርካታ እስላማዊ ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ እና መስጂዶች ተቋቁመዋል፡፡ ከተቋማቱ መካከል Ethiopian Islamic Affairs Supreme Council (EIASC) በዋናነት የሚጠቀሰው መሆኑን Østebø (2008፣417) ገልጸዋል፡፡ ከዚህ በላይ በዘመኑ ስለተቋቋሙ የተለያዩ መስሪያ ቤቶች እና ማህበራት በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በአጭሩ ማንሳት ያስፈለገበት ምክንያት በሀገሪቱ መውሊድ ይፋ በሆነ ሁኔታ እንዲከበር እነዚህ ተቋማት የተጫወቱትን ሚና ለማሳየት ነው፡፡

ደርግ ስልጣን እንደያዘ ለሁሉም ብሔረሰብ እና ሀይማኖት እንደሚቆረቆር ለመግለጽ ሁሉም ብሔረሰቦች እና ሀይማኖት እኩል ናቸው ብሎ አወጀ፡፡ እንደ መረጃ አቀባዩ ሼኽ ሙስጠፋ ጅብሪል[32] አገላለጽ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ይህን አዋጅ ተከትሎ ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ስለመብቱ መቆርቆር እና መጠየቅ ጀመረ፡፡ ይህን አዋጅ ተግባራዊ ማድረጉን ለማሳያነት እና ለህዝቡ ጥያቄ መልስ እየሰጠሁ ነው ለማለት ከተጠቀመባቸው ጉዳዮች መካከል የረቢኡል መውሊድ አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት መውሊድ ሶስተኛ እስላማዊ በዓል ሆኖ እንዲከበር ፈቃድ ሰጠ፡፡ Encyclopedia Aethiopica (ቅጽ 3 ገጽ 2007፡ 878-880) በዓሉ በኢትዮጵያ ውስጥ ህዝባዊ በዓል (Public holiday) በመሆን መከበር የጀመረው 1967 ዓ.ም ነው ይላል፡፡ ይህን ሀሳብ "… The military government later issued an official

[31] ወጣት እስላሞች መንፈሳዊ ክበብ ከመቋቋሙ በፊት "ሰላማዊ ማህበር" የሚባል ማህበር እንደነበር በዚህ ጽሁፍ መግቢያ ላይ ቀርቧል፡፡

[32] ቃለ መጠይቅ 13/04/07

decree that the three Islamic festivals would be observed as public holidays for the first time in the history of the country." በማለት Hussein (2006:10) ያስረዳሉ። በመሆኑም በዓሉ ህዝባዊ በዓል ከሆነበት አመት ጀምሮ መስሪያ ቤቶች እና ትምህርት ቤቶች ተዘግተው እንደማንኛውም ብሔራዊ በዓል እስካሁን ድረስ በመከበር ላይ ይገኛል።

## 4.1.7.2 በሀገራችን የመውሊድ አከባበር ምን ይመስላል?

በሀገራችን የረቢኡል አወል ሆነ ዓሊሞችን መሰረት አድርጎ የሚከበር መውሊድ በአከባበር ይዘታቸው በብዛት ተመሳሳይነት እንዳላቸው ከተመለከትኳቸው ጥናቶች መረዳት ችያለሁ። በረቢኡል አውል መውሊድ በብዛት የሚወሱት ነብዩ ሙሀመድ ሲሆን ዓሊሞችን መሰረት አድርገው በሚከበሩ መውሊዶች ላይ ግን በብዛት የሚወሱት መውሊዱ የሚከበርላቸው ዓሊም ገድል ነው። ይህን በማስመልከት በሀገራችን ያለውን የመውሊድ የአከባበር ሁኔታ ሀሰን (2008፣12-13) በሚከተለው መልኩ ዘርዝረውታል።

- ✓ በሼኽ አህመድ ዳኒ (እስከ 1321 ዓ.ሂ) የተደራጁ "ራምሳ" እና "ተራ" መንዙማ የተሰኙ የዚክር እና የዱዐ መድቢሎች ይደመጣሉ፤
- ✓ የሶሀባዎች፣ ታቢጾች እና የሌሎች ታላላቅ ሰዎች በተለይም የሀገራዊ ጓል ስብዕናቸው እና ገድል (ቅኔ) ይነገራል፤
- ✓ ነብዩን የሚያወድሱ ግጥሞች እና መንዙማዎች ይደመጣሉ፤
- ✓ በዐሊሞች መካከል የዒልም ውይይት እና መጠያየቅ ይደረጋል፤
- ✓ መውሊድ የዱዐ እና የመገናኛ መድረክ በመሆን ያገለግላል፤
- ✓ ድግስ ተደግሶ ድሆች ሶደቃ ይቋደሳሉ፤
- ✓ አላህን የሚያወድሱ ልዩ ልዩ ዚክሮች ይባላሉ፤እና
- ✓ በነብዩ ላይ ሶለዋት ማውረድ ናቸው።

መውሊድ አክባሪዎች መውሊድን ማክበር ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ እንዳለው የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ። በ2008 ዓ.ም የረቢኡል አወል መውሊድ ሲከበር በአዲስ አበባ በአንዋር መስጂድ በተገኘሁበት ወቅት መውሊድን መስጂድ ውስጥ ተሰባስበው የሚያከብሩ ሰዎችን

መውሊድን በማክበራቸው ምን ፋይዳ እንደሚያገኙ ጠይቄያቸዋለሁ፡፡ እነዚህ መውሊድ አክባሪዎች የሰጡኝ ምላሽ ጠቅለል ሲደረግ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ መውሊድ መከበሩ የራሱ የሆነ በርካታ ዓላማ እና ፋይዳ አለው፡፡ ከነዚህም መካከል ደስታን የመግለጫ አጋጣሚ፣ አላህን ማመስገኛ እና ማወደሻ አጋጣሚ፣ የነብዩን ገድል ማስታወሻ እና ማወደሻ መድረክ፣ ከነብዩ ጋር በፍቅር መተሳሰሪያ አጋጣሚ፣ የዳዕዋና የዚክር ማቅረቢያ መድረክ ፣ የእርስ በእርስ መገናኛ መድረክ (ኮንፍረስ)፣ እስላማዊ ባህርይን ማጠናከሪያ መድረክ፣ በመንዙማዎች አማካኝነት የመዝናኛ አጋጣሚ፣ ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው የሚል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ መውሊድ ዕውቀት መቅሰሚያ፣ ከተጠፋፉ ሰዎች መገናኛ እና መጠያየቅያ፣ በመንዙማዎች መዝናኛ፣ መደሰቻ፣ ነብዩን እና አላህን ማመስገኛ፣ የነብዩን እና የትላልቅ ዓሊሞችን ማስታወሻ፣ ለነብዩ ያለንን ልዩ ፍቅር ማሳያ፣ መውሊድ እንዳይረሳ እና እንዲደምቅ ማድረጊያ አጋጣሚ ከመሆኑ ባሻገር ሶደቃ በማውጣት ድሆችን በማብላት ምንዳ(አጅር) ማግኛ ሆኖ እንደሚያገለግል አክባሪዎች ያስረዳሉ፡፡[33]

ከዚህ በላይ የተመለከትነው ስለ ነብዩ ሙሀመድ የልደት ቀን አካባበር ሁኔታ ነው፡፡ ስለ ነብዩ ሙሀመድ መውሊድ በዚህ ጽሁፍ ማንሳት የተፈለገበት ምክንያት በሀገራችን የሚከበሩ ዓሊም ተኮር መውሊዶች መሰረታቸው የነብዩ መውሊድ ስለሆነ ነው፡፡ በሀገራችንም በርካታ ዓሊም ተኮር መውሊዶች ይከበራሉ፡፡

## 4.1.8 የመውሊድ አጀማመር እና አከባበር በስልጤ

መውሊድ ከጥንት ጀምሮ በደመቀ ሁኔታ ከሚያከብሩ ብሔረሰቦች መካከል የስልጤ ብሔረሰብ አንዱ ነው፡፡ ዘላለም (2013፣251) በሀገራችን ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ከሚያከብሩ እና በወልዮች ከሚያምኑ የሀገራችን ብሔረሰቦች መካከል የስልጤ ብሔረሰብ አንዱ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ የወለኔ ሼኽ የነበሩት ሼኽ በኽለት(1260ዎቹ እስከ 1340ዎቹ) ከጥንት ጀምሮ በጉራጌ እና አካባቢው መውሊድ ሲከበርባቸው ከነበሩ ቦታዎች መካከል ስልጤዎች የሚኖሩባቸው ስፍራዎች እንደሚገኙባቸው ስለ ጉራጌ ሼኾች ታሪክ በጻፉበት ኪታብ(መጻህፍ) ያስዳሉ፡፡ እንደ እኚህ ሼኽ እና መሰሎቻቸው አገላለጽ መውሊድ በአካባቢው መከበር ከጀመረ አምስት መቶ አመታት ተቆጥረዋል፡፡ በእነዚህ ዘመናት መውሊድ

[33] መረጃ አቀባዮቹ ሼኽ ሙስጠፋ ጅብሪል፣ አቶ ጀማል ሙሀመድ፣ ሀጅ በድሩ ሊገሶ እና ወጣት ዘይነዲን ሲራጃ ናቸው፡፡

የአካባቢው ህዝብ በርካታ ሃይማኖታ፣ ዊማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ተግባራትን ያከናውን እንደነበር የአካባቢው የሃይማኖት አባቶች ያስረዳሉ፡፡ በብሔረሰቡ ዘንድ በሚከበሩ መውሊዶች በርካታ ክንውኖች ይከናወናሉ፡፡ ከነዚህም መካከል

- ✓ ነብዩ ሙሀመድ እና መውሊዱ የመከበርበት መስጂድ መስረች ሼኽ ታሪክ በሰፊው ይወሳሉ፣
- ✓ በታላላቅ ኡስታዞች እና ሼኾች የተለያዩ ሃይማኖታዊ እና አለማዊ ትምህርቶች ይሰጣሉ፣
- ✓ በልጆች እና በወጣቶች የተዘጋጁ የተለያዩ መንዙማዎች በድቤ ታግዘው ይባላሉ፣
- ✓ የተለያዩ ምግቦች ተዘጋጅተው የተራቡ ሰዎች እንዲመገቡ ይደረጋል የሚሉት ዋና ዋና ክንውኖች ናቸው፡፡

የስልጤ ብሔረሰብ ከ1520ዎቹ ጀምሮ መውሊድ ሲከበርባቸው የነበሩ እና አሁንም የሚከበርባቸው መስጂዶች እና ቦታዎች የሚከተሉት እንደሆኑ የብሔረሰቡ ታሪክ አዋቂ መረጃ አቀባዮች የሰጡት መረጃ እና አብዱልፈታህ(1999፣321-327) የጻፈው መረጃ የሚከተለውን ይመስላል፡፡

**የሐጂ አሊዪ መውሊድ፡-** ይህ መውሊድ በአካባቢው ማለትም በሀዲያ እና አዘርነት አካበባቢ የመጀመሪያው መውሊድ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ ማለት በሐጂ አልዪ መስጂድ መውሊድ መከበር የጀመረው ከ500 ዓመት በፊት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ መውሊድ መከበር የጀመረው ሐጂ አሊዪ ኡምናን በሚባለው ቦታ መስጂድ አሰርተው የአካባቢው ህዝብ መስጂዱ ውስጥ እንዲሰግድ ካደረጉበት ዘመን ጀምሮ እንደሆነ ሀጂ አንዋር ያስረዳሉ፡፡ የስልጤ አባት በመባል የሚታወቁት ሐጂ አልዪ የመቃብር ስፍራ ውስጥ የሚገኝ ሲሆን በመውሊድ ሰሞን በምዕመናን ይጎበኛል፡፡ በዚህ መስጂድ ላለፉት አስር አመታት በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ መውሊድ ሳይከበር ቀርቷል፡፡ ነገር ግን ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የወረዳው አስተዳደር ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር በመነጋገር መስጂዱን የቱሪስት መስህብ ለማድረግ እና እንደ ቀድሞው መውሊድ በየአመት እንዲከበር ለማድረግ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

**የጊስት አሚናት ሰኢድ መስጂድ እና መውሊድ፡-** ይህ መስጂድ የሚገኝበት ቦታ ስልጢ ወረዳ ቦዜ ሳቦላ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ሲሆን የተመሰረተውም ከ450 እስከ 500 ዓመት በፊት እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህ መስጂድ የተቋቋመው ከሒጂ አልዪ ጋር ከወደ ሀረር መጥተዋል ከሚባሉት አምስቱ የስልጤ እናቶች መካከል አንዷ ለሆኑት ጊስት አሚናት መታሰቢያነት

ነው። በዚህ መስጂድ አመቱን ሙሉ የሶላት ስነ ስርዓ ይካሄደል። እንዲሁም በአመት አንዴ መውሊድ ይከበራል።

**የሀበሻው ቢላል መንደር እና መውሊድ፡-** ይህ ቦታ የሚገኘው በስልጤ ዞን በምዕራብ አዘርነት ወረዳ ሙጎ ተራራ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን በየአመቱ መውሊድ ይከበርበታል። ይህ መስጂድ የተቋቋመው በኢስላም የመጀመሪያው ሙአዚን የሚባለው ቢላል የዘር ሀረግ የሚመዘዘው ከዚህ አካባቢ ስለሆነ እንደሆነ ለቢላል መታሰበይነት እንደተቋቋመ የአካባቢው ሽማግሌዎች ይናገራሉ። ይህ መስጂድ መቼ እንደተቋቋመ እና መውሊዱ መቼ መከበር እንደተጀመረ ግልጽ የሆነ መረጃ የለም።

**የዳንጌ ሼኽ መስጂድ እና መውሊድ፡-** ይህ መስጂድ ከተመሰረተ ከ120 እስከ 135 ዓመት እንደሚሆን የሚገመት ሲሆን መስጂዱንም የመሰረቱት ሼኽ ሙሀመድ ኦብዩ እንደሆኑ ይነገራል። በዚህ መስጂድ በጣም ትልቅ ሀረም እና በርካታ ኸለዋዎች የሚገኙ ሲሆን በአመት አንድ ጊዜ መውሊድ ይከበርበታል።

**የገን ስልጤ መስጂድ እና መውሊድ፡-** ይህ መስጂድ የተመሰረተው የሐጂ አሊዩ ወንድ ልጅ በሆኑት እና ከሀጂ አሊዩ ቀጥሎ አካባቢውን ላስተዳደሩት ገን ስልጤ መታሰቢያ ነው። በዚህ መስጂድ የገን ስልጤ መቃብር እንደሚገኝ ይነገራል። ይህ መስጂድ የሚገኘው በዞን በአሊቾ ውሪሮ ወረዳ ቃዋቆቶ አካባቢ የሚገኝ ሲሆን አመቱን ሙሉ የቅራት እና የሶላት ስነ ስርዓት የሚካሄድበት ሲሆን በየአመቱ መውሊድ ይከበርበታል።

**የአልከሶ መስጂድ እና መውሊድ፡-** የአልከሶ መስጂድ በሼኽ በሽር አማካኝነት ከ1900 ዓ.ም እንደተመሰረተ እና ከዚህ አመት ጀምሮ መውሊድ የሚከበርበት ቦታ ነው። ይህ ቦታ የሚገኘው በስልጢ ወረዳ ከአልከሶ ሶስት ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ነው። ይህ መስጂድ በተመሰረተበት ዘመን ከ300 በላይ እስልምና ትምህርት የሚማሩ ተማሪዎች እንደነበሩ ይነገራል። በዚህ መስጂድ ሀረም ውስጥ የመስጂዱ መስራች እና የቤተሰቦቻቸው መካነ መቃብር የሚገኝ ሲሆን መውሊድ በሚከበርበት ወቅት ይጎበኛለል።

**የጎለጮባ ሼኽ መስጂድ እና መውሊድ፡-** ይህ መስጂድ የተቋቋመው በሼኽ አብደላ እንደሆነ እና ከ120 እስከ 140 ዓመት እንዳለው ይነገራል። ይህ መስጂድ የሚገኘው በዞኑ በዳሎቻ ወረዳ ጎለጮባ ቀበሌ ገበሬ ማህበር ውስጥ ነው። በዚህ መስጂድ በየአመቱ የረቢየል አወል መውሊድ እና የሼኹ መታሰቢያ መውሊድ እንደሚከበር ሼኽ ጀማል ያስረዳሉ።

ከዚህ በላይ የተመከትናቸው መውሊድ የመከበርባቸው መስጂዶች ለምሳሌ ያክል ተመለከትነ እንጅ በዞኑ መውሊድ የሚከበርባቸው በርካታ መስጂዶች ይገኛሉ ከነዚህ መካከል የጊስት ጣሂራት ፍልፍል መስጂድ፣ የአሳኖ ሼኽ መስጂድ፣ የአናጂና ወይም የኢነቆር ሼኽ መስጂድ፣ የጋለሜ ሼኽ መስጂድ፣ የሴቃቾ መስጂድ፣ የወዳቀ መስጂድ፣ የአበከሳዬ ዋጆ መስጂድ ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

ከዚህ በላይ ከተመለከትነው መረጃ የምንረዳው የስልጤ ብሔረሰብ መውሊድ ማክበር የጀመረው ከዛሬ 500 ዓመት በፊት ጀምሮ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ሐጂ አልይ በአካቢው መኖር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ መስጂድ በመስራት እና የአካባቢውን ህዝብ በመውሊድ በማሰባሰብ አለማዊ እና መንፈሳዊ ትምህርት ያስተምሩ እንደነበር ይነገራል፡፡

በስልጤ ብሔረሰብ ዘንድ ለአለፉት አምስት መቶ አመታት ያህል የተለያዩ መውሊዶች እየተከበሩ የነበሩ ቢሆኑም አብላጫዎቹ ሲቋረጡ ጥቂቶቹ ግን አሁንም በመከበር ላይ ይገኛሉ፡፡ ለእነዚህ መውሊዶች መቋረጥ ሁለት መሰረታዊ ምክንያቶች ይነገራሉ፡፡ የመጀመሪያው እና ዋነኛው በአከባቢው የሰለፍይ ወይም በተለምዶ የወሀብይ አመለካከት መስራፋፋቱ ነው፡፡ ከአለፉት ሰላሳ እና አርባ አመታት ወዲህ የአካባቢው ወጣቶች ከዞኑ ውጭ እና የተወሰኑት ከሀገር ውጭ በመሄድ እስላማዊ ትምህርት ተምረው በመመለስ በአካባቢው የሰለፊይ አስተምህሮትን በማስፋፋት ላይ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ወጣች አስላማዊ ትምህርትን ከማስራፋት ጎን ለጎን በአካባቢው ይፈጸማሉ የሚሏቸውን በእስልምና የተከለከሉ ወይም ከቁርአንም ሆነ ከሀዲስ ማስረጃ የላቸውም የሚሏቸውን እንደ መውሊድ ያሉ ጉዳዮችን በመቃወም ላይ ይገኛሉ፡፡ የእነዚህ ወጣቶች መውሊድን መቃወማቸው በብሔረሰቡ ዘንድ ይከበሩ የነበሩ በርካታ መውሊዶች እንዲቋረጥ ምክንያት ሆኗል፡፡ ሁለተኛው ምክንያት የኑሮ ውድነት ነው፡፡ መረጃ አቀባዮች በዞኑ ይከበሩ ለነበሩ መውሊዶች መቋረጥ እንደምክንያትነት የሚያቀርቡት የኑሮ መወደድን ነው፡፡ ከመረጃ አቀባዮቹ መካከል ሼኽ ጀማል "በዞኑ በተለያዩ ቦታዎች ለሚከበሩ መውሊዶች ከፍተኛ ወጪ ስለሚያስፈልጋቸው ይህን ወጪ ለማውጣት ህዝቡ አቅሙ ስላልፈቀደ ለመውሊድ ያለው ፍቅር ቀንሷል፡፡" ይላሉ፡፡ መረጃ አቀባዮቹ ይህን ቢሉም በአሁኑ ዘመን በአለማችን በመውሊድ ዙሪያ ካለው ሁኔታ አንጻር ሚዛን የሚደፋው ምክንያት ግን የመጀመሪያው ምክንያት ይመስላል፡፡

ባጠቃላይ መውሊድ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ይፋዊ በሆነ ሁኔታ ቢከበርም ከመነሻው ጀምሮ እስከሁን ድረስ በከበራው ላይ ውዝግብ አለ፡፡ በመሆኑም መውሊድ መከበር አለበት

የለበትም በሚለው ጉዳይ የሚንጸባረቁ ሁለት አይነት የአስተሳሰብ ፈለጎች አሉ፡፡ መውሊድ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በበርካታ ሀገራት የሚከበር ቢሆንም በዓለም በሚገኙ ሁሉም ሙስሊሞች ዘንድ ይከበራል ማለት ግን አይደለም፡፡ ምክንያቱም መውሊድ መከበር የለበትም በማለት በዓሉን የማያከብሩ በርካታ ሀገሮች እና ግለሰቦች አሉ፡፡ የመውሊድ በዓል መከበር አለበት የለበትም በሚለው ጉዳይ ላይ ውዝግብ በሰፊው መኖሩን Gori (2010፣51-52) ያስረዳሉ፡፡ የGori ሀሳብ በመውሊድ ክበራ ላይ በሙስሊሞች ዘንድ ልዩነት መኖሩን ያሳያል፡፡ የGoriን ሀሳብ Ostebo (2012፣181) ይጋሩታል፡፡

የመጀመሪያው አስተሳሰብ መውሊድ መከበር አለበት የሚለው የአስተሳሰብ ፈለግ የሚያራምደው ቡድን ነው፡፡ ሁለተኛው አስተሳሰብ ደግሞ መውሊድ መከበር የለበትም ክልክል (ቢድዐህ) ነው የሚሉት ናቸው፡፡

## 4.2. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ርእስ ስር ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራረቢነት ያላቸው ቀደምት ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ መውሊድ ከፎክሎር አንጻር በፒ.ኤች ዲግሪ ደረጃ ላይ የተደረገ ጥናት በብዛት ማግኘት አልተቻለም፡፡ ነገር ግን በስነ መለኮት፣ በስነሰብ እና በታሪክ የትምህርት ዘርፍ ከትምህርት ክፍላቸው ትኩረት አቅጣጫ አንጻር መውሊድን ዳሰዋል፡፡ ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

Yasuo and Ishihara (2009) “On the Filming of “Pilgrimage to Ya’a” በሚል ርዕስ ባቀረቡት አጭር ጽሁፍ በሀገራችን በተለይ በኦሮሚያ ክልል በተለያዩ ቦታዎች ስለሚገኙ ትላልቅ ዓሊሞች እና ዓሊሞቹን መሰረት አድርገው ስለሚከበሩ በዓላት አትተዋል፡፡ Terje Østebo (2014) ደግሞ “CLAIMS FOR AUTHORITY AT THE SHRINE OF SHAYKH HUSAYN, ETHIOPIA” በሚል ርዕስ በጻፉት አጭር መጣጥፍ የባሌው ሼኽ ሁሴን ማንነት እና የመውሊዳቸውን አካባበር በአጭሩ አሳይተዋል፡፡ Ishihara (2009) “Spirit Possession and Pilgrimage. The Formation and Configuration of the Tijjānī Cult in Western Oromoland” በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ ባጠቃላይ Ishihara በጥናታቸው ሼኽ አልፋሪቅ አህመድ ኡመር ማን እንደሆኑ እና እሳቸውን

ለመዘየር የሚሄዱ ሰዎች እነ ማን እንደሆኑ እና ዚያራው እንዴት እንደሚከናወን እና ለምን እንደሚከናወን አሳይተዋል፡፡

በ2004 Z. FAREEN "Celebrating the prophet: religious nationalism and the politics of Milad-un-Nabi festivals in India" በሚል ርዕስ በህንድ የነብዩ ሙሀመድ መውሊድ እንዴት እንደሚከበር በአጭር መጣጥፍ አሳይተዋል፡፡ እንደ ጸሀፊው የረቢየል አወል መውሊድ በአሁኑ ዘመን በህንድ በተለያዩ ግዛቶች በተለያዩ ክብረበዓላዊ ሁኔታ በመከበር ላይ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ በ2010 ሀይደርባድ በምትባለው ከተማ በርካታ ሙስሊሞች እና የህንዱ እምነት ተከታዮች በተገኙበት እንደተከበረ እና በዚህ መውሊድ ከእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች ውጭ የሌላ እምነት ተከታዮችም እንደሚሳተፉበት ጽፈዋል፡፡ በህንድ መውሊድ በዋናነት የሚከበረው ቤተሰብን በመጠየቅ እና የተለያዩ ባህላዊ ምግብ በማዘጋጀት እና በመመገብ እንደሆነ ጥናቱ ያሳያል፡፡ በመውሊድ በፖለቲካ እና በሌሎች ጉዳዮች የተጨቆኑ ሰዎች ተሰባስበው የሚወያዩበት እና የየተለያዩ ባህሎቻቸውን የሚያንጸባርቁበት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ መውሊድ ምንም እንኳን እነዚህ ጠቀሜታዎች ቢኖሩትም በአሁኑ ዘመን ክልክል ነው በማለት የሚያወግዙት ሰዎች(ወሀብያዎች) እየተበራከቱ መምጣታቸውን ጥናቱ ያስገነዝባል፡፡

Bronislav Ostřanský በ2008 "Egyptian mawlids in the context of contemporary Sufi spirituality" በሚል ርዕስ በግብጽ መውሊድ እንዴት እንደሚከበር በአጭር መጣጥፍ አሳይተዋል፡፡ ጸሀፊው በጥናታቸው መውሊድ በግብጽ ከ13ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ እንደሚከበር ጽፈዋል፡፡ ይህ መውሊድ ከሀገሪቱ ከተለያዩ አቅጣጫዎች የተሰባሰቡ የሱፊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ተሰብስበው በጋራ እንደሚያከብሩ ያስረዳሉ፡፡ ጸሀፊው አያይዘውም በግብጽ በርካታ ቅዱሳን ወይም ወሊዮች ባረፉበት ቦታ መውሊድ የሚከበር ሲሆን ከእነዚህ መካከል አህመድ አል-ባዳዊ እና ኢብራሂም አድ ዳሱቂ የሚባሉ ወሊዮች ዘንድ ግን መውሊድ በበለጠ ሁኔታ ይከበራል፡፡ በእነዚህ መውሊድ መከበሪያ ቦታዎች በረከትን አገኛለሁ በማለት ስለ ወልዮቹ ገድል እየተነገረ፣ ዚያራ እየተደረገ እና ሃይማኖታዊ ክንውን የሚከናወን ቢሆንም ድርጊቱን የሚነቅፉ እንዳሉ ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በርካታ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንደሚካሄድ ገልጸዋል፡፡ ጸሀፊው በአሁኑ ዘመን በግብጽ የሚከበሩ መውሊዶች የቁሳቁስ እጥረት እያጋጠማቸው እንደሆነ በማስረዳት ጥናታቸውን አጠቃለዋል፡፡

እነዚህን ጥናቶች ለምሳሌ ያክል አቀረብኩ እንጂ በስነሰብ እና በስነ መለኮት ትምህርት ዘርፍ ጥናቶች በክብረ በዓል እና መንዙማ ላይ ተሰርተዋል፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ጥናቶች በተለያዩ ጆርናሎች በመጣጥፍ መልክ የቀረቡ ናቸው፡፡ ከነዚህ መጣጥፎች በተጨማሪ በሀገራችንም ሆነ በዓለማችን መውሊድ ላይ ጥናቶች ተካሄደዋል- ምንም እንኳን ትኩረታቸው ፎክሎራዊ ጉዳይ ማሳየት ባይሆንም፡፡ ከዚህ በመቀጠል መውሊድን ትኩረታቸው አድርገው የተጠኑ እና ሌላ ጉዳዮችን ሲያጠኑ መውሊድን የዳሰሱ የመረቂያ ጥናቶችን እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

በ2009 ዓ.ም መሀመድ አሊ "አውሊያና የአውሊያ ስርዓት (ሱፊዝም) ፎክሎር ትንተና በቦረና-ወሎ" በሚል ርዕስ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሄዷል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ "አውሊያና የአውሊያ ስርዓት (ሱፊዝም) ፎክሎር ትንተና በቦረና-ወሎ ህብረተሰብ ጋር ያለው ግንኙነት እና የሚሰጠው ፋይዳ ምን እንደሆነ መግለጽ እና መተንተን" የሚል ነው፡፡ ለጥናቱ የሚሆን መረጃ በአንደኛ እና በሁለተኛ ደረጃ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ከሰበሰበ በኋላ በክዋኔ፣ በተግባራዊ እና በስነ ትርጓሜ ንድፈ ሀሳቦች ጥናቱን ተንትኗል፡፡ ይህ ጥናት በአስር ምዕራፎች ተተንትኖ የቀረበ ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር የሚመሳሰለው ስለመውሊድ በጻፈበት ምዕራፍ ነው፡፡ አጥኚው በወሎ በሶስት ቦታዎች መውሊድ እንዴት እንደሚከበር አሳይቷል፡፡ በእነዚህ ቦታዎች መውሊድ የሚያከብሩ ምዕመናን ከተለያዩ ቦታዎች እንደሚሰባሰቡ እና ዚክር፣ መንዙማ፣ ዝያራ፣ ስጦታ መስጠት፣ ከሰዎች ተገሎ በአንድ ቦታ ብቻ ተቀምጠው አላህን መማጸን እና ሌሎቹም ክንውኖች እንደሚከናወን ጥናቱ ያሳያል፡፡

የመሀመድ ጥናት መውሊድን እንደ አንድ ርዕሰ ጉዳይ መመልከቱ ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ ነገር ግን አጥኚው በመረጣቸው የመውሊድ መከበሪያ ቦታዎች መውሊድ እንዴት እንደሚከበር ቅደም ተከተሉን ተከትሎ ለፎክሎር ትኩረት ሰጥቶ ከመመልከት አንጻር ክፍተት እንዳለበት ተመልክቻለሁ፡፡ ምክንያቱት አንድ ክብረ በዓል ሲነሳ በዋናነት ስነ ቃል መነሳቱ አይቀርም የመሀመድ ጥናት በመውሊድ ክብረ በዓል ላይ ሆኖ ሳለ ለመንዙማ፣ ለምርቃት፣ እና ለቁሳዊ ጉዳዮች ብዙም ቦታ አልሰጠም፡፡ ባጠቃላይ መውሊድን በሚገባ ጥናቱ አሳይቷል ማለት ይከብዳል፡፡ አጥኚው መስክ ወደ ወሎ ቦረና በመሄድ ጥሬ መረጃ ሰብስቦ ከመተንተን ይልቅ ለጽንሰ ሀሳብ እና ለንድፈ ሀሳብ ትኩረት የሰጠ ይመስላል፤ ይህ በመሆኑም የትወራ ክፍሉ ጠንከር ብሎ የጥሬ መረጃ ክፍሉ ግን የሳሳ ይመስላል፡፡

በ2009 “The Structure of Wolof Sufi: Oral Narratives: Expanding the Labovian and Longacrean Model to Accommodate Wolof Oral Tradition” በሚል ርዕስ በሴኔጋል የሱፊ ተረኮች ላይ Mamarama Seck ለሶስተኛ ዲግሪ ጥናት አካሂዷል፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የወሎፍ ሱፊ ተረኮች ያላቸውን ደረጃ Pre-stage, Abstract, Orientation, Complication እና Evaluation የሚበሉትን መርምሮ ማሳየት ነው፡፡ አጥኚው በጥናቱ ዳራ ምትክ መግቢያ እና ሥነ ዘዴ (Methodology)፣ የተመረጡ ተረኮች እና የጥናቱ አደረጃጀት ቀርበዋል፡፡ በመቀጠልም ተረክ (Narrative) በሚለው አቢይ ርዕስ የተለያዩ ንድፈ ሀሳባዊ ሞዴሎች ቀርበዋል፡፡ አጥኚው የሱፊ ተረኮች የሚተረኩባቸው መውሊድን ጨምሮ የተለያዩ ክብረ በዓለትን ተመልክቷል፡፡ እንዲሁም የወሎፍ ሱፊ ተረኮች በሚለው አቢይ ርዕስ የተረኮቹ ባህላዊ አውድ እና ክዋኔ በሚመለከት በስፋት ቀርቧል፡፡ የእኔ ጥናትም ከዚህ ጥናት የሚቀራረበው በዚህ ርዕስ ላይ ነው፡፡ ምክንያቱም በሱፊዎች ዘንድ የሚነገሩ ተረኮችን በመሰብሰብ ተንትኗል፡፡ እኔም ምንም እንኳን ዋና ትኩረቴ መውሊድ ላይ ቢሆንም ከአልከሶ መውሊድ ጋር የተያያዙ ተረኮችን በመሰብሰብ ተንትኛለሁ፡፡

ባጠቃላይ ለእኔ ጥናት እና ሌሎቹ ጉዳዮች ከተመለከትኳቸው ጥናቶች አንጻር ዓላማውን ሙሉ በሙሉ ከማሳካት አንጻር፣ ግልጽ የሆነ መረጃ መሰብሰቢያ እና መተንተኛ ንድፈ ሀሳብ ከመጠቀም አንጻር ጥሬ መረጃዎችን ግልጽ በሆነ ቋንቋ እና መንገድ ከማቅረብ አንጻር ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ የMamarama Seck ጥናት ጠንካራ ሆኖ አግቼዋለሁ፡፡ ነገር ግን የመረጃ አሰባሰቡን ስናይ መረጃ የተሰበሰበው በቃለ መጠይቅ እና በሰነድ ፍተሻ ነው፡፡ በጥናቱ በጥናቱ ክብረ በዓላትን የዳሰሰ በመሆኑ ምልከታ እና ሌሎች የመረጃ መሳሪያዎችን እንደተጠቀመ ግልጽ በሆነ ሁኔታ አለማስቀመጡን እና ስለዘዴዎቹ አስፈላጊነት እና ተገቢነት ማስረጃን መሰረት ያደረገ ገለጻ አለማድረጉ እንደ ክፍተት ተመልክቼያቸዋለሁ፡፡ በዚህ ጥናት አሉ የምላቸውን ክፍተቶች በእኔ ጥናት ሞልቻለሁ፡፡

ገመቹ ጀማል ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያነት “Pilgrimages and Syncretism: Relgious Transformation among the Arsi Oromo Of Ethiopia” በሚል ርዕስ በ2013 ጥናት በ Tromsø ዩኒቨርስቲ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት አካሂዷል፡፡ የገመቹ ጥናት ሰባት ምዕራፎች አሉት፡፡ ገመቹ መጀመሪያ አጠቃላይ ጥናቱን አስተዋውቋል፡፡ በመቀጠልም ስለ ኦሮሞ ታሪክ እና ባህል ጥናቶች ምን እንደሚሉ ከዳሰሰ በኋላ ወደ ድሬ ሼኽና ሁሴን የሚደረግ ጉዞን፣ ስለ ሼኽና ሁሴን ማንነት፣ በአካበቢው ስለ ሚከበሩ ክብረ በዓላት እና አዮ

ሞሚና "Aayyoo Momina" ማንነት እና ስለ ክብረ በዓላቸው ምንነት በሰፊው አትቷል። ከዚህ በተጨማሪ የተወሰኑ ቃል ግጥሞችን እና አፈ ታሪኮችን እና ስለ እሬቻ በዓል ምንነት እና የእሬቻ አይነቶችን ዳሷል።

ገመቹ በጥናቱ ከመስክ የሰበሰበውን መረጃ የተነተነው ከምዕራፍ ሶስት ጀምሮ ነው። በዚህ ምዕራፍ በአካባቢው ቅዱስ ከሚባሉ ወንዶች መካከል ድሬ ሼኸና ሁሴን እና ከሴቶች ደግሞ አዮ ሞሚና "Aayyoo Momina" በመምረጥ ስለ ማንነታቸው እና ስለ ክብረ በዓላቸው አከባበር አሳይቷል። በዚህ ምዕራፍ ድሬ ሼኸና ሁሴን ወደ ባሌ እንዴት እንደመጡ እና እሳቸው ሲወለዱ ስለታዩ ተአምራቶች ያብራራል። እንደ ገመቹ አገላለጽ በአርሲ እና በባሌ እስልምና እንዲስፋፋ ያደረጉት ድሬ ሼኸና ሁሴን በመሆናቸው በአካባቢው ከፍተኛ ተቀባይነት እንዳላቸው ይገልጻል። በመሆኑም በየጊዜው እሳቸውን ለማስታወስ መውሊድ በሀረም ቸው ይከበራል። ባጠቃላይ የጥናቱ ትኩረት አርሲ ኦሮሞዎች እና የተለያዩ ባህላዊ ክብረ በዓላቸው ላይ ነው።

የገመቹ ጥናት የራሱ የሆነ ጥንካሬ እና ክፍተት አሉት። ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል መስክ ከመሄዱ በፊት ስለ ኦሮሞ ብሔረሰብ የሚያትቱ የተለያዩ ጽሁፎችን ተመልክቷል። እንዲሁም የቀደምት ጥናቶች ዳሰሳ አካሂዷል። መስክ ላይ ደግሞ ምልክታ እና ቃለ መጠይቅ አካሄዷል። በመስክ ቆይታው ከከበራው በተጨማሪ ለአፈ ታሪኮች እና ለቃል ግጥሞች ትኩረት ሰጥቷል። እናዚህ እና ሌሎቹም ነጥቦች የገመቹን ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ያመሳስሉታል። ከክፍተቶቹ መካከል የጥናቱ ዓላማ ምን እንደሆነ አልተገለጸም፣ ጥናቱ የሚመልሳቸው ጥያቄዎች የሉም፣ መረጃ ከሰበሰበ በኋላ በምን ስልት እና ንድፈ ሀሳብ እንደሚተነትን አያሳይም። መስክ ላይ ደግሞ መረጃ ሲሰበሰብ ስለ አንድ ርዕሰ ጉዳይ አንድ መረጃ አቀባይ የነገረውን መረጃ በሌላ መረጃ አቀባይ ለማረጋገጥ ስላደረገው ጥረት ምንም አላለም፣ በአጠቃላይ ከባህላዊ ክብረ በዓላት መካከል አንዱን ብቻ በመመረጥ በጥልቀት መርምሮ ከማቅረብ ይልቅ የተለያዩ ክብረ በዓላትን በወፍ በረር ቅኝት የቃኛቸው ይመስላል የሚሉት እንደ ክፍተት ተመልክቼያቸዋለሁ። በመሆኑም እነዚህ ክፍተቶች በእኔ ጥናት የሚሞሉ ይሆናል።

AMIRA KEDIR በ2014 እ.ኤ.አ "THE QATABRÉ SHEIKH, MAWLĪD CELEBRATION AND INTRA-FAITH DEBATE ON THE MAWLĪD

CELEBRATION" በሚል ርእስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በስነሰብ ትምህርት ክፍል ጥናት አካሂዳለች፡፡ የአሚራ ጥናት ዋና አላማ የቃጥባሬ መውሊድ አከባበር እና በከበራው ዙሪያ ያለውን ውዝግብ ማሳየት ነው፡፡ ይህን አላማ ከግብ ለማድረስ መረጃ በቃለ መጠይቅ እና በምልከታ በማሰባሰብ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተጠቅማ ተንትናለች፡፡ የአሚራ ጥናት ዋና ዋና ነጥቦች የሚከተሉት ናቸው፡፡ የቃጥባሬ መውሊድ የሚከበረው በረቢየል አወል ውስጥ ነው፡፡ ይህ ወር የተመረጠበት ምክንያት ነቢዩ ሙሀመድ የተወለዱበት ወር በመሆኑ ነው፡፡ ይህ በዓል ከ1942-1949 በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጧል፡፡ የበዓሉ ተሳታፊዎች የአካባቢው ተወላጆች ብቻ ሳይሆኑ ከሀገሪቱ የተለያዩ ክፍሎች የሚሰባሰቡ ናቸው፡፡ በበዓሉ በብዛት የሚሳተፉት ወንድ እና ሴት አዛውንቶች ሲሆኑ ወጣቶች ሰለፊያዊ አስተሳሰብ ስላላቸው መውሊዱን አያከብሩም በማለት ጥናቷን አጠቃላለች፡፡

የአሚራ እና የእኔን ጥናት በተወሰነ ደረጃ ተመሳስሎ እና ልዩነት አላቸው፡፡ ከሚያመሳስሏቸው ጉዳዮች መካከል ሁለቱም ጥናቶች ትኩረታቸው መውሊድ ላይ ነው፤ መውሊድ መከበር አለበት የለበትም የሚለውን ውዝግብ ያሳያሉ፡፡ እንዲሁም የበዓሉ መከበር ለምዕመናን የሚሰጠውን ፋይዳ ያብራራሉ፡፡ ሁለቱን ጥናቶች በነዚህ ነጥቦች ቢመሳሰሉም በሚከተሉት ነጥቦች ይለያያሉ፡፡ አሚራ በጥናቷ በመውሊድ በዓል የሚባሉ መንዙማዎችን አልተመለከተችም፡፡ በአብላጫ መውሊዶች የሚገኙት እና ከማህበረሰቡ ለየት ያለ ባህርይ ስላላቸው አናጂናዎች (ገሪቦች) ትኩረት አልሰጠችም፡፡ በበዓሉ ለምዕመናን ስለሚዘጋጀው ምግብ እና ሌሎችም ቁሳቁሶች ማብራሪያም ሆነ ስለቁሶቹ ትርጓሜ አላቀረበችም፡፡ በመጨረሻም በመስጂድ ቅጥር ግቢ ውስጥ ስላሉ ኸለዋዎች (ዳሶች) ምንም ያለችው ነገር የለም፡፡ በአጠቃላይ የአሚራ ጥናት አላማ የመውሊዱን አከባበር ማሳየት ቢልም ማሳየት የሚገባትን ጉዳዮች (ስነቃሎች፣ መንዙማዎች፣ ቁሳቁስ፣ ምግቦችን ወዘተ) በሚገባ አላሳየም ማለት ይቻላል፡፡ ስለዚህ እነዚህና ነጥቦች በአሚራ ጥናት ያልተተኮረባቸው ነጥቦች ሲሆኑ በእኔ ጥናት ግን ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡[34]

ERMAN HARUN በ2016 "THE ROYAL MAWLID CEREMONIES IN THE OTTOMAN EMPIRE (1789-1908)" በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦቶማን የአመራር ዘመን የረቢየል አወል መውሊድ የአከባበር ስርዓት ማሳየት ነው፡፡

[34] ስለ አናጂናዎች ወይም ገሪቦች በቃጥባሬ መውሊድ ላይ እንደሚሳተፉ በበዓሉ የታደሙ መረጃ አቀባዩ ገራድ ኑርሰቦ ነግረውኛል፡፡

አጥኚው በዚህ ጥናቱ የረቢየል አወል መውሊድ መቼ መከበር እንደተጀመረ፣ በቱርክ በኦቶማን የአመራር ዘመን እንዴት እንደተጀመረ እና በየጊዜው የመውሊዱ የአከባበር ሁኔታ ምን እንደሚመስል ለማሳየት ሞክሯል፡፡ በመሆኑም ከ1708 እስከ 1908 ድረስ በኦቶማን የአመራር ዘመን የሰነድ ፍተሻ በማከሄድ እንዴት እንደተጀመረ እና የአከባበር ስርዓቱ ምን እንደሚመስል አሳይቷል፡፡ ነገር ግን ይህ ጥናት እንደ አንድ ጥናት ስንመለከተው በርካታ ክፍተቶች አሉበት፡፡ ምክንያቱም የጥናቱ ጠቀሜታ ምን እንደሆነ፣ የንደፈ ሀሳብ፣ የመረጃ አሰባሰብ እና አተናተን ምን እንደሚመስል አላሳየም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ጥናቱ ምን ግኝት ላይ እንደደረሰ ምንም ያለው ነገር የለም፡፡

በ2006 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል አብዱልረህማን ፋንታሁን “የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼኽ ዳንግላ) የመውሊድ በዓል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት” በሚል ርእስ ጥናት አካሂዷል፡፡ የአብዱልረህማን ጥናት አምስት ምዕራፍ አለው፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ የዳንግላ መውሊድ አከባበር ማሳየት እና በበዓሉ የሚቀርቡ ቃል ግጥሞችን መተንተን ነው፡፡ አጥኚው ዓላማውን ከግብ ለማድረስ መረጃ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ሰብስቧል፡፡ የተሰበሰበው መረጃ በአይነታዊ የመተንተኛ ዘዴ ተንትኖ ቀርቧል፡፡ አጥኚው በጥናቱ በዋናነት ከተመለከታቸው ነጥቦች መካከል በመውሊድ በሚከበርበት ወቅት ዚያራ፣ ዱኣ፣ ምርቃት እና መንዙማ እንደሚኖር ያስረዳል፡፡ እነዚህ ክንውኖች የሚከናወኑበት ቦታ ሀረም ተብሎ እንደሚጠራ እና ለምዕመናኑ ምግብ እንዴት እንደሚዘጋጅ በተወሰነ ደረጃ አሳይቷል፡፡ መንዙማ በሚባልበት ወቅት ምዕመናኑ ዲቤ ስለሚጠቀሙ ለበዓሉ ድምቀት ይሰጠዋል የሚሉ እና ሌሎችንም ነጥቦች ዳሷል፡፡ አብዱልረህማን ጥናቱን ሲያጠቃልል በመውሊድ በዓል ጊዜ የሚባሉ መንዙማዎች ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ፎክሎራዊ ጠቀሜታ ስላላቸው በሰፊው ቢጠኑ መልካም ነው የሚል የግል አስተያየት አቅርቧል፡፡

የአብድልረህማን ጥናት የመውሊድ በዓል ከቅድመ ዝግጅቱ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለውን ሂደት ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ አያሳይም፡፡ በዓሉ ከወጣ በኋላ በአካባቢው ስላለው ሁኔታ ምንም ያለው ነገር የለም፡፡ ጥናቱ ለበዓሉ ታዳሚዎች ምግብ እንደሚዘጋጅ ቢጠቁምም አዘገጃጀቱ፣ አቀራረቡ እና አመጋገቡ ምን እንደሚመስል ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ አያብራራም፡፡ ነገር ግን እነዚህ ነጥቦች በወፍ በረር ቅኝት በሚመስል መልክ

መቅረባቸው ከእኔ ጥናት በተወሰነ ደረጃ ያመሳስለዋል፡፡ የአብድልረሀማን ጥናት በበዓሉ ጊዜ ለመገልገያነት ስለሚውሉ ቁሳቁሶች ትኩረት በመስጠት ከነትርጓሜያቸው አላቀረበም፡፡ እንዲሁም የመረጃ መተንተኛ ትዮሪው ምን እንደሆነ ከለመግለጹ ባሻገር የንድፈ ሀሳብ እና የጽንሰ ሀሰብ መምታታት ይስተዋልበታል፡፡ በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች በእኔ ጥናት ለመሙላት ሞክሬያለሁ፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው በተለያዩ ደረጃዎች የተጠኑ ጥናቶች የየራሳቸው የሆነ ጥንካሬ እና ክፍተት አለባቸው፡፡ የአንዳንዶቹ ክፍተት የስነ ዘዴ ሲሆን የአንዳዶቹ ደግሞ ለማሳካት አስበውት የተነሱትን ዓለማ ከግብ አለማድረስ እና አንዳንዶቹ ለማጥናት ያሰቡትን ርዕሰ ጉዳይ በሚገባ እና በጥልቀት ያለመመልከት ነው፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ግልጽ የሆነ ስነ ዘዴ እና ንድፈ ሀሳብ የሌላቸው ናቸው፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ አጥኚዎቹ ሲያጠኑ ጥናት በሚያካሄዱባቸው ቦታዎች ላይ የሚኖረውን ማህበረሰብ ከማሳየት አንጻር የጎላ ክፍተት ተመልክቼባቸዋለሁ፡፡ እነዚህን ክፍተቶች መመልከቴ የአልከሶ መውሊድን ሳጠና በአልከሶ እና አካባቢው ለሚኖሩ የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ትኩረት እንድሰጥ አድርጎኛል፡፡ በመሆኑም ከላይ በተመለከትናቸው ጥናቶች የተስተዋሉት ክፍተቶች በዚህ ጥናት ለመሙላት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

### 4.3 የጥናቱ የንድፈ ሀሳብ ማዕቀፍ

በዚህ ንኡስ ርእስ ስር ይህን ጥናት ለማጥናት ፋይዳ ያላቸው ንድፈ ሀሳቦች ይቀርባሉ፡፡ ንድፈ ሀሳቦቹም ክዋኔያዊ፣ ስነ ፋይዳዊ፣ እና ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳቦች ናቸው፡፡ ስለ እነዚህ ንድፈ ሀሳቦች ምንነት ማብራሪያ ካቀረብኩ በኋላ በዚህ ጥናት በምን ሁኔታ አገልግሎት እንደሰጡ እንመለከታለን፡፡

## 4.3.1 የክዋኔ ንድፈ ሀሳባዊ ምንነት እና አተገባበር

በዚህ ጥናት ከመስክ የተገኙ መረጃዎች በዋናነት የተተነተኑት ፎክሎርን ለማጥናት ዋነኛ መንገድ ሆኖ ባገኘው የክዋኔ ንድፈሀሳብ (performance theory) ስነ ዘዴያዊ መርሆዎች ነው፡፡ የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ ተጠኚ ተለዋዋጮችን የሚያጠናው በአውዳቸው ነው (Dundes, 1980; Bauman, 1983; Amos, 1993; Haford, 1995; Sims and Stephens, 2005)፡፡

በክዋኔ ንድፈሀሳብ ማንኛውም የፎክሎር ጥናት የሚያተኩረው በሦስት የፎክሎር አላባውያን ላይ ነው። በክዋኔ ጥናት ውስጥ አይቀሬ የሆኑትና የማንኛውም የፎክሎር አሀድ መሰረታዊ አላባ የሚባሉት ተጠኚ ፎክሎራዊ አሀድ (text)፣ ፎክሎራዊ አሀዱን አጓቢና አድማቂ ማስዋቢያዎች (texture)፣ እና የንባቦቹን ፍቺና አከዋወን የሚወስነው አውድ (context) ናቸው (Dundes፣1980)። በክዋኔ ንድፈሀሳብ ውስጥ ሦስቱም አላባውያን አይቀሬና አይነጣጠሌ ናቸው። አንዱን ካንዱ ለመለየት አስቸጋሪ ነው። አንዱ ካላንዱ ህልውና የለውም።

ቀደም ባሉ የፎክሎር ጥናቶች ውስጥ እንደ ፎክሎራዊ ተጠኚ አሀድ ብዙውን ጊዜ የሚታዩት የስነቃል ይዘቶች ናቸው። ፎክሎራዊ አሀድ ሲባልም የሚያመለክተው የሚነገሩ ቀልዶችን፣ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን፣ አፈታሪኮችን፣ ተረቶችን፣ ወዘተ. የያዙ የፎክሎራዊ አሀዶችን ይዘት ነው። ለምሳሌ በአንድ ቀልድ ውስጥ ፎክሎራዊ አሀድ የምንለው በቃላዊ ድምፆች ቅንብር ተደርሶ የተነገረውን የቀልድ ይዘት ነበር። ነገር ግን በአሁኑ ዘመን የፎክሎር ጥናቶች ውስጥ ፎክሎራዊ አሀድ ብዙ ነገሮችን የሚይዝ ፅንሰሀሳብ ሆኖ እናገኘዋለን (Sims and Stephens, 2005: 134)።

ተጠኚ ፎክሎራዊ አሀድ አያሌ የፎክሎር ቅርፆችን፣ አይነቶችንና ገፅታዎችን ሊያመለክት ይችላል። በፎክሎር ጥናቶች ውስጥ በፎክሎራዊ አሀድነት የሚጠናው ነገር እንደየአትኩሮታችን ማረፊያ ርዕሰ ጉዳዮች ይለያያል። ጥናታችን ለመተንተን ያሰበው ክዋኔን ከሆነ ክዋኔ ለዚህ ጥናት ፎክሎራዊ አሀዱ ነው። በቃላዊ የፍቅር ግጥሞች ውስጥ የትንተና ምርጫችን ግጥሞቹ ከሆኑ ተጠኚ አሀዳችን የግጥሞቹ ስንኞች ነው።

በዚህ አተያይ መሰረት ፎክሎራዊ አሀድ ከአንድ የፎክሎር አሀድ፣ ነጠላ ይዘት ጀምሮ ውስብስብነት እስካላቸው አያሌ የፎክሎር አይነቶችና ገፅታዎች ሊያካትት የሚችል ፍቺ አለው። በጥቅሉ ተጠኚ ፎክሎራዊ አሀድ ቃላትን፣ ቁሶችን፣ እሳቤዎችን፣ ድርጊቶችንና ጠባዮችን ሁሉ ሊያመለክት ይችላል።

'textures' በፎክሎራዊ አሀድ ላይ የሚጨመሩ፣ የሚያጅቡ፣ የሚያደምቁና የሚያስውቡ እንዲሁም በፎክሎራዊ አሀዱ ላይ ለውጥ ማስከተል የሚችሉ የክዋኔ አላባውያን ናቸው። እነዚህ አላባዎች የክዋኔውን ተሳታፊዎች አጠቃላይ ሁነቶችና አኳኋኖች፣ የመቼት አጠቃላይ ገፅታ፣ ድምቀቶችና ድባቦች፣ በክዋኔው ውስጥ የሚካተቱ ቁሶችን አጠቃቀም፣

የሚደረጉ እንቅስቃሴዎችን፣ የሚመለከቱ ናቸው፡፡ በእነዚህ ውስጥ ቁሳዊ፣ ሥነልሳናዊ፣ አካላዊ የተግባቦት ስርዓቶች ገጽታዎች ይካተቱባቸዋል፡፡

በክዋኔ ወቅት የሚታዩና የሚሰሙ ቃላት፣ ዜማ፣ ድምፀት፣ ድግግሞሽ፣ እፎይታዎች፣ እቃዎች፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎች፣ የከዋኙ የአቀራረብ ስልት፣ እንዲሁም የተቀባዮቹ ስሜት እንዴት እንደተንፀባረቀ የሚገለፅበት አላባ እንደሆኑ Dundes (1980፣25-26) ያሰረዳሉ፡፡ ከዋኙና ተሳታፊው አንድን ፎክሎራዊ አሀድ ሲከውኑ በራሳቸው ዘዴ ስለሆነ ክዋኔውን ለማሳመርም ሆነ ለማድመቅ ብለው ሌሎች ተጨማሪ ነገሮችን ይፈጽማሉ፡፡ ስለዚህ ዋናው የክዋኔ ገጽታ ይቀየራል፡፡ በመሆኑም ቴክስቸር በፎክሎራዊ አሀድ ላይ ለውጥ የሚያመጡ ናቸው፡፡

ክዋኔ አውዳዊ ነው፡፡ ክዋኔ በቦታ፣ በጊዜና በሁኔታ የተወሰነ ነው፡፡ ማንኛውም የፎክሎር ቅርጽ ያለቦታው ያለጊዜውና ያለሁኔታ አይከወንም አይኖርም፡፡ አካላዊ ኑረቱና ተግባቦታዊ ፋይዳው በዚያው ባህሉ በወሰነለት ወቅትና ሁኔታ ውስጥ የተቀነበበ ነው፡፡ በሌላ አባባል እያንዳንዱ የፎክሎር ክዋኔ በጊዜ ውሱን በቦታ ውሱን እና በሁኔታ ውሱን ነው፡፡ Mary Haford (1995፡ 328) አውድ "contecxere" ከሚለው የላቲን ቃል እንደመጣ ፍቺውም "to weave together, interweave, join together compose" ማለት እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ብያኔ እንደምንረዳው አውድ የነገሮችን የእርስ በርስ ተያያዥነት፣ ድርና ማግነት፣ በስልት ተጠላልፎና ተወሳስቦ በመገኘት አንድን ተጨባጭ ነገር መግለፅ የመቻልን ብቃት ያሳያል፡፡

ከ1970ዎቹ በፊት የነበሩት የፎክሎር ጥናቶች ትኩረት በአብዛኛው ያተኩር የነበረው በፎክሎር ተተኳሪ አሀድ (text) ላይ ነበር፡፡ የአጠናን ስነ ዘዴያቸውም አሀድ ተኮር (text-centered) ነበር፡፡ ክዋኔን ያጠኑት የነበረው ራሱን እንደቻለ ሁነት ሳይሆን ከፎክሎራዊ ውጤቶች ጋር አያይዘው እንደነበር Bauman (1984፣124) ያስረዳሉ፡፡ ክዋኔ ራሱን እንደቻለ የፎክሎር ማዕከላዊ ማጠንጠኛ ተደርጎ መጠናት የጀመረው በ1970ዎቹ ውስጥ ነው፡፡ አሁን የምናቀውም የክዋኔ ንድፈ ሀሳብ መሰረቱ የተጣለው በRichard Bauman የ1984 Verbal Art as Performance ጥናት ውስጥ እንደሆነ እና ከRichard Bauman በተጫማሪ በፎክሎራዊ ክዋኔ ንድፈ ሀሳብ Ben Dan Amos እና Kirshenblatt-Gimblett እንደሚታወቁ Sims and Stephens (2005፣133) ያስረዳሉ፡፡ ከስነ-ሰብ የጥናት ዘርፍ

ደግሞ "Roger Abrahams፣ Cliford Geertz፣ Richard Schenner፣ Erving Goffman እና Victor Turner እንደሆኑ Bauman (1992: 47) ያስረዳሉ፡፡

ክዋኔ አንድን ክስተት ወይም ባህል ሲተገበር ድርጊቱን ማሳየት ነው፡፡ ክዋኔ የከዋኝ እና የታዳሚ የጋራ ተግባቦት እንደተጠበቀ ሆኖ የአከዋወን ሁኔታው ከቦታ ቦታ፣ ከዘርፍ ዘርፍ፣ ከከዋኝ ከዋኝ ወዘተ እንደሚለያይ Finnegan (1992:337)፣ Bauman (1992፣4)፣ Sims and Stephens (2005፣125)፣ ዘሪሁን (1996፣22) እና ፈቃደ (1991፣65) የሚጋሩት ሀሳብ ነው፡፡ እንደ Bauman (1992:61) አገላለጽ በክዋኔ ወቅት የሚከወነው ጉዳይ፣ ከዋኙ፣ ታዳሚው፣ በክዋኔው ወቅት በአካባቢው ያሉ ጉዳዮችን በሙሉ አጣምሮ የያዘ ጉዳይ ነው፡፡ በክወና ወቅት በአካባቢው ስላሉ ጉዳዮች ትኩረት መስጠት ክዋኔው አውዳዊ እንዲሆን ከማስቻሉ ባሻገር ታዳሚው ክዋኔውን በአግባቡ እንዲረዳው ይረዳል፡፡ እንዲሁም Deborah(1995:430) ክዋኔ አንድን ነገር ውበት ባለው መልኩ ለመግለጽ የሚያገለግል ስነ ውበታዊ ቀመር መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ Deborah(1995፣480) አያይዘውም ክዋኔ ከዋኙና ታዳሚው በጋራ ተገናኝተው የሚፈጽሙት ተግባር እንደሆነና ታዳሚው የበለጠ እርካታ ለማግኘት ከማስቻሉ በሻገር ከዋኙ የውስጥ ስሜቱን በሚገባ ለመግለጽ እድል የሚፈጥርለት ሁኔታ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

አንድ ማህበረሰብ የሚያከብረውን ክብረ በዓል ስናጠና የአከዋወን ሁኔታውን ማጥናታችን የማይቀር ጉዳይ ነው፡፡ በክዋኔ የሚከወነው ጉዳይ የት፣ መቼ፣ ከማን ጋር፣ ለምን ተከወነ፣ ምን ይዘት አለው፣ በክዋኔው የሚስተዋሉ ቃላት፣ ድርጊቶች፣ ቴክስቸሮችና አውዶች ምን ገጽታ እንዳላቸው ለማወቅ ይረዳል፡፡ ክዋኔ ውስጣዊ እና ውጫዊ መዋቅሮች ያሉት እና ጥበባዊ በሆነ ኩነት የሀሳብና የስሜት ማስተላለፊያ ከመሆኑ በተጨማሪ ማንነትን ለሌላ ማሳያ ጥበብም ጭምር ነው፡፡ Rapport (1999፣37) "ክዋኔ የለም ማለት ክብረ በዓል የለም ማለት ነው" ይላሉ፡፡ ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ክብረ በዓል ያለ ክዋኔ ህልውና የለውም የሚለውን ነው፡፡

ፎክሎርን ለሚያጠና አንድ አጥኚ ክዋኔን ሲመለከት ሰዎች አንድን ድርጊት እንዴት እንደሚፈጥሩ፣ እንደሚለዋወጡ እና ከድርጊቱ መልእክት ጋር እንዴት እንደሚተዋወቁ መመልከት ይኖርበታል፡፡ የአንድን ፎክሎራዊ ጉዳይ ክዋኔ ለማጥናት ከግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው ሁለት መሰረታዊ አተያዮች እንዳሉ Bauman (1992፣5) ያስረዳሉ፡፡

እነሱም አንደኛው ማህበረሰቡ ጉዳዩን የሚያከናውነው ተስማምቶ ባዋቀረው ስርዓትና ደንብ መሰረት በመሆኑ ታዳሚው አዳዲስ ፎክሎሮችን የመፍጠር እድል ሊኖረው እንደሚችል የምንረዳበት ሀሳብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ ከዋኙ በተሳታፊዎች ብሎም በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚጠቀመው ቋንቋ፣ የአነጋገር ለዛ እና የአከዋወን ሁኔታ የሚያመላክት ሀሳብ እንደሆነ ምሁሩ ያስገነዝባሉ።

እንደ Finnegan (1992፣86) አገላለጽ ክዋኔ ከማህበረሰብ ባህል አንጻር የማህበረሰቡን አጠቃላይ ባህል ለማሳየት አይነተኛ መንገድ በመሆኑ እንደ ትዕምርት ልንመለከተው እንደምንችል ይገልጻሉ። ከዚህ ጋር አያይዘውም የአንድ ማህበረሰብ ባህል የማህበረሰቡን ባህል ቅርጽ፣ ይዘትና መዋቅር ለማወቅ የሚያስችል ትልቅ አቅም እንዳለው ያስገነዝባሉ። Finnegan (1992፣86) አያይዘውም ክዋኔ አጠቃላይ ከሰው ልጅ ባህል እና እንቅስቃሴ ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ክዋኔ ትይንታዊ ተግባቦት፣ ቅርጽ እና ይዘት አለው። ከፎክሎር ዘርፎች መካከል አንዱ የሆነው የስነቃል ተስተላልፎ በአንድ ጥበባዊ ስራ የተገደበ ሳይሆን ከአንድ ፈጠራ ወደ ሌላ ፈጠራ የሚሸጋገር እና ክዋኔው በሚከወንበት ወቅት ካለው ሁኔታ አንጻር የሚፈጠር እንደሆነ ያስረዳሉ። በፎክሎር ክዋኔን መሰረት ያደረገ ጥናት ለመከወኛ አጋጣሚ፣ ለከዋኝ፣ ለታዳሚ፣ ለቴክስት፣ ለአውድ፣ ለቅርጽ እና ለአስተያየት ትኩረት እንደሚሰጥ Finnegan (1992፡85)፣ Bauman (1992.290)፣ Goldstein (1964፣92) እና Sims (2005፣139) ይገልጻሉ።

ሀ. የመከወኛ አጋጣሚ፡- አንድን የፎክሎር ዘርፍ ለመከወን የግድ ከዋኝ እና ታዳሚ በመከወኛ ስፍራው መገኘት አለባቸው። ክዋኔ ያለታዳሚ ሊከወን ይችላል። ነገር ግን ክዋኔው ምሉዕ ሊሆን አይችልም፤ አልያም የፎክሎር አይነቱ የመከወኛ ቅርጹን ሊያጣ ይችላል። ከከዋኙ እና ከታዳሚው በተጨማሪ አንድን የፎክሎር ዘውግ ለመከወን የሚከወንበት አጋጣሚ ወይም ሰበብ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አንድ የፎክሎር ዘርፍ ያለ አንዳች ምክንያት ሊከወን አይችልም። ለምሳሌ የአንድን ማህበረሰብ የለቅሶ ክዋኔ ለመከወን ሰው መሞት አስፈላጊ ነው። የሰርግ ስነ ስርዓት ለመከወን ጋብቻ መኖር አለበት። የአልከሶ መውሊድን የከበራ ክዋኔ ለመከወን የአልከሶ በዓል መከበር አለበት። በአጠቃላይ ሌሎችንም የፎክሎር ዘውጎችን ብንመለከት የየራሳቸው የመከወኛ አጋጣሚ አላቸው። Finnegan (1992፡85) እና Sims (2005፣139) አንድ የፎክሎር ዘውግ ለመከወን ከፎክሎሩ ዘውጉ ባህርይ ጋር አብሮ የሚሄድ የመከወኛ ምክንያት ሊኖር እንደሚገባ ያስረዳሉ።

ለ. ከዋኙ፡- የአንድን ማህበረሰብ ባህል ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማሸጋገር አሻጋጋሪ ድልድይ ሆኖ የሚያገለግል አካል ያስፈልጋል፡፡ የትኛውም የፎክሎር ዘርፍ በመከወን ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ የሚችል አካል (ሰው) ከዋኝ እንለዋለን፡፡ ይህ ከዋኛ የአንድን ማህበረሰብ ባህል በአሁኑ ጊዜ ያለውን የአከዋወን ሁኔታ ለመጪው ትውልድ የሚያስተላልፍ ከመሆኑ ባለፈ በአሁን ጊዜ ላለው ታዳሚ የሚያቀርብ ነው፡፡ Finnegan (1992፣85) ስለ ክዋኔ ትኩረት ስንሰጥ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ከዋኝ ነው ካሉ በኋላ ከዋኙ የሚከውነው ብቻውን ነው ወይስ የሚያግዘው አካል አለ እና ክወናው የሚካሄደው በቡድን ወይስ በተናጠል ለሚለው ጉዳይ ጭምር ትኩረት መስጠት እንደሚያስፈልግ ያስረዳሉ፡፡ Goldstein (1964፣92) ደግሞ የከዋኙን የአከዋወን ስልት፣ ብቃት፣ ችሎታ፣ የቋንቋ አጠቃቀም እና አገላለጽ፣ የፊት ገጽታ፣ የአካል እቅስቃሴ፣ አለባበስ፣ አጋጊየጥ፣ በክወና ጊዜ ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህ ጥናት በበዓሉ ላይ ስነቃልም ሆነ ሌሎች የፎክሎር ዘርፎች የሚከውኑ ከዋኞች በክዋኔ ወቅት የሚያሳዩትን አጠቃላይ የአከዋወን ስርዓት ቀርቧል፡፡ ለምሳሌ መንዙማ በሚባልበት ወቅት ከዋኞቹ ምን ምን ቁሳቁስ ይጠቀማሉ፣ የአካል እንቅስቃሴያቸው እና የፊት ገጽታቸው ምን ይመስላል፣ ከዋኙ ስለሚከውነው ጉዳይ እውቀቱ እና ችሎታው ምን ያህል ነው፣[35] ዱኣ በሚደረግበት ወቅት ያለውን የአከዋወን ሁኔታ ምን ይመስላል እና ሌሎችም ነጥቦች ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

ሐ. ታዳሚ፡- ታዳሚ  አንድ የፎክሎር ዘውግ ሲከወን በቦታው ተገኝቶ የሚከታተል፣ የሚያዳምጥ፣ አልፎም የሚሳተፍ ነው፡፡ ታዳሚዎች በፎክሎር ክዋኔ ወቅት ትልቅ ሚና የሚጫወቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ታዳሚዎች ክዋኔ ውበት እንዲኖረው እና እንዳይኖረው የማድረግ ትልቅ አቅም አላቸው፡፡ ለምሳሌ ከዋኙ በጥሩ ሁኔታ የሚከውነው ከሆነ የበለጠ ጥሩ እንዲሆን ወይም ውበት እንዲላበስ ለማድረግ ከዋኙን ያግዛሉ፤ ያበረታታሉ፡፡ በተቃራኒው የከዋኙ የአከዋወን ሁኔታ ጥሩ አይደለም ብለው ካሰቡና የተለያዩ ምክንያቶችን መሰረት በማድረግ የበለጠ እንዲበላሽ ከፈለጉ ከዋኙን በመረበሽ እና በማጥላላት ክዋኔው ውበት እንዳይኖረው ሊያደርጉ ይችላሉ[36]፡፡ የታዳሚያን ሚና በክወና ወቅት ከዚህም ያለፈ ሊሆን ይችላል፡፡ የከዋኙ የአከዋወን ሁኔታ ካልተመቻቸው አልያም በክዋኔው ስሜት ውስጥ

---

[35] የከዋኙን እውቀት እና የአከዋወን ችሎታ መረዳት የተቻለው በክወና ወቅት በቦታው ከታደሙ ታዳሚያን ነው፡፡

[36] ለምሳሌ ከከዋኙ ሰው ጋር ጥሩ ግንኙነት የሌለው ሰው (ቡድን) በመከወኛ ስፍራው በመገኘት ከዋኙን በመረበሽ በጥሩ ሁኔታ እንዳይከውን እና በታዳሚው ተቀባይነት እንዳያገኝ ሊያደርግ ይችላል፡፡

ገብቶ ከዋኙን ወደ ጎን በመተው እራሱ መከወን ሊጀምር ይችላል፡፡ Bauman (1992፣25) ታዳሚ የነበረ ሰው በክዋኔው ተመስጦ ወይም አንዳች የሚገፋፋው ጉዳይ ሲያጋጥመው ወደ ተሳታፊ በኋላም ወደ ከዋኝነት ይሸጋገራል ይላሉ፡፡

ለምሳሌ በስልጤ ብሔረሰብ ባህል አንድ መንገደኛ መንገድ ሲሄድ ለቅሶ ካጋጠመው የሞተውን ሰው ባያውቀውም ለቅሶ ይደርሳል፡፡ እንዲሁም መንገድ ላይ አስክሬን ካጋጠመውም ሳይሸኝ ማለፍ ክልክል ነው፤ አስከሬኑን ከአልቃሹ ጋር በመሆን ይሸኛል፡፡ በዚህ ጊዜ መንገደኛው (ታዳሚ ነው) በአልቃሾቹና በሚቀርበው ሙሾ አማካኝነት ማን (ማንንም ሳይጠይቅ) እንደሞተ/ች፣ ዕድሜው/ዋ፣ ማህበራዊ ደረጃውንና አሟሟቱን ያውቃል፡፡ በዚህ ጊዜ ልቡ ይነካና ማልቀስ ይጀምራል፡፡ በዚህ ሁኔታ ከታዳሚ ወደ ከዋኝ[37] ሊሸጋገር ይችላል፡፡ Goldstein (1964፡95) አንድ በክዋኔ ላይ ትኩረቱን አድርጎ የሚያጠና ተመራማሪ የታዳሚዎች ሚና ምን እንደሚመስል ለመመልከት ከዋኔውን እንዴት ያበረታታሉ፣ ይደግፋሉ፣ ይቃወማሉ ወዘተ ለሚሉት ነጥቦች ትኩረት መስጠት አስፈላጊ መሆኑን ይግልጻሉ፡፡ ስለዚህ በአልከሶ መስጂድ እና አካባቢው ከዋኔ በሚካሄድበት ወቅት ከከዋኙ ባልተናነሰ ለታዳሚው ትኩረት በመስጠት ምልከታ አካሂጃለሁ፡፡

መ.ቴክስት፡- ቴክስት (texere) የሚለው የላቲን ቃል መሆኑንና መሸመን ወይም የእጅ ሙያ መስራት ከሚለው መምጣቱን Sims (2005፡19) ይገልጻሉ፡፡ ከፎክሎር አንጻር ስንመለከተው በአንድ የፎክሎር ዘርፍ ውስጥ የሚከወነው ርዕሰ ጉዳይ ቴክስት ልንለው እንችላለን፡፡ ለምሳሌ በአንድ የስነቃል ክዋኔ ውስጥ የሚባለው ወይም የሚነገረው ስነቃል ቴክስት ይባላል፡፡ እንደ Sims (2005፡20) አገላለጽ ቴክስት የሚለው ቃል ቃላትን፣ ቁሳቁሶችን፣ ሀሳቦችን፣ ወዘተ የሚያጠቃልል ሰፊ ጽንስ ሀሳብ ነው፡፡ አንድን የፎክሎር ቴክስት ቀድሞ ከነበረበት አውድ ልዩ ወደ ሆነው አውድ ብንወስድ የቴክስቱ ትክክለኛ ፍቺ ሊዛባ አልያም ሙሉ በሙሉ ትርጉሙን ሊያጣ ይችላል፡፡ በመሆኑም አንድን ቴክስት በተገቢው ሁኔታ ለመረዳት ቴክስቱን በአውድ በመሰብሰብ አውዳዊ በሆነ አኳኋን መተንተን ያስፈልጋል በማለት Ben-Amos (1993፡210-211) ያብራራሉ፡፡ በዚህ ጥናት በዋናነት ትኩረት የሰጣቸው ቴክስቶች በመውሊድ ከበራው ወቅት የሚፈጸሙ ስርአቶች፣ ስነቃሎች፣ ቁሶች፣ ዕምነቶች ወዘተ ናቸው፡፡

---

[37] በብሔረሰቡ በለቅሶ ጊዜ ዝም ብሎ እንባ ከማፍሰስ በአለፍ የተለያዩ የአካል ክፍሎችን በማንቀሳቀስ ማልቀስ እና  የሚች ጥሩ ባህርይ ማውሳት የተለመደ ነው፡፡

ሠ.አውድ:- አውድ አንድ የፎክሎር ቅንጣት የሚከወንበት ቦታ፣ ድርጊት፣ ድባብ፣ አጠቃላይ አካባቢውን ወዘተ የሚያጠቃልል ጽንሰ ሀሳብ ነው፡፡ እንደ Sims (2005፡137) አገላለጽ አውድ አንድ የፎክሎር ዘውግ ሲከወን በአካባቢው ያሉ ነገሮችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ በዋናነትም ሰዎችን፣ መቼቶችን፣ በክወና ወቅት የሚፈጠሩ አጋጣሚዎችን፣ አገላለጾችን፣ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ ሀሳቦችን ወዘተ አካቶ ይይዛል፡፡ ስለዚህ አውድ ሲባል አንድ ፎክሎር ሲከወን በዙሪያው ያሉ ጉዳዮችን በሙሉ ያጠቃልላል፡፡ አወድን የተለያዩ ምሁራን በተለያየ ጎራ ከፋፍለውታል፡፡ ከእነዚህም መካከል Bauman and Briggs (1990፡68) አውድን በስድስት ጎራ መድበው ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተውበታል፡፡ እነሱም አውዳዊ ትርጉም፣ ተቋማዊ አውድ፣ ማህበራዊ መሰረት፣ ተግባቦታዊ አውድ ፣ግለሰባዊ አወድ እና የሁኔታዎች አውድ መሆናቸውን ዘርዝሯል፡፡ አያይዘውም እነዚህን ስድስት ጎራዎች በሁለት ከፍለው ጠቅለል አድርገው ባህላዊ አውድ እና ማህበራዊ አውድ ብለው መድበዋቸዋል፡፡ እነ Bauman እነዚህ ሁለት ምድቦች በስራቸው ምን ምን ጉዳዮችን እንደሚያዙ አብራርተው በሰፊው አቅርበዋል፡፡ ከእነ Bauman በተጨማሪ Ben-Amos (1971፣9) ባህላዊ አውድ ትኩረቱ ቴክስት ወይም ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሲሆን ማህበራዊ አውድ ደግሞ በርዕስ ጉዳዩ ባለቤት (ማህበረሰቡ) ላይ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

ረ. ቅርጽ:- ሁሉም የፎክሎር ዘውጎች የየራሳቸው የሆነ የመከወኛ ቅርጽ አላቸው፡፡ ይህ ማለት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ፎክሎር የየራሱ የሆነ የአከዋወን ቅርጽ ወይም ሂደት አለው፡፡ አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን ተጀምሮ እስኪፈጸም ድረስ የራሱ የሆነ ቅርጽ ወይም የአካሄድ ቅደም ተከተል አለው ማለት ነው፡፡ እንደ Sims (2005፡95) አገላለጽ የፎክሎር ቅርጽ ማለት አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን የፎክሎሩ አጀማመር፣ ሂደት፣እና አፈጻጸምን ያካትታል፡፡ በዚህም ጥናት በበዓሉ ወቅት የሚከወን ማንኛውም ክዋኔ ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከ ፍጻሜው ድረስ ያለው ሄደት አውዱን በጠበቀ ሁኔታ ቅደም ተከተሉን ጠብቆ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

የዚህን ጥናት መረጃ መተንተኛ ሁነኛ ዘዴ ተብሎ የተመረጠው ክዋኔያዊ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ እነ Sims (2005፡138) "ክብረ በዓላት ያለ ክዋኔ ትርጉም የላቸውም፤ ክብረ በአላት በራሳቸው ክዋኔዎች ናቸው" ይላሉ፡፡ ይህ ዘዴ የተመረጠበት ዋነኛ ምክንያት የመውሊድን የአከባበር ሁኔታ እና ፎክሎራዊ ገጽታ ያለ ክዋኔ ማሳየት ስለማይቻል ነው፡፡ ስለዚህ

የአልከሶ መውሊድ ምን እንደሚመስል ያለ ክዋኔ ማቅረብ ጥናቱ በዓሉን እና ፎክሎራዊ ገጽታውን በትክክል የማሳየት አቅሙ አነስተኛ ስለሚያደርገው ይህ ይህን ንድፈ ሀሳብ ተከትሎ መረጃውን ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ በመሆኑም በበዓሉ አጠቃላይ የፎክሎር ዘውጎች ሲከወኑ ከፎክሎር አንጻር ተቃኝተው ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ይህ ጥናት በዋናነት የክዋኔ ንድፈ ሀሳብን ተከትሎ የተካሄደ ሲሆን አንዳንድ መረጃዎችን ለመተንተን ሥነ ፋይዳ (ተግባራዊ) እና ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳቦች አገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል ስለ ንድፈ ሀሳቦቹ ምንነት እና በዚህ ጥናት እንዴት አገልግሎት እንደሰጡ ቀጥለን እንለከታለን፡፡

### 4.3.2 ሥነ ፋይዳ (ተግባራዊ) ንድፈ ሀሳብ

የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ የተለያዩ የአተያይ አንፃሮች ያላቸው ንድፈ ሀሳባዊ መርሆዎችን ያቀፈ የፎክሎር ማጥኛ ስነ ዘዴ ነው፡፡ ይህም ጥናት በተግባራዊነት ቅንብብ ስር ሆነው የተለያዩ የአጠናን አቅጣጫዎችንና የትኩረት አንፃሮችን ያቃረቡትን የሥስቱንም ማለትም የBronislaw Malinowski፣ የReginald Radcliffe-Brown እና የEmile Durkheim ንድፈሀሳባዊ ዘዴዎችን በመቀም መውሊድ የማክበር ልማድ ከተጠኚው ማህበረሰብ ጋር ያለውን ትስስር ለማስረዳት ተሞክሯል፡፡

ስለ ፎክሎር ተግባር ወይም ፋይዳ ከጻፉ ምሁራን መካከል Oring(1976፣70) አንዱ ናቸው፡፡ እንደ Oring አገላለጽ የፎክሎር ፋይዳ ወይም ተግባር በሶስት መሰረቶች ላይ እንደሚመሰረት ያስረዳሉ፡፡

> Functionalism thus emerges as a particular theoretical orientation which assesrts that (1) sociocultural patterns have consequence which are independent of the conscious intation of the actors who perform them, (2) these patterns may be explained or understood interms of these consequences, and (3) these consequences are explanatory only if they contribute and are necessary to the proper integration and functioning of the individual or society (Oring 1976፣70)

ይህ ንድፈ ሀሳብ የአንድን ማህበረሰብ ባህል (ፎክሎር) በማህበረሰቡ ውስጥ ማህበራዊ ፋይዳ ወይም ተግባር አለው የሚል ሀሳብ የሚያቀነቅን ነው፡፡ ስለዚህ የዚህ ንድፈ ሀሳብ ዋና ትኩረት በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ፎክሎር የራሱ የሆነ ጠቀሜታ እንዳለው ማሳየት ነው፡፡ እንደGreen (1997፡386) አመለካከት ማንኛውም ፎክሎር ለሚተገብረው ማህበረሰብ ጥቅም አለው:: ምክንያቱም ይህ ማህበረሰብ ይህን ፎክሎር ያለ አንዳች ጥቅም ሊተገብረው አይችልም፡፡ ፎክሎር ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው Bascom (1954፡344-346) ያስረዳሉ፡፡ የሥነ ፋይዳ ንድፈ ሀሳብ እሳቤን ማወቅ አንድ የሰዎች ቡድን በአንድ ውስን ሁነትና ውስን ክዋኔ ውስጥ ምን እየሰሩ እንደሆነ ለመረዳት ያስችላል፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከወን ማንኛውም ነገር ያለውን ተግባርና አገልግሎት ወይም ፋይዳ ለመመርመር እንደሚረዳ Okpewho (1992፣173) ያስረዳሉ፡፡ Malinowski (1985፣254) ደግሞ እያንዳንዱ የፎክሎር ዘውግ ለሰው ልጆች ትርጉምና አገልግሎት አላቸው ካሉ በኋላ ይህም ማለት ዘውጉ ለምን ዓላማ እንደሚነገር፣ እንደሚከወንና ምን አገልገሎት እንዳለው አውድን መሠረት አድርጎ የሚገለጽበትና የሚተነትንበት ስልት መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ይህ ንድፈ ሀሳብ አንድ ባህል፣ ባህል ሆኖ ለመዝለቅ ለማህበረሰቡ የሚሰጠው አንዳች አገልግሎት መኖር እንዳለበት የሚያመላክት ሲሆን ባህል ማህበረሰቡን ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ የሚገለገልበትና ማህበረሰቡንም ለማስተማር፣ ንቁና ጥበበኛ ለማድረግ፣ ውስጣዊ ስሜቱን ለመግለጽና ከራሱ ከማህበረሰቡ ህግና ደንብ ለማምለጥ እንዲሁም ባህሉን ራሱን ለመትከል ያገለግላል፡፡ Sims & Stephens (2005፣174) እና Okpewho (1992፣10) ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሰጠው ጥቅም አኳያ ታይቶ መዳኘት እንዳለበት በዚህ ዓይነት ባህል ለማህበረሰቡ ከሚሠጣቸው ጠቀሜታዎች አኳያ እየተመለከቱ ማጥናት ማህበረሰቡ ስለራሱ፣ ስለአካባቢውና ስለዓለም ያለውን አመለካከት ለማወቅ አይነተኛ መንገድ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ሥነ ፋይዳ  በአውድ የተሰበሰበ መረጃ ከመተንተን በተጨማሪ ትርጉም ያለው ፍቺ መስጠት አስፈላጊ መሆኑን የሚደግፍ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ መሰረቱ ማብራራት ነው፡፡ ነገር ግን ጥናቱ አውድን መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ ከማብራራት ይልቅ ወደ ፍቺ እና ትርጓሜ ያደላል፡፡ እንደ Bacsom (1954:334) እና Sims (2005፡175) አገላለጽ ይህ ንድፈ ሀሳብ የባህል ተግባር የማህበረሰቡን ክዋኔ የከዋኙን ማንነት፣ የታዳሚውን ሁኔታ፣ እና

የማህበረሰቡን አመለካከት እንደሚያካትት ያስረዳሉ። በአጠቃላይ የመውሊዱ የአከባበር ስርዓት ለሚያከብረው ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ጠቀሜታ አለው።

Bacsom (1954፣334) አንድ የፎክ ቡድን (Folk Group) ከሚያከብረው ከበራ ጠቅላል ባለ እይታ ሲታይ አራት ዋና ዋና ተግባራት ወይም ጠቀሜታዎች እንዳሉት ያስረዳሉ። ጠቀሜታዎቹም የማስተማር ተግባር፣ ባህሉ ካሳለፈው ባህላዊ ጫን ራስን ለማሸሽ፣ ተቀባይነት ባለው ፎክሎራዊ ልማድ ስር የመተዳደር እና የሚተገብሩት ፎክሎር እውቅና እንዲኖረው የማድረግ እንደሆኑ ያስረዳሉ። ፎክሎር በተለይ ስነ ቃል ከሀገራን ፎክሎር አንጻር ያለውን ጠቀሜታ ፈቃደ አዘዘ የስነቃል መመሪያ በሚለው መጽሀፋቸው ከBacsom ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሀሰብ አስፍረው ይገኛል።

እንደ Fetterman (1998፡25-26) አገላለጽ ፎክሎርና የፎክሎር ትርጉም ከሰው ጋር የተሳሰረ መሆኑንና ፎክሎር የማስተማር፣ የማዝናናት፣ የማስተላለፍ እና ባህላዊ ማንነትን የማስጠበቅ ተግባር እንዳለው ይገልጻሉ። ሥነ ፋይዳ ማለት በቡድኖች መካከል ያለውን ማህበራዊ ግንኙነት የሚመለከት ንድፈ-ሃሳብም ጭምር ነው። ሥነ ፋይዳ (ተግባራዊ) ንድፈ ሀሳብ የአንድን ቡድን ቃላዊ፣ ተለምዶዊና ጽሁፋዊ ሰነዶችን በመመርመር ሰዎች እነዚህን ጉዳዮች ለመጋራት ካላቸው ጥቅም አንጻር ለምን እና እንዴት በሚል ጥያቄዎች አማካኝነት ፈትሾ ተግባራቸውን የሚያሳይ ንድፈ ሀሳብ ነው:: ለፎክሎር ፍቺ መስጠትም በማህበረሰቡ ውስጥ ያለውን ተግባር መመርመር መሆኑ መታወቅ እንዳለበት Sims and Stephens (2005፡175) ያስረዳሉ። በመሆኑም በዚህ ጥናት የአልከሶ መውሊድ አክባሪዎች ከከበራው የሚያገኙትን ሀይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ስነልቦናዊ ፋይዳ ምን እንደሆነ ተተንትኖ ቀርቧል።

## 4.3.4 ለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳብ

በዚህ ንድፈ ሀሳብ ትርጉም አንድ ማህበረሰብ የሚተገብረው ባህል በውስጣዊም ይሁን ውጫዊ ጉዳዮች መነሻነት፣ በሰው ሰራሽም ሆነ ተፈጥሯዊ በሆኑ ጉዳዮች ምክንያት እየተለወጠ ይሄዳል የሚል ነው:: Sims and Stephens (2005፣65) በየትኛውም የጊዜ ርዝመት የሚደረግ ድግግሞሽ ልማድን ይፈጥራል። የልማድ መደጋገም ደግሞ ተከታታይነትን ይፈጥራል። ተከታታይነት ተመሳሳይነት ወይም ቀድሞ የነበረውን መስሎ

መቀጠል ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም ልማድ በተደጋገመ ቁጥር ራሱን መስሎ አይወጣም፡፡ ሊለወጥም ላይለወጥም ይችላል፡፡ ተከታታይነት የሚለው ቃል በቡድኑ ውስጥ የልማዱን ትርጉም ወይም ጥቅም የያዙ ድርጊቶችን የሚመለከት ነው፡፡ ይህ ተከታታይነት የልምድን ድግግሞሽ የሚያሳይ ፅንሰ ሃሳብ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ድግግሞሹ የሚቋረጥበት ብሎም የሚጠፋበት አልያም በተወሰነ  ሁኔታ ለውጥ ሊፈጥር የሚችልበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህም ለውጥ (ተለዋጭነት) ወደ ሚለው ሌላው የልማድ ባህርይ ወደ ሆነው ለውጥ የሚወስድ ጉዳይ ይሆናል፡፡ ለውጥ የባህል ወይም የፎክሎር አንዱ ባህርይ ነው፡፡

ለውጥን የኢትዮጵያ ቋንቋና ጥናት ምርምር ማዕከል፣ አማርኛ መዝገበ ቃላት (1993፣21) “ለውጥ” የሚለውን ቃል አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት ሲል ይበይነዋል፡፡ የቃሉ ግስ የሆነውን ለወጠን ደግሞ የአንድን ነገር ቀድሞ የነበረ ሁኔታ፣ ባህርይ፣  መልክ፣ በሌላ እንዲቀየር፣ እንዲተካ አደረገ፡፡ አንድ ነገር ቀድሞ የነበረውን ሁኔታ፣ ባህርይ፣ መልክ በሌላ ቀየረ፣ ተበላሸ፣ ቀድሞ ከነበረው አሻሻለ የሚል ትርጉም ሰጥቶት ይገኛል፡፡ ከዚህ እና መሰል ብያኔዎች አንጻር ለውጥ የሚለው ቃል በነበረው ተጨባጭ ሁኔት ላይ ጊዜ የፈጠራቸውን ማሻሻያዎች፣ መተኪያዎችና ሁነቶች መፈጠራቸውን የሚያሳይ ፅንሰ ሃሳብ እንደሆነ መረዳት ይቻላል፡፡ የለውጥ ትርጓሜ  በፎክሎር እሳቤ ውስጥ ቦታ ያለው መሆኑን Tolken (1996፣126) እና Dorson (1972፣180) ያስረዳሉ፡፡ Sims (2005) ደግሞ “Most of the time though, (folklole) change and evolve naturally, and what appears to be an ending is really an adaptation part of the process of folklore” በማለት የፎክሎርን የለውጥ ሁኔታ ገልጸውታል፡፡

በፎክሎር ለውጥ እንዲካሄድ ምክንያት የሚሆኑ በርካታ ጉዳዮች ይጠቀሳሉ፡፡ ይህን በማስመልከት Schoemaker(1990) እና Bell(1992) የሚከተለውን ይላሉ፡፡ ፎክሎር ሊለወጥ ከሚችልባቸው ጉዳዮች መካከል ግጭት፣ ከሎሎች ቡድኖች ባህል/ነፎክሎር/ ጋር የሚደረግ ግንኙነት፣ የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ አመለካከት፣ የህዝብ አሰፋፋር፣ ፖለቲካዊ ርዮት አለም፣ እና የኢኮኖሚ ለውጥ ወዘተ በአንድም ሆነ በሌላ መልኩ በፎክሎር ላይ ለውጥ ያስከትላሉ፡፡ Dorson(1972፣44) ደግሞ “Foklorest is to examine closely the processe of syncretism, adaptation, acculturation, retention, accommodation, revitalization, recession, and disappearance that determine the ultimat product.” በማለት የለውጡን ሁኔታ እና መንስዔ ዘርዝረዋል፡፡

ይህ ማለት ለውጥ እና ቀጣይነት ሁሌም በሁሉም የፎክሎር ዘውጎች መገለጫ ባህርይ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አንድ የፎክሎር ዘውግ ከቦታ ቦታ፣ ከጊዜ ጊዜ እና ከሁኔታ ሁኔታ አንጻር ሊለወጥ፣ ሊሻሻል እና አንዳንዴም ሊጠፋ ይችላል፡፡ ለዚህ ማብራሪያ የሚሆን አንድ ምሳሌ ከፎክሎር ዘውጎች መካከል አንዱ የሆነውን ስነቃልን ወስድን ከስነቃል አይነቶች ደግሞ ቃል ግጥምን ወስደን እንመልከት፡፡

በአባይ ወንዝ አካባቢ የሚኖር ሰው አባይን አቋርጦ ወደ ማዶ ለመሻገር ውሃ ሞልቶ አላሻግር ቢለው

አባይ ጉደል ብለው አለኝ በታህሳስ
የማን ሆድ ይችላል እስከዚያ ድረስ

ብሎ እንደገጠመ ይነገራል፡፡ ሌላኛው ሰው ደግሞ ኑሮው ጊቤ ወንዝ አካባቢ ከሆነ ከዚህ በላይ የተመለከትነውን ቃል ግጥም እንደሚከተለው አሻሽሎ ሊለው ይችላል፡፡

ጊቤን ጉደል ብለው አለኝ በታህሳስ
የማን ሆድ ይችላል እስከዚያ ድረስ

ከነዚህ ሁለት ቃል ግጥሞች መረዳት የሚቻለው አንድ የፎክሎር ዘውግ ከቦታ ቦታ መጠነኛ ለውጥ ተደርጎበት ሊቀርብ  እንደሚችል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ለውጡ ከቦታ ቦታ ብቻ ሳይሆን ከሁኔታ ሁኔታ አንጻርም ለውጥ ሊያመጣ ይችላል፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የአልከሶን መውሊድ አከባበር ስርዓት እና በመውሊዱ የሚባሉ ስነቃሎችን በየጊዜው መጠነኛ ለውጥ እያመጡ መሆናቸውን መረጃ አቀባዮች ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም የተሰበሰበው መረጃ ሲተነትን የአከባበር ስርአቱ ያሳየውን ለውጥ እና ቀጣይነት አሳይቻለሁ፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# 5. የአልከስዬ አጭር የህይወት ታሪክ፣ ከራማ እና የመስጂዳቸው አመሰራረት

አልከሶ የመስጂዱ እና መስጂዱ የሚገኝበት ቦታ ስም ሲሆን አልከስዬ ደግሞ የመስጂዱ መስራች ስም ነው፡፡ የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ ስለ አልከስዬ አጭር የህይወት ታሪክ እና ስለ ከራማቸው የሚነገረውን ማቅረብ፣ እሳቸው ተንብየውታል የሚባሉትን ትንቢቶችና ስለእሳቸው የሚነገሩ አፈታኮች እና ሚቶች መተንተን ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አልከሶ መስጂድ አመሰራረት እና በመስጂዱ ዙሪያ የሚገኙ ኸለዋዎች ተዳሰዋል፡፡ በመሆኑም ይህ ምዕራፍ በገላጭ የመተንተኛ ስልት ቀርቧል፡፡

## 5.1. የአልከስዬ አጭር የህይወት ታሪክ

አልከስዬ ሙሉ ስማቸው ሼኽ በሽር ኡስማን ይባላል፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አልከስዬ ሼኽ ኡስማን ሰሏቸው አንዳንዶቹ ደግሞ አልከስዬ ሸካል አክበር ብለው ይጠሯቸው እንደነበረ የአካባቢው የዕድሜ ባለጸጋ የሆኑት ሼኽ ከዲር፣ ገራድ ኑርሰቦ፣ እና ሀጂ ሀምድኖ እንዲሁም በ1985 ዓ.ም "ስልጤ እና አልከስዬ" በሚል ርእስ የስልጢ ወረዳ ያሳተመው መጽሄት ይገልጻሉ፡፡ አልከስዬ የሚለውን መጠሪያ ያገኙት አልከሶ እሚባል ቦታ ላይ ሰፍረው መውሊድ እንዲከበር በማድረጋቸው እንደሆነ ይነገራል፡፡ አልከስዬ በ1875 ዓ.ም ከእናታቸው እመት አሚና እና ከአባታቸው ሼኽ ኡስማን በቀድሞው ጉራጌ ዞን በጉመር ወረዳ ውሪሮ አካባቢ ልዩ ስሙ ኢዛዝ (አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ይህን ቦታ ኡንጆፎ ይሉታል) በሚባል ስፍራ ተወልደዋል፡፡ ከይረዲን(2004) እና አባስ(2004) አልከስዬ የተወለዱት በ1858 ዓ.ም ነው ይላሉ፡፡ ከ1945 ዓ.ም ጀምሮ በሀረሙ ውስጥ በደረሳነት እንዲሁም በአሁኑ ጊዜ በኢማምነት እና በኡስታዝነት የሚያገለግሉት ሼኽ ከድር እና ገራድ ኑርሰቦ አልከስዬ የተወለዱት በ1858 ሳይሆን በ1875 ዓ.ም እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

አልከስዬ ኡንጆፎ ውስጥ እድሜያቸው ስድስት ዓመት እስኪሆን ድረስ ከእናታቸው እና ከአባታቸው ጋር ኑረዋል፡፡ የአልከስዬ አባት ሼኽ ስለነበሩ አልከስዬ በዚህ ዕድሜያቸው ቁርዓን መቅራት ጀምረዋል፤ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች አልከስዬ በስድስት ዓመታቸው ሙሉ

ቁርአንን እንደሸመደዱ(እንዳፈዙ) ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ አልከስዬ እስላማዊ ትምህርት መማር የጀመሩት ከአባታቸው ከሼኽ ኡስማን ነው፡፡ አልከስዬ ዕድሜያቸው ስድስት ዓመት አካባቢ ሲደርስ አባታቸውን በሞት አጥተዋል፡፡ ከአባታቸው ህልፈት በኋላ እናታቸው እመት አሚና የኑሮን ውጣ ወረድ ለብቻቸው መቋቋም ሲያቅታቸው አልከስዬን ይዘው ወደ ጎቤ የሚባል ቦታ በመሄድ ሌላ ትዳር መስረተዋል፡፡ አልከስዬም ለእንጀራ አባታቸው ከብትና ፍየል እየጠበቁ እና ቁርአን እየቀሩ ለተወሰኑ አመታት ቆይተዋል፡፡ አልከስዬ እንደማንኛውም የአካባቢው እረኞች ቁርአን በመቅራትም ሆነ በጨዋታ ምክንያትም አንድም ቀን በግም ሆነ ፍየል በአውሬ አስበልተው አያውቁም፡፡ በልጅነታቸው እንደ ህጻን ልጅ በጨዋታ ከማሰለፍ ይልቅ ቁርኣን በመቅራት፣ የተቸገረን ሰው በመርዳት እና በወላጆቻቸው የታዘዙትን ስራ በአግባቡ በመፈጸም አሳልፈዋል፡፡

አልከስዬ ኑሯቸውን እዛው ጎቤ አካባቢ በማድረግ ከልጅነታቸው ጀምሮ እስከ ወጣትነታቸው ድረስ በአካባቢው እና ወደ ወሎ ክፍለ ሀገር፣ አብሬት፣ ወለኔ እና የተለያዩ ቦታዎች በመዘዋወር እስላማዊ ትምህርትን በሚገባ ተምረው አጠናቀዋል፡፡ አልከስዬ በሃይማኖታዊ እውቀታቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ አንቱ የተባሉ ነበሩ፡፡ እስላማዊ ትምህርታቸውን ከአጠናቀቁ በኋላ በተለያዩ ስፍራዎች በመዘዋወር የዲን (የእስልምና) ትምህርት አስተምረዋል፡፡ በአካባቢው በነበራቸው ቆይታ በእስልምና እውቀታቸው አንቱ ከሚባሉ ሰዎች ግንባር ቀደም በመሆናቸው አልከስዬ ከሚለው ስማቸው የበለጠ ይታወቁ የነበረው የጎቤ ሼኽ በሚለው መጠሪያቸው እንደነበር ሀጂ ኑረዲን[38] ያስረዳሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ  አቶ ሙሀመድ[39] በተመሳሳይ ሁኔታ አጠናክረውታል፡፡

እንደ አቶ ግርማ[40] አገላለጽ ደግሞ እኚህ ሼኽ ከወጣትነት ዘመናቸው ጀምሮ በጎቤና በአካባቢው ለሚኖሩ ሰዎች ሶደቃ እንዲያወጡ እና መውሊድን በደንብ እንዲያከብሩ ይመክሩ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ አልከስዬ ለሶደቃ እና ለመውሊድም ልዩ ፍቅር እንደነበራቸው ያሳያል፡፡ በዚህም የተነሳ ከጎቤ ተነስተው አብሬት[41] ድረስ በመሄድ (ከጎቤ እስከ አብሬት በእግር ጉዞ

---

[38] ቃለ መጠይቅ 26/10/07
[39] ቃለ መጠይቅ 24/10/07
[40] ቃለ መጠይቅ 23/10/07
[41] የአብሬት መውሊድ ማለት በጉራጌ ዞን ቸሃ ወረዳ ውስጥ በአመት አንድ ጊዜ ለረመዳን ጾም አንድ ወር ሲቀረው የአብሬትዬ መውሊድ የሚከበርበት ቦታ ነው፡፡ አብሬት የቦታው ስም ሲሆን የሼኹ ስም አብሬትዬ

ሁለት ቀን ይፈጃል) የአብሬትን መውሊድ ያከብሩ እንደነበር አቶ ግርማ ይገልጻሉ፡፡ አልከስዬ ለረጅም አመታት አብሬት ደጋግመው ከመሄዳቸው የተነሳ የአብሬትዬ ሙሪድ(አገልጋይ) ሆነው ነበር፡፡ አልከስዬ የአብሬትዬ ጥሩ አገልጋይ (ሙሪድ) በመሆናቸው አብሬትዬ መርቀዋቸው ትልቅ ከራማ(መለኮታዊ ሀይል) እንዲኖራቸው ማድረግ እንደቻሉ በሰፊው እንደሚነገር ሼኽ ከድር[42] ያስረዳሉ፡፡

አልከስዬ በባህሪያቸው የዋህና ሩህሩህ እንደነበሩ እንደሚነገር የተለያዩ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ አቶ ግርማ[43] ከቀደምት አባቶች እንደሰማሁት በማለት “አልከስዬ ባህርያቸው ከሰው ጋር በቀላሉ ተግባቢ እና ለሰው ልጅ እንዲሁም ለማንኛውም ህይወት ላለው ፍጡር ተቆርቋሪ ነበሩ፡፡” በማለት ያስረዳሉ፡፡ አቶ ግርማ አያይዘውም ስለ አልከስዬ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> አልከስዬ በተለያየ ቦታ መሬትና ንብረት ቢኖራቸውም ለራሳቸው ከመጠቀም ይልቅ ለቸገረው ሰው መስጠት ይወዱ ነበር፡፡ እኔ እንዴት በጎተራ እህል አጠራቅሜ ሰዎች ተርበው ያድራሉ የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው፡፡ አልከስዬ ሰዎች እንዳይሰንፉና ጠንክረው እንዲሰሩ ይመክሩ ነበር፤ ተቸግረው ሲያዩ ግን እሳቸው ካላቸው ንብረት ያካፍሏቸው ነበር፡፡ አልከስዬ እሳቸው በነበሩበት ወቅት በአካባቢው ከሚኖሩ ሰዎች የተሻለ ሀብት እያላቸው ልጆቻቸውን ከማስተማር ይልቅ የሰው ልጅ ያስተምሩ ነበር፤ እሳቸው ከራሳቸው ይልቅ ለሌላ ሰው ቅድሚያ ይሰጡ ነበር፡፡

የአልከስዬን የዋህነት እና ሩሁሩሁነት የተለየዩ መረጃ አቀባዮች በተለያየ መንገድ ገልጸውታል፡፡ ከነዚህ መካከል አቶ አዘነ አንዱ ናቸው፡፡ አቶ አዘነ የአልከስዬን ባህርይ በሚከተለው ሁኔታ አብራርተውታል፡፡

> አሁን መሬት አላቸው ብዬ ሀለሁ አይደል አሁን እዛ ቆላው ክፍል እህል ይመረታል፡፡ ቆላው ክፍል ዘር አጣሁ ይላል ዘር አውጥተው ይሰጣሉ፡፡ ልጆቻቸው መመሪያ ሳያጡ አንድ ዶክተር ልጅ አላቸው ፕሮፌሰር ልጅ አላቸው

---

ወይም የአብሬት ሼኽ ነው፡፡ ትክክለኛ ስማቸው ሼኽ ሰኢድ አብደላ እንደሆነ እና አንዳንድ ሰዎች ደግሞ አበራሙዝ እንደሚሏቸው ኑሪዲን ደሊል በ2013 ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ በጻፈው ጥናት ይገልጻል፡፡

[42] ቃለ መጠይቅ 24/05/08

[43] ቃለ መጠይቅ 23/10/07

ኢንጂነር ልጅ አላቸው የላቸውም፡፡ ልጆቼን ሀገር ይጠብቅልኝ እኔ ደግሞ ደህን እጠብቃለሁ፡፡ ለኔ ልጄ የሀገር ድሀ ነው ይላሉ፡፡ አንድም ቀን አንዳች ያደረጉት ያልሆነ ነገር አላደረጉም፡፡ ታመው ውጭ ሄደው መታከም እየቻሉ አላደረጉትም፡፡ ልጆቻቸው እኮ መማር እና ትልቅ ቦታ መድረስ አቅቷቸው አይደለም፡፡ የእሳቸው አላማ የሀይማኖት ነው፡፡[44]

እንደ አቶ ነስሩ[45]፣ ወጣት አብድልባቅ[46] እና ሌሎችም አገላለጽ አልከስዬ በህይወት ዘመናቸው ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ለራሳቸውም ሆነ ለልጆቻቸው ቅድሚያ ሳይሰጡ እስልምናን እና ስልጤን ያገለገሉ ታላቅ ዓሊም ነበሩ፡፡ አልከስዬ ዘመናዊ ትምህርት ባይቀስሙም የተለያዩ ኪታቦችን፣ ሀዲሶችን እና ቁርኣንን ጠንቅቀው ያወቁ ስለነበሩ ለሳይንሳዊ ጉዳዮችም ቅርበት እንደነበራቸው ይነገራል፡፡ በመሆኑም የስልጤን ህዝብ መንፈሳዊ ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በርካታ አለማዊ ጉዳዮችን በማስተማር አሁን ላለበት ደረጃ እንዲደርስ ትልቅ ሚና ተጫውተው ያለፉ ሁለገብ የሀይማኖት አባት ነበሩ፡፡

የስልጤ ህዝብ አሁን ያለውን ገጽታ እንዲላበስ አልከስዬ ምን ያህል አስተዋጽኦ እንዳበረከቱ አባስ አብዱ 2004 “ታላቁ እስላማዊ ምሁር አልከስዬ” በሚል በጻፉት መጽሀፍ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ከ1870(?) እስከ 1938 ዓ.ም ያለ ምንም እረፍት በመስራት ሙሉ ስልጤ “ኢስላም ነኝ” እንዲል እና ወደ ቀድሞው ማንነቱ እንዲመለስ አደረጉ፡፡ በስልጤ ህዝብ ክልል ውስጥ ከ1900 እስከ 1950 ዓ.ም ባለው ከ65 የበለጡ ሀረም ዎችን(መርከዞች) ነበሩ፡፡ ስልጤዎች ኢስላምን በህይወታቸው እንዲተገብሩ ልጆቻቸውንም በኢስላም አንጻው ማሳደግ እንዲችሉ አልከስዬ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል፡፡ የስልጤ ህዝብ ከውጭና ከውስጥ የሚነሳን ጸረ ኢስላም ለመታገልና ለመጠበቅ በአያሌው ከአልከስዬ ትምህርት ተጠቅመዋል፡፡

[44] አቶ አዘነ፣ ቃለመጠይቅ፣ 23/10/ 2007፣አልከሶ፡፡
[45] ቃለ መጠይቅ 24/05/08
[46] ቃለ መጠይቅ 27/05/08

አቶ ግርማ[47] ደግሞ "…ለምትወደው ነገር ብዙ መሰዋትነት ትከፍላለህ፡፡ አልከስዬ እስከ ሊቢያ ሀገር ድረስ ሄደው የተለያየ መጻህፍ አሳትመው ለስልጤ ህዝብ አምጥተው መድረሳ አቋቁመው ሙስሊሙ ማህበረሰብ አይኑን እንዲከፍት ያደረጉ እሳቸው ናቸው፡፡" በማለት የአልከስዬን አስተዋጽኦ ያጠናክራሉ፡፡

አልከስዬ የስልጤ ህዝብ በተለየየ ጊዜ የተነሳበትን ጠላት ጠንክሮ እንዲመክት ይመክሩ እንደነበር ይነገራል፡፡ Dirk Bustorf (2009፣157) "Imam Sugato Zäyni. A war-lord of the Selt'é Gogot." በተሰኘው መጣጥፋቸው ጣሊያን ሀገራችንን በወረረበት ዘመን የስልጤ እና የአካባቢው ህዝብ ለወራሪው በቀላሉ እጅ እንዳይሰጥ ያደረጉት በዋናት ኢማም ሱጋቶ ዘይኔ[48] ናቸው፡፡ እኚህ ጦር መሪ ጣሊያንን በመሳሪያ ሲዋጉ አልከስዬ ደግሞ ውስጥ ለውስጥ የስልጤ ህዝብ በዲኑ(በሃይማኖቱ) እንዲጠነክር እና ለጣሊያን እጅ እንዳይሰጥ በማድረጉ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል ይላሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በተመሳሳይ ሁኔታ አባስ አብዶ በ2004 ባሰተመው እና ስለ አልከስዬ ባተተበት ክፍል ገልጾታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ østebø(2014፣28) "During the armed rebellion, Dirre Shaykh Eusayn soon became an important scene for the enactment of this political drama. It was the meeting place for exchanging news and collecting support for the struggle." በማለት ሼኽና ሁሴንም እንደ አልከስዬ በአከባቢው ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ይሳተፉ እንደነበር ያስረዳሉ፡፡ ከእነዚህ ሁለት አሊሞች በተጨማሪ የአብሬት ሼኽ በቸሀ አካባቢ እስልምና እንዲስፋፋ ከማድረጋቸው ባሻገር የአካባቢው ማህበረሰብ

47 ቃለ መጠይቅ 23/10/07

48 Sugato's homeland was the small country of Ennäqor in the territory of the Selt'é group of Bärbäré situated on a narrow strip of highland between the Azärnät lowland in the East, Lémo-Hadiyya in the South, Endägany-Guragé in the West, and Bärbäré-inhabited Mount Mugo in the North. For most of his lifetime Sugato's seat was the village of Suloludo, north of the market place of Duuna. Many of his military campaigns started near to his village at the sharp edge of the highland, because from here it is possible to oversee the major part of Selt'é country and to climb down to the lower regions with war-horses. Naturally, the fame of Sugato is the strongest in Ennäqor and among the Azärnät-Bärbäré in general, while among the other Selt'é groups he has to share it with that of their own leaders. In his patriline Sugato was from the Sabuuté *giɓóo* (Slt. "clan") of the *Asrasa'apt Bärbäré*, i.e. the "Seventeen [clans of the] Bärbäré". About Sugato's father, Zäyni Dachaso, tradition relates, that when he was young, he stole cattle from his kinsmen and sold this booty as far as Quch'é in Wällayta. Subsequently Zäyni had to flee from Ennäqor to Mafäd in Ennämor-Guragé. Later, he killed a man in Mafäd and, as a punishment, the Guragé threw him into a ditch so that his legs were severely injured and crippled thereafter. Zäyni returned to Ennäqor to live on the land of his wife Bézo, which was inherited from his wife's father(Bustorf,2009,157).

እንዴት ማህበራዊ ህይወቱን መምራት እንዳለበት ያስተምሩ እንደነበር ኑሪዲን(2008፣38) ያስረዳል፡፡

አልከስዬ በህይወት ዘመናቸው በተለያዩ ቦታዎች ሚስቶችን እንዳገቡና በርካታ ወንድ እና ሴት ልጆችን እንዳፈሩ ይነገራል፡፡ በስልጤ ዞን ውስጥ ሚስት ካገቡበት ቦታ መካከል አልከሶ፣ ዳሎቻ፣ ጎቤ፣ ጦራ፣ ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ አልከስዬ ይህን ያህል ሚስት አግብተው ይህን ያህል ልጆችን አፈሩ በሚለው ጉዳይ ላይ በግልጽ ለመናገር ፈቃደኛ ባለመሆናቸው በትክክል የሚስቶቻቸውን እና የልጆቻቸውን ቁጥር ማወቅ አልተቻለም፡፡ መረጃ አቀባዮቹ በዚህ ርዕስ ዙሪያ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ከለመሆናቸው በተጨማሪ አልከስዬ ሚስቶቻቸውን የገቡት በተራራቀ ቦታ ከመሆኑ የተነሳ እና የተወሰኑት ሚስቶቻቸው እና ልጆቻቸው እሳቸው በህይወት እያሉ ስላረፉ የሚስቶቻቸው እና የልጆቻቸውን ቁጥር ለማወቅ አልተቻለም፡፡ ነገር ግን አቶ ነስሮ (የአልከስዬ የልጅ ልጅ ልጅ ናቸው) የአልከስዬን አጠቃላይ የቤተሰብ ስም ዝርዝር የአዘጋጀ ሰው አለ ቢሉም ይህ ሰው ማን እንደሆነ እና የስም ዝርዝሩ በማን እጅ እንዳለ ግን ሊታወቅ አልተቻለም፡፡

## 5.2 የአልከስዬ አልከሶ አሰፋፈር

አልከስዬ የተለያዩ የስልጤ ብሔረሰብ የሚኖርባቸው አካባቢዎችን ተዟዙረው እስልምናን ሲያስተምሩ ኖረዋል፡፡ ከነዚህም አካባቢዎች መካከል ጎቤ ለረጅም አመታት ካስተማሩ በኋላ አገታ ወደ ሚባል ቦታ ሄደው ለአስራ ሶስት አመት ያህል እስላማዊ ትምህርት አስተምረዋል፡፡ ይህን በማስመልከት የአልከስዬ የልጅ ልጅ የሆኑት ሰይድ አሽራቅ ሳዳት “ቆላ ውስጥ ባለጨ ጎቤ ተብሎ በሚታወቀው ስፍራ የእስልምና ሃይማኖት ትምህርት ሲያስተምሩ ትንሽ ጊዜ ቆይተዋል፡፡ ከዚያም ተመልሰው አንድ አመት አልከሶ ከቆዩ በኋላ አገታ ተብሎ ከሚታወቀው ስፍራ በመሄድ ለአስራ ሶስት አመት ኖረዋል፡፡ ከአስራ ሶስት አመት ቆይታ በኋላ ነበር አልከሶ ውስጥ በቋሚነት መኖር የጀመሩት፡፡ አልከስዬ ቀድሞ ለበርካታ አመታት ይኖሩበት የነበውን ጎቤን ለቀው ወደ አልከሶ የመጡበት ምክንያት ጎቤ በባህርይው ወደ ቆላነት ስለሚያደላ ሙቀቱን መቋቋም ሲያቅታቸው እና ከራማቸው እየጨመረ እየጨመረ ሲመጣ አካባቢውን ልቀቁ ልቀቁ አላቸው፡፡ ከዛም ቀዝቃዛ ቦታ ሲያፈላልጉ አልከሶ አካባቢ ቀዝቃዛ ስለነበረ አሁን ያሉበት ቦታ መጥተው መኖር ሲጀምሩ ሼኽ በሽር ከሚለው ስማቸው ይልቅ አልከስዬ የሚለው መጠሪያቸው ገኖዋል ይላሉ፡፡ የሰይድ አሽራቅን ሀሳብ በተወሰነ

ደረጃ አቶ ሁሴይኒ እና ሼኽ በህረዲን[49] ይጋሩታል፡፡ ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች በተጨማሪ ይህን ሀሳብ በ2008 ዓ.ም በተደረገ የቡድን ውይይት የተሳተፉት የ80 አመት የእድሜ ባለጸጋው ሀጂ ኑረዲን እና አቶ አዘነ በተመሳሳይ ሁኔታ ተጋርተውታል፡፡ ነገር ግን አቶ ሁሴይኒ[50] "አልከስዬ ጎቤን ለቀው ወደ አልከሶ የሄዱት ጎቤ አካባቢ የሃይማኖት አባቶች በፈጠሩባቸው ችግር የተነሳ ነው" የሚል ሀሳብ አክለውበታል፡፡

ከዚህ ሀሳብ በተቃራኒው ደግሞ አልከስዬ ወደ አልከሶ ሀረም  የመጡበት ምክንያት ምን እንደሆነ ገሪብ መሀመድ አማን በሚከተለው ሁኔታ ያስረዳሉ፡፡

> እኔ እዚህ መውሊድ መምጣት ከጀመርኩ ብዙ አመት ሆኖኛል፡፡ አልከስዬ እዚህ አካባቢው ለምን እንደመጡም ሲወራ ዳጋግሜ ሰምቻለሁ፡፡ እንደሰማሁት ከሆነ እሳቸው እዚህ የመጡት በህልማቸው ቦታውን አይተውት ነው፡፡ አንድ ቀን ተኝተው እያሉ በህልማቸው የሆነ ነገር መጣና ተነስ ከዚህ፡፡ እላይ ሰዎች ሁሉ የጠሉት እና ማንም የማይፈልገው ቦታ አለ፡፡ እሱ ላይ ሂድና መስጂድ ስራበት፡፡ እሱ ቦታ ወደ ፊት በጣም የዱኣ ቦታ ይሆናል ይላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ እሳቸውም እሺህ ብለው ሲመጡ ቦታው ለኑሮ የማይመች እና ምንም ሰው የማይኖርበት ቦታ ሆነባቸው፡፡ ግን ትተውት ወደ መጡበት ሊሄዱ ፈለጉና በህልማቸው በተነገራቸው መሰረት እዚህ ቦታ ላይ መስጂድ ሰርተው መኖር ጀመሩ፡፡ የቦታው ስምም አልከሶ ይባል ነበር፡፡ አልከሶ ማለት በስልጥኛ ቋንቋ የማይፈለግ ማለት ነው፡፡ የዛኔ የማይፈለግ የነበረው ቦታ አሁን ተፈልጎ የማይገኝ ቦታ ሆኗል፡፡ አሁን ይህን ታሪክ ብዙ ሰው ብጠይቅ አይመልስልህም፡፡ ምክንያቱም ሰው የሳቸውን ታሪክ እየረሳው ነው፡፡ አልከስዬ ትልቅ ወልይ[51] ናቸው ግን ታሪካቸውንና ስራቸውን ያሁኑ ትውልድ እያበላሸው ነው፡፡[52]

---

[49] ቃለ መጠይቅ 26/10/07

[50] ቃለ መጠይቅ 14/05/2008፡፡ አቶ ሁሴይኒ ሰይድ ፈይድ ልጅ ናቸው፡፡ አቶ ሁሴይኒ ከሀዋሳ ዩኒቨርስቲ የስነስብ ተመራቂ ሲሆኑ በአሁኑ ጊዜ በስልጤ ዞን ባህል ቱሪዝምና የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ የባህል ባለሙያ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ፡፡

[51]The saints [Walis] are men believed to have been especially favored by God during their earthly lives and who continue after death to provide a link between God and the material world. Once dead they become more fully endowed with super natural power and the local centre or focus of that power are the tombs which the dead are believed to inhabit. They are holders of a mysterious power called Baraka used for the benefit of the faithful. Of course

ከገራብ መሀመድ በተጨማሪ በ2008 ዓ.ም መውሊድ ሲያከብሩ ያገኘኋቸው የእድሜ ባለጸጋዎች አልከስዬ ገራብ መሀመድ በገለጹት አኳኋን እንደመጡ ቢነግሩኝም በዚህ ጥናት ዋና መረጃ አቀባዮች መካከል ሼኽ ከድር፣ አቶ ሁሴይኒ፣ አቶ አዘነ ግን ይህን አፈ ታሪክ አያውቁትም፡፡ ስለዚህ አልከስዬ አልከሶ አሰፋፈር በተለያዩ ሰዎች የተለያዩ መረጃዎች የሚቀርቡ በመሆኑ ስለ አልከሶ አሰፋፈራቸው ይህ ነው የሚል ወጥነት ያለውን መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ ነው፡፡

አልከስዬ አልከሶ ላይ ከትመው መውሊዳቸው ማክበር የጀመሩት ከ1900 ዓ.ም ጀምሮ ነው የሚሉ የጽሁፍ ማስረጃዎች አሉ፡፡ በስልጢ ወረዳ የታተመው “አልከሶና አልከስዬ” እና የአባስ አብዶን “ታላቁ እስላማዊ ምሁር አልከስዬ” መጥቀስ ይቻላል፡፡ ነገር ግን የአካባቢው ነዋሪዎች ጊዜው 1899 ዓ.ም እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ በዓሉ የተጀመረበት የጊዜ ልዩነት እንዳለ ሆኖ እስከ 2009 ዓ.ም. ድረስ በደመቀ ሁኔታ 110 ጊዜ ተከብሯል፡፡

አልከስዬ ከጎቤ ወደ አልከሶ ከመጡ በኋላ አሁን አዲሱ መስጂድ በሚገኝበት ቦታ ከአሁኑ መስጂድ ጋር ተቀራራቢነት ቅርጽ ያለው መስጂድ ማሰራት ችለዋል፡፡ ከመስጂዱ በተጨማሪ ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ ቁርአን የሚቀሩ ልጆች የሚኖሩበት ኸለዋ አሰርተዋል፡፡ አልከስዬ መስጂዱን ከሰሩ በኋላ ከተለያዩ ቦታዎቸ የተሰባሰቡ በአንድ ጊዜ ከ300 በላይ ልጆች እስላማዊ ትምህርት ያስተምሩ ነበር፡፡ አልከስዬ ከመጡበት አመት ጀምሮ በሀረም ቸው ውስጥ መውሊድ በየአመቱ እንዲከበር አድርገዋል፡፡ እስከሁንም ድረስ በመከበር ላይ ይገኛል፡፡

እንደ አቶ ሁሰይኒ እና ሼኽ ከዲር አገላለጽ አልከስዬ በዚህ ሁኔታ የተለያዩ አካባቢዎች በመዘዋወር የአካባቢውን ህዝብ እስላማዊ ትምህርት ሲያስተምሩ፣ የተለያዩ ታአምራትን ሲፈጽሙ እና መውሊዳቸው በደመቀ ሁኔታ ሲያከብሩ ቆይተው በ1938 ዓ.ም ህይወታቸው አልፏል፡፡ የቀብር ስነስርአታቸውም እዛው ሀረማቸው ውስጥ ተፈጽሟል፡፡ የአልከስዬ አስክሬን ያረፈበት ቦታ በአሁኑ ጊዜ መውሊዳቸው ሲከበር እና በተለያዩ ጊዜያት ከተለያዩ

this force springs from Allah and does not stand against monotheist faith (Foucher፣1994:74-75).

[52]ቃለመጠይቅ፣ ገራብ መሀመድ፣14/09/08፣አልከሶ ሀረም


ቦታዎች በሚመጡ ሰዎች ይዘየራል (ይጎበኛል)። በዚህ ሀሳብ ሼኽ በሀሩም[53] እና ገራድ ኑርሰቦ ይስማማሉ።

አልከስዬ ባረፉበት ዘመን በአካባቢ በርካታ በርካታ አስደንጋጭ ክስተቶች እንደተከሰቱ ሼኽ ከድር[54] እና ሌሎችም መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ። ለዚህም እንደምሳሌ የሚጠቅሱት በአካባቢው ዝናብ በመጥፋቱ ከፍተኛ የሚባል ድርቅ ተከስቷል። በዚህ ድርቅም በርካታ ሰዎች ተጎተዋል፤ በርካታ ከብቶችም አልቀዋል። በዚህም የተነሳ የአካባቢው ነዋሪዎች ለተለያዩ በሽታዎች ተጋልጠዋል። የችግሩ ዋና ገፈት ቀማሾች በአልከሶ ሀረም ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ደረሳዎች ናቸው። በመሆኑም ከሳቸው ሞት በኋላ በሀረሙ ውስጥ ይኖሩ የነበሩት ደረሳዎች ቁጥር በጣም ቀንሷል።

ሼኽ ከድር[55] እና አቶ ሁሴይኒ[56] አልከስዬ ካረፉ በኋላ መስጂዱን እነ ማን እንዳስተዳደሩት በሚከተለው መልክ ይገልጻሉ። ከአልከስዬ ከቀጥሎ መስጂዱን ከ1938 እስከ 1941 ዓ.ም ድረስ ለሶስት አመት ያህል የመሩት የአልከስዬ የመጀመሪያ ልጅ የሆኑት ጌታዋ ናቸው። ከጌታዋ ቀጥሎ ከ1941 እስከ 1954 ዓ.ም ድረስ ለአስራ ሶስት አመት ያህል የመሩት የጌታዋ ታናሽ ወንድም ሳዳት ናቸው። ሳዳት መስጂዱን ለአስራ ሶስት አመት ያህል ጊዜ በሚያስተዳድሩበት ወቅት በእስልምና ሃይማኖት እውቀታቸው አንቱ ሊያስብላቸው የሚችል ስራ ሰርተዋል። እኚህ ሰው ትልቅ ዓሊም በመሆናቸው የሀይቆች እና ቡታጀራ ቃዲ(መሪ) ነበሩ። በወቅቱ ሀይቆች እና ቡታጀራ ተብሎ የሚጠራው አካባቢ ቡታጅራን፣ ዝዋይን፣ ሀላባን፣ ከንባታን፣ ሀዲያን እና ስልጤን ያካተተ ነበር። ከ1954 እስከ 1957 ዓ.ም ድረስ ለሶስት አመት ያህል ሰይድ አሽራፍ መስጂዱን ካስተዳደሩ በኋላ ቦታው ለፈይድ አስረክበዋል። ፈይድ ደግሞ የሳዳት ልጅ ናቸው። ፈይድ መስጂዱን ያስተዳደሩት ከ1957 እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ነው። በመሆኑም ከአልከስዬ ልጅ እና የልጅ ልጅ መካከል ረጅም ዘመን መስጂዱን ያስተደደሩት እሳቸው ናቸው። ይህ ማለት መስጂዱን እስካሁን የአልከስዬ ሶስት ልጆች እና አንድ የልጅ ልጅ አስተዳድረውታል። በአጠቃላይ የአልከሶ መውሊድ መከበር ከጀመረበት ወቅት ጀምሮ መስጂዱን የመሩ ሰዎች ዝምድና እና የመሩበት ጊዜ የሚከተለውን ይመስላል።

---

[53] ቃለ መጠይቅ 14/09/08
[54] ቃለ መጠይቅ 23/05/08
[55] ቃለ መጠይቅ 23/05/08
[56] ቃለ መጠይቅ 24/05/08



አልከስዬ 1899 -1938
ጌታዋ 1938-1941
ሳዳት 1941-1954
ሰይድ አሽራፍ 1954-1957
ፈይድ 1957-2006
?
?

## 5.3 የአልከስዬ ከራማ[57] ተረኮች

በፎክሎር ጥናት ውስጥ ሚት በሚል ርዕስ የምንመለከታቸውን ተረኮች ከእስልምና አንጻር ስንመለከታቸው ከራም በሚል ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ከራም ማለት ወልዮች ለሚፈጽሙት እና ሌሎች ሰዎች ሊፈጽሟቸው ለማይችሏቸው ተአምራቶች የተሰጠ ስያሜ እንደሆነ Umer(2005) ያስረዳሉ፡፡

መሀመድ(2009፣234) ተቀዳሚ ሙፍቲ ሀጂ ዑመር እንድሪስን በመጥቀስ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> አላህ አንቢያዎችን (ነብዮችን) በራሱ ፈቃድ እንደሚመረጥ ሁሉ የአንቢያ ወራሾች የሆኑ ወልዮቹንም በራሱ ፍቃድ ይመርጣል፡፡ ወልዩነት ስጦታና ምርጫ ነው፡፡ የአላህ ፈቃድ ካልሆነ እና ካልተሰጠ ምን ቢቀሩ(ቢማሩዑ)ለማነት እንጂ ወልይነት አይገኝም፡፡ ወልይነት እረቂቅ፣ ምስጢር፣ የሆነ ነገር ነው፡፡ ወልዮች እጃቸው የገባን ለድሀ የሚሰጡ፣ ከምድር ጣጣ የጸዱ ዛሂድ ናቸው፡፡ ቀን በጾም፣ ሌሊቱነረ በሶላት፣ ቁርኣን በመቅራት፣ በዱኣ፣ በዚክር በመሳሰሉ አምለኮዎች የሚያሳልፉ ትንሽ የሚተኙ፣ ትንሽ የሚበሉ፣ ትንሽ የሚናገሩ፣ ቀልባቸው ምላሳቸው ለአላህ እና ከመዘከር ሌላ የማያውቁ የሆኑ ናቸው፡፡ አላህ ዱኣቸውን ይሰማቸዋል፣ የተደበቀ

[57] ስለ አልከስዬ የሚነገሩ ከራማዎች እንዳንዶቹ ሚት ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ አፈታኮች ናቸው፡፡ ስለሚት (Myth) ቴዎድሮስ (2002፣256) የሚከተለውን ይላሉ፡፡ ሚት(Myth) እጅጉን ተለጣጭ (flexible) ተረክ ነው፡፡ ሚት ተለጣጭ ነው ስንል አንድም ባህሪው እንደ ሁኔታው ይለዋወጣል፤ የባህሪው ለውጥ ደግሞ የተረኩን ተግባር ወይም ሙያ ይቀይራል፤ ይሄንም ተከትሎ የጥበቡን ምንነት የምንገልጽበት ብያኔ የምንመረምርበት ንድፈ ሀሳብ በአንድ አይረጋም ማለት ነው፡፡ መሀመድ(2009፣141) ደግሞ “ሚት በተራኪያቸው ዘንድ የሚታመንባቸው፣ዋና ገጸ ባህሪያቸው አማልክት የሆኑ፣ መቼቶቻቸው ከእውኑ አለም በፊት እና ውጭ የሆኑ በተለይ ስለ ተፈጥሮም ሆነ ስለ ሰው አፈጣጠር እና መጨረሻ ስለ ልዩ ልዩ እንግዳ ተፈጥሮዎችና ክስተቶች ከየት መጣነት ወዘተ የሚተረክባቸው ናቸው፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡አፈ ታሪክ (Legend) ቴዎድሮስ (2002፣265) ባለቤቱ በሆነው ማህበረሰብ ዘንድ ከእውነት ተቆጥሮ የሚነገር ቃላዊ ተረክ ነው፡፡ በአፈ ታሪክ ውስጥ ከሚሳሉ ገጸ ባሕሪያት መሃል ዋና ዋናዎቹ ባብዛኛው ታሪክ (History) የሚያውቃቸው ተረኩ መቼት ባደረገው ዘመን እና ስፍራ በእውን የነበሩ ሰዎች ናቸው፡፡ ሰዎቹ በታሪክ የተሳተፉባቸው ታላላቅ ሁነቶች እና በሁነቶቹ ውስጥ የፈጸሟቸው ተጋድሏቸው (እንደ ተረኩ ዓይነት፣ መንፈሳ እና ዓለማዊ ተጋድሎዎች) በአብዛኛው በተረኩ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ አፈ ታሪክ በከፊል ታሪካዊ በፊል ደግሞ ፈጠራዊ (ምናባዊ) በመሆኑ ቃል ከዋኙ በታሪኩና በፈጠራው መካከል ሚዛን፣ ምጣኔና ህብር ይኖር ዘንዳ በእጅጉ ይደክማል፡፡ መሀመድ(2009፣ 141) “ሌጀንድ የሚባሉት በተራኪዎቻቸው የሚታመንባቸው፣ ገጸባህሪዎቻቸው ሰዎች የሆኑ፣ መቼቶቻቸው የእውኑ አለም የሆኑ፣ ከታወቂ ግለሰቦች እና ታሪካዊ ሁነቶች ጋር የሚተረኩ የተረክ አይነቶች ናቸው፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡

ይገልጥላቸዋል። የራቀውን አቅርቦ ያሳያቸዋል። የሰው አእምሮ ሊቀበለው የማይችለውን ተአምር ያሰራቸዋል።

Jon Abbink (2008፣119) ከራማ ለተመረጡ ሰዎች ብቻ ከፈጣሪ የሚለገስ ልዩ ችሎታ እንደሆነ "… it is also brought holy men with specific healing power to work `miracles` (Ar.: karama)." በማለት ገልጾታል። እንደ መሀመድ(2009፣142) አገላለጽ የወልዮች ከራማ በሂደት ወይም በድንገት የሚታወቅባው እንጂ ማንንም ለማሳመን ብለው የሚፈጽሙ አይደሉም። ሱፊዮች ከራማቸው እንዲታወቅ የማይፈልጉ፣ ተደርገው ይቆጠራሉ። ሆኖም ከራማዎቹ ከአውሊያዎቹ ፍላጎት እውቅና ውጭ ድንገት የሚከሰቱ ሆነው የወልዮቹን እምነት ለማጠናከር፣ አንዳንድ ፍለጎቶታቸውን ለማሟላት፣ ሰዎች በመልካም ሰብእና እንዲታነጹ ለሚያደርጉት ጥሪ ተሰሚና ተጽእኖም ለመፍጠር ሲባል ከፈጣሪ የሚሰጣቸው ጸጋ ነው።

የወልዮች ከራማ ከሚኖሩበት ማህበረሰብ ጋር እጅጉኑ የጠበቀ ቁርኝት ያለው ነው። ነገር ግን ግንኙነታቸው የተገደበ ወይም የተወሰነ ነው። በመሆኑም የወልዮች ከራማ ባብዛኛው በወቅቱ በሚታዩ ችግሮች፣ ፍላጎቶች፣ ተሳታፊዎች ዙሪያ የሚያጠነጥን ለህብረተሰቡ የተለየ ትርጉም የሚሰጥ እንደሆነ ይነገራል። ይህን ሀሳብ ከአልከስዬ ከራማ እንጻር የተወሰኑ ምሳሌዎችን በመውሰድ እንመለከታለን።

## በሆድ ውስጥ ስለቆዩበት ጊዜ የሚተረክ ከራማ

አልከስዬ በእናታቸው ሆድ ውስጥ ሶስት አመት ከሶስት ወር ያህል ቆይተዋል ተብሎ እንደሚነገር አቶ አዘነ[58] እና ሼኽ ከድር[59] ያስረዳሉ። በዚህ ጊዜ ቆይታቸው አንድ ሰው ሊኖረው የሚገባው ሙሉ አካላት ሳይጨምሩም ሳይቀንሱም እንደማንኛውም ህጻን ልጅ ተወልደዋል። የአልከስዬ እናት አልከስዬን ሶስት አመት ከሶስት ወር ያህል በሆዳቸው ሲይዙ እርጉዝ መሆናቸውን የሚያወቁት ሶስት ወራትን ብቻ ነው። ወራቶቹም "ረጀብ"፣ "ሸአባን" እና "ረመዳን" ናቸው። ሌላው ጊዜ ግን እርጉዝ መሆናቸውን አያውቁም ነበር (የቡድን ውይይት፣ ሼኽ ከድር፡ ጥር 25/2008 አልከሶ ሀረም)። እሜት አሚና አልከስዬን ነብሰ ጡር በነበሩበት ወቅት ቀድሞ አጋጥሟቸው የማያውቁት አዳዲስ ጉዳዮች እንዳጋጠማቸው

---

[58]24/10/07 አቶ አዘነ መጀመሪያ ክርስትያን የነበሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ናቸው። የእስልምና ስማቸውም ነስረዲን ይባላል።
[59] ቃለ መጠይቅ 24/05/08

ይነገራል፡፡ ከነዚህም መካከል አንድ ቀን አንድ ላም እመት አሚናን ልትወጋቸው ስትመጣ ሆድ ውስጥ ያሉት አልከስዬ "አደብ አድሪጊ ሂጂ ከዚህ" ሲሏት ላሚቷ እዛው ወድቃ እንደሞተች ሼኽ ጀማል[60] ያስረዳሉ፡፡

ልክ እንደ አልከስዬ በተለያዩ ቦታዎች ህጻናት እናታቸው ሆድ ውስጥ እያሉ ተናግረዋል የሚባሉ አፈ ታሪኮች(ሚቶች) እንዳሉ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ነጻነት (1998:21) "አበጋር-ባህላዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ሟሟያነት በጻፈችው ጥናት ስለ ዳውዶ ሚቶሎጅ ባተተችበት ክፍል የሚከተለውን ትላለች፡፡

ጀበርቲ የተባሉት ኢትዮጵያዊ ሰው ወደ አረብ አገር ለዚያራ (በክርስትናው በእስልምናው እንዳለው ነው) ሄደው የንጉሱን አስተናጋጅ ይወዱና "ላግባሽ!" ብለው ይጠይቋታል፡፡ "ንጉሱ ይህንን ቢሰማ ይሰይፍሃል" ትላቸዋለች፡፡ እሳቸውም "እንግዳውስ እባክሽ ዘይሪኝ?" ይሏታል፡፡ እሷም ትዘይራቸውና ወዲያው እሳቸውን የዘየረችባቸው እጇ ይታመማል፡፡ ንጉሱም በምን ምክንያት እንደታመመች ሲጠይቋት ሁኔታውን ታስረዳቸዋለች፡፡ ንጉሱም ከኢትዮጵያ የመጡትን ጀበርቲን ያስጠሩና ካስቀረቡ በኋላ "አገልጋዬን ያሳመምካት አስማተኛ ስለሆንክ ነው፤ ስለዚህ ትሰየፋለህ!" ይሏቸዋል፡፡ ጀበርቲም አስማተኛ አለመሆናቸውንና ልጅቷን መውደዳቸውን ደጋግመው ለንጉሱ በመንገራቸው ንጉሱም ለሶስት ቀን ብቻ አግብተዋት ከህመሟ ከተፈወሰች በኋላ በሶስተኛው ቀን ኒካ (የጋብቻ ውለታ) እንዲያወርዱ ይፈቅዱላቸዋል፡፡ በሶስተኛው ቀንም ንጉሱ ጀበርቲንን ያስጠሯቸውና "ከህመሟም ድናለች፤ ኒካውም ሶስት ቀን ሞልቶታልና ፍታና ሂድ!" ይሏቸዋል፡፡ ጀበርቲም "አልፈታም!" ይላሉ፡፡ ለምን ተብለው ሲጠየቁ "አይ በሆዷ ውስጥ ልጅ አለኝ" ብለው ይመልሳሉ፡፡ ንጉሱም በዚህን ጊዜ በጣም ተናድደው "እውነትም አስማተኛ ነህ" በማለት ሊሰይፏቸው ሲሉ ጀበርቲ "ህዝብ ጥራና ከህዝቡ መካከል በቀኝ ጎኗ ሁለት፣ በግራ ጎኗ ሁለት ሰው የሚያዳምጥ አሰልፍልኝ፡፡ ከዚያም በሆዷ ውስጥ ያለውን ልጅ ስጠራው አቤት እንደሚል ያረጋግጡና ውሸቴን ከሆነ ልሰየፍ" ይላሉ፡፡ ንጉሱም የተባለውን አድርጎ በሆዷ ውስጥ አለኝ የሚሉትን ልጅ እንዲጠሩ ፈቀዱላቸው፡፡ እሳቸውም ጮክ ብለው "እስማኤል!" ብለው ሲጣሩ በሆድ ውስጥ ያለው ልጅ "ለበይክ!" (አቤት ማለት ነው) አላቸው፡፡ አሁንም ደገሙና "እስማኤል ጀበርቲ!" ብለው ተጣሩ፡፡ እሱም እሆድ ውስጥ ሆኖ ገና በሶስተኛ ቀኑ "ለበይክ!" አለ በድጋሚ፡፡ ጀበርቲ ለሶስተኛ ጊዜ ሲጣሩ ልጁም ለሶስተኛ ጊዜ ለበይክ በማለት ምላሽ ሰጠ፡፡ በዚህ ጊዜ ንጉሱ

[60] ቃለ መጠይቅ 02/05/08

በሁኔታው ተደናግጠው በሀገሩ ውስጥ እንዲኖሩ ፈቀዱላቸው። ይህ የሚያሳየው በገራችን በእናታቸው ሆድ ውስጥ እያሉ ተናግረዋል የሚባሉ ሰዎች መኖራቸውን እነዚህ እና መሰል ሚቶች ያሳያሉ።

## አፍ ስለፈቱበት ጊዜ የሚተረክ ከራማ

አልከስዬ ከተወለዱም በኋላ በህጻንነት ዘመናቸው አንድ ህጻን ልጅ ሊፈጽማቸው የማይችላቸውን በርካታ ተአምራቶችን ፈጽመዋል ተብሎ ይነገራል። ከነዚህም መካከል አፍ በማይፈቱበት እድሜ መናገር ጀምረዋል እንዲሁም ሰዎች በሆዳቸው ያሰቡትን ያውቁ ነበር ይባላል። ይህን ጉዳይ አስመልክቶ ተደጋግሞ የሚነገር አንድ አፈ ታሪክ አለ። ይህን ማስረጃ አቶ አዘነ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> እሳቸው እንደተወለዱ እዝህ ስልጤ ላይ እሳቸው የተወለዱበት አካባቢ አንድ አረሺ ቡዳ ነበረ አሉ። ልጅ ተወለደ በሚባልበት ቦታ እያሄደ አይነጥላ ቡዳ የሚባላ ነበረ። አሁን እኺ ሰውዬ ተወለዱ ሲባል እሱ ይሄዳል። ልጄ ወንድ ከሆነ ከአባቱ ይሻል “ገረዳ ለሆንት ታዴሽ ተጥቀል”[61] ብለው ቁጭ ሲሉ “አንተ ሀገር የበላህ የአለህ አይን ቆራርጦ የበላህ እድሜህ ትጠርና ሌላ ቦታ የበላህው አንሶህ ብለህ ብለህ እኛም ጋ መጣህ” ህጻኑ ነው ገና እንደተወለደ እንደሱ የሚለው። “አንተ የዝጋቤር ቁጣ ይቆራርጥህ በል ውጣ አላህ ከራህመቱ ያውጣህ።” ሲሉት ከዚያ ወጥቶ ቤቱ ሄዶ ሞተ። ገና በህጻንነታቸው ነው ይህ የሆነው።[62]

ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው አልከስዬ ከተወለዱም በኋላ አንድ ህጻን ልጅ ሊፈጽመው የማይችለውን ድርጌት ይፈጽሙ ነበር ተብሎ እንደሚታመን ነው። ይህ ማለት አልከስዬ ሰዎች በቀላሉ ሊፈጽሟቸው የማይችሏቸው ከራማ እንዳለቸው ነው። በመሆኑም ከዚህ ተረክ አንጻር አልከስዬ ትልቅ ከራማ የነበራቸው ወልይ እንደነበሩ መረዳት ይቻላል።

---

[61] “ገረዳ ለሆንት ታዴሽ ተጥቀል” በስልጥኛ ቋንቋ ሲሆን ሴት ከሆነች ከእናቷ ትሻል የሚል ትርጉም አለው።

[62] ቃለ መጠይቅ፣ አቶ አዘነ ወ/ሚካኤል፣23/09/07፣አልከሶ።

## እናታቸው ከውሃ ሙላት ያዳኑበት ከራማ ተረክ

ሼኽ በህረዲን እና አቶ አዘነ ከነገሩኝ ተረክ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው በርካታ ተረኮችን ነግረውኛል፡፡ ከነዚህ መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡ አልከስዬ ከሚኖሩበት ቀዬ ማዶ ሰው ይሞታል፡፡ የአልከስዬ እናትም ወደዛ መሄድ ስለነበረባቸው ወደ ለቅሶ ቤት ሊሄዱ ሲነሱ "ቤቱን በደንብ ጠብቅ" ይሏቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አልከስዬ "እኛ የአንድ ሰው ቤት ብቻ አይደለም የምንጠብቀው የሁሉንም ሰው ቤት ነው የምንጠብቀው" የሚል ምላሽ ሲሰጧቸው እናትየውም የልጅ ወሬ ነው ብለው ይሄዳሉ፡፡ የአልከስዬ እናት ወደ ለቅሶ ቤት ሲሄዱ ወንዝ ለማቋረጥ ሲሞክሩ ሊወስዳቸው ሲል ያ ቤት ጠብቅ የተባለው ልጅ ፈጥኖ ደርሶ አዳናቸው፡፡ ያ ህጻን ልጅ አልከስዬ ነበሩ፡፡ እናትየውም ግራ ተጋብተው "እንዴት ልትደርስልኝ ቻልክ" ሲሏቸው "ውሃ ካልሞላበት ቦታ ተሻገሪ" ብለዋቸው ወደ መጡበት በቅጽበት ተመለሱ፡፡

በሀገራችን አልከስዬ ብቻ ሳይሆኑ በርካታ ሰዎች የዚህ አይነት ድርጊት(በቅጽበት ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ መሄድ) ፈጽመዋል ተብሎ ይነገራል፡፡ ለምሳሌ የወለኔ ሼኽ በጻፉት ኪታብ(መጽሀፍ) አንዳንድ ሼኾች ጠዋት የመን ሀገር ውስጥ የሱጺ ሶላት ሰግደው ለቁርስ ኢትዮጵያ ይደርሱ ነበር ተብሎ እንደሚነገር ጽፈዋል፡፡ ከእሳቸው በተጨማሪ በወሎ ስለ ዳውዶች ከሚነገሩ ሚቶች መካከል እነዚህ ሰዎች በቅጽበት ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ሀገር እንደሚሄዱ የሚነገርበት ሚት ይገኝበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አብሬትዬ ከወሎ ወደ ጉራጌ(ቸሀ) በቅጽበት እንደሄዱ የሚያሳዩ ሚቶች አሉ፡፡ ስለዚህ ይህን ሁኔታ ነብዩ ሙሀመድ ከምድር ተነስተው ወደ አርሽ ከደረጉት ቅጽበታዊ ጉዞ አንጻር አያይዘን ልንመለከተው እንችላለን፡፡

## ትኩስ ቡና በጀበና ይዘው ስለመቀሳቀሳቸው የሚነገር ከራማ ተረክ

አልከስዬ ወደ አብሬት በሚመላለሱበት ወቅት አንድ ልዩ ታምር እንደፈጸሙ አቶ ግርማ[63] እንደሚከተለው ተርከውልኛል፡፡ አልከስዬ አንድ ቀን ሙሪዶቻቸውን ከነበሩበት ኸለዋ ጠርተው "ዛሬ አብሬት መሄድ አለብን ይሏቸዋል፡፡ ስንሄድ ግን ባዶ እጃችንን ሳይሆን የፈላ ቡና በጀበና ይዘን ነው አሏቸው"፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሪዶቻቸው በአልከስዬ አነጋገር ግራ ቢጋቡም እሳቸው ምንም ማድረግ እንደማይሳናቸው ስለሚያውቁ በሀሳቡ ተስማምተው የፈላ ቡና ይዘው ጉዞ ወደ አብሬት ይጀምራሉ፡፡ አብሬትዬ ደግሞ አብሬት ሀረም ውስጥ ሳሉ

---

[63] ቃለ መጠይቅ 23/10/07

ሙሪዶቻቸው "ጀበና ቡና ፊልታ እየመጣች ነው ሲኒ አጥባችሁ አዘጋጁ ይሏቸዋል" ሙሪዶቹም በተባሉት መሰረት ሲኒ አጥበው እንዳዘጋጁ አልከስዬ ከሙሪዶቻቸው ጋር ጎቤ ላይ የፈላው ቡና ሳይቀዘቅዝ ይዘው በመግባት በጋራ መጠጣት ችለዋል፡፡ አብሬትዬም የአልከስዬን ትልቅነት እና ከራማ እንዳለቸው በመገንዘብ በተለያየ ጊዜ ወደ አልከሶ በመሄድ የአልከስዬን መውሊድ ከአልከስዬ ጋር አብረው አክብረዋል፡፡ ይህ ገለጻ ከፎክሎር አንጻር ሲታይ ሚት ልንለው እንችላለን፡፡ ከዚህ ሚት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሚት ብርሃን (2005፤15) ስለ ዳውዶ ሚቶሎጂ በጻፈው አጭር ጽሁፉ ሼኽ ዳውድ ወደ ኢትዮጵያ የገቡበትም ሁኔታ ሼኽ ዳውድ ሙሶላቸውን (መስገጃቸውን) ባህሩ ላይ አንጥፈው ሽለል (ሽርተት) ብለው በዓይን ቅጽበት እንደመጡ፣ ኩሊባስ በአየር ላይ በርረው እንደደረሱ፣ ሼኽ ሷቢር ደግሞ አንድ እግራቸውን ከቀይ ባህር ማዶ አረብ አገር፣ አንድ እግራቸውን ወዲህ ማዶ አበሻ አገር አድርገው ባህሩ በሁለት እግራቸው መሃል እንዳለ ተራምደው እንደተሻገሩ የቃል ታሪኮች እንደሚያስረዱ ይገልጻል፡፡ የዚህ አይነት ድርጊቶችን የሚፈጽሙ ሰዎች በሚቶሎጂ ጥናት ልዕለ ሰብአዊነት (super natural) ያላቸው ሰዎች በመባል ይታወቃሉ፡፡

## እንቅልፍ ያጣን ሰው በከራማቸው እንቅልፍ ስለማስገኘታቸው የሚተረክ ተረክ

አንድ ሰውዬ አሜሪካ ውስጥ ሲኖር ለአስራ ስድት አመታት ያህል አንድም ቀን እንቅልፍ ተኝቶ አያውቅም ነበር፡፡ ከዚህ ችግር ለመላቀቅ የተለያዩ የሐኪም ቤት ደጆችን ቢያንኳኳም ምን መፍትሔ ማግኘት አልቻለም፡፡ ይህ ሁኔታ ያሳሰበው ስለነበር አዲስ አበባ ለምትኖር እህቱ ያጋጠመውን ችግር ደጋግሞ ይነግራት ነበር፡፡ እሷም የወንድሟ ጉዳይ ስለሚያሳስባት ጉዳዩን ለተለያዩ ሰዎች መንገር የዘወትር ልምዷ አደረገችው፡፡ ከእለታት አንድ ቀን የተለያዩ መውሊዶች በሚከበሩበት ቦታ በመዘዋወር መውሊድን የሚያከብሩ ሴትዮ ሁኔታውን ስትነግራቸው "እስኪ ከአሜሪካ ይምጣና አልከሶ መውሊድ ይዘሺው ሂጂ፡፡ እዝያ መውሊድ ሄዶ ዱኣ የሚደረግለት ሰው ከማንኛውም ችግሩ ይፈወሳል ሲባል ሰምቻለሁ" ይሏታል፡፡ እሷም የሳቸውን ምክር ሰምታ ሁኔታውን ለወንድሟ ስትነግረው "እዚህ በሰለጠነ ሀገር መፍትሔ ያልተገኘለት ችግር እንዴት ገጠር ላይ ያውም ያለ ዘመናዊ ህክምና ይድናል" በማለት ሀሳቧን ቢቃወማትም በተቻላት አቅም አስማምታ እንዲመጣ አደረገችው፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጣ በኋላ የአልከሶ መውሊድ በሚከበርበት ጊዜ ይዛው በመምጣት ሁኔታው ለአልከስዬ አስረዳቻቸው፡፡ እሳቸውም "እኔ ጋ አምጡት" ብለው ካስመጡት በኋላ ዱኣ አድርገውለት ምግብ እንዲበላ አስደርገው አጠገባቸው ጋደም እንዲል ያደርጋሉ፡፡ ሰውየው

ለትንሽ ጊዜ አጠገባቸው አረፍ እንዳለ ወድያውኑ እንቅልፍ ወስዶት ከእንቅልፉ ሳይነቃ ለሶስት ቀን ያህል ተኝቷል፡፡ የወንድሟ ለረጅም ሰአት መተኛቱን የተመለከተቸው እህቱ ወንድሜ የሆነ ነገር ሆኖዋል በማለት አካባቢውን በለቅሶ ረበሸችው፡፡ ወንድሟ ከእንቅልፉ ሲናቃ ግን በደስታ ተዋጠች፡፡ ለአስራ ስድስት አመታት በእንቅልፍ እጦት ሲሰቃይ ኖሮ በዚህ ሁኔታ ፈውስ በማግኘቱ በጣም ተደስቶ ሌላ ጊዜ መውሊዱ ሲከበር ተመልሶ እንደሚመጣ በመናገር አመስግኖ ወደ መጣበት ተመልሷል፡፡

ወጣት ፈተረሁፍ[64] እንደነገረኝ ከሆነ ከዚህ በላይ ታሪኩ የቀረበው ሰው ከተወሰነ አመት በኂላ አልክስዬ ላደረጉለት ነገር ውለታ ለመመለስ መውሊድ በሚከበርበት ጊዜ በመምጣት “እርሶ ዱኣ ካደረጉልኝ ጊዜ ጀምሮ ይህው በሰላም ተኝቼ እኖራለሁና አሁን ይህን መስጂድ ሙሉ ወጪውን ሽፍኜ ላሰራው” ይላቸዋል፡፡ አልክስዬም “አይቻልም የኔ መስጂድ መስራት ያለበት በአንድ ግለሰብ ሳይሆን በብዙ ሰዎች መዋጮ ነው፡፡ መስጂድ መስራት ትልቅ ሀጅር(ምንዳ) አለው፡፡ አላህ በቆርአኑ በምድር ላይ መስጂድ የሰራ ሰው በጀነት ማረፊያ መስጂድ ይሰራለታል ስላለ ሀጅሩን ሁሉም መካፍል አለበት” በማለት መስጂዱን ለማሰራት ያቀረበላቸውን ሀሳብ ሳይቀበሉት ቀርተዋል፡፡

ከዚህ ተረክ መረዳት የሚቻለው አልክስዬ ምን ያህል የአላህን ቃል አክባሪ እንደሆኑ እና ለሙስሊሙ ማህበረሰብ ይቆረቆሩ እንደነበር ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ እሳቸው ለማንኛውም ሰው ዱኣ የሚያደርጉትም ሆነ የተቸገረን ሰው የሚረዱት ያ ሰው ብድር ይመልስልኛል ብለው ሳይሆን ከአላህ ዘንድ ምንዳ አገኛለሁ በማለት እና ለሰዎች ቀና አመለካከት ስላላቸው እንደሆነ ከዚህ በላይ ከቀረበው ተረክ መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው አልክስዬ የዋህ እና ሩሁሩህ ባህርይ ያላቸው ሰው ነበሩ፡፡ ለዚህ ማብራሪያ ጥሩ ማሳያ የሚሆን አንድ ቃል ግጥም ወጣቶች ሜዳ ላይ በ23/09/ 07 ዓ.ም አልክሶ ሀረም  ውስጥ መንዙማ በሚሉበት ወቅት የሰማሁትን አቀርባለሁ፡

[64] ቃለ መጠይቅ 15/09/08

| በስልጥኛ | አማርኛ |
| --- | --- |
| አልከስዬ ጉኒኒሙ | አልከስዬ ነብሰጡር ናቸው |
| ኢትመርሮን ሎልድኒሙ | ያዝናሉ ለልጆቻቸው |
| አልከስዬ ጉኒኒሙ | |
| ኢትመርሮን ሎልድኒሙ | |

የዚህ ቃል ግጥም ዋና መልዕክት አልከስዬ ለህዝባቸው ገራገር ናቸው የሚል ነው፡፡ የቃል ግጥሙን ዋና መልዕክት የያዘው ቃል "ጉኒኒሙ" የሚለው የስልጥኛ ቃል ሲሆን "ጉኒኒሙ"[65] የሚለው ቃል ወደ አማርኛ ሲተረጓም ነብሰጡር የሚል ትርጉም አለው፡፡ ነብሰጡር እናት ለልጇ በጣም እንደምትሳሳ ሁሉ አልከስዬም ለህዝባቸው ይሳሳሉ የሚል መልዕክት ቃል ግጥሙ ያስተላልፋል፡፡ ይህ ቃል ግጥም የቀረበው በተለዋጭ ዘይቤ ነው፡፡ ተለዋጭ ዘይቤን ዘሪሁን (1992፣111) "ተለዋጭ ዘይቤ የአንዱን ባህርይ ለሌላ በመስጠት የሚፈጠር የዘይቤ አይነት ነው፡፡ አንድ ቃል ወይም ሀረግ የአንድን ሰው፣ እንስሳ፣ ተክል ወይም ግኡዝ አካል ባህርይ፣ ቅርጽ፣ ወይም ድርጊት ወስዶ ለሌላ በመስጠት ሀሳቡን በጎላ ሁኔታና በምስል ይገልጻል" ይላሉ፡፡ ከዚህ በላይ የቀረበው ቃልግጥም ከዚህ ብያኔ አንጻር ሲታይ ቃል ግጥሙ በተለዋጭ ዘይቤ ቀርቧል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አልከስዬ እና ነብሰጡር እናት ተለዋዋጭ ሆነው ቀርበዋል፡፡

## የሞተ ሰው ስለመቀስቀሳቸው የሚተረክ ከራማ ተረክ

አልከስዬ ህሙማንን ከማዳን በተጨማሪ የሞተ ሰው እና እንስሳትን የመቀስቀስ ከራማ እንደነበራቸው የሚገልጹ ተረኮች አሉ፡፡ አቶ አዘነ በ2007 ዓ.ም የአልከሶ መውሊድን ሲያከብሩ ያገኘኋቸው እና አልከስዬ የሞቱ ሰዎችን እና እንስሳትን ይቀሰቅሳሉ ስለሚባለው አፈታክ በርካታ አፈታኮችን ይናገራሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

> አንድ ጊዜ አንድ ጉመር ውስጥ የምትኖር ሴት የምትወደው ልጅ ይሞትባታል፡፡ በዚህ ጊዜ በጣም ሀዘን ውስጥ ትወድቃለች፡፡ እያለቀሰች እያለ ስልጢ ውስጥ

---

[65] በስልጥኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ዘንድ ነብሰጡርን አንዳንድ አካባቢ "ጉን" ሲባል አንዳንድ አካባቢ ደግሞ "ሀሚል" ይሉታል፡፡ ነገር ግን "ጉን" ለእንስሳት ሲሆን "ሀሚል" ለሰው ልጅ እንደሆኑ በስልጥኛ ቋንቋ ከተጻፉ መጻሕፍት መረዳት ችያለሁ፡፡

አልከስዬ የሚባሉ የታመመን የሚያድኑ የሞተን ሕያው የሚያደርጉ ቃልቻ መኖራቸውን መስማቷ ታስታውሳለች፡፡ ይህ ጉዳይ ትዝ እናዳላት የአካባቢውን ሰዎች በማሰባሰብ የልጇን አስክሬን ይዛ ወደ አልከስዬ ትሄዳለች፡፡ አልከስዬ ጋር እንደደረሰች ሁኔታውን አስረድታ ልጇን እንዲያድኑላት ተማጸነች፡፡ በወቅቱ በተለያየ በሽታ ተይዘው የመጡ ሰዎች ከበሽታቸው ሲፈወሱ ስትመለከት የእሷም ልጅ ከሞት እንደሚመለስ ተስፋ አደረገች፡፡ ነገር ግን ለረጅም ሰአት ቁጭ ብላ ብትጠብቅም ልጇ ሊነቃ አልቻለም፡፡ በዚህ ጊዜ "ይህን ሁሉ ሰው ስያድኑ እንዴት የኔን ልጅ ማዳን ያቅታቸዋል" በማለት አብረዋት የመጡ ሰዎችን ወስደው እንዲቀብሩት አዘዘች፡፡ ይህን ሁኔታ የተመለከቱት አልከስዬ ኻዳሚዎቻቸውን (አገልጋዮቻቸው) በመጥራት እና አንድ ቀጭን አርጩሜ በመስጠት "ያሁኑን ሰዎች ቶሎ ተከትላችሁ ልጁን ሳይቀብሩት በእሱ አርጩሜ ሶስት ጊዜ ቢስሚላሂ ብላችሁ ነካኩት" አሏቸው፡፡ ኻዳሚዎቹም በታዘዙት ሁኔታ ሰዎቹ ጋር ሲደርሱ ጉድጓድ ቆፍረው ሊቀብሩት ሲሉ ደረሱ፡፡ አልከስዬ ባሏቸው መሰረት የልጁን አስክሬን በያዙት አርጩሜ ሶስት ጊዜ ቢስሚላሂ ሲሉት ልጁ በእንቅልፉ እንደሚነቃ ልጅ ባነነ፡፡[66]

ይህን ተረክ በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ ነስሩ፣ አቶ ግርማ፣ ሼኽ ከድር፣አቶ ማሙሽት፣ ሼኽ ጀማል እና ሌሎችም ተጋርተውታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሀጂ ኑረዲን[67] የሚከተለውን አፈ ታሪክ ነግረውኛል፡፡ አንድ ጊዜ አልከስዬ ወደ አብሬት ደርሰው ሲመለሱ መንገድ ላይ አንድ ባዘራ ሞታ የባዘራዋ ልጅ ደግሞ በድኑንን ስትጠባ ይመለከታሉ፡፡ ይህንን ሁኔታ አይቶ ማለፉን ልባቸው አላስችል ስላለው አብሯቸው ሲጓዙ ለነበሩ ሙሪዶቻቸው "ዛሬ አላሀን ላስቸግረው ነው፡፡ ለማንም እንዳትናገሩ" አሏቸው፡፡ ሙሪዶቹም በአልከስዬ ሁኔታ ግራ ተጋብተው "ለማንም አንናገርም" በማለት አልከስዬ የሚፈጽሙትን ለማየት ጓጉ፡፡ አልከስዬም የሞተችዋን ባዘራ ሶስት ጊዜ "ቢስሚላሂ ቢስሚላሂ ቢስሚላሂ ተነሺ" ብለው በያዙት ቀጭን ዱላ መታ መታ ሲያደርጓት ባዘራዋ ተነስታ የባዘራዋ ልጅ በአግባቡ መጥባት ችላለች፡፡

እነዚህ አፈ ታሪኮች የሚያሳዩት የአልከስዬ የዋህነት እና ርሁሩሁነት አንድ ችግር ሲፈጠር አይተው በዝምታ እንዳያልፉ ያደርጋቸው ነበር እና የሰው ልጅ ሊፈጽመው የማይችል ልዩ መለኮታዊ ሀይል እንደነበራቸው ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አልከስዬ ለችግሩ ወዲያውኑ

---

[66] አቶ አዘነ፣ ቃለመጠይቅ፣25/10/2007 ዓ.ም አልከሶ

[67] ቃለ መጠይቅ 23/09/07

መፍትሔ ያልሰጡት ወልዮች በባህሪያቸው ከራማቸውን እንዲያውቁባቸው ስለማይፈልጉ ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ እይታ ደግሞ መለኮታዊ ሀይል ወይም ልዕለ ሰብዕዊነት ያላቸው ሰዎች የዚህ አይነት ድርጊት ሊፈጽሙ እንደሚችሉ ቀደም ብለን የተመለከትናቸው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

## ምሶሶን በከራማቸው ስለማጓጓዛቸው የሚተረክ ከራማ ተረክ

በአልከሶ መስጂድ ሀረም  ውስጥ ከ30 ሜትር በላይ ቁመት ያለው ትልቅ ምሶሶ አለ፡፡ ይህ ምሶሶ ከየት እንደመጣ፣ እንዴት እንደመጣ እና ከመጣ በኋላ ለምን አገልግሎት ሊሰጥ እንዳልቻለ አቶ አዘነ[68] እና ሀጅ ኑረዲን[69] በሚከተለው መልክ ያስረዳሉ፡፡

ይህ ጊቢ ውስጥ የሚገኘው ምሶሶ የመጣው ከጎልጀ ነው፡፡ ቦታው ሀላባ አካባቢ የሚገኝ ነው፡፡ አልከስዬ መስጂዱን በሚያሰሩበት ወቅት ይህ ምሶሶ ጎልጀ የሚባለው ቦታ እንዳለ መስጂዱን ለሚሰሩ ሰዎች በመንገር እንዲያመጡ ያደርጋሉ፡፡ ሰዎቹም በታዘዙት መሰረት ምሶሰውን ቆርጠው ያመጣሉ፡፡ ምሶሶው ከጎልጀ እስከ አልከሶ በሚጓጓዝበት ወቅት ብዙም የሰው ሃይል አልጠየቀም፡፡ ለደንቡ ያህል አልፎ አልፎ የተወሰነ ቦታውን በገመድ ታስሮ እየተጎተተ እንጂ እራሱ ዳገት ቁልቁለቱን እየወጣ እና እየወረደ መጥቷል፡፡ ይህን ሁኔታ በአይናቸው መመልከታቸውን ሀጂ ኑረዲን አክለው ያስረዳሉ፡፡ ይህ ምሶሶ በዚህ ሁኔታ አልከሶ ከደረሰ በኋላ አልከስዬ ተመልክተውት "እኔ ያልኳችሁ ይህን ምሶሶ አይደለም፤ ከእሱ ጎን ሌላ ከዚህ ከፍ የሚል አለ እሱን ነው ያልኳችሁ፤ እንደገና ሂዱን ያንን ቆርጣችሁ አምጡ" ብለው አዘው አሁን መስጂዱ ውስጥ የቆመው ምሶሶ መጥቷል፡፡ ምሶሶው ሲመጣ እናቶች መንገድ ላይ ጠብቀው ቅቤ እንደቀቡት መስማታቸውን አቶ ሲራጅ[70] አብራርተዋል፡፡ መሳሳይ ሁኔታ እሸቱ(1973፣16) ባሌ ውስጥ የሚገኘው የአናጂና መስጂድ ሲሰራ መስጂዱ ከሚሰራብት አከባቢ ራቅ ያለ ቦታ ላይ የነበረ አንድ ቁመቱ ሶስት ሜትር ወደ ጎን ግማሽ ሜትር የሆነ ትልቅ ቋጥኝ ያለማንም እገዛ መስጂድ ወደ ሚሰራበት ቦታ ድረስ በራሱ ጊዜ በሼኽ ሁሴን ልዩ ታምር ታግዞ እንደመጣ እንደሚነገር ጽፏል፡፡

---

[68] ቃለ መጠይቅ 24/10/07
[69] ቃለ መጠይቅ 24/10/07
[70] ቃለ መጠይቅ 26/10/07



ፎቶ 4፡- “ታምረኛው ምሶሶ” የሚባለው ምሶሶ እንዴት እንደመጣ አቶ ሲራጂ ሲያስረዱ

እነዚህን ተረኮች በጥሬው ስንመለከታቸው በቀላሉ አሁን ያለውን ሰው ሊያሳምን አይችልም፡፡ ነገር ግን ከሚት አንጻር ስንመለከታው ተረኮቹ ተፈጽመው ሊሆን እንደሚችል የሚት ጥናት ያስገነዝባል፡፡ ከነዚህ አፈ ታሪኮች የምንረዳው አልከስዬ እና መስጂዱን ያስተዳደሩ ልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው የሰው ልጅ ሊፈጽመው የማይችለውን ልዩ ነገር መለኮታዊ በሆነ ሁኔታ የመፈጸም ልዩ ችሎታ የተጎናጸፉ መሆናቸውን ነው፡፡ የዚህ አይነት የተለየ ነገር የመፍጠር ተፈጥሯዊ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ከዚህ በፊት መታየታቸውን ቀደምት ጽሁፎች ያስረዳሉ፡፡ ለምሳሌ በወለኔ ሼኽ በአረብኛ ተጽፎ በአብድልፈታህ “ጥሩነ” በሚል ወደ አማርኛ በተረጎሙት መጽሀፍ(1998፣125) የዚህ አይነት ባህርይ የነበራቸው ሰዎች በ19ኛው ክፍለ ዘመን እንደነበሩ ያትታል፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው የአልከስዬ ከራማዎችን ከሚት አንጻር ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ከተረኮቹ አንጻር አልከስዬ ልዕለ ሰብአዊ (super natural) ባህርይ አላቸው ማለት እንችላለን፡፡ ልዕለ ሰብአዊ ማለት ምን ማለት እንደሆነ Trimingham(1952:257-258) ልዕለ ሰብአዊ መደባቸው ከፍጡራን ወገን የሆነ፣ በደረጃ ወይም በማእረግ ከሰው ልጆች ላቅ ያሉ፣ በመለኮት የተቀቡ በልዕለ ተፈጥሯዊ የተመረጡ ወይም የሰው ልጅ ሊፈጽመው ከሚችለው ተግባር በላይ አከናውነው ለዚያ ማእረግ የበቁ

ሰዎች መጠሪያ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡ ቴዎድሮስ (2002፣255) ከTrimingham ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሀሳብ ሰንዝረዋል፡፡ Trimingham(1952:257-258) ኢትዮጵያ ውስጥ በርካታ ማህበረሰቦች ልዕለ ሰብአዊ ባህርይ ያላቸው ወይም ቅዱሳን የሚሏቸው ሰዎች መኖራቸውን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ገለጻ መረዳት የምንችለው አልከስዬ እና መስጂዱን ያስተዳደሩ ልጆቻቸው እና የልጅ ልጆቻቸው ልዕለ ሰብአዊ (super natural) ባህርይ አላቸው ማለት እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ፈጸሟቸው የሚባሉ ሚቶች ልዕለ ሰብአዊ (super natural) ባህርይ ያላቸው ሰዎች የሚፈጽሙትን አይነት ድርጊት ነው፡፡

## 5.4. የአልከስዬ ትንቢቶች

ትንቢት ማለት በአንድ ዘመን የኖረ ሰው እሱ ኪሚኖርበት ዘመን ወደ ፊት ይከሰታል ብሎ የሚነገረውን ርዕስ ጉዳይን ይመለከታል፡፡ ብዙ ጊዜ የዚህ አይነት ባህሪ ያላቸው ሰዎች መለኮታዊ ቅባት የተቀቡ መሆናቸው ይነገራል፡፡ የተለያዩ ሰዎች በተለያዩ ጊዜያት የተነበዮቸው አንዳንድ ትንቢቶች እውን ሆነው እንደታዩ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በሀገራችን ወደ ፊት የሚከሰተውን ጉዳይ አስቀድመው የሚተነብዩ በርካታ ሰዎች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ የወለኔ ሼኽ በጉራጌ እና አካባቢው ይኖሩ የነበሩ ሼኾች ወደፊት የሚመጠውን ጉዳይ ይተነብዩ እንደነበር በክታባቸው(በመጸሀፋቸው) ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በታሪክ በሰፊው የሚታወቁትን ሼኽ ሁሴን ጅብሪልን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል፡ የሼኽ ሁሴን ጅብሪል ትንቢትን “ትዕቢተ ሼኽ ሁሴን ጅብሪል” በሚል ርእስ በቦጋለ ተፈሪ በ2002 ዓ.ም መታተሙ ይታወቃል፡፡ ከሼኽ ሁሴን ጅብሪል በተጨማሪ አልከስዬም ምንም እንኳን በአግባቡ ትንቢታቸው ተሰብስቦ ባይታተምም በርካታ ትንቢቶች እንደተነበዩ እና ከነዚህ ትንቢቶች መካከል ጥቂት የማይባሉት ተፈጽመው መታየታቸው ይነገራል፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል አልከስዬ በተለያዩ ወቅቶች ተንብየዋቸዋል ተብለው የሚነገሩ ትንቢቶችን እንመለከታለን፡፡

### ትንቢት አንድ

አልከስዬ የተለያዩ ተአምራቶችን ከመፈጸማቸው በተጨማሪ ወደ ፊት የሚከሰት ክስተት በራዒይ ይታያቸው እንደነበር ይነገራል፡፡ ከዚህ ጋር ከተያየዙ ትንቢቶች መካከል ጣሊያን ሀገራችንን ለአምስት አመት በወረረበት ወቅት የተከሰተው ነው፡፡ ጣልያን ሀገራችንን በወረረበት ዘመን የአልከስዬ ወልይነት በጣም የተስፋፋበት እና በርካታ በእሳቸው የሚያምኑ

ሰዎችን የበዙበት ወቅት ነበር፡፡ ይህን ሁኔታ ያልወደዱ አንዳንድ ሰዎች በወቅቱ ከጣሊያን ለመጡ እና አካባቢውን ለሚያስተዳድሩ ጣሊያናዊያን (ጣሊያኖች በወቅቱ ማረፊያ ያደረጉት ቡታጀራ ከተማን ነበር) በመሄድ “አልከስዬ የሚባል አንድ ሰው በእናንተ አያምንም ከአምስት አመት በላይ አይገዙም እያለ ህዝቡን እያሳመጸ ነው” በማለት ይናገራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የአካባቢው መሪ አዛዥ እኝህን ሰውዬ በምን ሁኔታ ይዘው መምጣት እንዳለባቸው ከባልደረቦች ጋር መመካከር ይጀምራሉ፡፡ ቡታጀራ ላይ ይህ ሲሆን አልከስዬ አልከሶ ላይ ሆነው የሚካሄደውን ነገር ያውቁ ነበር፡፡ በመሆኑም የአካባቢውን ሰው በመሰብሰብ “ሰሞኑን ጣሊያን የሚባል ወራሪ እኔን ለማሰር ከቡታጀራ ይመጣል፡፡ በመሆኑም እሮብ ዕለት ቡታጀራ ይወስዱኝና ሀሙስ እና አርብ እዛው ቆይቼ ቅዳሜ አልከሶ እገባለሁ፡፡ እናንተም አልከሶ ጠብቁኝ፡፡ በቡታጀራ ቆይታዬ ምንም ጉዳት አይደርስብኝም ብለው ህዝቡን አረጋጉት፡፡ አልከስዬ ባሉት መሰረት ወታደሮቹ እሮብ አለት ወደ ቡታጀራ ወሰዷቸው፡፡

በቡታጀራ ቆይታቸው ሹሙ “ለምድነው እኛን የምትጠላው ለምድነውስ አምስት አመት ድረስ ብቻ ይቆያሉ ብለህ የምታስወራው” በማለት በአስተርጓሚያቸው በኩል ሲጠይቋቸው “እኔ አይደለሁም የጠላሁህ አላህ ነው የጠላህ፡፡ ደግሞም እዚህ ሀገር የምትቆዩት ለአምስት አመት ብቻ ነው” በማለት ይመልሱላቸዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አስተርጓሚው ይገሏቸዋል ብሎ በመፍራት እሳቸው ያሉትን በመተው ለሹሙ ሌላ ነገር ሲናገር “ለምን እኔ ያልኩህን ትተህ ሌላ ነገር ትናገራለህ፤ እኔ ያልኩህን ንገረው ምንም አያመጣም” ስላሉት እሳቸው ያሉትን ተርጉሞ ነገረው፡፡ አስተዳዳሪው ሁኔታቸው ስለገረመው ፎቶ እንዲነሱ ለሰራተኞች አዘዘ፡፡ ፎቶ አንሺው አልከስዬን ፎቶ ለማንሳት አንድ ክፍል አስገብቶ ካሜራውን ሲደቅን በካሜራው ውስጥ ከአልከስዬ ይልቅ አንዴ ቀይ አንዴ ጥቁር የሚያስፈራ ነገር ስላጋጠመው ሁኔታውን ለአለቃው በማሳወቅ እሱም እንዲመለከት ያደርገዋል፡፡ በዚህ ጊዜ አዛገቡም ለማንሳት ሲሞክር ተመሳሳይ ነገር ሲያጋጥመው አልከስዬን “አንተ ሰው ምንድነህ” ሲላቸው “አንተ እኔን ፎቶ ለማንሳት አልተፈቀደልህም የእኔን ውስጥ የሚያውቀው አላህ ብቻ ነው” ብለው መለሱለት፡፡ አልከስዬ የጣሊያን ወታደሮች ወደ ቡታጀራ ከወሰዷቸው በኋላ እሳቸው እንዳሉት ምንም ጉዳት ሳይደርስባቸው በሰላም ወደ አልከሶ ተመልሰዋል፡፡ ይህን ሀሳብ ሼኽ ጀማል፣ሼኽ ከዲር፣ አቶ ግርማ፣ አቶ መሀመድ፣ አቶ ማሙሽት ወዘተ በተለያዩ ጊዜያት ተርከውልኛል፡፡

## ትንቢት ሁለት

አልከስዬ ከተነበዮቸው ጉዳዮች መካከል የወራቤ ከተማ ምስረታ አንዱ ነው፡፡ አልከስዬ ከዛሬ 70 እና 80 አመት በፊት ስልጤ የራሱን ዞን በመመስረት ወራቤን ዋና መዳረሻቸው አድርገው እንደሚኖሩ መተንበያቸውን ይነገራል፡፡ ይህ ትንበያ አስመልክቶ አቶ ነስሩ[71] "አልከስዬ አሁን ያለውን አልፎ ወደ ፊት የሚመጣውን በሚገባ ጠንቅቀው የሚያውቁ ነበሩ፡፡ ወደ ፊት ከሚፈጠሩ ነገሮች መካከል የወራቤ ጉዳይ አንዱ ነው፡፡ ወራቤ ላይ መንግስት ይቋቋማል፡፡ ትልልቅ ፎቆች ይሰራሉ፤ ከተማዋንም ሆነ ፎቆቹኑ የሚያስተዳድሩት የስልጤ ተወላጅ ልጆች ናቸው ብለዋል፡፡" ይላሉ፡፡ አልከስዬ ወራቤ ከተማ ወደ ፊት ትልቅ ከተማ ትሆናለች ብለው በተነበዩበት ዘመን እረኞች

| | |
|---|---|
| ወራቤ ፈቲቴ ባጃ | ወራቤ ሰፊዋ መሬት |
| ጌሰም ኢሳዱሻን በጋጃ[72] | ነገም ይከፋፈሉሻል በስንዝር በስንዝር |

በማለት በስነቃል ወደ ፊት የወራቤ መሬት እጣ ፋንታ ምን ሊሆን እንደሚችል ተንብየዋል በማለት አቶ አብዱልረዛቅ[73] ነግረውኛል፡፡ ቃል ግጥሙ ወደ አማርኛ ሲተረጎም፡- ወራቤ ዛሬ ሰፊ መሬት ናት ወደ ፊት ግን ህዝቡ ይህን ሰፊ መሬት በሜትር ይከፋፈለዋል የሚል መልዕክት አለው፡፡ ይህ ትንቢት በአሁኑ ጊዜ እውን ሆኗል፡፡ ያኔ የነበረው ሰፊ የእርሻ መሬት ወደ ከተማነት ተለውጧል፡፡ መሬትም "በሜትር ይሸጣል" የተባለው እውን ሆኖ የወራቤ ከተማ እና ዙሪያዋ ያለው መሬት በሜትር ተሸጦ አልቆ ቤት የሚሰራው ከከተማው ወጣ ተብሎ እንደሆነ ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት አልከስዬ ስለ ወራቤ ከተማ ምስረታ የተነበዩት ትንቢት እውን ሆኗል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ስልጤ ዞን ከጉራጌ ዞን ተለይቶ የራሱን ዞን መስርቷል፤ ወራቤ ከተማ ላይ በርካታ ፎቆች ተገንብተዋል፡፡ እንዲሁም በፍጥነት በማደግ ላይ ትገኛለች፡፡

## ትንቢት ሶስት

አልከስዬ ከወራቤ ከተማ ምስረታ እና እድገት በተጨማሪ የስልጤ ብሔረሰብ ተወላጆች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ ባለው ስልጣን ላይ ይቀመጣሉ ማለታቸውን ሼኽ ጀማል

---

[71] ቃለ መጠይቅ 24/05/08
[72] አቶ አብዱልረዛቅ ቃለመጠይቅ 23/05/08
[73] ቃለ መጠይቅ 25/09/08

ያስረዳሉ፡፡ ይህ በአልከስዬ ተነግሯል የተባለው ትንቢት በአሁኑ ጊዜ እውን ሆኖ ተመልክተናል ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ ጊዜ የብሔረሰቡ ተወላጆች ተምረው የዞኑን ህዝብ ከማገልገላቸው በተጨማሪ ከወረዳ እስከ ፌዴራል ድረስ ስልጣን ላይ ሆነው ህዝብን በማገልገል ላይ የሚገኙ መሪዎች አሉ፡፡ ይህ የሚያሳየን አልከስዬ ከተነበዩት መካከል የብሔረሰቡ ተወላጆች ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ስልጣን ይይዛሉ ያሉት ጉዳይ ተግባራዊ መሆኑን ነው፡፡

## ትንቢት አራት

አልከስዬ በዞኑ በተለያየ ቦታ በማዕድን የበለጸገ እንደሆነ እና ወደ ፊት አገልግሎት እንደሚሰጥ መተንበያቸውን ሼኽ ጀማል ያስረዳሉ፡፡ ሼኽ ጀማል አያይዘወም የበለጸገ ማዕድን ከሚባሉት መካከል በዋናነት ነዳጅ፣ ወርቅ፣ አልማዝ ወዘተ እንደሆነ እና በዞኑ እንደሚገኝ አልከስዬ መተንበያቸውን ያስረዳሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያየዘ በዞኑ "በሙጎ ተራራ ውስጥ ነዳጅ አለ" ተብሎ ይታሰባል፡፡ ይህን ነዳጅ አንዳንዶቹ የተፈጥሮ ነዳጅ ነው ሲሉ የተቀሩት ደግሞ ጣሊያን በአምስት አመቱ የወረራ ዘመን የደበቀው ነው ይላሉ፡፡ ያከባቢው ወጣቶች ነዳጁ ለማውጣት ብዙ ጊዜ ይሞክራሉ፡፡ አንድ ዘመን ላይ እነዚህ ወጣቶች ነዳጁን ለማውጣት መሬት በመቆፈር ላይ እያሉ መሬቱ ተደርምሶ ብዙ ወጣቶች መሞታቸውን ሲነገር ሰምቻለሁ፡፡ ለመሬቱ መደርመስ እንደ ምክንያትነት የሚነገረው "በተራረው ስር ሰይጣን ስላለ ስይጣኑ ተቆጥቶ ነው" ተብሎ እንደሚወራ አቶ አብዱልረዛቅ[74] ነግረውኛል፡፡

በሀገራችን የተጠኑ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ልክ እንደ አልከስዬ በርካታ ወልዮች ወደፊት የሚከሰተው ጉዳይ ይተነብዬ እንደነበር ይነገራል፡፡ ለምሳሌ በአብሬት መውሊድን ደጋግመው ያከበሩት አቶ አብዱልረዛቅ ስለ አብሬትዬ ትንቢት የሚከተለውን አጫውተውኛል፡፡

አብሬትዬ ቁራናቸውን የቀሩት በወሎ ክፍለ ሀገር ነው፡፡ በዚህ ቦታ ለረጅም አመታት በደረሳነት እና በአገልጋይነት አገልግለዋል፡፡ ወልይነታቸውን ወይም ከራማቸውንም ያገኙት በዚህው ቦታ ነው፡፡ አንድ ቀን ጠዋት ላይ አብሬትዬ በአስቀሪያቸው አማካኝነት ቁራን በመቅራት ላይ እያሉ አንድ ሰው እነሱ ያለበትን ጎጆ (ኸለዋ) ለማቃጠል በእጁ እሳት ይዞ ሲመጣ በራዕይ ታያቸው፡፡ ሁኔታውን ለአስተማሪያቸው ሲያጫውቷቸው "እሳት ይዞ የሚመጣው ጠላቴ ነው ሊያቃጥለኝ እየመጣ ነው፡፡ ምን ይሻላል" ሲሏቸው አብሬትዬም

[74] ቃለመጠይቅ፣ 25/05/08

"ቀላል ነው መፍትሔው እኔው ጋር አለ" በማለት ወደ ውጭሲወጣ እሳት የያዘው ሰውዬ እሳቱን ወደ ጎጆዋ ሲወረውረው እሳቸውም በአየር ላይ ተወርበ-ረው ጎጆዋን ከእሳት ተደጓት፡፡ ይህን ሁኔታ የተመለከቱት አስቀሪያቸው "አንተ በወልይነት ከእኔ ትበልጣለህ፡፡ ስለዚህ በእኔ ስር መሆን የለብህም፡፡ ሂድና በጉራጌ ህዝብ ዘንድ አብራ" በማለት መርቀው እንደሸኞቸው እና አብሬት የሚለው ስየሜም "ሂድ በጉራጌ ህዝብ ላይ አብራ ከሚለው እንደመጣ ይነገራል፡፡ ከአብሬትዬ በተጨማሪ የገባር ሼኽ፣ የወለኔ ሼኽ ፣ የቃጥባሬ ሼኽ ፣ሼኽ ሁሴይን እና ሌሎችም ወልይ ነበሩ የሚባሉ ሰዎች ወደፊት የሚፈጠርን ነገር ቀደም ብለው ይተነብዩ እንደነበር ይነገራል፡፡ ይህ እና መሰል አፈታሪኮች የሚያሳዩን በሀገራችን ወልይ ናቸው ተብለው የሚታመኑ ሰዎች በበርካታ ጉዳዮች ላይ ተቀራራቢነት ያለው ባህሪ እንዳላቸው፡፡ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸውን ትንቢቶች ከከራማ አንጻርም ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም አልከስዬ ተንብየዋቸዋል የሚባሉት ትንቢቶችን የፈጸሟቸው በአላህ በተሰጣቸው ከራማ በመነሳት ነው፡፡

በአጠቃላይ አልከስዬ በህይወት ዘመናቸው የአካባቢውን ማህበረሰብ በርካታ አለማዊ እና መንፈሳዊ ትምህርት በማስተማር ትልቅ ሚና ተጫውተው ያለፉ አሊም እና ወልይ እንደነበሩ ከህይወት ታሪካቸው መረዳት ይቻላል፡፡ አልከስዬ በህይወት ዘመናቸው ህዝቡን ለማስተማር ያልዳሰሱት አለማዊ እና መንፈሳዊ ጉዳዮች የሉም ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም አልከስዬ ሁለገብ ኢስለማዊ ምሁር ነበሩና፡፡ አልከስዬ በህይወት ዘመናቸው ከዳሰሷቸው ጉዳዮች መካከል ስለ እውቀት አስፈላጊነት፣ በስነ ምግባር ስለመታነጽ፣ ስለ ምክርና ተግሳጽ፣ መስኪኖችን ስለመደገፍ፣ ስለ አእምሮ፣ ስለ ብዝሀነት፣ ስለ ስለወራቤ ከተማ መቆርቆር፣ ስለ ሴቶች መብት፣ ስለስርአተ ምግብ፣ ስለ አካባቢ ጤናና ንጽህና አጠባበቅ፣ ስለ ህክምና፣ ስለ ዘላቂ ልማት፣ ስለ አለመግባባት አፈታት፣ ስለወንድማማችነት ወዘተ ጉዳዮች ተጠቃሾች እንደሆነ አባስ (2004፣85-86) ያስረዳሉ፡፡ ይህን ሀሳብ በተመሳሰይ ሁኔታ በ1985 ዓ.ም በታተመው "ስልጤና አልከስዬ" በሚል ርዕስ የታተመው መጽሄት ውስጥም ይገኛል፡፡ ወልዮች የዚህ አይነት ሚና መጫወት የሀገራችን ወልዮች የጋራ ባህሪ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ይህ Jon Abbink(2008፣118) "In Sufist religious practice, the intermediary role of holy men or Saints(Arabic pl.: awliya) plays a great role" በማለት ይገልጻሉ፡፡

## 5.5 የአለከሶ መስጂድ አመሰራረት

በዚህ ንዑስ ስር ስለአልከሶ መስጂድ አመሰራረት ከመመልከታችን በፊት መስጂድ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ምን ምን ክንውን እንደሚከናወንበት ከዚህ በታች በአጭሩ እንመልከት፡፡

በዓለማችን መስጂድ ለመጀመሪያ ጊዜ የገነቡት ነብዩ ሙሀመድ እንደሆኑ Damas Addeh and Sayida Fuad (2011፣10) "The first mosque was built by the prophet Mohammed in Medina, which was called Yathrab City, before the arrival of the prophet." በማለት ያስረዳሉ፡፡ The first mosque built in Islam is Quba mosque in Saudia Arabia. It is located on the southwestern part of Madina. The mosque is still standing and is considered the oldest mosque in the world. The Prophet, peace be upon him, helped building and was the one who positioned the first stones.[75] ነብዩ ሙሀመድ 610 እ.ኤ.አ ነብይ ተደርገው ከተላኩ በኋላ የተወለዱበትን አካባቢ(መካ- ሳውዲአረቢያ) ለአስራ ሶስት ዓመታት እስልምናን ለማስተማር ከተጠቀሙበት ቦታ አንዱ መስጂድ ነው፡፡ ነገር ግን መዲና ላይ በወቅቱ ይህ ነው የሚባል ጠንካር መስጂድ አልነበራቸውም፡፡ በዚህ ሁኔታ በመካ እና ዙሪያዋ ይኖሩ የነበሩ ህዝቦችን እስልምናን እንዲቀበሉ ሲያደርጉ ቆይተው በ622 ወደ መዲና ከተማ ተሰደዋል፡፡ ነብዩ መሀመድ መዲና ከደረሱ በኋላ ከየቦታው የተነሱባቸውን ጠላቶች በጦር እየተፋለሙ ጎን ለጎን ደግሞ የራሳቸውን መስጂድ መስጂደል አል-ሀረም አስገንብተዋል፡፡ በዚህ መስጂድ ውስጥ ሀይማኖታዊ ስነስርዓት ከማከናወን በተጨማሪ የተለያዩ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ ክንውን ይከናወንበት እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የዚህ አይነት ሁኔታ በአሁኑ ዘመን በሚገኙ መስጂዶች ውስጥ ይከናወናል፡፡ ይህን ሀሳብ በማስመልከት Saeid (2006፣2) የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> The mosque is considered the most important structure in the Islamic world; it is a building not only made for public worship, but it is also the place where Muslims may practice their political, social and educational activities. The mosque

[75] **https://www.quora.com acced 22/02/2018**

represents Islamic culture and civilization, and therefore, it imparts to cities their Islamic identification.

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በሙስሊሙ ዓለም መስጂድ በጣም ወሳኝ እንደሆነ እና የሚመሰረተውም ለሃይማኖታዊ ግልጋሎት ብቻ ሳይሆን ሙስሊሞች ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ትምህርታዊ ጉዳዮቻቸውን ለማከናወኛነት ጭምር ነው። ከዚህ በተጨማሪ መሲጂድ የሙስሊሞች መለያ እንደሆነ ከጥቅሱ እንረዳለን። ይህ ሀሳብ በተመሳሳይ ሁኔታ Damas and Sayida(2011፣25) "Following Islamic tradition, the mosque is not only a place for worship, but also a place for culture and education, for the provision of health services and in general, for social support and solidarity." በማለት ሙስሊሞች መስጂድን ለመንፈሳዊ ግልጋሎት ብቻ ሳይሆን ለምድራዊ ጥቅም ማከናወኛ መድረክነት እንደሚጠቀሙበት ያስረዳሉ። HILLENBRAND, R. (1994፣13) ደግሞ እስልምና ማንሰራራት በጀመረበት ወቅት መስጂድ ለማህበራዊ፣ ለፖለቲካዊ እና ለአለማዊ ትምህርት ማስኬጃነት ቢያገለግልም ሃይማኖቱ እየጠነከረ ሲመጣ የመስጂድ ተግባር ሶላት የመስገጃነት እና ቁርኣን ለማስተማሪያነት ብቻ እንዲያገለግል መደረጉን ያስረዳሉ።

በሀገራችን ያለውን ነበራዊ ሁኔታ ስንመለከት ከዚህ በላይ ከተመለከትነው ሀሳብ ጋር ተመሳሳይ ሆኖ እናገኘዋለን። ምክንያቱም የሀገራችን ሙስሊሞች ከጥንት ጀምሮ መብታቸውን ለማስጠበቅ እና በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ለመወያያነት እንደ አመቺ ቦታ ይጠቀሙ የነበረው መስጂድን ነበር። ይህ ማለት ደግሞ መስጂድ ከሃይማኖታዊ ግልጋሎት በተጨማሪ አለማዊ ጉዳይም ለማከናወን ይጠቅማል ማለት ነው። የአልከሶ መስጂድንም ብንመለከት ከተመሰረተበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁንም ድረስ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ክንውን ይከናወንበታል።

ስለ መስጂድ ይህን ያህል ካልን ከዚህ በመቀጠል የአልከሶ መውሊድ መቼ እና እንዴት እንደተመሰረተ ምን ምን ክንውን እንደሚከናወንበት እና አሁን ያለበት ገጽታ ምን እንደሚመስል እንመለከታለን።

የአልከሶ መስጂድ የሚገኘው በስልጤ ዞን በስልጢ ወረዳ ውስጥ ነው። የአልከሶ መስጂድ ከአልከሶ ከተማ ሶስት ኪ.ሜ ፣ ከዞኑ መቀመጫ ወራቤ 12 ኪ.ሜ እና ከአዲስ አበባ

በስተደቡብ 167 ኪ.ሜ ርቀት ላይ ይገኛል፡፡ እንደ ነስሩ[76] አገላለጽ የመስጂዱ ሀረም ጠቅላላ የቆዳ ስፋት ሃያ አምስት ሄክታር ነው፡፡ በቅርቡ ከዞኑ የመሬት አስተዳደር ጋር በመነጋገር የተለካ ሲሆን የይዞታ ማረጋገጫም ተሰጥቶታል፡፡ የመስጂዱ አሰራር ሙሉ በሙሉ የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራርን የተከተለ ነው፡፡ ሙስሊሞች መስጂድ ሲገነቡ ሃይማኖታቸውን፣ ባህላቸውን፣ ፍልስፍናቸውን በሚያንጸባርቅ ሁኔታ እንደሚገነቡት (Hamid፣2012፣12) ያስረዳሉ፡፡ ስልጤዎችም ቁሳዊ ባህላቸውን በመስጂዱ አንጸባርቀዋል ማለት ይቻላል፡፡

ከ20/09 እስከ 10/10/07 በሀረሙ ተገኝቼ እንደተመለከትኩት የመስጂዱ ዋና ሀረም ሶስት ዋና ዋና ትላቅ መግቢያ በሮች እና አራት ትናንሽ የመግቢያ እና የመውጫ በሮች አሉት፡፡ የሀረሙ ዙሪያ ሙሉ በሙሉ በእንጨት ፍልጥ የታጠረ ነው፡፡ ይህ አጥር ሁሌም በየአመቱ መውሊድ ሲቃረብ ይታደሳል፡፡ ዋናው መስጂድ (ሽምሰል ጀማል) ሶስት ትላልቅ በሮች እና አራት ትላልቅ ባለሁት ተካፋች መስኮቶች አሉት፡፡ እነዚህ በሮች በስተደቡብ በኩል ያለው ወንዶች፣ በበስተምስራቅ ያለው ሴቶች እንዲሁም በስተምዕራብ ያለው ታላላቅ እንግዶች እና ሼኾች ይጠቀሙበታል፡፡ መስጂዱ አናት ላይ ትልቅ ሚናራ[77] አለው፡፡

የመስጂዱን ዙሪያ ደግፈው የያዙ ሃያ ስምንት ቋሚ እንጨቶች አሉ፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው አልከስዬ 1899 ወይም 1900 ዓ.ም ጀምሮ አሁን ያለውን ሀረም መስርተው መኖር ጀምረዋል፡፡ ከተጠቀሰው ጊዜ ጀምሮ እስከ 1935 ዓ.ም ድረስ በጎጆ መልክ የተሰራ መስጂድ ውስጥ ካሰለፉ በኋላ በ1935 ዓ.ም አሁን ሀረሙ ውስጥ የሚገኘውን መስጂድ ማሰራት እንደጀመሩ ሼኽ ከድር እና ገራድ ኑርሰበ[78] ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ መረጃ አቀባዮች አያይዘውም የመስጂዱ ስምም "ሽምሰል ጀማል"[79] እንደሚባል እና አልከስዬ ራሳቸው ስያሜውን እንደሰየሙት ይናገራሉ፡፡ "ሽምሰል ጀማል" በ1935 ዓ.ም ተጀምሮ የተጠናቀቀው ከስድስት አመት በኋላ በ1941 ዓ.ም ነው፡፡ የመስጂዱ ግንባታ ስድስት አመት

---

[76]አቶ ነስሩ የፈይድ ልጅ ሲሆኑ ወደፊት መስጂዱን ያስተዳድራሉ ተብለው የሚጠበቁት ናቸው፡፡

[77] the minaret in mosque architecture states that during the Abbasid dynasty it emonstrated power of the religious authority. However, other dynasty that opposed to the Abbasid ower like the Fatimids would not build any minarets to their mosques. In East Africa, Iran and Arabia calls for prayer were mostly ade from the mosque courtyard or the roof top similar to the time of the Prophet Muhammad(2011፣19).

[78] ቃለ መጠይቅ 24/05/08

[79] ሽምሰል ጀማል አረብኛ ሲሆን ወደ አማርኛ ሲተረጓም የጸሀይ መውጫ የሚል ትርጎም አለው፡፡

ያህል የፈጀው ሌሎች በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም የአልከስዬ በ1938 ዓ.ም ህልፈተ ህይወት ዋና ምክንያት እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ይናገራሉ፡፡

መስጂዱ የተሰራው ከሩቅ ቦታ በሰው ጉልበት ተጓጉዘው በመጡ እንደ ጥድ፣ ዋርካ፣ ዋንዛ፣ የባህር ዛፍ ዝርያዎች እንደሆነ አቶ ነስሩ ይገልጻሉ፡፡ ለሸምሰል ጀማል መስጂድ ዙሪያ ማቆሚያ የሚሆን እንጨት የመጣው ከጎልጆ እንደሆነ አቶ ነስሩ[80] ይገልጻሉ፡፡ አቶ ነስሩ አያይዘውም ለመስጂዱ የዋለው እንጨት ጎልጆ ውስጥ መሬት ውስጥ የተቀበረ ነበር፡፡ እንጨቱ መሬት ውስጥ መኖሩን በወቅቱ የተናገሩት አልከስዬ ናቸው፤ ምክንያቱም አልከስዬ በቅርብ እና በሩቅ የሚገኙ ነገሮች የሚታያቸው ሰው ነበሩና ነው፡፡ በመሆኑም የዝያኔ መስጂዱ ሲሰራ ጎልጆ የሚባል ቦታ መሬት ውስጥ ተፈልጦ የተቀበረ ጠንካራ እንጨት መኖሩን ለአካባቢው ሰዎች በመንገር ከመሬት ውስጥ ቆፍረው በማውጣት ወደ አልከሶ እንዲጓጓዝ አድርገዋል፡፡ አቶ ነስሩ "እንጨቱ መሬት ውስጥ የተቀበረው በጣሊያኖች ሲሆን አዲስ አበባ ላይ ቤት ሊሰሩበት ያዘጋጁት እንደሆነ እና እስከሚያጓጉዙት ድረስ አፈር እንዳይበላው በድንጋይ በተዘጋጀ ጉድጓድ ውስጥ ያስቀመጡት እንደነበር ይነገራል" በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ ሼኽ ከድር እና ገራድ ኑርሰቦ አገላለጽ "ሸምሰል ጀማል" በ1935 ዓ.ም ተጀምሮ ከተለያዩ ቦታዎች በሰው ጉልበት በተዘጋጁ ቁሳቁሶች ታንጾ በ1941 ዓ.ም ተጠናቋል፡፡

ይህ ማለት መስጂዱ በአልከስዬ ዘመን ተጀምሮ የተጠናቀቀው ጌታዋ መስጂዱን በሚያስተዳድሩበት ዘመን ነው፡፡ መስጂዱ ተሰርቶ ሲጠናቀቅ የጣራው ክዳን ሙሉ በሙሉ በስንደዶ የተከደነ የነበረ ሲሆን በርካታ ዘመናትን ካገለለ በኋላ እያፈሰሰ ሲያስቸግር በፈይድ ዘመን ከዚህ በታች በምስሉ በምንመለከተው መልኩ ክዳኑ ሙሉ በሙሉ በቆርቆሮ ተቀይሯል፡፡

---

[80] ቃለ መጠይቅ 24/05/08



ፎቶ 5፡- አሮጌው የአልከሶ መስጂድ[81]

ይህ መስጂድ በጠቅላላው 750 ቆርቆዎችን ፈጅቷል፡፡ የመስጂዱ ውስጥ እና ውጭክፍል በጭቃ የተለሰነ ነው፡፡ እስከ 1954 ዓ.ም ድረስ ለአራት ጊዜ ተደጋግሞ ግድግዳው በጭቃ ተለስኗል፡፡ ይህ በመሆኑ በአሁኑ ወቅት ግድግዳው ሲታይ ዘመናዊ መንገድ በግንብ የታነጸ ይመስላል፡፡ የመስጂዱ ክዳን ሲቀየር የተወሰኑ ባለሀብቶች ወጪውን ሙሉ በሙሉ የመሸፈን ፍላጎት ቢኖራቸውም ፈይድ ግን መስጂድ መስራት በአላህ ዘንድ ከፍተኛ ምንዳ እንደሚያስገኝ ስለሚያውቁ በሁሉም የህብረተብ አካል መዋጮ ወጪው እንዲሸፈን አድርገዋል፡፡

የአልከሶ መስጂድ ከዚህ በላይ በቀረበው ምስል መልክ ለረጅም ጊዜ ሲያገለግል ከቆየ በኋላ በ2000 ዓ.ም እንደገና የመጀመሪያውን ቅርጹን ሳይለቅ ታድሷል፡፡ በእድሳቱ ወቅት የጣራው ቆርቆሮ ሙሉ በሙሉ የዝገት መከላከያ ቀለም ተቀብቷል፤ ያረጁ ቆርቆሮዎች ተቀይረዋል፡፡ እንዲሁም የውስጥ እና የውጭ ግድግዳው ዙሪያው አሻዋ ግርፍ ተደርጓል፡፡ የጣራውን ዙሪያ ደግፈው የሚይዙ እና የበሰበሱ ቋሚዎች ተቀይረዋል፤ የተወሰኑ መስኮቶች ታድሰዋል፡፡

በመስክ ቆይታዬ እንደተመለከትኩት የመስጂዱ አጠቃላይ ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጽታውን ስመለከተው የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ውጫዊ ገጽታውን የስልጤ የባህላዊ የቤት አሰራር

[81] ፎቶ በዞኑ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ

የተከተለ ሲሆን ጣራውን ወደ ላይ ደግፈው የያዙ 25 ቋሚ እንጨቶች አሉት፡፡ መስጂዱ አንድ ዋና በር በጸሀይ መውጫ በኩል ሲኖረው በጠቅላላው ስምንት መስኮቶች አሉት፡፡ ጣራው ጫፍ አናቱ ላይ አምስቱን የእስልምና መሰረቶችን[82] የሚወክሉ ኮኮቦችን የያዘ ከብረት የተዘጋጀ ነገር (ምናራ) አለው፡፡ ምናራው ላይ ዘመናው የድምጽ ማጉያ በአራቱም አቅጣጫ ተገጥሞለታል፡፡

ውስጣዊ ገጽታውን ስንመለከተው ደግሞ መስጂዱ ውስጥ በልዩ ታአምር ከጎልጆ ተነስቶ አልከሶ መጥቷዋል የሚባለው ምሶሶ መሀል ላይ ቆሞ ይገኛል፡፡ የምሶሶው ቁመት ከ30 ሜትር በላይ ሲሆን ውፈረቱ ሁለት ሜትር ያክል ነው፡፡ እንደ አቶ ሁሰይኒ[83] አገላለጽ ምሶሶው ወደ መሬት ሁለት ሜትር ያህል ተቀብሯል፡፡ ለምሶሶው የተቆፈረው ቦታ ክረምት ክረምት ውሃ ስለሚያመነጭ በትቦ ተጠልፎ ወደ ውጭእንዲወጣ ተደርጎ ውሃው ለውዱእ እና ለመጠጥነት እንዲያገለግል ተደርጓል፡፡ ይህን ውሃ ከ"ዘምዘም" ውሃ ጋር በማመሳሰል ለብዙ በሽታዎች ፈውስ ይሆናል ተብሎ ስለሚታመን ብዙ ሰዎች እንደሚጠጡት ሼኽ በህሩ[84] እና አቶ ሁሴይኒ ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የይህ ክብረ በዓል ቦታ ዘምዘም ውሀ እንዳለ Yasuo Matsunami and Minako Ishihara(2009፣ 520) "At the watering facility inside the compound of the Rauda mosque, many pilgrims queued to fill their water jugs with zamzam (holy water). Almost every pilgrim carried some zamzam back home for medicinal use." በማለት ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሀጅ የሚያደርጉ ሰዎች ዘምዘም ውሃን መድሃኒትነት አለው ብለው በማመን ወደ የመጡበት ሲመለሱ ዘምዘም ውሃ ይዘው እንደሚመለሰ ነው፡፡

ዘምዘም ማለት ሳውዲ አረቢያ መካ ከተማ መስጂደል አል ሀረም መስጂድ ውስጥ የሚመነጭ ውሃ ሲሆን ለብዙ አይነት በሽታዎች ፈውስ ነው ተብሎ በሙስሊሞች ይታመናል፡፡ በተለይ በአመት አንድ ጊዜ በሚካሄድው ሀጅ እና ኡምራ ወቅት ከተለያዩ ቦታዎች ወደ ሳውዲ አረብያ-መካ የሚሄዱ ምዕመናን ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ዘምዘም ውሃ ይዞ መመልስ የተለመደ ነው፡፡

---

[82] አምስቱ የእስልምና መሰረቶች የሚባሉት፣ በአላህ አንድነት እና በነብዩ ሙሀመድ መልዕክተኛነት ማመን፣ ሷላት መስግድ፣ የረመዳን ጾም መጾም፣ ዘካ ማውጣት፣ እና አቅም ከፈቀደ ሀጅ ማድረግ፣ ናቸው፡፡

[83] ቃለ መጠይቅ 23/05/08

[84] ቃለ መጠይቅ 14/09/08

በሸምሰል ጀማል በምሶሶው አስራ ስድስት ዋና ዋና ማገሮችን በዙሪያው የተመቱ ሲሆን እነዚህ ማገሮች ደግሞ ዋናው ግድግዳ ላይ ተሰክተው ለጣሪያው ቆርቆሮ ማረፊያ በመሆን አገልግለዋል፡፡ ወደ ላይ የቆመው ጣራ ወደ ታች እንዳይወርድ በአስራ ስድስት ወፋፍራም እንጨቶች (ወጋዎች) ወደ ላይ ተወጥሮ በትላልቅ ምስማሮች ተመቷል፡፡ እነዚህ እንጨቶች (ወጋዎች) ከስር የተሰኩት በምሶሶው ዙሪያ ነው፡፡ ከስር ደግሞ እንጨቶቹ (ወጋዎቹ) የበለጠ ጥንካሬ እንዲኖራቸው ስምንት ወፋፍራም ብረቶች በመስጂዱ ወለል ላይ ተተክለው ወደ ላይ ወጥረው ይዘዋቸዋል፡፡



ፎቶ 6፡- የታደሰው የአልከሶ መስጂድ[85]

በሸምሰል ጀማል መስጂድ ውስጥ በርካታ የምእመናኑ መገልገያ ቁሳቁሶች ይገኛሉ፡፡ ከነዚህም መካከል ከ100 በላይ የቡና መጠጫ ሲኒዎችን የሚይዘው የሲኒ መደርደሪያ (ረከቦት) አለ፡፡ ይህ የሲኒ መደርደሪያ የተሰራው በአካባቢው እጅ ባለሙያዎች አማካይነት ነው፡፡ የሲኒ

[85] ፎቶ በአጥኚው 04/06/08፣ አልከሶ

መደርደሪያው የሚያገለግለው በዋናው እና በወርሃዊው የሀሙስ መውሊድ ጊዜ ብቻ ነው፤ ምክንያቱም በሁለቱ የመውሊድ ጊዜያት በርካታ ሰዎች ስለሚገኙ ነው። ከነዚህ ጊዜያት ውጭ ግን የመስጂዱ ሰዎች የሚጠቃቀሙባቸው ሌሎች ሁለት መካከለኛ የሲኒ መደርደሪያዎች አሉ። በእነዚህ የሲኒ መደርደሪያዎች ላይ በዘመናዊ መንገድ ከተዘጋጁ የቡና መጠጫ ሲኒዎች በተጨማሪ ከቅል የተዘጋጁ የቡና መጠጫዎች አሉ። በነዚህ የቡና መጠጫዎች በብዛት ቡና የሚጠጡት በተለምዶ ገሪባ ወይም አናጂናዎች የሚባሉ ሰዎች እንደሆኑ በመስጂዱ ዙሪያ ነዋሪ የሆነው ፈተረሁፍ ገልጾልኛል። ከሲኒ መደርደሪያዎች በተጨማሪ መስጂዱ ውስጥ ድቤና የድቤ መምቻ ዱላዎች፣ የተለያዩ ኪታቦች እና ቁርአኖች፣ በአካባቢው ከሚዘጋጁ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ትራሶች፣ የከሰል ማቀጣጠያ ምድጃዎች፣ እጣን ማጨሻዎች፣ የተለያየ መጠን ያላቸው የቡና ማፍያ ጀበናዎች፣ ወዘተ ይገኙበታል። ከነዚህም ሌላ የተለያዩ የድምጽ ማጉያዎች፣ የማብራት አንፖሎች፣ የሶለር አንፖሎች እና ሃይማኖታዊ ትምህርት ማስተማሪያ ቁሳቁሶች ይገኛሉ።

መስጂዱ በአዲስ መልክ እንዲገነባ በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት እና በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጉባኤ ጠቅላይ ምክር ቤት ሚሊኒየም ጽህፈት ቤት አማካይነት ነሐሴ 11 ቀን 2000 ዓ.ም የመሰረት ድንጋይ ቢጣልም እስካሁን ድረስ የተደረገ እንቅስቃሴ ግን አለመኖሩን በመስክ ቆይታዬ ማረጋገጥ ችያለሁ። የመሰረተ ድንጋዩ ከተጣለ በኋላ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት ለምን ወደ ትግበራ ሊገባ እንዳልቻለ ግን የመስጂዱ አስተዳዳሪዎች ምንም መረጃ የላቸውም።

ባጠቃላይ በአሁኑ ጊዜ መስጂዱ ውጫዊ እና ውስጣዊ ይዞታው በጥሩ ሁኔታ የተያዘ ነው። መስጂዱ በረዳ ዙሪያውን በዘመናዊ ሁኔታ ሴራሚክ ተነጥፎለታል። በመስጂዱ ሀረም ወስጥ ለሚኖሩ ሰዎች በሙሉ ለእያዳንዱ ቤት የቧንቧ ውሃ እና መብራት ተዳርሷል። ከቤቶቹ በተጨማሪ የመስጂዱ ሀረም ዙሪያው መብራት ገብቶለታል። ከአልከሶ ከተማ እስከ መስጂድ ድረስ መኪና የሚያስገባ የጥርጊያ መንገድ ተሰርቷል። መስጂዱን እና አካባቢውን ለሚጎበኙ ሰዎች አመቱን ሙሉ ክፍት የሆነ ማረፊያ ቤቶች ከእነ አስተናጋጆቹ ተዘጋጅተዋል። የአልከሶ ሀረም አመቱን ሙሉ ክፍት ነው። በዚህ ሀረም ውስጥ አመቱን ሙሉ በቋሚነት የሚሮሩ ደረሳዎች እና ኡስታዞቸ አሉ። የእነዚህ ሰዎች ወጪ የሚሸፈነው በሀረሙ አስተዳዳሪዎች ነው። ሀረሙ ውስጥ በቆየሁበት ወቅት እንደተመለከትኩት ከቀኑ አራት ሰአት አከባቢ ሁሌም የማይቀር ቡና የመጠጣት ስነ ስርአት ይካሄዳል። በዚህ ሰአት

በተለየየ ቦታ ቁርአን ሲቀሩ የነበሩ ደረሳዎች እና ኡስታዞች እና ማንኛውም ሀረሙ ውስጥ የተገኘ ሰው ይታደምበታል፡፡ የአልከሶ መስጂድ አመቱን ሙሉ ክፍት ሲሆን በቀን አምስት ጊዜ የፈርድ(የግዴታ) ሶላት፣ የሁለቱ ኢድ- ሶላቶች የሚሰገድበት ይሰገድበታል፡፡ መውሊድ በደመቀ ሁኔታ ይከበርበታል፡፡

## 5.6 ኸለዋዎች በአልከሶ መስጂድ ዙሪያ

በዚህ ንዑስ ስር በአልከሶ መስጂድ ዙሪያ ስለሚገኙ ኸለዋዎች ከመመልከታችን በፊት ኸለዋ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ እንመልከት፡፡ በእስልምና ኸለዋ ማለት የሃይማኖቱ ተከታይ የሆኑ ሰዎች ራሳቸውን ከአለማዊ ጉዳዬ በመነጠል ትኩራታቸውን ሙሉ በሙሉ እመነታቸው ላይ ለፈጠራያቸው ለመገዛት የሚሰፍሩበት ወይም የሚቀመጡበት ቦታ ነው፡፡ ይህን በማስመልከት Muhammad Yusuf (2014:2) የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> The word *khalwa* can be translated as "seclusion", and in Islamic Spirituality, is used to refer to withdrawing oneself from *dunya*, the manifest world of form, typically for a period of intense meditation and reflection. By understanding, practicing, applying and incorporating *khalwa* in your life, the seeker has a powerful opportunity to not only transcend illusion and the vanity of the self, but to awaken to Truth, discovering the imminence of the Divine Presence and establishing a permanent connection with the Source of all that is.

ኸለዋ መግባት የጀመሩት ነብዩ ሙሀመድ እንደሆኑ Bilala(2009፣23) የቡኻሪን ትክክለኛ ሀዲስ በመጥቀስ "Khalwa was practiced by the Prophet Muhammad through out his life, both before and after receiving revelation. In fact, it was during immersions in khalwa that the Prophet received not only insight, but revelation itself." ይላሉ፡፡

ስለ መስጂድ ታሪክ ከጻፉ ጸሀፊዎች መካከል አንዱ Collins(2011) ሲሆኑ በመስጂድ ውስጥ ስለሚገኙ ኸለዋዎችም ጽፈዋል፡፡ እኚ ጸሀፊ በሙስሊሙ አለም ሁለት

physical *khalwa* and spiritual *khalwa*. *የሚባሉ እንዳሉ ያስረዳሉ። እንደ እኚ ጸሀፊ አገላለጽ አካላዊ ኸለዋ* (physical *khalwa*) *ማለት* "Physical *khalwa* is often used in schools of Islamic Spirituality to train students to disconnect from the world of forms and appearances, and to dissociate from the constant stream of common human consciousness, so as to prepare the mind and body for enlightenment." *ይህ ማለት አካለዊ ኸለዋ የእስልምና ሃይማኖት ተማሪዎች እስለማዊ ትምህርት የሚማሩበት እና ስልጠና የሚወስዱበት ስፍራ ባጠቃላይ አማኙ ራሱን ምድራዊ ከሆኑ ጉዳዮች አርቆ ለፈጣሪው የሚገዛበት ቦታ ነው።*

*መንፈሳዊ ኸለዋ* (Spiritual Khalwa) *ደግሞ* Spiritual Khalwa The goal of physical khalwa is the development of the ability to maintain its internal state of in-dependence progressively, and ultimately, perpetually. This was the way of the Prophet (S), who although immersed in the world and in the lives of his family, friends and community, nevertheless often withdrew into the Divine Presence in the cultivation of a permanent state of liberation and spiritual enlightenment.

*በአጠቃላይ ኸለዋ ማለት አንድ ሰው ለምድራዊ ሳይሆን ለመንፈሳዊ ጉዳይ ትኩረት በመስጥ ፈጣሪውን ለመገዛት የሚመርጠው ስፍራ ነው። በአልከሶ ሀረም ውስጥ የተለያዩ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ክንውን ከሚከናወንባቸው ስፍራዎች መካከል ኸለዋዎች ይገኙበታል:: በዚህ ሀረም ውስጥ በጠቅላላው ከሰማኒያ በላይ ኸለዋዎች አሉ። ከእነዚህ ኸለዋዎች መካከል ሃምሳዎች መግቢያ በሮቻቸው ላይ የማን ማረፊያ እንደሆኑ የሚገልጽ ስም የተለጠፈባቸው ሲሆኑ ሃያዎቹ ደግሞ ስም የሌላቸው ናቸው። ከኸለዋዎቹም መካከል ናሲር ኸለዋ፣ ሙከሬ ኸለዋ፣ የአድገራድ ኸለዋ፣ ዲሬ ኸለዋ፣ አባባለንጊ ኸለዋ፣ የሀጂ ሽፋ ኸለዋ፣ ቲቴ ኸለዋ፣ የሙዘይን ኸለዋ፣ ሚቶ ኸለዋ፣ ቢላሙያያኛ ኸለዋ፣ ኢሜቴ ሙታ ኸለዋ፣ አጌደሌ ኸለዋ፣ የቆቶ ኸለዋ፣ የጠረዋሻ ኸለዋ፣ ኤለሬ ኸለዋ፣ አይደር ኸለዋ፣ የሼኽ ሀሰን ኸለዋ፣ አጀረ ኸለዋ፣ ደኔቾ ኸለዋ፣ ኡጋሳ ኸለዋ፣ አአናቤ ኸለዋ፣ ሲንቀበጆ ኸለዋ፣ ናኦ ኸለዋ፣ አራትበር ኸለዋ፣ ንበሬ ኸለዋ፣ ናዝሬት ኸለዋ፣ አባ በኒያ ኸለዋ፣ ሻሻመኔ ኸለዋ፣ መተሀራ ኸለዋ፣ መቱ ኸለዋ፣ አምረ ኸለዋ፣ የፎለሌ ኸለዋ፣ አደራሽ አንድ፣ አዳረሽ ሁለት፣ አዳረሽ ሶስት፣ ኩርሲ ኸለዋ፣ አድሰቦ ኸለዋ፣ ዛዊዊ ኸለዋ፣ መናፈሻ ኸለዋ፣*

ሰጋ ኸለዋ፣ የጮፈሼ ኢሳቅ ኸለዋ፣ የዱጌ ሰይድ ኸለዋ፣ የሳዳት ኸለዋ፣ የሸምሴ ኸለዋ፣ ኩየራ ኸለዋ፣ የክርስትያን ኸለዋ፣ የሼኽ ሀቢብሳኒ ኸለዋ፣ የእንጆራ ኸለዋ፣ ሲዳማ ኸለዋ፣ ወንቴ ኸለዋ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ከዚህ በላይ የዘረዘርኳቸው ኸለዋዎች ቆሚ ኸለዋዎች ሲሆን ከነዚህ በተጨማሪ ቁጥራቸውን ለመግለጽ የሚዳግቱ በርካታ ጊዜያዊ ኸለዋዎች የመውሊድ ሰሞን ሀረሙ ውስጥ በምዕመናን ይዘጋጃሉ፡፡ እንደ ገራድ ኑርሰቦ አገላለጽ ብዙ ኸለዋዎች ቆርቆሮ የሆኑት በፈይድ ዘመን ነው፡፡ ከዝያ በፊት በነበረው ዘመን ሁሉም ኸለዋዎች ሳር ቤት ነበሩ፡፡

የተወሰኑ ኸለዋዎች በራቸው ላይ የተለጠፈ ስም ባይኖራቸውም የእነ ማን ማረፊያ እንደሆነ ግን ይታወቃል፡፡ እንደ ኤሊያስ[86] "ኸለዋዎቹ ከተሰሩ ረጅም ጊዜ ስለሆነ ስም ባይኖራቸውም የማን ማረፊያ እንደሆኑ ስለሚታውቅ የማን እንደሆነ መለየት ብዙም ችግር አያጋጥምም" ይላል፡፡ በሀረሙ ውስጥ የሚገኙ ኸለዋዎች በብዛት የተዘጋጁት ከተለያዩ ቦታዎች ከመጡ ምዕመናን ሲሆን አንዳንድ ኸለዋዎች ግን የመስጂዱ አስተዳደር ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ እና የራሳቸው ማረፊያ የሌላቸው ምዕመናን እንዲያርፍባቸው ተብለው የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የክርስትያን ኸለዋ፣ ሻሻመኔ ኸለዋ፣ ናዝሪት ኸለዋ፣ እና ሶስቱ ትላልቅ አዳራሾች በመስጂዱ አስተዳደር እንደተዘጋጁ ይነገራል፡፡ እነዚህ ኸለዋዎች ከተለያየ ቦታ በእንግድነት የሚመጡ በአሉን አክባሪዎች በዚህ ኸለዋ ስለሚሰባሰቡ ከአዳዲስ ሰው ጋር የመተዋወቅ እና ማህበራዊ ግንኙነት የመፍጠሪያ አጋጣሚ በመሆን የራሱን ሚና ይጫወታል፡፡

ከእነዚህ ኸለዋዎች መካከል ጥቂቶቹ አመቱን ሙሉ ክፍት ሲሆኑ አብላጫዎቹ ግን በአመት አንድ ጊዜ በመውሊድ ሰሞን ብቻ ይከፈታሉ፡፡ ሁሉም ኸለዋዎች የምእመናኑ የሚገለገሉባቸው ቁሳቁሶች አሏቸው፡፡ ሁሉም ኸለዋዎች መብራቶች ተገጥመውላቸዋል፡፡ ከነዚህ ኸለዋዎች መካከል አምስት ያህሉ የጎጆ ቤቶች ሲሆኑ የተቀሩት በዘመናው መንገድ በቆርቆሮ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ ጥቂት የማይባሉት ኸለዋዎች ደግሞ አርጅተው በመውደቅ ላይ ይገኛሉ፡፡ የተወሱኑት እድሳት የተደረገላቸው ሲሆን የተወሰኑት ወድቀዋል፡፡ ከነዚህ ኸለዋዎች በተጨማሪ አዳዲስ የተሰሩ እና በመሰራት ላይ ያሉ ኸለዋዎች ሀረሙ ግቢ ውስጥ ይገኛሉ፡፡ እነዚህ ኸለዋዎች በአልከሶ መስጂድ ዙርያ ብቻ ሳይሆኑ በተለያዩ ቦታዎች

[86] ቃለ መጠይቅ 24/09/07

መውሊድ በሚከበርባቸው መውሊዶች ሀረም  ውስጥ እንደሚገኙ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ለምሳሌ ኑረዲን ደሊል (2012፣18) ስለ አብሬትዬ በሚያትትበት ጽሁፉ በአብሬት መስጂድ ሀረም  ውስጥ ከአራት መቶ የማያንሱ ቋሚ እና ጊዜያዊ ኸለዋዎች እንደሚኖሩ ያስረዳል፡፡

በእነዚህ ኸለዋዎች ውስጥ መውሊድ ሲከበር ሃይማኖት ክንውን ከማከናወን በተጨማሪ በርካታ ማህበራዊ እና ፎክሎራዊ ተግባራት ይከናወነወበታል፡፡ ለምሳሌ በእነዚህ ኸለዋዎች ውስጥ ሶላት ይሰገዳል፣ ሀዲስ ይኘገራል፣ ዱኣ ይደረጋል፣ እና መንዙማ ይባላል፡፡ ከዚህ ተጨማሪ ከተለያዩ መንዶች የተሰባሰቡ ሰዎች በአከባቢቸው ስላሉ የተለያዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ይወያያሉ፤ እርስ በእርስ ይጨዋወታሉ፤ይቀላለዳሉ፡፡ እንዲሁም በመንዙማ አማካይነት ይደንሳሉ፤ ይጨፍራሉ፡፡ በሀገራችን በሚከበሩ መውሊዶች ውስጥ የሚከበሩ መውሊዶች ይዚህ አይነት ሁኔታ እንደለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ደሊል(2008፣50) በአብሬት መስጂድ ውስጥ በሚገኙ ኸለዋዎች ውስጥ ሃይማኖታዊ ስነ ስርዓት ከማከናወን በተጨማሪ በርካታ ባህላዊ እና ማህበራዊ ክንውን እንደሚከናወንባቸው ያስረዳል፡፡

በአልከሶ መስጂድ ዙሪያ የሚገኙ ኸለዋዎች በዋናው መውሊድ ሰሞን ልዩ ገጽታ ይላበሳሉ፡፡ እንዲሁም መውሊድ በደመቀ ሁኔታ ይከበርበታል፡፡ ሁሉም ኸለዋዎች ውስጥ ያለው የቸከባበር ሁኔታ ተመሳሳይነት ያለው በመሆኑ በሻሻመኔ ኸለዋ መውሊድ እንዴት እንደተከበረ በአጭሩ እንመልከት፡፡

በ2008 ዓ.ም በመጀመሪያ ያመራሁት ሻሸመኔ ኸለዋ ውስጥ ነበር፡፡ በዚህ ኸለዋ ውስጥ ምዕመናን በብዛት የተሰባሰቡት ከሻሸመኔ፣ ከወላይታ፣ ከአሰላ፣ ወዘተ ነው፡፡ ከነዚህ ሰዎች መካከል ስድስት ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ መውሊድ አክባሪዎች በጋራ ተሰብስበው ሲያክብሩ እና ተራ በተራ እየተነሱ በህይወት ዘመናቸው ያጋጠማቸውን የተለየ አጋጣሚ ሲናገሩ ለረጅም ጊዜ የሚተዋወቁ እንጂ በዝህች አጋጣሚ እና በዚህ ቦታ የተዋወቁ አይመስሉም፡፡[87] ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው የአልከሶ መውሊድ ለመውሊድ አክባሪዎች መውሊዱ ከሚያስገኘው ጠቀሜታ መካከል አንዱ ማህበራዊ ግንኙነት መፍጠሩ እና ማጠናከር ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ መውሊድ ተዋውቀው ዝምድና የፈጠሩ ሰዎች አሉ፡፡

[87] የአንዳንዶቹን በተለይ የክርስትያኖችን የህይወት ገጠመኝ በምዕራፍ ሰባት አስፍሬዋለሁ፡፡

በዚህ መውሊድ ከዚህ ባሻገር በጋብቻ ተሳስረው የጠነከረ ዝምድና የፈጠሩ በርካታ ሰዎችም እንዳሉ አቶ ሁሴይኒ[88] እና አቶ ነስረዲን[89] ያስረዳሉ፡፡

ባጠቃላይ  በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የተመለከትነው ስለ አልከስዬ ማንነት እሳቸው ካረፉ በኋላ መስጂዱን እነማን እንዳስተዳደሩት፣ እነዚህ መሪዎች መስጂዱን ስያስተዳድሩ ፈጽሟቸው የሚባሉ ልዩ ልዩ ተአምራቶችን በመመልከት ከሚት እና ከራማ አንጻር ተተንትነዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአልከሶ መስጂድ እንዴት እንደተሰራ፣ ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል እና በየጊዜው የተደረገለትን ጥገና እና አሁን ያለበትን ሁኔታ ተመልክተናል፡፡ በመጨረሻም በሀረሙ ውስጥ የሚገኙ ኸለዋዎች ምን እንደሚመስሉ እና አሁን ያሉበት ገጽታ እና መውሊድ በኸለዋዎች ውስጥ እንዴት እንደሚከበር የሻሻመኔ ኸለዋን በመውሰድ አሳይቻለሁ፡፡

በመስክ ቆይታ ከምልከታዬ መረዳት እንዳቻልኩት በዚህ ቀን በአብላጫ ኸለዋዎች ውስጥ ያለው የአከባበር ሁኔታ ተመሳሳይነት አለው፡፡ ነገር ግን በ2007ቱ እና በ2008ቱ በዋናው የመውሊድ ቀን ሌሊት ከተመለከትኳቸው ኸለዋዎች መካከል የተወሰኑት ውስጥ ልዩነት መኖሩን ተመልክቻላሁ፡፡ ምክንያቱም ኩየራ ኸለዋ፣ መተሀራ ኸለዋ፣ ሙከሬ ኸለዋ፣ አዳራሽ አንድ፣ አዳረሽ ሁለት፣  አዳረሽ ሶስት፣ ሲዳማ ኸለዋ፣ ክርስትያን ኸለዋ ወዘተ አብላጫው ሰው ጥግ ጥጉን ይዞ ተኝቶ ተመልክቻለሁ፡፡ ጥቂት ሰዎች ግን በቡድን በቡድን በመሆን በቴፕ ሪከርደር የተከፈተ ዘመናዊ ነሺዳ አንዳንዶቹ ሱዳንኛ እና ስልጥኛ ሙዚቃ እያዳመጡ መውሊዱን አክብረዋል፡፡ ስለዚህ መውሊድ ለእነዚህ ሰዎች ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ብቻ ሳይሆን የመዝናኛ አጋጣሚም ጭምር ነው፡፡ ስለዚህ ኸለዋዎች ሃይማኖታዊ ስርዓት ከማከናወን ባሻገር የተለያዩ ማህበራዊ እና ፎክሎራዊ ክንውኖች እንደሚከናወኑባቸው መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ እኔም በምልከታዬ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ከክውኖቹ መካከል በብዘት ለተቸገሩ ሰዎች ገንዘብ ማዋጣት እና ዱኣ ማድረግ  እንዲሁም እርስ በእርስ መመካከር የተለመዱ ማህበራዊ ክንውኖች ናቸው፡፡ ከፎክሎር አንጻር ደግሞ በመንዙማ ቃል ግጥሞች አማካይነት የተለያዩ ፎክሎራዊ ክንውኖች ይከናወናሉ፡፡ ለምሳሌ በግጥም መልክ እርስ በእርስ መፎካከር፣ አልፎ አልፎም በትግል መወዳደር፣ የተለያዩ ጭፈራዎችን በመጨፈር መወዳደር እና አሸናፊውን መሸለም የተለመዱ ፎክሎራዊ ክንውኖች ናቸው፡፡

---

[88] ቃለ መጠይቅ 23/06/08
[89] ቃለ መጠይቅ 26/09/07

# ምዕራፍ ስድስት

## 6. የአልከሶ መውሊድ ከበራዎች እና ፎክሎራዊ ገጽታ

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የአልከሶ መውሊድ አጠቃላይ የአከባበር ስርዓት ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም የአልከሶ መውሊድ አጠቃላይ የአከበባር ሰርአት ምን እንደሚመስል በዋናነት ለፎክሎራዊ ጉዳዮች ትኩረት በመስጠት ተቃኝቷል፡፡ ቅኝቱ ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ የሚካሄደውን የከበራ ስርዓት ምን እንደሚመስል ያሳያል፡፡ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት የተገኘው መረጃ አውዳዊ ንድፈ ሀሳብን በመከተል ተብራርቶና ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ ትንታኔው ሲካሄድ በቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ በምልከታ እና በተተኳሪ የቡድን ውይይት ለማረጋገጥ ተሞክሯል፡፡ በዚህ ሁኔታ በአንዱ ዜዴ የተገኘው መረጃ በሌላ ዘዴ የማረጋገጥ ስራ ከተሰራ በኋላ ወደ ትንታኔ ተገብቷል፡፡ የከበራ ስርዓቱን ቅድመ መውሊድ፣ የመውሊድ ጊዜ እና ድህር መውሊድ በማለት ከፋፍዬ አቅርቤዋለሁ፡፡

### 6.1 ቅድመ መውሊድ

በምዕራፍ ሶስት በስልጤ ብሔረሰብ ዘንድ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ መውሊድ እንደሚከበር እና አብላጫዎቹ በአሁን ጊዜ መከበራቸው መቋረጡን ተመልክተናል፡፡ ነገር ግን የተወሰኑ መውሊዶች በአሁኑም ዘመን በመከበር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የአልከሶ መውሊድ ዋነኛው ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል የአልከሶ መውሊድ የአከባበር ሁኔታ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ሁኔታ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡

በአልከሶ መስጂድ ውስጥ በየወሩ ሀሙስ ቀን የወሩ መውሊድ በሚል መውሊድ ይከበራል፡፡ ይህን እና ሌሎቹንም መውሊዶች በቃዲ[90] የሚመራ ኮሚቴ አለ፡፡ የዚህ ኮሚቴ መሪ ዋናው

[90] There are *kadis* who, in their liberal interpretation of religious law, do not hesitate to deviate from *taklidand* who, by means of the techniques *of takhoyyur* and *talfik,* have scored achievements not inferior to those of parliamentary legislation. In Saudi Arabia, the *kadis,* in the absence of an express provision as to a particular matter in authoritative Hanball literature–as designated by decree–are permitted to rely on elements from other doctrines as far as it is in the public interest to do so, and there have in fact been cases in which they applied the *maslaha* mechanism in their decisions. The *kadis* make use of their personal authority, sometimes with the assistance of mediators, to bring about a peaceful settlement of disputes and to give the effect of judgments to compromises that have been reached. They thereby continue a tradition of tribal arbitration. This method also prevents a confrontation

የመስጂዱ አስተዳዳሪ ወይም መሪ ናቸው። በሌላ አገላለጽ የመስጂዱ መሪ ቃዲ ናቸው። የእኚ መሪ ዋና የስራ ድርሻ ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን መከታተል ነው። ይህ ኮሚቴ በስር በርካታ ንዑሳን ከሚቴዎች አሉ። ለምሳሌ እንቀግዳ ተቀባይ፣ የምግብ ክፍል፣ የእንጨት ክፍል፣ የውሃ ክፍል፣ የመብራት ክፍል፣ ጸጥታ አስከባሪ ክፍል ወዘተ የሚሉ ናቸው። ሃይማኖታዊ ስርዓትን የሚያስኬዱ በሼኾች የተወቀረ ከሚቴም አለ። የዚህ ኮሚቴ ዋና ስራ በቃዲው ስር ሆነው ሃይማኖታዊ የሆኑ ጉዳዮችን ማስኬድ ነው። ይህ ማለት ሶላት በወቅቱ እና በአግባቡ እንዲሰገድ ማድረግ፣ በየቦታው እየተዘዋወሩ ሀዲስ መናገር ዋና ዋና ስራዎች ናቸው።

በአልከሶ መስጂድ በወር አንድ ጊዜ ሀሙስ እለት የሚከበረው ወርሃዊው መውሊድ ለአካባቢው ነዋሪዎች ሃይማኖታዊ ክንዋኔ የማከናወኛ አጋጣሚ ከመሆኑ ባሻገር ስለ አካባቢያቸው ጉዳይ መወያያ፣ የተጣላን ማስታረቂያ፣ የተበደለን መካሻ፣ ያጠፋን መቅጫ እና ማስተማሪያ፣ እንዲሁም የተራበን መመገቢያ አጋጣሚ በመሆን ያገለግላል። መውሊድ በአለማችን ለሃይማኖታዊ ግልጋሎት ብቻ ሳይሆን ለፖለቲካዊ ጥቅምም እንደሚውል የግብጽን ነባራዊ ሁኔታ በመጥቀስ Bronislav(2008)ያስረዳሉ። ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ወርሃዊ መውሊድ ለዋናው መውሊድ የሚሆን ገንዘብ እንዴት እንደሚሰባሰብ እና እነ ማን ወዴት ሄደው ማሰባሰብ እንዳለባቸው ወይይት ይደረጋል። ስለዚህ የሀሙስ ወርሃዊ መውሊድ ለዋናው መውሊድ ቅድመ ዝግጅት ማድረጊያ መድረክ በመሆን ያገለግላል ማለት ይቻላል። ዋናው የአልከሶ መውሊድ በአካባቢው ሰዎች ዘንድ በየወሩ የሀሙስ መውሊድ እና አመቱን ሙሉ የሚታሰብ ቢሆንም ቅድመ ዝግጅቱ የሚጀምረው ግን በዋናነት ሶስት ወር ሲቀረው ነው። የመስጂዱ አስተዳደር ግን ለበዓሉ አመቱን ሙሉ ይዘጋጅበታል ማለት ይቻላል። ይህን ጉዳይ አቶ ነስሩ[91] በሚከተለው መልክ አስረድተውኛል

መውሊዱ በዚህ እና መሰል ሁኔታ አመቱን ሙሉ ሲታሰብበት ይቆይና ሶስት ወር ሲቀረው ግን ዋናው ዝግጅት ይጀምራል። ዝግጅቱ የሚጀምረው በመስጂዱ አስተዳደሪ የተጻፈ ደብዳቤ በመያዝ የተወሰኑ ሰዎች የስልጤ ብሔረሰብ ተወላጆች እና መውሊድ ማክበር የሚፈልጉ

with religious law. The proceedings are simple, quick and matter-of-fact. Druze *kadis* are sometimes called upon to act as arbitrators in criminal cases heard before civil courts.

[91] ቃለ መጠይቅ 23/05/2008

ሰዎች ወደ ሚገኙባቸው ክፍለ ሀገራት በመሄድ የመውሊዱ መዳረስ በማብሰር መዋጮ እንዲያዋጡ ያደርጋሉ፡፡ አንድ ወር ሲቀረው ጀምሮ ግን ዝግጁቱ የበለጠ እየደመቀ ይሄዳል፡፡

መውሊዱ አንድ ወር ሲቀረው ከሚታሰብበት ጉዳይ መካከል አንዱ የጸጥታ ጉዳይ ነው፡፡ በበዓሉ የሚሳተፈው ህዝብ ከፍተኛ ስለሆነ ችግር እንዳይፈጠር ከወረዳው እና ከዞኑ የጸጥታ ሀይል ይመደባል፡፡ እንደ ገራድ ኑረሰቦ[92] እና ሃምሳ አለቃ ወርቁ[93] አገላለጽ መንግስት ለመውሊዱ ትኩረት መስጠት የጀመረው ከ1986 ዓ.ም ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመውሊዱ ሰሞን ችግር እንዳይፈጠር መንግስት የጸጥታ ሀይል መመደብ ጀምሯል፡፡ ከገራድ ኑርሰቦ በተጨማሪ ሀጂ ሀምዴኖ[94] መስጂዱም ሆነ መውሊዱ በመንግስት እውቅና የተሰጠው በፊይድ ዘመን ነው፡፡ ምክንያቱም እሳቸው ከመግስትንም ጋር የሚግባቡ ስለነበሩ መብራት፣ ውሃ፣ መንገድ ወዘተ እንዲገባ አስደርገዋል፡፡ አቶ ሁሴይኒ ደግሞ "በአሁኑ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች መንገድ ላይ እና ሀረም ድረስ በመግባት መውሊድ የሚያከብሩ ሰዎችን አታክብሩ ብለው መረበሽ ስለጀመሩ የጸጥታው ሁኔታ ከቀድሞው ተጠናክሯል" ይላሉ፡፡ በመሆኑም የመስጂዱ አስተዳደር ለወረዳው እና ለዞኑ የጸጥታ ሀይል መስሪያ ቤት የተለመደው ትብብር እንዲያደርጉ መልዕክት በመላክ ትብብር እንዲያደርጉላቸው ይጠይቃሉ፤ትብብርም ይደረጋል፡፡

ባጠቃላይ ቅድመ ዝግጅቱ ከላይ በተመለከትነው መሰረት ይጠናቀቅና በዓሉ ሲቃረብ የተለያዩ ነጋዴዎች ለንግዳቸው የሚሆን ጊዜያዊ ቤት ወይም ዳስ ያዘጋጃሉ፡፡ በዳሳቸው ውስጥ የተለያዩ ቁሳቁሶችን አቅርበው መሸጥ ይጀምራሉ፡፡ ጸጥታ አስከባሪዎችም በተዘጋጀላቸው ማረፊያ ቦታ ያርፋሉ፡፡ አብላጫ የበዓሉ ታደሚዎችም በየኸለዋዎቻቸው ዱኣ መቀመጥ ይጀምራሉ፡፡ በመስጂዱ አስተዳደር በኩል ደግሞ ከሩቅ ቦታ ለሚመጡ፣ የቅርብ ዘመድ ለሆኑ፣ እና ከመንግስት አካል ወይም ከእስልምና ጉዳይ መስሪያ ቤት ለሚመጡ ሰዎች ልዩ ማረፊያ ቦታ ይዘጋጃል፡፡ ለሁሉም ኸለዋዎች ኸዳሚ(አስተናጋጅ) ከእነ ረዳቶቻቸው በትክክል መመደቡ ይጣራል፤ ያልተመደበላቸው ካሉ ይመደብላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቅድመ ዝግጅቱ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ሶስት ወር ሲቀረው ተጀምሮ ለመውሊዱ ሁለት ቀን ሲቀረው ይጠናቀቃል በማለት አቶ ሁሴይኒ ፣ ገራድ ኑርሰቦ፣ እመት ሀረም እና ወ/ሮ ሉባባ ያስረዳሉ፡፡

---

[92] ቃለ መጠይቅ 24/05/08
[93] ቃለ መጠይቅ 26/05/08
[94] ቃለ መጠይቅ 25/08/07

ከዚህ በተጨማሪ በአመት አንድ ጊዜ በረቢየል አወል ወር ላይ ነብዩ ሙሀመድ የተወለዱበት ቀን በማስመልከት መውሊድ ይከበራል፡፡ በዚህ መውሊድ ቀን በዋናነት የሚካሄደው የነብዩን ታሪክ ማውሳት፣ መንዙማ ማለት፣ ቁርኣን መቅራት፣ ሷላት በጀማ(በጋራ) መስገድ፣ ምግብ አዘጋጅቶ የተራቡ ሰዎች መመገብ እና ዋናው የአልከሶ መውሊድ ስለመቃረቡ እና ምን ዝግጅት መደረግ እንዳለበት መወያየት እንደሆነ በ2007 ዓ.ም በቦታው ተገኝቼ ተመልክቻለሁ፡፡ ስለዚህ በአልከሶ ሀረም መውሊድ በየወሩ ሀሙስ ቀን፣ ነብዩ የተወለዱበት ቀን እና ለረመዳን አስራ አምስት ቀን ሲቀረው ዋናው መውሊድ ይከበራል፡፡ እሸቱ(1971፣23) አገላለጽ በሼኽ ሁሴን መስጂድ የሼኽ ሁሴን ደጋፊዎች ክብረ በዓል ለማክበር በአመት ሁለት ጊዜ ወደ ባሌ ይሄዳሉ፡፡ የመጀመሪያው እና ዋነኛው የካቲት ወር ላይ በደመቀ ሁኔታ የሚከበረው ሲሆን ሁለተኛው ነሀሴ የሚከበረው ነው ይላል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ Trimingham(1952፡253) የድሬ ሼኽና ሁሴን መውሊድ በአመት ሁለት ጊዜ ቢከበርም የካቲት ወር[95] ላይ ግን በደመቀ ሁኔታ እንደሚከበር ያስረዳሉ፡፡ በአልከሶ መስጂድ ግን መውሊድ በአንድ አመት ውስጥ እስከ አስራ አራት ጊዜ ሊከበር ይችላል፡፡ ምክንያቱም በየወሩ አንድ ቀን አለ፣ የረቢየል አወል መውሊድ አለ፡፡ እንዲሁም ዋናው መውሊድ በአመት አንድ ጊዜ ይከበራል፡፡ እነዚህ መውሊዶች ሲደመሩ እስከ አስራ አራት ይደርሳሉ፡፡

የመውሊዱ ቅድመ ዝግጅት የሚጠናቀቀው ቅዳሜ እለት ነው፡፡ ቅዳሜ ዕለት የአልከሶ ሀረም ገና በጠዋቱ ከፍተኛ ቁጥር ባለው የመውሊድ አክባሪዎች ይሞላል፡፡ አካባቢውም ከወትሮው በተለየ ሁኔታ ይደምቃል፡፡ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ህዝብ ያልኩበት ምክንያት በበዓሉ የሚሳተፈው የህዝብ ቁጥር በትክክል ስለማይታወቅ ነው፡፡ ሀጂ ኑረዲን[96] እና ገራድ ኑርሰቦ[97] በአጠቃላይ በበዓሉ በግምት ከሁለት መቶ ሺህ በላይ ምዕመናን እንደሚታደሙበት ሲናገሩ በ2009 ዓ.ም የዞኑ ባህል፣ ተሪዝም እና የመንግስት ኮሚኒኬሽን መምሪያ ያስጠናው ጥናት በአሁኑ ጊዜ በመውሊዱ የሚሳተፈው ህዝብ ብዛት እስከ ግማሽ ሚሊዮን ይደርሳል ይላል፡፡

---

[95] እነዚህ ጸሀፊዎች ዋናው መውሊድ የሚከበረው የካቲት ወር ነው ቢሉም የድሬ ሼኽና ሁሴን ዋናው መውሊድ የሚከበረው ከአረፋ በዓል ጋር ተያይዞ ስለሆነ የሚከበርበት ጊዜ ከአመት አመት ይለያያል፡፡

[96] ቃለ መጠይቅ 26/10/07

[97] ቃለ መጠይቅ 24/05/08

እነዚህ ምዕመናን ከተለያዩ ቦታዎች የሚሰባሰቡ በመሆናቸው ሀረሙ ውስጥ የመውሊድ ሰሞን ከስልጥኛ በተጨማሪ ብዙ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡ ከነዚህ መካከል ጉራጊኛ፣ ኦሮምኛ፣ ሀዲየኛ፣ አላብኛ፣ አማርኛ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ ይህ የቋንቋ ስብጥር የሚያሳየው መውሊዱን ከስልጤ ብሔረሰብ በተጨማሪ በርካታ ብሔረሰቦች እንደሚሳተፉበት ነው፡፡ ነገር ግን ከዋነው መስጂድ የሚተላለፈው መልዕክትም ሆነ በድምጽ ማጉያ ተዘዋውረው መልዕክት የሚያስተላልፉ ሰዎች የሚጠቀሙት ቋንቋ ስልጥኛ ነው፡፡

የአልከሶ መውሊድ አክባሪዎች የሚሰባሰቡት ከአዲስ አበባ፣ ናዝሬት፣ ከአሰላ፣ ከሻሸመኔ፣ ከወላይታ፣ ከቡታጀራ፣ ከወራቤ፣ ከዳሎቻ፣ ከጦራ፣ ከሳንኩራ ወዘተ ነው፡፡ ከነዚህ ቦታዎች በተጨማሪ በትክክል ከየት እንደመጡ ባይታወቅም በርካታ የቤት መኪናዎች በሀረሙ ዙሪያ ቆመው ይታያሉ፡፡ ይህ የሚያሳየው በሀገራች በሚከበሩ መውሊዶች ምዕመናን መውሊዱ ከሚከበርበት አከባቢ ማህበረሰብ በተጨማሪ ከሌላ ቦታ(ከሀገር ውስጥ እና ከውጭሀገር) እንደሚሳተፉ ነው፡፡ ስለዚህ ይሁኔታ በሀገራችን የሚከበሩ መውሊዶች የጋራ ባህሪ ነው ማለት ይቻላል፡፡ በዋናው የአልከሶ መውሊድ ሰሞን ከሀገር ውስጥ መውሊድ አክባሪዎች እና ጎብኚዎች በተጨማሪ የውጭ ሀገር ዜጎችም የመውሊድ አከባበሩን እና በከበራው ውስጥ ያለውን ትውፊት ለመመልከት አልከሶ ሀረም ይገኛሉ፡፡

Eshetu (1973: 28)፣ Trimingham (1952፣38) እና Gemechu (2013፣58) በድሬ ሼኽና ሁሴን መውሊድ ላይ መውሊድ አክባሪዎቹ ጉራጌዎች፣ ሲዳማዎች፣ ሶማሌዎች፣ እና አማራዎች እንዲሁም ከኢትዮጵየዊያን በተጨማሪ ሶማሊያዊያን፣ ኬኒያውያን፣ ኢራቃዊያን፣ ወዘተ እንደሚገኙ ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም ኑረዲን (2012፣56) ደግሞ በአብሬት መውሊድ ከጉራጌ ዞን እና ከኢትዮጵያውያን ውጭ የሆኑ ምዕመናን እንደሚሳተፉ ያስረዳል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሰሚራ (2006፣85) በጥሩሲና "ገዳም" ውስጥ በሚካሄደው መውሊድ ታዳሚዎች የሚሰባሰቡት ከጎንደር፣ ከሀረር፣ እና ከኮምበልቻ እንደሆነ ታስረዳለች፡፡ መሀመድ(2009) በወሎ ቦረና በሚካሄደው የመውሊድ ስርዓት ላይ ከተለያዩ ቦታዎች ምዕመናን እንደሚሰባሰቡ ያስረዳሉ፡፡ እንደ Yasuo and Minako (2009፣498) አገላለጽ የየሀን( Ya'a) ክብረ በዓል ለማክበር ወደ ስፍራው የሚጎዙ ምዕመናን ቦታው ላይ በብዛት የሚገኛት ከዋናው በዓል አንድ ቀን ቀደም ብለው ነው፡፡ ምዕመና የሚሰባሰቡትም ከአዲስ አበባ፣ ጎንደር፣ አሶሳ፣ ጊምቢ፣ ነቀምት ወዘተ ሲሆን እነዚህ ምዕመናን እዚህ ቦታ ላይ የሚገኙበት የየራሳቸው የሆነ ዓላማ አላው፡፡ ከኢትዮጵያ ውጭ በህንድ እና በግብጽ

በሚካሄዱ የመውሊድ ስርዓቶች ላይ የሚሳተፉ ምዕመናን ከተለያዩ ቦታዎች እንደሚሰባሰቡ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡

## 6.2 ዕለተ መውሊድ እና ዋና ዋና ፎክሎራዊ ክንውኖች

የአልከሶ መውሊድ ተጀምሮ እስከጠናቀቅ ድረስ በርካታ ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ(ፎክሎራዊ) ክንውኖች ይከናወናሉ፡፡ ከሃይማኖታዊ ክንውኖች መካከል ሶላት በጀማ መስገድ፣ ቁርኣን መቅራት፣ ሀዲስ መናገር እና ማድመጥ ይገኝበታል፡፡ እነዚህ ሃይማኖታዊ ክንውኖች ለብቻቸው ተነጥለው መቀመጣቸው ፎክሎራዊ ባህሪ የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ሃይማኖት በፎክሎር ስር ከመጠኑ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው (McCarel፣1986)፡፡ እርስ በእርስ ማህበራዊ ግንኙነት ማጠናከር፣ ዚያራ ማድረግ፣ ጫት በጋራ መቃም፣ ምርቃት መደራረግ፣ ባህላዊ አልባሳትን መልበስ፣ መንዙማዎችን የተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማዜም(ማለት) ወዘተ ደግሞ ከፎክሎራዊ ጉዳይ አንጻር የምንመለከታቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም እነዚህን እና መሰል ጉዳዮችን ቀጥለን እንመለከታቸዋለን፡፡

### 6.2.1 የሶላት የመስገድ ስነ ስርዓት

ሶላት በእስልምና ሃይማኖት አንድ ሰው እድሜው ሰባት እና ከዚያ በላይ የሆነ ሰው የግድ ሊፈጽመው ከሚችላቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ነው፡፡ ስለ ሶላት ምንነት Shaikh Muhammad Naasir-ud-Deen(2011) የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> The Prayer was one of the most important things which he explained to the people, verbally and practically, even praying on the pulpit once -standing, bowing and prostrating, and then saying to them, I have done this so that you may follow me and learn my prayer. He obligated us to copy him in his prayer, saying, Pray as you have seen me praying. He also gave the good tidings to whoever prayed like him that such a person has a covenant with Allah that He will enter him into the Garden, saying, There are five prayers which Allah, Mighty and Sublime, has made compulsory: he who performs ablution well for them, prays them at their proper

times, and is complete in their bowings, prostrations and humility, he has a guarantee from Allah that He will forgive him; but he who does not do so, has no guarantee from Allah: if He wishes, He will forgive him or if He wishes, He will punish him.

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ሶላት በእስልምና ትልቅ ቦታ ያለው እና በቀን አምስት ጊዜ በተቀመጠለት ሰዓት መሰረት የግድ ሊገበር የሚገባ ተግባር እና የነብዩ ፈለግ እንደሆነ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንድ ሰው ሙስሊም ከሆነ እና በቀን አምስት ጊዜ በአግባቡ ሶላት ከሰገደ ከአላህ ዘንድ ምንዳ እንደሚቸረው እና ይህን ካላደረገ ግን ቅጣት እንደሚጠብቀው ጥቅሱ ያስረዳል፡፡ ይህ ጥቅስ ቡኻሪ እና ሙስሊም በተለያዩ የሀዲስ መጽሀፎቻቸው አስፍረውት ይገኛል፡፡ ሙሀመድ አብዱልቃዲር የተባሉ ጸሀፊ ደግሞ አምስቱ የፈርድ የሶላት ወቅቶች ውጭ መስገድ ተቀባይነት እንደሌለው ጽፈዋል፡፡

ከዚህ አንጻር በአልከሶ መውሊድ ሰሞን በቀን አምስት ጊዜ ግዴታ(ፈርድ) ይሰገዳል፡፡ እነሱም ሱጺ(ፈጅር)፣ ዙሀር፣ አሱር፣ መግሪብ እና ኢሻ ናቸው፡፡ በዚህ መውሊድ ሰሞን ሶላት የመስገድ የራሱ የሆነ ቅድመ ዝግጅት ይደረጋል፡፡ የመጀመሪያው ውዱኡ ማድረግ ነው፡፡ ውዱኡ ከተደረገ በኋላ ወደ መስገጃ ቦታ በመሄድ ፊትን ወደ ሶላት መስገጃ አቅጣጫ ካባ ማዞር ግዴታ ነው፡፡ በዚህ መስጂድ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በአለማችን በየትኛውም አቅጣጫ የሚገኙ ሙስሊሞች ሶላት ሲሰግዱ ወደ ካባ ፊታቸውን የማዞር ግዴታ አለባቸው፡፡ ይህን በማስመልከት Fehervari (1970፣702-707) የሚከተለውን ይላሉ፡፡ “Qibla is the direction to face when Muslim pray at all times. Initially, the direction of the Qibla was towards the Al-Aqsa Mosque in Jerusalem. The Qibla was then directed towards Ka’aba in Mecca after about two years after Hijra when the Prophet Muhammad received a revelation from Allah the Almighty.” ይህ ማለት በአለማችን የሚገኙ ሙስሊሞች በየትኛውም የአለማችን ክፍል ቢገኙም ሶላትን ለመስገድ ፊታቸው ወደ ካዕባ የማዞር ግዴት አለባቸው፡፡

በአልከሶ ሶላት ሲሰገድ የምዕመናኑ የአቋቋም ወይም ቅደም ተከተል ሁኔታ የራሱ የሆነ ስርዓት አለው፡፡ አዛን ከተባለ በኋላ የሱና(ግዴታ ያልሆነ) ሶላት ከተሰገደ በኋላ ፈርደ ሶላት ይሰገዳል፡፡ በፈርድ ሶላት ጊዜ መጀመሪያ ኢማሙ ፊቱን ወደ ካባ በማዞር ከሁሉም ሰጋጆች

ፍት ለፊት ይቆማል። ከኢማሙ በመቀጠል ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ የሃይማኖት አባቶች ይቆማሉ። ከሃይማኖት አባቶች ጎን ደግሞ ከፌደራል፣ ከክልል፣ ከዞን እና ከወረዳ የተሰባሰቡ የመንግስት(ሙስሊም የሆኑ) እና የእስልምና ጉዳዮች መስሪያ ቤት ባለስልጣናት ይቆማሉ። ከእነዚህ በመቀጠል የአካባቢው እና ከሌላ ቦታ የመጡ የእድሜ ባለጸጋዎች እና የአገር ሽማግሌዎች ይቆማሉ። ከዚህ በኋላ ሌሎች ወንድ አዋቂዎች እና ልጆች ይቆማሉ። ከወንዶች በመቀጠል ከወንዶች በስተጀርባ በኩል ሴቶች በአስር ሜትር ያህል ራቅ ብለው ይቆማሉ። ኢማሙ ከላይ የገለጽኩት ሁኔታ በተክክል መከናወኑን ካረጋገጡ በኋላ መስገድ ይጀምራል።

ይህ ሁኔታ በአልከሶ ምስጂድ ብቻ ሳይሆን በየትኛውም ሶላት መስገጃ ስፍራ እና መስጂድ የሚካሄድ ስርዓት ነው። ለምሳሌ Yasuo and Ishihara (2009፣501) በያ(Ya'a) ያለው የሶላት አሰጋገድ ሁኔታ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል። "On arriving at the field, they sat down side-by-side forming lengthy parallel lines (Plate 5), turning their backs to the village, facing northward, the direction of Mecca. Women took their positions at the rear of men. The *Imam* of Ya'a sat in front of the lines, to guide the prayer." ይህ ማለት በያ ክብረ በዓል ማክበሪያ ቦታ እና በአልከሶ መውሊድ ማክበሪያ ቦታ ያለው የአሰጋገድ ሁኔታ ተመሳሳይ ነው ማለት ይቻላል።



ፎቶ 7፡- ምዕመናኑ የዙህር ሷላት ሲሰግዱ[98]

በመውሊድ ሰሞን የዚህ አይነት የአሰጋገድ ስርዓት በብዛት የሚስተዋለው በዙሁር እና በአሱር ሶላት ወቅት ብቻ ነው፡፡ በሌሎቹ ወቅቶች ግን ምዕመናን በያሉበት ይሰግዳሉ፡፡ ለምሳሌ በ2007 እና 2008 የዋናው መውሊድ ሰሞን ምዕመናኑ የዙሁር እና አሱር ሶላቶችን በዋናው ሀረም  ውስጥ ተሰብስበው ሲሰግዱ ሌሎቹን የሶላት ወቅቶችን ግን ኸለዋ ውስጥ ያሉት ኸለዋ ውስጥ፣ ዳስ ውስጥ ያሉት ዳስ ውስጥ ባጠቃላይ ሁሉም በያለበት ሰግዷል፡፡ ይህ ሁኔታ እንዳይፈጠር ሁሉም ምዕመናን በጋራ በአንድ ቦታ እንዲሰግድ ጥረት ቢደረግም በሚገኙበት ቦታ የሚሰግዱ ሰዎች ብዙ ጊዜ ፍቃደኛ ስላልሆን እንደተተው ሼኽ በህረዲን ይናገራሉ፡፡ በተመሰሳይ ሁኔታ አቶ ሁሴይኒ ደግሞ ብዙ ጊዜ ጫት የምቅሙ ሰዎች የተቀመጡበት ቦታ ስለሚሞቃቸው የመስገጃ ቦታ ሄዶ ከመስገድ ይልቅ በያሉበት ቦታ መስገድን ይመርጣሉ ይላሉ፡፡ ይህን ሁኔታ ከእስልምና አንጻር ስናየው በየቦታው ተበታትኖ መስገድ አይፈቀድም፡፡ በየትኛውም ቦታ ያለ ሰው በተለይ ወንድ የአዛን ጥሪ ከሰማ ወደ መሲጂድ የመሄድ ግዴታ አለት፡፡ ይህ ግዴታ ግን በአልከሶ መውሊድ ሰሞን በተወሰነ ደረጃ ሲጣስ ይስተዋላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ሰጋጆች በጎን በኩል ቢሆንም ከኢማሙ ፊት ቆመው ይሰግዳሉ፡፡ ይህም ሁኔታ ከሰላት አሰጋገድ መርህ አንጻር ስህተት ነው፡፡

[98] ፎቶ ባጥኚው፣ 14/09/07 አልከሶ

## 6.2.2. ሀዲስ መናገር

ሐዲስ ነብዩ ሙሐመድ ያደረጓቸውንና የተናገሯቸውን ነገሮች (የየዕለት ተግባራትና አስተምህሮዎች) የሚያወሱ የዘገባ ሰነዶች ሐዲስ ይባላሉ፡፡ ከነዚህም መካከል በተዓማኒነት ደረጃቸው የላቁና የተረጋገጡት እንዲሁም አብዛኞቹ ምሁራን የተስማሙባቸው ሐዲሶች ሰሂህ በመባል ይታወቃሉ፡፡ ሐዲስ ከቁርዓን ቀጥሎ የሚገኝ ሁለተኛው የእስልምና ምንጭ ነው፡፡ ሙስሊም ትክክለኛነቱ በተረጋገጠው ሀዲሳቸው ስለ ሀዲስ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ “The word ‘Hadith’ is mentioned in the Qur’an referring to the guidance given to Rasulullah by Allah. In Surah al-Dhuhaa, Allah Ta’ala describes the three conditions of Rasulullah being an orphan, wandering about (in search of guidance) and being poor. In response to wandering for guidance, Allah Ta’ala granted guidance to Rasulullah.” ካሉ በኋላ “The knowledge through which the sayings, the actions, the conditions and confirmations of Rasulullah are known. Conditions here refer to only voluntary conditions, not involuntary conditions”. በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንደ ሙስሊም አገላለጽ ሀዲስን ከሁለት ጉዳዮች አንጻር የምንመለከተው ሲሆን እነሱም አንደኛ "al-Riwaayah" refers to narrating of Ahaadith, writing them and preserving them. እና ሁለተኛ "al-Diraayah" refers to understanding the different aspects of Hadith, the chain of narrators, the authenticity of the Hadith and the meaning of the Hadith. ናቸው፡፡[99]

Billa (2012፣2) የተባሉ ጸሀፊ ከጥንት ጀምሮ ስለ እስልምና እና ነብዩ ሙሀመድ ትምህርት ከሚሰጥባቸው ወይም መልዕክት ከሚተላለፍባቸው መንገዶች መካከል ሀዲስ ዋነኛው እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ባጠቃላይ ሀዲስ ማለት ሙስሊሙ ማህበረሰብ ሊተዳደርባቸው እና ሊተገብራቸው የሚገቡ በነብዩ ሙሀመድ እና በሶሀቦቻቸው የተላለፉ መልዕክቶች መጠሪያ ነው፡፡ በመሆኑም የአልከሶ መውሊድ ሰሞን በርካታ ሀዲሶች ሲነገሩ ማዳመጥ የተለመደ ነው፡፡ የሀዲሶቹን ይዘት ዋና ዋና ይዘቶችን ስንመለከታቸው በሶስት ጎራ መድበን የምንመለከታቸው ናቸው፡፡ አንደኛ የአላህን፣ የነብዩ መሀመድን፣የአልከስዬን ትልቅነት የሚሰብኩ ናቸው፡፡ ሁለተኛ ስለ ወንደማማችነት ወይም መዋደድና መረዳዳት የሚሰብኩ

[99] *Sahih Muslim* Vol.2 Pg.414; Qadeemi Kutub Khana Karachi Pakistan - Hadith7435; edited by Sheikh Khalil Ma’moon Sheeha Dar al-Ma’rifah Beirut

ሲሆኑ በሶስተኛ ጎራ የሚመደበው ደግሞ በሃይማኖት መጠናከር አስፈላጊ እንደሆነ የሚያትቱ ናቸው፡፡ በመሆኑም በአልከሶ መውሊድ ሰሞን ሲነገሩ ከሰሟኋቸው ሀዲሶች ለምሳሌ ያህል የተወሰኑትን እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

**ስለ ነብዩ ሙሀመድ ታአምረኛነት የተነገሩ ሀዲሶች፡-**

ነብዩ ሙሀመድ በህወት ዘመናቸው በርካታ ፈተና እና ችግር ገጥሞቸዋል፡፡ በተለይ መንገድ ሲጓዙ እና በጦር ሜዳ ብዙ ጊዜ የውሀ እጥረት ይገጥማቸው ነበር፡፡ ከእለታት አንድ ቀን ቁረይሾችን ለመውጋት በሄዱበት ወቅት የውሀ እጥረት ገጠማቸው፡፡ እሳቸው እና ወታደሮቹ ሰላት ይሰግዱ የነበረው በተህሙም ነበር፡፡ በመሆኑም እሳቸው አለህን ጠይቀውት አያሣፍራቸው ነበረና እጃቸውን ወደ ላይ በማንሳት "ያ አላህ እንደ ምታየው እኔና ኡመቴ ይህው በውሀ ጥም እያለቅን ነው" ብላው እያለሙኑ እያለ ዱአቸውን ሳይጨርሱ ከጣቶቻቸው መሀል ከፍተኛ የሆነ ውሀ መፈለቅ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ አጠገባቸው የነበሩ ወታደሮች በሙሉ እሳቸው በአለሀ ዘንድ ምን ያህል ተሰሚነት እንዳላቸው ሲመለከቱ አለቀሱ፡፡ ቀጥለውም ከነብዩ እጅ በፈለቀው ውሀ ጥማቸውን ቆረጡ፣ ልባሳቸውን አጠቡ፣ ኡድኣ አድርገው በጀማ ሰገዱ፡፡[100]

በነብዩ ሙሀመድ ዘመን አልፎ  አልፎ ከፈተኛ የሚባል ረሀብ ያግጥማቸው ነበር፡፡ በመሆኑም እሳቸውም በጣም ተርበው ያውቃሉ፡፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ ከመቼውም በተለየ ሁኔታ ከፈተኛ የሆነ ድርቅ አጋጠመ፡፡ በዚህ ጊዜ የነብዩ ሙሀመድ ባለቤት አዒሻ ነበረች፡፡ በዚህ ችግር ግዜ በሁሉም ሰዎች ቤት ምንም የሚላስ የሚቀመስ እህል አልነበረም፡፡ ነገር ግን አዒሻ ለክፉ ቀን ብላ ደብቃ ያስቀመችው ሁለት ቁና እህል ነበረ፡፡ በመሆኑም ይህን እህል ምግብ ሰርታ ለበለቤቷ ነብዩ ሙሀመድ ስታቀርብ ከየት አመጣሽ ሲሏት ለክፉ ቀን ብዬ ደብቄ አስቀምጬው ነበር አለቻቸው፡፡ በዚህ ጊዜ እሳቸውም ደስ ብሏቸው በአከባቢው የነበረውን የተራብ ሰው በሙሉ ሰብስበው ያንን ትንሽ ምግብ አጥግበው አበሉ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ያንን ሁለት ቁና እህል ለሶስት ወር ያህል (ድርቁ እስኪጠፋ ድረስ) የአከባቢው ህዝብ በሙሉ እየቀለቡ ኖሩ እየተባለ ይነገራል፡፡[101]

---

[100] 24/09/07 አልከሶ ሀረም

[101] 24/09/07 አልከሶ ሀረም

ነብዩ ሙሀመድ በህይወት ዘመናቸው አላህን እጅ አንስተው ከለመኑት አሳፈሯቸው አያውቅም፡፡ ከሁሉም የሚገርመው ግን አንድ ጊዜ መካ እያሉ በአከባቢው አንድ አስቸጋሪ ሰው ነበረ፡፡ ይህ ሰው ከሌሎች ሰዎች አልፎ ነቢዩንም ይተነኮሰቸው ነበር፡፡ በመሆኑም እሳቸው ደጋግመው ቢመክሩትም ሊመለስ እና ሊስተካከል አልቻለም፡፡ ከዚህም አልፎ ተርፎ መዛተ ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ የሰውየው ሁኔታ ከአቅማቸው በላይ ስለሆነ እጃቸውን ወደ አላህ በማንሳት "ያ ረቢህ ለዚህ ሰው ሀጃውን ስጠው" ብለው ለመኑ፡፡ ነቢዩ ሙሀመድ ዱአቸውን አድርገው እንደረሱ ከአንድ መኖሪያ ቤት አንድ ደንባራ በቅሎ ስትበር ወጥታ እቃ ጠፍቶት እንደሚፈልግ ሰው መራሯጥ ጀመረች፡፡ በመጨረሻም ፊቷን ወደ ገበያ በማቅናት ፈረጠጠች፡፡ ገበያ እንደደረሰችም በብዙ ገበያተኞች መሀል ገብታ አንዳች ነገር መፈለግ ጀመረች፡፡ በፈለጋዋ ያኔ በነብዩ እና በኡመታቸው ሲያምጽ የነበረውን ሰው ከሰዎች መካከል ፈልጋ አገኘችው፡፡ በዚህ ጊዜ ሌላውን ገበያተኛ እና ዕቃውን ሳትነካ አማጬን ሰውዬ በገበያ መሀል ረጋግጣ ገደለቸው፡፡[102] ይህ የሚያሳየው ነቢዩ ሙሀመድ በአላህ ዘንድ ምን ያህል ተቀባይነት እና ትልቅ ቦታ እንዳለቸው ነው፡፡

**አላህ መሀሪ ነው የሚል ይዘት ያለው ሀዲስ፡-** በድሮ ዘመን በአንድ መንደር አንድ ክርስትያን ሴትዬ ከመስጂድ ጎን ትኖር ነበር፡፡ ለመስጂድ እና መስጂድ ገብተው ለሚሰግዱ ሙስሊሞች ከፍተኛ ጥላቻ ነበራት፡፡ በመሆኑም እነዚህ ሙስሊሞችን ስገቡ ሲወጡ አዛ(ማስቸገር) ታደርጋው ነበር፡፡ ምዕመናኑም ባገኟት ቁጥር የአላህ በላ ይውረድብ ይሏት ነበር፡፡ አንዷንዶቹ ደግሞ እሷ የእሳት እንደሆነች ይናገሩ ነበር፡፡ እቺ ሴት ለመስጁዱ ካላት ጥላቻ የተነሳ አንድ ቀን ስታልፍ መስጂዱ በር ላይ የተሸና ሽንት(ሰገራ) አንስታ መስጂዱ ለይ ስትወረውረው መስጂዱ ቀዳዳ ኖሮት ወደ ውስጥ ንፋስ ገብቶ ያስቸግር በነበረ ቀዳዳ ላይ ተለጥፎ ቀዳዳውን በመድፈኑ ንፋሱ ወደ ውስጥ መግባን አቆመ፡፡ በዚህ ሰበብ የተነሳ ይቺን ሴት አላህ ጀነት ወፈቃት (አስገባት) ይባላል፡፡

ከዚህ ሀዲስ የምረዳው የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር ምንም አይነት ጥፋት ቢያጠፋም አንድ ቀን እንኳን ቢሆን ለእስልምና የሚጠቅም ስራ ከሰራ እድሜ ልኩን ያጠፋውን ጥፋት እንደሚምረው ነው፡፡ በዚህ መውሊድ እነዚህን እና መሰል በርካታ ሀዲሶችን የሀይማኖት አባቶች በመናገር "አንድ ጥፋት አጥፋቻለሁ አላህ አይምረኝም በማለት ጥፋት ላይ ተወዘፋች

[102] 24/09/07 አልከሶ ሀረም

መቅረት የለባችሁም፡፡ ምክንያቱም አላህ ምህረትን ከጠየቁት ለጋሽ ነውና” የሚል መልዕክቶችን አስተላልፈዋል፡፡

**ስለ ወንድማሞች መዋደድ እና አላህ ስለቸራቻው ችሮታ የተነገረ ሀዲስ፡-** በአልከሶ መውሊድ ስለ ወንድማማችነት መዋደድ በርካታ ሀዲሶች ሲነገሩ ስምቻለሁ ከእነዚህ መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

በአንድ መንደር ላይ ሁለት በጣም የሚዋደዱ አርሶ አደር ወንድማሞች ነበሩ፡፡ እነዚህ ወንድማሞች ከመወደድ አላፉ ማንኛውንም ጥሩ ነገር ሲያገኙ ለእኔ ከማለት ይልቅ ለወንድሜ ማለት ይወዱ ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ለረጅም ጊዜ ሲኖሩ ቆይተው አንድ ዘመን ላይ የዘሩት ዘር አጥጋቢ ምርት ሳይሰጥ ይቀራል፡፡ በሆኑም እነዚህ ወንድማሞች በሆዳቸው አንደቸው ለአንዳቸው “ወንድሜ እህሉ አንሶት ቤተሰቦቹ ጾም ያድሩ ይሆን እንዴ” እያሉ ያስቡ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ አንደኛው ወንድም ለምን ወንደሜ ሳያውቅ በማታ ከእኔ ጎተራ እህል ቀንሼ እሱ ጎተራ አላስቀምጥም የሚል ሀሳብ ይመጣበትና ከራሱ ጎተራ እህል እየቀነሰ ወንድሙ ጎተራ ማስቀመጥ ይጀምራል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ሌላኛውም ወንድም ይህንኑ ተግባር ይፈጽማል፡፡ በዚህ ጊዜ ሁለቱም እንዴት መጋዘኔ አይቀንስም በማለት ጋራ ይጋባሉ፡፡ አንድ ቀን ግን አንደኛው ወንድም እህሉን ተሸክሞ ወደ ጎተራ ሲሄድ በተመሳሳይ ሰአት ሌላኛውም ተሸክሞ ሲሄድ መንገድ ላይ ይገጣጠማሉ፡፡ በዚህ ጊዜ እውነታው ሲጋለጥ ሁለቱም ተቃቅፈው አለቀሱ፡፡ አላህም ለእነዚህ ተዛዛኝ ወንድማሞች ጀነት እንደሚያስገባቸው ቃል ገባለቸው ይባላል፡፡[103] ከዚህ ሀዲስ የሰው ልጅ በምድር ላይ ሲኖር እርስ በእርስ መተዛዘን እንዳለበት እና ለሰው ልጅ የሚያዝን ሰው ፈጣሪም እንደሚያዝንለት እንረዳለን፡፡

**“መልካም ስራ የክፉ ቀን ስንቅ ነው” የሚል ይዘት ያለው ሀዲስ፡-** በአንድ ዘመን ላይ በአንድ ቦታ ሁለት ሰዎች መንገድ እያለ አንድ ሰፊ ጫካ ውስጥ ሲደርሱ ዝናብ መዝነብ ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ ከዝናቡ ለመጠለል አንድ አነስተኛ ዋሻ ውስጥ ይጠለላሉ፡፡ ሁለቱ ሰዎች ዋሻው ውስጥ እያሉ አንድ ትልቅ ቋጥኝ ከተራራው ላይ በመውረድ የዋሻውን መግቢያ መውጫ በር ይዘጋዋል፡፡ በዚህ ጊዜ እነዚህ ሰዎች መውጫ በማጣታቸው በጣም ግራ ተጋቡ፡፡ በመጨረሻም ፈጣሪን ከመለመን ውጭ ሌላ አማራጭ የለንም ብለው በማሰብ

[103] 16/09/08 አልከሶ ሀረም

ሁለቱም ፈጣሪያቸውን መለመን ጀመሩ። በዚህ መሀል አንደኛው "በህይወት ዘመንህ ምን መልካም ስራ ሰርተሀል እስኪ ሁለታችንም የሰራናቸውን መልካም ስራዎች በማስታወስ ፈጣሪን እንለምነው" ይላል። አያይዞም "እኔ በህይወት ዘመኔ አንድ መልካም ስራ ሰርቻለሁ ብዬ አምናለሁ። እሱም አንድ ቀን ከቤቴ ወተት አልቤ ይዤ ወደ እናቴ እና አባቴ ቤት ስሄድ ተኝተዋል። በዚህ ጊዜ በሩን ካንኳኳው እንቅልፋቸውን አቋርጥባቸዋለሁ ብዬ በመስጋት ከእቅላፋቸው ሲነቁ እሰጣቸዋለሁ ብዬ በሩ ላይ እንደቆምኩ ነገር ግን ሌሊቱን ሙሉ ባለመንቃታቸው ለሊቱ ነግቶ ሲነሱ ሰጥቻቸው ወደ ቤቴ ተመለስኩ።" አለ። በዚህ ጊዜ ተዘግቶ የነበረው በር በራሱ ጊዜ ትንሽ ተከፈተ። ሁለተኛው ደግሞ "ከእኔ ጎረቤት አንድ ቆንጆ የአጎቴ ልጅ ነበረች። ይህቺ ልጅ ብዙ ጊዜ ገንዘብ ይቸግራት ነበር። ዘንድ ቀን ቤቴ መጥታ ገንዘብ እንዳበድራት ጠየቀችኝ። እኔ ገንዘቡን አትመልሽልኝ። ለገንዘቡ ፋንታ ግን ወሲብ እንፈጽም አልኳት። እሶ ግን አይደረግ ገንዘቡ ይቅርብኝ እንጂ ብላ ከቤቴ ወጣች። ነገር ግን ችግር በጣም ስለበረታባት በሌላ ቀን ወደ ቤቴ በመምጣት በሀሳቤ መስማማቷን ነገረችኝ። እኔም በጣም ደስ ብሎኝ ልብሳችን አወላልቀን እላዬ ላይ ወጥቼ ግንኙነት ልንጀምር ስንል "ያለ ሀቅህ አትገናኝኝ አላህን ፍራ" ስትለኝ አላህን በመፍራት ከላዬ ላይ በመውረድ ልብሴን ለብሼ የማይመለስ ነው ብዬ ብር ሰጥቼ ከቤቴ ሸኘኋት።" በማለት ትረካው ሲጨርስ ተዘግቶ የነበረው ዋሻ ሙሉ በሙሉ ተከፍቶ ከዋሻው በሰላም ወጡ ይባላል።[104]

ይህ ሀዲስ መልካም ስራ መስራት ጥሩ ነው የሚል መልዕክት ያስተላልፋል። እንዲሁም መልካም ስራ መስራት ዞሮ ዞሮ አንድ ቀን ለራስ ይጠቅማል የሚል መልዕክት አለው። ምክንያቱም እነዚህ ባለታሪኮች በህይወት ዘመናቸው መልካም ስራ ባይሰሩ ኖሮ እዛው ዋሻ ስር ተቀብረው ሊቀሩ ይችሉ ነበር። ከዚህ ችግር ያዳናቸው የሰሩት መልካም ስራ ነው።

## 6.2.3 መንዙማ ማለት እና ማዳመጥ

በአልከሶ ስላለው የመንዙማ ስርዓት ከመልከታችን በፊት መንዙማ ማለት ምን ማለት ነው መንዙማ ከእስልምና አንጻር እንዴት ይታያል የሚለውን እንመልከት። ስለ መንዙማ የተለያዩ ሰዎች በተለያየ እይታ ተመልክተው ብያኔ ለመስጠት ሞክረዋል። ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን እንመልከት። መንዙማ ስርወ ቃሉ አረብኛ እንደሆነ እና ትርጉሙም በምጣኔ

[104] 16/09/08 አልከሶ ሀረም

የተጻፈ ግጥም እንደማለት ነው፡፡ ከኢትዮጵያ አንጻር ስንመለከተው ደግሞ እስለማዊ ሙዚቃ ሲሆን ለሃይማኖታዊ እና ለማህበራዊ ግልጋሎት እንደሚውል እና በዚህ እስላማዊ ሙዚቃ(መንዙማ) አማካኝነት አላህ፣ ነብዩ ሙሀመድ እና በተለያዩ ቦታዎች ቅዱሳን የሚባሉ ሰዎች የሚወደሱበት ነው፡፡

መ□ሊት በሀገራችን በሰፊው መከበር ከጀመረበት ከ18ኛ□ □አለ □መን ጀምሮ የሀይማኖቱ መሪዎች መንዙማን □ባዕላቸው ዋነኛው አካል ያደርጉት ነበር (Hussein, 2001):: መንዙማ በጥሬ ትርጉሙ «ቃላትን ... በጥሩ ሁኔታ ማሰናኘት» ማለት ሲሆን በሀገራችን ባለው ሰፊ ትርጉም ደግሞ አላህ፣ ነብያት፣ መሻይሆች... የሚሞገሱበት ሀይማኖታዊ ዝማሬ ማለት ነው:: «መንዙማ» በሀረር አካባቢ «ዚክሪ»፣ በባሌና አርሲ «ባሮ / ሰርመዬ / ዘከረ» □□ተ... በሚሉ □ተለ□□ መጥርያዎች □ሚታወቅ ሲሆን ሁሉም ግን ከሞላ ጎደል አላህን፤ ነብያትን፤ የሀይማኖቱ ታላላቅ ሰዎችን (ኢትዮጵያዊ የሆኑም ያልሆኑም) □ሚ□ሞ□ሱ እና የተለያዩ ማህበራዊና ታሪካዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱ ናቸው:: የእነዚህ ህብረተሰቦች የአካባቢዎቻቸውንና የባህሎቻቸውን መጠነኛ መለያየቶች ተከትሎም መንዙማዎቻቸው በአዘማመር፤ በ□□□□ እና በሚጠቀሙበት የአጃቢ መሳሪያዎች የተወሰኑ ልዩነቶች ይታዩባቸዋል:: መንዙማ በሀገራችን የሙስሊሙ ማህበረሰብ ዘንድ ትልቅ ስፍራ ነበረው:: ከዚህም አልፎ ቀደምት መሻይሆች በመንዙማ አማካኝነት እስልምናን ሙስሊም ላልሆኑ ወገኖች እንኳን □ስተምሩና ይማርኩ ነበር ይባላል:: አሁን ባለንበት ዘመንም ቢሆን የመስማት እድሉ ያላቸው ጥቂት □ማ□ባሉ □ሌላ እምነት ተከታይ የሆኑ ኢትዮጵያውያንም የመንዙማን ጥበብ ያደንቃሉ (ከማል 2013:2-3)::

ስለዚህ ሀሳብ Frishkopf (2002፣2) የሚከተለውን ይላሉ፡፡ Religious songs, especially madih, are commonly performed at life-cycle events. In Egypt, inshad performed for circumcisions, weddings, ormemorialsmay incorporate popular Arabic songs and instruments. ይህ ጥቅስ የሚያሳየው እስላማዊ ሙዚቃ(መንዙማ) በተለያዩ ክብረ በዓላት ላይ በተለያዩ የሙዚቃ መሳሪያዎች ተጅቦ እንደሚባል ነው፡፡ የመንዙማ ጀማሪዎች ሱፊዎች እንደሆኑ ይነገራል፡፡ ይህን በማስመልከት Al-Samaa (2004፣6) “Sufism is generally tolerant of music with a spiritual message; though frame drums and reed flutes are often preferred ,many local instruments are absorbed into themix. Sufi emphases upon spiritual love and

metaphorical interpretation generate ambiguity between sacred and secular love; any elevated love song supports Sufi interpretations, and may be used in Sufi ritual.” በማለት ያስረዳሉ፡፡

አንድ ክብረ በዓል ሲከበር በከበራው ወቅት በርካታ ፎክሎራዊ ጉዳዮች በጥምረት ይስተናገዳሉ፡፡ ለምሳሌ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነውን መውሊድን ብንመለከት በዓሉ ሲከበር ከበራውን ለማድመቅ የተለያዩ መንዙማ ዎች እና መነዙማዎች ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ መንዙማዎች በተለያዩ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች እና በተለያዩ የሰውነት እንቅስቃሴዎች ይታገዛሉ፡፡ መንዙማ አቅራቢዎች ደግሞ ለክወናቸው ድምቀት እንዲሰጥ ወይም ለአከዋወን በሚመቻቸው ሁኔታ በተለያዩ አልባሳት እና ጌጣጌጦች ይዋባሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ በአንድ ክብረ በዓል ውስጥ በርካታ የፎክሎር ዘርፎችን ማግኘት ይቻላል፡፡ በሌላ አገላለጽ ክብረ በዓል የሁሉም የፎክሎር አይነቶች ውህድ ውጤት ነው፡፡ ይህን በተመለከተ Sims እና Stephens (2005፣95) ክብረ በዓል የራሱ የሆነ የአተገባበር ውቅር አለው ይላሉ፡፡ አወቃቀሩም በብዛት ቡድናዊ ነው፡፡ አብላጫ ክብረ በዓላት የበርካታ ፎክሎር አይነቶች እንደ ቃላዊ (አባባሎች፣ ግጥም ወይም ሙዚቃ)፣ የአካል እንቅስቃሴ፣ ዳንስ፣ ቁሳቁስ፣ ምግብ፣ አለባበስ፣ አጋጌጥ ወዘተ ውጤት ነው ይላሉ፡፡ ስለ መንዙማ ይህ ያህል ካልን በአልከሶ መውሊድ ስላለው የመንዙማ ሁኔታ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

በአልከሶ መውሊድ ሰሞን በከፍተኛ ሁኔታ ከሚካሄዱ ስርዓቶች መካከል መንዙማ ይገኝበታል፡፡ ይህን መንዙማ ስንመለከተው አለማዊ እና መንፈሳዊ ይዘት ያላቸው ናቸው፡፡ ወጣቶች በብዛት የሚያዳምጧቸው መንዙማዎች በጣም ሞቅ ያሉ እና በበርካታ ዘመናዊ መሳሪያዎች የተጃቡ ናቸው፡፡ ዕድሜያቸው ከፍ ያሉ ሰዎች ግን በብዛት የሚያዳምጡት በዱቤ የተጀበ ነው፡፡ ከሚያዳምጡት በተጨማሪ ራሳቸው መንዙማ በሚሉበት ጊዜ ዱቤ ይጠቀማሉ፡፡ ከሚቀርቡበት ቋንቋ አንጻር ስንመለከተው ደግሞ በብዛት የአማርኛ፣ የስልጥኛ አረብኛ እና ቅልቅል ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በኦሮምኛ ቋንቋ የሚቀርቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም በመውሊድ ሰሞን የሰበሰብኳቸውን በሁሉም ቋንቋዎች ሲባሉ እና ሲደመጡ የሰበሰብኳቸው መንዙማዎች የሚከተለውን ይመስላሉ፡፡

## ሀ. የስልጥኛ መንዙማዎች

በ15/09/08 መውሊድ ሲከበር ወጣቶች ሀረሙ ውስጥ አንድ ጥግ ላይ ተሰብስበው በመቀመጥ የሚከተለውን መንዙማ ሲ+ያዳምጡ ሰምቻለሁ፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ አንድ**

በዚህ ቀን ሲደመጡ ከሰማኂቸው የስልጥኛ መንዙማ ዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

አላሁ ኤጋናህ ኢማነ ዋበና

ስራጥ ቤሌን ዘራመ አታጨንቀና

አላሁ ኤጋናህ ኢማነ ዋበና

ስራጥ ቤሌን ዘራመ አታጨንቀና

ጬጡንያን በለ ሰሀብቸ

ተያፎሎ ገቦ በኪቸ

ተፈዱንያን ቡርኩት ሰሀብቸ

ተሩንያን የኛይ ቀዲምቸ

አላሁ ኤጋናህ ኢማነ ዋበና

ስራጥ ቤሌን ዘራመ አታጨንቀና

ተጎሩንያን የኛይ ቀዲምቻ

ተመኩንያን በለ ሙእሚንቻ

አላሁ ኤጋናህ ኢማነ ዋበና

ስራጥ ቤሌን ዘራመ አታጨንቀና (25/09/07 አልከሶ ሀረም )

የዚህ መንዙማ ጸሀፊ በግጥሙ አላህን ምህረትን ይጠይቃል፡፡ አያይዞም በምድርም ላይም አታስጨንቀን ይላል፡፡ እንዲሁም አላህን በሃይማኖት ጠንካራ አድርገን ይላል፡፡ ከሞት በኋላ ባለውም ህይወታችን አታጨናንቀን ይላል፡፡ አስከትሎም ለእስልምና በርካታ ዋጋ የከፈሉ ሰዎች መኖራቸውንም ያትታል፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ ሁለት፡-**

ያ ረሱል አላህ

አሰላም አለይኩም አሰላም አለይኩም አሰለም አለይኩም ያረሱል አላህ

ሰላቱ ሰመድ ባቱም የውረድ ያ ረሱል አላህ አቱም ነቢዮ ዳነይ

አሰላም አለይኩም አሰላምአለይኩም አሰለም አለይኩም ያ ረሱሌአላህ

አሰላም አለይኩም አሰላምአለይኩም አሰለም አለይኩም ያ ረሱሌአላህ

ያ ረሱል አላህ

አሰላም አለይኩም አሰሊም አለይኩም አሰለም አለይኩም ያ ረሱሌአላህ

አሰላም አለይኩም አሰላም አለይኩም አሰለም አለይኩም ያ ረሱሌአላህ

ሰላቱ ሰመድ ባቱም የውረድ

ኡመቲ ኢባቻን ባቱሚ ሙሃባ ሰኢዲሰኢ ዲፊደጀ ከአበየ ያአደየያ

ያረሱል አላህ ከሞከሞ ነሙ በመጣሙ በመጣሙሙ ሀባያ ትበየቺያን

ተባድአትጌፈረኛንያቱሚሙሀባአደራያረሱልአላህቃላሙያከብረያው

የጠይባይ ከተማ አይነካሌን ደቺ ሂልም አሻኔ ወሰደ ይቀልቤያ

አቱም ነየመሰለ አላገፔነ እኛ በሬዳበሬ ዳየሌለሀ ምሳያ

ያትቤቻን ሙሀባ በፈጅር በማልት ደለከ ያባባይን ሁፍተከ ያቴንቺያን

የሙሀባይ መርካ ሊያዋልኩ የባሰም ያትፊቅረይየሄነ ይየደለያ

ኡመቲ ኢባቻን ባቱሚ ሙሃባ ሰኢዲሲ ዲፊከ አበየ አደየያ

ለሰብ ወልድ ፈረኮትዋ በያን አላህ ጂግባለን ያንዣንነ ውል ቲያ ቁያ

---------------------------------------------------------------------------------

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት ነብዩ መሀመድን ማወደስ ነው። በውዳሴው ውስጥ የእሳቸው ኡመት (ህዝብ) እሳቸውን እንደናፈቁ እና እሳቸው የሚገቡበት ጀነተል ፊርዶስ(ነብዩ መሀመድ የገቡበት ጀነት) መግባት እንደሚናፍቅ ያትታል። እንዲሁም መንዙማ ው የነብዩ ኡመት ለሳቸው ያለውን ፍቅር ለመግለጽ አባቴም እናቴም ፊዳ(መሰዋት) ይሁንልዎት ይላል።

**የስልጥኛ መንዙማ ሶስት፡-**

በ2008 የካቲት ወር ላይ በተከበረው ወርሃዊ መውሊድ በሀረሙ ውስጥ ሲደመጡ ከሰማኋቸው መንዙማ ዎች መካከል የሚከተለው የስልጥኛ መንዙማ ይገኝበታል።

ሰላት የውረድ በመሀመድ

በኛይ ሉክተኛ በአለሀይ ውድ

ረሱል የአለሀይ ውድ

የዲን ያዴ ወጄው እለማሁ ኤጋሙ

በዱንየ ደር ታሊ አለሀን የለገ

ሂኔው የሆኒ ነጋ ምንም ቢለጊገ

በላም ዲነት ቢብር ባደም ቢገዚ

አውለው እጄኛን ኤለ ሊትጋገዚ

ሰላት የውረድ በመሀመድ

በኛይ ሉክተኛ በአለሀይ ውድ

ረሱል የአለሀይ ውድ

ያለው ያረቢ መርሀባ በለና

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት ስላም በነብዩ መሀመድ ላይ ይውረድ የሚል እሳቸውን ማወደስ ነው፡፡ መንዙማው በስሩ ደግሞ የሰው ልጆች በህይወት ዘመናቸው(በምድር ላይ እያሉ) አላህን አጠናክረው መያዝ እንዳለባቸው ይመክራል፡፡ አያይዞም ሰዎች ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ ይልቅ ሰብሰብ ብለው ወደ መሰጂድ መሄድ እንዳለባቸው ይመክራል፡፡ አስከትሎም እስልምና አምስት መሰረቶች እንዳሉት ይገልጻል፡፡ እነሱም አንደኛ በአላህ አንድነት እና በነብዩ ሙሀመድ ነብይነት ማመን፣ ሁለተኛ ሶላት መስገድ፣ ሶስተኛ ዘካ ማውጣት፣ አራተኛ ረመዳን መጾም፣ አምስተኛ ሀጅ መሄድ እንደሆኖ ይገልጻል፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ አራት፡-**

በ2007ቱ ዋናው የመውሊድ ቀን በሀረሙ በርካታ የአማርኛ፣ የስልጥኛ እና የኦሮምኛ መንዙማ ዎች በቴፐሪከርድ ሲደመጥ ሰምቻለሁ፡፡ ከነዚህ መካከል የሚከተለው የስልጥኛ መንዙማ ይገኝበታል፡፡

የዱንያይ ንባረት ያመስለ ያበልጣን

ለአበድም ተይሞቲ እነብሬን ይመስላን

ውርው ባሌ ቲያንዚ ጥሽተንከ ያጅባን

ሀውጀው ያስቅ ላሌ ጌሰው ያትቤቻን

ምነም ለነበሪ መውቲ ይመጫን

ቲወዱያነይ ወልድ ሂንኩም ይልያን

ቲወዱያነይ ውድ ሂንኩም ይፋርቃን

ሊባሰይ ያጢለ ከፈናይ ያለብሳን

ታልጋይ ደር ያወርዳን ባፈር ያቲኛን

የጋረይ አበሮስ ሁለምከ ያትቤቻን

የቂያመ አያመ አለሀ በቁራን

የሮሬ ጊስ በለ ዡቦ ኤወዳን

ታጠበት ምሽት ጩሎሽ ያትሬሳን

በደል ያለይ ወልድ ያወጨ ኢጢላን

እኛው ምነ ላሽነ ቆተው ቀበትናን

የኢ አያም ዡቦ ቦዞኮ ያባን

ሰበይ ትያንዙይ የሰከረ ኢመስላን

ግን አልሰከሩን ሀዳቢኒስ ሀበደያን (23/09/07 አልከሶ ሀረም)

የዚህ መንዙማ ግጥም ገጣሚ በግጥሙ ለማስተላለፍ የፈለገው ዋና መልዕክት ምድራዊ ጉዳይ የሰው ልጅ ሞት እንዳለበት እስከሚረሳ ድረስ ያስረሳዋል የሚል ነው፡፡ በመሆኑም ዛሬ የሳቀ ነገ ያለቅሳል ይላል፡፡ አያይዞም ሞት ሲወስድ በምድር የነበረን ነገር በሙሉ ጥቅም የለውም፣ ከሚወዱትም ቤተሰብ ይለያያል፣ አልጋ ላይ የነበረን መሬት ላይ ያወርዳል፣ በዚህ ጊዜ ሰው የሰከረ ይመስላል ግን አልሰከረም ሁኔታው አስፈርቶታል ይላል፡፡ በመጨረሻም በህይወት ዘመን መጨረሻ ሞት እንደማይቀር እና ለዚህ መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን ይመክራል፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ አምስት፡-**

በአልከሶ መውሊድ ምዕመናን በተለያዩ ቦታዎች በመሰባሰብ ጫት እየቃሙ፣ ዱኣ እያደረጉ እና መንዙማ እያሉ መውሊድ ያከብራሉ፡፡ ጫት እየቃሙ፣ ዱኣ ማድረግ እና መንዙማ እያሉ መውሊድ ማክበር በገራችን የተለመደ ጉዳይ ነው፡፡ ለምሳሌ Yasuo and Ishihara (2009፣500) በጋራ በጻፉት መጣጥፍ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ “After the meal, the pilgrims returned to their *hadra* gatherings. Pilgrims chewed *čat* as they chanted the *manzuma*, conducted the *du`ā'* and chatted with one another.”

ከላይ በተገለጸው አኳኋን በአልከሶ ሲባሉ ከሰሚኒቸው መንዙማዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

በአዲ አለሀ ስረም እለዋሻርክና

አለሀው በልዳሌ ኤጠቅመነ ኤለና

ለምካት ለፈረጃት አለሀነ አልግፈርና

ያዴ ገረደይ አሽ አልቻሎታሽ

ሊችላን ሰብ ኢልመይ በልትሳሎታሽ

ጭልማይ ሽርከ ገዋ ገባሽ ኩሽሽባሽ

ናረ ሞ ሆነ ዮናን ያሼሽም ብታሽ

ጭንቂ ጠቢቂ ለሄራም አለሽ

በአዲ አለሀ ስረም እለዋሻርክና

አለሀው በልዳሌ ኤጠቅመነ ኤለና

ለምካት ለፈረጃት አለሀነ አልግፈርና

ትስሜሽ በሆነ አጥናቢኝ ሊውደሽ

አለሀው አለሀው ትዬኔ ወልደ ትጦቅሼሽ

በአለሀው በልዳሌ ዮበነኮ ኤለኮ ትችዬሽ

አለሀ ታበሽኮ ትትክናበዬሽ

አለሀን ትለጌኔ ሽርከ ብል ታሼሽ

የጦቀሺ አለሀ ያበሽኮ ትችዬሽ

ቆተይ ትነጥቁነ ለዳዶ ቶቤሽ

ለዳዶ ባፍሎት መላያሽ ትፈጄሽ

ዳዶ ዳዶ አውለ ከማሙ ጂጉ ባሽ

ሂና ሂኔ ኮስ ኮስ አለሀን ገፈርሽ

ሂነይ በሶታሽ አለሀን ታትኖዥሽ (23/09/07)

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት በአንድ አላህ ማጋራት(ማሻረክ) እንደሌለብን እና በሀዘንና በደስታ ወቅት ደራሽ መሆኑን ያስረዳል፡፡ አያይዞም አንዳንድ ሴቶች ባለማወቅ እና አዋቂዎችን ባለመጠየቅ ወደ አላህን ማጋራት(ማሻረክ) እንደሚሄዱ ያሳያል፡፡ በመቀጠልም አንዳንድ ሴቶች ልጅ ሲያጡ አላህን ይለምኑና ልጅ ካገኙ በኋላ አላህን ይረሱና ለሌላ አካል ይገብራሉ ይላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አንዳንድ ሴቶች አላህን በመርሳት ለሌላ አካል ትኩረት ይሰጣሉ፤ ይህ ሁኔታ አላህን ስለሚያስቆጣ መደረግ እንደሌለበት የመንዙማው ግጥም ያሳያል፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ ስድስት፡-**

ወልዳም ፈጀ ሄደ የሰብ ባዳ
ብር ሲያመጡ የኛን ኤታ
ወልዳም ፈጀ ሄደ የሰብ ባዳ
ብር ሲያመጡ የኛን ኤታ[105]

ልጆቹ እንዳሉ ሄዱ የሰው ሀገር
ወደ እኛ ሲያመጡ ብር

ይህ ቃል ግጥም የሚያትተው በአሁኑ ጊዜ ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ገንዘብ ፍለጋ እየተሰደደ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ መስጂድ ውስጥ የነበሩ ምዕመናን ደግሞ በብዛት ትልልቅ(በዕድሜ) ሰዎች ናቸው፡፡ በቦታው ከነበረው ሁኔታ እና ከሰዎቹ እድሜ አንጻር በአሁኑ ጊዜ ሀገር ለቆ ብር ፍለጋ የሰው ሀገር በህጋዊም ሆነ በህገ ወጥ መንገድ የመሰደዱ ጉዳይ ያሳሰባቸው ይመስላል፡፡ በሻሽመኔ ኸለዋ ውስጥ ከታዳሚው መሀል በመነሳት ልጁ ከሀገር ከወጣ ሃያ አመት እንደሆነው እና ለሃያ አመት ያህል የወለዱትን ልጅ አለማየት በጣም እንደሚያም ሲናገር መስማቴን ቀደም ብዬ ገልጫለሁ፡፡ ይዚህ ቃል ግጥም ይዘትም ሰውየው ከተናገሩት መልዕክት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ ሰባት፡-**

በሻሽመኔ ኸለዋ ውስጥ በምሽቱ በደመቀ ሁኔታ ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል መንዙማ ማለት አንዱ ነው፡፡ አብላጫ መንዙማዎች ይዘታቸው መንፈሳዊ ሲሆኑ ጥቂት የማይባሉ መንዙማዎች ይዘታቸው አለማዊ ነው፡፡ በኸለዋው ሲባሉ ከሰማኋቸው መንዙማዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

105 24/09/07 አልከሶ ሀረም

አልከስዬ ኤጋሙ ነሞ

ቦዘክ ፈሬናን ያሰላሞ

አልከስዬ ኤጋሙ ነሞ

ቦዘክ ፈሬናን ያሰላሞ [106]

እባኮትን አልከስዬ ይምጡ፤

በሰላሙ ሁኔታ በጣም ፈርተናል

ከዚህ ቃል ግጥም በፊት የተመለከትናቸው ስንቃሎች በብዛት የሚያትቱት ስለ አልከሶ እና አልከስዬ ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ቃል ግጥም በተወሰነ ደረጃ ከመጀመሪያዎቹ ይለያል፡፡ ምክንያቱም በውስጡ ሁለት ይዘት ያለው ነው፡፡ የመጀመሪያው ትርጉም በችግር ጊዜ አልከስዬ መፍትሔ አፈላላጊ ናቸው ተብሎ ስለሚታሰብ ምንም አይነት ችግር ሲያጋጥም አልከስዬ ድረሱ እንደሚባል ያሳያል፡፡ እኔም ሲባል ሰምቻለሁ፡፡ ይህ ማለት ደግሞ ህዝብ ለአልከስዬ ጥሩ ፍቅር እንዳለው ያሳያል፡፡ ሁለተኛው መልዕክት ቃል ግጥሙ በሚባልበት ወቅት በሀገሪቱ በነበረው ነባራዊ ሁኔታ አንጻር የተባለ ይመስላል፡፡ ይህን ቃል ግጥም ያገኘሁት ከለይ እንደገለጽኩት 23/09/2007 የመውሊድ ላይ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ የአልከሶ መውሊድ የሚከበርበት እና አጎራባች ወረዳዎች ዝናብ ጠፍቶ በከፍተኛ ሁኔታ ድርቅ የተከሰተበት ወቅት ነበር፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወቅቱ የ2007ቱ ሀገር አቀፍ ምርጫ የሚካሄድበት ስለነበር ከምርጫው ጋር ተያይዞ ችግር ይፈጠራል የምል ስጋት ነበር፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ባይበልጥ አልከስዬን እንዲያስታውስ ያደረገው ይመስላል- ከቃል ግጥሙ አንጻር፡፡ ስለዚህ የቃል ግጥሙ ገጣሚ በወቅቱ የነበረው ነባራዊ ሁኔታ አስገድዶት ይህን ቃል ግጥም እንዲገጥም አድርጎታል ማለት ይቻላል፡፡

በ17/09/08 ዓ.ም በቦታው በተገኘሁበት ወቅት ወጣቶቹ ወደ ሀረሙ ሲገቡ የተለያዩ መንዙማዎችን ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡ የተወሰኑት ዓላማዊ ይዘት ሲኖራቸው የተወሰኑት ሃይማኖታዊ ይዘት ያዘሉ ናቸው፡፡ ከሰማኋቸው መንዙማዎች መካከል የሚከተለው የስልጥኛ መንዙማ ይገኝበታል፡፡

[106] 23/09/07 ሻሻመኔ ኸለዋ፡፡

| በስልጥኛ | በአማርኛ |
|---|---|
| የለበሱይ ልባስ በነጠራ<br>ኢቄንጣን ተገግ አልጠቀላ<br>የለበሱይ ልባስ በነጠራ<br>ኢቄንጣን ተገግ አልጠቀላ | የለበሱት ልብስ ከቆሸሸ<br>ይንቃል ከራስ ያልተሻለ[107] |

በአልከሶ መውሊድ ሰሞን የሚባሉ ቃል ግጥሞች አለማዊም ሆነ ሃይማኖታዊ ይዘት ያላቸው በርካታ መንዙማዎች እንደሚባሉ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በላይ የቀረበው ቃል ግጥም የሚያትተው የንጽህናን አስፈላጊነት ነው፡፡ ግጥሙ አንድ ሰው የለበሰው ልብስ ከቆሸሸ እና ንጽህናውን ካልጠበቀ ከእሱ ያልተሻለ ሰው ሊንቀው እና ሊያዋርደው እንደሚችል ያሳያል፡፡ የአልከሶ መውሊድ ለምዕመናኑ ከሚያስገኘው ጠቀሜታ መካከል አንዱ ማህበራዊ ግንኙት ማጠናከሪያ እና የመመካከሪያ መድረክ ሆኖ ማገልገል እንደሆነ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ስለዚህ ይህ ቃል ግጥም ይህንን አገላለጽ ያጠናክርል፡፡ ምክንያቱም በቃል ግጥሙ በዋናነት እንዲተላለፍ የተፈለገው መልዕክት ንጽህና መጠበቅ በጣም አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን ንጽህናቸውን ለማይጠብቅ ልጆች እና ወጣቶች ማስተላለፍ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ሁኔታ የመመካከሪያ አጋጣሚ ሆኖ ማገልገሉ የመውሊዱ መከበር ለአክባሪዎች የማህበራዊ ግንኙነት ማጠናከሪያ በመሆን ያገለግላል፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ ስምንት፡-**

| | |
|---|---|
| ቤቴ አልከስዬ መዳኒቴ<br>አኪምኩም ለሁልም ኤቴ | ቤቴ መድሀኒቴ አልከስዬ<br>ሀኪም ኖት ለሁሉም ቦታዬ[108] |

ከዚህ በፊት መውሊድ አክባሪዎች አልከስዬ ወልይ እንደሆኑ እንደሚያምኑ ተመልክተናል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የባሌ እና አከባቢው ኦሮሞች ድሬ ሼኽና ሁሴንን ቅዱሳ ወይም ወልይ ናቸው ብለው እንደሚያምኑ እሸቱ(1973፣4) ያስረዳል፡፡ አልከስዬ ወልይ በመሆናቸው ደግሞ ለተለያዩ ችግሮች መፍትሔ እንደሚያገኙ እና ከተለያዩ በሽታዎች እንደሚፈውሱ በምዕመናኑ ዘንድ ይታመናል፡፡ ይህ ቃል ግጥምም የሚያትተው አልከስዬ ወልይነታቸውን ተጠቅመው ከተለያዩ በሽታዎች እንደሚፈውሱ ነው፡፡ የቃል ግጥሙን ዋና መልዕክት

---

[107] 17/09/08 አልከሶ ሀረም

[108] 26/09/07 አልከሶ ሀረም

የያዙት ቃላት “አኪምኩም ለሁልም ኤቴ” ወደ አማርኛ ሲተረጎም ሀኪም ኖት ለሁሉም ቦታዬ የሚል ነው፡፡ ይህ ማለት ለታመመ ሰው ዱኣ በማድረግ ይፈውሳሉ እንደ ማለት ነው፡፡ ለዚህ አባባል ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው አልከስዬ በተለያዩ ጊዜያት ለታመሙ ሰዎች ዱኣ በማድረግ እንደፈወሷቸው የሚያትቱ አፍታሪኮችን መመልከት ይቻላል፡፡

ሹፌር ንዳ ንዳ እስከ ጂዳ
ጂደ በጄጌ ገጌ ለንዳ
ሹፌር ንዳ ንዳ እስከ ጂዳ
ጂደ በጄጌ ገጌ ለንዳ

ሹፌር ንዳ ንዳ እስከ ጂዳ
ጂዳ ከደረስን እኔው ልንዳ[109]

ይህን ቃል ግጥም ሲሉ የሰማኋቸው በሀረሙ ውስጥ ተሰብስበው መንዙማ ከሚሉ ወጣት ወንድ እና ሴት መውሊድ አክባሪዎች ነው፡፡ የግጥሙ ይዘት የሚያሳየው ወጣቱ የህብረተሰብ ክፍል ወደ ሰው ሀገር ለመሄድ ምን ያህል ፍላጎት እንዳለው ነው፡፡ በእዛው ቀን እዛው እነዝያው ወጣቶች የሚከተለውን ቃል ግጥም ሲሉ ሰምቻለሁ፡፡

**የስልጥኛ መንዙማ ዘጠኝ፡-**

ሳውዲአሪቢያ የሄደ ለግዲካ
ለቱመመ ዋባን አደረካ
ሳውዲአሪቢያ የሄደ ለግዲካ
ለቱመመ ዋባን አደረካ

ሰውዲአረቢያ የሄደው ቢቸግረው ነው
እራሱን አደራ የሰጠው ግን ለእርሶ ነው

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት ሰው ሀገሩን ለቆ መሄድ አይፈልግም የሚል ነው፡፡ ነገር ግን የሚሰደደው ከተለያዩ ጉዳዮች አንጻር ነው፡፡ የዚህ ቃል ግጥም ዋና መልዕክት ያለው “ለግድካ” በሚለው ቃል ውስጥ ነው፡፡ የቃሉ ትርጉም ግድ ቢሆንበት እንደ ማለት ነው፡፡ ይህ ማለት ወጣቱ ከሀገሩ የሚሰደደው ወዶ ሳይሆን ሁኔታዎች አስገድደውት እንደሆነ ያሳያል፡፡ በቦታው መንዙማ ሲሉ ከነበሩ ወጣቶች መካከል አንዱን የዚህ መንዙማ ትርጉም ምን እንደሆነ ስጠይቀው “ሰው የተወለደበትን ሀገር ለቆ የሚሄደው ስለቸገረው ነው፡፡ ቢኖረው ኖሮ ሀገሩን አይለቅም ነበር የሚል ነው” የሚል ምላሽ ሰጥቶኛል፡፡ ለስደት ከሚዳርጉ ጉዳዮች

---

109 17/09/08 አልከሶ ሀረም

መካከል የድህነት መስፋፋት አንዱ እና ዋነኛው እንደሆነ ወጣቶቹ ደጋግመው የሚሉት መንዙማ ያሳያል፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው መንዙማዎች አጠቃላይ ዋና ይዘታቸው ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ከሃይማኖት አንጻር ስንመለከታቸው አላህ ምህረት እንዲሰጥ መለመን እና ነብዩ መሀመድን ማወደስ ነው፡፡ ከማህበራዊ ጉዳይ አንጻር ስንመለከተው ደግሞ መንዙማ አድማጮቹ አላህ ምድራዊ ፍላጎታቸውን እንዲያሟላላቸው የሚማጸኑ ናቸው፡፡

## ለ. የአማርኛ መንዙማዎች

በስልጥኛ እንደተመለከትናቸው መንዙማዎች ሁሉ የአማርኛ መንዙማዎችም ትኩራቸው ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ወይም አለማዊ ጉዳዮች ናቸው፡፡ በመሆኑም በመውሊድ ሰሞን ከሚባሉ መንዙማዎች መካከል የሚከተሉትን እንደምሳሌ እንመለከታለን፡፡

**የአማርኛ መንዙማ አንድ፡-**

ጓደኝነት ይቅር የአጉሉ ፍቅር

በሀላል ተጋብተሽ በትዳርሽ ኑሪ

በሀላል ተጋብተህ በትዳርህ ኑር

ኢስላም ከልክሎታል ጓደኛ አትያዝ

በጭፍን ፍቅር ኋላ እንዳትያዝ

በጣም ያስከትላል የሀራም መዘዝ

የሀራሙ ልጅ ነገ ሲረገዝ

ከዛም ያስከትላል ማሰብ መተከዝ

በመጥፎ በሽታ ነገ እንዳትያዝ

ስንቱ ወጣት አለ ከዲኑ የራቀ

ዲኑን ዱኒያውን ለይቶ ያላወቀ

ሴቶችን በዙሙት እያጨማለቀ

በሚሰራው ስራ ራሱን እያደነቀ

ከሀጅ ነብይ ሴቶች ጋር እየተሳሳቀ

ሀብቱንም የፈጀ በዚናና በሀምር

ወደድኩሽ እያለ ስልክ ሲደውል

አበድኩልሽ ብሎ ስልክ ሲደውል

በጮሌ ምላሱ ሴት ሲያታልል

የሩቁን ለመድረስ ቀጠሮ ሲቀጥር

ምንም ሳያስታውስ የአዘባል ቀብር

ሀራም ይዳፈራል ያለ ምንም ጥርጥር

በጊዜያዊ ስሜት መሸወድ ይቅር

መምረጥ ይሻላል የትዳር አጋር

ኪታቡ ባዘዘው በኒከሀ መኖር

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት በእስልምና የፍቅር ጓደኛ መያዝ አይፈቀድም የሚል ነው፡፡ አያይዞም በአሁኑ ጊዜ በርካታ ወጣቶች ጓደኛሞች እየሆኑ በአላህ ዘንድ የማይፈቀደውን ዝሙት ይፈጽማሉ፡፡ ይህ ደግሞ በአላህ ዘንድ ያስቀጣል፡፡ ይህ ከሚሆን እስልምና በሚያዘው መሰረት በትዳር ተጣምሮ እና ከሀራም ነገር ርቆ መኖሩ ተመራጭ እንደሆነ መንዙማው ያትታል፡፡

## የአማርኛ መንዙማ ሁለት፡-

በአልከሶ መውሊድ ሃይማኖታዊ ይዘት ካላቸው መንዙማዎች በተጨማሪ ስለ ሀገር የሚያወሱ መንዙማዎችም ይደመጣሉ፡፡ ከእነዚህ መካከል የሚከተለው ይገኝበታል፡፡

ያለው ያረቢ ያረህማን

ጠብቃት ሀበሻን

የቢላልን ሀገር የእነ ነጃሺን

በእዝነት አይን እያት አንተው ያረህማን

የቢላልን ሀገር የእነ ነጃሺን

በእዝነት አይን እያት አንተው ያረህማን

አለም መሸ ጨለመች ምድሪቱ

ደመናውም ከፋ ራደች ምድሪቱ

ባህሩም ጠቆረ ረገፉ አበቦች

ጸሀይቱም በረታች በሀበሻ ልጆች

ኑሮ ሊኳ ናረ ከሰው ልጅ በላይ

ንማው እያነሰ ሲወርድ ከሰማይ

ህይወት ጣሟን ጠፋ ጊዜ እርኤት ሆነ

አኼራ ተረስቶ ከዲን ሲኮን ኦና

ያለው ያረቢ ያረህማን

ጠብቃት ሀበሻን

የቢላልን ሀገር የእነ ነጃሺን

በእዝነት አይን እያት አንተው ያረህማን

ማጣት ተወግዶ ጭካኔና ምሬት

የሳቅ ዘመን አርገው የሰላም የእዝነት (23/09/07 አልከሶ ሀረም)

ይህ መንዙማ ወደ በሰባተኛው ክፍለ ዘመን ወደ ኋላ ይወስደናል፡፡ ምክንያቱም ሀበሻ(ኢትዮጵያ) ከንጉስ ነጃሺ እና ከቢላል ጋር የጠበቀ ቁርኝት እንዳላት ያትታል፡፡ የመንዙማው ዋና መልዕክት ግን የእነዚህ ከእስልምና ጋር የጠበቀ ቁርኝት ሰዎች ሀገር በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ተገኛለች በህዝቦቿ ፊታቸውን ወደ ስደት አዙረዋል፣ በመካከላቸውም ፍቅር ጠፍቷልና ይህ ጥላቻ ጠፍቶ ሰላም እንዲሰፍን አላህ ድረስላት የሚል ነው፡፡

**የአማርኛ መንዙማ ሶስት፡-**

በመውሊድ ከሚሳተፉ የህብረተሰቦች መካከል ወጣቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ወጣቶች በ23/09/07 ዓ.ም ከአልከሶ ከተማ በቡድን ቡድን ሆነው ወደ አልከሶ ሀረም ሲሄዱ የሚከተለውን መንዙማ በቴፕሪከርደር እያዳመጡ ሲሄዱ ሰምቻለሁ፡፡

አላህ አላሁ አላህ አላሁ አላህ አላሁ አላህ አላሁ አንተው ማረን እንዲሁ

ባሮቼ ታንተ መጡ ኸይር ስራ እንኳን ቢያጡ

አያግዳቸው ስልቱ አንተ ዘንድ ሲጮሁ

አላህ አላሁ አላህ አላሁ አላህ አላሁ አላህ አላሁ አንተው ማረን እንዲሁ

እባክህን አሳምረው ሀልቁን አታስቸግረው

ቀልቡን ወደ አንተ አዙረው ኸይር እንዲሰራ እዘዘው

ስጠን ከአንተ መውደድ ኸይርን እንድንለምደው

በመሀመድ አህመድ

ልታቀናው ሁሉንም አይቸግርህም ምንም

ዛሬስ እኔም ፈራሁ አድሰኝ ባባሁ

አላህ አላሁ አላህ አላሁ አላህ አላሁ አላህ አላሁ አንተው ማረን እንዲሁ

የዚህ አጭር መንዙማ ዋና መልዕክት የሰው ልጆች በምድር ላይ በርካታ ስህተት ይፈጽማሉ አንተ(አላህ) ደግሞ መሀሪ ነህና ማረን የሚል ነው፡፡

**የጉራጊኛ፣ የአማርኛ እና የአረብኛ ድብልቅ መንዙማ ሶስት፡-**

በዚህ ቀን ከላይ ከቀረበው መንዙማ በተጨማሪ የሚከተለው በአማርኛ፣ በጉራጊኛ እና በአረብኛ ቋንቋዎች ድብልቅ የቀረበ መንዙማም በሻሻመኔ ኸለዋ በ (23/09/2007)ሲባሉ ሰምቻለሁ፡፡

ጦሀ ነብይ ያሲን ጦሀ ነብይ ጦሀ ነብይ ያሲን ጦሀ ነብይ
አነቱ ነቢ ዘይኔ ለኡመቱ አሳቢ
ግቡልን የተንቢ
አህመድ ምርጡ የጦይባው ንጉሱ
ኡመቶቹ እሱን ሲያወድሱ
ይላሉ አህመዴ ይላሉ ያነቢ
ግቡልን የተንቢ
ዲናችንን ስማን ያረቢና
ከሳሪዎች አታድርገን ኦና
ይሁንብህ በእሱ በውዱ በነቢ
ግቡልን የተንቢ
ሀቢበላ ሀምድ ለረሱልአላህ ሸፋኖት ለኡመቱ ሁላ
ሁሉን አስተካክሎ ፈጠረው ያረቢ
ግቡልን የተንቢ
ልጥራ እንጂ እያልኩኝ አህመዴ
አንቱ እኮ ኖት የኢማን መንገዴ
ሁሉ ሰው ይለዋል ውድዬ ሀቢቢ
ግቡልን የተንቢ
ያ ሰይዲ ማን አለ እንደርሶ
አንቱ እኳ ኖት የዲኑ ምሶሶ
ያኔ በቂያማ ኡመቱን ሰብሳቢ
ግቡልን የተንቢ

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት ነብዩ ሙሀመድን ማወደስ ነው፡፡ በመሆኑም ገጣሚው በግጥሙ ኑ ይምጣብኝ ይላል፡፡ አያይዞም ከነብያት ሁሉ ምርጡ ነብይ እንደሆኑም

ያትታል። ከዚህ በተጨማሪ የውመል ቂያማ(የትእሳኤ ቀን) ለህዝባቸው እንደሚያስቡ እና በምድር ላይ ሲኖሩ ህይወት ተመቻችቶላቸው እንዳልኖሩ ይገልጻል።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው መንዙማዎች ትኩረታቸው ነብዩ መሀመድን ማወደስ፣ አላህን ምህረት መጠየቅ እና ኢትዮጵያን ሰላም አደርጋት የሚል ይዘት ያላቸው ናቸው።

## ሐ. የኦሮምኛ መንዙማዎች

በዚህ ቀን ከላይ ካቀረብኩት የአማርኛ መንዙማ በተጨማሪ በድሬ ሼኽና ሁሴን የሚዘወተረው ባሮ የተሰኘው መንዙማም ሲደምጥ ሰምቻለሁ። የመንዙማው ግጥም የሚከተለውን ይመስላል። ስለ ባሮ የተለያዩ ሰዎች ጽፈዋል ከማል የተለያዩ ሰዎችን በመጥቀስ የሚከተለውን ይላሉ።

> The spectacular dance while singing Baahroo in praise of *Sheikh* Hussein is known as *Ware.* During performing *Ware*, some people leap over fire to show their strong affection for the *Sheikh* (Danel 1984). According to Abechu (1981), while singing Baahroo in Hararghe there are two types of dancing styles: *Zeyara* and *Shubissa.* In *Zeyara* the participants sit in a circle. In *Shubissa* the participants stand in an oval shape circle, with men and women standing separately (Kemal 2014).

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ባሮ በድሬ ሼኽና ሁሴን በዋሬ ክብረ በዓል ጊዜ የሚዘመር ወይም የሚባል እንደሆነ እና በበአሉ የሚገኙ ምዕመናን ለድሬ ሼኽና ሁሴን ያላቸውን የጠበቀ ፍቅር የሚገልጹበት እንደሆነ ነው። ከዚህ በተጨማሪ ባሮ ከባሌ በተጨማሪ በሀረርጌም እንደሚባል ጥናቶች እንደሚያሳዩ ያትታል።

**የኦሮምኛ መንዙማ አንድ፡-**

Allaahu maraam nuruseenyi

Yaa ogeessa ogessa taru

Haajaa oboleetti fixaa

Tiyyaalle imam beektan garuu

Allahuu maraam abbiyyoo

Kan gabronni qabsiifate hoo

Kan jawaarri dawwooma qabu

Adda hin dhiifanne gadaa

Dhirrii dhirrattii dhiifate hoo

Allahu maraam nuruseeyni

Mangistii mangisttoota maraa

Siin jedhee numaaraan

Allahu maraam nuruseeyni abbiyyo

Baraa fagoo waan kessan odeesse jaboo

Ganda keessa dhufne gandaa abbaa milkii

Irra gadiitaa’I namni mudaa ta’ee

Allaahu maraam sh/husseen

Olla kessan bulte daddiyyoon

Hingargaarti malee

Hin gargaramtu tenna biyyon[110]

---

110 ይህን የኦሮምኛ መንዙማ ግጥም ወደ አማርኛ በመተርጎም እና መልዕክቱ ምን እንደሆነ በማስረዳት የተባበሩኝ በመደ ወላቡ ዩኒቨርስቲ መምህር የሆኑት ዶ/ር ሙሀመድ ጀማል ናቸው፡፡

**የኦሮምኛ መንዙማ ሁለት**

የዚህ መንዙማ ግጥም ዋና መልዕክት ሁለት ነው፡፡ አንደኛው ድሬ ሼኽና ሁሴን ትልቅነት እና ቅዱስነት የሚገልጽ ነው፡፡ ይህ መንዙማ መጀመሪያ ኑር ሁሴን ለወንድም ለሴትም በችግር ጊዜ ደራሽ ስለሆኑ አላህ ምህረትን ለግሳቸው ይላል፡፡ አስከትሎም ሼኽና ሁሴንን ከመንግስትም በላይ መንግስት ኖት እያለ የሞካሻቸዋል፡፡ ሁለተኛው ሼኽና ሁሴን ያረፉበት ቦታ አናጂና ከሌሎች ቦታዎች የተለየ- ቅዱስ እንደሆነ ያትታል፡፡ ይህ መንዙማ አናጂናን የስኬት መንደር በማለት ይገልጸዋል፡፡

አቶ መሀመድ ዳስ ውስጥ ሲያደምጡት ከነበረው መንዙማዎች መካከል የሚከተለው የድሬ ሼኽና ሁሴን ባሮ መንዙማ ይገኝበታል፡፡

Allahu maraam abbiyyo

Nu ilaalaa danbitti nu laalaa

Saala baaso jedha gariin

Yaabbiso jedha gaariin

Gabbiso jedha garii

Akka gariin jedhan sanii mitti

Gaafa heddu boora tiyya ciftanniyyo

Wayta lagni guutee gubbaan dhangala'u

Yaa sayyida dacha muluma agarree

Ganda tana geennaan jismiin nama fayyaa

Ana fayyaan gandaa kana wayya

Meeshaa taqabbalo jammare dambanyaan

Hayyee nasba kiyya hoo

Aabbiyyon milaana dhiisan qaxaruu

Arduna anaajiyyoo ganda shaaraddanii
Beenaa birka buunaa nauni araaddanii
Mukaa dame hin qabne jala hin dhabbatanii
Nama zarii hin qaabnee mala hin gaafatani

Anaajiina keessaa laallabani
Nama fayya hin qabne dawaan dhaqqabanii
Anaajiina baalee dirree dhaqatani
Dawaa dawaa caalu jawaaraan galatanii

Namni dirreen hin beekne makkaa dhaqaatani
Dirreen dawaa qabdii zamzama gaafatani
Ganda aanjiinaa qalbiin nama fayyaa
Jawaara gaafaannan ammumma argannaa[111]

የዚህ መንዙማ ዋና መልዕክት ቀደም ብለን ከተመለከትነው የኦሮምኛ መንዙማ(ባሮ) ጋር ይቀራረባል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም የሚያትቱት ስለ ድሬ ሼኽና ሁሴን እና አናጂና ነው፡፡ ይህ መንዙማ ድሬ ሼኽና ሁሴን የተመመን ሰው እንሚፈውሱ ያሳያል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ

[111] ይህን ኦሮምኛ መንዙማ መንዙማ የተረጎሙልኝ በመዳወላቡ ዩኒቭርስቲ የቋንቋ መምህርን የሆኑት ዶ/ር ሙሀመድ ጀማል እና አቶ ጃማይካ ከበደ ናቸው፡፡

የተመመ ሰው ወደ አናጂና ከሄደ ከበሽታው ይፈወሳል ይላል፡፡ ሌላው መንዙማው መጨረሻ ላይ የድሬ ሼኽና ሁሴን መንደርን ከመካ ጋር ያመሳስለዋል፡፡ በመሆኑም ዘምዘምን ፈለጋ ወደ መካ ትሄዳላችሁ፤ እዚህው ድሬም ዘምዘም አለላችሁ ማለት እንደሆነ መንዙማውን ሲያዳምጡ ያገኘኋቸው አቶ መሀመድ ነግረውኛል፡፡



ፎቶ 8፡- ምዕመናን በሽምሰል ጀማል ውስጥ ቁመው መንዙማ ሲሉ[112]

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ በሶስቱም ቋንቋዎች የቀረቡት መንዙማቸው ዋና ዋና መልዕክት አለማዊ እና መንፈሳዊ ነው፡፡ በመሆኑም መንዙማዎቹ በሃይማኖት መጠናከር አስፈላጊ መሆኑን ከመግለጽ በተጨማሪ አላህን፣ ነብዩ መሀመድን፣ አልከስዬን እና ሼኽ ሁሴንን የሚያወድሱ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምዕመናኑ በመንዙማዎች አማካኝነት ይመካከራሉ፤ ማህበራዊ ህይወት ያጠናክራሉ፡፡

[112] ፎቶ ባጥኚው 16/09/08 አልከሶ

### 6.2.4 ዱኣ (ምርቃት) እና ፎክሎራዊ ክንውኖች

ምርቃት በፎክሎር ጥናት ከሚጠኑ ርዕሰ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ማህበረሰብ በዱኣ አስተሳሰቡን፣ አመለካከቱን፣ አኗኗሩን ወዘተ ያንጸባርቃል፡፡ በመሆኑም በአልከሶ መውሊድ ሰሞን በተለያዩ ቦታዎች ከሚናወኑ ማህበራዊ ጉዳዮች መካከል ምርቃት(ዱኣ) አንዱ ስለሆነ ይህን ምርቃት ከክዋኔ ትወራ እና ፎክሎር አንጻር እንመለከተዋለን፡፡ መጀመሪያ ግን ዱአ (ምርቃት) ማለት ምን ማለት እንደሆነ እንመልከት፡፡

የሰው ልጅ ኑሮ የተመሰረተው በመዋቅራዊና በማህበራዊ የመረዳዳት ባህል ውስጥ ነው፡፡ መረዳዳቱን ግድ የሚያደርገው አንዱ ያለ ሌላው ድጋፍ ብቻውን መኖር ስለማይችል ነው፡፡ በአብሮ መኖር ዙሪያ ደግሞ አዎንታዊና አሉታዊ ሁኔታዎች ይፈጠራሉ፡፡ በህሊና ውስጥ የሚታዩ በጎና እኩይ ድርጊቶችም ለምርቃትና ርግማን መከሰት የሚያበረክቱት ድርሻ አለ፡፡ የምርቃት አጀማመር ከሰው ልጅ መፈጠር ጋር ፅኑ የሆነ ቁርኝት አለው:: የልማዳዊ ክዋኔዎቹ አጀማመርና አጠቃቀም እንደ ማህበራዊ ህጋዊ ሀይል ሆነው ማገልገላቸው እንደ ማህበረሰቡ ያረጁ ሲሆን ምርቃት የመቀበልና ያለመቀበል መግለጫ መልክ ሆነው ያገለግላሉ::

ዱኣ ወይም ምርቃት እንደየአገሩ ባህልና አከዋወንና አፈጻጸማቸው ይለያይ እንጂ መመረቅና መርገም በየትኛውም ህብረተሰብ የሚገኙ ጉዳዮች ናቸው:: ምርቃትን ከመባረክ ማያያዝ የብልፅግናና የምስጋና መሰረትነት እንዳለው መግለጽ ከማስረጃዎቹ አንዱ እንደሆነ Bloomer እና Tzadok (2000፡1) ይገልጻሉ:: የምርቃንና ርግማን መሰንዘሪያ ቃላት በሰው ህይወት ላይ ተፅእኖ የማሳደርና ዕጣፈንታንም የመወሰን ሀይል ያላቸው ሲሆኑ ለአመታት ምናልባትም ለብዙ ሺህ ዓመታት ከትውልድ ወደ ትውልድ ሊሸጋገሩ እንደሚችሉ Derek(1994፡11) ይገልጻሉ::

ምርቃት አንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ማህበረሰቡ በጋራ መጠቀሚያነት የያዛቸውን እሴቶች /በመቻቻል አብሮ መኖር፣ ሀቀኝነት፣ በህግና ደንብ መተዳደር፣ ገንቢ የሆኑ ባህላዊ ልማዶችን ማክበር ወዘተ. አክብሮ ሲገኝ በቃላት ወይም በተግባራዊ ምላሽ ወይም በሁለቱም የሚበረታታበት ማህበራዊ ክስተት ሲሆን በማህበረሰቡ ዘንድ መከበር፣ መባረክን ብሎም መታቀፍን ያስከትላል:: በአልከሶ መውሊድም ቢሆን የሚካሄደው ምርቃት ከዚህ ሀሳብ ጋር ተያዥነት ያለው ነው::

የዚህን ጥናት ጥሬ መረጃ ለመተንተን ከመረጥኩት ንድፈ ሀሳብ መካከል አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ አንዱ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሀሳብ ደግሞ አንድን መረጃ አውዱን በጠበቀ ሁኔታ ከነክዋኔው መቅረብ እንዳለበት ያስገነዝባል፡፡ እኔም የሰበሰብኳቸውን መረጃዎች ለመተንተን አውዳዊ ንድፈ ሀሳብ መርህን ለመከተል ሞክሬያለሁ፡፡ ለምሳሌ የሚከተለው ምርቃት ከነሙሉ አውዱ እንዴት እንደቀረበ እንመልከት፡፡ የዱአ አቀራረብ ሁኔታውን ስንመለከት መጀመሪያ አንድ በእድሜው ከፍ ያለ ሰው(መራቂው ልንለው እንችላለን) ሲመርቅ ሌላው ታዳሚ አሚን በማለት ይቀበላል፡፡ ለምሳሌ ከዚህ በታች ያሉትን ምርቃቶች እንመልከት፡፡

መራቂው፡- ቢስሚላሂ አረህማን አረሂም አላሁምዱሊላሂ ረቢልአለሚን

ታዳሚው፡- ሶሏላህ አለይህ ወሰለም

መራቂው፡- የተመኘሽውን አላህ ያስገኝልህ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ባለቤትህን አልከስዬ አፊያ(ጤነኛ) አደርገው ልብሷን እንድትለብስ ያደርጓት

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ቤት ያለ ሚስት ቤት አይልም አላህ ቤትህን ቤት ያድርግልህ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ሚስትህ ሚስት ብቻ ሳትሆን የቤትህ ምሶሶ እና ትክክለኛ ሚስት ትሁንልህ

ታዳሚው፡- አሜን

በዚህ መሀል አንድ ተመሳሳይ ችግር ያለበት ሰውዬ በመነሳት “የሔምቴ ጣመ በጋር ቀሬታት አልከስዬ አኩ ፊያ ሊያሱኝ (የእኔም ባለቤት እቤት ቀርታለችና አልከስዬ አሁን እንዲያድኑልኝ)” በማለት ሰላሳ ብር በመስጠት ዱኣ የሚያደርጉት ሽማግሌ አጠገብ ሆኖ በመጎንበስ ደጋግሞ አሜን አሜን ማለት ጀመረ፡፡ በዚህ ጊዜ ድቤ መቺው ድቤ በደንብ ደጋግሞ እየመታ ድምጹን ከፍ በማድረግ “አልከስዬ ጂጉ (አልከስዬ ድረሱ)” በማለት ሁኔታውን የበለጠ አደመቀው፡፡ ሽማግሌውም ዱኣቸውን ቀጠሉ፡፡

መራቂው፡- የቸገረህ ሁሉ ዛሬ አልከስዬ ከችግርህ ያላቁህ

ታዳሚው፡- አሜን ---- (በዚህ ታዳሚው ሁሉም ተነስቶ በመቆም ደጋግሞ አሜን አሜን ማለት ጀመረ፡፡)

መራቂው፡- ሁላችሁም ቆማቸዋል የሚቆም ልጅ ይፈጠርላችሁ

ታዳሚው፡- አሜን (በዚህ ጊዜ የድቤ ድምጽ እና የአሜንታው ድምጽ የበለጠ ደምቆ ተሰማ)

መራቂው፡- ዱኒያ ፊቱን ያዞረችበት በሙሉ ዛሬ በአልከስዪ እና በአላህ መጀን ብለናታል ፊቷን ትስጣችሁ፡፡

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አላህ መጃን አልከስዪ መጃን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አላህ ዛሬ እሺ በለን ባንተ ይሁንብህ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አልከስዪ ሀረም  አላህ የተለመነውን ሁሉ እሺ ይላል ይላሉ አባቶቻችን እሺ እንዳልካቸው ሰዎች እኛንም እሺ በለን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- እናንተ ከችግራችሁ ተላቃችሁ የዛሬ አመት በዚቺው ቦታ መጥታችሁ አምና በተደረገልን ዱኣ ተሳክቶልናል ብላችሁ በሬ የምታበሉ ሰው አላህ ያድርጋችሁ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ሁላችሁንም አላህ ከመጥፎ ነገር ናጃ ይበላችሁ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ተናግሮ ተሰሚ ያድረገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ዘርቶ አጫጅ ያድርገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ነግዶ አትራፊ ያደርገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አግብቶ ወላጅ ያደርገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ጠይቆ ጥያቄው መቅቡል የሚሆንለት ሰው አላህ ያደርገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- መውሊዳችንን አላህ መቅቡል ያደርግልን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- በአመት አመት የሚገናኝ ሰው ያደርገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ልፋታችንን ሁሉ አላህ ባዶ አያድርግብን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ያልከስዬ ሙሀባ በሁላችንም ልብ ውስጥ ይግባ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂ፡- ዱኣችን መቁብል ይሁን

መራቂው፡- ይሁን አሁን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ይሁን አሁን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አላሁ መሰሊ፡፡ (መራቂው “አላሁ መሰሊ” ብለው ምርቃታቸውን ሲጨርሱ የእሳቸውን እጅ ለመሳም ብዙ ሰዎች ወደ እሳቸው ሮጡ፡፡) በዚህ ጊዜ የመራቂውን እጅ ለመሳም በተደረገው እሽቅድምድም የተነሳ በመስገጃው ላይ ቡና፣ ሻይ እና ውሃ ፈሶበታል፡፡ በ2008 በተካሄደው ተተኳሪ የቡድን ወይይት ወቅት ይህ ጉዳይ ተነስቶ መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉ ወገኖች “መስጂድ ውስጥ መውሊድ ማክበር ከሚያስከትለው ችግር መካከል አንዱ መስገጃዎችን መነጀስ ነው” ብለዋል፡፡ ይህን ሀሳብ መሀመድ (2008፣158) ይጋሩታል፡፡

ምልከታዬ ተሳትፏዊ ምልከታ ስለነበር እኔም እንደ ማንኛውም መውሊድ አክባሪ በመሆን “በአመት አመት በአልከሶ መውሊድ እንዲያደርሰን” በማለት አቅሜ የፈቀደውን ያህል ብር ስሰጥ አንድ ሽማግሌ እንዲህ ብለው መረቁ፡፡

መራቂው፡- በል አንተ ወጣት ነህ ወጣት ሁን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- እንዳልከውም በአመት አመት ያድርሰን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- የዘመኑ ወጣት የያዘውን ያዝ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ተሻግረው እንደሄዱ ወንዶች ተሻግረህ ሂድ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- የአልከሶን መውሊድ አክብረው የተጠቀሙ ያድርግህ ያድርገን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- በል በሚቀጥለው አመት በሰው መኪና ሳይሆን በራስህ መኪና ሀረም ድረስ ከቤተሰብህ እንድትመጣ አላህ ያድርግህ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ነግደህ አትርፍ፣ አግበተህ ወልደህ ክበድ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- በሉ እኛ ብለናል አላህም ይበል አላሁመሰሊ

ታዳሚው፡- አሜን አላሁመሰሊ ሲሉ እኔም በቦታው ሲደረግ እንዳየሁት ከተቀመጥኩበት ቦታ በፍጥነት በመነሳት የመራቂውን እጅ በመሳም በእጃቸው ይዘውት የነበረውን ጫት በመቀበል ቀድሞ ወደ ነበርኩበት ቦታ ተመልሼ ተቀመጥኩ፡፡

እሁድ ማታ ሸምሰል ጀማል ውስጥ በነበርኩበት ወቅት መንዙማ አብቅቶ ምዕመናኑ ቁጭ እንዳሉ አንድ ከከተማ የመጡ የሚመስሉ ሰውዬ ተነስተው "ቢስሚላሂ አራህማን አረሂም የአልከስዬ መውሊድን በአመት አመት ያድረሰን፡፡ መውሊዳችንንም አላህ መቅቡል ያድርግልን፡፡ መውሊድን ለማጥፋት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች አላህ አደብ ይስጣቸው" በማለት መቶ ብር ከኪሳቸው አውጥተው በቦታው ዱኣ ለሚያድርጉት ሽማግሌ ሰጡ፡፡ በዚህ ጊዜ በቦታው የነበሩት ሰዎች "አስገባ፣ አልከስዬ፣ ደውራሙ" ወዘተ በሚል ቃላት መስጂዱን አደመቁት፡፡ ከዚህ በመቀጠልም ብሩን የተቀበሉት ሰውዬ የሚከተለውን ዱኣ አደረጉ፡፡

መራቂው፡- ቢስሚላሂ አራህማን አረሂም አለሀምዱሊላሂ ረቢል አለሚን በል ትንሽ ሰተህል አላህ ትልቅ ነገር ይስጥህ፡፡

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አልከስዬ መጀን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አላህ መጀን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አላህ እሺ በለን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- የአልከስዬ መውሊድን ሳትለያየን በአመት አመት በሰላም በጤና በፍቅር አድረሰን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- በአሁኑ ዘመን በዲናችን ትንሽ ኺላፍ(ልዩነት) የሚፈጥሩ ሰዎች መተው መውሊድን ለማጥፋት እየተንቀሳቀሱ ናቸው፡፡ መውሊድ የጥንት ነው፡፡ ዛሬ አልተጀመረም፡፡ መውሊድ ነብዩን ማላቅ ስለሆነ አላህም ይወደዋል፡፡ መውሊድን እናጥፋ ለሚሉ ሰዎች አላህ ቀልብ ይስጣቸው፡፡

ታዳሚው፡- አሜን አሜን (በዚህ ጊዜ አሜን ማለቱ ደምቆ ተሰማ)

መራቂው፡- አንተም በሰጠህው ብር ፋንታ ብዙ ብር ኪስህ ውስጥ ይግባ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ሌሎቻቹም እጃችሁ ይፈተና ያላችሁን ስጡና አላህ የበለጠ ይስጣችሁ

ታዳሚው፡- አሜን አሜን (በዚህ ጊዜ ከተለያየ አቅጣጫ ወደ መራቂው ብዙ ብር ተወረወረ፡፡ ሰጪው ግን ማን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ወደ መራቂው ሰውዬ በመሄድ ሀጃቸውን በመንገር ዱኣ አድርጉልኝ አሉ፡ መራቂውም ዱኣቸውን ቀጠሉ)፡፡

መራቂው፡- በሉ ሁላችሁም የፈለጋቹትን አግኙ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ባሰባቹት ድረሱ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- የወለዳቹት ይበረክ ለቁም ነገር ይብቃ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ሀፊዘል ቁርአን ይሁንላቹሁ

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- እኛ ብለናል አለም ይበል

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- አልከስዬም ይበሉ በደውሩ መጀን

ታዳሚው፡- አሜን

መራቂው፡- ይሁን ይሁን ይሁን አላሁ መሰሊ (አላሁ መሰሊ የዱኣ ማሳረጊያ ቃል ነው)፡፡

ታዳሚው፡- አሜን፡፡ በዚህ ጊዜ ዱኣ ተደርጎ ሲያልቅ ሁሌም እንደሚደረገው የመራቂውን እጅ ለመሳም ብዙ ሰዎች ይሽቀዳደማሉ፡፡ በተመለከትኳቸው ዱኣዎች ሁሉ ዱኣ ሲያልቅ ዱኣ የተደረገለት ሰው የመራቂውን እጅ ለማሳም ሲሽቀዳደም ተመልክቻለሁ፡፡ ይህ ሁኔታ ለምን እንደሆነ በሽምሰል ጀማል ዱኣ ተደርጎላቸው እጅ የሳሙ አንድ ሰውዬ ቀረብ ብዬ ዱኣ ከተደረገሎት በኂላ ለምን የመራቂውን እጅ ሳሙ ስላቸው "የተለመደ ነው ድሮም አለ፡፡ ዱኣ ያደረገልህን ሰው እጅ መሳም አጅር አለው፡፡ ለዛ ነው ሁሉም ሰው ለመሳም የሚሽቀዳደመው፡፡" የሚል ምላሽ ሲሰጡኝ ወጣት አብድልባቅ ጀማል ደግሞ "ዝም ብለው ነው የሰው እጅ መሳም ምን ትርጉም አለው፤ ይሄ ሽርክ ነው ቢተውት ይሻለቸዋል አላህን እያስቆጡት ነው" በሚል ድርጊቱን ተቃውሟል፡፡

በሁሉም ኸለዋዎች ተዘዋውሬ እንደተመለከትኩት አንድም ሴት ወጣት ትሁን የእድሜ ባለጸገ ዱኣ ስታደርግ አላየሁም፡፡ ምክንያቱን ምን እንደሆነ ከጎኔ የተቀመጡትን አንድ እናት ስጠይቃቸው "በእኛ ሀገር ለሁሉም ነገር ቅድሚያ የሚሰጠው ለወንድ ነው፡፡ ትንሽም ቢሆን፡፡ ስለዚህ ወንዶች ባሉበት ቦታ እኛ ሴቶች ዱኣ አናደርግም፡፡ ሴቶች ብቻ ከተሰበሰብን ግን ዱኣ እናደርጋለን፡፡ እኛ ዱኣ ብናደርግ ምን አይነት አይን አይናውጣ ባለጌ ናት ወንድ አስቀምጣ እሷ ዱኣ ታደርጋለች ይሉናንል ብለን ስለምንፈራ ነው፡፡ ወንዶችም እነሱ እያሉ እኛ ዱኣ ስናደርግ ደስ አይላቸውም" የሚል ምላሽ ሰተውኛል፡፡ ከእኚ እናት ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ ወ/ሮ ሉባባም[113] ነግረውኛል፡፡ በአይናጌ ኸለዋ ያገኘኋቸው አቶ ከማል ደግሞ "ሴቶች ዱኣ የማያደርጉት ወንዶች ከልክለዋቸው ሳይሆን ስለሚፈሩ ነው፡፡ ከወንድ የተሻለ ዱኣ የሚያደርጉ ሴቶች በየቤቱ ሞልተዋል፡፡ ቤታቸው ውስጥ በደንብ ዱኣ ያደርጋሉ፡፡ ነገር ግን በዚህ አይነት በጣም ብዙ ሰዎች በተሰበሰቡበት ቦታ ደፍረው ዱኣ አያደርጉም" ብለውኛል፡፡ የአቶ ከማልን ሀሳብ አቶ ኤሊያስ፣ እና ወ/ት ሀድራ ተጋርተውታል፡፡

[113] ቃለ መጠይቅ 26/05/08

ከዚህ ምርቃት ጋር አያይዤ ማንሳት የምፈልገው ጉዳይ ግንቦት 24/2007 ዓ.ም አልከሶ ሀረም ውስጥ ባዘጋጀሁት የቡድን ውይይት የአልከሶ መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉ ወገኖች መውሊድ በሚከበርበት ወቅት በርካታ ሺርኮች(ማጋራት) ይካሄዳሉ ካሉ በኋላ ለምሳሌነት ከቀረቡት ነጥብ መካከል ከዚህ በላይ የተመለከትነውን እና መሰል ምርቃቶችን በማንሳት "በመውሊድ አልከስዬ እና አላህ ይሻረካሉ" ይላሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የዚህ አይነት ዱኣ በድሬ ሼኽና ሁሴን የዋሬ ክብረ በዓል ላይ እንዳለ እና ይህን ጉዳይ የሰለፊያ ወይም የወሀቢያ አስተሳሰብ የሚከተሉ ሰዎች እንደሚቃወሙት Østebø (2008:142) እና ገመቹ (2007፣98) ጽፈዋል፡፡

## 6.2.5 ዚያራ

ዚያራ ማለት መውሊድ በሚከበርበት ወቅት መውሊድ የሚከበርብት ቦታ የሚገኘውን የወልይ መቃብር ስፍራ እና የቦታውን ወልይ በህይወት ካሉ በአካል በመሄድ መዘየር ነው፡፡ Ostransky(2008፣140) ዚየራ ማለት የወልዮችን የመቃብር ስፍራ እና ወልዩ በህይወት ካሉ እጃቸውን በመሳም በረከት ለማግኘት በመሳብ የሚከሄድ ክንውን እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ Minako (2009፣512) ደግሞ በሙስሊሙ አለም ወልይ ወይም ቅዱስ ናቸው ተብለው የሚታመኑ ሰዎች በየጊዜው እንደሚዘየሩ እና በህይወት የሌሉ ከሆነ ደግሞ የመቃብር ስፍራቸው እንደሚዘየር ያስረዳሉ፡፡፡ Bronislav(2008፣133) የተባሉ ጸሀፊ ግብጽ ውስጥ ስላለው የመውሊድ አከባበር ስርዓት በሚያትተው ጽሁፋቸው "Many Muslims-either regularly or occasionally-performed ziyāra, a visit to the shrine of a holy person. Mawlid reminds the life and miracles of a saint that are made possible through his miracle-making force or blessing (baraka), the source of which is God (Allāh)" በማለት ያስዳሉ፡፡ Ostebo (2012:172) ዚያራ ማለት ቅዱሳን የሚባሉ ሰዎችን እና ቦታዎችን የመጎብኘት ስርዓት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ Renard(2005:248) "The practice of journerying to holy sites, pareticulariy the tombs of important religious figures such as shaykhs, founders of orders, and Friends of God" ይህ ማለት ዚያራ የሚካሄደው ቅዱሳን በሚባሉ ስፍራዎች፣ በተለይ ታዋቂ የሃይማኖት መሪዎች፣ ሼኾች፣ ወዘተ የመቃብር ስፍራ መዘየር ማለት ነው፡፡

በአልከሶ መውሊድ ሰሞን ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል አንዱ ዚያራ ነው፡፡ ዚያራው ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው የአልከስዬን እና የቤተሰቦቻቸው የቀብር ቦታ መዘየር

(መጎብኘት) ሲሆን ሁለተኛ በአሁኑ ወቅት መስጂዱ በመምራት ላይ ያሉትን መሪ ኸለዋቸው ድረስ በመሄድ ስጦታ በመስጠት መዘየር እና ዱአ ማስደረግ ነው፡፡ እነዚህን የዚያራ አይነቶች ከዚህ በመቀጠል ምን እንደሚመስሉ እንመለከታለን፡፡

### 6.2.5.1 የዶሪህ/የመቃብር ቦታ ዚያራ

በአለማችን ወልዮችን መሰረት በማድረግ ከሚካሄዱ ክንውኖች መካከል አንዱ የወልዩን መቃብር በተለያዩ አከኂኖች መዘየር(መጎብኘት) እንደሆነ Bronislav(2008፣128) እና Ostobe(2014፣29) ያስረዳሉ፡፡ መሀመድ (2009፣990-) ዚያራ ከሀዲስ አንጻር ስንመለከተው የሚከተለውን እንደሚመስል ያሰረዳሉ፡፡

> ሱፍዮች መቃብር ዚያራን በሚመለከት ከነብዩ ሙሀመድ ተግባርና ሀዲስ ጋር የተያያዘ መነሻ አላቸው፡፡ የመጀመሪያው ነብዩ ሙሀመድ በህይወት በነበሩበት ጊዜ Baqi Cemetery የተባለውን ቦታ ይጎበኙ የነበረበትን ቦታ ይጎበኙ የነበሩትን ሀዲስ መነሻ ያደርጋሉ፡፡ ሁለተኛው ነብዩ "ቀብርን መጎብኘት ከልክያችሁ ነበር፡፡ ከእንግዲህ ግን ጎብኙ፡፡ ወይም "ቀብርን መጎብኘት የፈለገ መጎብኘት ይችላል፤ መጪውንም ዓለም ያስታውሳል፡፡" ያሉትን ሀዲሳቸውን መሰረት ያደርጋሉ፡፡

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው ዚያራ ሀዲሳዊ መሰረት እንዳለው ነው፡፡ ይህን ሀሳብ ተቀዳሚ ሙፍቲህ ዑመር እንድሪስ ይጋሩታል፡፡

እነዚህ አገላለጾች በአልከሶ መውሊድም ይንጸባረቃል፡፡ ምክንያቱም በአልከሶ መውሊድ ሰሞን ከሚካሄዱ ክንውኖች መካከል አንዱ አልከስዬ እና ቤተሰቦቻቸው ያረፉበት የቀብር ቦታን የተለያዩ ክንውኖችን እየከወኑ መዘየር ነው፡፡ በአልከሶ ሀረም ውስጥ ከሸምሰል ጀማል መስጂድ ፊት ለፊት የአልከስዬ እና ቤተሰቦቻቸው አስክሬን ማረፊያ ስፍራ ይገኛል፡፡ ይህን ቦታ አልከስዬ በህይወት እያሉ የቀብር ቦታቸው እንዲሆን እንደመረጡት በመቃብር ስፍራው የአገኘኋቸው እና መቃብሩን የሚዘይሩ ሰዎችን የሚያስተናግዱት ሼኽ በህሩ የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ይሄ ቦታ የተመረጠው በአልከስዬ ነው፡፡ አልከስዬ ሊሞቱ አንድ ሳምንት ሲቀራቸው ይህ ቦታ ለእሳቸው ማረፊያ እንዲሆን ወስነዋል፡፡ አሁን የእሳቸው አስክሬን ያለበት ጎጆ የተሰራው እሳቸው በህይወት እያሉ ያሰሩት

ነው፡፡ ራሳቸው እዝህ ድረስ መተው እዚህ ቦታ ላይ ጎጆ ቤት ስርታችሁ ውስጡ ላይ ቅበሩኝ ብለዋል፡፡ ከእሳቸው በተጨማሪ የሳቸው የቅርብ ቤተሰብ ሲያርፍ እዚህ እንዲቀበር ተናዘዋል ይባላል፡፡ አሁን የምታየው በሙሉ የእሳቸው ልጅ እና የልጅ ልጅ ነው፡፡ አንድ ባዳ ሰው የለበትም፡፡ ሚስታቸውም የተቀበሩት እዚህ ነው፡፡ የሳቸው ልጆች የሆኑት ፈይድ፣ ጌታዋና ሌሎችም እዚህ ነው የተቀበሩት፡፡[114]

የሼኽ ባህሩን ሀሳብ አቶ ሁሰይኒ፣ ወጣት ፈተረሁፍ፣ እመት ሀድራ ፣ ሼኽ ከድር፣ ገራድ ኑርሰቦ እና ሌሎችም መረጃ አቀባዮች ይጋሩታል፡፡ በመቃብር ስፍራው ውስጥ በርካታ በዘመናዊ እና በባህላዊ መንገድ የተሰሩ ቤቶች ይታያሉ፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ የመቃብር ድንጋዮች በብዛት የታያሉ፡፡ መጀመሪያ ወደ ግቢ ሲገባ የሚታየው አንድ ትልቅ በስልጤ የባህል ቤት አሰራር ዘዴ የተሰራ የጎጆ ቤት ነው፡፡ ጎጆ ቤቱ የአልከስዬ አስክሬን ያረፈበት ቦታ ነው፡፡ ከአልከስዬ ቀጥሎ የበይድ፣ የሰይድ አሽራፍ፣ የሳዳት፣ የጌታዋ፣ የፈይድ ወዘተ መቃብሮች ልክ እንደ አልከስዬው የመቃብር ቤት የራሳቸው የሆኑ ቤቶች ተዘጋጅቶላቸው ይገኛል፡፡ የአልከስዬ አስክሬን ያረፈበት ቤት ሳር(ጎጆ) ቤት ሲሆን የሌሎች ግን በዘናመዊ መንገድ በግንብ የተሰራ ነው፡፡ እንደ ሼኽ በህሩ አገላለጽ ሁሉም የአልከስዬ ልጆች እና የልጅ ልጆች ሲሞት አስክሬናቸው አልከስዬ በተቀበሩበት ግቢ ውስጥ የሚያርፍበት ቤት ይዘጋጃል፡፡ ከአልከስዬ ልጆች እና የልጅ ልጆች ውጭ ግን ሜዳው ላይ ይቀበራሉ እንጂ ልክ እንደ አልከስዬ ቤት እንደማይዘጋጅላቸው አቶ ሁሴይኒ በመግለጽ ይህ የሆነው የተለየ ምክንያት ኖሮ ሳይሆን የተለመደ ስለሆነ ነው ይላሉ፡፡

አቶ ሁሴይኒ[115] እንደነገሩኝ ከሆነ ይህ ቦታ የሚዘየረው በየወሩ የመውሊድ ቀን እና በአመት አንዴ በዋናው መውሊድ ጊዜ ብቻ ነው፡፡ ይህን ቦታ ለዘየር የራሱ የሆነ ሸርጥ(ደንብ) አለው፡፡ እነዚህ ደንቦች ምን ምን ምን እንደሆኑ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡

***ሀ. መወሰን(መነየት)፡-*** *የመጀመሪያው ሸርጥ የመቃብር ቦታውን ለመዘየር መነየት(መወሰን)* ነው፡፡ ሁለተኛው ለሰላት እንደሚዘጋጅ ሰው ዉዱእ ማድረግ ነው፡፡ ሶስተኛው ከቅጥር ጊቢው ውጭ ጫማውን ማውለቅ ወዘተ ናቸው፡፡ እነዚህን ቅድመ ዝግጅቶችን ያደረገ ማንኛውም ሰው ገብቶ መዘየር ይችላል፡፡ እኔም ከዚህ በላይ የተቀመጡትን ሸርጦች በማሟላት

---

114 ቃለ መጠይቅ፣ ሼኽ በህሩ፣ 14/09/2008

115 ቃለ መጠይቅ 27/05/080

በ15/09/2008 ዓ.ም የመውሊዱን የአካባበር ሁኔታ ለመመልከት በሄድኩበት ወቅት የአልከስዬን እና የቤተሰቦቻቸውን የመቃብር ስፍራ በሼኽ በህሩ ረዳትነት ጎብኝቻለሁ።[116] የዚህ አይነት የአዘያየር ሁኔታ በልሎችም መውሊዶች ላይ እንደሚካሄድ ጥናቶች ያሳያሉ። ለምሳሌ Yasuo and Minako (2009፣502) በሀገራችን መውሊድ ከሚከበርባቸው ቦታዎች መካከል አንዱ በሆነው የያ( Ya'a) ያለውን ሁኔታ እንደሚከተለው ይገልጹታል። የያ (Ya'a) ለዚየራ የሄዱ ምዕመናን የአልፈሩቅ አህመድን ሙዝየም ይጎበኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ የአልፈሩቅ አህመድን አስክሬን ይዘይራሉ(እጅ ይነሳሉ) እና ይስማሉ። እነዚህ ምዕመናን በዝየራው ቦታ እስከ ሰላሳ ደቂቃ ይቆያሉ።

**ለ. ስጦታ(ሀዲያ) ማቅረብ፦** ዘያሪዎች ወደ አስክሬኑ ወዳረፈበት ክፍል የሚገቡ ሰዎች መግቢያ በሩ ላይ ሽቶ፣ እጣን እና ሰንደል ለቦታው ጠባቂ እያስረከቡ ይገባሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ ውስጥ ሳይገቡ በሩ ጥግ ላይ አጎንብሰውና ግንባራቸውን መሬት በማስነካት ዱኣ ያደርጋሉ። በዚህ ሁኔታ ዚያራ ወቅት የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይዞ መግባት የተለመደ ነው። ለምሳሌ Yasuo and Minako (2009፣502) "Many pilgrims leave ignited incense sticks somewhere near the entrance, or on the fringe of the tomb behind the curtain covering it. There also was a rare case of a pilgrim leaving his letter for *Al-Faki* at the tomb." በማለት በያ የሚካሄደው የአዘያየር ሁኔታ ይገልጻሉ። ይህ የአዘያየር ሁኔታ አልከሶ ካለው የአዘያየር ሁኔታ ተመሳሳይ ነው።

**ሐ. መለመን ወይም ዱኣ ማድረግ፦** ምዕመናን ዚያራ ከሚያካሄዱበት ጉዳይ መካከል አንዱ የተለያየ ችግር አጋጥሟቸው ከችግራቸው እንዲላቀቁ ወይም ከበሽታ እንዲፈወሱ ዱኣ ለማድረግ ወይም ወሊዩን ለመለመን እንሚሄዱ መሀመድ(2009)፣ እሸቱ(1973) ገመቹ(2012) እና ሌሎቹም በጠኗቸው ጥናቶች ያሳያሉ። በአልከሶ መውሊድም በዚየራ ወቅት የዚህ አይነት ሁኔታ አለ። ለምሳሌ ሼኽ አብዱረዛቅ በ2007 በዋነው የመውሊድ ቀን የአልከስዬን ዶሪህ ሲዘይሩ እና ዱኣ ሲያደርጉ ያገኘኋቸው ሲሆን ለምን ዚየራ እንደሚያደርጉ ስጠይቃቸው የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል፡

> እዚህ ቦታ ላይ ብዙ ሰዎች ሽርክ ይሰራል ይላሉ። አሁን አንተ ዞረህ እንዳየህው ምንም ሽርክ አይሰራም። አልከስዬ ከእኛ የተሻሉ ለአላህ የቀረቡ

[116] አቶ ሁሴይኒ አስቀድመው ቪዲዮ መቅረጽም ሆነ ፎቶ ማንሳት እንደማይፈቀድ ስለነገሩኝ በጉብኝት ወቅቴ የተመለከትኩትን ነገር በማስታወሻ ደብተሬ ከመያዝ በስተቀር ፎቶም ሆነ ቪዲዮ አልቀረጽኩም።

ትልቅ አሊም ስለነበሩ የእሳቸው ዱኣ በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ነበረው፡፡ አሁንም ቢሆን በእሳቸው መቃብር ቦታ የሚደረግ ዱኣ መቅቡል (ተቀባይነት ያለው) ነው፡፡ ያ ስለሆነ ነው ሰዎች ከሩቅ ቦታ መተው እዚህ ዱኣ የሚደርጉት፡፡ የሚሰጡት ስጦታ በኒያ(በፍላጎት) እንጂ ግዴታ አይደለም፡፡ ሰዎችም እዚህ መተው የሚለምኑት አልከስዬን ሳይሆን አላህን ነው፡፡ አልከስዬን የሚለምን ሰው ካለ ስህተቱ የራሱ ነው፡፡ አልከስዬ እኮ እኔ እንዲህ አደርጋለሁ አላሉም፡፡ ግን የተነገራውን ችግር ለአላህ በመንገር ይፈቱ ነበር፡፡ አሁን እኔም ከጅማ ነው የመጣሁት ዚያራ የማደርገው አባቴ ስለሞቱ እሳቸው ጀነት እንዲገቡ ዱኣ ለማድረግ ነው፡፡ ለሌላ ነገር አይደለም፡፡ በዚህ አይነት አላህ በመረጣጨው ሰዎች ማሪፊያ ቦታ የተደረገ ዱኣ ተቀባይነት አለው፡፡ የመቃብር ዚየራን ነብዩም ፈቅደውታል፡፡



ፎቶ 9፦ አጥኚው ለሼኽ አብዱልረዛቅ ከዚያራ መልስ ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ[117]

ከእኚህ መረጃ አቀባዮች በተጨማሪ በርካታ ሰዎች የአልከስዬን የመቃብር ስፍራ ይጎበኛሉ፡፡ እነዚህ ዘያሪዎች የሚዘይሩበት እና በስፍራው ዱኣ የሚያደርጉበት የየራሳቸው የሆነ ዓላማ ወይም ምክንያት አላቸው፡፡ እነዚህን ጉዳዮች ከጤና፣ ከኢኮኖሚ፣እና ከሃይማኖት አንጻር ልንመለከታቸው እንችላለን፡፡ ከጤና አንጻር ስንመለከተው በተለያዩ በሽታዎች የተጠቀ ሰዎች እና ልጅ ያጡ ሰዎች ለዚየራ እና ዱኣ ለማድረግ ይሄዳሉ፡፡ ከኢኮኖሚ አንጻር ስንመለከተው

[117] ፎቶ በፈተረሁፍ 16/09/07 አለከሶ ሀረም

ደግሞ የንግድ ስራ እና እርሻ ሰርተው ውጤታማ ያልሆኑ ሰዎች በስራቸው ስኬታማ እንዲሆኑ ዱኣ ለማድረግ ዚያራ ወደ ሚካሄድበት ስፍራ ይሄዳሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ወጣት በቦታው ዚየራ ሲኬድ አግኝቼው ለምን ዚየራ ሲያደርግ አግቼው ለምን ዚየራ እንደሚያደርግ ስጠይቀው "ብዙ ወጣቶች እዚህ እየመጡ የተለያዩ ነገሮችን እየነየቱ በንግዳቸው ትርፋማ ሲሆኑ ስላየሁ እኔም ልሞክር ብዬ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥቶኛል፡፡ ከሃይማኖት አንጻር ስንመለከተው ደግሞ ነብዩ ሙሀመድ "የመቃብር ስፍራዎችን ዘይሩ ለሞቱ ሰዎችም ዱኣ አድርጉ፣ እናንተም ሞትን አስታውስ" ብለዋል ኪለው ሀዲስ በመነሳት ወደ መቃብር ስፍራው በመሄድ ዚያራ እና ዱኣ የሚያደርጉ ሰዎች አሉ፡፡

ባጠቃላይ ዘያሪዎች ዶህሪ የመዘየሪያ ዋነኛ ምክንያት አልከስዬ በህይወት እያሉ ለእነዚህ ችግሮች መፍትሄ ይሰጡ ስለነበሩ አሁንም በእሳቸው የመቃብር ስፍራ የሚደረግ ዱኣ ወይም ልመና ተቀባይነት አለው የሚል ነው፡፡ ይህን አባባል በሌላ እይታ እስናየው አልከስዬ ሞተው እንኳን የማማለድ ስራ ይሰራሉ የሚል አንድምታ አለው፡፡ የአልከስዬን እና ቤተሰቦቻቸውን የመቃብር ስፍራ ወንድም ሴትም መዘየር ይችላል፡፡ ነገር ግን ሼኽ በህሩ በጉብኝታችን ወቅት እንደገሩኝ ከሆነ ሴት ልጅ ያለ ቅርብ ዘመዷ ወይም ባለቤቷ ውጭ መዘየር አትችልም፡፡ ሴቶች ለምን ያለ ወንድ እንደማይዘይሩ ሼኽ ባህሩ "ሴት ልጅ በእስልምና ከቅርብ ዘመዷ ወይም ከባለቤቷ ውጭ እንደፈለገችው እንድትንቀሳቀስ አይፈቀድላትም፡፡ ይሄም የእስልምና መስፋፊያ ቦታ ስለሆነ ሴቶች ብቻቸውን እንዲገኙ አይፈቀድላቸውም፡፡ ይሄ እስላማዊ ደንብ ነው፡፡" በማለት አስረድተውኛል፡፡ Trimingham (1952)፣ Eshetu (1973)፣ Østebø (2008)፣ Braukämper (2002)፣ Pankhurst (1994)፣ Amira (2014)፣ Gemechu (2014) አብዱልረህማን (2006) እና ሌሎችም ባጠኗቸው ጥናቶች ላይ ልክ እንደ አልከሶው ሁኔታ ዚያራ እንደሚካሄድ ጽፈዋል፡፡ ስለዚህ ዚያራ የሀገራችን መውሊዶች የጋራ ገጽታ ነው ማለት ይቻላል፡፡

### 6.2.5.2 የመስጂዱን መሪ (ቃዲ)መዘየር

ሁለተኛው የዚያራ አይነት በህይወት ያሉ የመስጂዱን መሪ የተለያዩ ስጦታዎችን ይዞ በመሄድ መዘየር ነው፡፡ ዚያራው የሚካሄደው ከሸምስል ጀማል ፊት ለፊት በሚገኘው የመስጂዱ መሪ የእንግዳ መቀበያ ኸለዋ በረንዳ እና ውስጥ ክፍል ነው፡፡ ይህ ቦታ እና የአዘያየር ሁኔታ አልከስዬም በነበሩበት ወቅትም እንደነበር ሼኽ ከድር እና ገራድ ኑርሰቦ

ያስረዳሉ። እነዚህ መረጃ አቀባዮች አያይዘውም አልከስዬም እንደ አሁኑ በረንዳ ላይ በመቀመጥ ሊዚያራቸው የመጣን ሰው ያስተናግዱ ነበር። ነገር ግን እድሜያቸው እየጨመረ ሲመጣ ወልይነታቸው እየጨመረ ሲሄድ እሳቸው ውጭ መውጣት ትተው በእሳቸው ቦታ ሌላ ሰዎች ተቀምጠው ዱኣ ያደርጉ ነበር።

በቦታው ተገኝቼ እንደተመለከትኩት ይህ የዚያራ ኸለዋ በዘመናዊ መልክ በግንብ የተሰራ ሲሆን ሰፊ በረንዳ አለው። ወደ ውስጥ ሲገባ ደግሞ አራት መካከለኛ ክፍሎችን ይዟል። የውስጥ ይዞታው ሙሉ በሙሉ ዘመናዊ ነው። ወጣት ሽምሴ[118] ይህ ኸለዋ ከመውሊድ ውጭ ለተለየየ ጉዳይ የሚመጣ ሰው የሚያርፍበት ክፍል መሆኑን ይናገራል። ሽምሴ ማለት በማንኛውም ጊዜ ወደ አልከሶ ሀረም ብንሄድ የምናገኘው የእንግዳ ማረፊያ ቤቱ ቁልፍ የሚይዝ እና እንግዳ ተቀብሎ የሚያስተናግድ ወጣት ኻዳሚ ነው። ከ20/09/2007 እስከ 10/10/2007 እና ከ10/09/2008 እስከ 25/09/ 2008 ዓ.ም መስክ ላይ ቆይቼ መውሊድ ሲከበር እንዳየሁት በዚህ ኸለዋ በረንዳ ላይ የእድሜ ባለጸጋዎች በረንዳ ላይ ተቀምጠው የተለያዩ ሰዎች ለመውሊዱ የሚያመጡትን ስጦታ ይቀበላሉ፤ ይዘይራሉ፤ ዱኣ ያደርጋሉ። በስጦታ ከሚመጡ ቁሳቁሶች መካከል የተለያዩ የበሰሉ እና ጥሬ ምግቦች፣ በግ፣ ፍየል፣ በሬ፣ ጫት፣ እጣን፣ ሰንደል ወዘተ ይገኙበታል። ከበሰለ ምግብ ውስጥ በብዛት የሚቀርበው "ፊናንቾ" እና "አተካኖ" ናቸው። እነዚህ ዘያሪዎች ያመጡትን ስጦታ ከመስጠታቸው በፊት ያለባቸውን ሀጃ(ጉዳይ) ስጦታውን ተቀብሎ ለሚያቀብለው ሰውዬ ይነግሩታል። እሱም የተነገረውን ጉዳይ ለሽማግሌዎች እና ለመሪው በመንገር ዱኣ እንዲያደርጉላቸው ያደርጋል። በዚህ ጊዜ መሪው ወይም አንድ ሽማግሌ በተቀመጡበት ቦታ ለባለ ጉዳዩ ዱኣ ያደርጋሉ። እዚህ ቦታ መጥቶ ዱኣ ከማስደረግ በተጨማሪ የገሪቦች አለቃ ጋርም ዱኣ የሚያስደርጉ ሰዎች አሉ።

ዱኣ በሚያደርጉበት ጊዜ ዱአ የሚደረግለት ሰው በጉልበቱ በመበርከክ ወይም ጎንበስ በማለት አሜን ይላል። በዱኣ ወቅት በቦታው ያሉ ሰዎችም አሜን በማለት ያግዛሉ። ዱኣው እንዳበቃም ዱኣ የተደረገለት ሮጦ በመሄድ ዱኣ ያደረገለትን ሰው እጅ ይስማል። ዱኣ የሚደረግለት ሰው በጉልበቱ እንደሚንበረከክ ወይም ጎንበስ እንደሚል በ24/09/2007 በረንዳ ላይ ዱኣ ሲያደርጉ የነበሩትን ሼኽ ከድር ስጠይቃቸው "ምንም የተለየ ምክንያት ኖሯቸው ሳይሆን ለቦታው እና ለሽማግሌዎች ያላቸውን ክብር ለመግለጽ ነው" የሚል ምላሽ

[118] ቃለ መጠይቅ 24/05/08

ሰጥተውኛል። በዝያን ቀን በረንዳ ላይ ዱኣ ሲደረግላቸው ጎንበስ ብለው አሜን ሲሉ የነበሩት አቶ መሀመድ ዳውድ ከሼኽ ከድር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሀሳብ ሰጥተዋል።

በዚህ የዚያራ ቦታ በረንዳ ላይ ዚያራቸውን አድርገው ከሚሄዱት በተጨማሪ ውስጥ ክፍል ገብተው የሚዘይሩ እና ዱኣ የሚያስደርጉም አሉ። ውስጥ ክፍል ገብቼ እንደተመለከትኩት በረንዳ ላይ ከሚካሄደው ስርዓት የተለየ ነገር የለም። ነገር ግን ዱኣው ረዘም ይላል፤ የሰው ብዛትም የለም። ውስጥ ክፍል ዘይረው ሲወጡ ያገኘኋቸው አንድ ስማቸውን ሊነግሩኝ ፈቃደኛ የልሆኑ ሰውዬ "ውስጥ የገባሁት ለሌላ ጉዳይ አይደለም። ለዚያራና ለዱኣ ነው። ሌላ ምንም አልሰራሁም። እዚህ በረንዳ ላይም መዘየርና ዱኣ ማስደረግ እችል ነበር። ግን እዚህ ጫጫታ ይበዛል" ብለውኛል።[119]

በቦታው እንደተመለከትኩት ስጦታ ለመስጠት የሚመጡ ሰዎች ወደ ስጦታ መስጫው ቦታ ሲመጡ ፊታቸው ላይ የመጨነቅ ስሜት ይነበብባቸዋል። ነገር ግን ስጦታውን ሰጥተው ሀጃቸውን ተናግረው ዱኣ ተደርጎላቸው ሲመለሱ ፊታቸው ላይ ቀድሞ ይነበብ የነበረው ጭንቀት አይታይም። ሼኽ ከድር[120] ደግሞ "አንድ ሰው ለመስጂድ አቅሙ የፈቀደውን ነይቶ ከሰጠ ሀጅ እንዳደረገ ይቆጠራል ይሉ ነበር አልከስዬ" ካለሁ በኋላ "ብዙ ሰው ስጦታ የሚሰጠው ሀጅ መሄድ ስለማይችል እዚህ ሀጅ ላድርግ በማለት ነው።" ይላሉ። ከሼኽ ከድር ሀሳብ እና ስጦታ ሰጥተው ከሚውጡ ሰዎች የፊት ገጽታ ከሚታየው ሁኔታ አንጻር የደስታቸው ሁኔታ የተፈጠረው "ሐጅ አድርጌያለሁ" ከማለት የመነጨ ሊሆን ይችላል። ይህ ደግሞ መውሊድ አክባሪዎች መውሊዱን በማክበራቸው ከሚያገኙት ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ መካከል አንዱ ነው።

---

[119] የሰውየውን የፊት ገጽታ ስመለከተው "ምን አገባህ" አይነት ነገር ይነበብበት ነበር።

[120] ቃለመጠይቅ 24/06/08



ፎቶ 10፡- ስጦታ ለመስጠት ቃል የገቡ ሰዎች ስጦታቸውን ለመስጠት ሲሄዱ[121]

ዚያራን በተመለከተ Pankhurst (1994፣934-935) ያቀረቡትን ሀሳብ ምዕራፍ ሶስት ላይ ተመልክተናል፡፡ ከአልከሶ መውሊድ አንጻር ስንመለከተው ደግሞ የሚከተለውን ይመስላል፡፡ ለክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ አምስት አይነት መሰረታዊ ገጽታ እንዳለው ያስረዳሉ፡፡ እነዚህ አምስት የዚያራ ገጽታዎች በአልከሶ መውሊድ መኖራቸውን ማረጋገጥ ይቻላል፡፡

1.ኛ ዚየራ አለ ማለት አንድ የሚከበር ክብረ በዓል አለ ማለት ነው፡፡ ከዚህ አንጻር ክብረ በዓሉ የአልከሶ መውሊድ ነው፡፡

2ኛ. ከተለያዩ ቦታዎች የሚነሱ ተጓዦች የሚደርሱበታ አንድ የጋራ የሆነ ቦታ አላቸው፡፡ የሚደርሱበት ቦታ የሃይሞኖት መሪ የሚኖሩበት ስፍራ፣ የተቀደሰ ቦታ፣ተፍጥሯዊ የሆነ ቦታ፣ ተራራ፣ ወዘተ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህ አንጻር ምዕመናኑ የሚሰባሰቡት በአልከሶ መስጂድ እና ሀረም ውስጥ ነው፡፡

3ኛ. ዘያሪዎቹ የሚዘይሩት በተወሰነ ጊዜ እና ቀን አላቸው፡፡ የአልከስዬ የመቃብር ቦታ እና የመስጂዱ መሪ የሚዘየሩት በብዛት በዋናው የአልከሶ መውሊድ ቀን እና በረቢየል አወል መውሊድ ሰሞን ነው፡፡

[121] ፎቶ ባጥኚው፣ 23/04/07 አልከሶ ሀረም

4ኛ. ሁሉም ባይባልም አብላጫ ዘያሪዎች የሚዘይሩት ምድራዊ ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ሳይሆን መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት ነው፡፡ ይህም ጉዳይ በአልከሶ መውሊድ ይጸባረቃል፡፡

5ኛ. ወደ ዚያራ ቦታ ተጓዦቹ በብዛት የሚጓዙት በተነጠል ሳይሆን በቡድን ነው፡፡ የአልከሶ መውሊድ አክባሪዎችም በብዛት የሚጓዙት በቡድን በቡድን ነው፡፡ ስለዚህ Pankhurst ለክብረ በዓል የሚደረግ ጉዞ አምስት አይነት መሰረታዊ ገጽታ አለው ያሉት ጉዳይ በአልከሶ መውሊድም የሚንጸባረቅ መሆኑን ከዚህ በላይ በተመለከትነው ሁኔታ መረዳት ይቻላል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው በአልከሶ መውሊድ የሚካሄደው ጉዞ በሌሎች መውሊዶች ከሚካሄደው ጉዞ ተመሳሳይነት አለው ማለት ይቻላል፡፡ ይህን ሁኔታ ከፎክሎር አንጻር ስንመለከተው በሀገራሰባዊ እምነት ስር ልንመለከተው ይችላል፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው ዚያራ የሚካሄደው በመቃብር ስፍራ እና በመስጂዱ መሪ ኸለዋ ነው፡፡ ዚያራ የሚካሄደው መንፈሳዊ እና አለማዊ ጥቅም አገኛለሁ ከሚል ሀሳብ የመነጨ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ምዕመናን ይህን ዚያራ የሚያደርጉት ከሁለቱ አንዱን አገኛለሁ በሚል ነው፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ ሁለቱንም ጥቅም ለማግኘት አስበው የሚመጡ ሰዎችም እንዳሉ ከዚህ በላይ ከቀረበው ትንተና መረዳት ይቻላል፡፡ የዚህ አይነት ዚያራ በአልከሶ መስጂድ ብቻ የሚካሄድ ሳይሆን በሌሎቹም ሙስሊሞች በሚኖሩባቸው ሀገራት እንደሚካሄድ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ምንም እንኳን በአሁኑ ጊዜ ተቃውሞ ቢያጋጥመውም፡፡

### 6.2.6 ጫት የመቃም ስነ ስርዓት እና ፎክሎራዊ ክንውኖች

የሰው ልጅ ጫትን መጠቀም ከጀመሩ ከአንድ ሺህ አመት በላይ እንዳስቆጠረ Getahun and Krikorian (1973)፣ Lemessa (2001)፣ Gebissa, (2012) እና ሌሎቹም ያስረዳሉ፡፡ በነዚህ ዘመናት ውስጥ በአንድ ቦታ ተወስኖ አልተቀመጠም፡፡ ጥናቶች እንደሚገልጹት በአንድ አካባቢ ብቻ ይበቅል የነበረው የጫት ተክል ሀገራትን አቋርጦ አህጉራትን አዳርሷል Fitzgerald (2009)፡፡ ከአንድ አካባቢ ህዝብ ባህልና እምነት ጋር ይያያዝ የነበረው የመቃም ልማድ ከተለያዩ አካባቢዎች ባህሎችና እምነቶች ጋር ተቆራኝቷል (Solomon፣ 2011; Gebissa, 2010)፡፡ በምስራቅና ደቡባዊ ምስራቅ የአፍሪካ ሀገሮች፣ በአረቢያን የባህር ሰርጥ አካባቢ በሚገኙ ሀገሮች እንዲሁም ከስደት ጋር ተያይዞ በአውስትራሊያ፣ በአንዳንድ የምስራቅ አውሮፓ ሀገሮች እና በአሜሪካ እየተቃመ እንደሆነ Gebissa (2012) እና

Solomon (2011) ያስረዳሉ። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያመለክቱትም ጫት በተለያዩ ምክንያቶች በአለም ላይ ያሰፋው የቃሚዎቹን ቁጥርና መልክዓምድራዊ ንፍቀ-ክበቡን ብቻ አይደለም፤ ማህበራዊና ግለሰባዊ ተግባራቱን፣ የአቃቃም ስርዓትና ክዋኔውን፣ ትዕምርታዊ ውክልናውንና ማህበራዊ ፍቺዎቹንም አስፍቷል። የተለያዩ አተያዮች በተራቸው ጫትን የአነጋጋሪና አነታራኪ ፍቺዎች ማደሪያ ትዕምርት እንዲሆን አድርገውታል። የአንዱ ህዝብ ባህል "የአላህ ቅጠል" (Gebissa, 2004)፣ "የገነት አበባ" (Getahun & Krikorian, 1973: 353) እያለ በመጥራት የማንነቱ መገለጫ ትዕምርት ሲያደርገው ይስተዋላል። አንዳንዶች ጫት መቃም ማህበራዊና ባህላዊ መሰረት ያለው ተግባር እንደሆነ ይገልፃሉ፤ ማህበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር ረገድ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ይናገራሉ (Lamina RM & Lamina S, 2013: 80)። ሌሎች ደግሞ ቅጠሉን ሰዎች የሚያኙት (የሚቅሙት) ለመነቃቃት ነው Kandari et al, (2014፣ 579) ይላሉ።

ጫትን ከሀገራችን ነበራዊ ሁኔታ አንጻር ስንመለከተው ጫትን የመቃም ባህልም በአብዛኛው ተያይዞ የሚገኘው የአለማችን የእስልምና መናገሻ ከሆነችው ከሐረር ከተማ ጋር ነው። ጫትን የመቃም ባህል በሐረር አካባቢ ለአያሌ ዘመናት የቆየ ልማድ እንደመሆኑ መጠን ከአካባቢው ህዝብ ባህላዊ ማንነትና መለያ ጋር የጠበቀ ትስስር እንዳለው Gebissa (2012) ያስረዳሉ። ምን እንኳን ከሀገራችን አንጻር ጫት የመቃም ጉዳይ በተለይ ሁኔታ የምስራቁ የሀገራችን ክፍል ቢወሳም ሁሉም የሀገሬቱ ክልሎች የመቃም ልምድ እንደተሰራፋ ይነገራል። በአሁኑ ዘመን ጫት እና መውሊድ የጠበቀ ቁርኝት አላቸው። በመሆኑም በአልከሶ መውሊድ ሰሞን ጫት በተለያዩ ፎክሎራዊ ክንውኖች ታጅቦ ይቃማል።

በአልከሶ መውሊድ በደመቀ ሁኔታ እና በስፋት ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል ጫት መቃም ይገኝበታል። በዚህ መውሊድ ጫትን በተናጠል ከመቃም ይልቅ በቡድን ቡድን ሆኖ መቃም የተለመደ ነው። አልፎ አልፎ ግን ሜዳ ላይ ወይም ዳስ ውስጥ ለብቻቸው ጫት የምቅሙ ወንዶች ያገጥማሉ። ሴተች ግን ሁሌም የምቅሙት በቡድን ነው። የቡዱኑ አወቃቀር ወንድ እና ሴት ድብልቅ አልያም ወንዶች ለብቻቸው ሴቶች ለብቻቸው ሊሆን ይችላል። የአቀማመጥ ሁኔታው በብዛት ክብ ነው። ጫት ለመቃም የተሰናዱ ሰዎች መቃም ከመጀመራቸው በፊት በቅድሚያ የሚያስፈልጋቸውን እንደ ውሃ፣ ለስላሳ፣ ሰንደል፣ እጣን፣ ስኳር ወዘተ ቀድመው ያዘጋጃሉ። ይህን ቅድመ ሁኔታ ከጠናቀቁ በኋላ ወጣቶች ዝም ብለው መቃም ሲጀምሩ ሌሎች ግን ዱኣ በማደረግ መቃም ይጀምራሉ። የመቃም ስነ ስርዓቱ ሲካሄድ ጫቱ አንድ ሰው አጠገብ ይቀመጥና(የጫት አለቃ ይባላል፤ የሚመረጥበት ይህ ነው

የሚባል መስፈርት የለም) እየቆነጠረ ይወረውራል አልያም አንድ ሰው ተነስቶ ከዋናው ጫት እየቆነጠረ በክቡ መሀል እየዞረ ያከፋፍላል፡፡

ጫትን የምቅሙ ምዕመናን ለምን ጫት እንደምቅሙ ሲጠየቁ በብዛት የሚሰጡት መልስ "በጫት ተቀምጠው በሰከነ ሁኔታ አላህን መለመን ልመናው ስኬታማ ይሆናል ወይም ተቀባይነት አለው" የሚል ነው፡፡ በአልከሶ መውሊድ ግን ያለው ነባራዊ ሁኔታ ጫት ቃሚ መረጃ አቀባዮቹ ከሚሉት እውነታ የራቀ ነው፡፡ በተለያየ ጊዜ መስክ ሄጄ እንደተመለከትኩት ጫት መቃም ከመጀመሩ በፊት አልፎ አልፎ ዱኣ ከማድረግ ባለፈ ጫትን በሰከነ ሁኔታ እየቀሙ አላህን የመለመን ስርዓት ሲካሄድ አልተመለከትኩም፡፡ ከዚህ በተቃራኒው በቴፕሪከርደ ሙዚቃ የሚመስል በዘመናዊ መሰሪያ የታጀበ መንዙማ ማዳመጥ እና በዲቤ የታገዘ መንዙማ ማለት በብዛት የሚታይ ጉዳይ ነው፡፡

ምንም እንኳን ጫትን የምቅሙ ሰዎች ጥቅሙ አላህን ለመለመን ነው ብሉም ጫት ስቅሙና ከቃሙ በኋላ ያለነው ነባራዊ ሁኔታ እነርሱ ከሚናገሩት በተቃራኒው በተለይ ወጣት ወንዶች ጫት ከቃሙና ከተናቃቁ(ከመረቀኑ) በኋላ ቀን እና ማታ ሳይል ወጣት ሴቶች በግልጽ ይተኗኮላሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመቃሚያ ገንዘብ ሲያጡ እዛው በጊዜያዊነት በተቋቋሙ የንግድ ቦታዎች የራሳቸውን ቁሳቁስ ይሸጣሉ፡፡ አልፎ አልፎ ደግሞ የሰው ቁሳቁስ ሰርቀው የሚሸጡ እና የሚያዙም አሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው ጫትን በመቃም ከሚገኘው ጠቀሜታ አንጻር ጉዳቱ ያመዝናል፡፡ ምክንያም ጫት መቃም ለኢኮኖሚ እና ለጤና ጠንቅ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ ሁኔታ ትልቅ ትንሽ ወንድ ሴት ሳይል ሜዳ ላይ እንደልብ መቃሙ ከስር ያለው ትውልድ እንደ ባህል ስለሚቀበለው ጫትን መቅም ጥቅም እንጂ ጉዳት እንዳለው  እንዳያስብ እያደረገው ነው፡፡

ባጠቃላይ በአልከሶ መውሊድ ከበራ ሰሞን ጫት በመቃም ውስጥ በርካታ ፎክሎራዊ ክንውኖች ሲከናወኑ እንመለከታለን፡፡ በመጀመሪያ እነዚህ ቃሚዎች ያሰባሰባቸው ጫት ስለሆነ የጫት ፎክ ልንላቸው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም ያሰባሰባቸው ጫቱ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የሰዎቹ አቀማመጥ፣ አለባበስ፣ አጨዋወት፣ አጨፋፈር፣ አቀላለድ፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት አቃቃም ወዘተ በሙሉ ፎክሎር ነው፡፡ በመሆኑም አራቱ የፎክሎር ዘርፎች በዚህ የጫት መቃም አውድ ውስጥ ይገለጣል፡፡ ምክንያቱም ጫት ሲቃም መንዙማ ሲባል ዱኣ ይዳረጋል ግጥሞችን እና የዱኣ ንግግሮችን ከስነቃል አንጻር መመልከት ይቻላል፡፡ መንዙማ ሲባል የሚደረጉ ውዝዋዜዎችን ከሀገረሰባዊ ትወን ጥበባት አንጻር ልንቃኘው

እንችላለን፡፡ መንዙማ በሚባልበት እና ጫት በሚቃምበት ወቅት የተለያዩ የአለባበስ እና ያጋጌጥ ስርዓት ስላለ ከቁሳዊ ባህል አንጻር ሊዳሰስ ይችላል፡፡ እንደሁም በጫት ቅመያ ወቅት የተለያዩ ልማዳዊ (ምልጃን ጨምሮ) ስለሚካሄድ የተለያዩ ሀገረሰባዊ ልማዶችን ልንመለከት እንችላለን፡፡ ስለዚህ በጫት መቃም ስነስርዓት ውስጥ አራቱም የፎክሎር ዡነሮች ይገኛሉ ማለት ይቻላል፡፡



ፎቶ 11፡- መውሊድ አክባሪዎች ሜዳ ላይ ጫት ስቅሙ[122]

## 6.3. የወጣቶች የመውሊድ አከባበር እና ፎክሎራዊ ክንውን

ክብረ በዓላት ሲከበሩ መዝናናት፣ መጨፈር፣ ከዘወትራዊው ስራ ተገሎ መዋልን የሚያካትቱ ቢሆንም ከዚህ የተለየ ሥነ ልቦናዊ ጠቀሜታ አላቸው፡፡ የክብረ በዓል አቢይ ጉዳይ ተደርጎ የሚወሰደው ሰዎች ባንድነት ሆነው እንዲጫዎቱና እንዲቦርቁ ማድረጉ እንደሆነ ፈቃደ (2003፣14) ያስረዳሉ፡፡ በአልከሶ መውሊድ ከሚሳተፉ የማህበረሰብ ክፍሎች መካከል ሴት እና ወንድ ወጣቶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ወጣቶች ይህን በዓል እንደ አንድ ሃይማኖታዊ ክብረ በዓል ከመመልከት በተጨማሪ የመዝናኛ፣ የመተዋወቂያ እና ለጋብቻ መተጫጫ መድረክነት ይጠቀሙበታል፡፡ ከዚህ አንጻር ስንመለከተው የፈቃደ (2003፣14) አባባል

[122] ፎቶ ባጥኚው 16/09/07 አልከሶ

በአልከሶ መውሊድም ይንጸባረቃል፡፡ ምክንያቱም ወጣቶች በዚህ ክበረ በዓል ይዝናናሉ፣ ይጫወታሉ፡፡ ወጣት ፈተረሁፍ[123] እንደነገረኝ ከሆነ የአልከሶ መውሊድ አክባሪ ወጣቶች ለመውሊድ አስራ አምስት ቀን ያህል ሲቀረው ወደ መውሊድ ቦታ እንደሚሄዱ ለቤተሰቦቻቸው ያሳውቃሉ፡፡ ወጣቶች ወደ አልከሶ መውሊድ የሚሄዱት በተናጠል ሳይሆን በቡድን ነው፡፡ የቡድኑ አባላት ወንድ እና ሴት ናቸው፡፡ በመሆኑም በመውሊድ ቆይታ ጊዜያቸውን ሲያሳልፉ ለሚያስፈልጋቸው ወጪ ገንዘብ ያዋጣሉ፡፡ ሴቶች ፀጉራቸውን ይሰራሉ፣ ወንዶች ደግሞ ጸጉራቸውን ይስተካከላሉ፡፡ እንዲሁም ወደ መውሊዱ ቦታ ሲሄዱ የሚለብሱትን ልብስ ያጥባሉ፡፡ ጥቂት የማይባሉት ደግሞ አዲስ ልብስ ይገዛሉ፡፡ በ2008 ዓ.ም ጥር 24 በተካሄደው ውይይት እነዚህ ወጣቶች ገንዘብ ካዋጡ በኋላ መንዙማዎችን የሚያዳምጡበት ቴፕ እና ባትሪ ድንጋይ እንደሚገዙ ወጣት አብድልባቅ አስረድቷል፡፡ እንደ አብድልባቅ አገላለጽ ከዚህ በተጨማሪ ቡና፣ ጫት፣ ስኳር፣ ሰንደል ወዘተ ይገዛሉ፡፡ እነዚህን ቅድመ ዝግጅቶችን ካጠናቀቁ በኋላ በቡድን በቡድን በመሆን ጫት እየቃሙ መንዙማ እያሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ዘመናዊ እና ባህላዊ ስልጥኛ እና አማርኛ ዘፈን እየዘፈኑ ወደ አልከሶ መውሊድ መከበሪያ ቦታ ያመራሉ፡፡

ግንቦት 24/2008 በተካሄደው ውይይት እነዚህ ወጣቶች ገንዘብ ካዋጡ በኋላ መንዙማዎችን የሚያዳምጡበት ቴፕ እና ባትሪ ድንጋይ እንደሚገዙ ወጣት አብድልባቅ አስረድቷል፡፡ እንደ አብድልባቅ አገላለጽ ከዚህ በተጨማሪ ቡና፣ ጫት፣ ስኳር፣ ሰንደል ወዘተ ይገዛሉ፡፡ እነዚህን ቅድመ ዝግጅቶችን ካጠናነቀቁ በኋላ በቡድን በቡድን በመሆን ጫት እየቃሙ መንዙማ እያሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ዘመናዊ እና ባህልዊ ስልጥኛ እና አማርኛ ዘፈን እየዘፈኑ ወደ አልከሶ መውሊድ መከበሪያ ቦታ ያመራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በትክክል መኖሩን እኔም በመስክ ቆይታዬ ጊዜ አረጋግጫለሁ፡፡

ወጣቶች አልከሶ ሀረም ላይ መክተም የሚጀምሩት በብዛት ቅዳሜ ጠዋት ጀምሮ ነው፡፡ እነዚህ ወጣቶች በየኸለዋው ከመግባት ይልቅ የሚመርጡት በሜዳ ላይ ዳስ በመስራት አልያም ያለ ዳስ ሜዳ ላይ ማሳለፍ ነው፡፡ ይህ ለምን እንደሆነ በሜዳ ላይ ተሰብስበው ጫት እየቃሙ እና መንዙማ ከሚሉ ወጣቶች መካከል አንዱ የሆነውን ወጣት ኑረዲንን[124] ስጠይቀው "---ያው ኸለዋ ውስጥ ሽማግሌዎች ይበዛሉ፡፡ እንደልባችን ለመጫወት

[123] ቃለ መጠይቅ 24/10/07
[124] ቃለ መጠይቅ 23/09/08

አይመቸንም፡፡ ደግሞም ኸለዋ ውስጥ ሴት እና ወንድ አንድ ላይ ሆኖ ጫት መቃም እና መጫወት ሽማግሌዎች ስለማይወዱ ነው ውጭ ላይ የምናሳልፈው” የሚል ምላሽ ሰጥቶኛል፡፡ ወጣት ኑረዲን እንዳለውም ተዘዋውሬ የተመለከትኳቸው ኸለዋዎች ውስጥ ብዙም ወጣቶች አይገኙባቸውም፡፡ ይህ ሲባል ግን ኸለዋ ውስጥ መውሊዱን የሚያከብሩ ወጣቶች የሉም ማለት አይደለም፡፡ እነዚህ ወጣቶች ኸለዋ ውስጥ የማያሳልፉት ኸለዋ ውስጥ ሴት እና ወንድ ስለማይደባለቅ እና በሽማግሌዎች አጠገብ እንደፈለጉ መጫወት ስለማይችሉ ነው፡፡ ከኸለዋ ውጭግን ወንድ እና ሴት አንድ ላይ በመሆን ያሳልፋሉ፡፡ ከዚህ ሁኔታ የምንረዳው የተወሰኑ ወጣቶች ወደ መውሊዱ የሚሄዱት መውሊድ ለማክበር ብቻ ሳይሆን ለመዝናናት እና ከተቃራኒ ጾታ ጋር ለማሳለፍ ነው፡፡

እነዚህ ወጣቶች ሀረሙ ውስጥ ከተገናኙ በኋላ ሁለት ሁለት ወይም ሶስት ሶስት በመሆን በሀረሙ ዙሪያ እየዞሩ ወይም አረንጓዴ እና ነፋሻማ ቦታ መርጠው በመቀመጥ አመቱን እንዴት እንዳሳለፉ ይጨዋወታሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጥምረቱ ወንድ ከወንድ፣ ሴት ከወንድ አልያም ሴት ከሴት ጋር ሊሆን  ይችላል፡፡ በዚህ ሁኔታ እስከ ዙሀር ሷላት ድረስ ይቆዩና የሷላት ሰአት ሲደርስ ዉዱእ በማድረግ ወደ መስገጃ ቦታ ይሄዳሉ፡፡ ከዙሀር ሷላት በኋላ የተወሰኑ ቡድኖች ቤታቸው አዘጋጅተው ያመጡትን ምግብ ሲመገቡ የተወሰኑ ቡድኖች ደግሞ እዚያው በጊዜያዊነት ወደ ተዘጋጁ ሆቴሎች በመሄድ ምሳቸውን ይበላሉ፡፡ ምሳቸውን ከበሉ በኋላ በሀረሙ ውስጥ በተለያየ ቦታ ላይ ጫት መቃም እና ድቤ እየመቱ መንዙማ እያሉ ይጫወታሉ፡፡ በዚህ ጊዜ የወጣቶቹ ቁጥር እየጨመረ ይሄዳል፡፡ የወጣቶቹ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ በአካባቢው ያለው ድባብ ይደምቃል፡፡ እነዚህ ወጣቶች ከመንዙማ(በድቤ የታገዘ) ይልቅ የሚያዘወትሩት መንዙማ (በዘመናዊ መሳሪያ የተቀነባበረ) ነው፡፡ ከተማ ላይ በስፋት የሚደመጡ መንዙማ ዎች የአልከሶ መውሊድ አክባሪዎች ሲያዳምጡት እና አመቱን ሙሉ እሱን ብቻ ሲለማመዱ የከረሙ በሚመስል መልኩ ከቴፕ ሪከርደሩ ጋር እኩል ሲሉ ወይም ሲጫወቱ ተመልክቻለሁ፡፡

ሌላው በዚህ ቦታ የተመለከትኩት ከወጣቶች መካከል አንዱ በመነሳት እዝያ ቦታ ላይ የተሰበሰበውን ሰው በቀልድ እያዋዛ “በሉ ዋቡ አላህ ዮበማን” (በሉ ስጡ ከሰጣችሁ አላህ ይሰጣችኋል) በማለት መመረቅ ይጀምራል፡፡ በዚህ ጊዜ በቦታው የተሰበሰበው ሰውም ጫት እና የተለየዩ ነገሮችን መግዣ የሚሆን ገንዘብ ያዋጣል፡፡ ይህ የመመረቅ እና ገንዘብ የማዋጣቱ ሁኔታ የሚካሄደው በጨዋታ መሀል መሀል ሲሆን ዋና ትኩረታቸው ጫት

መቃም (ጫት በመቃሙ ሂደት ሴቶች ከወንዶች እኩል ይሳተፋሉ) እና መንዙማ ወይም መንዙማ  እያሉ መዝናናት ነው፡፡ በዚህ መድረክ በዚህ ሁኔታ የተዋጣው ገንዘብ ጫት፣ ስኳር፣ ሰንደል፣ ለስላሳ መጠጦች፣ ወዘተ ይገዛበታል፡፡





ፎቶ 12፡- ወጣቶች ሜዳ ላይ መውሊዱን ሲያከብሩ[125]

እነዚህ በቡድን በቡድን ሆነው ሜዳ ላይ ዳስ ጥለው በዓሉን ቀን ከሌሊት ሳይሉ የሚያሳልፉት ወጣቶች ሙሉ ጊዜያቸውን የሚያሳልፉት ጫት በመቃም እና መንዙማ በማለት ነው፡፡ የተወሰኑ ቡድኖች ደግሞ በዘመናዊ መሳሪያዎች የተቀነባበረ መንዙማ በማድመጥ የሚዝናኑ እንዳሉ መውሊድ ከመከበሩ በፊት በነበረ የቡድን ውይይት ተነስቷል፤ እኔም በምልከታዬ አረጋግጫለሁ፡፡ በውይይቱ ወቅት ወጣት ፈተረሁፍ እንደገለጸው በዚህ መውሊድ የሚሰባሰቡ ወጣቶች ሁለት አላማ ያላቸው ናቸው፡፡ አንደኛው መውሊዱን በማክበሬ በሃይማኖታዊ ህይወቴ አንዳች ምንዳ አገኛለሁ በማለት ሲሆን ሁለተኛው አላማው መዝናናት ነው፡፡ ለመዝናናት ወደ አልከሶ መውሊድ የሚሄዱት በብዛት የከተማ ልጆች ናቸው፡፡ ለምሳሌ በ2008 ዓ.ም ወደ መስክ በሄድኩበት ወቅት ቅዳሜ እለት አልከሶ ከተማ ላይ ሲጋራ ሲያጨሱ እና ጫት ሲቅሙ ያየኋቸው ወጣቶች በነጋታው እሁድ እለት ሙስሊሞች በብዛት ወደ መስጂድ ሲሄዱ የሚለብሱት አለባበስ ለብሰው መውሊዱ ላይ

[125] ፎቶ ባጥኚው፣ 24/05/08 አልከሶ ሀረም

ተግኝተው ከመውሊድ አክባሪዎች እኩል በመውሊዱ ሲሳተፉ ተመልክቻለሁ፡፡ እነዚህ ወጣቶች ከተሰበሰበው ህዝብ መሀል ዞር በማለት ዛፍ ስር ቁጭ ብለው ሲጋራ ሲያጨሱም አጋጥመውኛል፡፡ የእነዚህ ወጣቶች አላማ ወጣት ፈተረሁፍ ካስቀመጣቸው ሁለት አላማዎች ውጭነው፡፡ ምክንያቱም ወጣቶቹ መውሊድ ከማክበር እና ከመዝናናት ባለፈ ተቃራኒ ጾታ ፍለጋ እንደመጡ በቦታ የሚፈጽሙት ድርጊት ይናገራል፣ያሳያል፡፡

በዚህ ቀን ሌሊቱን በዋናነት የሚያደምቀው የወጣቶቹ በመንዙማ እና በመንዙማ ታግዞ የሚቀርበው የጨዋታ ሁኔታ ነው፡፡ በዚህ ሰአት ትኩረታቸው መውሊዱ ወይም መዝናናቱ ላይ ሳይሆን በተቃራኒ ጾታ ላይ የሚያደርጉ በርካታ ወጣቶች አሉ፡፡ በዚህ ቀን ምሽቱ ላይ ከሚዝናኑ ወጣቶች መካከል አለባበሱ ዘመነኛ የሚመስል እና ጸጉሩን በዘመናዊ ሁኔታ የተቆረጠ አንድ ወጣት ላይ አይኔ አረፈ፡፡ ይህ ወጣት አንድ ቦታ ላይ ሆኖ መውሊዱን ከማክበር አልያም ከመዝናነት ይልቅ ከአንድ ቡድን ወደ ሌላ ቡድን ዝም ብሎ ይመላለሳል፡፡ የዚህ ወጣት አላማ ምን እንደሆነ ለማወቅ እከታተለው ጀመር፡፡ ለረጅም ደቂቃዎች በዚህ ሁኔታ ካሳለፈ በኋላ አንድ ቡድን ላይ በርከት ያሉ ሴት ወጣቶች በሚበዙበት ቡድን ጋር ተቀላቅሎ መንዙማ ማለት ጀመረ፡፡ መንዙማ እያለ እያለ ከጎኑ ከቆመች አንዲት ወጣት ልጅ ጋር መነጋገር ጀመሩ፡፡ ለተወሰኑ ደቂቃዎች በዚህ ሁኔታ ካሳለፉ በኋላ ከወጣቶቹ ራቅ ብለው ከፍታማ ቦታ ተቀምጠው ማውራት ጀመሩ፡፡ ወሬው ቀስ በቀስ ወደ ልፊያ ተሻጋረ፡፡ ሲላፉ የተመለከቷቸው ልጆች ስለሳቁባቸው መልሰው ከቡድኑ ጋር ተቀላቀሉ፡፡ አሁንም ለትንሽ ጊዜ ከቡድኑ ጋር ተቀላቅለው ካሳለፉ በኋላ ከተለያየ አቅጣጫ በመውጣት አንድ ጨለማ ቦታ ተገናኝተው ወደ አልከሶ ከተማ የሚወስደውን የመኪና መንገድ ይዘው ወደ ከተማ ሄዱ፡፡ የእነዚህን ሁለት ወጣቶችን ሁኔታ አነሳሁ እንጂ የዚህ አይነት ድርጊት የሚፈጽሙ በርካታ ወጣቶችን በመውሊድ ሰሞን ሌሊት ላይ ማግኘት ይቻላል፡፡ ከላይ እንደገለጽኩት በአልከሶ ሀረም የመውሊድ ሰሞን የመጸዳጃ ቦታ በተለይ የሴቶች እጥረት አለ፡፡ ይህ በመሆኑ ወጣት ሴቶች ለመጸዳዳት ወደ ጨለማ ቦታ እና ጫካ ሲሄዱ ወንዶች ሲተናኮሏቸው ተመልክቻለሁ፡፡

ይህ ሁኔታ መውሊድ የሚከበርበት ዓላማው እንዲስት ያደረገው ይመስላል፡፡ መውሊድ መከበር አለበት የሚሉ መረጃ አቀባዮች የዚህ አይነት ድርጊት አይፈጸምም የሚሉ እንዳሉ ሁሉ ድርጊቱ በተወሰነ ደረጃ አለ እሱንም የማጥፋት ስራ እየተሰራ ነው ይላሉ፡፡ ባጠቃላይ ግን ማታ ማታ ወጣቶቹ መውሊድን ለማክበር በሚል የሚሰባሰቡበት ቦታ እስላማዊ ክብረ

በዓል የሚከበርበት ቦታ አይመስልም። መውሊድ አክባሪዎች ይህ ሁኔታ የለም ቢሉም እኔ በ2007 እና 2008 ዓ.ም መውሊድ ሌሊቶች ላይ ወጣቶች ያለ ማንም ከልካይ ወይም ተቆጣጣሪ እንደፈለጉ ሲሆኑ መመልከት ችያለሁ።

ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ሳሰባስብ ካነጋገርኳቸው ወጣቶች መካከል አብድልባቅ (በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ተሳትፏል) አንዱ ነው። አብዱልባቅ በልጅነቱ መውሊድን ያከብር ነበር። አሁን ግን ወጣት ሲሆን "መውሊድን ማክበር ቢደዐህ ነው" በማለት ማክበር ትቷል። በወቅቱ መውሊድን ሲያከብር በወጣቶች መካከል የነበረውን ግንኙነት አልከሶ ከተማ ባነጋገርኩት ጊዜ የሚከተለውን ሀሳብ ሰንዝሯል።

> ድሮ ልጅ እያለሁ ቁርአን እና ኪታብ ባልቀራሁኝ ጊዜ የአልከሶ መውሊድን አከብር ነበር። አሁን ግን ቁርአኑን እና ኪታቡን በሚገባ ካወኩት በኋላ መውሊድን ማክበር ትቻላሁ። መውሊድን ማክበር በቁርአንም ሆነ በሀዲስ ቦታ የለውም። መውሊድ ፈጠራ ነው። አሁን የአልከሶን መውሊድ በከፍተኛ ሁኔታ ዝና(ዝሙት) ማስፋፊያ አጋጣሚ ሆኗል። እነዚህ ወጣቶች ሁለት እና ሶስት ቀን ያህል እንዳሻቸው ይሆኑበታል። ይህ ደግሞ በሙስሊም እጅግ አስነዋሪ ተግባር ነው። በርግጥ አልከስዬ ታላቅ አሊም ነበሩ። የእሳቸው መልካም ስራ በአሁኑ ትውልድ እየተበላሸ ነው። ከቡታጅራ፣ ከዳሎቻ፣ ከወራቤ ከሌሎቹም ቦታዎች በዝያን ቀን ሴት ፍለጋ ወንዶች ይመጣሉ። መተውም የፈለጉትን አሳክተው ይመለሳሉ። ይህ ድርጊት የሚፈጸምበት መውሊድን ነው ማክበር ይበቃል የሚሉት አብድልባቅ[126]።

ይህ ሲባል ግን ሁሉም ወጣቶች በአልከሶ መውሊድ የሚገኙት ሀራም የሆነ ድርጊት ለመፈጸም ይሄዳሉ ማለት አይደለም። በንጹህ ልቦናቸው መውሊድን ለማክበር የሚሄዱም አሉ። የዚህ አይነት ወጣቶች የምናገኛቸው ሜዳ ላይ ወይም ዳስ ውስጥ ሳይሆን በየኸለዋዎች ወይም ሸምሰል ጀማል ውስጥ ነው። ሸምሰል ጀማል ውስጥ ከአዛውንቶች ጋር መውሊድ ሲያከብር ያገኘሁትን ወጣት ፈረጀን የአንተ አቻዎች መውሊድን የሚያከብሩት ዳስ ውስጥ ወይም ሜዳ ላይ ነው አንተ ለምን ከእነሱ ጋር አልተቀላቀልክም? የሚል ጥያቄ

[126] ቃለ መጠይቅ 23/05/08

ሳቀርብለት ፈረጂ[127] "ሜዳ ላይ ያለው የወጣቶች መውሊድ አከባበር ደስ አይለኝም። ወጣቶቹ ጥሩ ስራ አይሰሩም። አላህን አይፈሩም። ከሀጅነብይ(ዝምድን ከሌለው ሰው ለማለት ነው) ጋር እንዲህ ለመሆን አላህ አልፈቀደም። እኔ ወደዛ መሄድ አልፈልግም። እዚሁ ነው መውሊዱን አክብሬ ወደ ቤቴ መሄድ የምፈልገው" ብሎኛል። ልክ እንደዚሁ ወጣት ሁሉ ጥቂት የማይባሉ ወጣቶች በየኸለዋው እና ሸምሰል ጀማል ውስጥ በትላልቅ ሰዎች መካከል በመሆን መውሊዱን ያከብራሉ። የእነዚህ ወጣቶች አላማ መውሊዱን ማክበር እንደሆነ ከሁኔታቸው እና ከሚያሳልፉበት ቦታ አንጻር መረዳት ይቻላል።

በአልከሶ መውሊድ ጊዜያዊ ደስታ ለማግኘት ብቻ ብለው የማይመጡም ወጣቶች አሉ። ሩቅ አስበው ውሃ አጣጫቸውንም ፍለጋ የሚመጡ እንዳሉ እና በመውሊዱ በአጋጣሚ ተገናኝተው ትዳር የመሰረቱ ሰዎች እንዳሉም ይነገራል። አቶ ሁሴይኒ[128] የአልከሶ መውሊድ አንዳንድ ሰዎች እንደሚሉት ወጣቶች የሚገናኙት ለሀራም ስራ ብቻ ነው ቢሉም ለሀላል ስራም የሚገናኙ እና በዚህ መውሊድ በርካታ ወጣቶች ተገናኝተው ተጫጭተው ለቁም ነገር የበቁ አሉ። ለምሳሌ ሱንኪቴ የምትባል ወጣት ከአንድ ወጣት ጋር (የወጣቱን ስም አያስታውሱትም) በአልከሶ ሀረም ተዋውቃ ለትዳር መስርተው ልጆችን አፍተው እንደሚኖሩ ይናገራሉ። አቶ ኑሪ ሼኽ ከድር ከባለቤታቸው ጋር የተገናኙት በአልከሶ መውሊድ ሰሞን እንደሆነ እና በአሁኑ ጊዜ የሶስት ልጆች አባት እና እናት እንደሆኑ ያስረዳሉ።

በዚህ መውሊድ አብላጫ ምዕመናን አለባበሳቸው እስላማዊ ስርዓት የተከተለ ቢሆንም ጥቂት የማይባሉ ወጣቶቹ በተለይ ሴቶች ለብሰው ሀረም ውስጥ የሚገቡት ልብስ እና የአጋጌጣቸው ሁኔታ እስላማዊ ስነ ስርዓት የሚካሄድበት ቦታ ተለብሶ የሚኬድ አለባበስ አይደለም። የእነዚህ ወጣቶች አለባበስ የስልጤ ብሔረሰብ ወጣት ሴቶች የሚለብሱት አለባበስ አያንጸባርቅም። ምክንያቱም እነዚህ ወጣቶች በብዛት የሚለብሱት ጉርድ ቀሚሶችን ሲሆን ከላይ የሚደርቡት ልብስ ደግሞ ሰውነታቸውን የሚያሳይ ነው። ይህ አለባበሳቸው በወጣት ወንዶች ዘንድ ትንኮሳ እንዲደርስባቸው በር ሲከፍት ተመልክቻለሁ። ከዚህ በተቃራኒው ደግሞ የብሔረሰቡ ወጣቶች የሚለብሱትን ባህላዊ አለባበስ እና እስላማዊ የአለባበስ ስርዓት ተከትለው ልብሳቸውን ለብሰው የመጡ ጥቂት ወጣቶች አልፎ አልፎ አጋጥመውኛል። ስለዚህ ከነዚህ ጥቂት ወጣቶች አንጻር እና አባቶች እና እናቶች አለባበስ አንጻር የአልከሶ

[127] ቃለ መጠይቅ 17/09/08

[128] ቃለ መጠይቅ 23/05/08

መውሊድ መከበሩ የስልጤ ብሔረሰብ ባህሉን የማንጸባረቂያ አጋጣሚ ወይም መድረክ በመሆን አገልግሏል ማለት ይቻላል፡፡



ፎቶ 13፡- የወጣቶች እና የልጆች አለባበስ በከፊል[129]

ባጠቃላይ በአልከሶ መውሊድ ወጣቶች የመውሊዱ ዋና ተሳታፊ እና አድማቂዎች ናቸው፡፡ ምክንያቱም በየኸለዋዎቹ፣ ዳሶቹ፣ አዳራሾቹ፣ መኖሪያ ቤቶች ወዘተ ብንዘዋወር የሚጨፍሩት፣ ድቤ የሚመቱ እና መንዙማ የሚያወጡት በብዛት ወጣቶች ናቸው፡፡ በከፍተኛ ሁኔታ ጫት የሚቅሙትም ወጣቶች ናቸው፡፡ በመውሊዱ ከጸጥታ አስከባሪ ጀምሮ እስከ ምግብ ማብሰል እና ማድረስ ያለው ስራ ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም ለዚያራ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች፣ በጎች፣ ፍየሎች፣ ወይፈኖች ወዘተ ወደ ዚያራ ቦታ የሚያቀርቡት ወጣቶች ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን በበዓሉ ልጆች፣ ጎልማሳዎች እና አዛውንቶች ምንም ሚና የላቸውም ማለት አይደለም፡፡ ሁሉም አቅማቸው በፈቀደው ያህል ይሳተፋሉ፡፡ ከጾታ አንጻር ሁለቱም ጾታዎች የየራሳቸው ሚና አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ምግብ የማብሰሉን ሚና በዋናነት የሚጫወቱት ሴቶች ሲሆኑ በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኙ ምዕመናን ምግብ የማድረሱን ስራ የሚሰሩት ደግሞ ወንዶች ናቸው፡፡ የወንዶች ሚና ምግብ ማድረስ ብቻ ሳይሆን ምግብም ያዘጋጃሉ፡፡ ለምሳሌ በ2007 እና በ2008 ዓ.ም የዋናው መውሊድ ከበራ ሰሞን ወንዶች በሬ እና በግ አርደው በቀይ እና በአልጫ ወጥ መልክ አዘጋጅተው ሲያቀርቡ

[129] ፎቶ በአጥኚው፣ 23/09/07 ዓ.ም

ተመልክቻለሁ። አልከሶ ሀረም ውስጥ ወንዶች ሳይሳተፉበት ሲዘጋጅ ያየሁት ምግብ እንጀራ ብቻ ነው። ስለዚህ መውሊዱን በማክበር እና ስራ በመስራት ሴቶች እና ወንዶች እኩል አስተዋጽኦ አላቸው ማለት ይቻላል።

## 6.4 የድሬ ሼኽና ሁሴን ወዳጆች በአልከሶ መውሊድ

በአልከሶ መውሊድ ከገጠር እስከ ከተማ ከልጅ እስከ አዋቂ ያሉ ሰዎች በሙሉ እንደሚሳተፉ ቀደም ብለን ተመልክተናል። ከነዚህ ከሚሰባሰቡ ሰዎች መካከል በተለምዶ የድሬ ሼኽና ሁሴን ወዳጆች የሚባሉ ሰዎች ይገኙበታል። እነዚህ ሰዎች ከሌላው መውሊድ አክባሪዎች አንዳንድ ሰዎች ገሪብ ይሏቸዋል። በድሬ ሼኽና ሁሴን መውሊድ አከባበር እና በከበራው ስለሚገኙ ምዕመናን በርካታ ምሁራን ጥናቶችን አካሂደዋል። ከእነዚህ መካከል Ostebo(2012) ይገኙበታል። በመሆኑም እኚ አጥኚ ገሪብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ የሚከተለውን ይላሉ። “The word geriba which in Arabic means “something peculiar” or “something strange”, is the term used for individual. They are easily recognised by their dhanqe, symbolising their devotion to the shrine.” (Ostebo 2012፣94)። ገሪባ የሚለው ቃል አረብኛ ሲሆን ትርጉሙም አዲስ ክስተት ወይም ለየት ያለ ነገር ማለት ነው። ቃሉ በአሁኑ ዘመን አገልግሎት እየሰጠ ያለው ለድሬ ሼኽና ሁሴን አፍቃሪ ለሆኑ እና ረጅም መንገድ ለጉብኝት (ለዚያራ) የሚጓዙ ግለሰቦች ለመግለጽ ነው። ገሪቦችን በሚይዙት ደንቄ በቀላሉ ልንለያቸው እንችላለን።

ከእኚ እና መሰል አጥኚዎች ሀሳብ በተጨማሪ ገሪቦች ደግሞ ራሳቸውን በተለያዩ ሁኔታዎች ይገልጻሉ። ለምሳሌ ገሪብ መሀመድ ስለ ገሪብ ምንነት የሚከተለውን ይላሉ።

> ገሪብ ማለት እንደማንኛውም ሰው ሰው ነው። ብዙ ሰው የተለየን ፍጡር አድርጎ ያየናል። አንድ ሰው ገሪብ ለመባል የሚያሟላቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ። ዋና ባሌ ድሬ ሼኽና ሁሴን ተገብቶ ደንቄ ወይም አላማ ገዝቶ ማስመረቅ አለበት። አንድ ሰው እዛ መሄድ ካልተመቸው ወይም ካልቻለ የሄደ ሰው ገዝቶ ሊያስመርቅለት ይችላል። ገሪብ ደግሞ ሁለት አይነት ነው ያለው አንዱ እንደኛ ቤት ንብረት የእርሻ መሬት ትዳር የሌለው ነው። ሁለተኛው ቤት ንብረት፣ ትዳር ያለው ነው። እሱ ሙሉ በሙሉ ገሪብ አይደለም። ትክክለኛ ገሪብ እኛ ነን። እኛ በወንድም እርዳታ ነው የምንኖረው። እነሱ ግን መሬት

አላቸው ያርሳሉ ልጅ ሚስት አላቸው እንዴት ገሪብ ይሆናሉ፡፡ እነሱ መባል ያለባቸው ልክ እንደ ሌሎቹ ሰዎች የድሬ ሼኽና ሁሴን ወዳጅ ነው፡፡[130]

እነዚህ ሰዎች(ገሪቦች) በአልከሶ ሀረም ውስጥ መውሊድን የሚያከብሩት ትልቅ ዋርካ ስር ነው፡፡ ገሪቦች የሚቀመጡበት ቦታ ላይ ያለው ዋርካ ወደ ላይ ሲታይ የቅርጫፎቹ አቀማመጥ በእጃቸው ከሚይዙት ደንቁ(አላማ)[131] ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ ይህ የሚያሳየው ሁለቱን አንዳች የሚያቀራኛቸው ተምሳሌታዊ የሆነ ነገር ሊኖራቸው እንደሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም የዋርካው ቅርጫፍ ተቆርጦ ቢወርድ እያንዳንዱ ደንቁ(አላማ) መሆን ይችላልና ነው፡፡ እነዚህ ገሪቦች በእጃቸው ደንቁ፣ ቡና መጠጫ ቆርያ፣ ከስር ሹል ብረት የተደረገለት ዱላ፣ ጨሌ ወዘተ ይይዛሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የድሬ ሼኽና ሁሴንን መውሊድ የሚያከብሩ ገሪቦች ደንቁን ጨምሮ የተለያዩ ቁሳቁሶችን እንደሚጠቀሙ Ostebo (2012;178-179) “Cultural objects such as the dhanqe, halange (whip), boku (sceptre), as well as spears and the knives used for ritual slaughtering were commonly used by the guardians at the shrines and by several of the warra fuqra.” በማለት ገልጸውታል፡፡

በአልከሶ ገሪቦች መውሊድ በሚያከብሩበት ወቅት የራሳቸው የሆነ መሪ ወይም አለቃ ገሪብ አላቸው፡፡ በ2007 የአልከሶ መውሊድ ከበራ ሰሞን የአልከሶ መውሊድ አክባሪ ገሪቦች አለቃ ገሪብ ሼኽ ሰኢድ ኢሼቾ እንደሚባል ገሪብ አወል[132] ነግረውኛል፡፡ ገሪቦች ለአለቃቸው ልዩ ፍቅር አላቸው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በወርካዋ ስር የተሰባሰቡ ሰዎች ሲነጋገሩ እርስ በእርስ አይደማመጡም፡፡ ነገር ግን አለቃቸው ተነስተው “ኡስስስ” ሲሉ ሁሉም በአንድ ጊዜ ጸጥ ይላሉ፡፡ እንዲሁም ቆመው የነበሩ ባሉበት ቦታ ይቀመጣሉ፡፡ በ2008 የአልከሶ መውሊድ ላይ ግን በ2007 የነበሩት የገሪቦች አለቃ ቦታቸው አልነበሩም፡፡ በቦታው የነበረው የሰው ብዛት ቀንሷል፡፡ እንዲሁም የአከባበር ስርአቱም ከ2007 ቀዝቅዞ አግኝቼዋለሁ፡፡ ይህ ሁኔታ ለምን እንደሆነ ለገሪብ ሙሀመድ[133] ሳቀርብላቸው “አምና የነበሩት አለቃ ባለፈው

[130] ቃለ መጠይቅ፣ ገሪብ መሀመድ፣14/9/ 2008
[131] ደንቁን Ostebo (2012 :94) Y-fork shaped stick (*dhanqe*) ይሉታል፡፡
[132] ቃለ መጠይቅ 23/09/2007
[133] ቃለ መጠይቅ 14/09/2008

ሞተዋል፡፡ አሁን ቦታውን የያዙት የእሳቸው ምክትል ናቸው” በማለት የቀዘቀዘበትን እና ስርዓት ያጣበትን ምክንያት ተናግረዋል፡፡



ፎቶ 14፡- ገሪቦች የአልከሶን መውሊድ የሚያከብሩበት ዋርካ[134]

እነዚህ ገሪቦች የሚሰባሰቡትም በዋናነት ከስልጤ ዞን፣ ከጉራጌ ዞን፣ ከናዝሬት፣ ከአርሲ፣ ከባሌ፣ ከአላባ፣ ከጅማ፣ ከአዲስ አበባ ወዘተ እንደሆነ ገሪብ ተውፊቂ[135] አስረድተውኛል፡፡ ገሪቦችን ከሌላው ሰው በቀላሉ ልንለያቸው እንችላለን፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ደንቁ(አላማ) እና ቆሪያ(ቡና መጠጫ ቅል) በእጃቸው ይይዛሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሁሉም ገሪቦች ጫት ይቅማሉ፤ አብላጫዎቹ ደግሞ ሲጋራ ያጨሳሉ፡፡ እንዲሁም አልፎ አልፎ ካልሆነ በስተቀር ሁሉም ንጽህናቸውን አይጠብቁም፡፡ ሷላትም የሷላት ወቅት ጠብቀው አይሰግዱም፡፡ ከዋርካው ስር ውጭ በቡድን በቡድን ሴት እና ወንድ በመሆን ጫት ይቅማሉ፤ ጫት ሲቅሙ አጠገባቸው እሳት በማንደድ ቡና ያፈላሉ፤ ቡና ማፍያቸው ጀበና ሳይሆን ማንቆርቆሪያ ነው፡፡ ማንቆርቆሪያውን ለመጣድ የሚጠቀሙት ጉልቻ ሳይሆን ሶስት ድንጋዮችን ነው፡፡ ነገር ግን አልፎ አልፎ በባለ ሁለት እጀታ ጀበና ቡና የሚያፈሉ ገሪቦች አጋጥመውኛል፡፡ ቡና የሚጠጡት በሲኒ ሳይሆን በቅል ሲሆን ይህን ቅል ገሪቦች ቆሪያ ብለው ይጠሩታል፡፡ እነዚህ ገሪቦች ከጥቂቱ በስተቀር አብላጫዎቹ በልመና ስራ ይሰማራሉ፡፡

---

134 ፎቶ በአጥኚው፣ 20/09/07 አልከሶ ሀረም

135 ቃለ መጠይቅ 14/09/08

ገራብ መሀመድ[136] እንደነገሩኝ እነዚህ ሰዎች ሁለት አይነት ናቸው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሙሉ በሙሉ ገራብ የሆኑ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ ለገራብነት ፍቅር ያላቸው የድሬ የሼኽ ሁሴን ወዳጆች ናቸው፡፡ በዚህ ሀሳብ በተመሳሳይ ሁኔታ ገራብ ቶፊቅም ተጋርተውታል፡፡

ገራብ መሀመድ[137] "ሀብት ንብረት፣ ትዳር ያላቸው ሰዎች ገራብ አይባሉም" ይላሉ፡፡ ነገር ግን ባልና ሚስት ሆነው ልጆች ያላቸው ሰዎች ራሳቸውን ገራብ ብለው እንደሚጠሩ አረጋግጫለሁ፡፡ እነዚህ ሰዎች በአለባበሳቸው፣ በመውሊድ አከባበራቸው፣ በአጠቃላይ ሁኔታቸውም ሙሉ በሙሉ ገራብ ከሆኑ ሰዎች ጋር ይመሳሰላሉ፡፡ እነዚህ ባለትዳር ገራቦች ወደ አልከሶ መውሊድ ሲሄዱ ቤት ውስጥ ያሉ ልጆቻቸውን በሙሉ ይዘው እንደሆነ ከገራቦች ጋር ቁጭ ብለው ጫት ሲቅሙ ያገኘኋቸው አቶ ስራጅ[138] አጫውተውኛል፡፡

እነዚህ ሰዎች ራሳቸውን አንድም ይሁኑ ብዙ "እኛ" ብለው ይጠራሉ፡፡ ለገራብ ቶፊቅ[139] ለምን አንድ ሆናችሁ ራሳችሁን እኛ ትላላችሁ ስላቸው "እኛ አንድ ብንሆንም አንድ አይደለንም፡፡ በውስጣችን ብዙ የተሀደረብን (የሰፈረብን ለማለት ነው) ነገር አለ፡፡ ከእሱ ጭምር ነው እኛ የምንለው" የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡[140] ገራቦች ልክ እንደ እነርሱ ገራብ ሆኖ ታዋቂ ከሆነ ገና ከሩቅ ሲያዩት ቆመው በጩኸት፣ በእልልታ እና በጭብጨባ አካባቢውን በማድመቅ ይቀበሉታል፡ አብላጫ ገራቦች ቀሚስ ስለሚለብሱ እና ጭንቅላታቸው ላይ ሻሽ ስለሚያስሩ ጾታቸውን በቀላሉ መለየት አይቻልም፡፡

በ24/09/2007 እና በ16/09/2008 ዓ.ም የአልከሶ መውሊድ ሲከበር እንዳየሁት እነዚህ ገራቦች ትልቁ ዋርካ ስር መውሊዱን የሚያከብሩት ብቻቸውን አይደለም፡፡ በርካታ ገራብ ያልሆኑ ሰዎች መውሊድ አክባሪዎች (ምናልባት የገራብ ወይም የድሬ ሼኽና ሁሴን ወዳጅ የሆኑ ሰዎች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡[141]) በዋርካው ስር በመገኘት በገራቦች አጠገብ መውሊዱን

---

[136] ገራብ መሀመድ የሕይወት ታሪካቸውን ሲነግሩኝ በአሁኑ ጊዜ የሚኖሩት ናዝሬት ከተማ ላይ አንድ ግለሰብ አንድ ትንሽዬ መኖሪያ ቤት ሰጥቷቸው ነው፡፡ እኚህ ገራብ በሀገራችን በሚከበሩ መውሊዶች ላይ በአብላጫዎቹ እንደሚገኙ ይናገራሉ፡፡ ከሄዱባቸው መውሊዶች መካከል የድሬ ሼኽና ሁሴን፣ የአብሬት፣ በአለባ የኑረላህ አህመድ፣ የቃጥባሬ፣ የዳና፣ ወዘተ መውሊዶች ተጠቃሾች ናቸው፡፡

[137] ቃለ መጠይቅ 16/09/08

[138] ቃለ መጠይቅ 26/10/07

[139] ይህ ግለሰብ በዳሎቻ ወረዳ አስተዳደር ግለሰቡ ገራብ እንደሆነ እና አንድ ወጥ የሆነ መኖሪያ ስፍራ እንደሌላው የሚገልጽ መታወቂያ አሰርቶ መታወቂያውን በአንገቱ አድርጎት ይንቀሳቀሳል፡፡

[140] ሴት ገራብ ለማነጋገር ያደረኩት ጥረት "ወንዶችን ጠይቅ እኛ ምንም አናውቅም እነሱ ያሉንን ነው የምንሰማው" በሚል ምክንያት አልተሳካልኝም፡፡ ወንድ ገራቦች ሚስቶቻቸ ከሌላ ወንድ ቁጭ ብለው ሲነጋገሩ ይቅርና ሌላ ገራብ ሰላም ሲላቸው ደስ እንደማይላቸው በቦታው ካለው ሁኔታ አንጻር ተረድቻለሁ፡፡

[141] ገራቦች እነዚህ ሰዎች የድሬ ሼክና ሁሴን ወዳጆች ስለሆኑ ቀስ በቀስ ገራብ የሚሆን እድል አላቸው ይላሉ፡፡

ያከብራሉ፡፡ እንዲሁም ገሪብ ያልሆኑ ሰዎች ጫት፣ ሰንደል፣ ስኳር፣ ገንዘብ፣ ምግብ ወዘተ ለገሪቦች አለቃ በመስጠት ዱኣ ያስደርጋሉ፡፡ በገሪቦች አጠገብ መውሊዱን የሚያከብሩ ሰዎች የየራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው፡፡ ለምሳሌ በ17/09/2007 አንድ ስሙን ሊነግረኛ ፈቃደኛ ያልሆነ ወጣት የአልከሶን መውሊድ ለማክበር ከጅማ መምጣቱን ነግሮኝ የመጣበትም ምክንያት "ስራ በተለያየ ጊዜና ሁኔታ ብሞክርም አልሳካልህ ስላለኝ ገሪቦች ጋር ዱኣ ላስደርግ መጥቻለሁ፡፡ ጅማ ላይ ብዙ ሰዎች በገሪብ ዱኣ አስደርገው የተሳካለቸው ነጋዴዎች አሉ" በማለት ነግሮኛል፡፡ ከዚህ ወጣት ሀሳብ የምንረዳው ወደ አልከሶ መውሊድ የሄደው ለመውሊድ ወይም ለአልከስዬ ልዩ ፍቅር ስላለው ሳይሆን በቦታው በመገኘት ዱኣ በማስደረግ ምድራዊ ፍላጎት ለሟሟላት ነው፡፡ የዚህን ወጣት ሀሳብ አቀረብኩ እንጂ ልክ እንደዚህ ወጣት ምድራዊ ፍላጎታቸውን ለሚሟላት አስበው የሚመጡ በርካታ ሰዎች አሉ፡፡

ገሪቦች መውሊዱን ሲያከብሩ በምንኛ ቋንቋ እንደሆነ ባይታወቅም በየመሀሉ እየተነሱ ሁለት ጆሯቸውን በሁለት እጃቸው በመያዝ እና ወደ ሰማይ በማንጋጠጥ ይናገራሉ፤ይጮሀሉ፡፡ በዚህ ጊዜ በቦታው ተቀምጠው ከነበሩ ሰዎች መካከል የተወሰኑት በመነሳት የተቀሩት ደግሞ ቁጭ ባሉበት ገሪቡ የሚናገረው ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ይላሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ቦታው በእልልታ እና በጩኸት ይደምቃል፡፡ ይህ ጩኸት ምን እንደሆነ እና ምን ማለት እንደሆነ በቦታው የነበሩትን ሰዎች ስጠይቃቸው አንድም ትርጉሙን የሚነግረኝ ሰው አጥቻለሁ፡፡ ገሪቦች በዚህ ስፍራ መውሊዱን የሚያከብሩት ቀን ብቻ ሳይሆን ማታም ጭምር ነው፡፡ ዝናብ ካልዘነበ በስተቀር አልከሶ ሀረም  ተገኝተው እስከ ሚሄዱ ድረስ ጊዜያቸውን ሙሉ በሙሉ የሚያሳልፉት እዛው ትልቁ ዋርካ ስር ነው፡፡

ለእነዚህ ገሪቦች እንደ ሌላው መውሊድ አክባሪ በየትኛውም የምግብ መመገቢያ ወቅት በመውሊዱ አዘጋጆች ምግብ ሲቀርብላቸው አልተመለከትኩም፡፡ ነገር ግን የተለያዩ ለእነሱ ፍቅር ያላቸው ሰዎች ምግብ ስለሚያመጡላቸው እሱን ይመገባሉ፤በመስጂዱ ለሚዘጋጀው ምግብ ብዙም ትኩረት አይሰጡም፡፡ በ16/09/2008 ዋናው መውሊድ በሚከበርበት ቀን ለተለያዩ ኸለዋዎች ምግብ ሲያደርስ ያገኘሁትን አንድ ወጣት ኻዳሚ ለምን ለገሪቦች ምግብ እንደማይቀርብላቸው ስጠይቀው "እነሱ እኮ ረሀብ የለባቸውም፡፡ ብዙ የሚመጀንባቸው (የሚያምንባቸው ለማለት ነው) ሰው ስላለ በቂ ምግብ ይመጣላቸዋል፡፡ ደግሞ ዝምብሎ ምግብ አይበሉም አሪፍ አሪፍ ምግብ ነው የሚፈልጉት፡፡ የራባቸውማ ምስኪኖቹ ከህዝቡ

እየተቀላቀሉ ይበላሉ፡፡" የሚል ምላሽ ሰጥቶኛል፡፡ ኻዳሚው እንዳለኝም የተወሰኑ ገሪቦች ከአሱር ሷላት በኂላ ህዝቡ ተሰብስቦ ምግብ በሚመገብበት ቦታ ላይ ሲመገቡ ተመልክቻለሁ፡፡

በመስክ ቆይታዬ እነዚህ ገሪቦች መውሊዱን በሚያከብሩት ዋርካ ስር ተቀምጬ መውሊዱን እንዴት እንደሚያከብሩ ተመልክቻለሁ፡፡ ከእነዚህ ገሪቦች ጋር አብሬ በመሆን በከፊል እነርሱ የሚያደርጉትን በማድረግ መረጃ መሰብሰብ ችያለሁ፡፡ በሌላ አገላለጽ ተሳትፏዊ ምልከታ አካሂጃለሁ፡፡ የአልከሶ መውሊድን ከሚያደምቁ ጉዳዮች መካከል የእነዚህ የገሪቦች የአከባበር ሁኔታ አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ከላይ እንደተገለጸው እነዚህ ገሪቦች መውሊዱን የሚያከብሩት ዋርካ ስር ሜዳ ላይ በመሆኑ እነሱን ለማየት የሚሰበሰበው ሰው አካባቢውን በተለያዩ ጫዋታዎች ደመቅ ያደርገዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ገሪቦች በየመሀሉ እየተነሱ የሚጮሁት ጩኸት እና እነርሱን ለማየት የሚሰበሰበው ሰው ለመውሊዱ ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል፡፡



ፎቶ 15፡- አጥኚው ከገሪቦች ጋር ቃለ መጠይቅ ሲያደርግ[142]

ባጠቃላይ እነዚህ ገሪቦች በአልከሶ መውሊድ መገኘታቸው ለመውሊዱ ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል፡፡ ከገሪብ ውጭየሆኑ ሰዎች ወደ አልከሶ መውሊድ ለምን እንደሄዱ ወይም ለምን መውልድ እንደሚያከብሩ ሲጠየቁ የተለያየ ዓላማ እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ነገር ግን ገሪቦች

[142] ፎቶ ባንድ መውሊድ አከባሪ፣ 14/09/08 አልከሶ ሀረም

ለምን መውሊድ እንደሚያከብሩ ገሪብ አቢዳን[143] ስጠይቃቸው "ዘመዶቻችን ድሮም ጀምሮ ስለሚያከብሩት ነው" ከማለት የዘለለ ምለሽ ሊሰጡኝ አልቻሉም፡፡ በቦታው የነበሩ በርካታ ገሪቦች የገሪብ አቢዳን ሀሳብ አንጸባርቀዋል፡፡ ይህን ጥያቄ ለገሪብ ቶውፌቅ[144] ሳቀርብላቸው ግን "መውሊድ ባለበት ቦታ ሁሉ እንድንሄድ የመያደርገን ነገር ውስጣችን አለ" ብለውኛል፡፡

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የተመለከትነው የአልከሶ መውሊድ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ሂደት ነው፡፡ በዚህ ሂደት ቅድመ ዝግጅቱ ሶስት ወር ሲቀረው ይጀምራል፡፡ ዝግጅቱ ለዋናው መውሊድ አንድ ቀን እስኪቀረው ድረስ ይካሄድና ለረመዳን አስራ አምስት ቀን ሲቀረው እሁድ ዕለት በደመቀ ሁኔታ ይከበራል፡፡ በዚህ ከበራ ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ ሰዎች ይሳተፉበታል፡፡ በመሆኑም በመውሊዱ በርካታ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ ክንዋኔዎች ይከናወኑበታል፡፡ በዚህ በተጨማሪ ዚያራም ይካሄዳል፡፡ ይህን መውሊድ ከሚያደምቁት ሰዎች መካከል ገሪቦች(የድሬ ሼኽና ሁሴን ወዳጆች) ይገኙበታል፡፡ ባጠቃላይ የአልከሶ መውሊድ ቅድመ ዝግጅት ወራትን ቢፈጅም ከዚህ በላይ በተመለከትነው ሁኔታ አርብ ቀን ተጀምሮ በደመቀ ሁኔታ እየተከበረ እስከ ማክሰኞ (ስልስላ) ድረስ ይቆይና ይጠናቀቃል፡፡ በዚህ መውሊድ ከተለያዩ ቦታዎች ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከልጅ እስከ አዋቂ፣ ከሙስሊም እስከ ክርስትያን፣ እና ሁለቱም ጾታዎች ይሳተፋሉ፡፡ የመውሊዱ አክብሪዎች ከመውሊዱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ እንደሚያገኙም ከዚህ ጥናት መረዳት ይቻላል፡፡

## 6.5. ድህረ መውሊድ

መውሊድ እሁድ እለት በደመቀ ሁኔታ ከተከበረ በኊላ የመዝግያ ስነ ስርዓት ማክሰኞ ቀን ይካሄዳል፡፡ ማክሰኞ እለት በአካባቢው ስልስላ[145] በመባል ይታወቃል፡፡ እንደ Trimingham (1971፣237) አገላለጽ ሁለት አይነት ስልስላ አለ፡፡ አንደኛው በስልስላ ቀን የመውሊዱ ወይም የክበረ በዓሉ ጀማሪ ሼኽ ማንነት የዘር ሀረግ የሚመዘዝበት እና የሚወደስበት ነው፡፡

---

[143] ቃለ መጠይቅ 28/09/07

[144] ቃለ መጠይቅ 14/09/08

[145]The authority each regional khalifa(general referred to as the sheikh) is founded upon a chain of tradition which has two division: silsilat al-baraka(chain of benediction) which connect him with the founder of the order and silsilat al-wird(chain of initiation) which connects the founder with the prophet. It is the practice of some of the orders to recite these chains as part of their spiritual exercises (Trimingham 1971፣237).

ሁለተኛው የመውሊዱ ወይም የክበረ በዓሉ ጀማሪ ሼኽን ከነብዩ መሀመድ ጋር ለማገናኘት የሚሞከርበት ሂደት ነው፡፡ በአልከሶ ያለው የስልስላ አይነት የትኛው እንደሆነ ቀጥለን እንመልከት፡፡

እንደ አቶ ሁሴይኒ[146] እና አቶ ሰናይ[147] አገላለጽ "ስልስላ" ማለት በመውሊድ አክባሪዎች ዘንድ መሰነባበቻ እንደማለት ነው፡፡ መውሊዱ በደመቀ ሁኔታ ከአርብ ጀምሮ ሲከበር ይቆይና ማክሰኞ ዕለት ስልስላ በሚል መርሐ ግብር ይዘጋል፡፡ የአልከሶ ሀረም ሰኞ እለት ቀዝቀዝ ያለው መልሶ የስልስላ ቀን ይደምቃል፡፡ በስልስላ ቀን የሚገኙ ምዕመናንን በብዛት ከአልከሶ እና አካባቢዋ የተሰባሰቡ ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች አብላጫዎቹ እሁድ እለት ከአሱር ሷላት በኋላ ወደ ቤታቸው ሄደው ተመልሰው የሚመጡ እንደሆኑ ወ/ት ሙናጃ[148] ትናገራለች፡፡ ከእነዚህ በተጨማሪ በየኸለዋዎቹ መውሊዱን ሲያከብሩ የቆዩ እና ወደ ቤታቸው ያልሄዱም ይገኙበታል፡፡ ስልስላ የእሁዱን ያህል የሰው ብዛት እና ድምቀት የለውም፡፡ የስልስላ የአከባበር ሁኔታው ከሌላው ቀን የተለየ አይደለም፡፡ በዚህ ቀን እንደማንኛውም የመውሊድ ቀናቶች ጫት ይቃማል፣ መንዙማ ይባላል፣ መንዙማዎች ይደመጣሉ፣ ምርቃት ይካሄዳል፣ ቁርአን ይቀራል፣ ነብዩ ሙሀመድ እና አልከስዬ ይታወሳሉ፤ ይወደሳሉ፣ ሷላት ይሰገዳል፣ እንዲሁም ምግብ ይዘጋጃል-ይበላል፡፡

በዚህ ቀን በብዛት የሚዘጋጀው "ማዳ" በመባል የሚታወቀው ምግብ እንደሆነ እና "ማዳ" ማለት ከቡላ የሚዘጋጅና ብዙ አይብ እና ቅቤ የሚፈልግ ምግብ እንደሆነ ወ/ሮ ሙርሽዳ[149] ለአጋዥ መረጃ ሰብሳቢያ ሰሚራ ነግረዋታል፡፡ ወ/ሮ ሙርሽዳ አያይዘውም "በዚህ ቀን የሚዘጋጀው ማዳ ሀጃ(ጉዳይ) ያለባቸው ሰዎች ዱኣ ለማስደረግ የሚያመጡት ነው" ይላሉ፡፡ በዚህ ቀን የምግብ ዝግጅቱ እንደ ሌላ ቀን ብዙ የሰው ሀይል እና ጊዜ አይጠይቅም፡፡ ምክንያቱም እንደ ሌሎቹ የመውሊድ ቀናት ብዙ ሰው አይገኝም፡፡ በስልስላ ቀን የሚገኘው የሰው ብዛት አነስተኛ ስለሆነ በቦታው የተገኙ ምዕመናን በበቂ ሁኔታ ምግብ ያገኛሉ፡፡

የስልስላ ቀን የአልከሶ ሀረም እና ሽምሰል ጀማል የሚደምቁት እስከ አሱር ሷላት ድረስ ነው፡፡ ከአሱር ሷላት በኋላ ከትልቁ መስጂድ(ሽምሰል ጀማል) የመሰነባበቻ ንግግር ይተላለፋል፡፡ ከመልዕክቱም መካከል "ዘንድሮ አላህ የአልከሶን መውሊድ እንድናከብር

146 ቃለ መጠይቅ 27/05/08
147 ቃለ መጠይቅ 23/10/07
148 ቃለ መጠይቅ 24/10/07
149 ቃለ መጠይቅ 24/05/08

ስላደረግን አለሀምዱሊላሂ፤ የሚቀጥለውንም አመት በሰላም ያድረስን" የሚል ዱኣ በ18/09/2008 ዓ.ም ሲደረግ ሰምቻለሁ፡፡ በመቀጠልም ምዕመናኑ ራሳቸውን ከተለያዩ ሀራም(ክልክል) ከሆኑ ነገሮች እንዲጠብቁ፣ ሁሉም ሰው በዲኑ(በሃይማኖቱ) እንዲጠናከር፣ ሁሉም ሰው በየተሰማራበት ስራ መስክ ጠንክሮ እንዲሰራ፣ የተቸገረ ሰው እንዲረዱ ወዘተ አይነት ይዘት ያላቸው መልዕክቶች ተላልፈዋል፡፡ ከአሱር ሷላት በኋላ አብላጫ ሰዎች ወደ መጡበት መሄድ ስለሚጀምሩ ሀረሙ ጭር እያለ ይሄዳል፡፡ በመሆኑም ይህ ቀን የመውሊዱ የፍጻሜ ቀን ይሆናል፡፡ ይህ ሲባል ከስልስላ በኋላ በሀረሙም ውስጥ ሆነ በኸለዋዎች ውስጥ መውሊዱን የሚያከብሩ ሰዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ከሩቅ ቦታ የመጡ ሰዎች ዋና መውሊድ ከተከበረ በኋላ እስከ ሳምንት ድረስ ይቆያሉ፡፡

በ25/09/2007 ዓ.ም የስልስላ ቀን የሰኢድ ዱንጋ ኸለዋ ውስጥ መውሊድ ሲያከብሩ ያገኘኋቸው ሰዎች መውሊዱን ሲያከብሩ እስከ ሳምንት ድረስ እዛው እንደሚቆዩ ነግረውኛል፡፡ በአጠቃላይ ግን በመውሊዱ አዘጋጆች ዘንድ ግን መውሊዱ አብቅቷል የሚባለው የስልስላ ቀን ነው፡፡ ቀደም ብለን በአልከሶ መውሊድ የሚተገበረው የትኛው አይነት ስልስላ ነው የሚል ጥያቄ ማንሳታችን ይታወቃል፡፡ ከዚህ በላይ ከተመለከትነው መረጃ አንጻር በአልከሶ መውሊድ ሁለቱም ማለትም ነብዩ ሙሀመድን እና አልከስዬን የማወደስ የስልስላ አይነቶች ይካሄዳሉ፡፡ አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ደግሞ በስልጤ ዞን ያለው የስልስላ አይነት ቀድሪያ የሚባለው የስልስላ አይነት ነው ይላሉ፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# 7. ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ በአልከሶ መውሊድ

የዚህ ምዕራፍ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች ተቃኝተውበታል፡፡ አንደኛው በአልከሶ መውሊድ የንግድ እንቅስቃሴ ምን እንደሚመስል የተቃኘበት ነው፡፡ ሁለተኛው ነጥብ በመውሊድ ሰሞን የሚካሄዱ ማህበራዊ ጉዳዮችን የተዳሰሰበት ነው፡፡ ይህን ምዕራፍ ለመተንተን የተጠቀምኩበት ንድፈ ሀሳብ ስነ ፋይዳ ወይም ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብን ነው፡፡

## 7.1 የንግድ እንቅስቃሴ በአልከሶ መውሊድ

በተለያዩ ቦታዎች በሚከበሩ ክብረ በዓላት ላይ ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል ንግድ አንዱ ነው፡፡ በዚህ ንግድ ከተለያዩ ቦታች የሚሰባሰቡ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሳተፉበት በመሆኑ እርስ በእርስ ማህበራዊ ግንኙነት ያጠናክሩበታል እንዲሁም እንደ ገቢ ምንጭነት ይጠቀሙበታል፡፡ በአልከሶ መውሊድ ሰሞን የሚካሄደው ክንውኖች መካከል ንግድ አንዱ ነው፡፡

በአልከሶ መውሊድ ሰሞን በአልከሶ ከተማ እና አካባቢው በከፍተኛ ሁኔታ የንግድ እንቅስቃሴ ይካሄዳል፡፡ የንግድ እንቅስቃሴው የሚካሄደው መውሊዱ በሚከበርበት ቦታ ብቻ አይደለም፡፡ ምክንያቱም መውሊዱ በሚከበርበት ቦታ ዙሪያ ያሉ ገበያዎች በሙሉ መውሊዱ አንድ ሳምንት ሲቀረው ጀምሮ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በሚገዙ ሰዎች ይጨናነቃሉ፡፡ በአካባቢው የሚኖሩ ነጋዴዎችም የአልከሶ መውሊድን መቃረብ በጉጉት ይጠብቁታል፡፡ ምክንያቱም የመውሊዱ መምጣት ለእነሱ የገቢ ምንጫቸው በመሆኑ ነው፡፡ ይህ በአንድ ክብረ በዓል ላይ የተለያዩ የንግድ እንቅስቃሴዎች መካሄዳው አለማቀፋዊ ጉዳይ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ፈለቀ (2004፤145) "ሃይማኖታዊ ተቋማት ለቱሪዝም መስብህ በመሆን የመጀመሪያዎቹ ምንጮች መሆናቸው በታሪክ ይታወቃል፡፡" ይላሉ፡፡

በመውሊድ ሰሞን በአልከሶ ሀረም እና ዙሪያው ጊዜያዊ የንግድ ቦታዎች ተቋቁመው በከፍተኛ ሁኔታ የንግድ እንቅስቃሴ ይካሄዳል፡፡ በንግድ እቅስቃሴው ከአካባቢው ማህበረሰብ በተጨማሪ ከቡታጅራ፣ ከአረቅጥ፣ ከሀዲያ ዞን፣ ከአሊቾ፣ ከአዘርነት፣ ከዳሎቻ፣ ከወራቤ

የሚመጡ ነጋዴዎች እንደሚሳተፉ በንግድ ስራ ተሰማርታ ያገኘኋት ወ/ት ሙናጃ[150] ገልጻልኛለች፡፡ እነዚህ ነጋዴዎች ዋናው በዓል ሊከበር ሶስት ቀን ሲቀረው (ከሀሙስ ጀምሮ) በሀረሙ ውስጥ በተለያዩ ቁሳቁሶች ዳሶችን በማዘጋጀት ስራቸውን ይጀምራሉ፡፡ በዚህ የንግድ ስራዎች ከህጻን እስከ አዋቂ ሁለቱም ጾታዎች ይሳተፋሉ፡፡

በበዓሉ ለሽያጭ ከሚቀርቡት ቁሳቁሶች መካከል ከምግብ አንጻር እንጀራ በሽሮ ወጥ፣ እንጅራ በስጋ ወጥ፣ ዳቦ፣ ቂጣ፣ ቆሎ፣ሎርናቄ፣ የተለያዩ የብስኩት አይነቶች፣ ከረሜላዎች፣ ወዘተ ሲገኙበት ከመጠጦች ቃሪቦ፣ ሻሜታ፣ የተለያዩ የፋብሪካ ለስላሳ መጠጦች፣ በውሃ የሚበጠበጡ የዱቄት ለስላሳዎች፣ ሻይ፣ ቡና ይገኙበታል፡፡ ከምግብ እና ከመጠጥ በተጨማሪ የተለያዩ የአዋቂ፣ የልጅ፣ የሴት፣ እና የወንድ ጫማዎች፤ አልባሳት እና የመዋቢያ ቁሳቁሶች፣ ሰንደል፣ የተለያዩ ፌስታሎች. ምላጭ፣ መርፌ ወዘተ ለሽያጭ ይቀርባሉ፡፡ ከእነዚህ ቁሳቁሶች በተጨማሪ ከሸክላ በእጅ ባለሙያዎች የሚሰሩ የተለያዩ ጀበና፣ "ቢጥር"(ጣባ)፣ "ቁኜ"(ወተት መጠጫ)፣ ወዘተ የመሳሰሉ የመመገቢያ ቁሳቆሶች እና ጀበናዎች ለሽያጭ ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ቁሳቁሶች የስልጤ ብሔረሰብ መገልገያ ቁሳቁሶች በመሆናቸው ብሔረሰቡ ቁሳዊ ባህሉ ለማያውቁት ሰዎች ለማስተዋወቅ የአልከሶ መውሊድ አንዱ አጋጣሚ ነው፡፡





ፎቶ 16፡- ለንግድ ስራ የሚቀርቡ ቁሳቁሶች በከፊል[151]

---

150 ቃለ መጠይቅ 24/10/07

151 ፎቶ በአጥኚው፣ 14/10/07 አልከሶ  ሀረም

በተለያዩ በሀገራችን በሚከበሩ ክብረ በዓላት ላይ የንግድ እንቅስቃሴ በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚካሄድ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ Yasuo Matsunami and Minako Ishihara (2009፣ 498) የሀ(Ya'a) ክብረ በዓልን ለማክበር ስለሚደረግ ጉዞ እና ስለ ክብረ በዓሉ አከባበር ባተቱበት መጣጥፍ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ በዚህ ክብረ በዓል ሰሞን ሰንደል፣ ሱኳር፣ ክብሪት፣ ጫት ወዘተ ለሽያጭ እንደሚቀርብ እና ለአከባቢው ሰዎች ትልቅ የገቢ ምንጭ በመሆኑ በመውሊድ ሰሞን በአንድ ምሽት እስከ ሁለት መቶ ብር እንደሚያፈኙ ያስረዳሉ፡፡

በአልከሶ እና አካባቢው አዋቂ ወንዶች እና ሴቶች የሚዘወተረው ጫት በመውሊድ ጊዜ እና ከመውሊድ ውጭበከፍተኛ ሁኔታ ይቃማል፡፡ በመሆኑም በአልከሶ መውሊድ ሰሞን የጫት ገበያ ከወትሮው ለየት ባለ ሁኔታ ይጧጧፋል፡፡ ጫት በአካባቢው የሚመረተው በቂ ስላልሆነ ከቡታጀራ፣ ከጦራ፣ ከዳሎቻ፣ ከኢንሴኖ፣ ከእንድብር ወዘተ እንደሚመጣ በ2008 የአልከሶ መውሊድ ቀን ጫት ሲነግዱ ያገኘኋቸው አቶ በረካ ነግረውኛል፡፡ በአጠቃላይ በበዓሉ ከአልባሳት እስከ ምግብ እና መጠጥ ድረስ ያሉ ቁሳቁሶች ለሽያጭ ይቀርባሉ፡፡

አልከሶ ሀረም ውስጥ ነጋዴዎች የሚሸጥ ቁሳቁስ ማቅረብ የሚጀምሩት ከሀሙስ ጀምሮ ቢሆንም የንግድ ስራቸውን በደመቀ ሁኔታ ማካሄድ የሚጀምሩት ግን ከቅዳሜ ጀምሮ ነው፡፡ ቅዳሜ እለት በቦታው ተገኝቼ መመልከት እንደቻልኩት ገና በጠዋቱ ሁሉም ነጋዴዎች በአዘጋጁት ጊዜያዊ መነገጃ ቦታ ላይ የሚሸጡትን ቁሳቁስ አዘጋጅተው ገዢዎችን ይጠባበቃሉ፡፡ የገበያው እንቅስቃሴ የሚጀመረው ወደ አራት ሰአት አካባቢ ነው፡፡ በዚህ ሰአት በብዛት የሚሸጠው ጫት ቢሆንም የተለያዩ የልጆች አልባሳት በየቦታው ወላጆች ለልጆቻቸው ሲገዙ ይታያል፡፡ እንደ እመት ሀረም [152] አገላለጽ በአልከሶ እና አካባቢው የአልከሶ መውሊድ እንደ ማንኛውም አመት በዓል ስለሚቆጠር ለልጆች ልብስ መግዛት የተለመደ ነው፡፡ ከልጆች በተጨማሪ አዋቂዎች በተለይ ወንዶች የመስገጃ ልብስ(ጀለቢያ) ሲገዙ መመልከት የተለመደ ነው፡፡ ቅዳሜ ቀን ልብስ የተገዛላቸው ልጆች የተገዛላቸውን ልብስ ለብሰው መውሊዱ ላይ ይገኛሉ፡፡

አቶ በረካ በአልከሶ ሀረም ውስጥ ጫት ሲነግዱ ያገኘኋቸው ሲሆን ጥር 25/2008 ዓ.ም በተዘጋጀው የቡድን ውይይት ላይ የአልከሶ መውሊድ መከበር አለበት ከሚሉት ወገኖች

[152] ቃለ መጠይቅ 24/10/2008

በመሆን የተሳተፉ እና ጫት ነጋዴ ናቸው፡፡ አቶ በረካ በቃለ መጠይቅ ወቅት እንደተናገሩት ከሆነ የአልከሶ መውሊድን ሃያ አመት በላይ ያከበሩ ሲሆኑ ላለፉት ስምንት አመታት ያህል አልከሶ መውሊድ ሰሞን ጫት ነግደዋል፡፡ አቶ በረካ ለንግዱ ወደ አልከሶ የሚሄዱት ለዋናው መውሊድ ሁለት ቀን ሲቀረው ነው፡፡ ከአርብ ጠዋት ጀምሮ እስከ ቅዳሜ ማታ ድረስ በዋናው መስጂድ ጥግ ላይ መደብ በማዘጋጀት ጫት ይሸጣሉ፡፡ እሁድ ጠዋት ጀምሮ ግን ከሀረሙ ውጭመሸጥ ይጀምራሉ፡፡ አቶ በረካ ንግዱን ሲጀምሩ ስራው ብዙም ትርፋማ አላደረጋቸውም ነበር ነገር ግን ስራውን በደንብ ሲለምዱት የተሻለ ትርፍ እያገኙ ስለሄዱ አጠናክረው ይዘውታል፡፡ “የጫት ንግድ የጀመርኩ ሰሞን አንድ ዙርባ ጫት ሁለትም ሶስትም ብር ይሸጥ ነበር፡፡ አሁን ግን ከሰላሳ ብር በታች የለም፡፡ ጥቅሙም ከድሮ አሁን ይሻላል” ይላሉ፡፡ እሳቸው ጫት በሚሸጡበት ወቅት ባለቤታቸው ደግሞ ሻይ አፍልተው ይሸጣሉ፡፡ አቶ በረካ ለስምንት አመት ያህል ቢነግዱም ባለቤታቸው ከእርሳቸው ጋር በዚህ ሁኔታ መነገድ ከጀመሩ ገና ሁለት አመታቸው ነው፡፡ ወደ ዚህ ስራ የገቡት የንግዱ ሁኔታ እንደሚያዋጣ ባለቤታቸው ስለነገሯቸው እንደሆነ ይናገራሉ፡፡



ፎቶ 17፡- በንግድ ስራ የተሰማሩ ልጆች እና ወጣቶች[153]

[153] ፎቶ ባጥኚው፣23/05/08 አልከሶ ከሀረም  ውጭ

እንደ ባዱዲን ሁሉ በርካታ ወጣቶች እና ጎልማሶች በአልከሶ ሀረም እና ከሀረሙ ውጭ ቀንና ማታ ይነግዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ቀን እና ማታ ብቻቸውን ሲሰሩ የተወሰኑት ደግሞ ተቀያሪ አላቸው፡፡ ለምሳሌ ወ/ት ሙናጃ ማታ ስትነግድ አድራ ጠዋት እዛው ዳሱ ውስጥ ተኝታ ተራዋን እህቷ ትነግዳለች፡፡ እንደ ሙናጃ[154] አገላለጽ የንግድ ስራውን ከእህቷ ጋር በጋራ የሚሰሩ ሲሆን መደበኛ ስራቸው ትምህርት ቢሆንም ቅዳሜ እና እሁድ የንግድ ስራ ይሰራሉ፡፡ ከቅዳሜና እሁድ በተጨማሪ በየአመቱ አልከሶ መውሊድ ላይ በመገኘት ንግድ ይነግዳሉ፡፡ የንግድ ስራውን የሚጀምሩት ቅዳሜ ጠዋት ሲሆን እስከ ማክሰኞ ድረስ ይቆያሉ፡፡

በመውሊድ ቀን አልከሶ ሀረም መረጃ ለመሰብሰብ በቦታው ተገኝቼ እንደተመለከትኩት በንግድ ስራው እድሜያቸው ከስምንት አመት ያልበለጠ ልጆች ይሳተፋሉ፡፡ ልጆቹ በብዛት ቡና እና ሻይ በማንቆርቆሪያ አፍልተው አዙረው ይሸጣሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ የዱቄት ለስላሳዎችን በውሃ በመበጥበጥ እና በኮዳ በማድረግ ይሸጣሉ፡፡ እነዚህ ልጆች በንግድ ስራ የሚሰማሩት አንዳንዶቹ ቤተሰቦቻቸው ነጋዴዎች ሆነው እነሱን ለማገዝ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ ለራሳቸው ነው፡፡ አድማማ ጀማል የአስራ አራት አመት ልጅ ነው፡፡ የመውሊድ ቀን ቡና እና ሻይ አዙሮ ሲሸጥ ያገኘሁት ሲሆን በእሁድ ቀን ስራው ብቻ ሰላሳ ብር ያህል እንደሰራ ነግሮኛል፡፡ አድማማ በዚህ ሁኔታ ያገኘውን ገንዘብ ለደብተር እና ለእስክሪብቶ መግዣ ያውለዋል፡፡ እንደ አድማም ሁሉ በርካታ ታዳጊዎች በዚህ ሁኔታ የተለያዩ ቁሳቁሶችን በመሸጥ ለራሳቸው እና ለቤተሰባቸው ገቢ ያስገኛሉ፡፡

ወ/ሮ ሩቂያ መኖሪያቸው ጉራጌ ዞን ጎመር ወረዳ አረቅጥ የሚባል ቦታ ሲሆን እሁድ ጠዋት የተለያዩ ከሸክላ የተሰሩ ቁሳቁሶችን ለገበያ አቀርበዋል፡፡ ወ/ሮ ሩቂያ ከመቼ ጀምረው እና እንዴት ሊመጡ እንደቻሉ በሚከተለው ሁኔታ ገልጸውታል፡፡

> እኔ እዚህ መምጣት ከጀመርኩ ሶስት አመት ይሆነኛል፡፡ የምመጣውም ከጉራጌ ሀገር አረቅጥ ከሚባል ቦታ ነው፡፡ ቦታው በዚህ አቋራጭ ነው፡፡ በዳጋቱ ቁልቁል ትወርዳለህ፡፡ እዚህ የምሸጠው ጣባ ከነ ክዳኑ፤ ጀበና፣ እና የቅቤ ማንጠሪያ ነው፡፡ እቃውን በብዛት የሚገዙን ከአዲስ አበባ፣ ከናዝሬት፣ ሌሎችም ከተማዎች የመጡ ሰዎች ናቸው፡፡ ከተማ ይዘው ለመሄድ ነው፡፡

[154] ቃለ መጠይቅ 24/10/07

ገበያውም ጥሩ ነው፡፡ እስከ ማክሰኞ ማታ ድረስ እንሸጥና ማክሰኞ አመሻሽ ወደ ቤታችን እንሄዳለን፡፡[155]

በአልከሶ መውሊድ የገቢ ምንጭ ቁሳቁስ መሸጥ ብቻ አይደለም፡፡ ቁሳቁሶችን ከመሸጥ በተጨማሪ የተለያየ እቃ ማከራየት እና አገልግሎት መስጠት ሌሎች የገቢ ምንጮች ናቸው፡፡ ምዕመናን ሀረሙ ውስጥ በሚገኙ ኸለዋዎች ውስጥ ቀን እና ማታ መውሊዱን ያከብራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ጫት መቃም፣ ዱኣ ማድረግ፣ መንዙማ ማለት የተለመደ መሆኑን ቀደም ብለን ተመልከተናል፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ ድባቡ በዋናነት የሚደምቀው በመንዙማ እና ድቤ ነው፡፡ ይህን አጋጣሚ በመጠቀም ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ እና የአካባቢው ወጣቶች ድቤ በማከራየት ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ እነዚህ ወጣቶች በቡድን በቡድን በመሆን ድቤዎችን ከማከራየታቸው በተጨማሪ ገንዘብ ተከፍሏቸው ድቤ በመምታት እና መንዙማ በኸለዋው ውስጥ በማለት ገንዘብ ማግኘታቸው የተለመደ ድርጊት ነው፡፡

ሸምሱ ሱልጣን በ14/09/2007 እሁድ ማታ በሻሸመኔ ኸለዋ ውስጥ መንዙማ እያወጣ እና ድቤ እየመታ ምዕመናኑን ሲያዝናና ያገኘሁት ወጣት ነው፡፡ ወጣት ሸምሱ ይህን ስራ መስራት ከጀመረ አምስት አመት አልፎታል፡፡ ወጣቱ ስራውን ለመስራት የሚያስፈልገውን ነገር በሙሉ አሟልቶ አርብ ማታ ጀምሮ አልከሶ ሀረም ውስጥ ይገኛል፡፡ ወጣቱ እንደነገረኝ ከሆነ ቅዳሜ፣ እሁድ እና ሰኞ ቀን እና ማታ በየኸለዋዎቹ እየተዘዋወረ ይሰራል፡፡ የሚያገኘው ገንዘብ ከቀን ቀን እና ከኸለዋ ኸለዋ ይለያያል፡፡ አንዳንድ ቀን እስከ ሶስት መቶ ብር ሲያገኝ አንዳንድ ቀን ደግሞ እስከ ሁለት መቶ ብር ድረስ ያገኛል፡፡ እንደ ሸምሱ ሁሉ በርካታ ወጣቶች በየኸለዋው እና ዳሱ በመዘዋወር ይህን ስራ በመስራት ገቢ እንደሚያገኙ መረዳት ችያለሁ፡፡ ከነዚህ ወጣቶች በተጨማሪ በእድሜ የገፉ ሰዎች እና ገሪቦች እየተዘዋወሩ ይህን ስራ ይሰራሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰዎች ይህን ስራ የሚሰሩት እንደ ወጣቶቹ ገንዘብ ለማግኘት አስበው ሳይሆን "በየኸላዋው በመዘዋወር ሰዎችን ማስደሰት አላህን ማስደሰት ነው" ብለው ስለሚያምኑ ነው፡፡

የስነ ፋይዳ ንድፈ ሀሳብ አንድ ክብረ በዓል በአንድ ቦታ መከበሩ ለክብረ በዓል አክባሪዎች እና ለአካባቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያስገኛል እንደሚል ቀደም ብለን

155 ቃለ መጠይቅ 15/09/08

ተመልክተናል፡፡ በመሆኑም የአልከሶ መውሊድ መከበር ለአካባቢው ማህበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ ጠቀሜታ አለው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም መውሊዱ ለአካባቢው ብሎም ከሩቅ ለሚመጡ ሰዎች ከሚያስገኘው ጠቀሜታ መካከል አንዱና ዋነኛው የገቢ ምንጭ በመሆን ማገልገሉ ነው፡፡ ምክንያቱም በመውሊድ ሰሞን በንግዱ ወንድ ሴት ሳይለይ ከአዋቂ እስከ ልጅ ድረስ ሁሉም ይሳተፋሉ፡፡

አቶ ሁሴይኒ[156] "በአልከሶ መውሊድ ከድሮም ጀምሮ የውጭ ሀገር ዜጎች ለጉብኝት ይመጣሉ" ብለውኛል፡፡ ፊለቀ (2004፣145) "ሃይማኖታዊ ተቋማት ለቱሪዝም መስብህ በመሆን የመጀመሪያዎቹ ምንጮች መሆናቸው በታሪክ ይታወቃል" ይላሉ፡፡ የአልከሶ መውሊድም መከበሩ ለአካባቢው ብሎም ለዞኑ እንደ ቱሪዝም መስህብ በመሆን ያገለግላል ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለአካባቢው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያስገኛል፡፡ በሀገራች ከሚከበሩ መውሊዶች መካከል በድሬ ሼኽና ሁሴን፣ በአብሬት፣ በዳኒዬ፣ በቃጥባሬ ወዘተ መውሊዶች የውጭዜጎች እንደሚገኙ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ የእነዚህ የውጭ ዜጎች በመውሊዶች መገኘት ሁለት አላማ አለው፡፡ አንደኛው መውሊዱን ለማክበር ሲሆን ሁለተኛው ለመዝናናት ወይም ለመጎብኘት ነው፡፡

## 7.2 በአልከሶ መውሊድ ለሽያጭ እና ለስጦታ የሚቀርቡ ምግቦችና መጠጦች

በአልከሶ መውሊድ በርካታ የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግቦች፣ ማባያዎች እና መጠጦች ይቀርባሉ፡፡ እነዚህ ምግቦች፣ ማባያዎች እና መጠጦች አንዳንዶች ለሽያጭ የሚቀርቡ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ምዕመናኑ በመውሊዱ ለሚኖራቸው ቆይታ ቤታቸው አዘጋጅተው የሚያመጧቸው ናቸው፡፡ አልከሶ መውሊድ ላይ የተገኘ ማንኛውም ሰው የመውሊድ ምግብ ሳይመገብ ወይም ሳይቀምስ አይመለስም፡፡ ለዚህ ሁሉ ህዝብ ለማዳረስ በአንድ ሳምንት ውስጥ እስከ ሶስት መቶ የሚደርሱ በሬዎች እንደሚታረዱ ገራድ ኑርሰቦ እና ሀጅ ሀሚዲኖ እንደሚያስረዱ ቀደም ብለን ተመልክተናል፡፡ ገራድ ኑርሰቦ አያይዘውም "በጎች እና ፍየሎች በየቦታው ስለሚታረዱ ቁጥራቸውን መገመት አዳጋች ነው" ይላሉ፡፡ ከስጋ ነገሮች በተጨማሪ በበዓሉ ለምዕመናን የሚቀርቡት ቆጮ፣ ቂጣ፣ ዳቦ፣ እንጀራ፣ እና የሌሎችንም የምግብ አይነቶች መጠን መናገር አይቻልም፡፡ ምክንያቱም ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ምዕመናን

---

156 ቃለ መጠይቅ 23/05/08

ባዶ እጃቸውን አይመጡም፡፡ ከአንዳንድ አካባቢዎች የሚመጡ ምዕመናን በበዓሉ ቦታ ለሚቆዩበት ቀን ያህል ምግብ ይዘው ስለሚመጡ የሚፈልጉት እንደ ስጋ ያሉ ማባያዎችን ነው፡፡ በዓለማችን በሚከበሩ መውሊዶች ልክ እንደ አልከሶ መውሊድ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች ይቀርባሉ፡፡ ለምሳሌ FAREEN(2014፣219) በህንድ ሀገር ስላለው የመውሊድ በዓል አከባበር በሚያስረዱበት መጣጥፍ "Milad-un-Nabi has a centuries-long history in Hyderabad, it was typically celebrated by casual family visits and the preparation of traditional food items." በማለት ገልጸውታል፡፡



ፎቶ 18፡-የሥጋ ጥብስ በቅርጫት ተደርጎ ሲከፋፈል[157]

[157] ፎቶ በአጥኚው 14/09/08

ባጠቃላይ የመውሊድ ሰሞን ለምግብነት እና ለመጠጥነት የሚቀርቡ ምግቦች እና መጠጦች የሚከተሉት ናቸው፡፡

| ባህላዊ ምግቦች | ማባያዎች | መጠጦች[158] |
|---|---|---|
| ፍናንቾ | የቆጡይ ሀምል | ሻሜታ |
| አተካኖ | ካሽትዬ | ብርዝ(ስህር) |
| ቢላምብሎ | ቆጤየጄሩይ ሀምል | ኬነቶ |
| ድፎ | ያምል ክልፋን | ቃሪቦ..... |
| ዳቦ | አዝማሞጃት | |
| ጦረሾ | ፊንታፊንቶ | |
| ጣቢታ | ክልፍን | |
| | ወላንዳ | |



ፎቶ 19፡- እናቶች በአልከሶ ሀረም ጣቢታ እና አተካኖ ሲያዘጋጁ[159]

[158] በስልጤ ብሔረሰብ የባህል መጠጦች በብዛት የሚዘጋጁት ከገብስ፣ ከወተት፣ ከማር እና ከቡና ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ የመጠጥ አይነቶች በብዛት መውሊድ ላይ ይቀርባሉ፡፡

[159] ፎቶ በአጥኚው 23/06/10/07 አልከሶ ሀረም - የምግብ ኸለዋ ውስጥ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በአልከሶ መውሊድ የሚቀርቡ የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ ምግብና መጠጥ እዚህ ማንሳት የፈለኩበት ምክንያት አለኝ፡፡ ይህውም የብሔረሰቡ ባህላዊ ምግብ እና መጠጥ ከእነ አሰራሩ ምን እንደሚመስል በተወሰነ ደረጃ ለማሳየት ነው፡፡ ምክንያቱም የዚህ ጥናት አንዱ ዝርዝር ዓላማ መውሊድ የሚከበርበትን አካባቢ ማህበረሰብ ባህል ማስተዋወቅ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብሔረሰቡ መውሊድን በመጠቀም ቁሳዊ ባህሉ የሆነውን ምግብን ከሌላ ቦታ ለመጡ ሰዎችን እግረመንገዱን እንዴት እንደሚያስተዋውቅ ለማሳየት ነው፡፡

## 7.3 ማህበራዊ ክንውኖች በአልከሶ መውሊድ

በአልከሶ መውሊድ ከሃይማኖታዊ ስነስርዓት በተጨማሪ በርካታ ማህበራዊ ክንውኖች ይከናወናሉ፡፡ ከእነዚህ ክንውኖች መካከል የዞኑ ባህልና ቱሪዝም መምሪያ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ያደርጋል፣ የሃይማኖት እና የመንግስት ሹማምንት ንግግር ያደርጋሉ፣ ለተቸገሩ ሰዎች ገንዘብ ይዋጣል፣ ለልማት የሚውል ገንዘብ ይሰባሰባል፡፡ ስለነዚህ ነጥቦች ቀጥለን በአጭር በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

በአልከሶ መውሊድ ቀን በየአመቱ የሃይማኖት አባቶች እና የመንግስት ሹማምንት በቦታው በመገኘት ንግግር ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ በ2007 ዓ.ም የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ፕሬዝዳንት ተወካዮች፣ የስልጤ ዞን እስልምና ጉዳይ ተወካዮች፣ የመከላከያ ሚኒስተሩ አቶ ስራጅ ፈርጌሳ፣ እና ሌሎቹም ተገኝተዋል፡፡ በ2008ዓ.ም ደግሞ የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳይ ፕሬዝዳንት ጽህፈት ቤት ተወካዮች፣ የስልጤ ዞን እስልምና ጉዳይ ፕሬዝዳንት፣ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች ክልል መንግስት እስልምና ጉዳይ ፕሬዝዳንት ተወካዮች ተገኝተዋል፡፡ እነዚህ ባለስልጣናት ከዙህር ሷላት በኋላ ተራ በተራ ሃይማኖታዊ እና አለማዊ ይዘት ያላቸውን ንግግሮችን አድርገዋል፡፡ ንግግሮቻቸው ከሃይማኖታዊነት ይልቅ ወደ አለማዊነት(ፖለቲካዊነት) የሚያደሉ ናቸው፡፡

ሙስሊም ያልሆኑ የመንግስት ሹማምንት በዚህ አይነት የሙስሊሞች ክብረ በዓል ላይ ተገኝተው ንግግር ማድረጋቸው የራሱ የሆነ አንድምታ አለው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም የእነዚህ ሰዎች ንግግር ሙሉ በሙሉ ፖለቲካዊ ይዘት ያለውና ህዝቡ መንግስት የሚለውን ብቻ እንዲቀበል የሚለምን፣ የሚያዝ እና የሚያስፈራራ ይዘት ያለው ነው፡፡ የዚህ አይነት የመንግስት ባለስልጣኖች በመውሊድ ቦታ ተገኝተው ንግግር ማድረግ በሌሎችም በሀገራችን በሚከበሩ መውሊዶች ላይ እንዳለ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ገመቹ (2007፣98) ስለ ዋሬ

ክብረ በዓል  ባጠናበት ጥናቱ በወቅቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባኤ አቶ አባ ዱላ ገመዳ እና ሌሎችም ተገኝተው ንግግር ማድረጋቸውን አትቷል፡፡

ሌላው በመውሊድ ሰሞን የሚከሄደው ማህበራዊ ክንውን ለጎን የስልጤ ዞን ባህል፣ ቱሪዝምና የመንግስት ኮሚኒኬሽን ጉዳዮች መምሪያ በመኪና እየተዘዋወረ የተለያዩ ይዘት ያላቸውን መልዕክቶችን አስተላልፈዋል፡፡ ከሚተላለፉ መልዕክቶች መካከል ስለ ኤች አይ ቪ ኤድስ፣ ስለ መኪና አደጋ እና የመንገድ አጠቃቅም፣ ስለ ትክክለኛ ያልሆነ ብር፣ ስለ ሙስና፣ ስለ አሸባሪ ወዘተ ይገኙበታል፡፡ በመኪና በመዘዋወር የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ከመስራት በተጨማሪ የተለያዩ በራሪ ወረቀቶች ይበተናሉ፤ በየግድግዳው ይለጥፋሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ ለሁለት ቀን ህብረተሰቡን የተለያዩ ትምህርቶችን ያስተምራሉ፡፡

በአልከሶ መውሊድ ሰሞን ለተቸገሩ በተለያዩ ጉዳዮች ችግር ላጋጠማቸው ሰዎች ገንዘብ ይዋጣል፡፡ ለምሳሌ በ2007 ዓ.ም አንድ ግለሰብ ነዋሪነቱ ጂማ ከተማ የሆነ እና በንግድ ስራ ተሰማርቶ የሚኖር ማንነታቸው ባልታወቁ ሰዎች ፊቱ ላይ አሲድ ተደፍቶበት እና ንብረቱ ተዘርፎ አልከሶ ሀረም  የገንብ ድጋፍ ተደርጎለታል፡፡ በ2008 ዓ.ም ደግሞ አንድ እናት ልጃቸው በተለያዩ በሽታዎች ስለተያዘ ወደ አዲስ አበባ ወስደው ማሳከም እንዳለባቸው የአካባቢያቸው ሀኪሞ እንደነገሯቸው እና አዲስ አበባ ወስደው ማሳከም ስለማይችሉ እርዳት እንዲደረግላቸው ጠይቀው እርዳታ ተደርጎላቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዚህ አመት በዞኑ በተለያዩ ቦታዎች በዝናብ መጥፋት ምክንያት የተነሳ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ገንዘብ ተሰባስቧል፡፡  ይህ ሁኔታ የሚያሳየው የአልከሶ መውሊድ በአካባቢው መከበሩ ለአካባቢው ሰዎች ማህበራዊ ፋይዳ እንዳለው ነው፡፡ ምክንያቱም በመውሊድ ምክንያት ተሰባስበው እርስ በእርስ ይደጋገፋሉ፡፡

በ2007 እና በ2008 የመውሊድ ሰሞን ለመስጂድ እና ለልማት የሚውል ገንዘብ እንዲዋጣ ተደርጎል፡፡ በተለይ በ2007 ዓ.ም በዞኑ በተለያዩ ቦታዎች የሚገኙ መንገዶች ክረምት ክረምት ክረምት ጭቃ ስለሚሄኑ የታመሙ ሰዎችንም ሆነ ሚጥ ያያዛትን ሴት ወደ ሀኪም ቤት ለመውሰድ አስቸጋሪ ስለሆነ እነዚህ መንገዶች ለማሰራት የሚሆን ገንዘብ ተሰባስቧል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዳሎቻ ወረዳ የሚገኘው የፈይድን መስጂድ ለማሰራት እርዳታ ተይቆ ገንዘብ ተዋጥቷል፡፡

ባጠቃላይ የአልከሶ መውሊድ በዚህ ቦታ መከበሩ ለአካባቢው ብሎም ለዞኑ እና አጎራባች ወረዳዎች ማህበራዊ ፋይዳው የጎላ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያም በዚህ መውሊድ ተሰባስበው ችግራቸውን እርስ በእርስ ይወያየሉ እንዲሁም የተቸገረን ሰው ይረዳሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ፡፡

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የተመለከትነው በአልከሶ መውሊድ የወጣቶች ግንኙነት፣ የንግድ እንቅስቃሴ እና የምግብ አዘገጃጀት እና የአመጋገብ ስርአት ምን እንደሚመስል ነው፡፡ በዚህ መውሊድ ወጣቶች ከቅዳሜ ጠዋት ጀምረው እስከ ሰኞ ድረስ በየኸለዋው፣ በየዳሱ፣ እና በየሜዳው በደመቀ ሁኔታ መውሊዱን ያከብራሉ፤ ይዝናናሉ፤ ማህበራዊ ግንኙነት ይፈጥራሉ፤ ማህበራዊ ግንኙነታቸው ትዳር እስከ መመስረት ይደርሳል፡፡ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው በአልከሶ መውሊድ ከሚከናወኑ ክንውኖች መካከል አንዱና ዋነኛው ንግድ ነው፡፡ በዚህ ቦታ ከስልጤ ዞን እና ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ ነጋዴዎች ከአርብ ጀምረው በሀረሙ ውስጥ የተለያዩ ሸቀጣ ሸቀጦችን በማቅረብ እስከ ማክሰኞ ድረስ የንግድ ስራ ይሰራሉ፡፡ ሌላው በዚህ ምዕራፍ የተመለከትነው የምግብ ስርአቱን ነው፡፡ በዚህ ክብረ በዓል የብሔረሰቡ አብላጫ የባህል ምግቦች እና መጠጦች ይቀርባሉ፡፡ አብላጫዎቹ ምዕመናን ቤታቸው አዘጋጅተው የሚያመጧቸው ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ እዛው ሀረም ውስጥ የሚዘጋጁ ናቸው፡

# ምዕራፍ ስምንት

## 8. የሃይማኖት መስተጋብር በአልከሶ መውሊድ

የዚህ ምዕራፍ ዋና ዓላማ የሃይማኖት መስተጋብር በአልከሶ መውሊድ ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ መውሊድ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የሚሳተፉ በመሆኑ ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች መውሊዱን ለምን ዓላማ እና እንዴት እንደሚያከብሩ ተዳሷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በመውሊዱ ሰሞን እና ውጭ በአካባቢው ያለው የሃይማኖት መስተጋብር ምን እንደሚመስል እና ይህ መስተጋብር ለማህበረሰቡ ምን ገጽታ እንዳላበሰው ተቃኝቷል፡፡

ኢትዮጵያ የተለያየ ሀይማኖት ያላቸው ህዝቦች ተቻችለውና ተከባብረው የሚኖሩባት ሀገር ናት፡፡ በሀገራችን በአሁኑ ጊዜ የሚስተዋለው የሃይማኖት መቻቻል መሰረቱን የጣለው በ7ኛው ክፍለ ዘመን 615 አካባቢ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ ዘመን እስልምና ወደ ሀገራችን የገባበት ጊዜ ነው፡፡ እስልምና ኢትዮጵያ ውስጥ የገባው በ7ኛው ክፍለ ዘመን በቀይ ባህር በኩል እንደሆነ Trimingham (1952፡42) እና የተለያዩ የታሪክ ምሁራን ገልጸዋል፡፡ እስልምና በነቢዩ ሙሀመድ መልዕክተኞች አማካኝነት ወደ ኢትዮድያ ከገባ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በርካታ ዓመታትን አስቆጥሯል Hussein (2006:4) እና Trimingham (1952፡42)፡፡ Nejib (2015:1) ደግሞ “In Islamic history and tradition, Ethiopia (Abyssinia or Al-Habasha) is known as the "Haven of the First Migration or Hijra." For Muslims, Ethiopia is synonymous with freedom from persecution and emancipation from fear.” ይላሉ፡፡

ስለ ሀይማኖት መቻቻል ውዱ ጣፊጠ (2004፣204) ባህልና ልማት በኢትየጵያ በሚል ርዕስ ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ በሚያዘጋጀው መጽሀፍ ውስጥ የሚከተለውን ይላሉ፡፡ “የሃይማኖት መቻቻል ጽንሰ ሀሳብ የተጀመረው በአውሮጳ ሲሆን ይህም በአስራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን በተጀመረውና ሪፎርሜሽን (Reformation) በተባለው የሃይማኖት ንቅናቄ ጊዜ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት በሃይማኖት ልዩነቶች ምክንያት ሰዎች መሰደድ እና በሞት የመቀጣት እድል ያጋጥማቸው ነበር፡፡ ከዚህ ጊዜ በኋላ የሃይማኖት መቻቻል ጉዳይ ስር እየሰደደ ሄደ፡፡”

በሀገራች መልካም የሚባል መስተጋብር ከሚስተዋልበት ስፍራ መካከል የስልጤ ዞንን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም መውሊድ መሰረቱ ኢስላማዊ ጉዳይ ሆኖ እያለ ከሙስሊሞች እኩል ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ክርስትያኖችም ገንዘብ በማዋጣት እና አስፈላጊውን ትብብር በማድረግ በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ፡፡ ሙስሊሞቹም ቢሆኑ እነዚህን መውሊድ አክባሪ ክርስትያኖች ሙስሊም አይደላችሁም፤ መውሊድ የእናንተ ጉዳይ አይደለምና አትድረሱብን ብለው በዓሉን እንዳያከብሩ አይከለክሏቸውም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በየቦታው ለመውሊዱ የሚውለው ወጪ ገንዘብ ሲሰባሰብ እንዳይረሱ በማለት እና ለምን መጀመሪያ አልተጠየቀኩም እንዳይሉ ገንዘብ የሚያሰባስበው አካል መጀመሪያ የሚጠይቀው ክርስትያኖችን እንደሆነ አቶ ሁሴይኒ እና አቶ ታደሰ ያስረዳሉ፡፡

ይህ ማለት በአልከሶ መውሊድ ከእስልምና ሀይማኖት በተጨማሪ የክርስትና እምነት ተከታዮችም ይገኛሉ ማለት ነው፡፡ ይህ ሲባል በስልጤ ዞንም ሆነ በአልከሶ አካባቢ የሚገኙ ክርስትያኖች በሙሉ መውሊድን ያከብራሉ ማለት ግን አይደለም፡፡ ምክንያቱም በመውሊድ ሰሞን በርካታ ክርስትያኖች በስራ ቦታቸው ተገኝተው ስራቸውን ይሰራሉ፡፡ ስለዚህ በዚህ ጥናት ክርስትያኖች ስል በአካባቢው የሚገኙ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮችን በሙሉ ለማለት ሳይሆን መውሊድን የሚያከብሩ ክርስትያኖችን ለመግለጽ ብቻ ነው፡፡

የአልከሶ መውሊድ መከበር ከጀመረበት ወቅት ጀምሮ ክርስትያኖች በበዓሉ ይሳተፉ እንደነበር አቶ ታደሰ[160] ይነገራሉ፡፡ አቶ ሰናይ[161] ደግሞ እነዚህ ክርስቲያን ምዕመናን እንደማገኘውም የሙስሊም ማህበረሰብ በሚኖሩበት አካባቢ ለአልከሶ መውሊድ ገንዘብ ሲዋጣ እንደሚያዋጡ ያስረዳሉ፡፡ ይህንን ሀሳብ በተመሳሳይ ሁኔታ አቶ አዘነ ትክክል መሆኑን አጠናክረውታል፡፡ እነዚህ ክርስትያኖች በአልከሶ መስጂድ ሀረም  ውስጥ የራሳቸው ኸለዋ አላቸው፡፡ ኸለዋው አልከስዬ ለክርስትያን ወገኖች ማረፊያ ይሆን ዘንድ በአካባቢው ይኖሩ ከነበሩ ክርስትያን ምዕመናን ጋር በመተባበር አሰርተውታል፡፡ ይህ ኸለዋ ሲሰራ ከሁለት ወይም ከሶስት ክርስትያኖች በላይ እንዳልተሳተፉበት እንዲሁም ከእንጨት ጀምሮ የሚያስፈልገው ወጪ በሙሉ የተሸፈነው በአካባቢው ሙስሊም ማህበረሰብ እና በመስጂዱ አስተዳደር እንደሆነ አባቴ ነግረውኛል በማለት አቶ ግርማ[162] ተናግረዋል፡፡ ስለዚህ ከነዚህ ሀሳቦች የምንረዳው

---

[160] ቃለ መጠይቅ 20/09/07
[161] ቃለ መጠይቅ 23/10/07
[162] ቃለ መጠይቅ 23/10/07

የአልከሶ መውሊድ መከበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች ይሳተፉ እንደነበር ነው፡፡

ክርስትያኖች የአልከሶን መውሊድ እንዴትና መቼ መከበር እንደጀመሩ የበዓሉ ዝግጅት የክርስትያን አስተባበሪ የሆኑት አቶ ታደሰ ታዬ[163] የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> ክርስትያኖች መውሊድን ማክበር የጀመሩት መውሊዱ መከበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ በዓሉን ማክበር ከጀመሩ ሰዎች መካከል የእኔ አባት አቶ ታዬ አንዱ ናቸው፡፡ አባቴ የአልከስዬ አገልጋይ (ኻዳሚ) ነበሩ፡፡ እሳቸው እንደነገሩኝ ከሆነ አልከስዬ ሰውን ሙስሊም ክርስትያን ብለው አይለዩም ነበር፡፡ በእሳቸው ዘንድ ሁሉም ሰው እኩል ነው፡፡ በመሆኑም የክርስትያን ማረፊያ ለብቻው ስላልነበረ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ክርስትያኖች ከእሳቸው እኩል ትልቁ መስጂድ ውስጥ ያርፉ ነበር፡፡ የመውሊዱ ድምቀት እየጨመረ ሲመጣና የክርስትያኖች ቁጥር ሲበዛ አሁን ያለው ከእሳቸው ማረፊያ ቤት ጀርባ ያለው ኸለዋ ተሰራ፡፡ የክርስትያኖች ኸለዋ ከእሳቸው ማረፊያ ቅርብ የሆነበት ምክንያት እነዚህ ሰዎች ሙስሊም ሳይሆኑ የእኔን መውሊድ የሚያከብሩ ሰዎች ሙስሊም ህዝብ ምናልባት ሊበድላቸው እና ሊጨቁናቸው ስለሚችል እኔ በቅርብ ርቀት እጠብቃቸዋለሁ በማለት ነው፡፡

የአቶ ታደሰን ሀሳብ ሃምሳ አለቃ ወርቁ፣ ሼኽ ከዲር፣ በርከፌት ኑርሰቦ እና አቶ ግርማ በተመሳሳይ ሁኔታ ያስረዳሉ፡፡

የአልከሶ መውሊድን የሚያከብሩ ክርስትያኖች የአከባበር ስርአቱን የሚመራላቸው በአቶ ታደሰ ታዬ የሚመራ ኮሚቴ አላቸው፡፡ እነዚህ ኮሚቴዎች ከቅዳሜ ጠዋት ጀምሮ በኸለዋቸው የመገኘት እና የበዓሉን ቅድመ ዝግጅት ማስጀመር ሀላፊነት የተጣለበቸው ናቸው፡፡ ከኮሚቴው ውጭ ይሆኑ ሰዎች ግን በብዛት ወደ በክርስትያን ኸለዋ ውስጥ የሚሰባሰቡት ከቅዳሜ ማታ ጀምሮ ነው፡፡

---

[163] ቃለ መጠይቅ 17/09/08

እነዚህ ክርስትያን ምዕመናን በመስጂዱ ሀረም  ውስጥ የሚገኙት ከቅዳሜ እለት ጀምሮ ነው፡፡ በሀገራችን በሚከበሩ መውሊዶች ክርስትያኖች እንደሚሳተፉ ቀደምት ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ብርሀኑ (1998፡32) ለሁለተኛ ዲግሪ ማሚያ በጻፈው ጽሁፍ በወሎ በሚከበሩ መውሊዶች ላይ ክርስትያኖች እንደሚሳተፉ ጽፏል፡፡ ይህን ጉዳይ ባሳየበት ርእስ በመውሊድ የሁለቱም እምነት ተከታዮች እንደሚሳተፉ ለማሳየት በአካባቢው ከሚባሉ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተለውን አስፈሯል፡፡

እንደምን ነው አና
እንደምን ነው ዳና
እንደምን ነው ገታ አድባርና አውጋሩ፤
የሚመጀኑበት እስላም ክርስትያኑ፡፡
ቃልቻው በመስጂድ ቄሱ በመቅደሱ፤
ሴት ወንድ በቤቱ፤ ሁልጊዜ ይላሉ ሞሚና ድረሱ፡፡

ከብርሃኑ በተጨማሪ ሰሚራ(2004)፣ እና መሀመድ(2009) በወሎ በሚከበሩ መውሊዶች ላይ ክርስትያኖች እንደሚታደሙ ያስረዳሉ፡፡

የአልከሶ መውሊድ አክባሪ ክርስትያን ምእመናን ቅዳሜ እለት ቦታው ላይ እንደደረሱ ለበዓሉ በሚደረገው ቅድመ ዝግጅት ላይ ይሳተፋሉ፡፡ ተሳትፏቸውም እንደ ሆኔታው እንጨት በማዘጋጀት፣ የሀረሙን አጥር በማደስ፣ ውሃ በሌለበት ቦታ ውሃ በማቅረብ ወዘተ ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ እስከ ቅዳሜ ጠዋት ድረስ ይቆዩና ከቅዳሜ ጠዋት ጀምሮ የራሳቸውን ኸለዋ ማጽዳት ይጀምራሉ፡፡ ኸለዋው አመቱን ሙሉ ዝግ ሆኖ ስለሚቆይ እሱን በማጽዳት እና ግምጃ ቤት የተቀመጠውን የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሳቸውን ወደ ኸለዋቸው በመውሰድ በማጽዳት እና በማስተካከል ቀኑን ያሳልፋሉ፡፡ ምዕመናኑ የሚሰባሰቡት ከተለያየ ቦታ ቢሆንም በዋናነት የሚመጡት በስልጤ ዞን ውስጥ ከሚገኙ የተለያዩ ወረዳዎች ነው፡፡ ከነዚህ ወረዳዎች በተጨማሪ ከሀዲያ ዞን፣ ከቡታጀራ፣ ከአላባ ልዩ ወረዳ፣ ከዝዋይ፣ ከአዳማ፣ ከሻሸመኔ፣ ከወላይታ፣ ከአሰላ፣ ከአዲስ አበባ ወዘተ የሚመጡም አሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች ከሩቅ ቦታ ተነስተው ወደ አልከሶ መውሊድ የሚመጡት በብዛት እነሱ በሚኖሩበት አካባቢ ከሚኖሩ

የስልጤ ብሔረሰብ ተወላጆች ጋር ነው፡፡ በዚህ ሁኔታ እንጂ ለብቻቸው የአልከሶን መውሊድ ለማክበር ብለው ከሩቅ ቦታ የሚመጡ ክርስትያኖች እንደሌሉ አቶ ታደሰ[164] ይናገራሉ፡፡



ፎቶ 20፡- በአልከሶ ሀረም  የክርስትያኖች ማረፊያ ኸለዋ[165]

በመውሊድ ሰሞን አንዳንድ ከሩቅ ቦታ የሚመጡ ክርስትያን ምዕመናን ወደ ክርስትያን ኸለዋ ከመሄድ ይልቅ አብረዋቸው ከመጡ ሙስሊሞች ጋር በሙስሊም ኸለዋ ውስጥ በዓሉን ማሳለፍ የተለመደ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ለሚቆዩበት ቀን ያህል ምግብ አዘጋጅተው ስለ ሚመጡ ምግብ ለመመገብ ወደ ክርስትያን ኸለዋ በብዛት አይሄዱም፡፡ አንዳንዶቹ የሙስሊም የክርስትያን ሳይሉ ያገኙትን ሲመገቡ የተወሰኑት ደግሞ ከሀረሙ ውጭ በመውጣት ምግብ ገዝተው ይመገባሉ፡፡

ከአልከሶ መውሊድ በተጨማሪ በሀገራችን በሚከበሩ ክብረ በዓላት ላይ ክርስትያኖች እንደሚሳተፉ Yasuo and Ishihara (2009፣500) በሚከተለው ሁኔታ ያስረዳሉ፡፡ “There were also a number of Christian pilgrims coming from Gojjam and Asosa. For these pilgrims, the stew with meat was not served and they were given chicken or sheep to be slaughtered and cooked by themselves. During the daytime and in the evening.” ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በሌሎቹም በሀገራችን በሚከበሩ

164 ቃለ መጠይቅ 14/09/08

165 ፎቶ በአጥኚው 23/09/07፣ አልከሶ፡፡ ይህ የክርስትያን ማረፊያ በ2008 ዓ.ም ለመውሊድ ውጭ እና ውስጥ ክፍሉ ታድሷል፡፡

መውሊዶች በመውሊድ ሰሞን ክርስትያኖች በራሳቸው ማረፊያ ቦታ ሃይማኖታቸው በሚያዘው ሁኔታ ምግብ አዘጋጅተው እንደሚመገቡ ነው፡፡

## 8.1 የክርስትያን ምዕመናን የምግብ አዘገጃጀት እና አመጋገብ

የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የአልከሶን መውሊድ የሚያከብሩበት ኸለዋ እንዳላቸው ሁሉ የራሳቸውን ምግብ የሚያበስሉበት የምግብ ማብሰያ ቁሳቁስም አላቸው፡፡ ለበዓሉ ከተሰባሰቡ የእርድ ከብቶች መካከል አንድ ይሰጣቸዋል፡፡ የተሰጣቸውን በሬ ራሳቸው አርደው በቀይ ወጥ፣ በቅቅል እና በጥብስ መልክ ያዘጋጃሉ፡፡ ወጥ የሚሰሩበት በርበሬ፣ ዘይት፣ ሽንኩርት እና የማገዶ እንጨት ይሰጣቸዋል፡፡ እንጀራ እና የተለያዩ ዳቦዎችን ግን የመጋገሪያ ቦታ ስለሌላቸው ከሙስሊም ምግብ ማዘጋጃ ኸለዋ ይወስዳሉ፡፡ በኸለዋቸው ውስጥ በቆየሁበት ወቅት እንደተመለከትኩት በርካታ ምዕመናን የሚመጡበት ሁኔታ ካለ ተጨማሪ የሚያርዱት ነገር ይሰጣቸዋል፤ እንጅራና ዳቦ ተጨማሪ ካስፈለጋቸው ለሙስሊም ከተዘጋጅው እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል፡፡ በ16/09/2008 የመውሊድ ቀን እነዚህ ክርስትያኖች ስጋ በጊዜ ጨርሰው ለእርድ የሚሆን ወይፈን ጥየቃ ሲሄዱ ተመልክቻለሁ፡፡ ስለዚህ በአልከሶ መውሊድ የክርስትያኖች መብት ከሙስሊሞች እኩል ነው ማለት ይቻላል፡፡

በክርስትያን ኸለዋ በቆየሁበት ወቅት ምግብ ሲዘጋጅ የተመለከትኩት በወንዶች ነው፡፡ በዚህ በዓል በምግብ ዝግጅት ሴቶች የማይሳተፉት ሴቶቹ ከሩቅ ቦታ ስለሚመጡና ስለሚደክማቸው እንደሆነ ሌላ ምንም የተለየ ምክንያት እንደሌላቸው አቶ ግርማ ከተማ[166] ነግረውኛል፡፡ ወንዶች ምግብ ማዘጋጀት ብቻ ሳይሆን ከውጭ ለሚመጡ ሴት ምዕመናን ለእጅ ውሀ ከማቅረብ እስከ ምግብ ማቅረብና የተመገቡበት እቃ ማንሳት ድረስ ያለውን ስራ ይሰራሉ፡፡ ወ/ሮ ላቀች ደስታ[167] ሰኞ ጠዋት በክርስትያን ኸለዋ ውስጥ ከባለቤታቸው ጋር ምግብ ሲመገቡ ከገኘኋቸው ሴቶች መካከል አንዷ ናቸው፡፡ ወ/ሮ ላቀች "አልከስዬ ድሮም ጀምሮ ወንድና ሴት እኩል ናቸው ይሉ ስለነበረ ወንዶችም እሳቸውን ስለሚሰሙ ከእኛ ቀደም ብለው በመምጣት በሬ አርደው ምግብ ይሰራሉ፡፡ እኛም ቀስ ብለን ከኋላ መጥተን እጃችንን ታጥበን መብላት ብቻ ነው፡፡ በአልከሶ መውሊድ ወንድ ሴት የሚባል ነገር የለም፡፡" ይላሉ፡፡ በመውሊድ ሰሞን ከሙስሊም ወንዶች ይልቅ ክርስትያን ወንዶች የበለጠ ስራ ይሰራሉ፡፡

---

166 ቃለመጠይቅ 16/09/2008

167 ቃለ መጠይቅ 24/09/07

ምክንያቱም ሙስሊም ወንዶች የሚያዘጋጁት ስጋ ነክ ማባያዎችን ብቻ ነው፡፡ ክርስትያን ወንዶች ግን ማረፊያ ቤታቸውን ከማጽዳት ጀምሮ ሁሉንም ስራ ይሰራሉ፡፡

ክርስትያን ምዕመናን በዓሉን የሚያከብሩት በክርስትያን ኸለዋ ብቻ አይደለም፡፡ ከክርስትያን ኸለዋዎች ውጭ በተለያዩ የሙስሊም ኸለዋዎች የሚያከብሩም አሉ፡፡ ይህ ማለት መጀመሪያ ላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት አንዳንድ ክርስትያን ምዕመናን ወደ አልከሶ የሚሄዱት እነሱ ከሚኖሩበት አካባቢ ሙስሊሞች ጋር ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህ ክርስትያኖች አብረዋቸው የመጡ ሙስሊሞች በሚያርፉበት የሙስሊም ኸለዋ ውስጥ ያርፋሉ፡፡ እነዚህ ክርስትያኖች አንዳንዶቹ ወደ ክርስትያን ኸለዋ ሄደው ምግብ ይመገባሉ፡፡ አብላጫዎቹ ግን ከቤታቸው ሳይበላሽ ለበርካታ ቀናት የሚቆይ ምግብ አዘጋጅተው ይዘው ይመጣሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ ወደ ከተማ በመሄድ በልተው ይመጣሉ፤ አልያም እዝያው አካባቢ በጊዜያዊነት በተሰሩ ዳሶች ውስጥ ለሽያጭ የሚቀርቡ ምግቦችን ገዝተው ይመገባሉ፡፡

የአልከሶ መውሊድ የወረዳው፣ የዞኑ፣ የክልሉ እና የፌደራል መገናኛ ብዙሃን የስርጭት ሽፋን ይሰጡታል፡፡ የመውሊዱን የአከባበር ስርዓት ለመዘገብ ከሚመጡ ጋዜጠኞች መካከል የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ጋዜጠኖች ምግብ ፍለጋ ወደ ከተማ ከመሄድ ይልቅ ክርስትያን ኸለዋ በመሄድ ምግብ ይመገባሉ፡፡ በ2007 ዓ.ም የመውሊድ በዓልን ለመዘገብ አልከሶ ከተገኙ ጋዜጠኞች መካከል ጋዜጠኛ ግርማ ይገኝበታል፡፡ ግርማ ከአዲስ አበባ ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት (ኢዜአ) ለመዘገብ አልከሶ ተገኝቷል፡፡ ግርማን ያገኘሁት ክርስትያን ኸለዋ ውስጥ ምሳ ሲበላ ነው፡፡ እንደ ግርማ[168] አገላለጽ በበዓሉ ሲገኝ የመጀመሪያው ነው፡፡ ምግብ ፍለጋ ወደ ከተማ ለመሄድ ፈልጎ መንገድ ሲጠይቅ ከተማ ከምትሄድ ለምን ክርስትያኖች ጋ ሄደህ አትበላም ተብሎ ወደ ክርስትያን ኸለዋ እንደተላከ ይናገራል፡፡ አቶ ግርማ በዚህ አይነት የደመቀ የሙስሊም በዓል ላይ እንዲህ ለክርስትያንም ትኩረት ሰጥቶ ቦታና ምግብ መዘጋጀቱ ገርሞኛል የሚል ሀሳብ ከሰነዘረ በኋላ በአስተናጋጆቹ የእንግዳ አቀባበል መደስቱን ገልጾዋል፡፡ እንደ ግርማ ሁሉ በርካታ ክርስትያን ፖሊሶች፣ ጸጥታ አስከባሪዎች፣ ጋዜጠኞች እና ሹፌሮች በክርስትያን ኸለዋ ተገኝተው ምግብ ሲመገቡ እና ጫት ስቅሙ መመልከት ችያለሁ፡፡

---

[168] ቃለ መጠይቅ 24/09/07



ፎቶ 21፡- ክርስትያን ምዕመናን ጫት እየቃሙ መውሊድ ሲያከብሩ

## 8.2 የክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች መውሊድ የሚያከብሩበት ምክንያት

የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መውሊድን የሚያከብሩበት የየራሳቸው የሆነ ምክንያት አላቸው፡፡ በመሆኑም በአልከሶ መውሊድ ክርስትያኖች ለምን መውሊድን እንደሚያከብሩ የተለያዩ ጥናቶች ተካሂደዋል፡፡ ለምሳሌYasuo እና Ishihara የሀ ላይ ክርስትያኖች በሙስሊም ክብረ በዓል(መውሊድ) ላይ የሚሳተፉበት የየራሳቸው ምክንያት እንዳላቸው ያስረዳሉ፡፡ ከምክንያቶቹም መካከል በመውሊዱ በመገኘት ዱኣ በማስረደግ እና በመጸለይ ሀብት ለማፍራት፣ ጤናን ለማግኘት፣ ዘር የሌላቸው ዘር ለማግኘት፣ ከሙስሊሞች ጋር አንድነታቸውን ለማጠናከር እንደሆና ያስገነዝባሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በግብጽ፣ በታንዛኒያ፣ በማሊ፣ በህንደ፣ በቱርክ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎች በሙስሊሞች ቅዱሳን ናቸው የተባሉ ቦታዎች የተለያዩ አለማዊ እና መንፈሳዊ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በአመት በተወሰነ ጊዜ ወደ ስፍራው እንደሚሄዱ የተለያዩ ጥናቶች ያሳሉ፡፡

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በሀገራን በሚከበሩ መውሊዶች የሚሳተፉ የክርስትና እምነት ተከታዮች በመውሊድ ላይ ለመሳተፍ በርካታ ምክንያት እንዳላቸው ሁሉ በአልከሶ

መውሊድም የሚሳተፉ ክርስትያን ምዕመናን የየራሳቸው ምክንያት አላቸው። በመሆኑም ከዚህ በመቀጠል በዚህ መውሊድ ክርስትያን ምዕመናን ለምን ዓላማ ወይም ምክንያት እንደሚሳተፉ የተወሰኑ መሳያዎችን እንመለከታለን።

**ማሳያ አንድ፡- የአቶ ታደሰ ምክንያት**

አቶ ታደሰ መውሊድን መውሊድን ከሚያከብሩ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች መካከል አንዱ ናቸው። እኚህ መውሊድ አክባሪ መውሊድን እንዴት እና በምን ምክንያት ማክበር እንደጀመሩ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> እኔ መውሊድ ማክበር የጀመርኩት ገና በስድስት አመቴ ነው። በህጻንነቴ በጣም ታማሚ ነበርኩኝ አሉ። አባቴ እኔን ለማሳከም ያልሄዱበት ሀኪም እና አዋቂ ቤት የለም። ግን ማንም ከበሽታዬ ሊፈውሰኝ አልቻለም። አባቴ እና እናቴ በስተርጅና ያገኙኝ አንድ ልጃቸው ስለሆኑኩኝ ሊሞትብኝ ነው ብለው በጣም ተረበሹ። በየሄዱበትም በእስተርጅና ያገኘነው አንድ ልጅ ሊሞትብን ነው ብለው መናገር ጀመሩ። አባቴ አንድ ቀን ከአንድ ሰውዬ ጋር ገበያ ሄደው ሲመለሱ ስለሁኔታው ለሰውየው አጫወቱት። ሰውየውም ካዳመጣቸው በኋላ አልከሶ በሚባል ቦታ አልከስዬ የሚባሉ የታመመን የሚያድኑ ሰውዬ አሉ ብዙ ሰው በሀኪም ለፍቼ ደክሜ ያላገኘሁትን ፈውስ እሳቸው ጋ አግቻለሁ ሲሉ ሰምቻለሁ እስኪ እዚያ ሞክርለት አሉት። አባቴም ወደ አልከስዬ በመሄድ ስላጋጠመው ችግር ነገራቸው። እሳቸውም ዋናው የመውሊድ ጊዜ ልጁን ይዘህው ና አሉት። እሱም በተባለው መሰረት የመውሊድ በዓሉ በሚከበርበት ወቅት እኔን ይዞኝ ሄደና ለአልከስዬ አሳዩኝ። አልከስዬም ቁርአን ከቀሩ እና ዱኣ ካደረጉብኝ በኋላ በእጃቸው ምራቃቸውን ትፍ ትፍ ብለው ሙሉ ሰውነቴን አሹኝ። ከዚያ ቀን ጀምሮ ከበሽታዬ ተፈወስኩኝ፤ አባቴም በጣም ደስ አላቸው። እስካሁንም ድረስ ምንም አይነት ህመም ይዞኝ አያውቅም። ይህ የሆነው በስድስት አመቴ ነው። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ አባቴ በህይወት በነበሩበት ወቅት ሁሌም ይዘውኝ ይመጡ ነበር። አሁን እድሜዬ ወደ ስልሳ ስምንት እየተጠጋ ነው። ከስድት አመቴ ጀምሮ መውሊድ ቀርቼ አላውቅም።[169]

[169] ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰ፣ 23/09/07

ከአቶ ታደሰ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አቶ ታደሰ የአልከሶን መውሊድ የሚያከብሩት ምክንያት በልጅነታቸው በበሽታ ይሰቃዩ እንደነበረ እና በመውሊድ ቦታ ተገኝተው ዱኣ ተደርጎላቸው ከህመማቸው በመፈወሳቸው የተነሳ ከልጅነታቸው ጀምሮ እስካሁንም እንደሚያከብሩ ነው፡፡

**ማሳያ ሁለት፡- የአቶ ደነቀ ተፈራ ምክንያት**

ሌላው በቦታው ሽለዋ ሲያጸዱ እና ምግብ ሲያዘጋጁ ያገኘኋቸው አቶ ደነቀ ተፈራ መውሊድን ለረጅም ጊዜ ማክበራቸውና ምንም ምክንያት ቢያጋጥማቸው የአልከሶን መውሊድ እንደማይቀሩ አጫውተውኛል፡፡ አቶ ደነቀ ተፈራ ደግሞ ለአልከሶ መውሊድ ከፍተኛ የሆነ ፍቅርና አክብሮት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ እኚህ መረጃ አቀባይ አያይዘውም አንድ ዘመን ላይ ያጋጠማቸውን ክስተትም እንደሚከተለው አጫውተውኛል፡፡ አንድ ዘመን ላይ የአልከሶ መውሊድ በሚከበርበት ወቅት አባታቸው በጣም ይታመማሉ፡፡ የአጋጣሚ ነገር ሆነና ዋናው የአልከሶ መውሊድ በሚከበርበት ቀን ይሞታሉ፡፡ አቶ ደሳለኝ በዚህ ጊዜ "ቀርቼ የማላውቀውን መውሊድ እንዴት እቀራለሁ" በማለት ግራ ይገባቸዋል፡፡ ለቅሶ ቢሆንም "አልቀርም በማንኛውም ሰአት ቢሆን ደርሼ እመጣለሁ" ብለው ይወስናሉ፡፡ አባትየው ወደ ስድስት ሰአት አካባቢ ከተቀበሩ በኋላ "ወደ ከተማ ሄጄ አንዳንድ እቃዎችን ገዝቼ እመጣለሁ" በማለት ወደ አልከሶ መውሊድ በመሄድ ለተወሰነ ሰዓትም ቢሆን በዓሉን አክብረው እንደተመለሱ ያስታውሳሉ፡፡ አቶ ደሳለኝ "ወደ ፊትም ቢሆን በህይወት እስካለሁ ድረስ አልቀርም፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን ሁሉም የእኛ አካባቢ ክርስትያኖች እንደሱ ነው የሚያስቡት" ይላሉ፡፡

ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው እነዚህ ክርስትያኖች ለአልከሶ መውሊድ እና ለአልከስዬ ልዩ ክብር እና ፍቅር እንዳላቸው ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ምዕመናን በህይወት ዘመናቸው ትልልቅ ጉዳዮች ቢያጋጥማቸው እንኳን ከአልከሶ መውሊድ እንደማይቀሩ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በሀገራችን ሁለቱ ሀይማኖቶች ምን ያህል ቁርኝት እንዳለቸው የሚያሳይ ነው፡፡ ነገር ግን ሁሉም ክርስትያን ምዕመናን ወደ አልከሶ መውሊድ የሚሄዱት ለመውሊድ እና ለአልከስዬ ልዩ ፍቅር ስላላቸው ብቻ ሳይሆን ከራሳቸው ጋር በተየያዘ በዓላማዊም ሆነ በምድራዊ ህይወታቸው አንዳች ፋይዳ ለማግኘት በማሰብ ነው፡፡ እነዚህ ሰዎች ወደ አልከሶ የሚሄዱት ስለ ቦታው ሌሎች ሰዎች ሲናገሩ ሰምተው አሊያም "በህልሜ" መጣብኝ በሚል ምክንያት

ነው። የዚህ አይነት ሁኔታ በሀገራችን በሚከበሩ መውሊዶች ላይ እንዳሉ በዚህ ጥናት የዳሰስኳቸው ጥናቶች ያሳያሉ።

**ማሳያ ሶስት፡- የአቶ ግርማ ከተማ ምክንያት**

ክርስትያኖች የእስልምና ሀይማኖት ተከተይ ሳይሆኑ በአልከሶ መውሊድ ከሙስሊሙ ማህበረሰብ እኩል ይሳተፋሉ። ሙስሊም ሳይሆኑ ለምን መውሊድ እንደሚያከብሩ የተለያየ ምክንያት ያቀርባሉ። አቶ ግርማ ከተማ የቡታጅራ ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ መውሊዱን ሲያከብሩ ከአገኘኋቸው ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች መካከል አንዱ ናቸው። አቶ ግርማ ክርስትያን ሆነው ለምን መውሊድን ያከብራሉ ለሚለው ጥያቄ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል።

> አባቴ ትዳር ከያዘ አስራ አራት አመት ያህል ቢቆይም ልጅ መውለድ አልቻለም። በመሆኑም በሌላ ሴት ለመሞከር ሌላ ሴት ከሶዶ ያመጣል። አዲስ ያመጣትም ሚስት ስድስት ወር ያህል አብራው ብትቆይም ማርገዝ አልቻለችም። በዚህ ጊዜ ለችግር ሁሉ መፍትሄ ይሰጣሉ ወደ ሚባሉት ሳዳት(የአልከስዬ ልጀ ናቸው) ጋር ጫትና አዲሷን ሚስቱን ይዞ በመሄድ ያጋጠመውን ነገር አስረዳቸው። እሳቸውም ጫቱን በመፍታት ዱኣ ካደረጉ በኋላ እንካ ጫቱን ወስደህ ስጣት በማለት ሰጡት። ሴት ዋና መስጂድ ስለማይገባ እሷ አልቀረበችም ነበር። እሱም በተባለው መሰረት ጫቱን ሰጧት ቃመችው። ይህ በሆነ በሰባት ወሩ ያቺ ሴት እኔን ተገላገለች። እኔም በአልከሶ መውሊድ ዱኣ የተገኘሁ ስለሆንኩኝ የአልከሶን መውሊድ ለማክበር ሁሌም በየ አመቱ እመጣለሁ። አንድ ጊዜ ለስራ ጉዳይ ወደ ከሚሴ ሄጄ እያለሁ መውሊዱ የሚከበርበት ወቅት ደረሰ። ወደዚህ ለመምጣት አለቃዬ ከለከለኝ። እኔም ከፈለገ ስራው ይቅር እንጂ አልቀርም ነገ እሄዳለው ብዬ ወሰንኩ። ያጋጣሚ ነገር ሆነና ፈይድ ማታ በህልሜ መተው እየሳሙ ናፍቆቱ ወጣልህ እንዴ እያሉ አናገሩኝ። ጠዋቱን ህልሜን ለአንድ ሴትዮ ስነገራት እንዲ ከሆነማ ቦታው ድረስ እንደሄድክ ይቆጠርልሀል ብላኝ ቀርቻለሁ።[170]

ከአቶ ግርማ ሀሳብ መረዳት የሚቻለው አልከስዬ እና እሳቸውን ተክተው መስጂዱን ያስተዳደሩ መሪዎች ዱአ ያደረጉበት ጉዳይ ስኬታማ እንደሚሆን እና ክርስትያን ምዕመናን

[170] ቃለ መጠይቅ፣ 24/10/ 2007

እንደሚያምኑባቸው ነው፡፡ እንዲሁም አብላጫ ክርስትያኖች ወደ አልከሶ መውሊድ የሚሄዱት ለመዝናናት አስበው ብቻ ሳይሆን አንዳች አለማዊም ሆነ መንፈሳዊ ጠቀሜታ አገኛለሁ በማለት ነው፡፡ ለዚህ ሀሳብ ማጠናከሪያ የሚሆነው የአቶ ታደሰ ታዬ እና የአቶ ደሳለኝን ሀሳብ ማየት ይቻላል፡፡ እነዚህ ሁለት ክርስትያን ምዕመናን የስልጢ ወረዳ ነዋሪዎች ሲሆኑ በተለያየ ጊዜ ራሳቸውና ልጆቻቸውን የተለያየ አይነት በሽታ ያጠቃቸው እንደነበረ እና የአልከሶ መውሊድ በመሄድ ማክበር እና ዱአ ማስደረግ ከጀመሩ በኋላ እነሱም ሆነ ልጆቻቸው ከተለያዩ በሽታዎች ነጻ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

**ማሳያ አራት፡- የወ/ሮ መሰረት ምክንያት**

ወ/ሮ መሰረት ሻሽመኔ ኸለዋ ውስጥ ሚያዝያ 24/2007 ዓ.ም ካገኘኋቸው ክርስትያን የአልከሶ መውሊድ አክባሪዎች ውስጥ አንዷ ናቸው፡፡ ወ/ሮ መሰረት እንደነገሩኝ ከሆነ መኖሪያቸው ሻሽመኔ ሲሆን ወደ መውሊድ የሄዱት ከጉረቤታቸውን ከወ/ሮ ማይሙና ጋር ነው፡፡ ወ/ሮ መሰረት በዚህ በዓል ሲሳተፉ ለሁለተኛ ጊዜ ነው፡፡ ወ/ሮ መሰረት በዚህ በዓል መሳተፍ እንዴት እንደጀመሩ ሁለት ዓመታትን ያህል ወደ ኋላ በትዝታ በመሄድ እንደሚከተለው ተርከውልኛል፡፡

> የዛሬ ሁለት አመት አካባቢ በህልሜ አንድ ትልቅ ጭንቅላታቸው ላይ ነጭ ሻሽ የጠቀለሉ ሰውዬ በሬን አንኳኩ፡፡ እኔም ማነው ብዬ ተነስቼ ከፈትኩላቸው፡፡ እሳቸውም በር ላይ ቆመው “ባልሽን ባሁኑ ጊዜ ሰይጣን ሊያሳስተው ነውና በደንብ ጠብቂው” አሉኝ፡፡ በወቅቱ ባለቤቴ ለስራ ጉዳይ ሌላ ቦታ ሄዶ ስለነበረ ምን ነካው ብዬ ደንግጬ ምን ሆነ ብዬ ስጠይቃቸው “ለጊዜው ምንም አልሆነም ሲመለስ ግን አደራ በደንብ ጠብቂው” ብለውኝ ከአጠገቤ ተሰወሩ፡፡ እኔም ከእንቅልፌ ብንን ስል ማንም የለም፡፡ ደንግጬ አማትቤ ተመልሼ ተኛሁኝ፡፡ ይህን ህልም ባየሁኝ ሁለተኛ ቀን ባለቤቴ ለስራ ከሄደበት ሀገር ተመለሰ፡፡ የተወሰነ ቀናትን ከቆየ በኋላ በምን ምክንያት እንደሆነ በማይታወቅ ሁኔታ ራሱን አጠፋ፡፡ በዚህ ጊዜ ያኔ በህልሜ መተው ሰውየው የነገሩኝ ነገር ለሰው ባለመናገሬ እና ባለቤቴን በደንብ ባለመጠበቄ በጣም ተጸጸትኩ፡፡ ለቅሶ ለመድረስ ለመጡ ሰዎች ያጋጠመኝን ህልም ስነግራቸው ከለቀስተኞቹ መካከል አንድ ሙስሊም ስትዮ “በህልምሽ መተው ጉዳዩን የነገሩሽ ስልጤ ሀገር ውስጥ የነበሩ ትልቅ አልከስዬ የሚባሉ ወልይ ድሮ ነበሩ፡፡ እሳቸው የሚወዱትን ሰው በህልም እየመጡ እንዳንቺ ያናግራሉ” አለችኝ፡፡

እኔም ይህን ከሰማሁ በኋላ ስለሳቸው አጠያይቄ ሁኔታውን ካጣራሁ በኋላ ወደ ዚህ ከሚመጡ ሰዎች ጋር መምጣት ጀመርኩ፡፡ እዚህ ከመጣሁ በኋላ የእኔ አይነት ታሪክ ያላቸው ሰዎቸ አጋጥመውኛል፡፡[171]

**ማሳያ አምስት፡- የአቶ ማሙሽት ምክንያት**

ሻሸመኔ ኸለዋ ውስጥ ጫት ሲቅሙ የገኘኋቸው እና ከወላይታ ሶዶ ከተማ የመጡት አቶ ማሙሸት አንዱ ናቸው፡፡ አቶ ማሙሸት[172] እንደነገሩኝ የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ ሲሆኑ ወደ አልከሶ መውሊድ ሲመጡ ለሁለተኛ ጊዜ ነው፡፡ አቶ ማሙሸት ወደ አልከሶ መውሊድ የመጡት አብሯቸው ከሚሰራው የአካባቢው ተወላጅ ከሆነው ወጣት ሱልጣን ጋር በመሆን ነው፡፡ ወደ አልከሶ ለመሄድ ያነሳሳቸው ጉዳይ ወጣት ሱልጣን በየአመቱ ወደ አልከሶ መውሊድ ደርሶ ከተመለሰ በኋላ ስለ በዓሉ ድምቀት እና አልከስዬ ስለሚፈጽሙት ልዩ የሆነ ነገር ሲናገር ደጋግመው መስማታቸው ቀልባቸውን እንደገዛው ይናገራሉ፡፡ እሳቸውም በበዓሉ በመገኛታቸው ልዩ የሆነ ደስታ እንደፈጠረባቸው አስረድተው "ካሁን በኋላ በጣም አስቸጋሪ ጉዳይ ካልገጠመኝ በስተቀር አልከሶ በየአመቱ አልቀርም" ብለዋል፡፡ አቶ ማሙሸት ምግብ ለማግኘት ተሳፍረው ወደ ከተማ በቀን አንድ ጊዜ በመሄድ ምግብ እንደሚመገቡ እና ለሌላ ጊዜም የሚሆናቸውን ምግብና ውሀ ገዛዝተው እንደሚመለሱ ያስረዳሉ፡፡ እንደ አቶ ማሙሸት አገላለጽ በሀረሙ ዙርያ የሚሸጡ ምግቦች እና መጠጦችን የማይጠቀሙት ንጽህናቸው በሚገባ አይጠበቅም ከሚል ስጋት የመነጨ ነው፡፡ እንዲሁም በክርስትያን ኸለዋ የሚዘጋጁ ምግቦች ሲዘጋጅ ሄደው መመልከታቸውና ምግቦቹ የሚዘጋጁበት ቦታ እና ቁሳቁሶቹ ምግቡን ለመመገብ የሚጋብዝ እንዳልሆነ ይናገራሉ፡፡ እኔም እንደተመለከትኩት ኸለዋው አመቱ ሙሉ ተዘግቶ ስለሚከርም ውስጡ ሲገባ ምግብ ለመመገብም ሆነ ለረጅም ጊዜ ለመቆየት አይጋብዝም፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ ከተመለከትናቸው ማሳያዎች መረዳት የሚቻለው በአልከሶ መውሊድ የሚሳተፉ የክርስትና ሃይማኖት መውሊድ አክባሪዎች በመውሊድ የሚሳተፉበት የየራሳቸው ምክንያቶች እንዳሏቸው ነው፡፡ ከነዚህም መካከል አንዳንዶቹ በመውሊድ ሰሞን ዱኣ ተፈርጎላቸው ከበሽታ የተፈወሱ ሲሆኑ የተወሰኑት ደግሞ ስለአልከስዬ ሙስሊሞች ሲናገሩ

[171] ቃለ መጠይቅ፣ 25/10/07፣ አልከሶ
[172] ቃለ መጠይቅ 25/10/07

በመስማታቸው ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ የተለያዩ አለማዊ ጠቀሜታዎችን ለማግኘት በመሆኑ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል፡፡

## 8.3. በመውሊድ የሙስሊሞች እና የክርስትያኖች ተመሳስሎ

በአልከሶ ሀረም ውስጥም ክርስትያኖች የሙስሊም የአለባበስ ስርዓት የሚከተሉ መኖራቸውንም ተመልክቻለሁ፡፡ ለምሳሌ በክርስትያን ኸለዋ ውስጥ ለክርስትያን ምዕመናን ምግብ ሲያቀርቡ ያገኘኋቸው አቶ ታደሰ ታዬ የሙስሊም ኮፍያ አድርገው ነበር፡፡ አቶ ታደሰ ክርስትያን ሆነው እንዴት የሙስሊም ኮፍያ ሊያደርጉ እንደቻሉ ስጠይቃቸው "እኔ ሙስሊም አይደለሁም የመንዝ አማራ ክርስትያን ነኝ፡፡ ድሮ አባቴ እዝህ መተው ወልደውኝ ነው፡፡ እኛ ሀገር ሙስሊም ክርስትያን የሚባል ነገር የለም፡፡ የተመቸንን ነው የምንለብሰው፡፡ልጆቻችንም ቢሆኑ ትምህርት ቤትም ሆነ የት ሲሄዱ እንደ ሙስሊም ልጆች ነው የሚለብሱት እኛ ከእነሱ የምንለየው በስጋ ብቻ ነው" የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡ እነዚህ ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች ምግብ ከበሉ በኋላ የሚያመሰግኑት አልከስዬን እና አላህን ነው፡፡ ክርስተያኖች በንግግራቸው መሀል "አለሀምዱሊላሂ"፣ "አላህ ካለ"፣ "ኢንሻአላህ" የመሳሰሉ የአረብኛ ቃላትን ስለሚጠቀሙ ሙስሊም ይመስላሉ፡፡

ምግብ ለመመገብ ወደ ክርስትያን ከለዋ የሚመጡ ክርስትያን ልጆች እና አዋቂ ሴቶች አለባበስ በአካባቢው ከሚኖሩ ሙስሊም ማህበረሰብ ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ እነዚህን ክርስትያን ምዕመናን በአለባበስም ሆነ በአነጋገር ከአካባቢው ሙስሊሞች ጋር ተመሳሳይ ናቸው፡፡ በመሆኑም ክርስትያን መሆናቸውን በምንም መለየት አይቻለም፤ ምናልባት በአንገታቸው ማህተብ ካሰሩ በእሱ ልንለያቸው እንችላለን፡፡ ከሌላ ቦታ የመጡትም ሆነ እዝያው ተወልደው ያደጉ ክርስትያኖች የአካባቢውን ሙስሊሞች ባህል፣ ወግ እና ስርዓት በሚገባ ተላምደውት ሁኔታቸው ሁሉ ሙስሊም ይመስላሉ፡፡ ለዚህ ማሳያ አንድ ምሳሌ ላቅርብ፡፡ በአልከሶ መውሊድ በዓል ላይ ሲጫወቱ ከተመለከትኳቸው ልጆች መካከል አንዱ በአንገቱ ማህተብ አስሯል፡፡ ነገር ግን ሲምል እግዝአብሔርን ወይም ማርያምን ወዘተ ከማለት ይልቅ ወላሂ ይላል፡፡ አቶ ታደሰ በጭቅላታቸው ላይ የሙስሊም ኮፍያ በአንገታቸው ደግሞ የክርስትና ሃይማኖት መገለጫ የሆነውን ጥቁር ክር (ማተብ) አስረው የሙስሊሞችን የመውሊድ በዓል ያከብራሉ፡፡



ፎቶ 22፡- አቶ ታደሰ ታዬ የሙስሊም ኮፊያ ለብሰው መውሊድ ሲያከብሩ [173]

ይህ የሚያሳየው በአካባቢው የሁለቱ ሃይማኖት (እስልምና እና ክርስትና) ተከታዮች ምን ያህል ተከባብረው እና አብረው እንደሚኖሩ ነው፡፡ ይህ ተከባብረው አብሮ መኖራቸው አልፎ አልፎ ትዳር መስርተው እንዲኖሩ አድርጓል፡፡ ለምሳሌ በ2007 ዓ.ም የመውሊድ በዓልን ለመመልከት ወደ ስፍራው በሄድኩበት ወቅት ያረፍኩበት ቤት ውስጥ አንዷ ልጅ ሙስሊምና የሙስሊም ቤተሰብ ልጅ ሆና እያለ ክርስትያን አግብታ አንድ ወንድ ልጅ ወልዳለች፡፡ ምንም እንኳን ክርስትያን አግብታ ሩቅ ቦታ ብትሄድም የአልከሶን መውሊድ ለማክበር ለዋናው በዓል ሁለት ቀን ሲቀረው አልከሶ ቤተሰቦቿ ጋር ተገኝታለች፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አቶ ደሳለኝ የመጀመሪያ ሚስታቸው ክርስትያን ስትሆን ሁለተኛ ሚስታቸው ደግሞ ሙስሊም እንደሆነች ይገልጻሉ፡፡ አቶ ታደሰ ደግሞ አንድ ሴት ልጃቸው ሙስሊም ለማግባት እንደምትፈልግ ስትጠይቃቸው “አንቺ ካመንሽበት መብትሽ ነው” ብለው እንደፈቀዱላት አስረድተው ልጃቸው ሙስሊም ባል አግብታ በአሁኑ ጊዜ የሁለት ልጆች እናት እንደሆነች ገልጸዋል፡፡

173 ፎቶ ባጥኚው፣ 24/09/07 አልከሶ- ክርስትያን ኽለዋ

መስጂድ ውስጥ ከሙስሊሞች እኩል ጫት የሚቅሙ እና መንዙማ የሚሉ ክርስትያኖችም አጋጥመውኛል፡፡ አቶ ክፍሌ ዋናው የአልከሶ መውሊድ በሚከበርት እለት እሁድ ቀን በዙሀር ሷላት ወቅት ከዋናው መስጂድ ሲወጡ እኔ ደግሞ ለመስገድ ስገባ ተገጣጠምን፡፡ በዚህ ጊዜ "ምንን ኢለሰግዲ ኢንዶ" (ምነው አይሰገድም እንዴ) አልኳቸው አቶ ክፍሌም[174] "ኢኘ በሰላቲ ኤለነቢ" (እኛ በሰላቱ የለንበትም) የሚል ምላሽ ሰጡኝ፡፡ ነገሩ ግራ ሆኖብኝ እንዴት ብዬ ብጠይቃቸው "እኔ ክርስትያን ነኝ እዚህ የገባሁት ከቤቴ ጫት ይዤ በመምጣት ዱአ ለማስደረግ ነው፡፡ በየአመቱ ጫት ይዤ በመምጣት እዚህ ውስጥ ዱኣ አስደርጋለሁ፡፡ ከሙስሊሞች እኩል ተጣጥቤ ጫት እቅማለሁ ነሺዳም እላለሁ፡፡ ልክ አዛን ሲል ግን ስለማልሰግድ ወጥቼ ከተሰገደ በኋላ ተመልሼ እገባለሁ፡፡ እኔ ብቻ ሳልሆን ብዙ ክርስትያኖች እንደሱ ያደርጋሉ፡፡ እንዳለ ቀደም ብለው ወጥተዋል፡፡ እኔ ጥግ ስለነበርኩ ነው ቶሎ ያልወጣሁት" የሚል ምላሽ ሰጥተውኛል፡፡

እነዚህ ክርስትያን ምዕመናን በዓሉን በደመቀ ሁኔታ ሲያከብሩ እስከ ሰኞ ምሽት ድረስ ይቆያሉ፡፡ የተወሰኑት ግን በዓሉን ባከበሩ በነጋታው ወደ መጡበት ቦታ ይመለሳሉ፡፡ የተወሰኑት ግን "ስልስላ"[175] እስከሚከበር ድረስ ይቆያሉ፡፡ የኮሚቴው አባላት ግን ስልስላው ከወጣ በኋላ በቦታው በመቆየት ኸለዋውን ያጸዳሉ፤ ምግብ ያዘጋጁበት እና የተመገቡበት ቁሳቁስ ለእቃ ግምጃ ቤት በመመለስ ለሚቀጥለው አመት በሰላም ያገናኘን በማለት ተመራርቀው ይለያያሉ፡፡

ሙስሊም ምዕመናን መውሊድ ለሚያከብሩ ክርስትያን ምዕመናን ጥሩ አክብሮት እና አመለካከት አላቸው፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ክርስትያኖች በአልከሶ መውሊድ መሳተፍ የጀመሩት መውሊዱ መከበር ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ምንም አይነት ችግር ሳያጋጥማቸው ከሙስሊም እኩል የሚበላ እና የሚጠጣ ነገር ተሰጥቷቸው በዓሉን እስካሁንም ድረስ በደመቀ ሁኔታ እንደሚያከብሩ አቶ ታደሰ[176] ያስረዳሉ፡፡

---

[174] ቃለ መጠይቅ 24/09/07

[175] ቀደም ባለው ምዕራፍ እንደተመለከትነው "ሲልስላ" ማለት በዓሉ እሁድ ተከብሮ በሶስተኛው ቀን ማክሰኞ እለት ለመሰነባበቻነት የሚዘጋጅ ልዩ ዝግጅት ነው፡፡ አብላጫ ምዕመናንም ወደ የመጡበት መሄድ የሚጀምሩት ከስልስላ በኋላ ነው፡፡

[176] ቃለ መጠይቅ 14/09/07

አቶ ግርማ ሙስሊሞች ለእነሱ ጥሩ አመለካከት እንዳላቸው እና በየመሀሉ እየተመላለሱ “አትቦዝኑ ተጫወቱ” እያሉ እንዳይከፋን ያደርጋሉ ይላሉ፡፡ እኔም ቦታው ላይ በነበርኩበት ወቅት የተወሰኑ ወንዶች እና ሴቶች ክርስትያኖች እንዳይቦዝኑ በማለት በክርስትያን ኸለዋ ውሰጥ ከክርስትያኖች ጋር ቡና ሲሰጡ እና ጫት ስቅሙ መመልከት ችያለሁ፡፡ አቶ ኡመር መውሊድን ለማክበር ከአሊቾ ዊሪሮ የመጡ ሲሆን እሁድ ማታ በዓሉን ያከበሩት ክርስትያን ኸለዋ ውስጥ ጫት በመቃም ነው፡፡ አቶ ኡመር የሙስሊም ኸለዋ እያለ የክርስትያን ኸለዋን የመረጡበት ምክንያት ሲናገሩ “አንደኛ እኔን ተከትሎ የመጣ ክርስትያን ጓደኛዬ እዚህ ስላለ እሱ ይቦዝናል በማለት ነው፡፡ ሁለተኛ የሙስሊም ኸለዋ ግርግር ይበዛበታል፡፡ እዚህ ግን ምንም ግርግር የለም” የሚል ሀሳብ አቅርበዋል፡፡ ከዚህ ሁኔታ መረዳት የሚቻለው ሙስሊሞች ለክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች ጥሩ አመለካከት እንዳለቸው ነው፡፡ ምክንያቱም የተወሰኑ ሙስሊም ምዕመናን የራሳቸው ማረፊያ ቦታ እያላቸው በክርስትያን ኸለዋ ውስጥ በዓሉን ያሳልፋሉ፡፡ ብዙሃን ክርስትያኖችም ከሩቅ ቦታ ስለሚመጡ በአልከሶ መስጂድ አካባቢ የሚኖሩ ሙስሊሞች አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያቀርቡላቸዋል፡፡

አቶ ሲራጅ ነዋሪነታቸው ዳሎቻ ወረዳ ሲሆን ላለፉት አርባ አመታት አንድም ጊዜ ሳያቋርጡ የአልከሶ መውሊድን ያከበሩ የእድሜ ባለጸጋ ናቸው፡፡ አቶ ሲራጅ[177] ስለ ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች ሲናገሩ

> እነሱ እኮ ክርስትያን ናቸው ማለት አይቻልም ሙስሊም በላቸው፡፡ እነሱ አይሰግዱም እንጂ ሁል ነገራቸው የሙስሊም ነው፡፡ መስጂድ ውስጥ ይገባሉ፡፡ ጫት ይቅማሉ፡፡ ለዱኣ ገንዘብ ሲዋጣ ያዋጣሉ፡፡ ዱኣ ሲለመን አሚን ይላሉ፡፡ እኔ መውሊድን ማክበር ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ አዚህ ቀርተው አያውቁም፡፡ አልከስዬን በጣም ነው የሚወዷቸው፡፡ ብዙ ሙስሊሞችም መውሊዱን እነሱ ኸለዋ ውስጥ ያከብራሉ፡፡

ይህ የሚያሳየው የአልከሶ መውሊድ የሙስሊሞች ክብረ በዓል ቢሆንም የክርስትያኖችም በደመቀ ሁኔታ እንደሚያከብሩት ነው፡፡

177 ቃለ መጠይቅ 23/10/2007

እንደ አቶ ግርማ[178] አገላለጽ ለእነዚህ መውሊድ አክባሪ ክርስትያኖች በድሮ ጊዜ ፈይድ(የአልከስዬ የልጅ ልጅ እንደሆኑ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ) አቅመ ደካማ ከሆኑ ወደ መጡበት መመለሻ ብር ይጥዋቸው ነበር፡፡ ነገር ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ይሄ እርዳታ ቀርቷል፡፡ በድሮ ጊዜ አባባ እኛን እሳቸው ጋር በማስጠራት አትቅሩ እናንተ የያዛችሁት በላ እኮ ቀላል አይደለም ይሉን ነበር በማለት ያስረዳሉ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በድሮ ጊዜ ለክርስትያን ምዕመናን የመጓጓዣ ገንዘብ ይሰጣቸው እንደነበር አቶ ሁሴይኒ እና ገራድ ኑርሰቦ በመግለጽ የአቶ ግርማን ሀሳብ ያጠናክራሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በመውሊድ ድሮ ይተገበር እንደነበረ እና በአሁኑ ወቅት ከቀሩ ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው፡፡

ባጠቃላይ እነዚህ ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች የአልከሶ መውሊድን እንደ ሙስሊም የራሳቸው በዓል እንደሆነ ያከብሩታል፡፡ በበዓሉ ከመሳተፋቸው በተጨማሪ ለመውሊዱ ለሚወጣው ወጪ አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ያዋጣሉ፡፡ የዚህ አይነት እስላማዊ ክብረ በዓል ላይ የሙስሊሞች እና የክርስትያኖች መልካም መስተጋብር መኖሩን Gemechu (2007፣89) በአርሲ ኦሮሞ ዘንድ በሰፊው በሚከበረው ፈረቀሳ ላይ ባካሄደው ጥናት ገልጸዋል፡፡ ባጠቃላይ በአልከሶ ሀረም  የክርስትያን ኸለዋ መኖሩን ቀደም ብዬ ገልጫለሁ፡፡ ክርስትያን መውሊድ አክባሪዎች የየራሳቸው ምክንያት ቢኖራቸውም በአካባቢው ለመውሊድ ገንዘብ ሲዋጣ ያዋጣሉ፤ መውሊድንም በደመቀ ሁኔታ ያከብራሉ፡፡

ባጠቃላይ በአልከሶ መውሊድ ሰሞን በሙስሊሞች እና በክርስትያኖች መካከል ያለው መስተጋብር ከዚህ በላይ የተመለከትነው ይመስላል፡፡ የእነዚህ ሁለት የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ማህበረሰቦች ከመውሊድ ሰሞን ውጭ ያላቸው ግንኙነት ምን ይመስላል የሚለውን መመልከት ያስፍልጋል፡፡ እነዚህ ማህበረሰቦች በመውሊድ ጊዜ ያላቸው ግንኙነት ይህን ከመሰለ ከበዓሉ በፊት እና በኋላ ያላቸው ግንኙኘትስ ምን ይመስላል የሚለውን በአጭሩ እንመልከት፡፡

በአልከሶ እና አካባቢው የሚኖሩ ሙስሊም እና ክርስትያን ማህበረሰቦች ከመውሊድ በፊትም ሆነ በኋላ ልክ እንደ መውሊድ ሰሞን ተሳስበው እና ተከባብረው ይኖራሉ፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ማህበረሰቦች እርስ በእርስ ተጋብተው እና ተዋልደው በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ

178 ቃለ መጠይቅ 23/10/2007

በተጨማሪ አቶ ሲራጅ[179] እና አቶ ታደሰ[180] እንደነገሩኝ የሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች በተለያዩ ማህበረዊ ጉዳዮች እንደ እድር፣ እቁብ፣ የደቦ ስራ ወዘተ በጋራ ይሳተፋሉ። እንዲሁም ክርስትያኖች መስጂድ ወይም መድረሳ በአካባቢያቸው ሲሰራ እንደ ማንኛውም ሙስሊም ቁሳቁስ በማዋጣትም ሆነ በጉልበታቸው ያግዛሉ። ስለዚህ የአልከሶ መውሊድ የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች የሚሳተፉበት በመሆኑ ሰላም የሰፈነበት ክብረ በዓል ነው ማለት ይቻላል። ምክንያቱም በመውሊዱ የተለያየ ሃይማኖት ያላቸው ሰዎች በነጻነት ይሳተፋሉ። ከመሳተፍም ባሻገር እኩል መዋጮ ያዋጣሉ። መውሊድ እስላማዊ መሰረት ቢኖረውም የአልከሶ መውሊድ ግን የሙስሊሞች ብቻ አይደለም ማለት ይቻላል። ይህ ሁኔታ የአልከሶ እና የአካባቢው ማህበረሰብ ከመውሊድ በፊት፣ በመውሊድ ሰሞን እና ከመውሊድ በኋላ ጥሩ የሚባል ግንኙነት እንዲኖራቸው ማድረግ ችሏል። ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እርስ በእርስ ተዋደው፣ ተጋብተው እና ተዋልደው እንደሚኖሩ ቀደም ብለን ተመልክተናል።

ይህ የሚያሳየው በአካባቢው በሁለቱ ሀይማኖቶች መካከል መተሳሰብ እና መከባበር መኖሩን ነው። ይህ መተሳሰብ እና መከባበር በአካባቢው ብሎም በሀገራችን ሰላምና ልማት ላይ ትልቅ አዎንታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። ምክንያቱም እነዚህ ሁለት የተለያየ ሀይማኖት የሚከተሉ ምዕመናን የማይተሳሰቡ እና የማይከባበሩ ቢሆን ኖሮ አይደለም በዚህ ሁኔታ ተሰብስበው የአንዱን በዓል አንዱ ሊያከብር ቀርቶ በሆነ ባልሆነ ጉዳዮች እየተጋጩ የአካባቢውን ሰላም ሊያደፈርሱ ይችላሉ። ሰላም ከሌለ ደግሞ በአካባቢው ሰላማዊ በሆነ ሁኔታ የልማት እቅስቃሴ ማካሄድ አዳጋች ይሆናል። በመሆኑም በአካባቢው ሰላም ኖሮ ልማቱ በአግባቡ ካልተሳለጠ ድህነት ይንሰራፋል። የዚህ አይነት ሁኔታ በአንድ አካባቢ መኖሩ የሚጎዳው አካባቢው ብቻ ሳይሆን ሀገሪቱንም ጭምር ነው። ምክንያቱም ችግር ያለበት አካባቢ በድርቅ ሊመታ ወይም የምግብ እጥረት ሊከሰት ይችላል። ይህ በሚሆንበት ጊዜ መንግስት ለሌላ ጉዳይ ማዋል የሚገባውን ገንዘብ እነዚህ ሰዎች ለመርዳት ስለሚያውለው በሀገር እኮኖሚ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ይኖረዋል። በተቃራኒው በአካባቢው ሰላም ኖሮ ልማቱ በአግባቡ የሚከናወን ከሆነ ግን ከዚህ በላይ የተገለጸው ችግር ላይከሰት ይችላል።

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ የተመለከትነው በአልከሶ መውሊድ ከሙስሊሞች በተጨማሪ ክርስትያኖችም እንደሚሳተፉበት ነው። እነዚህ ክርስትያን ምዕመናን እንደማንኛውም

179 ቃለ መጠይቅ 26/10/07

180 ቃለመጠየቅ 23/10/07

መውሊድ አክባሪ መዋጮ ሲዋጣ አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ገንዘብ ያዋጣሉ፡፡ ሀረም ውስጥ ደግሞ የራሳቸው የሆነ ማረፊያ ኸለዋ እና ምግብ ማዘጋጃ ቦታ አላቸው፡፡ በዚህ ኸለዋ ከተለያዩ ቦታዎች የሚመጡ ክርስትያን ምዕመናን እዚህ ኸለዋ ውስጥ ያርፋሉ፤ ምግብም ይመገባሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ምዕራፍ በአልከሶ እና በአካባቢው የሚኖሩ ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች ተቻችለው እና ተከባብረው እንደሚኖሩ አሳይቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በብሔረሰቡ ዘንድ ከመውሊድ ውጪም መልካም የሚባል የሃይማኖት መስተጋብር መኖሩን ተመልክተናል፡፡

# ምዕራፍ ዘጠኝ

# 9. ለውጥ፣ ቀጣይነት እና የከበራው ፋይዳዎች

ይህ ምዕራፍ አራት ዋና ዋና ነጥቦችን የምንመለከትበት ነው፡፡ አንደኛ በአልከሶ በመውሊድ ምን ምን ጉዳዮች ከቀድሞው ተለወጡ እና ምን ምን ጉዳዮችስ ቀጠሉ የሚለው ጉዳይ ነው፡፡ ሁለተኛ መውሊዱ እንዲቀጥል የሚያደርጉ ምቹ ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ እና መውሊዱ እንዳይቀጥል የሚያደርጉ ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ የምንዳስስበት ነው፡፡ ሶስተኛው መውሊድ በሀገራችን በበርካታ አካባቢዎች የሚከበር በመሆኑ በአልከሶ መወሊድ ስልጤዎች ምን የተለየ አሻራ አሳረፉበት ወይም ስልጤዎች በአልከሶ መውሊድ ባህላቸውን (ቁሳዊ እና መንፈሳዊ)፣ልማዳቸውን፣ ማህበራዊ ግንኙነታቸውን እንዴት አንጸባረቁበት የምንመለከትበት፡፡ አራተኛው ነጥብ የመውሊዱ መከበር ያለው ፋይዳ ምን እንደሆነ የተዳሰሰበት ክፍል ነው፡፡ ይህን ምዕራፍ ለመተንተን የተጠቀምኩት በዋናነት ለውጥና ቀጣይነት እና ስነ ፋይዳ ንድፈ ሀሳቦችን ነው፡፡

## 9.1 የአልከሶ መውሊድ ለውጥ፣ ቀጣይነት እና የለውጡ ዋና ዋና ምክንያቶች

ይህ ንዑስ ርዕስ ስር የአልከሶ መውሊድ በየጊዜው ያመጣውን ወይም ያሳየውን ለውጥ ያሳያል፡፡ በመሆኑም ለውጡን ከማህበራዊ፣ ከኢኮኖሚያዊ፣ ከባህላዊ(ፎክሎር) እና ከሃይማኖታዊ ጉዳዮች አንጻር እንመለከታለን፡፡ ይህን ከመመልከታችን በፊት ለውጥ እና ቀጣይንት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአጭሩ እንመልከት፡፡ ስለ ለውጥ እና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳብ የጻፉት Tolken (1996፣126) እና Dorson (1972፣180) የአንድ ማህበረሰብ ባህል በጊዜ ሂደት ሊለወጥ እና ሊቀጥል እንደሚችል ያስረዳሉ፡፡ (østebø,2014፣27) ደግሞ ከሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> The political and socio-economic developments during the Derg regime and increasing pressure from the Salafi movement had significant impacts on the pilgrimage and the character of the shrine. The number of pilgrims decreased markedly, affecting the rituals of sacrifice, and consequently dramatically reducing the community's income.

በደርግ ዘመን በተስተዋለው ፖለቲካዊ እና ማህበረ ኢኮኖሚያዊ እድገት የተነሳ የሰለፍ እንቅስቃሴ በማደግ ለሃይማኖታዊ ክብረበዓለት የሚደረጉ ጉዞዎች እና ቅዱሳን ስፍራዎችና በስፍራዎች የሚከበሩ ክብረበዓዎች እየቀነሱ እንደመጡ ከዚህ በላይ የተመለከትነው ጥቅስ ያሳያል፡፡

ከእነዚህ ሁለት ምሁራን ሀሳብ የምንዳው ባህሎች እና ሃይማኖታዊ ክብረ በዓላትን ለማክበር የሚደረጉ ጉዞዎች በተለያዩ ምክንያቶች የተነሳ ለውጦች እንደተስተዋለባቸው ነው፡፡ በአልከሶ መውሊድ ይህ ሁኔታ ይንጸባረቃል፡፡ ምክንያቱም መረጃ አቀባዮች በርካታ የአከባበር ጉዳዮች የቀድሞ ይዘታቸውን እየለቀቁ መምጣታቸውን ያስገነዝባሉ፡፡ ለምሳሌ ያክል የሚከተሉትን እንመልከት፡፡

**ዚያራ፡-** መውሊድ መከበር ከጀመረበት ዘመን ጀምሮ በአልከሶ ሀረም ከሚከናወኑ ጉዳዮች መካከል ዚያራ አንዱ ነው፡፡ ዚያራው እንደ ድሮው አለ፡፡ ነገር ግን የአዘያየር ሁኔታው እና ለዚያራ የሚመጡ ሰዎች ይዘውት የሚመጡት ቁሳቁስ ግን በተወሰነ ደረጃ ለውጥ አሳይተዋል፡፡ እንደ ሼኽ ከዲር አገላለጽ በድሮ ጊዜ የዚያራ ቦታ ሴቶች እንደልባቸው አይገቡም ነበር በአሁኑ ጊዜ ግን ሴቶች እንደልባቸው መግባት ጀምረዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ግን እንደማይፈቀድ ቀደም ብዬ አንድ ማሳያ ማቅረቤን እዚህ ላይ ማስታወስ ያስፈልጋል፡፡

**ቁሳቁሶች፡-** ሌላው የተስተዋለው ለውጥ በቀደምት ዘመናት ከተለያዩ ወረዳዎች የሚመጡ ምዕመናን ወደ ዚያራ ቦታ ሲመጡ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይዘው ይመጡ እንደነበር እና በአሁኑ ጊዜ ግን እየቀረ መምጣቱን የአካባቢው የዕድሜ ባለጸጋዎች ይናራሉ፡፡ ለምሳሌ በድሮ ጊዜ ከሳንኩራ ጤፍ በብዛት ይመጣ ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ ግን በምን ምክንያት እንደሆነ ባይታወቅም የሳንኩራ ሰዎች ጤፍ ማምጣት ትተዋል፡፡ እንዲሁም ድሮ በመውሊድ ሰሞን ግመል ይመጣና ይታረድ ነበር በአሁን ጊዜ ግን ይህ ሁኔታ ቀርቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ብርዝ(በስልጥኛው ስህር) ብዛት የመውሊድ ሰሞን ይሰራ ነበር ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ ይህ ብርዝ ቀርቷል ማለት ይቻላል፡፡ ከዚህ በላይ የገለጽኳቸው ጉዳዮች ለመቅረታቸው በዋናነት እንደ ምክንያት የሚቀርበው በአሁኑ ጊዜ የሚስተዋለው የኑሮ ውድነት እንደ ምዕመናኑ ይናገራሉ፡፡

**ረብሻ እና ሁካታ፡-** መውሊዱን ከአከባበር አንጻር ስንመለከተው ከቀድሞው በተለየ ሁኔታ ረብሻና ሁካታ እየበዛ መምጣቱን ገራድ ኑርሰቦ እና ሌሎቹም መውሊዱን ለረጅም ጊዜ

ያከበሩ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡ በዚያራ ቦታ ፈይደ(የአልከስዬ የልጅ ልጅ) በነበሩበት ወቅት ያልነበረ ስርዓት የማጣት እና ቦታው ሃይማኖታዊ ስርዐት የሚካሄድበት ቦታ የማይመስልበት ደረጃ መድረሱን ገራድ ኑርሰቦ ያስረዳሉ፡፡ እኔም መስክ ላይ በነበርኩበት ወቅት ለዚያራ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ይዘው የመስጂዱን መሪ ለመዘየር ሲሄዱ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ሲነጋገሩ ሰምቻለሁ፡፡ ሼኽ ከዲር ግን በቀደሙት ዘመናት በዝያራው ቦታ ድምጽን ከፍ አድርጎ መናገር ያልነበረ ጉዳይ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ ገራድ ኑርሰቦ[181] "በዚህ ቦታ የሚካሄደው ዚያራ ከጊዜ ወደ ጊዜ አደቡን(ስርዓቱን) እያጣ መጥቶዋል፡፡ በድሮ ጊዜ መገፋፋት፣ መሽቀዳደም፣ መጫጮህ፣ አልነበረም፡፡ አሁን ግን አንዳንድ ጊዜ ቦታው ገበያ በሚመስል ሁኔታ ጫጫታ እየበዛ መጥቶዋል፡፡" ብለዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በድሮ ጊዜ ግመል ይመጣ እንደነበረ እና በምን ምክንያት እንደቀረ እንደማይታወቅ በመግለጽ የድሮውን እና የአሁኑንን ሁኔታ በንጽጽር አቅርበዋል፡፡ የገራድ ኑርሰቦን ሀሳብ ሼኽ ከድር እና ሁሴይኒ ይስማሙበታል፡፡ ከእነዚህ መረጃ አቀባዮች ሀሳብ የምንረዳው ዚያራው እንደ ቀድሞው የቀጠለ ሲሆን የአዘያየር ሁኔታው ግን የተወሰነ ለውጥ እንዳለው ነው፡፡

**የወጣቶች ግንኙነት፡-** ሌላው በአልከሶ መውሊድ ለውጥ አሳይተዋል ከሚባሉ ጉዳዮች መካከል የወጣቶች ግንኙነት ይገኝበታል፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው የአልከሶን መውሊድ ከሚያደምቁት ምዕመናን መካከል ወጣቶች እንደሚገኙበት ተመልክተናል፡፡ እነዚህ ወጣቶች ምንም እንኳን ለመውሊዱ ድምቀት ቢሰጡትም በተቃራኒው ደግሞ የመውሊዱን መልካም ገጽታ በተወሰነ ደረጃ እያበላሹት መሆኑን መውሊዱን ለረጅም ጊዜ ያከበሩ ምዕመናን ይናገራሉ፡፡ ምክንያቱም በምዕራፍ ሰባት እንደተመለከትነው እነዚህ ወጣቶች ከተቃራኒ ጾታ ጋር በመሆን እስላማዊ ስነ ስርዓት በሚካሄድበት ቦታ መደረግ የሌለባቸውን ድርጊቶችን ይፈጽማሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአሁኑ ጊዜ ወጣቶች የአለባበስ እና የአጋጌጥ ሁኔታ ከቀድሞው በተለይ እና እስላማዊ ስርዓት የሚከናወንበት ቦታ ሲገባ ሊለበስ የሚገባ አለባበስ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ወጣቶች አለባበስ እና አጋጌጥ እስላማዊ አለባበስ ወይም የስልጤ ብሔረሰብን ባህላዊ አለባበስ የሚንጸባርቅ አይደለም፡፡ ይህ ሁኔታ በአልከስዬም ሆነ እሳቸውን ተክተው ሀረሙን በመሩ አሊሞች ዘመን ያልነበረ እና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመጣ ለውጥ እንደሆነ መረጃ አቀባዮች ይናገራሉ፡፡

---

[181] ቃለ መጠይቅ 24/05/08

**የጥበቃ መመደብ፡-** በአልከሶ መውሊድ ድሮ ባልነበረ ሁኔታ የጥበቃ ወታደር ከወረዳው ይመደባል፡፡ አቶ ሁሰይኒ እና ገራድ ኑርሰቦ ይህ የሆነበት ምክንያት ሁለት እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ አንደኛው አንዳንድ መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉ ሰዎች መንገድ ላይ እና ወደ ሀረም መሄጃ ቦታ ላይ በመቆም መውሊድ ለማክበር የሚሄዱ ሰዎችን ስለሚተናኮሉ ነው፡፡ ሁለተኛው ቀደም ብዬ እንገለጽኩት ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ የከተማ ወጣቶች ወደ አልከሶ ሀረም በመሄድ ወጣት ሴቶችን ስለሚተናኮሉ እሱን ለመከላከል ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተወሰኑ ወጣቶች በቡድን በመሆን ጥል የሚፈጥሩበት አጋጣሚ አለ፡፡ ወጣት ፈተረሁፍ "በጉዞው ላይ አንዱ ቡድን ከአንዱ ቡድን ጋር እርስ በእርስ መጫወት እና መበሻሸቅ የተለመደ ነው፡፡ በዚህ ብሽሽቅ እና መቀላለድ መካከል አልፎ አልፎ ጥል የሚፈጠርበት ሁኔታም አለ" ይላል፡፡ ፈተረሁፍ አያይዞም መንገድ ላይ ሲበሻሸቁ የመጡ ወጣቶች በመውሊድ ቦታ ላይ ተደባድበው መውሊዱን የረበሹበት ጊዜ አለ ሲል ሃምሳ አለቃ ወርቁ[1] ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በወጣቶች ዘንድ ጥል የሚፈጠረው በብሽሽቅ ብቻ ሳይሆን "የአካባቢዬን ሴት ልጅ ለከፍክብኝ ወይም እኔ የምፈልጋትን ልጅ ለምን ነካህብኝ" በሚል ጉዳይ ጭምር እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

**ከፍተኛ የመንግስት ሹማምንት እና የሃይማኖት መሪዎች መገኘት፡-** ከ2000 ዓ.ም ወዲህ ከፍተኛ የመንግስት ሹማምንት ሙስሊም ያልሆኑ ጭምር እና ከመጅሊስ(ከፌደራል፣ ከክልል…) የሚመጡ የሃይማኖት መሪዎች በመውሊዱ መገኘት ጀምረዋል፡፡ እነዚህ ሙስሊም ያልሆኑ የመንግስት ሹማምንት ወደ አልከሶ የሚሄዱት መውሊዱን ለማክበር ሳይሆን መንግስት ለመውሊዱ ትኩረት እንደሚሰጠው ለማሳየት እንደሆነ በ2008 ዓ.ም የመውሊድ አዘጋጅ ኮሜቴ መሪ የነበሩት አቶ ነስሮ ፈይድ ይናገራሉ፡፡ እነዚህ ሹማምንት በመውሊድ በተገኙበት ወቅት የሚያደርጉት ንግግር ከሃይማኖታዊ ይልቅ አለማዊ ይዘት ይበዛበታል፡፡

**የምግብ ስርዓት፡-** ሌላው በአልከሶ መውሊድ ከተለወጡ ጉዳዮች መካከል ለምዕመናን የሚዘጋጀው ምግብ ነው፡፡ ቀደም ብለን ስለ ለውጥ እና ቀጣይነት ንድፈ ሀሳብ በተመለከትነበት ክፍል የአንድ ማህበረሰብ ባህል በጊዜ ሂደት ሊለወጥ እንደሚችል ተመልክተናል፡፡ ይህ ሁኔታ በአልከሶ መውሊድም እንደተከሰተ መረዳት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በድሮ ጊዜ በአልከሶ መውሊድ ስጋ ይዘጋጅ የነበረው በጥብስ መልክ ነበር፡፡ ነገር

ግን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ስጋ በቀይ እና በአልጫ ወጥ መልክ መዘጋጀት ጀምሯል፡፡ ስለዚህ የምግብ ስርዓቱ አለ፤ የሚዘጋጀው የምግብ አይነት ግን በተወሰነ ደረጃ ለውጥ አምጥቷል፡፡

**የመገናኛ ብዙኂን ሽፋን መስጠት፡-** ሌላው ቀድሞ በተለየ ሁኔታ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ የመውሊዱ የአከባበር ስነ ስርአት ከወረዳ፣ ከዞን፣ ከክልል እና ከፌደራል የመጡ የመገናኛ ብዙኂን ባለሙያዎች ሽፋን ይሰጡታል፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች በመውሊዱ በመገኘት ምልከት እና ቃለመጠይቅ በማድረግ በመውሊዱ የነበረውን ሁኔታ በተለያዩ ሚዲያዎች ያስራጩታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ የመገናኛ ብዙኂን ሰዎች የመውሊዱን የአከባበር ስርዓት እንደወረደ ከማስተላለፍ ይልቅ እነርሱ ካቀዱት ዓላማ አንጻር ስለሚያቀርቡት የመውሊዱን ትክክለኛ ገጽታ እያቀረቡ እንዳለሆነ ከተለያዩ የመገናኛ ብዙኂን አንጻር መረዳት ችያለሁ፡፡ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ከወትሮው በተለየ ሁኔታ የአልከሶ መውሊድ የሚከበረበት ቀን በመገናኛ ብዙኀን መነገር ጀምሯል፡፡ ለምሳሌ የ2009ኙ የአልከሶ መውሊድ ግንቦት 6/2009 ዓ.ም እንደሚከበር በፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ተገልጾ በሀገራችን የሚገኙ መውሊድ አክባሪዎች በተጠቀሰው ቀን አልከሶ ሀረም  እንዲገኙ ተጋብዘዋል፡፡

**የመንዙማዎች እና የነሺዳዎች ይዘት፡-** በአልከሶ መውሊድ የሚደመጡ መንዙማዎች እና ነሺዳዎች ይዘታቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተለወጠ ነው፡፡ እንደ መረጃ አቀባዮች አገላለጽ በመውሊድ ሰሞን ይሰሙ የነበሩ መንዙማዎች ትኩረታቸው ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ እና አልከስዬን የሚያወድስ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለይ በወጣቶች ዘንድ የሚባሉ መንዙማዎች እና የሚደመጡ ነሺዳዎች የሚያስተላልፉት ይዘት እየተለወጠ መጥቷል፡፡ ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ማሰባሰብ ከጀምርኩበት 2006 ዓ.ም ወዲህ እንኳን በወጣቶች እና በየኸለዋው የሚደመጡ መንዙማዎች እና ነሺዳዎች ከሃይማኖታዊ ይዘታቸው ይልቅ አለማዊ(ምድራዊ) ይዘታቸው እየጎላ መጥቷል፡፡ ለምሳሌ በ2008ቱ ዋናው መውሊድ ቀን ወጣት ወንዶች እና ሴቶች በቡድን በቡድን በመሆን እርስ በእርስ መንዙማ በሚመስል ሁኔታ ሲበሻሽቁ ሰምቻለሁ፡፡ ባጠቃላይ በተዘዋወርኩባቸው ኸለዋዎች ምዕመናን የሚሏቸው መንዙማዎች በብዛት አላህ በምድር ላይ እያሉ ምድራዊ ፍላጎታቸውን እንዲያሟሉላቸው የሚማጸኑባቸው ናቸው፡፡ ይህ የመንዙማዎች ይዘት እየተለወጠ መምጣት የጀመረው ካለፉት አስር አመታት ወዲህ እንደሆነ እና በአሁኑ ጊዜ ሰው ልጅ ከሞት በኂላ ላለው ህይወቱ ይልቅ በዚህ ምድር ላለው ህይወቱ ቅድሚያ እየሰጠ መምጣቱን በሰኢድ ኸለዋ  ጫት እየቃሙ መንዙማ ሲሉ

ያገኛኋቸው አቶ ፈረጂ[182] አስረድተውኛል፡፡ ይህን ሀሳብ በተመሳሳይ ሁኔታ ሀጂ ሀምድኖም ይጋሩታል፡፡

የመንዙማዎች ይዘት፣ስርዓት እና ልምድ መበረዝ በአልከሶ ብቻ የሚስተዋል ሳይሆን ሀገር አቀፍ ችግር እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ለምሳሌ ከማል(2008፣12) የሚከተለውን ይላሉ፡፡

> በአሁኑ ወቅት □ህ ሀገር በቀል የሆነው የመንዙማ ስርአትና ልምድ ከማደግና ከማበብ ይልቅ እየተዳከመ ሄዷል፡፡ በተለይ አሁን መንዙማ ስለደረሰበት የመዳከምና የመረሳት ደረጃ የሚከተሉት ሦስት ዋናዋና ምክንያቶች ሊጠቀሱ ይችላሉ፡- አንደኛ፣ በሀይማኖቱ ተከታዮች ዘንድ ስለመንዙማ ያሉ የተለያዩ አመለካከቶች ሁለተኛ፣ ከ1983ቱ የመንግስት ለውጥ ጋር ተያይዞ የሀገራችን □ተለያዩ ብሄረሰቦች በቋንቋቸው የመጠቀምና ቋንቋቸውን የማሳደግ እትሉ መመቻቸቱ እና ሦስተኛ የእንግሊዘኛና ዓረበኛ ነሺዳዎች መስፋፋት፡፡

**ሃይማኖታዊ ጉዳይ፡-** የአልከሶ መውሊድ ካሳየው ለውጥ መካከል ሃይማኖታዊ ጉዳይ ተጠቃሽ ነው፡፡ ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በዚህ መውሊድ መውሊድን ለማክበር ከሚሰባሰቡ ሰዎች መካከል ሷላትን በአግባቡ የማይሰግዱ እና ሀረም ውስጥ ያለ ዉዱእ የሚገቡ መኖራቸውን ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ ይህንንም ያረጋገጥኩት በምልከታ ነው፡፡ የመውሊድ ሰሞን በርካታ ወጣቶች ተጸዳድተው ሳይተጣጠቡ ወይም ዉድኡ ሳያደርጉ ወደ ሀረም ሲገቡ ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በርካታ በመውሊዱ የተገኙ ምዕመናን በሀረሙ ጥግ ጥግ ይጸዳዳሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ከዚህ በፊት ያልነበረ እና ከቅርብ ጊዜህ ወዲህ እየተከሰተ እና ከአመት አመት የዚህ ሁኔታ እየሰፋ መምጣቱን ሀጂ ሀምዲኖ እና አቶ መሀመድ አስረድተውኛል፡፡

**ውዝግብ፡-** የአልከሶ መውሊድ ከአዋቂ እስከ ልጅ ከሙስሊም እስከ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል ክርስትያን ቢሳተፍበትም በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድ ግን መከፋፈልን እየፈጠረ ነው፡፡ የሃይማኖት መስተጋብር ጉዳይ ሲነሳ ሁል ጊዜ የሚነሳ በሁለት የተለያዩ ሀይማኖቶች መካከል ያለውን ነው፡፡ ነገር ግን በአንድ ሀይማኖት ውስጥም በሀይማኖቱ ተከታይ ምዕመናን መካከል በተወሰኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ አለመስማማት ወይም አለመግባባት ሊፈጠር

[182] ቃለመጠይቅ 17/09/08 አልከሶ ሀረም

ይችላል፡፡ የዚህ አይነት ሁኔታ በአሁኑ ወቅት አለማችን እያስተናገደች መሆኑን ቀደም ብለን በምዕራፍ ሶስት ተመልክተናል፡፡ በተወሰኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አለመስማማት ከሚታይባቸው ሃይማኖቶች መከካል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው መውሊድ መጥቀስ ይቻላል፡፡

ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በአሁኑ ጊዜ በሙስሊሞች መካከል ልዩነት በመፍጠር ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል መውሊድ አንዱ ነው፡፡ መውሊድ መከበር አለበት የለበትም የሚለው ጉዳይ አለማቀፋዊ ጉዳይ ቢሆንም ይህ ውዝግብ በአልከሶ መውሊድም ይንጸባረቃል፡፡ ጥናቱን ከመጀመሬ በፊት ያነጋገርኳቸው የአካባቢው ሰዎች ይህ ውዝግብ የአልከሶ መውሊድን አልነካውም ቢሉኝም የአልከሶ መውሊድ የችግሩ ገፈት ቀማሽ መሆኑን በጥናቴ ማረጋገጥ ችያለሁ፡፡ በአሁኑ ጊዜ በተለይ ወጣቱ የሙስሊሙ ክፍል መውሊድ መከበር የለበትም በማለት መውሊድን የሚያከብሩ ሰዎችን ይቃወማሉ፡፡ ለዚህ ጥናት የሚሆን መረጃ ሳሰባስብ ለመረጃ መሰብሰቢያነት ከተጠቀምኩበት የመረጃ መሰብሰቢያ ስልት መካከልአንዱ ተተኳሪ የቡድን ውይይት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ዘዴ መውሊድን የሚያከብሩት ለምን እንደሚያከብሩ እና የማያከበሩት ለምን እንደማያከብሩ በቡድን እንዲወያዩ በቀን 23/06/08 ማድረግ ቀደም ብዬ ገልጫለሁ፡፡ ከውይይቱ መረዳት እንደቻለኩት አክባሪዎች ማክበራችን ትክክል ነው ሲሉ የማያከብሩት ደግሞ ትክክለኛው ነገር አለማክበሩ ነው ብለው ይከራከራሉ፡፡

ሌላው ልዩነት የሚፈጥረው መንዙማ ጉዳይ ነው፡፡ መውሊድን የሚያከብሩት “ወገኖች ነብዩን የሚያወድስ እስከሆነ ድረስ በየትኛውም የሙዚቃ መሳሪያ ቢታገዝም ክልክል የሚሆንበት ጉዳይ ይለም” ሲሉ መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉት ግን “በእስልምና ሃይማኖት በሀዲስም ሆነ በቁርአን ሙዚቃ መሞዘቅ፣ ማዳመጥ፣ መሳሪያ ታግዞ ነብዩ መሀመድንም ሆነ አላህን ማወደስ ይፈቀዳል የሚል ነገር የለም” ይላሉ፡፡ መከበር አለበት የሚሉ ወገኖች ደግሞ ይህን ሀሳብ ሲቃወሙ “ነብዩ መሀመድ አንድ ጊዜ ጦር ሜዳ ሄደው ከጠላት ጋር ተፋልመው ድል አድርገው ሲመለሱ ወደ ጦር ሜዳ ያልሄዱ አቅመ ደካማዎች እና ሴቶች እያጨበጨቡ እና ድቤ እየመቱ ሲቀበሏቸው ሀራም ነው ተው ብለው አልከለከሉም” የሚለውን ሀሳብ በማቅረብ ይከራከራሉ፡፡ እንዲሁም ድቤ እየመቱ እሳቸውን ማወደስ ችግር የለውም ይላሉ፡፡ ከዚህ ሌላ ከውይይቱ እንደተመለከትኩት አንዳንድ ሰዎች ነብዩንም ሆነ አላህን ስናወድስ ዘመናዊ የሙዚቃ መሳሪያ ሳይሆን ድቤ ብቻ ብንጠቀም ችግር የለውም ሲሉ አንዳንዶቹ ደግሞ ድቤም ሆነ የሙዚቃ መሳሪያ መጠቀም በእስልምና አይፈቀደም

ይላሉ፡፡ ይህ ውዝግብ ረጅም እድሜ ያለው ሳይሆን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰፊው እየተከሰተ ያለ ክስተት እንደሆነ በቡድን ውይይቱ ወቅት ተገልጾዋል፡፡

ባጠቃላይ ካደረኩት ቃለመጠይቅ እና ውይይት መረዳት የቻልኩት መውሊድ መከበር የለበትም በሚለው ቡድን ስር የተሳተፉት በብዛት በተለምዶ ሰለፊያዊ (ወሃቢያዊ) አመለካከት ያላቸው ሲሆን መከበር አለበት በሚለው ቡድን ስር ያሉት ደግሞ በብዛት የተገኙት በእድሜ የገፉ ሰዎች ወይም በተለምዶ ሱፊያዊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን መውሊድ መከበር አለበት ከሚሉት ውስጥ ወጣቶች የሉም ማለት አይደለም፤ መከበር የለበትም ከሚሉት ወገኖች ደግሞ በእድሜ የገፉ ሰዎች የሉም ማለት አይደለም፡፡ ከውይይቱ፣ በመስክ ቆይታዬ እና በመውሊድ ከበራ ወቅት ከተመለከትኩት አንጻር በመውሊድ ከበራ ላይ ያለው ውዝግብ በሁለቱ አካላት መካከል መልካም የሚባል ግንኙነት እንዳይኖራቸው እያደረገ መሆኑን መገንዘብ ችያለሁ፡፡ ይህን ውዝግብ እዚህ ማንሳት የፈለኩበት ዋናው ምክንያት መውሉዱ ከ1900 ጀምሮ እየተከበረ እንደሆነ እና የአከባበር እና የአክባሪዎች ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ ለውጥ እያሳየ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት ሌሎችም ለውጦች ሊኖሩም ይችላሉ፡፡ እንዲሁም ወደ ፊትም ሌላ ለውጥ ሊመጣ ይችላል፡፡ የተወሰኑት የአከባበር ሁኔታዎች ሳይለወጡ ሊቀጥሉ ይችላሉ፡፡ የባህል ለውጥ እና ቀጣይነት ማለት ይህ ነው፡፡

ይህን ርዕሰ ጉዳይ እዚህ ቦታ ላይ ማሳየት የፈለኩበት ዋና ዋና ምክንያቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛ የመውሊድ አክባሪዎች ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዴት እየተለወጠ መምጣቱ ማሳየት ነው፡፡ ሁለተኛ የመውሊዱ መከበር በአካባቢው ማህበረሰብ ምን አይነት ማህበራዊ ገጽታ እንዳለው እና የማህበረሰቡ ግንኙነት በአካባቢው ልማት እና ሰላም ላይ ምን አይነት ተጽእኖ እንዳለው ማሳየት የዚህ ጥናት አንዱ ዓላማ በመሆኑ ነው፡፡

## 9.2 የአልከሶ መውሊድ ከበራ ተግዳሮቶች

ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በተጠናከረ ሁኔታ መውሊድ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ሲከበር ኖሯል፡፡የተወሰኑት መውሊዶች በተለያዩ ሁኔታዎች መከበሩ ሲቋረጥ የተወሰኑት ደግሞ በአሁኑ ጊዜ በተለያዩ ምክንያቶች ተቋርጠዋል፡፡ ይህን ሁኔታ በስልጤ ዞን ያለውን ነባራዊ ሁኔታ ከዚህ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡ የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው የአልከሶ

መውሊድ በአሁኑ ጊዜ በተጠናከረ ሁኔታ ቢከበርም ወደፊት በተጠናከረ ሁኔታ እንዳይቀጥል የሚያደርጉ ሁኔታዎች አሉ፡፡ በመሆኑም በዚህ ንዑስ ርዕስ መውሊዱ ላይ የሚስተዋሉ ተግዳሮቶች ምን ምን እንደሆኑ ቀጥለን እንመለከታለን፡፡ መውሊድ እንዳይቀጥል ከሚያደርጉ ተግዳሮቶችን ከሃይማኖት፣ ከማህበራዊ እና ከኢኮኖሚ አንጻር የሚታዩ ናቸው፡፡ ከሃይማኖት አንጻር የሰለፊይ(ወሀብይ) ይጠቀሳል፡፡ ከማህበራዊ አንጻር የትውልዱ ምክንያታዊ መሆን ሲሆን ከኢኮኖሚ አንጻር ደግሞ የኑሮ ውድነት ይጠቀሳል፡፡

**ሀ. የሰለፍ(ወሀብይ) ተጽእኖ**

መውሊድ በደመቀ ሁኔታ እንዳይከበር ከተጋረጠበት ጋሬጣ መካከል ዋናኛው የሰለፊይ(የወሀብይ) አስተምሮ ነው፡፡ ሰለፊዝም መውሊድ ላይ የሚያሳድረውን ተጽእኖ ከመመልከታችን በፊት ስለ ሰለፊይ ጥቂት እንመልከት፡፡

Østebø (2008:18) ሰለፊዝም የሚለው ቃል "The term Salafi emerged from the Arabic word al salaf al salih" ከሚለው እንደመጣ ትርጉሙም "pious ancestors`." እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ Ostebo (2012፡180) በሌላ ጽሁፋቸው ደግሞ Salafism was by them rendered an integrated part of mainstream Islamic theology and the standard for the reformers' quest in rectifying religious practices and deepening Islamic piety among their compatriots. ይላሉ፡፡ "Sufism, is the esoteric school of Islam, founded on the pursuit of spiritual truth as a definite goal to attain: the truth of understanding reality as it truly is, as knowledge, and so achieving ma'arefat."[183]፡፡ የሰለፊዝም መስራች ደግሞ Mohammed Ibn Abd al Wahhab (ca.1703—1792) እንደሆነ Foucher (1994፣72) ያስረዳሉ፡፡

በአሁኑ ዘመን በሀገራችን ሰለፍ(ሰለፊዝም) ከሚለው ቃል ይልቅ ጎልቶ የሚሰማው ወሀብይ የሚለው ነው፡፡ ስለዚህ ወሀብይ ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን እንመልከት፡፡ ወሀብይ መሀመድ አብድልወሀብ ከሚባል ሰውደረባዊ ግለሰብ እንደሆነ ይነገራል፡፡ ይህን ሀሰብ አደም ካሚል እንደሚከተለው በሰፊው ያብራሩታል፡፡

[183] http://ias.org/sufism/introduction-to-sufism/ acceced 05/11/2017

ዋህቢያ ማለት የአገርም የሃይማኖትም ስም አይደለም። እዚህ አገር እየተንፀባረቀ ያለው ትልቁ ችግር ይኼ ነው። ዋህቢያ የሰው ስም ነው። መሐመድ ዱን አብድልዋህበረ የሚባለው ግለሰብ የሃይማኖት ሊቅ ነበረ፤ በእሱ ነው ስያሜው የተገኘው። ይህ ግለሰብ ሳዑዱ ዓረቢያ ዑውይና በምትባል አካባቢ ከ 1703 እስከ 1791 ዓ.ም. የነበረ ነው። ስለዚህ ዋህቢያ ብል እምነት የለም ግን ‹‹ሰለፊ›› ልንል እንችላለን። ሰለፊ ምንዴን ነው? በቁርዓንና በሐዱስ የሚመሩ ናቸው። እዚህ ላይ ፖለቲካና ኢኮኖሚ ውስጥ አይገቡም። እንደ እምነት በጣኦት ማምለክን ይቃወማል፤ በመቃብር መገዘትን ይቃወማል፤ ለፈጣሪ የተሰጠውን የብቸኝነት ኃይል አስተምሮ አስቀምጦ የሄደ ግለሰብ ነው።[184]

ሰለፊዝም ወደ ሀገራችን የገባው በ18ኛው ክፍለ ዘመን ከሳውዲ አረቢያ እንደሆነ Ishihara (1996፣125) ሲገልጹ Despalt (2005:499) ደግሞ ሰለፊዝምን በመቀበል ሀረሮች የመጀመሪያዎቹ ሲሆኑ ባሌ እና አርሲ (በ20ኛው ክፍለ ዘመን) ተከታዮች ናቸው ይላሉ። በሀገራችን ሰለፊዝምን በብዛት ወሃቢያ በመባል እንደሚጠራ Zerihun (2013: 151)ያስረዳሉ። ሰለፊዝም ኢትዮጵያ ውስጥ በተጠናከረ ሁኔታ መራመድ የጀመረው ግን ከ1983 ዓ.ም ወዲህ እንደሆነ Østebø (2014፣21) ያስረዳሉ። በሀገራችን ሰለፊዝም በሰፋት ከሚስተዋልበት ስፍራ መካከል የስልጤ ዞን አንዱ ነው። በመሆኑም ይህ የእስልምና ሃይማኖት ጽንፍ ከሚያራመደው አስተሳሰብ መካከል ዚያራ መካሄድ የለበትም እና መውሊድ መከበር ቢድአ ነው የሚለው ጉዳይ ይጠቀሳል። ይህ አስተሳሰብ በአልከሶ መውሊድ ላይ ተጽእኖ በመፍጠር ላይ ይገኛል። በመሆኑም ይህ አስተሳሰብ የመውሊድ ከበራን ከመቃወም በተጨማሪ የአካባቢውን ማህበረሰብ እየከፋፈለ ነው።

የሀይማኖት የመቻቻል ጉዳይ ሲነሳ ሁል ጊዜ የሚነሳ በሁለት የተለያዩ ሀይማኖቶች መካከል ያለውን ነው። ነገር ግን በአንድ ሀይማኖት ውስጥም በሀይማኖቱ ተከታይ ምዕመናን መካከል በተወሰኑ ርእሰ ጉዳዮች ላይ አለመስማማት ወይም አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል። የዚህ አይነት ሁኔታ በአሁኑ ወቅት አለማችን እያስተናገደች መሆኑን ቀደም ብለን በምዕራፍ ሶስት ተመልክተናል። በአንድ ሀይማኖት ተከታዮች ዘንድ በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ አለመስማማት ከሚታይባቸው ሃይማኖቶች መከካል የዚህ ጥናት ትኩረት የሆነው

[184] ቃለመጠይቅ አደም ካሚል 2004 ዓ.ም

የእስልምና ሃይማኖትን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በአሁኑ ጊዜ በሙስሊሞች መካከል ልዩነት በመፍጠር ከሚጠቀሱ ጉዳዮች መካከል መውሊድ አንዱ ነው፡፡ ይህ ልዩነት ደግሞ የመውሊድ ህልውና እየተፈታተነው ይገኛል፡፡ የመውሊድ በዓል መከበር አለበት የለበትም የሚለው ጉዳይ ላይ በሙስሊሙ ማህበረሰብ መካከል ልዩነት እንዳለ በ2007 ከታካሄደው ውይይት መረዳት ተችሏል፡፡ ከመረጃ አቀባዮች ንግግር እንደተረዳሁት ከሁለቱ ጎራዎች የተውጣጡ ሰዎች በዚህ ዙሪያ ተወያይተው ስምምነት ላይ መድረስ አልቻሉም፡፡ በእነዚህ አካባቢዎች በሚኖሩ ሙስሊሞች መካከል የሚስተዋለው መጠነኛ ልዩነት ቀስ በቀስ ስር እየሰደደ በመሄድ በመካከላቸው ትልቅ ልዩነት ሊፈጥር የሚችልበት ሁኔታ መኖሩን ከውይይቱ መረዳት ችያለሁ፡፡

ወጣት አብድልባቅ በወይይቱ የተሳተፈ እና መውሊድ መከበር የለበትም ከሚሉት ወገኖች ነው፡፡ አብድልባቅ (08፣25/2007) መውሊድን ማክበር በእስልምና ቦታ የሌለው እንደሆነ እና መከበር አለበት በማለት መውሊድን ማክበር የተሳሳተ መንገድ ነውና ሊታረሙ ይገባል በማለት በሚከተለው ሁኔታ ማብራሪያ እና ምክር አዘል ሀሳብ ሰንዝሯል፡፡

> መውሊድ ኢስላማዊ መሰረት የሌለው ነው፡፡ በቅርብ ጊዜ የተለያየ የራሳቸውን ጥቅም ለማስጠበቅ የሚፈለጉ ሰዎች የፈጠሩት ነው፡፡ መውሊድን በተለይ የአንድን ሰው መውሊድ ማውጣት መጥፎ ስራ ነው፡፡ ነብዩ መውሊድ አላከበሩም፡፡ በሀገራችንም በቅርብ ነው መከበር የጀመረው፡፡ በመውሊድ ቀን ብዙ ሀራም የሆኑና ሽርክ ስራዎች ይሰራሉ፡፡ አሁን ድሮ የአልከሶ መውሊድን በማከብርበት ጊዜ ብዙ ሽርክ ስራዎች ሲሰሩ አይቻለሁ፡፡ አልከስዬ ድረሱልን ይባላል፡፡ አልከስዬ ልጅ አጥቻለሁ ልጅ ስጡኝ ይላሉ፡፡ መስጊድ ውስጥ ጫት ይቃማል፡፡ መስጅድ ውስጥ ከበሮ ይመታል፡፡ ወንዶችና ሴቶች አንድ ላይ ይጨፍራሉ፡፡ የአልከስዬን መቃብር ይስማሉ፤ ይሰገዱለታል፡፡ የመውሊድ ቀን ፈርድ ሷላት በአግባቡ አይሰገድም፡፡ በጣም ብዙ ብዙ ነገሮችን መዘርዘር ይቻላል ከፈለክ፡፡ ስለዚህ በአልከሶ መውሊድ ውስጥ የሚካሄደው ነገር ሁሉ ሽርክና ሀራም ነው፡፡ ሰዎቹ አላህንና አልከስዬን ያመሳስሏቸዋል፡፡ ሁሉንም ማድረግ የአላህ አቅም ብቻ ነው አልከስዬ እኮ እንደ እኛ ሰው ናቸው፡፡ በርግጥ ትልቅ አሊም ነበሩ ብዙ ትልልቅ ቁርአን የቀሩ ሰዎችን አፍርተዋል፡፡

ባጠቃላይ ከዚህ ውይይት መረዳት የቻልኩት መውሊድ መከበር የለበትም የሚለው ቡድን ስር የተሳተፉት በብዛት ሰለፊያዊ (ወሃቢያዊ) አመለካከት ያላቸው ሲሆን መከበር አለበት በሚለው ቡድን ስር ያሉት ደግሞ በብዛት የተገኙት በእድሜ የገፉ ሰዎች ወይም ሱፊያዊ አመለካከት ያላቸው ሰዎች ናቸው፡፡ ይህ ሲባል ግን መውሊድ መከበር አለበት ከሚሉት ውስጥ ወጣቶች የሉም፤ መከበር የለበትም ከሚሉት ወገኖች ደግሞ በእድሜ የገፉ ሰዎች የሉም ማለት  አይደለም፡፡

መውሊድ መከበር አለበት የሚሉ ወገኖች(ሰለፎች) መከበር የለበትም የሚሉትን ወገኖች እስልምናን እንዲያበላሹ የቀጠራቸው አህባሾች ናቸው ይሏቸወል፡፡ አህባሽ ማነው? ዓላማውስ ምንድን ነው? የሚለውን በአጭሩ ቀጥለን እንመልከት፡፡

**Z. Alzamil  የተባሉ ጸሀፊ "Al-Ahbash:- Their History And Their eliefs" በሚለው አጭር መጣጥፍ የአህባሽ አመሰራረት እንዴት እንደሆ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡፡**

> **Habashi's History:** This group called Ahbash relating to their first leader Abdullah Al-Harawi Al-Habashi. He came to Lebanon from Ethiopia (Habashah), that why they called him Al-habashi. He left Addis Ababa after he made a Fitnah there its called Kolob Fitnah. The Addis Ababa's people know him as Shikh Al-Fitnah according to evidence from some of his relative. What he did there, he work with the ruler of Endraji -the son in law for the Ethiopia's president Helaselasi -against Islamic Associations there, and he helped him to close all the Islamic National Association's schools for memorizing the Holy Quran in Hrar city in 1940 (1367 Hejrah), and they issued their judge on the schools' manager - Ibrahim Hassan- to jail him twenty three years, also he helped that ruler to internment the scholars there. He did that for those people, because they are Wahabi. For that reason, the people called him after that is the Shikh Al-Fitnah. (**Alzamil 2011፣1**)

ከዚህ ጥቅስ የምረዳው አህባሽ የሚለው ስያሜ የመጣው ከቡድኑ መሪ አብዱላህ አል ሀራዊ አል ሀበሻ ከሚለው ነው። እኚህ ሰው በእስልምና አዲስ ነገር በመጨመራቸው እና ህብረተሰቡን በማወዛገባቸው ሼኽ ፊትና የሚል ተቀጥያ ስም ተሰጥቷቸው እንደነበር ጥቅሱ ያስረዳል።

አደም ካሚል ደግሞ አህባሽ ማለት ምን ማለት እንደሆነ በአሁኑ ጊዜ ያለውን ሁኔታ እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

> አህባሽ የራሱ የሆነ አጀንዳ አለው። ይጠቅማል አይጠቅምም እንየው። በአሁኑ ጊዜ ለምን አህባሽ ተመረጠ? በጥንቃቄ ታይቷል አልታየም? በእውነት ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስሊም ኡለማዎች የሉም ወይ? ከሉባኖስ ተበድረን ኡለማዎችን የምናመጣው እዚህ ምን አጥተን ነው? ሊባኖስ የኢትዮጵያ ምኗ ነች? ይኼን ማወቅ አለብን። የአህባሽ አይዲዮልጂ የእስልምናን መሠረት ሐሳብን ይንዳል። አምስቱን ማዕዝናትና ስድስቱን የኢማን ማዕዘናትን ይንዳል። ይኼ የራሱ መጽሐፍ ነው መሠረቱ፤ አብደላ ሐረሪ የእምነቱ ስያሜው አህባሽ ብሎ ሰጠው። አብደላ ሐረሪ በሐረር ውስጥ የተወለደ ነው። ጅማ ሂድ የአስተሳሰብ ችግር ፈጠረ። ከዚያ ተነስቶ ወደ ደውይ (ወሎ) ሄደ። ቀጥልም ወደ ራያ ከዚያም ወደ ሐረር ተመልሶ በወቅቱ ከነበሩት ሊቃውንት ጋር ልዩነት ፈጠረ። ኡሊማዎችን አሳሰረ፣ ትምህርት ቤቶችን አዘጋ። ሁከት ፈጣሪው ሼክ ብለው ሰየሙት። ብዙ ኡሊማዎች ወደ ግብፅና ሱዳን ተሰደዋል በእሱ ምክንያት። ወደ ሶሪያ፣ ሊባኖስ፣ እስራኤል ሄደዋል።[185]

ወሀቢያዎች አህባሾች እና ሱፊዎች አንድ አይነት አመለካከት አላቸው ቢሉም አንዳንድ ጸሀፊዎች ግን ሁለቱ የእስልምና አስተሳሰቦች የተለያዩ እንደሆኑ ያገነዝባሉ። ለምሳሌ እንደ አህመድ(2004) አገላለጽ አህባሽ በእስራኤል፣ በአሜሪካ፣ ባጠቃላይ በምዕራቡ ዓለም እጅግ በጣም በረቀቀ ስልት በእስልምና ላይ የተቋቋመ አጀንዳ ነው። ለዚህም በዓለም የሚገኙ የሱፊዝም እና የሰለፊያ ዑለማዎች፣ ማህበሮች እና ድርጅቶች የወግዛሉ እንዲሁም ከእስልምና ውጭ ናቸው ብለው ያምናሉ። ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ሱፊ፣ አህባሽ እና

[185] ቃለመጠይቅ 2004

የሰለፊያ የተለያዩ የእስልምና አጀንዳዎች ናቸው፡፡ እነዚህ መከከፋፈሎች በመውሊድ ከበራ ላይ የየራሳቸውን ተጽእኖ በማሳደር ላይ ይገኛሉ፡፡

ባጠቃላይ ከውይይቱ፣ በመስክ ቆይታዬ ካደረኩት ምልከታ እና ከመረጃ አቀባዮች መረጃ አንጻር በመውሊድ ከበራ ላይ ያለው ውዝግብ በሁለቱ አካላት መካከል መልካም የሚባል ግንኙነት እንዳይኖር እያደረገ መሆኑን መገንዘብ ችያለሁ፡፡ ይህን ለማለት ያስደፈረኝ ጉዳይ በዞኑ የመሬት ጥበት ስላለ በዘመናዊ ማረሻ መሳሪያዎችን አርሶአደሮቹ ብዛት ሲጠቀሙ አላየሁም፡፡ በመሆኑም የእርሻ ስራው የሚከናወነው በእጅ በደቦ መልኩ አልያም በበሬ ነው፡፡ የደቦ ስራ በሚሰራበት ወቅት በቀድሞው ጊዜ በቅርብ ያሉ ሰዎች በመጣመር ይሰሩ ነበር፡፡ በአሁን ጊዜ ግን ይህ ሁኔታ እንደ ድሮው በሰፊው አይስታዋልም፡፡ በአቅራቢያ ካሉ ሰዎች ጋር ተጣምሮ ከመስራት ይልቅ አንዱ አንደኛውን “ወሀብይ ስለሆነ ከእሱ ጋር አልሰራም” ሲል ሌላኛው ደግሞ “እሱ አህባሽ ስለሆነ ከእሱ ጋር አልሰራም” በመባባል ቀያቸውን ለቀው ራቅ ያለ ቦታ በመሄድ ከመሰሎቻቸው ጋር ይሰራሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ አንዱ ወገን አንዱን መናቅ አልፎ አልፎ የሚስተዋል ጉዳይ ነው፡ በመሆኑም ሁለቱ አካላት በጋራ ለመስገድ ብዙም ፍላጎት የላቸውም፡፡ ምክንያቱም ሁለቱ በጋራ በሚሰግዱበት ጊዜ የሰላቱ መሪ “ኢማም” ማን መሆን አለበት በሚለው ጉዳይ ላይ አይስማሙም፡፡ይህ በመሆኑ ለየብቻ የሚሰግዱበት ሁኔታ መኖሩ ወጣት አብድልባቅ[186] ነግሮኛል፡፡ እኔም መስክ ላይ በቆየሁበት ወቅት አረጋግጫለሁ፡፡

ይህ መከፋፈል ቀስ በቅስ እየሰፋ ይሄድና አላስፈላጊ ወደ ሆነ ሁኔታ ሊያመራ እንደሚችል ሁኔታዎች ያሳያሉ፡፡ እስካሁን ባለው ሁኔታ ምልከታ እና ቃለመጠይቅ ባደረኩባቸው አካባቢዎች ችግሩ የሚስተዋለው በጎረቤታሞች ወይም አብረው በሚሰሩ ሰዎች መካከል ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ሁኔታ በቤተሰቦች መካከል ሊፈጠር የሚችልበት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በአንድ ቤተሰብ አባላት መካከል እንኳን አንተ ልክ አይደለህም አንቺ ልክ አይደለሽም የሚባባሉበት ሁኔታ መኖሩ አልከሶ ከተማ ላይ አንድ ሻይ ቤት ቁጭ ብዬ ወደ አልከሶ ሀረም  የሚሄድ መኪና ስጠብቅ ወንድም እና እህት ይህን ሲባባሉ ሰምቻለሁ፡፡

[186] ቃለ መጠይቅ 08/25/2007 አልከሶ ከተማ

ይህ ሁኔታ ምንያህል ስር እየሰደደ እንደሆነ የሚከተለውን ምሳሌ እንመልከት፡፡ በስልጤ ዞን ተወልዳ ያደገች እና የመውሉድ በዓል ለብዙ አመታት ጀምሮ በደመቀ ሁኔታ የሚከበርበት ቤት አንዷት ልጅ ወደ አንድ ዩኒቨርስቲ ለትምህርት ሄዳ ክርምት ወደ ቤተሰብ ስትመለስ ለቤተሰቦቿ "እኛ ቤት በርካታ ቢድዐህ የሆኑ ነገሮች ይሰራሉና ሊቆሙ ይገባል" የሚል ሀሳብ ታቀርባለች፡፡ ቢድዐህ ብላ ካቀረበቻቸው ጉዳዮች መካከል መውሊድ ማክበር ፣ ቡና ሲፈላ ጀባ ማለት ወዘተ ተጠቃሾች ናቸው፡፡ ቤተሰቡ ግን በቀላሉ እጅ ሊሰጧት ባለመቻላቸው በቤተሰቡ መካከል ቀድሞ የነበረው ፍቅር ጠፍቶ አብሮ እስከ አለመብላት ተደረሰ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከቀጠለ በኋላ ልጅቱ ትምህርቷን ጨርሳ ወድያውኑ ቤተሰብ ሳታሳውቅ ባል አግብታ ሄደች፡፡ ቤተሰቡም ምንም ቢሆን ልጃችን ናት ብለው ለመጠየቅ ሄደው ከባል ቤተሰብ ጋር ተዋውቀው ሰላም አወረዱ፡፡ ከአመት በኋላ ልጅቱ ወልዳ የእሷ ቤተሰቦች አቅማቸው የፈቀደውን ያህል ምግብ አዘጋጅተው ወደ አራሷ ቤት ሲሄዱ "እናንተ ሙስሊሞች አይደላችሁም፤ እናንተ የሰራችሁትን ምግብ መብላት አይገባም" ብላ ቤሰቦቿ ይዘው የሄዱትን ምግብ ይዘው እንዲመለሱ ማድረጓን ወጣት ነኢማ መሀመድ ጥር 2006 ዓ.ም ባደረኩላት ቃለመጠይቅ ነግራኛለች፡፡ ሁለተኛው ምሳሌዬ በ2005 ዓ.ም በተደረገው የእስልምና ምክር ቤት ምርጫ ጊዜ አጎቴ የሆኑት አቶ አህመድ ዓሊ "ልጄ የመውሊድ አክባሪ መረጣ ላይ ለመሳተፍ የምርጫ ካርድ ወስደህ መንግስት ያዘጋጀውን ካድሬ ትመርጥና እገልሀለሁ ብሎ አስፈራርቶኛል" ብለው ነገረውኝ ልጁን አግኝቼ አባቱን እንደሱ መናገር ሳይሆን ትክክል ያልሆነ ነገር ካለ በትዕግስት እና በስርዓቱ ማስረዳት እንዳለበት መናገሬን አስታውሳለሁ፡፡

ባጠቃላይ በዞኑ ያለው በተለይ የወጣቱ ሁኔታ ሲታይ መውሊድ ወደ ፊት እንዳሁኑ በደመቀ ሁኔታ የመከበሩ ሁኔታ አደጋ ውስጥ የሚወድቅ ይመስላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የመውሊድ ሰሞን መውሊድ መከበሩን የማይደግፉ መውሊድ አንዳንድ(ሰለፎች) ሰዎች መንገድ ላይ በመቆም ወደ መውሊድ የሚሄዱ ሰዎችን ወደ መውሊድ መሄድ እንደሌለባቸው ከማስተማር በተጨማሪ እስከ ማስፈራራት ደርሰዋል፡፡ ይህን የማስፈራራት ሁኔታ በመፍራት ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ወደ መውሊድ ከመሄድ የሚቆጠቡ አሉ፡፡ በተለይ በ2007 ዓ.ም የመውሊድ ቀን "በሀረም ው በመውሊድ አክባሪዎች ላይ ወሀቢያዎች ጥቃት ሊያደርሱ ነው" የሚል ወሬ በማፈሱ የጠወሰኑ ሰዎች በጊዜ ወደ ቤታቸው ተመልሰዋል፡፡ ከማስፈራራት በተጨማሪ በተለዩ ጊዜዎች ወደ መስጂዶች በመዘዋወር እና በየቤቱ በመሄድ መውሊድ ምንም እስላማዊ

መሰረት እንደሌለው የሚያስተምሩ ሰዎች በዝተዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአማርኛ እና በስልጥኛ ቋንቋዎች መውልድ ምንም አይነት የቁርኣንም ሆነ የሀዲስ ድጋፍ እንደሌላው የሚያጥቁ የተለያዩ ሀዲሶች በካሴት ታትመው በዞኑ የሚገኙ በመሆናቸው ህብረተሰቡ በብዛት ያደምጣቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ መውሊድ የሚያከብሩ ሰዎች ሀሳባቸውን እያስቀየራቸው እንደሆነ የሰበሰብኳቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ስለዚህ ሰለፊዝም በመውሊድ ላይ ከተጋረጡ ጋሬጣዎች መካከል የአንበሳውን ደርሻ ይወስዳል፡፡ ባጠቃላይ እነዚህ እና ሌሎችም ሃይማኖታዊ ምክንያቶች በመውሊድ አከባበር እና ቀጣይነት ላይ ከፍተኛ የሆነ ተጽእኖ እየፈጠሩበት ይገኛል፡፡

**ለ. በአመክኒዮ የሚያምን ትውልድ እየተፈጠረ መሆኑ፡-** አለማችን ከድሮው በተሻለ ሁኔታ ለእያንዳንዱ ጉዳይ በምክንያት የሚያምን ትውልድ እየተፈጠረ እንደሆነ ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ እንደእነዚህ ጥናቶች አገላለጽ የዚህ ዘመን ትውልድ ለምን? ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ይቻላል እንዴ? እና ሌሎቹንም ጥያቄዎች በማንሳት የአንድን ነገር ትክክለኛነት ለማረጋገጥ እንደሚጥር ያሳያሉ፡፡ ይህ ሁኔታ በሀገራችን የሚስተዋሉ ስለመሆናቸው አያጠያይቅም፡፡ ምክንያቱም መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉ ሰዎች ለተቃውሞቻቸው ከሚያቀርቡት ምክንያት መካከል በመውሊድ ይገኛሉ የሚባሉ ቱርፋቶች አሳማኝ አይደሉም የሚለው ይገኝበታል፡፡ ለምሳሌ ሁሴን "አሁን እነሱ በዚያራ ስም መቃብር ይስማሉ፣ ከመቃብሩ አፈር አንስተው ይቀባሉ፣ አልከስዬ ድረሱልን፣ ልጅ አጥቻለሁ ልጅ ስጡኝ ሌላም ሌላም ይላሉ፡፡ ይህ እኮ የሚያስቅ ነው፡፡ አንተ ስታስበው ይህ እንዴት ሊሆን ይችላል፡፡ የማይሆን እኮ ነው፡፡ ሁሉንም አላህ ብቻ ነው የሚያሳካው፡፡ አሁንም እስኪ መንዙማዎች ምን እንደሚሉ ስማቸው፣ ያላህ ያስፈራል እኮ" በማለት በመወሊድ ሰሞን የሚከናወኑ ጉዳዮች ምክንያታዊ እንዳልሆኑ ያስረዳል፡፡ ይህ ሀሳብ ሀሳብ በተተኳሪ የቡድን ውይይት ወቅት ተነስቶ በሰፊው ውይይት ተደርጎበታል፡፡ ከውይይቱ እንደተረዳሁት መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉት ወገኞች "በመውሊድ ሰሞን የሚከናወኑ ክንውኖች ሃይማኖታዊም ሆነ ሌላ ምክንያት የሌለው" የለውም ብለው እንደሚያምኑ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በወደፊቱ የአልከሶ መውሊድ ከበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እየፈጠረ መምጣቱን መረዳት ይቻላል፡፡

**ሐ. የመገናኛ ብዙኋን መስራፋት፡-** በአሁኑ ጊዜ ከሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር የሚሰራጩ የተሌቪዥን ፐርግራሞች መብዛታቸው እና ከዚህ በፊት ከነበረው ሁኔታ በብዛት ተደማጭነት ማግኘታቸው መውሊድ እና መሰል ከበራዎች ላይ ተጽዕኖ በመፍጠር ላይ

ይገኛሉ። ከእነዚህ ጣቢያዎች መካከል Peace Tv፣ Huda Tv እና Africa Tv በሀገራችን በስፋት የሚደመጡ የሙስሊም ጣቢያዎች ናቸው። ከዚህ በተጨማሪ በሀገራችን የሚታተሙ እና ከውጭ የሚገቡ የሙስሊም ጋዜጦቶች እና መጽሔቶች ይገኛሉ። ለምሳሌ በሀገራችን ቋንቋዎች (አማርኛ፣ኦሮምኛ፣ ትግርኛ፣ ሶማሊኛ) ትምህርት የሚሰጠው የቴሊቪዥን ጣቢያ የሆነ አፍሪካ ቲቪ ስለ ቢድኣ እና ተውሂድ(ቅድምያ ለሃይማኖት) ትምህርት በመስጠት ላይ ይገኛል። እነዚህ የተሌቭዥን ጠቢያ ቢድኣ ከሚላቸው ጉዳዮች መካከል በወልዮች ከሞቱ በኂላ ማመን፣ የቀብር ዚያራ፣ የመውሊድ ከከበራ ወዘተ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ይህ የተሌቭዥን ጣቢያ በአልከሶ መውሊድም አሉታዊ ተጽእኖ በመፍጠር ላይ ይገኛል። ይህን በማስመልከት ሼኽ አብዱልረዛቅ "አሁን አንዳንድ እንደ አፍሪካ ቲቪ ያሉ ጣቢያዎችን የሚከታተሉ ወጣች የእሱን ወሬ እየሰሙ በደንብ ሳያጣሩ መውሊድ ቢድኣ ነው የሚሉ አሉ። እዚህ አልከሶ መንገድ ላይ ቆመው የአልከሶን መውሊድ የሚቃወሙ አሉ።" የሼኽ አብዱረዛቅን ሀሳብ አቶ ሁሴይኒ ይጋሩታል።

**መ. የኑሮ መወደድ፡-** የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ሲለው የአኗኗር ዘይቤውም አብሮ ይለወጣል። ይህ ማለት የአንድ ሀገር ኢኮኖሚ ሲያድግ የግለሰቦች ገቢም ስለሚጨምር ፍላጎታቸውን ያሟላሉ። በተቃራኒው የኢኮኖሚ ውድቀት ሲያጋጥም አሊያም የኑሮ ውድነት ሲኖር ደግሞ መሰረታዊ ፈላቶችን ማሟላት ያዳግታል። ቅርብ አመታት ወዲህ በአለማችን ብሎም በሀገራችን የኑሮ መወደድ የህዝቡን የአኗኗር ሁኔታ እየለወጠው ይገኛል። ይህ ሁኔታ ማህበረሰቡ በየጊዜው ተሰብስቦ በሚያከብራቸው ክብረ በዓላትም ጭምር የራሱን አሻራ ያሳርፈል። የኑሮ ውድነት በአከባበር ስርዓቱ ላይ አሉታዊ ጥላ ካጠላባቸው ክብረ በዓላት መካከል የአልከሶ መውሊድ አንዱ ነው። ምክንያቱም ምእመናን ወደ መውሊድ ሲሄዱ ይዘዋቸው ይሄዱ የነበሩ በርካታ ቁሳቁሶች መጠናቸው እየቀነሰ እና ሙሉ በሙሉ እየቀሩ መጥተዋል። ስለዚህ ጉዳይ አቶ ሁሴይኒ[187] የሚከተለውን ይላሉ።

> በአሁኑ ጊዜ የመውሊድ አከባበር በተወሰነ ደረጃ በመለወጥ ላይ ነው። ከለውጡ መካከል ድሮ ድሮ በአልከሶ መውሊድ ግመል በስጦታ መጥቶ ይታረድ ነበር አሁን ግን አይታድም። የሳንኩራ ወረዳ ሰዎች ጤፍ በብዛት ያመጡ ነበር አሁን ግን ማምጣ ትተዋል። እንደገና ብርዝ በብዛት ይሰራ

[187] ቃለመጠይቅ 23/05/08 ወራቤ

ነበር አሁን ማር ስለተወደደ የልም። የሰው ብዛት እየጨመረ ስለሄደ ስጋም እንደ ድሮ ማዳረስ እያስቸገረ ነው። በአሁኑ ጊዜ የመውሊዱ ትልቅ ወጪ የሚሸፈነው አልከስዬ ከያዙት ይዞታ ነው። ሰው እንደልቡ እንዲያመጣ የከለለው የኑሮ ውድነት እና የልጅ መብዛት ይመስለኛል።

የአቶ ሁሰይኒን ሀሳብ በርካታ መረጃ አቀባዮች ይስማሙበታል ምክንያቱም ስለ መውሊድ ለውጥ በቡድን ውይይት በተካሄደበት ውቀት ሀሰቦ ተነስቶ የአቶ ሁሴይኚ ሀሳብ ትክክል መሆኑን አረጋግጫለሁ። ይህ ለውጥ እና የኑሮ መወደድ መውሊዱ እንዳሁኑ በሰፊው የመከበር እድሉን እያጠበበው ሊሄድ ይጭላል። ምክንያቱም ሌሎች ተጽእኖች ተጨምረውበት ወደ መውሊዱ የሚሄዱ ቁሳቁሶች መቅረባቸው ከቀነሰ ብሎም ከጠፋ ወደ መውሊዱ የሚሄዱ ምዕመናንም ቁጥር እየቀነሰ ይሄዳል። ወደ መውሊድ ከመሄዱ ሰዎች መካከል ምግብ ፍለጋ የሚሄዱ በርካታ ሰዎች አሉና። የተሳታፊዎች ቁጥር እየቀነሰ መሄዱ ደግሞ የመውሊዱን ድምቀት እየቀነሰው ይሄዳል።

ባጠቃላይ ከዚህ በላይ የተመለከትናቸው ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶች በመውሊድ ከበራ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩ ናቸው። ወደ ፊት ከአሁኑ በበለጠ ሁኔታ የተጽእኖ ጡንቻቸው እየፈረጠመ እንደሚሄድ ሁኔታዎች ያሳያሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ የመውሊድን የዘላቂነት ህልውና አደጋ ላይ ሊጥለው ይችላል።

መውሊድ ወደ ፊት በመቀጠሉ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩ በርካታ ጉዳዮች ቢኖሩም በተወሰነ ደረጃ ደግሞ እንደቀጥል የሚያደርጉ ሁኔታዎች አሉ። ለምሳሌ የሚከተሉትን ጉዳዮች በዋናነት መመልከት ይቻላል።

**ሀ.የመንግስት ድጋፍ መኖሩ፡-** መንግስት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በተለይ ከ2000 ዓ.ም ጀምሮ አክራሪ ብሎ የሚጠራቸው እና በተለምዶ ወሀብያዎች የሚባሉትን ለማዳከም ከሚጠቀምባቸው መንገዶች መካከል አንዱ ሱፊዝምን እና አህባሽን ማጠናከር ነው። ይህን ሀሳብ ostobe(2014) እና ሌሎቹም ይጋሩታል። በመሆኑም መንግት በአሁኑ ዘመን በሱፊ ማዕከሎች የሚካሄዱ እንቅስቃሴዎችን በመደገፍ ላይ ይገኛል። ድጋፉ በሀሳብ እና በቁሳቁስ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። ድጋፉ የጸጥታ ሀይል ከመመደብ ጀምሮ አልፎ አልፎ ደግሞ

የገንዘብ ድጋፍ ያደርጋል- በተለይ ከ2005 ወደህ ጀምሮ። ስለዚህ የመውሊድ ደጋፊው መንግስት ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ የመውሊድ ህልውና ተጠብቆ ሊቆይ ይችላል።

**ለ.አባቶች እና እናቶች ልዩ ፍቅር፡-** አባቶች እና እናቶች ለመውሊድ ልዩ ፍቅር እንዳላቸው ለመረዳት በመውሊድ ሰሞን የሚሰባሰቡ ምዕመናን መመልከት ይቻላል። በአልከሶም ሆነ እኔ በተመለከትኳቸው በስልጤ ዞን በሚከበሩ መውሊዶች መውሊድን ከሚያከብሩ ምዕመናን መካከል አዛውንቶች ይበዛሉ። ስለዚህ እነዚህ አዛውንቶች በህይወት እስካሉ ድረስ መውሊድ መከበሩ ሊቀጥል ይችላል። በእርግጥ እነዚህ አባቶች እና እናቶች ሲያልፉ ወጣቶች አዛውንቶቹን ቦታ ካልተኩ የመውሊድ እጣ ፋንታ ምንድን ነው የሚለው አጠያያቂ ቢሆንም።

**ሐ.ቁጥራቸው ጥቂት የመይባል ወጣቶች መከተላቸው፡-** በዓሉ መከበር የለበትም የሚሉት ወገኖች ወጣቶች መሆናቸውን ከተመለከትኩ በኋላ መከበር አለበትም ለሚሉ ወገኖች ከስር ያለው ትውልድ በብዛት መውሊድ መከበር የለበትም በማለት እያከበሩ አይደለምና ወደ ፊት መውሊድ ያለመከበር እድል ሊገጥመው አይችልም? የሚል ጥያቄ አቀረብኩላቸው። አቶ ኑረዲን (08፣25/2007) "ወጣቶቹ እየበሰሉ ሲሄዱ መውሊድን ማክበር ምን ያህል ጥቅም እንዳለው ሲረዱ መልሰው ማክበር ይጀምራሉ። የአልከሶ መውሊድን ሲከበር ተመልከት በዓሉን የሚያከብረው ሰው ቁጥር ሲጨምር እንጂ ሲቀንስ አይተሀል አላየህማ አንተ አዲስ ነህ።" የሚል ሀሳብ ካቀረቡ በኋላ "የአልከሶን መውሊድ ማክበር ብዙ ጥቅም አለው። ወጣቱም ያንን ጥቅም ስያይ እሱም ይሳተፋል። ደግሞም በአሁኑ ጊዜ መውሊድ ሲከበር ስታይ ከሽማግሌ ይልቅ ህጻናት እና ወጣቶች ናቸው" ብለዋል።

የአልከሶ መውሊድ በጊዜ ሂደት ውስጥ ከተስተዋሉበት ለውጦች መካከል የስልጤ ብሔረሰብ በርካታ ቁሳዊ እና መንሳዊ እሴቶች በየጊዜው እየጎሉ በመሄድ ላይ እንዳሉ ይነገራል። በመሆኑም ከዚህ በታች በአልከሶ መውልድ ምን ምን የስልጤ ብሔረሰብ ባህል እንደሚጸባረቅ እና እንዴት እንደሚጸባረቅ እንመለከታለን።

## 9.3 በአልከሶ መውሊድ የተንጸባረቁ ስልጤ ብሔረሰብ ባህሎች

መውሊድ በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች እንደሚከበሩ ከዚህ በፊት የተመለከትናቸው ጥናቶች ያሳያሉ፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው መውሊድ ደግሞ መሰረቱ ሃይማኖት ነው፡፡ ስለዚህ የሁሉም መውሊዶች መከበር መሰረታቸው ሃይማኖት ቢሆንም አክባሪዎቹ የራሳቸውን አሻራ እየጨመሩ እንደሚያከብሩት Trimingham (1952:226) ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ስልጤዎችም መውሊድን የራሳቸውን የባህል አሻራ በማከል ያከብሩታል፡፡ ስለዚህ ስልጤዎች በአልከሶ መውሊድ እነሱን የሚገልጽ ምን አሻራ አሳረፉበት የሚለውን ቀጥዬ እንደሚከተለው አቀርባለሁ፡፡

**ሸምሰል ጀማል መስጂድ፡-** ስልጤዎች በአልከሶ ሀረም እና መውሊድ ምን አሻራቸውን አሰረፉ ብለንስንመረምር መጀመሪያ የምናገኘው ትልቁን ሸምሰል ጀማል መስጂድን ነው፡፡ ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ይህ መስጂድ የሚገኘው አልከሶ ሀረም ውስጥ ነው፡፡ ይህ መስጂድ ውስጣዊ እና ውጫዊ ገጽታውን ስንመለከት የስልጤ ብሔረሰብን የቤት አሰራር ሁኔታ የተከተለ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሀረሙ ውስጥ ጥቂት የማይባሉ ኸለዋዎች የብሔረሰቡን የቤት አሰራር ተከትለው ተሰርተው እናገኛለን፡፡ ስለዚህ ስልጤዎች ቁሳዊ ባህላቸውን(የቤት አሰራራን) በዚህ መስጂድ አማካይነት አስተዋውቀዋል ማለት ይቻላል፡፡

**ባህላዊ ምግብ፡-** በአልከሶ መውሊድ የስልጤ ብሔረሰብ ባህሉን ከሚያንጸባርቅበት መንገድ መካከል ባህላዊ ምግብ አንዱ ነው፡፡ ምክንያቱም ቀደም ብለን በዚህ ክብረ በዓል በርካታ የብሔረሰቡ ባህላዊ ምግቦች እና መጠጦች ለምግብነት እንደሚቀርቡ ተመልክተናል፡፡ በዚህ በዓል ከብሔረሰቡ ውጭያሉ ኢትዮጵያዊያን እና ኢትዮጵያዊ ያልሆኑ ሰዎች የሚገኙ በመሆኑ ይህ መውሊድ መከበሩ ብሔረሰቡ ባህላዊ ምግቡን የሚያስተዋውቅበት መድረክ በመሆን አገልግሎል፡፡ ይህን ሁኔታ ስልጤዎች በመውሊድ የራሳቸውን የቁሳዊ ባህል አሻራ አሳርፈውበታል ለማለት ያስችላል፡፡

**ሰላምታ አሰጣጥ ፡-** በመውሊድ ሰሞን ከሚንጸባረቁ ባህላዊ ጉዳዮች መካከል የሰላምታ አሰጣጥ ስርአት አንዱ ነው፡፡ እንደሚታወቀው በሀገራችን ሰላምታ ሲሰጣጡ ወይም ሲሳሳሙ (ተመሳሳይም ይሁን ተቃራኒ ጾታ) በሁለት ጉንጭ ከመሳሳም ይልቅ በአንድ ጉንጭ ከሚሳሳሙ ብሔረሰቦች መካከል የስልጤ ብሔረሰብ አንዱ ነው፡፡ በስልጤዎች ዘንድ ይህ

መሳሳም ከንፍር ለከንፈር(አሁን በብዛት ባይስተዋልም) የሚሆንበት ሁኔታ አለ፡፡ ይህ የአሳሳም ሁኔታ በመውሊድ ሰሞን ይንጸበራቃል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በአልከሶ ሀረም ከእስላማዊ ሰላምታ አሰጣጥ(አሰላምአለይኩም) ከማለት ይልቅ ባህላዊ ሰላምታ አሰጣጥ(ፈያም አለሙ፣ ፈያም ሲነበትኩሞም፣ ወልድ ፈያን… ሲተረጎም በሳላም አላችሁ፣ ሰላም ሰንብታችኂላ፣ ልጆች ደህን ናቸው ወዘተ) ይበዛበታል፡፡ ይህን ሁኔታ ስልጤዎች የሰላምታ አሰጣጥ ባህላቸውን በመውሊድ ሰሞን ያስተዋውቃሉ ለማለት ያስደፍራል፡፡

**ባህላዊ አልባት፡-** ስልጤዎች በመውሊድ ሰሞን ከሚያንጸባርቁት ባህላዊ ጉዳይ መካከልባህላዊ የአለባበስ ስርአት ነው፡፡ በዚህ መውሊድ ሁሉም ምዕመናን ባይባልም በተለይ ጎልማሶች እና አዛውንቶች የብሔረሰቡን የባህል አልባሳት ለብሰው ይታያሉ፡፡ እነዚህ ምዕመናን ቀይ በነጭ ወይም ቀይ በጥቁር የሆኑትን ደማቅ ባህላዊ አልባሳት ለብሰው በሀረሙ መገኘታቸው ለመውሊዱ ልዩ ድምቀት ይሰጠዋል፡፡ ይህ አለባበስ ለመውሊዱ ድምቀት ከመስጠቱ ባሻገር ብሔረሰቡ ባህላዊ ልብሱን በመውሊድ ሰሞን በመልበስ መውሊድ ላይ የራሱን ባህል ያንጸባርቃል፡፡

Smith (1972፣168) "በበዓል ወቅት በዓል አክባሪዎች ባህላዊ ልብስ ለብሰው እና አጊጠው፣ በእጅ የተሰሩ ቁሳዊ ባህሎችን ይዘው በመዘመር፣ ባህላዊ ጭፈራዎችን እና ከክብረ በዓሉ ጋር የተያያዙ ሥነ ቃላዊ እና ባህላዊ እና ልማዳዊ ጉዳዮችን ያከናውናሉ" ይላሉ፡፡ የSmith አገላለጽ በአልከሶ መውሊድ ላይ ከሚስተዋለው የአለባበስ እና የአጋጌጥ ሁኔታ አንጻር ትክክል ነው ማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም ስልጤዎች መውሊድን ሲያከብሩ እግረ መንገዳቸውም ባህላቸውን ያንጸባርቃሉ፡፡ በመስክ ቆይታዬ እንደተመለከትኩት የስልጤ ብሔረሰብ ባህላዊ ጭፈራዎች የሚባሉት (ቦልቦሌ፣ መስቃን፣ሱክሱኬ…) አልፎ አልፎ ወጣቶች ሲጨፍሯቸው ተመልክቻለሁ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ጭፈራዎች የቀድሞ ባህላዊ ይዘታቸውን የጠበቁ ሳይሆን ዘመናዊነት ይስተዋልባቸዋል፡፡ ከአለባበስ እና ከአጋጌጥ አንጻር ደግሞ የብሔረሰቡ ባህላዊ ልብስ ሁለቱም ጾታ እና በየትኛውም የእድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ ሰዎች ሲለብሱ ተመልክቻለሁ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ወንዶች የብሔረሰቡን ባህል እና እስልምናን የሚያንጸባርቀውን ኮፊያ(ክብ እና ነጭ ሆኖ በመሀል በመሀል ቀይ ጣል ጣል ያለበት) በብዛት ለብሰው አይቻለሁ፡፡

**መንዙማዎች፡-** በአልከሶ መውሊድ የሚካሄዱ ስርዓቶች አብላጫዎቹ የስልጤን ባህል የሚያሳዩ ናቸው፡፡ ሃይማኖታዊ ጉዳይ ከሚባሉት ጉዳዮች መካከል በዋናነት የሚካሄደው የሷላት ስግደት እና የተወሰኑ የመንዙማ ስርዓት ብቻ ነው፡፡ በዚህ መውሊድ ሃይማኖታዊ መሰረት ያለው የመንዙማ ስርዐት ይካሄዳል፡፡ ከሰበሰብኳቸው የመንዙማ ግጥሞች አንጻር አብላጫዎቹ ግጥሞች ከሃይማኖታዊነት ይልቅ ማህበራዊ ጉዳይ ይበዛባቸዋል፤ በተለይ በነዚህ መንዙማዎች የሚነሱ ጉዳዮች የአልከስዬን ትልቅንት የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ ከማህበራዊ ጉዳዮች መከካል ደግሞ የብሔረሰቡን ባህል፣ ታሪክ፣ አኗኗር፣ አስተሳሰብ፣ የእርስ በእርስ ግንኙነት ወዘተ የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡ በመሆኑም የስልጤ ብሔረሰብ የአልከሶ መውሊድ እንደወረደ ሃይማኖታዊ ይዘት ባለው መልክ ከማክበር ይልቅ የራሱን ባህል በማንጸባረቅ ያከብረዋል ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ በፊት የተመለከትኳቸው ትኩረታቸውን መውሊድ ላይ ያደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተለያዩ ቦታዎች የሚከበሩ መውሊዶች ከበራቸው ላይ በብዛት የሚካሄደው ሃይማኖታዊ ክንውን ነው፡፡ ነገር ግን ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት በአልከሶ መውሊድ ሲካሄድ የተመለከትኩት ከሃይማኖታዊ ጉዳይ ይልቅ ማህበራዊ ጉዳይ ነው፡፡ ስልጤዎች መውሊድን ሃይማኖታዊ ጉዳይ ብቻ አድርገው ከማሰብ ይልቅ ማህበራዊ ጉዳዮችን በመጨመር ያከብሩታል፡፡ ስለዚህ “ሃይማኖት ባህል ነው” የሚለው አስተሳሰብ እንደለ ሆኖ ስልጤዎች መውሊድን የባህላቸው አንድ አካል አድርገውታል፡፡ ምክንያቱም በተለይ ልጆች እና ወጣቶች መውሊዱን የሚያከብሩበት ሁኔታ መውሊድ ሃይማኖታዊ መሰረት እንዳለው አያውቁም ለማለት በሚያስደፍር ደረጃ ለማህበራዊ ጉዳይ ትኩረት ይሰጣሉ፡፡ የአልከሶ መውሊድ ከሃይማኖታዊ ክብረ በዓልነት ባለፈ የስልጤ ብሔረሰብ ባህል የሚጸባረቅበት በዓል ጭምር ነው፡፡

## 9.4 የመውሊዱ መከበር ፋይዳ/ተግባር

Bascom (1989፣334) አንድ የፎክ ቡድን (Folk Group) ከሚያከብረው ከበራ ጠቅላል ባለ እይታ ሲታይ አራት ዋና ዋና ተግባራት ወይም ጠቀሜታዎች እንዳሉት ማስረዳታቸውን በምዕራፍ ሶስት ተመልክተናል፡፡ እነዚህ አራት ዋና ዋና ተግባራት የስልጤ ብሄረሰብ በመውሊድ ሰሞን ተግባራዊ ያደርጋቸዋል፡፡በመሆኑም የአልከሶ መውሊድ ከዚህ በላይ በተመለከትነው ሁኔታ መከበሩ ለአከባቢው ማህበረሰብ ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታዎችን ያስገኛል፡፡

ጠቀሜታውን ከሃይማኖት፣ ከኢኮኖሚ፣ ከልማት፣ ከማህበራዊ ግንኙነት እና ከስነልቦና አንጻር የምንመለከተው ነው፡፡

**ሃይማኖታዊ ፋይዳ፡-** በመውሊድ ሰሞን በርካታ ህዝብ ተሰብስቦ በቀን አምስት ጊዜ በጀማ (በጋራ) ፈርድ(ግዴታ) እና በርካታ ሱና(ግዴታ ያልሆነ) ሶላት ይሰገዳል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ሀዲሶች ስለሚነገር እና ስለሚያዳምጥ የመውሊድ በአካባቢው መከበሩ ለአካባቢው እና መውሊድ ለማክበር ከተለያዩ ቦታዎች ለተሰባሰቡ ምዕመናን ሃይማኖታዊ ጠቀሜታው የጎላ ነው፡፡

**ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ፡-** በመውሊድ ሰሞን ከፍተኛ የሆነ የንግድ እንቅስቃሴ ስለሚካሄድ የአካባቢው ማህበረሰብ በዚህ የንግድ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ ነው፡፡ ይህን ክብረ በዓል ከልማት አንጻር ስንመለከተው መውሊድ በሚከበርበት አካባቢ በርካታ መሰረተ ልማት እንዲሟላ ምክንያት ሆኗል፡፡ ለምሳሌ ከአልከሶ ከተማ እስከ አልከሶ ሀረም የመኪና መንገድ ተሰርቷል፡፡የዚህ መንገድ የአካባቢው ማህበረሰብ ከወራቤም ሆነከአልከሶ ከተማ እስከ ቤቱ በር ድረስ በመኪና እንደሄድ እና የንግድ እንቅስቃሴ እንዲኖር አስችሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአልከሶ ሀረም የንጽህ ውሃ(የቧንቧ) ተጠቃሚ ነው፡፡ ይህ ውሃ የመጣው ከአልከሶ ከተማ ስለሆነ ከከተማው እስከ ሀረሙ እና በሀረሙ ዙሪያ የሚኖሩ አርሶ አደሮች እና ነጋዴዎች የዚህ ውሃ ተጠቀሚዎች ናቸው፡፡ እንደ አቶ ነስሮ እና ሀጂ ሀምዲኖ አገላለጽ የአልከሶ ሀረም እስከ 2000 ዓ.ም የመብራት ሀይል ተጠቃሚ አልነበረም፡፡ ነገር ግን ከላይ ከተጠቀሰው ዘመን ጀምሮ ዋና መስጂድ እና የተወሰኑ ኸለዋዎች መብራት ገብቶላቸዋል(በአሁን ጊዜ ሁሉም ኸለዋዎች መብራት አላቸው)፡፡ የዚህ ሀረም የመብራት መኖር በሀረሙ ዙሪያ የሚገኙ መኖሪያ ቤቶች የመብራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ምክንያት እንደሆነ እሜት ሀረም ያስረዳሉ፡፡ ስለዚህ ከከተማው እስከ ሀረሙ የመኪና መንገድ መኖሩ የሀረሙ የአካባቢው ማህበረሰቦች በመኪና ወደ ፈለጉት ስፍራ እንዲሄዱ እና እናቶች ምጥ በሚይዛቸው ጊዜ አንቡላንስ በራቸው ድረስ እንዲመጣ አስችሏል፡፡ የንጽህ ውሃ በሀረሙ መኖሩ ደግሞ የአካባቢው ማህበረሰብ የንጽህ ውሃ ተጠቀሚ እንዲሆን ምክንያት ሆኗል፡፡ መብራት መኖሩ ህብረተሰቡ የተለያዩ የመገናኛ ብዙሃንን የመከታተል እድል ፈጥሮለታል፡፡ ይህ እንድል ያስቻለኝ ጥቂት ቤቶች ላይ የተሌቪዥን አንቴና እና "ዲሽ" ጣራቸው ላይ ተሰቅሎ ተመልክቻለሁ፡፡ ስለዚህ የመውሊዱ መከበር የአካባቢውን መህበረሰብ የአኗኗር ዘይቤ ለውጦታል ማለት ይቻላል፡፡

**ስነልቦናዊ ፋይዳ፡-** ምዕመናን ከመውሊድ ከሚያገኙት ጠቀሜታ መካከል አንዱ ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ ይገኝበታል፡፡ ምዕመናን መውሊድ ሲያከብሩ በደስታ በመታጀብ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ለምዕመናኑ ስነልቦናዊ ጠቀሜታ ያስገኛሉ፡፡ በተለይ ደግሞ መውሊድ አክባሪዎች በተለየዩ ጉዳዮች ውጥረት ውስጥ ገብተው ወደ ዚያራ ቦታ ሄደው የተለያዩ ቁሳቁሶችን ሰጥተው እና ዱኣ አድርገው ሲመለሱ ቀደም ብሎ አእምሯቸውን ወጥሯቸው የነበረው ጉዳይ ቀለል ሲላቸው ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ በ14/9/2008 ዓ.ም መውሊድ ሲከበር አንድ እናት ከልጃቸው ጋር በመሆን በአህያ ብዙ ፊናንቾ(ቆጮ) ጭነው አምጥተው ዱኣ አስደርገው ሲመለሱ አግቼ ይሄን ሁሉ ቆጮ ለምንድን ነው ያመጡት? አልኳቸው፡፡ እሳቸውም “አምና ቃል ገብቼ ነበር፡፡” አሉኝ፡፡ እኔም ለምን? ምን ሲሉ? አልኳቸው፡፡ እሳቸውም “ይሄ ልጄ (የልጃቸውን ጸጉር እየዳበሱ) ጸጉሩ አመድ ቡን ይለው ነበር፡፡ አምና በዚህ ጊዜ መጥቼ ብር ሰጥቼ ልጄን ከተሻለው የዛሬ አመት አንድ ትልቅ እንሰት እሰጣለሁ ብዬ ቃል ገባሁ፡፡ ልጄም አፊያ(ጤነኛ) ስለሆነልኝ እንስቱን ፍቄ ምንም ሳላስቀር ከልጁ ጋር ይዤ መጣሁ” ብለውኛል፡፡ ከእኚህ እናት እና መሰሎቻቸው ሁኔታ መረዳት የሚቻለው በመውሊዱ ወቅት ስጦታ መስጠታቸው ስነልቦናዊ ጠቀሜታ እንደሚያስገኝላቸው ነው፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች እዚህ ቦታ ላይ በመምጣት ስጦታ በመስጠት ዱኣ አስደርገው ለጊዜውም ቢሆን ከጭንቃታቸው ይገላገላሉ፡፡

ለዚህ ምሳሌ የሚሆነው ቀደም ብዬ የገለጽኩት ሰዎቹ ወደ መነየቻ ቦታ ሲመጡ የነበራቸው የጭንቀት ፊት ስጦታቸውን(ንያቸውን) ሰጥተው ሲመለሱ ያ ሁሉ ጭንቀት እንደሚለቃቸው ከፊት ገጽታቸው መረዳት ይቻላል፡፡ ምዕናን ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ የሚያገኙት ስጦታ በመስጠት እና ዱኣ በማድረግና በማስደርግ ብቻ አይደለም፡፡ ለአልከሶ መውሊድ የተዘጋጀ ምግብ መመገብ በረከት አለው ብለው ስለሚያምኑ አልከሶ ሀረም ተግኝተው ምግብ ሳይመገቡም ሆነ ሳይቀምሱ አይመለሱም፡፡ በመሆኑም ይህን ምግብ በመመገብ ስነ ልቦናዊ እርካታ ያገኛሉ፡፡

ባጠቃላይ ልክ እንደ እኚህ እናት ሁሉ በርካታ ምዕመናን ለተለያዩ ችግሮቻቸው መፍትሔ ለማፈላለግ ወደ አልከሶ መውሊድ ይሄዳሉ፡፡በመሆኑም አልከሶ ሀረም በመሄድ ዱኣ አስደርጌ ከችግሬ ተገላገልኩ፣ ከበሽታዬ ተፈወስኩ እና ሌሎችን የምስክርነት ቃላቸውን የሚሰጡ ምዕመናን በርካታ ናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ ለምዕመናን ስነ ልቦናዊ ፋይዳ አለው ማለት ይቻላል፡፡

**ማህበራዊ ፋይዳ፡-** የመውሊድ አክባሪዎች በመውለድ በመሰባሰብ እርስ በእርስ እና ከክርስትያን ምዕመናን ጋር መልካም ግንኙነት በመፍጠር ማህበራዊ ግንኙነታቸውን ያጠናክራሉ። ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶች በዚህ መውሊድ ተገናኝተው ይጫወታሉ ይዝናናሉ እንዲሁም ማህበራዊ ግንኙኘት በመፍጠር እስከትዳር የሚደርሱ አሉ። ስለዚህ የዚህ አይነት ማህበራዊ ግንኙነት ማጠናከሩ የመውሊዱ መከበር ማህበራዊ ፋይዳ አለው ማለት ያስችላል። የአልከሶ መውሊድ መከበሩ ለመውሊዱ አክባሪዎች ከሚያስገኘው ጠቀሜታ መካከል አንዱ ማህበራዊ ትስስር መፍጠር ነው። ይህን በማስመልከት Fletcher (1966፣89) ክብረ በዓል አንድ ማህበረሰብ ውስጥ የመረዳዳት፣ በህብረት የመስራት፣ የመቀራረብ እና ግንኙነት የመፍጠር ተግባር እንዳለው ያስረዳሉ። ሰዎች ማህበራዊ ኑሮ እንዲመሰርቱ በደስታ፣ በሀዘን፣ በእርቅ፣ በሽምግልና አንዲገናኙ እና የመዋሀድ ኃይል እንዲኖራቸው ያስችላል። ኃይማኖታዊ ክብረ በዓላት በህብረት የሚካሄዱ በመሆናቸው በተመሳሳይ እምነት ውስጥ ያሉ ሰዎችን የጠበቀ መተሳሰር እና ቅርበት እንዲኖራቸው ያደርጋል። በሚያከብሩት ሰዎች መካከልም እርስ በርስ የመረዳዳት ስሜታቸውን እንዲያዳብሩ ያደርጋል። እኚህ ምሁር የገለጹት ሀሳብ በአልከሶ መውሊድም ይጸባረቃል።

ባጠቃላይ በዚህ ምዕራፍ በዋናነት የተመለከትነው የአልከሶ መውሊድ በጊዜ ሄደት በተለያዩ ምክንያቶች ያሳየውን ለውጥ፣ የስልጤ ብሔረሰብ በመውሊድ ምን ምን ባህሎቹን እንዳንጸባረቀ፣ በመውሊድ ከበራ ላይ የተጋረጡ  ጋሬጣዎች እና ምቾች ሁኔታዎች ምን ምን እንደሆኑ ነው።

# ምዕራፍ አስር

# 10. የጥናቱ ማጠቃለያ እና የይሁንታ ሀሳቦች

በዚህ ምዕራፍ ስር አጠቃላይ የጥናቱ ማጠቃለያ፣ በጥናቱ የተገኙ ግኝቶች እና የይሁንታ ሀሳቦች ተጨምቀው ቀርበዋል።

## 10.1 የጥናቱ ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአልከሶ መውሊድ የአከባበር ስርዓት እና ፎክሎራዊ ገጽታ ማሳየት ነው። በዚህ ዋና ዓላማ ስር የሚመዘዙ በርካታ ንዑሳን ዓላማዎች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል። የመውሊድ በዓል አጀማመር እና አከባበር በስልጤ ብሔረሰብ ምን እንደሚመስል ማሳየት፣ በመውሊድ ከበራ ወቅት ምን ምን ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና ሃይማኖታዊ ክንውኖች እንደሚከናወኑ ማብራራት፣ በመውሊድ የሃይማኖት መስተጋብር ምን እንደሚመስልእና መስተጋብሩ በአካባቢው ልማት እና ማህበራዊ ህይወት ላይ ምን አይነትተ ጽዕኖ እንዳለው ማሳየት፣ እና በመውሊድ የወደ ፊት ከበራ ላይ ምን አይነት ተጽእኖ የሚጥሩ ጉዳዮች ምንም እንደሆነ ማሳየት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ይህን ጥናት እንዳጠና ያነሳሳኝ ምክንያት የብሔረሰቡ ባህል በስፋት እና በጥልቀት አለመጠናቱ እና ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ጥናቶች ክፍተት እንዳለባቸው መረዳቴ ነው።

ይህ ጥናት በዋናነት የተካሄደው በአይነታዊ የምርምር ስልት ነው። በዚህ የምርምር ስልት ስር ክዋኔያዊ፣ ተግባራዊ፣ ለውጥ እና ቀጣይነት እና ኢትኖግራፊ ንድፈ ሀሳቦችን ተግባራዊ ሆኗል። ወደ መስክ ከጥቅምት 2007 ዓ.ም እስከ ጥር 2009 ዓ.ም ድረስ አምስት ጊዜ በመሄድ መረጃ በቃለ መጠይቅ፣ በምልከታ እና በተተኳሪ ቡድን ውይይት የተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎችን በመጠቀም ተሰብስቧል።

በዚህ ጥናት የአልከሶ መውሊድ ከቅድመ ዝግጅት እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ሂደት ምን እንደሚመስል ቀርቧል። በመሆኑም ቅድመ ዝግጅቱ ሶስት ወር ሲቀረው ይጀመራል። ዝግጅቱ ለዋናው መውሊድ አንድ ቀን እስኪቀረው ድረስ ይካሄድና ለረመዳን አስራ አምስት ቀን ሲቀረው እሁድ ዕለት በደመቀ ሁኔታ ይከበራል። በዚህ ከበራ ከተለያዩ ቦታዎች የተሰባሰቡ ሰዎች ይሳተፉበታል። በመሆኑም በመውሊዱ በርካታ ሃይማኖታዊ እና ማህበራዊ

ክንዋኔዎች ይከናወኑበታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዚያራም ይካሄዳል፡፡ ዚየራው ሁለት አይነት ነው፡፡ አንደኛው የአልከስዬ እና ቤተሰቦቻቸው ያረፈበት የመቃብር ስፍራ መጎብኘት ነው፡፡ ሁለተኛው በአሁኑ ወቅት መስጂዱን የሚመሩት መሪ ጋር በመሄድ ስጦታ እያበረከቱ መዘየር ነው፡፡ በዚህ ቀን ዘያሪዎች የአልከስዬ እና የቤተሰቦቻቸው የማቃብር ስፍራ ሰንደል፣ እጣን እና ሽቶ ይዘው በመግባት ይዘይራሉ፡፡ ወደ መሪዎች ሲሄዱ ደግሞ ከጥሬ ብር ጀምሮ የተለያዩ ምግቦችን እና የሚታረዱ እንሰሳትን ይዘው ይሄዳሉ፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት ከተዳሰሱት መካከል ስለ ድሬ ሼከና ሁሴን ወዳጆች እና የመውሊድ አከባበራቸው፣ የወጣቶች ግንኙነት፣ የንግድ እንቅስቃሴ እና የአመጋገብ ስርዓት ምን እንደሚመስል፣ በዚህ ክብረ በዓል የብሔረሰቡ የባህል ምግቦች እና መጠጦች እንዴት እንደሚዘጋጅ በዋናነት ከተዳሰሱበት መካከል ይገኙበታል ተዳሷል፡፡ በአልከሶ መውሊድ ከእስልምና ሀይማኖት በተጨማሪ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባል የተለያየ ዓላማ እና ምክንያት ያላቸው የክርስትና ሀይማኖት ተከታዮችም ይሳተፋሉ፡፡ ስለዚህ ይህ ሁኔታ በአካባቢው ሙስሊሞች እና ክርስትያኖች ተከባብረው እና ተቻችለው እንደሚኖሩ ያሳያል፡፡

በአጠቃላይ በዚህ ጥናት የአልከስዬ አጭር የህይወት ታሪክ፣ ከራማ እና የመስጂዳቸው አመሰራረት፣ የአልከሶ መውሊድ ከበራ እና ፎክሎራዊ ገጽታ፣ በመውሊድ ሰሞን የሚካሄዱ ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እንቅስቃሴ፣ በአልከሶ መውሊድ የሃይማኖት መስተጋብር ምን እንሚመስል፣ በአልከሶ መውሊድ ከበራ ላይ እየተስተዋለ ያለው ለውጥ፣ እና በመቀጠል ላይ ያሉ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ እና መውሊድ አክባሪዎች ከበራው የሚያገኙት ፋይዳ ምን ምን እንደሆነ በዋናነት የተዳሰሱ ነጥቦች ናቸው፡፡

የአልከሶ መውሊድ ቅድመ ዝግጅት ወራትን ቢፈጅም ከዚህ በላይ በተመለከትነው ሁኔታ አርብ ቀን ተጀምሮ በደመቀ ሁኔታ እየተከበረ እስከ ማክሰኞ (ስልስላ) ድረስ ይቆይና ይጠናቀቃል፡፡ በዚህ መውሊድ ከተለያዩ ቦታዎች ከገጠር እስከ ከተማ፣ ከልጅ እስከ አዋቂ፣ ከሙስሊም እስከ ክርስትያን፣ እና ሁለቱም ጾታዎች ይሳተፋሉ፡፡ የመውሊዱ አክብሪዎች ከመውሊዱ ባህላዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነ ልቦናዊ ጠቀሜታ እንደሚያገኙ ከዚህ ጥናት መረዳት ይቻላል፡፡

## 10.2 የጥናቱ ግኝቶች

ይህ ጥናት የአልከሶ መውሊድን ከቅድመ ዝግጅት ጀምሮ እስከ ፍጻሜ ድረስ ያለውን ሁኔታ በጥልቀት ተመልክቷል። ይህ በመሆኑም ጥናቱ የተለያዩ ጉዳዮችን ማረጋገጥ ችሏል። የሚከተሉት ዋነ ዋናዎቹ ናቸው።

- በአልከሶ ሀረም መውሊድ በአመት እስከ አስራ አራት ጊዜ ሊከበር እንደሚችል ይህ ጥናት ማረጋገጥ ችሏል። ምክንያቱም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው በአልከሶ መስጂድ በየወሩ ሀሙስ ቀን መውሊድ ይከበራል። ይህ ሲቆጠር አስራ ሁለት ይሆናል። ከዚህ በተጨማሪ በአመት አንዴ የአልከስዬ መውሊድ ይከበራል። እንዲሁም በአመት አንዴ የረቢየል አወል መውሊድ ይከበራል። እነዚህ ባጠቃላይ ሲደመሩ አስራ አራት ይደርሳሉ። ነገር ግን የረቢየል አወል ሀሙስ ቀን የወሩ መውሊድ በሚውልበት አጋጣሚ ከዋለ በሀረሙ መውሊድ አስራ ሶስት ጊዜ ይከበራል ማለት ነው።
- በዚህ መውሊድ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ምዕመናን የብሔረሰቡን የባህል ልብስ ይለብሳሉ። ከዚህ በተጨማሪ ወጣቶች የብሔረሰቡን የተለያዩ ባህላዊ ጭፈራዎችን ይጨፍራሉ። እንዲሁም ብሔረሰቡን የቤት አሰራር ጥበቡን በሽምሰል ጀማል አማካይኘነት እና በመንዙማ አማካኘነት ስነ ቃሉን ያንጸባርቃል። ስለዚህ ብሔረሰቡ የፎክሎር ዘርፍ የሆኑትን ቁሳዊ፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበቡን እና አጠቃላይ መንፈሳዊ እሴቱን በዚህ መውሊድ እንደሚያጠናክር እና እንደምያንጸባርቅ በዚህ ጥናት ተረጋግጧል።
- በአልከሶ መውሊድ ከሙስሊሞች በተጨማሪ ሙስሊም ያልሆኑ ሰዎችም እንደሚሳተፉ እና በአልከሶ ሀረም የሃይማኖት መልካም መስተጋብር መኖሩን በጥናቱ ከተረጋገጡ ጉዳዮች መካከል ይገኝበታል።
- የአልከሶ መውሊድ ከዚህ በላይ እንደተመለከትነው የአልከሶ መውሊድ በደመቀ ሁኔታ ቢከበር ሃይማኖታዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች በመውሊዱ ከበራ ቀጠይነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩበት እንደሆነ ይህ ጥናት አረጋግጦል።
- የአልከሶ መውሊድ አክባሪዎች አልከስዬንና እሳቸውን ተክተው መስጂዱን ያስተዳደሩ መሪዎች ቅዱሳን ወይም ወሊዮች ናቸው ብለው እንደሚያምኑ ጥናቱ አረጋግጧል። እነዚህ ምዕመናን ይህን እንዲሉ ያስቻላቸው እነዚህ መሪዎች በተለያዩ ጊዜያት የሰው ልጅ ሊፈጽመው የማይችለውን ድርጊት መፈጸም ይችላሉ ብለው ስለሚያስቡ ነው።

➢ በአጠቃላይ መውሊዱ መከበር ለአካባቢው ማህበረሰብ እና ለአጎራባች ወረዳዎች ሃይማኖታዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ጠቀሜታ እንዳለው ጥናቱ አሳይቷል፡፡

## 10.3 የይሁንታ ሀሳቦች

አንድ አጥኚ ጥናቱ አጥንቶ ካጠናቀቀ በኋላ ከጥናቱ ውጤት በመነሳት ተመራማሪዎችም ሆኑ ሌሎች አካላት አጥኚው ካጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ወደ ፊት ምን ማድረግ እንዳለበት የይሁንታ ሀሳብ ማቅረብ እንዳለበት ምሁራን ያስገነዝባሉ፡፡ እኔም ከዚህ ጥናት በመነሳት የሚከተሉትን የይሁንታ ሀሳቦችን አቅሪቤያለሁ፡፡

➢ በጥናቱ እንደተመላከተው የአልከሶ መውሊድ በአሁኑ ወቅት እየሰፋ እና እየደመቀ ሄዷል፡፡ ይህ መውሊድ መስፋቱ እና መድመቁ ለአካባቢው እና ለዞኑ የገቢ ምንጭ በመሆን እያገለገለ ነው፡፡ በመሆኑም መውሊዱን በሰፊው የማስተዋወቅ ስራ ቢሰራ ለአካባቢው እና ለዞኑ በርካታ ጠቀሜታዎችን ስለሚያስገኝ የዞኑ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ እና የመስጂዱ አስተዳዳሪዎች መውሊዱን ቢያስተዋውቁ መልካም ነው፡፡

➢ በዚህ ጥናት የአልከስዬ እና እሳቸውን ተክተው መስጂዱን ያስተዳደሩ ልጆቻቸው እናየልጅ ልጆች ታሪክ እና ፈጸሟቸው የሚባሉ ተአምራቶችን ወይም ከራማዎች ሙሉ በሙሉ ባይሆንም በተወሰነ ደረጃ አቅርቤያለሁ፡፡ በአሁን ጊዜ በህይወት ያሉ ታሪክ እና ባህል አዋቂዎች ሲያልፉ ታሪኩ ሊጠፋ ስለሚችል ታሪክና ባህል አዋቂዎች በህይወት እያሉ ምሁራን ስለእነዚህ መሪዎች(አልከስዬ…) ታሪክ ትኩረት ቢሰጡት እንዲሁም የዞኑ አስተዳደር አንዱ ስራው የብሔረሰቡን ባህል፣ ቋንቋ እና ታሪክ ማጥናት በመሆኑ ይህን ጉዳይ በሰፊው እንዲጠና ቢያደርግ መልካም ነው፡፡

➢ ለአልከሶ ሀረም ድምቀት ከሰጡት ጉዳዮች መካከል በትልቁ መስጂድ ዙሪያ የሚገኙት ኸለዋዎች ናቸው፡፡ ከነዚህ መካከል የተወሱኑት እድሳት የተደረገላቸው ቢሆንም የተወሰኑት ወድቀዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የሀረሙን ውበት እየቀነሱት ስለሆነ የመስጂዱ አስተዳደር እና ከተለያዩ ቦታዎች መጥተው በየኸለዋው የሚያርፉ ምዕመናን ትኩረት ሰጥተው ቢያሳድሷቸው የሀረሙ ውበት ይኖረዋል፡፡ እንዲሁም ምዕመናኑ ውበት ባለው እና ንጽህ ቦታ መውሊዱን እንዲያከብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ስለዚህ የመስጂዱ መሪዎች እና ምዕመናኑ ሊያስቡበት ይገባል፡፡

➢ በአልከሶ መውሊድ ከልጅ እስከ አዋቂ ከሙስሊም እስከ ቁጥራቸው ጥቂት የማይባሉ ክርስትያን እንደሚሳተፉ ቀድም ብለን ተመልክተናል፡፡ በዚህ መውሊድ የሚሳተፉ ወጣቶች ለመውሊዱ ልዩ ውበት ሰጥቶታል፡፡ ነገር ግን እነዚህ ወጣቶች በመውሊድ ሰሞን በተለይ ምሽት ላይ ከተቃራኒ ጾታ ጋር የሚፈጽሙት ግኑኙነት በእስልምና ሃይማኖት የማይፈቀድ ከመሆኑ በተጨማሪ የመውሊዱን መልካም ገጽታ እያጎደፈው ስለሆነ በቦታው የሚገኙ የጸጥታ አስከባሪዎች እና የመስጂዱ አስተዳደር ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥተው ቢያስተካክሉት መልካም ነው፡፡

➢ በአልከሶ መውሊድ ሰሞን ሊታሰብባቸው ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል የመጸዳጃ ቦታ አንዱ ነው፡፡ እኔ እንደተመለከትኩት በሀረሙ ውስጥ የመጸዳጃ ቤቶች ብዛት ሁለት ሲሆኑ ከሀረሙ ወጪ አንድ አለ፡፡ እነዚህም ደረጃቸውን ጠብቀው የተሰሩ አይደሉም፡፡ ከሁለት መቶ እስከ አምስት መቶ ሺህ በላይ ህዝብ ይሳተፍበታል ተብሎ ለሚገምት መውሊድ እነዚህ መጸዳጃ ቤቶች በቂ አይደሉም፡፡ እንዲሁም አሁን ያሉበት ይዞታ አስተማማኝ ስላልሆነ አደጋ ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡ በእነዚህ መጸዳጃ ቤቶች የሚጠቀሙት ወንዶች ብቻ ሲሆኑ ሴቶች ሙሉ በሙሉ መጸዳጃ ቦታ የላቸውም ማለት ይቻላል፡፡ ምሽት ላይ ደግሞ እዛው ሀረሙ ውስጥ የሚጸዳዱ ሰዎች አጋጥመውኛል፡፡ ከሀረሙ ውጭ በመውጣት በሀረሙ ዙሪያ ባለው አጥር ስር ስለሚጸዳዱ የአካባቢውን ንጽህና በከፍተኛ ሁኔታ አጉድፎታል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምሽት ላይ ለመጸዳዳት ከሀረሙ ውጭ የሚወጡ ወጣት ሴቶች የተለያየ ችግር እየገጠማቸው ስለሆነ የመስጂዱ አስተዳደር በየቦታው ለወንዶች ለብቻ ለሴቶች ለብቻ መጸዳጃ ቤት ሊያዘጋጅ ይገባዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምዕመናን የመውሊድ ሰሞን በውሀ እጦት እየተሰቃዩ ስለሆነ የውሀ አቅርቦት ጉዳይ የመስጂዱ መሪዎች እና የውሃ ጉዳይ የሚመለከታቸው አካላት ሊያስቡበት ይገባል፡፡

➢ የአልከሶ መውሊድ መከበሩ ለአካባቢው ማህበረሰብ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት፡፡ ነገር ግን በአሁኑ ጊዜ መውሊዱ መከበር አለበት የለበትም በሚሉ ሰዎች መካከል ውዝግብ እየተፈጠረ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ የአንድ መንደር ሰዎች በጋራ(በደቦ) ስራ እንዳይሰሩ እና በጀማ(በጋራ) ሷላት እንዳይሰግዱ እያደረጋቸው ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እየሰፋ ከሄደ በአካባቢው ማህበረሰብ ትልቅ ችግር ሊፈጥር ስለሚችል ሁለቱም አካላት ተወያይተው በመሀከላቸው ያለውን ችግር ሊፈቱ ይገባል፡፡ ይህ ካልሆነ የመውሊዱ መከበር ለማህበረሰቡ ካለው ጠቀሜታ ይልቅ ጉዳቱ ሊያመዝን ይችላል፡፡

➢ በዚህ መውሊድ በመንዙማ አማካይነት በርካታ ቃል ግጥሞች ይባላሉ እንዲሁም በርካታ አፈታሪኮች ይነገራሉ፡፡ እነዚህ የብሔረሰቡ የስነቃል ሀብቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጠፉ እና

እየተበረዙ ስለሆነ የዞኑ ባህል እና ቱሪዝም መምሪያ እንዲሰበሰቡ እና እንዲታተሙ ቢያደርግ መልካም ነው፡፡

- በመጨረሻም ወደ ፊት ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ በተያያዘ ሊጠኑ የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት አልከሶ ሀረምን፣ የአልከስዬና የቤተሰባቸውን ታሪክ እና የመውሊዱን አከባበር ሙሉ በሙሉ አሳይቷል ብዬ አላምንም፡፡ ምክንያም ይህ ጥናት መውሊዱን ለመመልከት የሞከረው ከፎክሎር አንጻር ነው፡፡ በመሆኑም ሌሎች ምሁራን ይህን ጉዳይ ከተለያየ የጥናት ትኩረት አቅጣጫ አንጻር ሊያጠኑት ይገባል፡፡

# የተጣቀሱ ምንጮች


ሀሰን ታጁ፤ (ተርጓሚ) *ሪያዱ አስ-ሷሊሂን፤* አዲስ አበባ፣ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣ቅፅ 1፣ 2004።

---------------፤ *መውሊድ የታላቁ ነብይ መታሰቢያ፤ (ማተሚያ ቦታ እና ድርጅት ያልተጠቀሰ)፣ 2008።*

ሁሴን ሙሃመድ፤ *የስልጢኛ አማርኛ እንግሊዘኛ ቃሙስ፤* አዲስ አበባ ፣ የትምህርት መሳሪያዎች ማደራጃና ማከፋፈያ ድርጅት፣ 1987።

ሁሰይኒ ሰኢድ እነ ሻፊ ሙዜ፤ *"የስልጤ ልዩ መገለጫዎች(ICONS) አጭር የዳሰሳ ጥናት፤* ለ11ኛው ለስልጤ ባህል፣ቋንቋ እና ታሪክ ሲፓዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፤ 2009።

ላጲሶ ጌ.ዲሌቦ፤ *የኢትዮጵያ ረጅም የህዝብ እና የመንግስት ታሪክ፤* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣1990።

መሐመድ ሁሴን፤ "የገባሮች ሼኽ የህይወት ታሪክና የበአላቸው አከባበርና ግጥሞቻቸው"፤ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ (ዲማጽ)፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 1997።

መሀመድ ዓሊ፤ "አውሊያና የአውሊያ ስርዓት (ሱፊዝም) ፎክሎር ትንተና በቦረነ -ደበቡ ወሎ"፤ የዶክተሬት ዲግሪ ጥናት፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2009።

ሙሐመድ አህመድ፤ *መውሊድ ታሪክ፣ ግድፈት፣ እርምት- ለሐሰን ታጁ መውሊድ መጽሐፍ የተሰጠ ምላሽ፤* (ማተሚያ ቦታ እና ድርጅት ያልተጠቀሰ)፣2008።

ማርክዚዝም ሌኒኒዝም *መዝገበ ቃላት*። አዲስ አበባ፣ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት፣ 1978።

ሰሚራ መሀመድ፤ "ጡሩሲና የሙስሊም "ገዳም" እና "በገዳሙ" ውስጥ የሚከበሩ በአላት ስርአተ ክዋኔ።" ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ 2005።

ሰይድ መሀመድ እና መሀመድ ሳኒ፤ *ቅዱስ ቁርአን የአማርኛ ትርጉም፤* አዲስ አበባ፣ ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣ 2ኛ እትም፣ 1993።

ስልጢ ወረዳ አስተዳደር ቢሮ፤ *አልክሶና አልክስዬ።* ንግድ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ፣1985።

ረውዳ ስራጅ፤ *"የስልጢኛ ቋንቋ የመግልጽ አቅም"፤* ለ3ተኛው ለስልጤ ቋንቋ ባህልና ታሪክ ሲፓዚየም የቀረበ ጥናታዊ ጽሑፍ፤ ማስተር ማተሚያ ቤት፣ 2002፡፡

በአራዳ እና በልደታ ክፍለ ከተማ እስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት የተዘጋጀ መጽሄት፤ *የመውሊድ እውነታዎች፤* አዲስ አበባ፣ ግራፊክስ ኤም.ዲ አድቨርት፣2008፡፡

በኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ምክር ቤት የተዘጋጀ፤ "ሂጅራ መጽሔት" ቁጥር 4፣ ቅጽ 2፣ 1991፡፡

በወጣት እስላሞች መንፈሳዊ ክበብ ተዘጋጅቶ የቀረበ፤ "ቢላል መጽሔት" የመጀመሪያ ዕትም፣ አዲስ አበባ፣ አዲስ ማተሚያ ቤት፣ 1967፡፡

ባሕሩ ዘውዴ፤ *የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1847 እስከ 1983፤* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣2007፡፡

ቦጋለ ተፈሪ፤ *ትንቢተ ሼኽ ሁሴን ጅብሪል*፡፡ አዲስ አበባ፣ አስናቀ ማተሚያ ቤት፣ 2002፡፡

ቴዎድሮስ ገብሬ፤ *በይነ-ዲሲፕሊናዊ የሥነ ጽሑፍ ንባቡ*፡ አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣2002፡፡

ነጻነት መኮንን፣ "አበጋር-ባህልዊ የግጭት አፈታት በተሁለደሬ ወረዳ"፣ ለኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ 1998፡፡

አህመዲን ጀበል፤ *3ተ አጼዎች እና ኢትዮጵያዊያን ሙስሊሞች፡ (ማተሚያ ቦታ እና ድርጅት ያልተጠቀሰ)*፣2008፡፡

አለም እሸቱ፤ *መሠረታዊ የምርምርና ዘገባ አጻጻፍ፤* አዲስ አበባ፣ ቅድስት ማርያም ኮሌጅ የሊብራል አርትስ ፋክልቲ፣ 1992፡፡

አባስ አብዱ፤ *የኢትዮጵያ ሀብለ በራሄ ብሔረሰብ ታሪክ እና ታላቁ እስላማዊ ምሁር አልከስዬ፡፡* አዲስ አበባ፣ መረዋ አሳታሚ ድርጅት፣2004፡፡

አብዱልረህማን ፋንታሁን፤ "የሐጅ ሁሴን ዓለሙ (የነሼኽ ዳንግላ) የመውሊድ በአል ስርዓትና ቃላዊ ግጥሞች (መንዙማዎች) ክዋኔ ጥናት"፤ ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣2006፡፡

አብድልፈታህ አብደላ፤ (ተርጓ) *ጥሮነ፡ የኢትዮጵያ ቀደምትና ትላልቅ ኡለማዎች ታሪክ፤* አዲስ አበባ፣ ድሬ ማተሚያ ቤት፣1998፡፡

-------- *የኢትዮጵያ ታላላቅ ኢስላማዊ ታሪካዊ ቦታዎች፡፡* አዲስ አበባ፣አሳታሚ አብድልፈታ አብደላ፣ 1999፡፡

አብድልፈታ ሁልዳር፤ *የስልጤ ብሔራዊ መገለጫዎችና ለኢትዮጵያዊነት ያበረከቱት አስተዋጽኦ፤* አዲስ አበባ፣ ፓን አፍሪካ ማዕከል፣ 2002፡፡

አብዲ ተማም፤ "የስልጤ ብሔረሰብ ተረት ይዘታዊ ትንተና"፡፡ ለቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋ እና ስነጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ ጂማ ዩኒቨርስቲ፣2003፡፡

-------------- "የስልጤ ብሔረሰብ የባህል ምግብ አዘገጃጀት፣ አቀራረብ እና የአመጋገብ ስነ ስርዓት፡፡" ለኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ፣ የኢትዮጵያ ስነ ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣2003፡፡

አብርሃም ሁሴን እና ሀብታሙ ወንድሙ፤ *የስልጥኛ ቋንቋ ተናጋሪ ህዝብ የአዘርነት በርበሬ ህብረተሰብ ባህልና ታሪክ፤* አዲስ አበባ፣ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1984፡፡

አደም ካሚል፤ *የሐበሻ አሻራ በእስላም፤* አዲስ አበባ፣ መረዋ ማተሚያ ቤት፣2008፡፡

ተሰማ ሀብተ ሚካኤል ግጽው፡፡ *የዐማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አሳታሚው ያልተገለፀ፣ 2002 ፡፡

ከይረዲን ተዘራ፤ *ሴረ የስልጤ ህዝብ ታሪክ፣ ባህል እና ቋንቋ ከ886-1993*፤ አዲስ አበባ፣ ኢልፕስ ማተሚያ ቤት፣ 2004፡፡

ኪሩቤል ሽንቁጤ፤ "የቃጥባሬው ሼኽ ህይወት ታሪክ እና የበዓላቸው አከባበር፣ ግጥሞቻቸው"፤ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ (ዲማጽ)፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣1986፡፡

ዓሊ የሱፍ፤ "የሼኽ መሀመድ ነጃ የህይወት ታሪክ፣ የሀረም ቸው ክዋኔ እና ግጥሞቻቸው"፤ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ (ዲማጽ)፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣1995፡፡

ዘሪሁን አስፋው፤ *የስነጽሁፍ መሰረታዊያን፤* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1991፡፡

የህያ አባ ጀበል (ተርጓሚ)፤*ረውደቱል አንዋር የነብዩ ሙሐመድ የህይወት ታሪክ፡፡ አዲስ አበባ፣ነጃሺ ማተሚያ ቤት፣1413 ዓ.ሂ፡፡*

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናት ማዕከል፤ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት፤* አዲስ አበባ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ፕሬስ፣ 2001፡፡

ያለው እንዳወቅ፤ *የምርምር መሰረታዊ መርሆችና አተገባበር፤* ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣2004፡፡

ድንበሩ ዓለሙና ሌሎቹም፤ *ጎንት የጉራጌ ህዝብ ታሪክ፣ ባህልና ቋንቋ፤* አዲስ አበባ፣ አርቲስትክስ ማተሚያ ድርጅት፣ 1988፡፡

ፅጌ ንጋቱ፤ "የሼኽ ሰይድ ቡሽራ ታምራት አፈ ታሪክና የመውሊድ በዓል አከባበር በገታ/ወሎ" ፤ የቢ.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ (ዲማጽ)፣የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ስነ ጽሁፍ ትምህርት ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣1982።

ፈለቀ ታደለ፤ "ባህልና ልማት" ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፤ ፎረም ፎርሶሻል ስተዲስ ፤ አዲስ አበባ፣ ኢሲሊፐስ ማተሚያ ቤት፣ 2004።

ፈቃደ አዘዘ፤ *የስነቃል መምሪያ፤* አዲስ አበባ፣ ኢተርናሽናል ጀርመናዊ የጎልማሶች ትምህርት መረዳጃ ተቋም፣ 1991።

-------------፤ "የመስክ ስራ የስነቃል አሰባሰብ፣ አከለሳሰፍ፣ አተናተን እና አሰናነድ፤" ለ"ባህልና የባህል አመራር ልማት፣ ሀገር- አቀፍ ኮንፈረንስ"፣ ዝግጅት ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር፣ አዲስ አበባ፣ 1999።

------------፤ "ቁዘማ: ፎክሎር /ባህል/ እና ልማት በኢትዮጵያ፤" ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፤ ፎረም ፎርሶሻል ስተዲስ ፤ አዲስ አበባ፣ ኢሲሊፐስ ማተሚያ ቤት፣ 2004።

ውዱ ጣፈጠ፤ "የሃይማኖት መቻቻል በኢትዮጵያ፤" ባህልና ልማት በኢትዮጵያ፤ ፎረም ፎርሶሻል ስተዲስ ፤ አዲስ አበባ፣ ኢሲሊፐስ ማተሚያ ቤት፣ 2004።

Abdalla Bujra. *Islam in Eastern Africa:Historical Legacy and Contemporary Challenges.* Executive Director, Development Policy Management Forum (DPMF) August 2002.

Abun-Nasr, Jamil M. *The Tijaniyya: a Sufi Order in the Modern World.* London: Oxford University Press, 1965.

Ahmed Zekaria "SOME REMARKS ON THE SHRINES OF HARAR." *Saints Biograhies and History in Africa.* Ed. Bertrand, Hirsch and Manfred Kropp. Haftad.2003.

Alexei Vassiliev, *The History of Saudi Arabia*. New York: New York University Press, 2000.

AKAHORI Masayuki, "Towards a Dynamic View of Sufism and Saint Veneration in Islam: An Anthropological Approach" *Kyoto Bulletin of Islamic Area Studies,* 2015, pp. 57—68.

Al-Islam. "Ethiopian Muslim Experience in Three Regimes." *Journal of Al-Islam,* 2010 No. 14.

AR-RAHEEQ AL-MAKHTUM. *The Biography of the Noble Prophet*. Saudi Arabia. UK. USA. Pakistan. Maktaba Dar-us-salam publishers and Distributors. 1996.

Amira Kedir "The Qatbare Sheikh Mawlid Celebration and intera faith debate on the mawlid celebration" MA Thesis, Deparment of Social Anthropology Addis Ababa University, 2014.

Assefa Mamo. "Some Prominent Features of Menzuma in Wollo Region". MA Thesis, department of Foreign Language, Addis Ababa University, 1987.

Bascom. William R. "Four Functions of Folklore". *The Journal of American Folklore.* 1972. Vol.67.

Bauman, Richard, and Briggs L,Charles. *Poetics and Performance as Critical Perspectives on Language and Social Life፡* Annual Review of Anthropology.Newyork: 1990.

Bauman, Richard, (ed) *Folklore Cultural Performances and Popular Entertainment*. NewYork፤ oxford University Press, 1992.

Bender, M.L. et. al eds *Languages in Ethiopia.* London; Oxford University Press, 1976.

Bell, Catherine. *Ritual: Perspective and Dimensions*. Oxford, Oxford University, 1997.

Ben-Amos, Dan. "Toward a Definition of Folklore in Context." *Journal of American Folklore.* 1971.

------------------------. "Folklore in Context." *Journal of African Studies,* vol.15፡ 2006.

Berhanu, Gebeyehu. "Islamic oral Poetry In Wallo: a Preliminary Descriptive Analysis." MA Thesis, department of Foreign Language, Addis Ababa University,1998.

Best, J. W. *Research in Education*. New Delhi; Prentice Hall of India Private Limited, 1981.

Braukämper, Ulrich. *Islamic History and Culture in Southern Ethiopia: Collected Essays*. Münster, Hamburg and London: Lit, 2002.

Brills, E.J. *Encyclopedia of islam.* New york.Vol. 4 1987.

Brown, Corinne. *Understanding Other Cultures*. Prentice Hall Inc; Engliwood Cliffs N.J, 1963.

Bronislav Ostřanský. *Egyptian mawlids in the context of contemporary Sufi spirituality.* 2008, 132-143.

Bloomer, George G. "The witching craft: reversing the curse. " Specialy prepared for the last spretual were fare conference (date is undefined).

Central Statistical Agency."The 2007 Population and Housing Census of Ethiopia- Result for south Region." Addis Ababa, 2010.

Creswell, John W. *Research Design: Qualitative, Quantitative, and Mixed Methods Approach.* 4th ed. Thousand Oaks, CA: SAGE, 2014.

Dawson, Catherine. *A Practical Guide to RESEARCH METHODSA friend Manual for Mastering research techniques and projects.* British Library Cataloguing in Publication, Oxford United Kingdom, 2007.

Damas Addeh and Sayida Fuad. *The Legal framework of Mosque building and Muslim religious affairs in Egypt: towards a strengthening of State control.* 2011.

Denzin, NK. Sociological Methods. New York: McGraw-Hill. 1978.

Denzin N. and Lincoln Y. (eds.) Hand book of Qualitative Research. London SAGE Publications, 2000.

Derek, Prince. "Explaining Blessing and Curses. " Nelson World Ltd. 9 Holdon Avenue, Bletchley, Milton Keynes, England, 1994.

Desplat, Patrik and Terje Ostebo (eds.). *Muslim Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics, and Islamic Reformism.* New York: Palgrave Macmillan, 2013.

Desplat, Patrick. "The articulation of religious identities and their boundaries in Ethiopia: labeling difference and processes of contextualization in Islam." In: *Journal of Religion* in *Africa*, 2005.:PP 483-503.

Dundes, Alan. *Analytic Essay in Folklore*. The Hague: Mouton: 1975.

Dirk Bustorf. "Imam Sugato Zäyni. A war-lord of the Selt'é Gogot." Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies. 2009.

Dorson, Richard M. *Folklore and Folk life: An Introduction.* Chicago, the University of Chicago Press, 1972.

Eickelman, D.F. and J. Piscatori (eds). *Muslim Travelers: Pilgrimage, Migration, and the Religious Imagination,* London: Routledge,1990.

Eliyas Taha. "understanding rituals and analyzing songs performed at Dirre sheikh Hussein" MA Thesis, department of Social Antropology, Addis Ababa University,2012.

Eshetu Setegn. "Shaikh Hussayn of Bale and his followers." (B.A. Senior Essay,) Haile Sellasie I University, 1973.

ERMAN HARUN "THE ROYAL MAWLID CEREMONIES IN THE OTTOMAN EMPIRE (1789-1908)".DEPARTMENT OF HISTORY,İHSAN DOĞRAMACI BİLKENT UNIVERSITY, ANKARA, 2016.

Emmanuel Osewe "Emerging Religious Movements and Their Implications in African History and Heritage." European Scientific Journal vol.12, No.2 2016, pp 154-139.

Falassi, A. *Time out of time: Essays on the festival.* Albuquerque: Chicago, University of New Mexico Press,1987.

Finnegan, Ruth. *Oral literature in Africa*. London and New York፡ Routledge, 1970.

Ferraro, Garry. *Cultural anthropology an applied perspective*. U.S.A; an international Thomson publishing company,1998.

FRISHMAN, M. "Islam and the Form of the Mosque" in Ed. FRISHMAN, M. and KHAN, H. *the Mosques: History, Architectural Development and Regional Diversity*, *Thames and Hudson,* London, 1994, pp 17-42.

Foucher, Emile. "The Cult of Muslim Saints in Harar: Religious Dimension." Proceedings of the 11th International Conference of Ethiopian Studies, Addis Ababa. Institute of Ethiopian Studies,1994.

Jackson, Bruce. *Fieldwork. Urbana and Chicago*: University of Illinois Press. 1987.

Jon Abbink, "An Historical Antroplocical Approch to Islam in Ethiopia: Issues of Identity and Politcs" Journal of African Cultural studies, 1989.pp 109-124.

--------------- "Religious freedom and the political order: the Ethiopian 'secular state' and the containment of Muslim identity politics." *Journal of Eastern African Studies,* 2014, 346-365.

John, Arberry. *The Doctrine of the sufi (kitab al-Taarruf li-madhab ahl al-tasawwuf).* Cambridge University Press,1976.

Rory McCarthy. "Re-thinking secularism in post-independence Tunisia",*The Journal of North African Studies*, 2014, PP 733-750.

Jonathan, Brown. SALAFIS AND SUFIS IN EGYP. Washington DC, Carnegie Endowment for International Peace. 2011.

Hadjivayanis, Ida . *Norms of Swahili Translations in Tanzania: An Analysis of Selected Translated Prose*. PhD Thesis, 2011.

Haggai, Erlic. *Saudi Arabia and Ethiopia: Islam, Christianity, and Politics Entwined.* USA: Lynne Rienner Publishers, Inc, 2007.

Harrassousitz, O and Wiesbaden *Encyclopedia of Eathiopica*.1996.

Hammersley, Martyn, and Paul Atkinsion. Ethnography Principles in Practice. London: Routledge, 1991.

Hisham Muhammad Kabbani. MAWLID Its Permissibility Its Necessity Its Reality. As- Sunna. USA. Foundation of America, 1998.

Hussein, Ahmed. "The Historiography of Islam in Ethiopia." *Journal of Islamic Studies,* 1992.

------------ "Islam In Nineteeth Century Wallo, Ethiopia Revival, Reform and Reaction." Brill, Leinden: Boston, 2001

----------- “Some Aspects of the *Darg*'s Policy towards Islam in Ethiopia (1974-1991)” *symposium on the Cross and the Crescent: Christian-Islamic Relations in Ethiopia*, organized by the Goethe Institute, 2002.

---------------“Conversion to/from Islam and Christianity in the History of Ethiopia” *Third International Colloquium on Muslim/Christian Encounters in Africa,* Evanston, Northwestern University, 2003.

-------------“The State and Islam in Twentieth-Century Ethiopia” International symposium on Islamic Civilization in Eastern Africa, Kampala, 2003.

-------------."Coexistence and/or Confrontation: Towards a Reappraisal of Christian Muslim Encounter in Contemporary Ethiopia."*Journal of Religion in Africa,* 2006.

Hope,Collins. *The Mosque as a Political, Economic, and Social Institution 622 —Present.* Syracuse University Honors Program Capstone Projects, 2011

Ishihara, Minako. “Textual Analysis of a Poetic Verse in a Muslim Oromo Society in Jimma Area, South Western Ethiopia.” *Senri Ethnological Studies*, 1996.

………..`”Spirit Possession and Pilgrimage the Formation and Configuration of the Tijjānī Cult in Western Oromoland.” In: Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies, Trondheim፡ 2009,

Gazi- Mikhail. “The position of Mosques in Islamic cities and its location design in new cities”. Damascus University Journal Vol. (28) - No. (1) 2012, pp 49-67.

Gemechu Jemal. “The Faraqasa indigenous pilgrimage center: History and ritual practices” MA Thesis, Faculty of Social Science, University of Tromsø, Norway, May 2007.

--------------“Pilgrimages and Syncretism: Religious Transformation among the Arsi Oromo of Ethiopia”, Dissrtation, Religious Studies Universtiy of Bayreuth, Germany, 2013.

Glassie, Henry. *Material Culture.* Bloomington and Indiana; Indiana university press,1991.

Gesler, Wil. "Sacred Spaces, Sacred Places: The Geography of Pilgrimages." *Annals of the Association of American Geographers* 88, no. 3, 535-537 1998.

Geoffroy, Eric. *Introduction to Sufism: The inner path of Islam.* world wisdom, inc, 2010.

Goldschmidt, Arthur. *A Concise History of the Middle East.* Boulder: Westview Press. 1977.

Goldstein, Kenneth S. A *Guide For Field Workers in Folklore*. Folklore Associates, INC. Hatboro, Pennsylvania, USA. 1964.

Gori, Alessandro. "Texts in the *Mawlid* Collection in Harar: Some First Critical Observations." African Study Monographs, vol.41. 2010.

Kapchan, A. Deborah. "Performance." *The Journal of American Folklore.* New York: Vol. 108, 1995.

Khosro, Movahed. Mosque as a religious building for community development. Department of Architecture, Shiraz Branch, Islamic Azad University, Iran,2008.

Kaplan, Steven. "Christian Pilgrimages" In *Encyclopaedia Aethiopica*, Vol. 4. Edited by Siegbert Uhlig, 151-153. Wiesbaden: Harrassowitz, 2010.

Kedir Adem. "Socio Cultural Facuters as the basis of interrelationshipis a case study on Harari and siltie Socities" MA Thesis, department of Indgenous Cultural Studies, Addis Ababa University,2008.

Kothari. CR, *Research Methodology*: *Methods and Techniques*. india: new age international limited publisher, 1985.

Levine, Donald. *Great Ethiopia: The Evolution of a Multienic Society.* Chicago: university of Chicago Press 1974.

Lings, George. *What is Sufism?* U.K Cox and Wyman ltd. 1988.

Nuredin Delil. “The life and works of the Shaykh Abret (1908-78) with special reference to his Arabic Manuscripts.” MA Thesis, department of Philology, Addis Ababa University,2007.

Mamarama Seck,. “The Structure of Wolof Sufi: Oral Narratives: Expanding the Labovian and Longacrean Model to Accommodate Wolof Oral Tradition” (Dissertation Paper). Graduate School of the University of Florida. 2009.

--------------------“Contemporary Islamic Discourses in Senegal: Between the Local and the Global.” Ed Eunice N . Sahle. *Globalization and Socio-Cultural Processes in Contemporary Africa,* 2015, PP 93-121.

Martin, Richard *Encyclopedia of Islam and the Muslim World.* New York: Macmillan Reference. 2004.

Motz, Mrkiyn. “The concept of belief”. *The Journal of America*. Vo 111.1998.

Mullen.B. Patrik. “The Function of Magic folk belief among Texas coastal Fishermen.” *The Journal of America.* Vo 82. 1969.

Mustafa Kabha, and Erlich Haggai. “Al-Ahbash and Wahhabiyya Interpretations of Islam.” *International Journal of Middle East Studies,* No. 4, 2006.

Mohamed Bakari and Saad Yahya (Editors), Islam in Kenya, Proceedings of the national Seminar on Contemporary Islam in Kenya, Mewa Publications, 1995.

Muhammad Yusuf. “History of Mosque” *Journal of Islamic Thought and Civilization, no 5* 2012

Newby, Gordon. *A Concise Encyclopedia of Islam*. Oxford: One world. 2006.

Nishi, Makoto. “Making and Unmaking of the Nation-State and Ethnicity in Modern Ethiopia: A Study on the History of the Silt’e People”. African Study Monographs 29, pp,157-168. 2005.

Oring Elliate. *Folk Groups and Folklore Geners: An Introduction.* Utah State University Press, USA. 1986.

Østebø, Terje. “The Question of Becoming: Islamic Reform Movements in Contemporary Ethiopia” *Journal of Religion in Africa. Vol.* 38. 2008.

-------------------“Religious Change and Islam: The Emergence of the Salafi Movement in Bale, Ethiopia.” *Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies,* 2009.

----------------------- *Localizing Salafism: Religious change among Oromo Muslims in Bale, Ethiopia.* Leiden: Brill. 2012.

………………… “Clamis for Authority at the Shrine of Shaykh Husayn, Ethiopia” *Journal of Islamic Studies*, 2014.

Rappaport, Roy A. *Folklore, Cultural Performances, and Popular Entrainments*, New York, Oxford University Press፣1992.

--------------------- Ritual and Religion the making of humanity, New York, Cambridge University Press 1999.

Robert N. McCauley and E. Thomas Lawson. *Bringing Ritual to Mind Psychological Foundations of Cultural Forms.* United Kingdom 2002.

Pankhurst, Alula. 1994. ‘Reflections on Pilgrimages in Ethiopia.’ New Trends in Ethiopian Studies: Papers of the 12th International Conference of Ethiopian Studies, Lawrenceville: The Red Sea Press, Vol. 2, pp. 933-953.

Patton, MQ. *Qualitative Evaluation and Research Methods.* (2nd Ed), Thousand oaks, CA: Sage Publications. 2001.

Philo, Joseph. *Called to Harmony : Christianity and Islam in Tanzania at the Crossroads.* Boston College University Libraries.2011

Saleh ibn Fawzan. *The ruling concerning Mawlid an-nabawi.* UAE, published by Quran sunnah Education Program, 2001.

Sarah Vaughan. “Ethnicity and Power in Ethiopia”. PhD Dissertation,The University of dinburg, 2003.

Schielke, Samuli and Liza Debevec (eds.) *Ordinary Lives and Grand Schemes: An Anthropology of Everyday Religion*. New York: Berghahn Books. 2012.

Schoemaker George H. *The Emergence of Folklore in every day life: A field guide and Source Book.* Bloomington, Trickster Press, Indiana University,1990.

Semira Ali. "A Historical Studay of the Islamic Shrine of GÄTA (South Wollo), 1863 to the Present." MA Thesis, department of History, Addis Ababa University,2015.

Shack, Wiliam Alfred. *The gurage: a people of the Enset*. London, Oxford University,1966.

Shimels Habte. "The Faraqasa pilgrimage center" B.A Thesis, department of History, Addis Ababa University,1989.

Sims, Martha C. and Stephens, Martine. *Living Folklore: An Introduction to the Study of People and their Tradition. Logan:* Utah State University Press, 2005.

Stoddard, Robert H. "Major Pilgrimage Places of the World" In *Pilgrimage in the old and new Worlds.* Edited by S. M. Bhardwaj, 17-36. Berlin: Reimer, 1994.

Süleyman, Celebi ed. *Necla Pekolcay For an exhaustive narration of a mawlid ceremony in Fatimid Empire.* İstanbul: Dergah Yayinlari, 2005.

Syed B, Soharwardy. *Why Should You Celebrate the Birthday of Prophet Muhammad* ፣Canada, Islamic Supreme Council of Canada. 2005.

Taddesse Tamrat. "Islam and Trade in Ethiopia c. 900-1332." In *Proceedings of the 1st annual conference of the provisional council for the social sciences in East Africa,* Dar es Salaam: University of Dar es Salaam, vol. 3, 1970.pp. 76-87,

TIGLU GEZA. LANGUAGE PLANNING AND POLICY IN THE SILT'E ZONE Dissertation, DEPARTMENT OF ENGLISH AND THE SCHOOL OF GRADUATE STUDIES, Addis Ababa Universty, 2015.

Trimingham J, Spenser. *Islam in Ethiopia*. London and New York: Oxford University Press, 1952.

------------------.*The Influence of Islam upon Africa.(*2nd Ed)*,* London: Longmann,1980.

Toelken, Barre. *The Dynamic of Folklore*. Logan, Utah: Utah State University Press, 1996.

Yasuo Matsunami and Minako Ishihara. "On the Filming of "Pilgrimage to Ya'a"." In: Proceedings of the 16th International Conference of Ethiopian Studies Trondheim 2009.

York, Michael. "Contemporary pagan pilgrimages" in *From Medieval Pilgrimage to Religious Tourism: The Social and Cultural Economics of Piety*. Edited by William H Swatos and Luigi Tomasi, 137-158. Connecticut: Praeger, 2002.

Willia Bento, (ed) *Encyclopedia of Britanica*. Library of congress, USA, vol.4,200.

Zerihun Woldeselassie. "Wali venerating Practices, Identity Politics, and Islamic Reformism among the Siltie." (ed) Terje Ostebo, *Muslim Ethiopia: The Christian Legacy, Identity Politics, and Islamic Reformism.* New York: Palgrave Macmillan, 2013.

Z.FAREEN PARVEZ."Celebrating the prophet: religious nationalism and the politics of Milad-un-Nabi festivals in India", *JOURNAL OF THE ASSOCIATION FOR THE STUDY OF ETHNICITY AND NATIONALISM.* 2014, PP 218—238.

Zulkiple A. G."History, Distribution and Affiliation of Mosque in Muslim Minority of Sri Lanka". *International Journal of Humanities and Social Science* Vol. 3, No. 1, 2013, pp 182-191.

## አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች መግለጫ በፊደል ቅደም ተከተል መሰረት

| ተ.ቁ | ስም | ዕድሜ | ጾታ | ስራ | ቃለመጠይቅ የተደረገበት ቀን | ቃለመጠይቅ የተደረገት ቦታ | መረጃ አቀባዮቹ በጥናቱ ውስጥ ያላቸው ሚና | | የመኖሪያ አድራሻ | ሃይማኖት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | | ዋና | አጠቃላይ | | |
| 1 | ሀጅ ኑረዲን | 80 | ወ | አርሶ አደር | 26/10/07 | አልከሶ | ✓ | | አልቾ | ሙስሊም |
| 2 | ሀጅ ዑመር እንድሪስ | 60 | ወ | የሃይማኖ መሪ | 25/05/08 | አዲስ አበባ | | ✓ | አዲስ አበባ | ሙስሊም |
| 3 | ሃምሳ አላቃ ወርቁ | 48 | ወ | ፖሊስ | 26/05/08 | አልከሶ | | ✓ | ባልጩ | ክርስትያን |
| 4 | ሼኽ ማህሙድ*[188] | 60 | ወ | አርሶ አደር | 24/05/08 | አልከሶ | ✓ | | አዲስ አበባ | ሙስሊም |
| 5 | ሼኽ በህረዲን | 75 | ወ | አርሶ አደር | 26/10/07 | አልከሶ | ✓ | | አሊቾ | ሙስሊም |
| 6 | ሼኽ ነስሮ አህመዲን | 65 | ወ | ኢማም | 27/05/08 | አልከሶ | | ✓ | አልከሶ | ሙስሊም |
| 7 | ሼኽ አህመድ ሽሪፍ | 50 | ወ | ነጋዴ | 13/03/08 | አዲስ አበባ | | ✓ | አዲስ አበባ | ሙስሊም |
| 8 | ሼኽ አ/ረዛቅ ሱልጣን | 35 | ወ | ነጋዴ | 24/10/07 | አልከሶ | ✓ | | ጅማ | ሙስሊም |
| 9 | ሼኽ ከድር አህመድ | 73 | ወ | ኢማም | 24/05/08ና 24/05/08 | ሀረም | ✓ | | አልከሶ | ሙስሊም |
| 10 | ሼኽ ጀማል ዳሎቻ | 75 | ወ | አርሶ አደር | 02/05/08 | ዳሎቻ | ✓ | | ዳሎቻ | ሙስሊም |
| 11 | ሼኽ በህሩ | 48 | ወ | አርሶ አደር | 14/09/08 | አልከሶ | | ✓ | አልከሶ | ሙስሊም |
| 12 | ሽምሴ | 26 | ወ | አርሶ አደር | 24/05/08 | አልከሶ | | ✓ | አልከሶ | ሙስሊም |
| 13 | ባዱዲን መሀመድ | 25 | ወ | ነጋዴ | 26/05/08 | አልከሶ | | ✓ | አልከሶ | ሙስሊም |
| 14 | ነጂባ ሱልጣን | 14 | ወ | ተማሪ | 26/05/08 | አልከሶ | | ✓ | አልከሶ | ሙስሊም |

[188] ‘*’ ምልክት ያለባቸው በቡድን ውይይት የተሳተፉ ናቸው፡፡

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 15 | አቶ ሁሰይኒ ሰይድ | 35 | ወ | የመንግስት | 27/05/08፤ 15/09/08 | ወራቤ እና አልከሶ | ✓ | | ወራቤ | ሙስሊም |
| 16 | አቶ መሀመድ እንድሪ | 58 | ወ | ነጋዴ | 18/06/06 | አዲስ አበባ | | ✓ | አዲስ አበባ | ሙስሊም |
| 17 | አቶ መሀመድ ጣሃ* | 45 | ወ | አርሶ አደር | 26/10/07 | አልከሶ | | ✓ | አርሲ | ሙስሊም |
| 18 | አቶ ማሙሸት | 38 | ወ | ነጋዴ | 25/10/07 | አልከሶ | | ✓ | ወላይታ | ክርስትያን |
| 19 | አቶ ሰናይ ደሳለኝ* | 51 | ወ | አርሶ አደር | 23/10/07ና 15/09/08 | አልከሶ | ✓ | | ባልጩ | ክርስትያን |
| 20 | አቶ ሲራጅ ጣሀ* | 42 | ወ | አርሶ አደር | 26/10/07 | አልከሶ | | ✓ | አርሲ | ሙስሊም |
| 21 | አቶ ታደሰ ታዬ | 48 | ወ | አርሶ አደር | 23/10/07 | አልከሶ | ✓ | | ባልጩ | ክርስትያን |
| 22 | አቶ ነስሩ ፈይድ | 40 | ወ | ነጋዴ | 24/05/08 | ወራቤ | ✓ | | ወራቤ | ሙስሊም |
| 23 | አቶ ኑሪ ሼኽ ከድር* | 45 | ወ | አርሶ አደር | 14/09/08 | አልከሶ | ✓ | | ዳሎቻ | ሙስሊም |
| 24 | አቶ አብድልረዛቅ | 40 | ወ | አርሶ አደር | 02/01/09 | ዜባድ | | ✓ | መን- ዘባድ | ሙስሊም |
| 25 | አቶ አዘነ ወ/ገብርኤል | 45 | ወ | የመንግስት | 24/10/07 | አልከሶ | ✓ | | ዳሎቻ | ሙስሊም |
| 26 | አቶ ደነቀ ተፈራ | 50 | ወ | አርሶ አደር | 24/09/07 | አልከሶ | | ✓ | ባልጩ | ክርስትያን |
| 27 | አቶ ግርማ ከተማ* | 58 | ወ | አርሶ አደር | 23/10/07 | ቡታጅራ | ✓ | | ቡታጀራ | ክርስትያን |
| 28 | አቶ ሙአዝ | 32 | ወ | - - | 14/09/08 | አልከሶ ሀረም | | ✓ | የመን | ሙስሊም |
| 29 | አቶ አሚር | 38 | ወ | - - | 14/09/08 | አልከሶ ሀረም | | ✓ | የመን | ሙስሊም |
| 30 | አብድልባቅ ጀማል* | 25 | ወ | ደረሳ | 27/05/08 | ወራቤ | ✓ | | አዘርነት | ሙስሊም |
| 31 | አድራ ጀማል | 28 | ሴ | አርሶ አደር | 26/05/08 | አልከሶ | | ✓ | አልከሶ | ሙስሊም |
| 32 | እመት ሀረም * | 55 | ሴ | የቤት እመቤት | 24/10/07 | አልሶ | ✓ | | ቀጫጭ | ሙስሊም |
| 33 | እመት ኸድጃ | 40 | ሴ | የቤት እመቤት | 23/05/08 | አልከሶ | ✓ | | ቀጫጭ | ሙስሊም |
| 34 | እመት ሙናጃ | 35 | ሴ | አርሶ አደር | 23/05/08 | አልከሶ ከተማ | | ✓ | አይናቤ | ሙስሊም |

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 35 | ኤሊያስ ሰይድ | 35 | ወ | የመንግስት | 24/09/07ና | አልከሶ | | ✓ | ወራቤ | ሙስሊም |
| 36 | ወ/ሮ ሉባባ | 38 | ሴ | አርሶ አደር | 26/05/08 | አልከሶ | ✓ | | አልከሶ | ሙስሊም |
| 37 | ወ/ሮ ላቀች | 35 | ሴ | አርሶ አደር | 24/10/07 | አልከሶ | | ✓ | ስልጢ | ክርስትያን |
| 38 | ወ/ሮ መሰረት | 35 | ሴ | የቤት እመቤት | 25/10/07 | አልከሶ | ✓ | | ሻሻመኔ | ክርስትያን |
| 39 | ወ/ት ሙናጃ | 22 | ሴ | ነጋዴናተማሪ | 24/10/07 | አልከሶ | | ✓ | ማዞሪያ | ሙስሊም |
| 40 | ወ/ሮ ሙርሽዳ* | 40 | ሴ | የቤት እመቤት | 24/05/08 | አልከሶ | | ✓ | ስልጢ | ሙስሊም |
| 41 | ወ/ሮ ሙሪዳ | 25 | ሴ | ነጋዴ | 16/09/08 | አልከሶ | | ✓ | ስልጢ | ሙስሊም |
| 42 | ወ/ሮ ስርቦቴ ከማል | 36 | ሴ | አርሶ አደር | 24/05/08 | አልከሶ | ✓ | | | ሙስሊም |
| 43 | ወ/ት ሰሚራ | 28 | ሴ | የቤት እመቤት | 04/05/08 | አዲስ አበባ | | ✓ | አዲስ አበባ | ሙስሊም |
| 44 | ወ/ሮ ረውዳ ዳውድ | 32 | ሴ | አርሶ አደር | 24/10/07 | አልከሶ | | ✓ | ቀጣጥ | ሙስሊም |
| 45 | ወ/ት ሩቂያ | 26 | ሴ | ነጋዴ | 15/09/08 | አልከሶ | | ✓ | አረቅጥ | ሙስሊም |
| 46 | ወ/ሮ ራቢያ ከድር | 45 | ሴ | አርሶ አደር | 23/09/08 | አልከሶ | | ✓ | ወራቤ | ሙስሊም |
| 47 | ወ/ሮ ዙልፍቴ * | 35 | ሴ | አርሶ አደር | 15/09/08 | አልከሶ | | ✓ | ጦራ | ሙስሊም |
| 48 | ወ/ሮ ዙልፋ ሱሩር | 40 | ሴ | አርሶ አደር | 04/05/08 | አልከሶ | | ✓ | አሊቾ | ሙስሊም |
| 49 | ገራድ ኑርሰቦ አሊ | 80 | ወ | አርሶ አደር | 24/05/08 | አልከሶ ሀረም | ✓ | | አልከሶ | ሙስሊም |
| 50 | ገሪብ ሙሀመድ | 50 | ወ | ገሪብ | 14/09/08 | አልከሶ ሀረም | ✓ | | ናዝሬት | ሙስሊም |
| 51 | ገሪብ ተውፊቂ | 41 | ወ | ገሪብ | 14/09/08 | አልከሶ ሀረም | | ✓ | ያልተወሰነ | ሙስሊም |
| 52 | ገሪብ አቢዳ | 48 | ሴ | ገሪብ | 28/09/07 | ወራቤ | | ✓ | ያልተወሰነ | ሙስሊም |
| 53 | ገበየሁ አየለ | 16 | ወ | ተማሪ | 24/10/08 | አልከሶ | | ✓ | ዳሎቻ | ክርስትያን |
| 54 | ዜጠኛ ግርማ | 40 | ወ | ጋዜጠኛ | 24/09/07 | አልከሶ | | ✓ | አዲስ አበባ | ክርስትያን |
| 55 | ፈረጂ ሼኽ ሙስጠፋ | 28 | ወ | አርሶ አደር | 17/09/08 | አልከሶ | | ✓ | ጦራ | ሙስሊም |
| 56 | ፈተረሁፍ ሰይድ | 25 | ወ | አርሶ አደር | 24/10/07ና | አልከሶ | ✓ | | አልከሶ | ሙስሊም |

## አባሪ ሁለት፡- ለመረጃ አቀባዮች የተዘጋጁ ጥያቄዎች

አጠቃላይ መግቢያ ይህ ጥናት በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ለሶስተኛ ዲግሪ (ለዶክተሬት ዲግሪ) ሟሟያ የሚጻፍ ነው፡፡ የጥናቱም ዓላማ በስልጤ ዞን በስልጢ ወረዳ የሚገኘውን የአልከሶ መውሊድ አጠቃላይ የአከባበር ስርዓት፣ ባህላዊ እና ማህበራዊ ገጽታ ምን እንደሚመስል ከፎክሎር አንጻር መመርመር፣ መተንተን እና መሰነድ ነው፡፡ በመሆኑም የዚህ ጥናት ዓላማ እንዲሳካ ለቃለ መጠይቅ ውድ ጊዜዎቶን መሰዋት ስላደረጉልኝ እና ለቀና ትብብርዎ በቅድሚያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡

### ሀ. የቃለ መጠይቅ መረጃ አቀባዮች ግላዊ መረጃ

1. ስም__________________________________________
2. እድሜ ________________________________________
3. ጾታ _________________________________________
4. ሃይማኖት _____________________________________
5. ስራ _________________________________________
6. የት/ደረጃ ______________________________________
7. የመጡበት ቦታ/ቀበሌ ______________________________
8. ቃለ መጠይቅ የተካሄደበት ቦታ___________________________
9. ቃለ መጠይቁ የተካሄደበት ቀን _________________________

### ለ. ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. መውሊድ በስልጤ ብሔረሰብ ዘንድ መቼ እና እንዴት መከበር ጀመረ?
2. የአልከሶን መውሊድ መቼ ማክበር ጀመሩ? ለምን ማክበር ጀመሩ?
3. ስለ አልከስዬ የሚያውቁትን በሙሉ ዘርዝርው ቢነገሩኝ?
4. አልከስዬ እና እሳቸው ካለፉ በኋላ መስጂዱን የመሩ ሰዎች ፈጸሟቸው  የሚባሉ ልዩ ልዩ አፈ ታሪኮችን ይገሩኝ?
5. የአልከሶ መውሊዱ ከመቼ እስከ መቼ ይከበራል?  ይህ ጊዜስ ለምን ተመረጠ?

6. የአከባበር ስረአቱ ምን እንደሚመስል አብራርተው ይገሩኝ?
7. ለበአሉ የሚሆነው ወጪ በማን ይሸፈናል? እንዴትስ ይሰበሰባል?
8. በመውሊድ ጊዜ የሚባሉ መንዙማዎችን ይገሩኝ? መንዙማውን ለማድመቅ የሚያገለግሉ ምን ምን ቁሳቁሶች አሉ?
9. በመውሊድ ቀን ምን ምን ምግቦች እና መጠጦች ይዘጋጃሉ? የአቀራረብ ስርዓቱስ ምን ይመስላል?
10. በመውሊዱ የስልጤ ብሔረሰብ ባህል እንዴት ይጸባረቃል?
11. የሃይማኖት መስተጋብር በአልከሶ መውሊድ እንዴት ይጸባረቃል?
12. መውሊድ መከበር የለበትም የሚሉ ሰዎች አሉ በዚህ ላይ ምን አስተያየት አሎት?
13. የአልከሶ መውሊድ በዚህ ሁኔታ መከበሩ ምን ጥቅም እና ጉዳት አለው ብለው ያስባሉ?
14. እርሷ መከበር ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ የመውሊዱ የአከባበር ስርዓት ለውጥ አለው? ለውጥ ካለውስ ለውጡ ምንድን ነው? የለውጡ ምክንያት ምድንነው ብለው ያስባሉ?
15. በእርሷ እይታ መውሊድ እንዲቀጥል እና እንዳይቀጥል የሚያደርገው ምን ተጽእኖች አለ ይላሉ?

## ሐ. ለተተኳሪ የቡድን ወይይት ተወያዮች የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የአልከሶ መውሊድ መከበር የጀመረው መቼ ነው? እንዴትስ መከበር ጀመረ?
2. የአልከሶ መውሊድን ለምን ያህል ጊዜ አክብረዋል? የማያከብሩ ከሆና ለምን አያከብሩም?
3. መውሊድ መከበር የለበትም የምትሉ ወገኖች መውሊድ መከበር የለበትም የምትሉት ከምን አንጻር ነው?
4. መውሊድ መከበር አለበት የምትሉ ወገኖች መውሊድ መከበር አለበት የምትሉት ከምን አንጻር ነው?
5. አልከስዬ ፈጸሟቸው የሚባሉ ልዩ ልዩ ታምራቶች ምን ምን ናቸው? ከተናገሯቸው ትንቢቶች መካከልስ ተግባራዊ ሆኖ የታየበት አጋጣሚ አለ? ካለስ ምን ምን ናቸው?
6. የመውሊዱ መከበር ምን ምን ጠቀሜታ እና ጉዳት አለው?
7. በእርሶ እይታ መውሊድ ወደ ፊት የመቀጠል እድል አለው? መልሶ ይቀጥላልም ሆነ አይቀጥልም ለምን?

8. በመውሊድ መከበር አለበት የለበትም የሚል የተለያየ አመለካከት ካላችሁ ይህ ልይናታችሁ በአካባቢው ማህበራዊ እና ልማታዊ እንቅስቃሴ ምን አይነት ተጽእኖ ይኖረዋል ብላችሁ ታስባለችሁ?

### መ. ለክርስትያን ምዕመናን የቀረቡ ጥያቄዎች

1. የአልከሶ መውሊድን መቼ እና ለምን ማክበር ጀመሩ?
2. አልከሶ ሀረም  የሚገኙት ከመቼ ጀምሮ ነው?
3. የእናንተን ሽለዋ ይዘጋጀው(የሰራው) ማን ነው? መቼ?
4. ሀረም ው ውስጥ ከተገኛችሁ በኋላ ምን ምን ክንውን ታከናውናላችሁ?
5. የእናንተ ወጪ የሚሸፈነው በማን ነው? እንዴት?
6. ምግባችሁን የሚያዘጋጀው ማን ነው?
7. ከለዋዋችሁ ውስጥ የምትቆዩት እስከ መቼ ድረስ ነው?
8. የእስልምን ሃይማኖት ተከታይ ሳትሆኑ እንዴት የሙስሊም በአል የሆነው መውሊድ ታከብራላችሁ?
9. መውሊዱን በማክበሮት ምን ምን ጥቅም ያገኛሉ?
10. ሙስሊም ምዕመናን ለእናንተ ያላቸው አመለካከት ምን ይመስላል?

# ማረጋገጫ

ይህ ጥናት የአልከሶ መውሊድ የአከባበር ስርዓት እና ፎክሎራዊ ገጽታ በስልጤ ብሔረሰብ በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ የሂውማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ፣ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነፅሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል፣ የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር፣ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረብኩት ጥናት ነው፡፡ ይህ ጥናት ከዚህ በፊት በማንኛውም አካል ያልተሰራ እና የራሴ ወጥ ስራ ነው፡፡ የተጠቀምሁባቸው ድርሳናትም በትክክል ዋቢ የሆኑ ናቸው፡፡ እንዲሁም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲም የጥናቱ ህጋዊ የባለቤትነት መብት ያለው መሆኑን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡- አብዲ ተማም ዓሊ ፊርማ ---------------------------

ግንቦት 2010 ዓ.ም